የኢትዮጵያ አንድነት እና ኢጣሊያ

በዶክተር ተወልደ ተኩእ

ሚያዝያ 1990 ዓ. ም.

አዲስ አበባ

ማሳሰቢያ

ገጽ 293 የነበረው 295 ተብሎ ይነበብ ፤

ገጽ 295 የነበረው 293 ተብሎ ይነበብ ፤

ለተፈጠረው የገጽ ቁጥር ስህተት በቅድሚያ ይቅርታ

እንጠይቃለን ።

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

ማውጫ

1. መቅድም ገጽ 1-9

2. ክፍል አንድ የኢትዮጵያ ታሪክ ምዕራፍ አንድ ጥንታዊት ኢትዮጵያ ገጽ 9-38

3. ምዕራፍ 2 የአክሱም ዘመን ገጽ 38-59

4. ምዕራፍ 3 ኢትዮጵያ ድኅረ ዘጉዋ በሰሎሞናውያን ነገሥታት ዘመን ገጽ 59-131

5. ምዕራፍ 4 ኢትዮጵያ ከሰሎሞናዊ አገዛዝ በኋላ ገጽ 131-154

6. ምዕራፍ 5 የኢጣሊያ ቅኝ ግዛት አመሠራረት ገጽ 154-190

7. ምዕራፍ 6 የኢጣሊያ ካቶሊክ ሚሲዮናውያን ለኢጣሊያ ቅኝ ግዛት ማግኘት የነበራቸው ሚና ገጽ 190-238

8. ምዕርፍ 7 የሰሐቲና የዶጋሊ ጦርነቶች 238-264

9. ምዕራፍ 8 በአፄ የሐንስ በምትመራው ኢትዮጵያ ላይ በጣሊያኖች የተፈጸመባት የግዳክም ስውር ደባ ገጽ 264-300

10. ምዕራፍ 9 ኢጣሊያ በኢትዮጵያ ላይ ያደረገቻቸው ወረራዎችና ጦርነቶች ገጽ 300-346

11. ምዕራፍ 10 ኤርትራ በቋንቋ በጉላ ወዘተ ገጽ 346-380

12. ምዕራፍ 11 ስማይጨው ጦርነት ዝግጅት ገጽ 380-422

13. ምዕራፍ 12 የማይጨው ጦርነት ገጽ 422-457

14. ምዕራፍ 13 የኢጣሊያ ቂም በቀል ገጽ 457-485

15. ምዕራፍ 14 ኢትዮጵያ በኢጣሊያ ቅኝ አገዛዝ አስተዳደርና የአርበኝነት ዘመን የመጀመሪያ ዓመት ታሪክ ገጽ 485 565

ክፍል 2 የኢጣሊያ ዘረኝነት 565 640

ዋቢ መጻሕፍቶች ገጽ 640 642

ማውጫ 642

መቅድም ፤

ኢትዮጵያ ረጅም ታሪክና ሥልጣኔ አላቸው ከሚባሉ ሀገሮች አንዷ ናት። ኢትዮጵያዊት ንግሥት ማባ የእስራኤል ንጉሥ ሰሎሞንን ለማየትና ዕውቀቱንም ለማድነት ወደ ኢየሩሳሌም ከተጓዘችበት ጊዜ ጀምሮ፤ እኛ ኢትዮጵያውያን የሀገራችን የታሪክ መነሻ አድርገን ስለምንቆጥረው፤ ኢትዮጵያ የ 3000 /የሶስት ሺህ/ ዓመት ታሪክ አላት ማለት እንወዳለን። ይህ አባባል ሐቅ ሊሆን የሚችለው ሰለሞናዊ ሐረግ ያላቸው የኢትዮጵያ ነገሥታት የታሪካችን መነሻ ለማድረግ የፈለግን እንደሆነ ነው እንጂ የኢትዮጵያ ታሪክ መነሻና መቅጠሪያ ልናደርገው ስለማይቻል አባባሉ እርማት ሊደረግበት ይገባል። መላው ዓለም የሚያውቀው የዓለም ሥልጣኔ መሠረትና ምንጭ የሆነው የግብጽ ታሪክና ሥልጣኔ ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ ከግብጽ ታሪክ ጋር የተቆራኘ ነው። የጥንት ግብጾችና ኢትዮጵያውያን አንድ ዓይነት የኩሽ ዘር ስለሆን ፤ ከአሁኖች የግብጽ ነዋሪዎች /ዐረቦች/ ይልቅ፤ የጥንታዊት ግብጽ ታሪክና ሥልጣኔ ባለቤቶችና ወራሾች እኛ መሆናችን ሊሰግን ይገባል። የግብጽ ታሪክና ሥልጣኔ የተጀመረው ከ 4000 /አራት ሺህ ዓመት/ ከክርስቶስ ልደት በፊት መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን፤ ማለት ከዛሬ 6000 /ስድስት ሺህ ዓመት/። የኢትድጵያ ታሪክም ከግብፅ እኩል ወይም ቀደምትነት ያለው በመሆኑ ቢያንስ 6000 ዓመት ታሪክ አለን ማለት እንችል ነበር። በዚህም ሳንወሰን በዘር መጠሪያችን መሠረትም በብሉይ ኪዳን ኩሽ የሞረው ከክርስቶስ ልደት 6000 /ስድስት ሺህ/ ዓመት በፊት ስለሆነ የኢትዮጵያ ታሪክ የተጀመረው ከዛሬ 8000 /ስምንት ሺህ / ዓመት በፊት ነው ለማለት እንችላለን።

በታሪክ ሂደት እንኳ ብናየው የኩሽ ወይም የካም ኢትዮጵያውያን ዘሮች በኢትዮጵያና በግብጽ ብቻ ተወስነው አልኖሩም። ነዮች /አሪያኖች/ ወደ አውሮፓ ከመፍለሳቸው በፊት የካም ወይም የሴም ዘሮች ኢውሮፓ ሰፍረው እንደነበሩና የመጀመሪያ የሥልጣኔ መሠረት እንደጣሉ በታሪክ ጸሐፊዎች የሚታመንበት ጉዳይ ነው። የታሪክ አባት ተብሉ የሚጠራው ግሪካዊ ሄሮዶቱስ በግሪክ ሀገር ነዮች ከመሰፈራቸው በፊት ነዋሪዎቹ ፐላስጂ Pelasgi የተባሉ ከአፍሪካ ወይም ከእስያ ፈልሰው የመጡ የካም ወይም የሴም ዘሮች ነበሩ ብሉ ጽፎዋል። ከእነሱ ሌላ ከአፍሪካና ከእስያ የመጡ ግሪክ ሀገር የሰፈሩ 1ኛ. ቸክሮፕ Cecrope ፤ 2ኛ ዳናዎ Danao ፤ 3ኛ. ፔሎፕ Pelope 4ኛ. ካድሞ Cadmo የተባሉ የካም ወይም የሴም ዘሮች ነበሩ። ይህ ሁሉ የኢትዮጵያን ጥንታዊነትና ገናናነት ምን ያህል እንደሆነ የሚያሳየን ነው። አፍሪካውያን ስለ አውሮፓ ባህል ሥልጣኔና ታሪክ የፃፉት ነገር የለም። ባንፃሩ ግን ኤውሮጳውያን ስለ አፍሪካ ብዙ ጽፈዋል፤ እዙንም እየፃፉ ናቸው። በተለይም ስለጥንታዊት ግብጽ ታሪክና ሥልጣኔ ብዙ አስተያየቶች ሰንዝረዋል። ከነዚህ አስተያየቶች መሐል ጥቂቶቹ ሀገር ጉብኚዎችና ታሪክ አጥኚዎች አፍሪካን ተዘዋውረው በጉበኙበት ጊዜ የግብጽ ሥልጣኔ መሰል ምልክቶች በመላው አፍሪካ ተሰፋፍቶ ነበረ በማለት አስተያየታቸውን ይሰጡ ነበር። ነገር ግን ሌሎች የግብጽ ታሪክ ተመራማሪዎች ይህ ከዘህ በላይ የተሰጠው አስተያየት ትክክል አለመሆኑን አስተውለው፤ ነገሩ የተገላቢጦሽ መሆኑን ገልጸው ጽፈዋል። ይህ ማለት ከግብጽ ወደ ሌላው አፍሪካ ሳይሆን፤ ግብጽ ከሌሎች አፍሪካውያን የሥልጣኔዋን መሠረት እንዳገኘች የሚጠቁሙ ናቸው። የቁሳቁስ ምልክቶች ብቻ ሳይሆን በመላው አፍሪካ እትዮጵያውያንን የሚመሳሰሉ ቀያይ ሰዎች መገኘታቸው የግብጽ ግዛት ከመላው አፍሪካ

ተስፋፍቶ እንደነበረ የሚጠቁም ነው በግለት ተተችቷል። ነገር ግን ይህ አባባልም ትክክል እንዳልሆነ ተታራኒ አስተያየት ተሰንዝሮበታል። በመላው አፍሪካ የተገኙ የግብጽ ሥልጣኔ መሰል ቁሣቁሶች ከግብጾች ተሠርተው የተሠራጩ ሳይሆን የአፍሪካውያን የራሳቸው የፈጠራ ውጤት መሆኑን በብዙ ተመራማሪዎች የታመነበት ጉዳይ ሆኖዋል። ግብጻውያንን የሚመስሉ ተያይ ሰዎች በመላው አፍሪካ ቢገኙም ግብፆች ግይሆኑ ኢትዮጵውያን መሆናቸውን ታምኖበታል።

እኛ ከምናስበው በላይ በተንት ጊዜ ኢትዮጵውያን በአፍሪታ በሰፈው ተሠራጭተው ስለነበረ በዘመናችን አፍሪካውያን የኢትዮጵያ ደም የሌላቸው አይገኙም። ኢትዮጵያ ምንም እንኳን ያልተከለሱ፣ ያልተበረዙ የኩሽ ዘሮች የሚገኙባት ብቸኛ ሀገር ብትሆንም አብዛኛው ኢትዮጵውያን ከሌሎች አፍሪካውያን ዘር የተደባለቁ ናቸው። በንግሥት ሳባ ጊዜ የኢትዮጵያ የግዛት ወሰን እንደዛሬ ከግብጽና ከኢትዮጵያ መሐል ሱዳን ሳትፈጠር ፣ ከዛሬይቱ ግብጽ ወደ ሰሜን መሐል ገብቶ ከበረኒስ /Berenice / ከኢኒተር በስተሰሜን ከ24 ዲግሪ ከምድር ወገብ፣ ግሰት ከራስ ባናስ / Ras Banas/ ጀምሮ፣ እስከ 20 ዲግሪ ደቡብ ከምድር ወገብ የመጽሐፍ ቅዱስ /አፈር/ የነፃዋ ሶርላ ይደርስ እንደ ነበረ የእንግሊዝ ሙዚየም /ብሪቲሽ ሙዚየም/ ሥራ አስኪያጅ የነበሩት ግስተር ቤንትና /Mr. Bent / ሊስችም ምሁራን ገልፀውታል። ሚስተር ቤንትን በመጥቀስ ኢጣሊያዊ ሻለቃ ፐሪኒ /Perini / [1] "መረብ ምላሽ" በሚል አርእስት በደረሰው መጽሐፍ እንደተነገረው፣ ሰንግሥተ ሣባ ወደ ኢየሩሣሌም እንድትጓዝና ከንጉሥ ሰለሞን ጋራ እንድትገናኝ መርከቦች የተሠሩላት በሶርላ ወደብ ነበረ።

የታሪክ አባት ሔሮዶቱስ የግብጽ ስርወ መንግሥት ከተመሠረተ ጀምሮ እስከ 18ኛው ስርወ መንግሥት /ዲናስቲ/ ግለት ከክርስቶስ ልደት በፊት 3400 እስከ 17888 ዓመት፣ 330 ነገሥታት እንደነገሡና ከእነሱ ውስጥም 18 ኢትዮጵውያን እንደነበሩ ጽፈዋል። በዚህ መሠረት ኢትዮጵያ በግብጽ ታሪክ ከፍተኛ ሚና እንደተጫወተች ያስረዳል። ለኢትዮጵያ በጎ የማይመኙ ግልያኖች እንኳን፣ ግብጽ የመጀመሪያ የሥልጣኔ ጮራ ያገኘችው ከኢትዮጵያ ነው ብለው ጽፈዋል።[2]

የኢትዮጵያ ታሪክ የተጻፈው በኤውሮፓውያን ነው። ኤውሮፓውያን ዛሬ በሥልጣኔ በጣም የተራቀቁ ናቸው። ያገራችንን ታሪክ በመፃፋቸው በእጅጉ ውስታ የሰማናል። ይሁን እንጂ ችሎታ ቢኖረን ያገራችን ታሪክ ራሳችን ብንጽፈው ይመረጣል። ዛሬ አውሮጳውያን በመላው ዓለም በሥልጣኔም በኃይልም፣ በበጎ ሥነ ምግባርም የመሪነትን ሥፍራ ይዘው ይገኛሉ። ነገር ግን የሥልጣኔ ጀግሮዎች እያደሉም። የዘመናዊ ሥልጣኔ ጀግሮዎችና አንጋፋዎች ግብፆች ሲሆኑ፣ ከእነሱ ቀጥሎም እሲሮ-ባቢሎናውያን ነበሩ። ከእነሱ ቀጥሎም ይሁዶች ነበሩ። እንዲሁም በጥንታዊ ሥልጣኔ በተደምትነት የሚጠሩ ፈኒሺያኖች ነበሩ።

እነዘህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱ ሕዝቦች የካምና የሴም ዘሮች ነበሩ። ከእነሱ ቀጥሎ ግን የዓለምን ሥልጣኔ ወደ ላቀ ደረጃ ያደረሱ የነጭ ዝርያ ያላቸው መሲዮ ፐርሺያኖችና ግሪኮች ናቸው። በተለይ ግሪክ ለዓለም ሥልጣኔ ያበረከቱትው አስተዋጽኦ በጣም ከፍተኛ ነው። ግሪኮች በሥልጣኔ ከፍተኛ ደረጃ በደረሱበት ጊዜ በሰሜን ድንበራቸው ወረራ ያደረጉባቸው

[1] Perini Mereb Melash p. 19-20

[2] La Formazione Impero Coloniale Italiano (F.I.C.I) V.I p 62

የነበሩ፣ ኋላ ቀር ዘላን የነጭ ዘሮች ..."ባርባሪያን".. /ኋላ ቀርና ጨካኞች / ብለው ይጠሩዋቸው ነበር። እንዲሁም ግሪክኛ ቋንቋ መናገር የግይችሉ ሁሉ ሮማውያንም ጭምር "ባርባሪያን" ተብለው ይጠሩ ነበር። ዛሬ ባርባሪያን ተብለው ይጠሩ የነበሩ ሕዝቦች የዘመናችን የተራቀቀ ሥልጣኔ የመሪነቱን ቦታ ይዘዋል። ግሪክ ግን በኤውሮጳ ወደ መጨረሻ ደረጃ ትገኛለች።

300 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት የግሪክ ሥልጣኔ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ በነበረበት ጊዜ ከውጭ ኃይል እንቅፋት ባያጋጥመው ኖሮ፣ ዓለም በበለጠ ፍጥነት በሥልጣኔ ተራምዶ ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት አስቀድመን አሁን ያለንበት የሥልጣኔ ዕድገት ደረጃ በደረሰን ነበር። መንግሥታውያን ኩተሞች እውቀትን ለማስፋፋት ብቻ የተመሠረቱ መሆናቸውን የሚያሳይ አቋም ሰብዙ ሺህ ዓመታት ይዘው ከኖሩ በኋላ፣ በመጪረሻ በማከሲዶናዊ ንጉሥ ፊሊጶስና በልጁ በታላቁ እስክንድር አንድነታቸውን መሥርተው ኃይልኛ ግእከላዊ መንግሥት ባቋቋመበት ጊዜ፣ የጥንታዊት ግሪክ ባህል በተሰየ የሥነ ጽሁፍ ኤለኒክ ይባል የነበረው "ኤሊኒሲቲክ" ተብሎ ጥራቱ ያነሰ ሆኖ ነበር። በሌላ በኩል ግን ግሪክ በተጠናከረ ሁኔታ ለመላው ዓለም የዕውቀት ግእከል ለመሆን በቅታ ነበር። ነገር ግን በዚሁ ጊዜ ከግሪክ በስተምዕራብ በሮም ቡኃይል ብቻ የሚያምን ዕውቀት አልባ አንድ ጠንካራ መንግሥት ተመሥርቶ ግዛቱን በግስፋፋት ላይ ይገኝ ነበር። አውሮፓውያን ሁሉ የሮግ መንግሥት አክብሮትና አምልኮት እንዳላቸው አውቃለሁ። ነገር ግን በገለልተኛ ዓይን ሲታይ የሮግ መንግሥት ለዓለም ሥልጣኔ ያበረከተው ነገር ቢኖር ከጥቅሙ ጉዱቱ በጣም እመዝኖ ይገኛል። የሮግ መንግሥት ታሪክ ሲታይ የግሪክን ሥልጣኔ ታሪኪንና ነፃነቷን ለግጥፋት ባጠቃላይ የዓለምን ሥልጣኔ ለግውደምና ለመቀልበስ የተመሠረተ ይመሰላል። የግሪክን ሥልጣኔ ግውደም የጀመረው በደቡባዊ እጣሊያ፣ በግሪክ አስተዳደር ዓይነት የተቋቋመው በዕውቀትና በሀብት የበለፀጉ መንግሥታዊ ኩተሞች ነበሩ። እነዚህ ኩተሞች በቋንቋና በባህል ግሪካዊ ሆነው፣ አጠቃላይ ስግቸው /ግኛ ግሪኮያ/ /ትልቋ ግሪክ/ ተብለው ይጠሩ ነበር። የመጀመሪያውን ፅዋ የቀመሰችው በደቡባዊ እጣሊያ የምትገኘው የግሪክ ትልቋ መንግሥታዊ ኩተማ በጣሊያንኛ ታራንቶ TARANTO ባላቲኒኛ ታራንቱስ TARANTUS በግሪክኛ ታራስ TARAS ተብላ የምተጠራ ነበረ። ታራንቶ የተቆረቆረችው ከስፓርታ የፈለሱ ግሪኮች ከክርስቶስ ልደት በፊት በ708 ነበረ። ከ10 ዓመታት መከላከል በኋላ በሮግውያን እጅ የወደቀችው ለ436 ዓመት ግሪካዊት መንግሥታዊ ኩተማ ሆና ከቆየች በኋላ በ270 ነበረ። ከታራንቶ ጋራ ሊሉት በደቡባዊ እጣሊያ ይገኙ የነበሩ የግሪክ አነሰተኛ መንግሥታዊ ኩተሞች በሮግውያን እጅ ወደቁ። 68 ዓመት ከታራንቶ መውደቅ በኋላ፣ ሮግውያን የግሪክ ሥልጣኔን በእጠቃላይ የዓለም ሥልጣኔን ለግውደም ከፈጽሙዋቸው ወንጀሎች ትልቁ በሲሲሊ ደሴት የምትገኘውን ዝነኛዋን የሲራኩዝ የግሪክ መንግሥታዊ ኩተግን ከክርስቶስ ልደት በፊት በ200 ዓመት በቁጥጥራቸው ሥር ግድረጋቸው ነው። ሲራኩዝ በእውቀት ግእከልነቷ በእኩል ደረጃ ከአቴናና ከእስክንድሪያ ትወዳደር ነበር፣ በሕዝብ ብዛት ግን በአንደኝነት ደረጃ ነበረች። ከክርስቶስ ልደት በፊት በ4ኛ ምዕተ ዓመት ግግሽ ሚሊዮን ሕዝብ ይኖርባት ነበር። ከታላላቆቹ ዜጉቿ መካከል ዝነኛው የሂሣብ ምሁር አርኪመደስ ነበር። አርኪመደስ ከሰር አይነክ ኒዮቶንና ከአልበርት አንሰታይን እኩል ደረጃ የታላቅ ሳይንቲስት ሰም ተሰጥቶታል። የእሱ ግኝቶች ለ17 ምእተ ዓመታት ተረሱተው ከቆዩ በኋላ እንደ አጋጣሚ በሶስተኛ ወገን ለኤውሮጳውያን ቅጅ

እስከተገኘበት ጊዜ ለዓለም ሥልጣኔ አስተዋጽኦ ማያደርጉ ቀርቷል። ይህ ማለት የዓለም ሥልጣኔ ለ17 ምዕተ ዓመታት ወደ ኋላ ቀርቷል ማለት ነው። ይኼውም ሲራኩዝ ርግውያን እጅ በመውደቋና እርኪመደስ በርግዊው መታደር በግፍ በመገደሉ ምክንያት ነው።[1] ሲራኩዝ በርግውያን እጅ በወደቀችበት ወቅት እርኪሚዲስ ኩጣዋን ከርግውያን ወረራ ለመከላከል እቅድ አውጪ ነበር። ርግውያን ኩጣዋን በተቆጣጠሩት ሰዓትም እርኪሚደስ ቤቱ ውስጥ ሆኖ የጂእሜትሪ ሥዕል ይሠራ ስለነበር ርግዊው መታደር እቤቱ ውስጥ ሲገባ እንዳይረበሽው ቢጠይቀው መታደሩ ተናዶ ገደለው። ዛሬ ቢራኩዝ ክሲሲሊ ደሴት 9 አውራጃዎች አንዷ ብትሆንም፤ በ1987 ዓ.ም. ቤተደረገው የሕዝብ ቆጠራ የነዋሪዎቿ ብዛት 123,000 ሆኖ ከ9ቱ የአውራጃ ከተሞች በ4ኛ ደረጃ ትገኛለች።

ርግውያን የዓለምን ሥልጣኔ የግውደም ሥራቸውን በመቀጠል የደቡባዊ ኢጣሊያ እና ደሴቶቿ ይዞታቸውን ካጠናከሩ በኋላ ዋናው ጠላታቸውና ተቀናቃኛቸው የነበረችው ዝንኛዋና ትልቋ አፍሪካዊት ሀገር ካርታጅ "ፑኒክ" ጦርነቶች ተብለው በሚጠሩ በ119 ዓመታት ውስጥ ሶስት ዙር ጦርነቶች ካካሄዱ በኋላ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ146 ዓመት ኩጣዋን በተቆጣጠሩ ጊዜ በዓለም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በእግት ከግጋየታቸው ሴላ፣ ዳግም እንዳያንሰራራ በግረሻ አረሷት። ካርታጅ በጊዜው ከነበሩ ኃያላን መንግሥታት አንዷ ነበረች። ግዛቷ በሰሜን አፍሪካና በሜዲተራንያን ብቻ ሳትወሰን እስከ ምዕራብ አፍሪካ ጊኒ፣ ምዕራብ፣ ምሥራቅ ኢሙሮፓ እስከ ባልቲክ ባሕር ይደርስ ነበር። ካርታጅ የተቆረቆረችው በፈኒሳውያን ከክርስቶስ ልደት በፊት በ850 ነበር።

በ146 ከክርስቶስ ልደት በፊት ነበር የግሪክ ነፃነትም ግብቂያ የሆነው። ግሪኮች ከርግውያን ለመከላከል በመጨረሻ በኮሪንት ተሰብስበው ጦርነት ገጥመው ነበር። ነገር[1] ግን ግሪኮች ስለተሸነፉ ኮሪንት ተቃጥላ ዘብቷም ወደ ሮም ተዘርፎ ተወሰደ። በጊዜው ይኖር የነበረው ታዋቂው የግሪክ ታሪክ ፀሐፊ ፖሊዚየስ POLIBIUS [1] ስለ ግሪክና ካርታጅ አወዳደቅ በማወዳደር ሲጽፍ ምንም እንኳን ካርታጂያውያን የደረሰባቸው ጥፋት ከግሪኮች የበለጠ ከባድ ቢሆንም እንዳንድ ሰው ግን በግሪኮች የደረሰ ውድመት ከካርታጂናውያን እያንስም እንዲያውም ይበልጣል ይላሉ ምክንያቱም ካርታጂናውያን በመሉ ከገፀ ምድር የጠፉ ስለሆነ የማያፍሩበት ምክንያት አይኖርም፤ ግሪኮች ግን ውርደታቸው ለልጆቻቸው የማተላለፍ ስለሆነ ከካርታጂናውያን የበለጠ የሚያሳዝኑ ናቸው።

በትምህርት ማእከልነቷ በዘመኑ ከነበሩት ታዋቂ ታላላት ኩጣዎች አንዷ የነበረችው የግብጽ እስክንድሪያ፤ በተለይም በዝነኛው ቤተመፃህፍቷ፤ የምሁራን መሰብሰቢያ ማእከል ሆና ስታገለግል የነበረችው፤ የለሎች ታላላት ኩጣዎች ተመሣሣይ እጣ በርግውያን ወራሪዎች ግያደርሳት ብዙ ጊዜ አልቆየችም። በ48 ከክርስቶስ ልደት በፊት ጁሊየስ ቄሣር የሥልጣን ተቀናቃኝ ፖምፕዮስን ለመውጋት ወደ ግብጽ በዘመተበት ጊዜ ከፋፍለህ ግዛ በሚለው የቆየ የሮግውያን ፍልስፍና ለሥልጣን ሽኩቻ ያታገሉ ከነበሩት ሁለት የግብጽ መሪዎች ከሊዎፓትራን በመደገፍ ግብጽችን እርስ በርስ በማዋጋር እንዳለ ዝንው የእስክንድሪያ ቤተመፃህፍት ስለተቃጠለ

[1] New Standard Encyclopedia VA 1965

[1] Calogero Fazio Corso di Storia V.1 p. 205

እገልግሎትና ሕልውናው አቋርጦ ፤ የዓለም ሥልጣኔም ለብዙ ዓመታት ወደ ኋላ እንዲመለስ ሆነ።

በአውሮፓውያን የታሪክ ፀሐፊዎች "ሚድል ኤጅስ" Middle ages የተባለው የታሪክ የጨለማ ዘመን ግማሹ የክርስትና የሃይማኖት እምነት በሚላን አዋጅ መሠረት ግንም ሰው እንዲያምንበት በደፋ የተፈቀደበት ቀን /313 ዓ.ም./ የጨለማ ዘመን መጀመሪያ ብለው ሲቆጥሩ ፤ ሌሎች ደግሞ የመጨረሻ ምዕራባዊው ሮግዊ ንጉሠ ነገሥት ከሥልጣን የወረደበት ቀን /476 ዓ.ም./ የዘመኑ የመጀመሪያ መቁጠሪያ አድርገው ይቁጥሩታል። ነገር ግን ይህ አሰተሳሰብ ስሕተት ነው፤ ምክንያቱም በተጠቀሱት ሁለቱ ዘመናት የዓለም ሥልጣኔ ወደ ኋላ እንዲመለስ ወይንም ወደ ጨለማ ዘመን እንዲገባ የሚያበቃ የተሠሩ ልዩ ክንዋኔዎች የሉም።

የዓለም ሥልጣኔ ወደ ጨለማ ዘመን የገባ ወይንም ወደፊት እንዳያራመድ እንቅፋት የሆነበት ምክንያቶች ከላይ የተጠቀሱ ዘመናት ሳያሆኑ የግሪክ ነፃነት ያከተመበት ዓመት /146 /፤ ካርታጅ ከገፀ ምድር የጠፋችበት ዘመን /146/ መሆን ይገባዋል። ወይንም ደግሞ እርኪመዲስ በርግዊ መታደር የተገደለበት ዘመን፤ ሲራኩዝ በርግውያን እጅ የገባችበት ጊዜ /202 ከክርስቶስ ልደት በፊት/ የዓለም ሥልጣኔ ወደ ጨለማ ዘመን እንደገባ ብለን መቁጠር ብንጀምር የበለጠ ትርጉም ይኖረው ነበር። ከዚህም ሌላ በደቡባዊ የዛሬዋ ኢጣሊያ ከግሪክ መንግሥታዊ ኩጣዎች አንዷ ታራንቶ በርም እጅ ከወደቀችበት ዘመን ጀምሮ /270 ከክርስቶስ ልደት በፊት የእስክንድሪያ ቤተመፃህፍት እስኩተቃጠለበት ዘመን 48 ከክርስቶስ ልደት በፊት ባሉት ዓመታት ውስጥ የዓለም ሥልጣኔ ወደ ጨለማ ዘመን ገባ ብለን በማሰብ "የሚድል ኤጅስ" የመጀመሪያ የመቁጠሪያ ዘመን ብደረግ መሠረት ያለው አቆጣጠር በሆነ ነበር። ርግውያን የዓለምን ሥልጣኔ አውዳሚዎች ናቸው እንጂ ገሚዘዎች አይደለም። ሮግ የምትታወቀው የዓለም አቀፍ መንግሥት ዋና ኩጣ ለተወሰነ ጊዜ ዘመሆኗ ነው። የሮግ ታሪክ መራሽ መሆን የሚገባው ዓለም አቀፋዊው የሮግ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ነው። ጣሊያኖች ሮግውያን ነን እያሉ ይኮሩብታል፤ ሐቁ ግን ሮግ የዓለም አቀፍ መንግሥት ዋና ኩጣ ነበረች እንጂ በተለይ የኢጣሊያ ዋና ኩጣ አልነበረችም። ሮግ በኢጣሊያ ሀገር መገኘት ለኢጣሊያ ያበረከተችው ጉዳት እንጂ ምንም ጥቅም የለም። ሮግ አንድ ብሔራዊ መንግሥት በኢጣሊያ ምድር እንዳያቋጠጥ አውደሚ ሚና ተጫውታለች። በመጀመሪያ በኢጣሊያ ምድር ቀደምት ኗሪ ጉሣዎች ለምሳሌ በሲገራውያን ወይንም በኢትሩትካውያን መሪነት ብሔራዊ ስሜት ያለው መንግሥት እንዳይቋቋም ሮግ እንቅፋት ከመሆንዋም በላይ ቋንቋቸው ባህላቸውን አጥፍታለች። ኢታሊክ Italic የሚባል ጉሣ ከሄሌኒክ የሚዛመዱ፤ ላቲኖች በተለይም ሳኒዎች የተባሉ ጉሣዎች ወዘተ... በኢጣሊያ ምድር ብሔራዊ መንግሥት ለማቋቋም ያደረጉት መከራ በሮም አምባገነናዊ አገዛዝ ሁሉም ቋንቋቸውና ባህላቸው ጠፍቶ በግያንሠርሩበት ሁኔታ ተደመሰሱ። ስለዚህ ሮም ካርታጅናውያን ብቻ አላጠፋችም። ዛሬ ኢጣሊያዊ ተብሎ የሚጠራ አብዛኛው ከሮግ ፍጅት የተረፉ ጉሣዎች ናቸው። ይህ ባይሆን ኖሮ በሊሉች የአውሮፓ ሀገሮች ከተቋቋሙ የባርባሪያን አዲስ መንግሥታት አስቀድግ ኢጣሊያ የራሷ መንግሥት ለመመሥረት በቻለች ነበር። ጣሊያኖች ሁሉ ግን ሮግዊነት ስለሚሰግቸው በሮም ተጨፍጭር ታሪካቸው ከምድረ ገጽ የጠፋ ሕዝብ ጣላቸው እድርገው በመገመት ይደሰቱበታል።

ሮማውያን ግለት የአንድ ነባ ስምም አልነበረም። የ 3 ጉላ ቅልቅል ናቸው፤ እነሱም ራሚ Rammi = Latini ላቲናውያን 2ኛ. Tizii = Sabini ሳቢናውያን 3ኛ. Luceri Etruschi ኤትሩስካውያን የተባሉ ናቸው። ጥቂት እረኞች ይኖሩበት የነበረች የሮማ ስም ነው፤ ትርጉሙም ከወንዝ አጠገብ ግለት ነው። ሮማውያን የራሳቸውን ቋንቋ አልነበራቸውም። በጉረቤታቸው በላቲኖች ቋንቋ ይጠቀሙ ነበር። በዘራቸው የ3 ጉላ ቅልቅል ሲሆኑ፤ በባሕል በኩል ብዙ ነገር ከኤትሩስካውያን የወረሱት ነው። በአጠቃላይ ሮማ የኢጣሊያ በተለይ ዋና ከተማ አልነበረችም፤ ስምሃሌ ቪያና ፤ ሊዝቦን ፤ ማድሪድ፤ ፓሪስ፤ ሰንደን፤ በርሊን የየሀገሮቻቸው በፖሰቲካ በአስተዳደር በትምህርት በኤኮኖሚ ግእከል በመሆን ነው ያደጉና አገልግሎት የሰጡ። ሮማ ግን ለኢጣሊያ ግእከል ሆና አታውቅም፤ በኢጣሊያ አንድነት ትግል እንደግእከል፤ መዛቢያ ሆና አላገሰገሰችም። ኢጣሊያ አንድነቷን አግኝታ ከተቋቋመች በኋላ የጥንታዊት ሮማ ዝና ሰማግኘት ከርዕሰ ሊቃነ ጳጳሱ ግዛት በኃይል ነጥቃ ነው ኢጣሊያ እንደተሰጣፊ የራሷ ዋና ከተማ ያደረገቻት።

የኢጣሊያ ታሪክ ፀሐፊዎች ምዕራባዊው የሮማ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ከግከተሙ በፊት /476/ ግንኛውም የሮማ መንግሥታት ከኢጣሊያ ብሔራዊ ጥቅም አኳያ ይወሰኗቸው የነበሩ እርምጃዎች ከግድነት በስተቀር ሊተቹ አይታዩም። የኢጣሊያ ታሪክ ፀሐፊዎች በቁጭት የሚጽፉት ከ476 ዓ.ም. በኋላ በኢጣሊያ ሰለተቋቋመው የባርባሪያን መንግሥታት ነው። የመጀመሪያ ባርባሪያን መንግሥት በኢጣሊያ የተቋቋመው በእድሪያቲክ ባሕር የምትገኘው በራቨና ዋና ከተማ በግድረግ በኤዶዋከሬ መሪነት ነበረ። ይህ በትክክል ጎሣው የማይታወቀው ባርባሪያን መሪ በራሱ ወታደሮች ለአመጽ እነሣስቶ የመጨረሻ ምዕራባዊ ንጉሠ ነገሥት ሮሙለሥ አውገስቱስ አውርዶ ራት ያለ ቦታ ወሰዶ ወደ አሰር ቤት ካባው በኋላ፤ ራሱን ዝት አድርጉ በመገመት ባርባሪያን እንደመሆኑ መጠን ንጉሠ ነገሥት መሆን የማይገባው፤ የማይችልና ህግ እንደማይፈቅድለት በማመን የንጉሠ ነገሥት ዘውድ ሰምሥራቃዊው ንጉሠ ነገሥት ዜኖ በመላክ አስረከበ። ይህ 476 ዓ.ም. ምዕራባዊ የሮም ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ፍጻሜ ተብሎ በታሪክ ይታወቃል። ኤዶዋከሬ ፓትሪሲያን /እንደራሴ/ የሚል ማዕረግ ከንጉሠ ነገሥት ዜኖ ተሰጥቶት ይገዛ ነበር። ኤዶዋከሬን አሸንፎ ሥልጣን የያዘ የኦስትሮጉቶች መሪ ቴዎዶሪክ Teodoric ነበር። እሱም እንደ ኤዶዋከሬ በምሥራቅ ንጉሠ ነገሥት ስም ኢጣሊያን ከአሰተዳደረ በኋላ በ526 ዐረፈ።

የኢጣሊያ ታሪክ ፀሐፊዎች በቁጭት የሚተቹት ኤዶዋከረና ቴናዶሪክ ሰምሥራቃዊ ንጉሠ ነገሥት ዜኖ በግጉበደድ ፋንታ የራሳቸው ዘውድ ጭነው ሥልጣን ቢይዙ ኖሮ በኢጣሊያ ምድር አንድ ኢጣሊያዊ መንግሥት ይመሠረት ነበር በግለት ነው፤ ምዕራባዊ ንጉሠ ነገሥት መንግሥትም ህልውናው ሣይቋረጥ ይቀጥል ነበር ይላሉ።

የቀድሞ ቀኝ ገዥዎቻችን ጣሊያኖች ከስር መሠረታቸው ግወት ለእኛ በጣም አስፈላጊ ነው። አባቶቻችን የሚሏቸው ሮማውያን ካርታድናውያንን እና ሌሎችን ሕዝቦች ከምድረ ገጽ እንዳጠፉ ሁሉ እኛንም ለግተፋት እቅድ አውጥተዉብን እንደ ነበረ ግስረጃዎች አሉን። እንኳንስ የሰው ልጅ አውሬዎችም ዘራቸው እንዳይጠፋ መከላከያ ይደረግላቸዋል። ካርታጂናውያንም በሮማውያን ተፈጅተው ከምድረ ገጽ ሲጠፉ የተንት ግብፃውያንም ከዓረቦች ወረራ በኋላ ባህላቸው ዘራቸውንና ቋንቋቸው ከዓረብ ጋር ተደባልቆ ጠፍቷል። በእኛ ላይ ከዚህ የባሰ ወንጀል ለመፈጸም እመቺ ጊዜና ሁኔታ ነበር ይጠባበቁ የነበረ፣ የተመቸ ጊዜ ግይመጣ ስለቀረ እኛ

ከአደጋ አመለጥን። የቀድሞ ቅኝ ገዢዎቻችን ሀገር ኢጣሊያ በየዘመናቱ የወጣላቸው በረቾች ሰዎች እፍታ በዘፍተኛ ኃላፊነትንና በታሣሣ አስቀምጣቸዋለች፣ አከብራቸዋለች። ፀረ ዘረኝነት ወደንም የበጎ አድራጊ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ አቋም ያላቸው ሰዎች ግን እፍታ አታውቅም። ይህ ነው ደግሞ ከሌሎች የአውሮፓ ሀገሮች ልዩ የሚያደርጋት።

ጥንታዊት ግብጽ ስተመሠረት ጀምሮ፤ ከመመሥረትዋ በፊትም ኢትዮጵያ ሥልጣኔዋን በመጋራት እንደኖረች እንደ ሄሮዶቶስ የመሳሰሉ ታሪክ ፀሐፊዎች ሌሎችም ይመሰክራሉ። አቶ ተክለ ፃድቅ መኩሪያ በደረሰው መጽሐፍም ኢትዮጵያውያን ነገሥታት ፤በግብጽ 25ኛ ስርወ መንግሥት /ጲኖስቲ /፤ብዙ የአውሮፓ ታሪክ ፀሐፊዎችን በመጥቀስ የፈርኦን ዘውድ ጭነው ግብጽን እንደገዙ መዝግበዋል።

ግብጽና ኢትዮጵያ ምንም እንኳን ጉረቤት ቢሆኑም በጣም የተለያየ የመፊት አቀማመጥ አላቸው። ግብጽ ሜዳማ በመሆኗ እንዲሁም ሶስት ክፍላተ ዓለም አኅፃኝ በመሆኗ /ግሰት አፍሪካ፣ እስያና ኤውሮፓ/ ሰውጭ ወራሪዎች፣ የተጋሰጠች ስትሆን ኢትዮጵያ ግን ተራራማ በመሆኗ ለውጭ ጠላት ወራሪ አትመችም ይህም በመሆኑ ግብጽ በረጅም ጊዜ ታሪኳ ብዙ ወራሪ ኃይሎች ደፍረዋታል። ከክርስቶስ ልደት በፊት 1090 ጀምሮ አሲራውያን፣ ባቢሎናውያን፣ ፐርሲያውያን እንዲሁም ኢትዮጵያውያንና ሊቢያውያን በየተራ ግብጽን ወረው ገዝተዋል። ከክርስቶስ ልደት በፊት በ332 ታላቁ እስክንድር የግዛቱ አንድ ክፍል አድርጓታል። በ30 ከክርስቶስ ልደት በፊት የሮማ የግሪክ Bizantine ግዛት ሆነች። በ616 ዓ.ም. በፐርሲያኖች ተወራ ተያዘች። በ639 ዓ.ም. በዓረቦች ተይዛ እስላማዊት ዓረባዊት ሀገር ሆነች። በ1517 ግብጽ በቱርክ ኦቶማኖች እገዛዝ ሥር ወደቀች። በ1798 ቀዳማዊ ናፖሊዮን ግብጽን ከያዘ በኋላ በእንግሊዝ እስገዳጅነት ሲለቅ የአልባንያ ተወላጅ መሐመድ ዓሊ ከ1801 ጀምሮ ለ40 ዓመታት ግብጽን ገዝቷል።

ኢትዮጵያ ከግብጽ ጋራ በጉርብትናም በሃይማኖትም የጠበቀ ግንኙነት ቢኖራትም የግብጽ መነሣትና መውደቅ የበይ ተመልካች ሆና ከግየት በስተቀር ወራሪዎች ከግብጽ አልፈው ወደ ኢትዮጵያ የመጡበት ጊዜ የለም። 1 ኢትዩጵያ ግብጽን ብቻ ባይሆን ከጥንት ጀመሮ የነበሩ ኃያላን መንግሥታት እንደ ባቢሎናውያን፣ አሲራውያን፣ ሮማውያን፣ ቢዛንቲናውያን፣ ኦቶማን ተርኮች ወዘተ... ሲወጡና ሲወርዱ አይታለች። በቅርብ ጊዜም ቀንደኛ ጠላቶቿ የኢጣሊያና የጀርመን አምባገነን አብሪተኞች ዓለመን ሙሉ በግፍ ለመግዛት ሲነሱና ሲወድቁ አይታለች። ያለ ኢጣሊያ በስተቀር ኢትዮጵያን ለመያዝ የተመኘ ሀገር የለም። መጠነኛ ሙከራ ያደረጉት ቱርክና ግብጽ ብቻ ነበሩ። እነሱም በቀላሉ በኢትዮጵያ ጦር ተሸንፈው ከሀገራችን ወጥተዋል። ኢጣሊያኖች በአውሮፓ በውትድርና ጀግንት ጥሩ ዝና እንደሌላቸው የታወቀ ነው፤ ለዚህም ግስረጃ መጥቀስ ቢያስፈልግ በ2ኛ የዓለም ጦርነት ጊዜ ኢጣሊያ ትንሿን ግሪክ ግሸነፍ

---

1 አቶ ትክለ ፃድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ኑቢያ አክሱም ዛጉዌ 1ኛ [illegible] ገጽ 118-119

አቅቷት፣ ጀርመኖች ጣልቃ ሲገቡ ግን ሣምንት ባልሞላ ጊዜ የግሪክን ጦር መደምሰስ መቻላቸው የጣሊያኖች ደካማነት አሣያቷል።

ኢትዮጵያን ለመያዝ ግን ኢጣሊያ የተሳካላት አንድ ዘዴ ይዛ ነው። ይኸውም የጥንት ሮማውያን ዋና መፈክራቸውና ዘዴያቸው የነበረው የከፋፍለህ ግዛ ሰልት በመጠቀም ነው። በዚሁ ዘዴ ባይጠቀሙ ምሽጋችን ዘሆኑት ቡተራራዎቻችን ገብተው አሸንፈውን ሊገዙን ባልቻሉ ነበር። ጣልያኖች ጥሩ ተዋጊዎች ካለመሆናቸው ሌላ በቅኝ አገዛዝም ልምድ አልነበራቸውም። ከሌሎች ልምድ መውሰድም ፈቃደኞች አልነበሩም። ምክንያቱም ሮማውያን ነን እያሉ አጉል ትምክህተኝነት ሰላላቸው ነው። ጣሊያኖች ባለፈው ጊዜ እርሰ በርሳችን በማጣላት ተሳክቶላቸው የቅኝ ግዛታቸው ለማድረግ ከመቻቻቻቸው ባሻገር አሁንም እርሰ በርሳችን የምንፋጀው እነሱ በመሐላችን አቀጣጥለውት በሄዱት መርዝ ነው።

ከዚህ በመነሣት ነው ጣልያኖች በቅኝ ግዛት ሲያስተዳድሩን በነበረ ጊዜ ያደረሰብንን በደል ባጭሩ በዚሁ መጽሐፍ የምዘረዝረው። ታሪካችን ከጣሊያን ቅኝ ገዢዎች ጊዜ የተጀመረ እይደለም። ታሪካችንም ጠንቅቀን ማወቅ ግዴታ እንደለብን ለማሰገንዘብ የኢትዮጵያ ታሪክ ዋና ዋና ክንውኖች ባጭሩ አቅርቤያለሁ።

ክፍል አንድ

የኢትዮጵያ ታሪክ
ምዕራፍ አንድ ጥንታዊት ኢትዮጵያ

1. የኢትዮጵያውያን ጥንታዊነት

የኢጣሊያ መንግሥት የአስብን ወደብ ለመግዛት ከባላባቶቹ ጋራ በተደራጣሪነት የረዳው ሣፔቶ የተባለው ኢጣሊያዊ ዜጋ ተደም ሲል ሚሲዮናዊ የነበረ ነው። ሳፔቶ ሊጉሪያ የተባለው የኢጣሊያ ከፍለ ሀገር ተወላጅ ነው። ሊጉራውያን በኢጣሊያ ዘንር ከስፈሩት ጉሣዎች ተደምትነት ያላቸው ናቸው። አርያኖች ወይንም ካውካዚያኖች ነርሱች አደደሉም። አውሮፓ ከመስፈራቸው በፊት እስያ ይኖሩ የነበረ ናቸው። ዝርያቸው በደንብ ተሰይቶ የማይታወቅ ቢሆንም የሴም ወይንም ኔም ዘሮች እንደሆኑ ይገመታሉ። የኢጣሊያን ስም በመሳ ዓለም ያስጠሯት በመርከብ ሥራና በባህር ጉዞ ሙያ ነው። አሜሪካን ያገኘ ሰው ኮለምቦስ ሊጉሪያዊ ነው። ሌላ አርያን ነጭ ያልሆኑ ኤትሩስካን የተባሉ ጉሳዎች የኢጣሊያ ሥም ግናና ያደረጉት በኪነ ጥበብና ሥነ ጽሁፍ ነው፤ ለኢጣሊያም ቋንቋ የፈጠሩ እነሱ ናቸው። ሳፔቶ ሰለሀገራችን ሚሃናዊ የሆነ ሀጉ እመለካከት የነበረው ሰው ነው። ይኸውም ለመገመት የሚቻለው /ኢትዮጵያ [1] ቡተባለው በደረሰው መጽሐፉ ነው። ሰዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ አንድ ከገጽ 3 እስከ 17 ሰለ ኢትዮጵያ ጥንታዊነት እና የሥልጣኔ ቀደምትነት ያቀረበው ጽሁፍ ከዘህ በታች ዋና ዋና ነጥቦችን ለአብነት እጠቅሳለሁ። የኢትዮጵያ ታሪክ ከጥንት ጉብፃውያን ታሪክ ቀደምትነት አለው ብለው ከሚሥኑ እንዱ ፕሮፌሰር ሳፔቶ ነው። በአንፃሩም ኢጣሊያዊው ዋና የኢትዮጵያ ታሪክ አዋቂ ተብሎ የሚታወቀው ኮንቲ ሮሲኒ ይህ አባባል ከማይቀበሉት እንዱ ነው። ሳፔቶ ወደ ኢትዮጵያን የጉብጽ ሥልጣኔ በኑር ልጅ ብሎ ይጠራታል። ሳፔቶ ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቱ በፊት ሶሪያ በነበረበት ጊዜ ሰለ መካከለኛው ምሥራቅ ሀገሮች የጥንት ሥልጣኔ በሚገባ አጥንቷል። የኢትዮጵያ ሥልጣኔና ታሪክ ከነዚህ አገሮች በማነፃፀር ነው የሚያስቀምጠው። የዛሬ ኢትዮጵያውያን ዝቅተኛ የድህነትና የኋላቀልና አኗኗር ሲታይባቸው፤ በጥንት ጊዜ ከፍተኛ የሥልጣኔ ደረጃ ደርሰው እንደነበሩ ማመን ያዳግታል። በኢትዮጵያ ምድር የሚታዩ የጥንት ከፍተኛ የሥልጣኔ ምልክቶች ብዙዎቹ የታሪክ ፀሐፊዎች ከውጪ የመጡ ሰዎች የገነቡዋቸው ናቸው ብለው ያምናሉ። እኛም ኢትዮጵያውያን ራሳችን እንደ አክሱም ሐውልት የመሳሰሉት በጥንታውያን አባቶቻችን ተሠርቷል ብለን ደፍረን ለመናገር እንቸገራለን። ፕሮፌሰር ሳፔቶ ግን ኢትዮጵያውያን ራሳቸው የከፍተኛ የጥንት ሥልጣኔያቸው ባለቤት እንደ ነበሩ ማስረጃ በማቅረብ ይደመድማል /ገጽ 9/። የኢትዮጵያ ንግሥታትና ሕዝብ አሁን የሚኖርበት የኋላ ቀር የቤት አሠራር፣ ከሚጠቀመባቸው ልብሶች፣ ቁሳቁሶች፣ የሥነ ጽሁፍም ባለመኖሩ ሊታወቅ በጣም ኋላ ቀር ባህላቸው፣ የታሪካቸውና የንግሥታታቸው ከበሬታ ከተረት አያልፍም ነበር። የሕዝቡም አኩሪ ሥራ፣ ዘራቸው ከፍ ለማድረግ የሌላቸውን ሙያ በልበ

[1] G Sapeto Ethiopia p. 3-17

ወለድ ታሪክ ዝና ለግሣንት የፈጠሩዋቸው ናቸው ለግለት ግንም ለው በቻለ ነበረ። ነገር ግን የኢትዮጵያውያን በኢትዮግራፊ፣ ቋንቋ፣ ህግጋት፣ ባህል ዘለቅ እድርጉ ለመረመረ ሰው ሁሉ በህግ፣ በሐይግኖት፣ በፖለቲካ፣ በንጉሥቶቻቸው ትልቅነት በሐውልቶቻቸው ግዙፍነት በመካከለኛ ምሥራቅ ህገሮች ታሪክ ውስጥ ዝነኞች ያደርጋቸዋል። ይህ ባይሆን ኖሮ ግግሽ የሰው ልጅ የሲቪል፣ የሀይግኖት፣ የባህል ታሪክ መካድ ያስፈልገን ነበር። ሄሮዶትስን፣ የጥንት ጉብዝውያን ቀሣውስት ታሪክን መካድ ያስፈልገን ነበር። ሳፕቶ የመካከለኛ ምሥራቅ አገሮች የጥንት ሥልጣኔ ያጠናና በጥልቀት የተመራመረ በመሆኑ ስለ ኢትዮጵያ በጽሁፎቻቸው የሚያወሱ ባገኘው እውቀት መሠረት እነዚህ ሕዝቦች በግጥሞቻቸው፣ በተረቶቻቸው ኢትዮጵያውያን ኃይለኞች አግልኩቶች እንደ ነበሩዋቸው፣ ከፍተኛ ቤተ መቅደስና ቤተመንግሥቶች እንደ ነበሩዋቸው፣ የተደራጀ የጦር ኃይልና ሰፊ ንግድ እንደነበራቸው፣ በፖለቲካና በህይግኖት በግኀበር የመኖር ባህል በዓለም ጀግራፎች መሆናቸውን የሚገልፁ የተረት ንጥም ጽሑፎች መካድ ያስፈልገናል ብሏል። ስለዚህ የኢትዮጵያን ትልቅነት ለመካድ ታሪክቸው መካድ ያስፈልጋል። ታሪክቸው ግን በሀውልቶች፣ በቋንቋ፣ በሀውልቶች የተቀረጹ ጽሁፎች የግያሻግ ማስረጃ ያለው ታሪክ ነው፣ የታወቁና የተከበሩ የታሪክ ምሁራንን ያረጋገጡት ነው። ከክርሰትና በፊት የኢትዮጵያ ነገሥታት ሥልጣን የሚያገኙት ከእግዚአብሔር መሆኑን የሚገልጽ በግዕዝ የተፃፈ ጽሑፍ በአክሱም ይገኛል። እንደ አንዳንድ የመካከለኛ ምሥራቅ ህገሮች የኢትዮጵያ ነገሥታት ከሌሎች ሰዎች የተለዩ ልዩ ፍጡር ሆነው ባይቆጠሩም ሥልጣናቸው ከእግዚአብሔር የተሰጠ መሆኑን ኢትዮጵያውያን እምነት አሳቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተነገረው የእስራኤላውያን ዓይነት የመንግሥት ሥልጣን እሰከ ቅርቡ ጊዜ ድረስ በኤሮፓ ከነበረው የነገሥታት መለክታዊ ሥልጣን ብዙ ልዩነት የለውም። ሩቅ ሣንሄድ አጼ ኃይለ ሥላሴ የተድሞ የኢትዮጵያ ነገሥታት በማስታወስ ሥዮመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው ሲጠሩ እንደነበረ እናውቃለን፣ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። ሴቶች ነገሥታት ሳይሆኑ በወንድ ነገሥታት ብቻ ለብዙ ጊዜ በመገዛት ኢትዮጵያ በዓለም ብቸኛ ህገር ያደርጋታል። እንደ እስራኤላውያን ሠለሞናዊ መለክታዊ በወንድ ነገሥታት ብቻ የተሠረተ አገዛዝ በኢትዮጵያም የመጀመሪያ ልጅ የወንድ ልጅ ብቻ ንጉሣዊ አገዛዝ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ነው ተብሎ ይታመንበታል። ማንኛውም ወንድ ልጅ ለመጀመሪያ ልጅ ሥልጣን ቢነጥቅ ሕገ ወጥ እያሰኝም። በሴቶች ከተያዘ ግን ህገ ወጥ ይሆናል። ከማን እንደተጀመረ ይህ ደንብ በውል ባይታወቅም ንግሥተ ሣባ ያወጣችው ደንብ ነው ብለው የሚያምኑም አሉ። ሌሎች ደግሞ ከንግሥተ ሣባ በፊት ከአሰራኤላውያንም በፊት የተለመደ ደንብ ነው ይላሉ። ከኢትዮጵያውያን የመጣ ባህልና የንጉሣውያን መዛግብቶች መሠረት አንድ ፅ ብራዊ አዛርያስ የተባለው ቄስ ከመሴ ብሉይ ኪዳን ህጉች የይሁዳዊ ንጉሣዊ ህገ መንግሥት እንደመጣ ይናገራሉ። ከፍልስጥኤም ነገሥታት ደምብ ቱዳማዊ ግኒልክ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣ እንደ ይሁዳውያን ዳዊትና ሰለሞን ሥልጣን ሰጥቶት እንደተባው ያምናሉ። የሰው ሥልጣን ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ፣ ህግ አውጪ ህግ አሰፈፃሚ ብቻ እንደነበረ እና በመለክታዊና መንፈሳዊ ሥልጣን ከእግዚአብሔር የሚያገናኝ ስለሆነ የቄሶች ተግባር እንደነበረ ያምናሉ። ስለዚህ ነው የኢትዮጵያ ንጉሥ እንደጥንታዊት ግብጽ ጥንታዊት ፕርሲያና እንደ አለፈው ሮማዊ ጳጳስ መንግሥት ንጉሡ መንፈሰዊ ሥልጣን የሌለው።

የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው የተጠሩበት ጊዜም ነበረ። ለዚህም ማስረጃ ሊጠቀስ የሚያለው በአክሱም ሐውልት የሚገኘው ጽሑፍ ከይፀናና ሳይፀና የግርስ /አርዩስ/ ልጆች እያሉ አንደገብፃውያን ፈርኦኖች የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠሩ እንደ ነበር ነው። ከክርስትና በኋላ ግን በአክሱምና ኑቪያ ሀውልቶችና ጽሑፎች የእግዚአብሔር ልጆች አይባሉም። ሆኖም ሥልጣናቸው ከእግዚአብሔር እንደተሰጣቸው አድርገው ያቀርባሉ። ነገር ግን በኢትዮጵያ በተጋባር የሚታየው መንፈሳዊ አባቶችና ቄሶች በመሾምና ከሥልጣን በግውረድ ቤተክህነትን በንጉሡ ፍርድ ቤት በግቅረብ ጣልቃ ገብነት ይታያል። ይህ ግን ለንጉሡ ሕገ ወጥ ተግባር አይቆጠርበትም። ምክንያቱም በሲኖዶስ የቤተ ክህነት ህግ ንጉሡ መጠቀም ስለሚችል ጣልቃ ገብነት ህጋዊ የሚያደርጉ አንቀጾች በህግጋቱ ይገኛሉ። በዚሁ ሥልጣን በመጠቀም ነው አፄ ሱሲኒዮስ የካቶሊክ ህይግኖት የመንግሥት ሃይግኖት አንዲሆን ያዘዘው ምክንያቱም የሀጉ አንቀጽ የንጉሡ ፈቃድ የህዝቡም የሀገሪቱም መሆኑን ያሳል። የሱሲኒዮስ ልጅ አፄ ፋሲለደስ በመብቱ ተጠቅሞ ካቶሊክ ሚሲዮናውያን እና ኢትዮጲያውያን ካቶሊኮች እንዲገደሉ አድርጓል አፄ ቴዎድሮስም በዚህ ህግ ተጠቅሞ ካቶሊክ ኦርቶዶክስም ቄሶች መነኮሳት ራሱ ፓትሪያርኩም ይሾምና ይሽር ነበር፣ ይሽም ሆኖ በኢትዮጵያ ምን ጊዜም ንጉሡ እንደመለኮታዊ ተቆጥሮ አያውቅም። ከሃይግኖት ድጋፍ ቢያገኝም በሥልጣኑ ቢጠቀምበትም ፈላጭ ቆራጭነቱ የሰው ልጅ በመሆን ነው። በዚህ የተነሳ በኢትዮጵያ በሌሎች የመካከለኛ ምሥራቅ ህገሮች የታየው የጭቆና አገዛዝ አልተከሰተም። የኢትዮጵያ ንጉሣዊ አገዛዝ ልዩ ባህርይ በሌሎች ህገሮች እንደታየው የውጭ ዜጋ ወይም ዘር የሆነ መሪ /ንጉሥ/ በሥልጣን የወጣበት ጊዜ የለም። ስለዚህ የኢትዮጵያ ነገሥታት የነገሡባት ህገርና ሕዝብ እንደ ባዕድ ጠላት በጦርነትና ዘመቻ የተገኘ ለባርነት፣ ለከባድ ግብር መጠቅሚያ፣ እሴያም ለእልቂት መዳረግ የተከሰተበት ወቅት የለም። የኢትዮጵያ ትልቅነትና ጥንታዊነት ብሉ ከሚያቀርባቸው ማስረጃዎች ፕሮፌሰር ሳፕቶ ነገሥታት በአክሱም የነገሥታት ዘውድ ሲጭኑ ይደረግ የነበረ እክባበር ነው። ለዚህም የአጼ ሱሱኒዮስ ለምሣሌነት ይጠቀሳል።

2. የአጼ ሱሱኒዮስ መንግሥ ሥነ ሥርዓት

ምንም እንኳን የመንግሥቱ ዋና ከተማ ጉንደር ብትሆንም አጼ ሱሲንዮስ አዲስ የአስተዳደር ዘመን ለመፍጠር በማሰብ ተረስቶ የነበረው የጥንት ነገሥታት የሥልጣን መረከብ ሥነ ሥርዓትና ከመንፈሳዊ ቅባት ጋራ የንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ መጫን እንደገና ታድሶ እንዲከበር ወሰነ። በምሥራቃውያን ንጉሠ ነገሥታት አለባበስ ዓይነት አሸብርቆ ሌሎች የመንግሥት ሹሞች በሙሉ ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ታይቶ በማይታወቅ የአለባበስ ውበት አሸብርቀው ወደ አክሱም ተጓዘ። ንጉሠ ነገሥቱ ቡኒ ቀለም ጨርቅ ለብሰዋል። በቀኝ እጁ መስቀል ጨብጧል፣ የኢትዮጵያ ነገሥታት በትረ መንግሥት ብርቅና ውድ የሆኑ ቁሣቁሶች በተሸለመ ፈረሰ ጀርባ ወጥቶ የእጀቡ ለልፍ ይመራ ነበር። በአክሱም ቤተ ክርስቲያን ፊት ሰፊት እንደደረሰ በእግሩ ወደ መሬት ወረደ። የቤተ ክርስቲያን ልጃገረዶች የቤተክርስቲያን በር ደረጃዎች ለመውጣት ሲሞክር በደረጃዎች ላይ ነጭ ልብስ የለበሱ ልጃገረዶች ወደ እሱ በግምራት መንገዱን በመዝጋት "ማንነህ እንተ በአክሱም ቤተክርስቲያን መግባት "የምትፈልግ" ብለው በመጠየቅ ጥሶ

እንዳይገባ ከለከሉት ሰጥያቄው ንጉሥ ነገሥቱ "እኔ የእናንተ ንጉሥ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ነኝ" ብሎ መሰሰላቸው። ልጃገረዶቹም "አይደለህም አንተ የእኛ ንጉሥ ነገሥት ዘኢትዮጵያ አይደለህም" አሉት። ሰሶስት ጊዜ በዚህ ዓይነት ሰመግባት ሞከር ልጃገረዶቹ እንዳይገባ ከለከሉት። በአራተኛ ጊዜ "እኔ የጽዮን ንጉሥ ነኝ" በማለት ቤተመቅደሱን ለሚጠብቁ ልጃገረዶች በመናገር ጉራዲውን አውጥቶ መጋረጃውን ቀዶ ሲገባ እልልታና ጭብጨባ በማሲንቆና በከበሮ የታጀበ በቀድሞ ጊዜ ያሰፉት ነገሥታት ይቀበሉበት የነበረ የተቀደሰ ድንጋይ ተወሰደ። የምሁራን ዜማ ጭፈራ፣ የከሀናት ቅዳሴና ፀሎት እያደረጉሰት በእግዚአብሔር ስም ኢትዮጵያን እንዲመራ ሰከርሰትና ሀይማኖት እምነት ሰመድከም ተቃራኒዎችንም ሰግጥፉት ከግሰ በኋላ ከእከሰም ቤተክርስቲያን ጳጳስ እጅ ሹመቱንና በትረ መንግሥቱን ተቀበሰ። በፕሮፌሰር ሳፕቶ አባባል የኢትዮጵያ ነገሥታት ዋና ኩተግ ከእከሰም ወደ ላሊበላ፣ ወደ ሸዋ ጉንደር መዛወር ሕዝቡ በነገሥታቱ አክብሮትና ከእግዚአብሔር የተቀቡ መሆናቸውን መቀበል እንደሚቀንስ ጽፏል። በመቀጠል ሰፕቶ እንደሚያሰበው የኢትዮጵያ ነገሥታት ቤጦ ኃይል ሥልጣናቸው ለመጨበጥ ቢችሱም ዋና ኩተግውና መቀመጫቸው ወደ እከሱም ካሳዛወሩ በቀር የእከሱም ንጉሠ ነገሥት ወይም የጽዮን ንጉሠ ነገሥት ተብሰው በእከሱም ዘውድ ጭነው ካልተቀቡ በቀር እንደ ድሮ ጊዜ ሥልጣናቸው ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው መሆኑን በሕዝቡ ፀንቶ ሊኖር አይችልም። በርግም የዚህ አይነት ሁኔታ ነበር የተፈጠረው። የሕዝቡ ስሜት ያወቀ ይመስላል ልጅ ካሣ የነበረው የትግራይ መስፍን ንጉሠ ነገሥት በሆነበት ጊዜ በእከሱም ሥርዓተ አንጋገሥ እንዲከበር ያደረገው። የኢትዮጵያ ነገሥታት በአውሮፓ እንደ ተከሰተው በሕዝብ ዐመጽ አልተደመሰሱም። ደግሞ በምሥራቃውያን ነገሥታት እንደተፈጠረው በመጥፎ ሥነ ምግባራቸው ከሥልጣን አልወረዱም። የኢትዮጵያ ነገሥታት ሥልጣናቸው እየቀነሰ የመጣ በነገሥታት ችሎታ ማነስ፣ አርቆ መመልከት ማነስ፣ እንዲሁም ደካማ በመሆናቸው የተነሳ ነው። የመንግሥት ሥልጣን በእጃቸው ብቻ ግድረግ ሲገባቸው ለበታች ሹሞች በማስረከባቸው ነው።

3. <u>የኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት ሞገስ</u>

ከዛሬ ጉስቋላ ሹሞች ሳይቀሩ የሣር ቤቶች ኑሮ የማይጣጣም፣ በቋንቋ፣ በንግግር የተዋበ አነጋገር እና በሥነ ሥርዓት ጥንታዊነታቸው ምልክት የሆነው የኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት አቀባበልና ሥነ ሥርዓት ከጥንት የዓረብ ቤተ መንግሥቶችና ከቀድሞ የስፔይን በዓለም ኃይለኛ መንግሥት ደርሳ በነበረችበት ጊዜ የነበረው ውብ ሥነ ሥርዓት የሚወዳደር ነው። ለተመልካች ግልጽ ሆኖ የሚታየው በጥንት ጊዜ የኢትዮጵያ የተሻገ መደብ በቋንቋ ንግግር ከፍተኛ ውበት እንደነበረው ሁሉ በባህልና በፍትህ፣ አቀባበል ሥነ ሥርዓት በሀብት ከበለፀጉ እና ኩተደራጁ ሀገሮች የሚወዳደር ነበር። ሳፕቶ ሰግስረጃነት ራፍሬይ የተባለው ደራሲ እጼ ዮሐንስ ለፈረንግዩ ምክትል ቆንስል ያደረገው አቀባበል ሥነ ሥርዓት ይጠቅሣል። አቀባበሱ አውነትም ከፍ ያለ ነበረ። በአንድ ድንኳን መጨረሻ ዳር በተዋቡ ምንጣፎች ላይ የተዘረጋ አልጋ ላይ እንደ መለኮት ተከራምቶ በወርቅ የተዋበ በባርኖስ ተሸፎኖ ሶስት ጊዜ የወርቅ ዙሪያ ያለው ዘውድ በራሱ አጥልቆ ንጉሠ ነገሥቱ ተቀምጠ ነበረ። በዙሪያው በክብ ረጅም ቀይ ጨርቅ በወርቅ የተዋበ በራሳቸው የወርቅ ዘውድ ያጠለቁ ራሶች ነበሩ። ከእነሱ በስተጓላም በእጃቸው

ጠረ የጨበጡ በክንዳቸው ጋሻ የያዙ፣ ትክሻቸው በእውራ ቆዳ የተሸፈነ ጉራዴ የታጠቁ ራሳቸው ባዶ፣ ጠጉራቸው የተሠራ እና ቅቤ የተቀባ ብዛት ያላቸው መኳንንቶችና ሠረኖች ቁመው ነበሩ። በዚሁ ሥነ ሥርዓት ምንም የቀረ ነገር ያለ አይመስለኝም። የኢትዮጵያ ነገሥታት ልዩ ምልክት ሆኖ የቆየው አንበሳም አልቀረም ነበረ። እሱም በነናስና በሥጋው መሉ በመሉ ነፃ ሆኖ እየተንቀሳቀሰ ከጊታው እግር ተኝቶ ይታያ ነበር። ቢያንኪ የሚባለው ሲፋ ኢጣሊያዊ፣ ሀገሩን ሰገብኝት የመጣ ከአጼ ዮሐንስ ዮቀደሰገለት አቀባበል እንደሚኩተሰው ያገልፀዋል። ግዚው 3 ትሳልት የሚያሣዩአቸው ቤቶች የያዙ ነበረ። ቤቶቹ ከሊሰች በዘገሩ ውስጥ ከሚሠሩ ቤቶች የተሻሰ ትልቅ በደሀና የተገነቡ የተሻሰ፣ ጽዳት ያላቸው ናቸው። ሥመጨረሻ ጌት ለሚርማዊነታቸው መኝታ ከፍል የሚያስገል ንፁህ ከፍል ነው ሰማለት ይቻላል። ግንቦቹ 6 ሜትር ርዝመት ያላቸው በሚያቃና በማር የተሠሩ፣ አንዳንድ ከፍ ያለ ደረጃ ያላቸው ኢትዮጵያውያን በሚጠቀመብት ሲሚነት የተሠሩ ነበር። እጼ ዮሐንስ ቁሜ ብለው ነበር ዘያንም እንደ ሐዘኞች ተቆራምደው ተቀምጠው ነበረ። ሐበሾች እንደ ቱርኮች ዓይነት በትንሽ አልጋ ያመቀመጥ ያዘወትራሉ። አልጋው በሰፊ ምንጣፍና በጨርቅ ልብስ የተሸፈነ ነበረ፣ በእኒዚያ የሹማምንቶች ጉጆ ቤቶችም ሆነ በንጉሠ ነገሥቱ ሕንፃዎች ብዛት ያላቸው በተለያየ ስም የሚጠሩ ባሰባቶች የተሞላ ነዘፈ ማለትም የቤተ መንግሥት ዘቦች፣ እሽከሮች፣ የእልፍን እስከልካይ፣ የክብር ዘቦች የሥነ ሥርዓት አስከባሪዎች፣ እንግዳ ተቀባዮች፣ የጠር አሰቆች (የሲንሬል ከፍተኛ ባሰሥልጣኖች፣ ቄሶች፣ የደብር አሰቆች፣ ደብተራዎች፣ ፊፊሎች፣ የቤተ ክህነት ትምህርት እዋቂዎች፣ የክዋከበት እዋቂዎች ወዘተ...፣ በፊዎችም አለቃና አዛዦች አሏቸው። ግብሣው ከመጀመሩ በፊት የሚባርከውና በመጨረሻ ቡራኬ አስምቶ የሚያሰናብት ካህን ነበረ። ስንጉሠ ነገሥቱ ጥሬ ሥጋ የሚያጕርስ፣ መጠጦችን የሚያማስል፣ የሚያድል፣ ትርፍራፊዎችን የሚሰበስቡ ወዙ ነበሩ።

4. <u>ፌዊዳሊዝም በኢትዮጵያ</u>

ፌዊዳሊዝም በማእከላዊ መንግሥት መሉ በመሉ የማይታዘዙ ከልላዊ አዛዝ የሰፈነበት አስተዳደር ነው። በኢትዮጵያ የዚህ ዓይነት አስተዳደር የጀመረው ሰለሞናዊ ሐረግ የላቸው ነገሥታት ወርደው የዛጉዌ መንግሥት ሲመሠረት ነው። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ የውጪ ወረራና መሣፍንቶች የሥልጣን ሽኩቻ፣ የከፍለ ሀገሮች እርስ በርስ ቅራኔዎች፣ የሀይማኖት ከርከሮች፣ የአንዳንድ እለቆች እምባገነንነት ተፈጠሩ። እነዚህ ሁሉ ተዳምረው የከፍለ ሀገሮች ዋና ኩተግ፣ ዜጉችም ከንጉሣቸው የሚያስተሳስራቸው የነበረ አንድ መንፈስ ተቃወሰ የመንግሥት አንድነት ለወታደራዊና የፊዊዳላዊ አዛዝ ተሸነሸነ። በዚህ መሠረት በኢትዮጵያ ፊፊዊዳሊዝም መጥፎ ተክል ተፈጠረ። ይህ ሁኔታ የአንድ ሀገር ሕዝቦች ከአንድ እናት ሀገር የተወለዱ ልጆች ሲሆኑ የተለያዩ ጉሣዎች መሆናቸው በማስመሰል የአንድ ሀገር ህዝብ እንደ ጠላት እንዳእደረጋቸው ፕሮፌሰር ሳፕቶ ዘግበዋል።

5. <u>የኢትዮጵያ ስም አጠራር</u>

እኛ በምሥራቅ አፍሪካ የምንገኝ ሕዝቦች ስለታሪካችን አንዳንድ ውሱን ግለጻዎች ለመስጠት ብንችልም በተለይ ስለስማችን አጠራር ግን የምናውቀው ነገር ምንም የለም። ሁሉም የውጭ አገር ሰዎች የሰጡን ስም ነው። አብዛኛው የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊዎች ኢትዮጵያ ግለት በግሪክ ቋንቋ የመጣ ነው ይላሉ። ፊቱ በፀሐይ የተቃጠለ ሕዝብ ግለት ነው ብለው ይተረጉሙታል፤ ሀበሻ ግለት ደግሞ ድብልቅ፤ ህዝብ ነው ብለው ይተረጉሙታል። የኢጣሊያ ቅኝ ገዥዎች ኢትዮጵያን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥረው በነበሩበት ጊዜ ከላይ የተጠቀሱ ሁለት ስማችንን ትተው ኢጣሊያዊ ምሥራቃዊት አፍሪካ የሚል ስም ሰጥተውን በዚህ ስም በይፋ ሰንጠራ ነበረ። ይህ ስም ኤርትራንና ሱማሊያን የሚያጠቃልል ነበረ። ስለስማችን አጠራር በሚመለከት የተሰጡት አስተያየቶች ከዚህ በታች ለማቅረብ ይቻላል።

1ኛ. የኢትዮጵያ ታሪክ ምሁር የሆነው ኮንቲሮሲኒ በ1937 ዓ.ም. በደረሰው መጽሐፍ የራሱ መንግሥት ያወጣው ስም "ምሥራቃዊት ኢጣሊያዊት አፍሪካ" የሚለው አጠራር ወደ ጐን በመተውና በመቃወም "ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ[1] በተባለው መጽሐፍ ከ3ቱ ከላይ ኩተጠሱ ስሞች ኢትዮጵያ የሚል በመምረጥ ትክክለኛ ስማችን መሆን ያለበት ስለአመነበት አሰፍሮበታል። 1000 ዓመት ከዘርስቶስ ልደት በፊት ይኖር የነበረው ታዋቂው የታሪክ ፃሐፊ ሄሮር ሀገራችንን ኢትዮጵያ እያለ ገጥሞላታል። ከሱ በፊትም በመጽሐፍ ቅዱስ ብሉይ ኪዳን ኢትዮጵያ ስም ተጠቅሶ ይገኛል። ስለዚህ ኢትዮጵያ የሚለው ስማችን ዋንኛዎቹ አያጠራጥርም። ኮንቲ ሮሲኒ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፍ እዘሻ ማለት በዓረቢኛ ቋንቋ ድብልቅ ሕዝብ ከሚለው ቃል የተወሰደ ነው የሚለው አባባል ከእውነት የራቀ መሆኑን ጠቅሶ ሐበሻ የአንድ የትግራይ ጐሣ ሰም መሆኑን ገልጿል። የሐበሻ ስማችን ከኢትዮጵያ ስማችን በጥንታዊነት ቀደምትነት እንዳለው ኮንቲ ሮሲኒ ጠቅሶ ኢትዮጵያ የተለመደው ከብርስቶና ሲሆን እዘሻ ግን ከዘርስትና በፊት የምንጠራበት ነበር። ኢትዮጵያ የተከለለች ከተፈጥሮዋ ገጽታዋ አንድ ምድረ ገጽ አንድነት ያላት አገር ስትሆን ዋና አካሏ ግዙፍ የሆኑ ተራራማ ቦታዎቿ ናቸው። እንደዚሁም ጥልቀት ባላቸው የመሬት ቁፋሮ የተከፋፈሉ ከፍተኛ ቦታዎች ያላት አገር ናት። በምሥራቅ ቀይ ባህር የአደን ባህረሰላጤና የሀንድ ውቅያኖስ ያዋስኗታል። በምዕራብ የሚያዋስኗት የናይል ወንዝና የናይል ሰፊ ቆላማ ቦታዎች ናቸው። በሰሜን የናይል ቆላማ ቦታ ቅጥያ ሲሆን፣ እንደዚሁም በደቡብ የዚሁ ቆላማ ቦታ ቅጥያ ያዋስኗታል። ኢትዮጵያ በዘርዋ በኩል ዋናው የኩሽ ህዝብ ሀገር ተብላ ልትጠራ ትችላለች። በሰሜን ከናይል ወንዝ በሱተምሥራት እስከ መዕል አካልዋ የሆነ አንድ ክፍል ብቻ ተቆርሰቦታል። ይህም ማለት ሰሜን ሱዳን ከሰላ አውራጃ ማለት ነው። በደቡብና ምሥራቅም ከዘርቸቸው አንድ ክፍል የሆነ ኮትርብ ጊዜ ወዲህ ተቆርሰላት ይገኛል። ኬኒያና ጅቡቲ። አቢሲኒያ ሲባል በደቡብ በኩል አዋሽን የሚያዋስናት ሲሆን በዘርና በቋንቋን የኩሽና የሴም ቋንቋ የወሰዱ ሕዝቦች የሚኖሩባት ናት። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ሲባል ሁለቱሮ ምድረ ገጽና ዘር ክልል የሚያመለክት ሲሆን አቢሲኒያ ሲባል ግን የአንድ ታሪክዊ ሂደት ወይም ጠቅት የሚገልጽ ነው። የኢጣሊያ ቅኝ ገዥዎች እውጥተውልን

[1] Conti - Rossini Ethiopia e genti d' Etiopia p 1-2

ያስቀረ 3ኛ ስም ግን በታሪክም ረገድ በቋንቋም በዘርም አጉል አጠራር ስለሆነ እንደ ከኒያ ኡጋንዳ ታንዛኒያ የመሰሰሉት ምሥራቅ አፍሪካ ሰላሉ፣ ይልቅስ የነበረ ፋሽስታዊ እዝዝን ማይፈራ ኮንቲ ሮሲኒ ወድቅ አድርጉታል። ኮንቲ ሮሲኒ በተጠቀሰው መጽሐፉ ስለ ኢትዮጵያ ወሰኖች አንስቶ ሲጽፍ ኢትዮጵያ ግለት በ3ኛ መቶ ከፍለ ዘመን የተገኘው የኢትዮጵያ ግስረጃ ኢትዮጵያውያን ከሐበሻ መንግሥት በስተምዕራብ የሚኖሩ ህዝቦች ናቸው ብሎ መዝግቧል። ከዚህ ጊዜ በኋላ የኢትዮጵያ አጠራር በኢትዮጵያውያን እየተለመደ መጥቷል። ግሪኮችም ኢትዮጵያውያን ብለው የሚጠሯቸው በደቡብ የሚገኙ ህዝቦች አስክ አትላንቲክ ውቅያኖስ ነበረ። 2ኛ. አቶ ተክለ የድቅ መኩሪያ[1] ስለ ኢትዮጵያና ሐበሻ ስም አጠራር ጠቅሰ በዓፈው እንደፈረንጆች አባባል ሐበሻ ግለት የዘር ድብልቅ መሆኑ እንዳለ በመቀበል ነው። እንደዚሁም ሐበሻና ሌሎች የሴም ጉሣዎች ከዓረብ ወደ ኢትዮጵያ የፈለሱ መሆናቸውን የሚለው የፈረንጆች አባባል እንዳለ በመቀበል ነው። አንድ የስም አጠራር በሚመለከት በሚጠራበት ህዝብ ተቀባይነት የሚያገኝ መሆን አለበት። ኤውሮጳውያን በእውቀት ከእኛ የሚበልጡ ስለሆነ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ስለ ስማችን ትርጉም ከዓረብ ሀገር ስለመምጣታችን የሚነግሩን ታሪክ ምናልባት በቀላሉ እውነት መስሏቸው ሊቀበሉ ይችሉ ይሆናል። ሌላ ኢትዮጵያውያን ግን ከእምነታችን ውጪ የሆነ ይህ አባባል አይቀበሉትም። ከእምነታችንና ባህላችን ውጪ ስለሆነ በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ ተቀባይነት የለውም በእውነተኛ ታሪክ ያሁን በተማማተ ታሪክ ይሁን ባይታወቅም በሰሜን የሚገኙ ብዙ ኢትዮጵያውያን ከእስራኤል እንደሚወለዱ እምነት አላቸው። ከዓረብ ዝርያ እንዳለ ግን አያምኑበትም። ሐበሻ ድብልቅ ዘር መሆናችን የሚለው አባባል እንደተራ ሰይብ ችላ ብለን ከማለፍ በስተቀር ተቀባይነት አይኖረውም። ሐበሻ ተብለን መጠራታችን እንኩራበታለን እንጂ አናፍርበትም። ይህ ነገር በስሙተት ተደጋግሞ የተነገረ ነገር በጊዜ ብዛት እንደ ሀቅ ይወሰዳል የሚለው አባባል የተሰወደብን የፈጠራ አተረጓጐም ከመሆን አያልፍም። ኮንቲ ሮሲኒ ስለኢትዮጵያ ታሪክ የደረሰው ዋና መጽሐፉ ከደቡብ ዓረቢያ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ዓረቦች መግባታቸውን በሰፊው የፃፈ ሲሆን፣ መልሰ ግን በሌላ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿ በሚለው መጽሐፉ ገጽ 44 ስለ ሐበሻ ሕዝብ ከዓረቦች በኩል መፍለሳቸው ያሰው አስተያየት ሲጽፍ "ከእሰልምና በፊት በዓረብ ሀገር ይኖሩ የነበሩ ዘፈኖች ተረቶች ሐበሻ እውነተኛ እፍረከዊ ከዓረቦች የተለየ ተብሉ ይወሰድ ነበረ። ምን ጊዜም ከዓረብ ፈልሰው ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ገቡ ሰለሚባሉ ሕዝቦች ከዓረቦች የተጠቀሰ ነገር አይገኝም" ሲል ይህ አባባሉ ግን እርሱ ብርሱ የሚጋጭ ያደርገዋል። ስለዚህ ዓረቦችና ኢትዮጵያውያን የማይቀበሉት ከኢአውሮጳውያንም በቂ ማስረጃ ያልቀረበበት የዓረብ ከልስ ተብለን መጠራታችን ተገቢ አይመስለኝም።

3ኛ. ስለአበሻ ስማችን ጥልቅ ምርምር ያካሂደው ሰው ፈረንሳዊው ሻን ደረስ ነው[2] በአፍሪካ ቀንድ የሚል እርእስት መጽሐፉ ከዘርስቶስ ልደት በፊት 1500 ዓመት በጥንታዊት ግብጽ የተደረገው የባህር ጉዞ ቡቲ ሊቱ መቅደስ ተቀርጸ የሚገኘውን ታሪካዊ ስዕል በማመረምርበት ጊዜ ነበረ። ይህ 5 መርከቦች ያቀፈ 350 ሰዎች ባህረተኞች ተካፍለውበት የነበረ ኮንቲ ሮሲኒ በዓለም የመጀመሪያ ትልቁ የባህርና የምድር ገጽታ (ጂኦግራፊ) ጉዞ ብሎ

[1] ተክለ ፃድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ነባያ አክሱም ጥንዱ ገጽ 16-18

[2] Jean Doresse Histoire Sommaire de la Corne Orientale d'Afrique p 56

ሰይሞታል። ይህ ታሪካዊ ጉዞ ለግዘጋጆት ስሟን ታዋቂ ያደረገው አታሱ /ራግካ/ ግካራ ተብላ የምትጠራ ንግሥት በትሆን፣ እንደንግሥት የራሷን ሐውልት እንድታሠራ፣ በራስዋ ስም ቤተመቅደስእንድታሠራ በ18ኛው ዲናስቲ የቱትሞሲስ 1ኛ ልጅ ናት። የቱትሞሲስ 3ኛ እህትና ሚስትም ናት። መርከቦቹ የሄዱበት ሀገር ምን ይባላል ወደ ሚስው ጥያቄ ስንባባ እምላኩ አሞን ንግሥቷን በማመልኩት የተናገረው ቃል ጃን ዶራስ የሄሮግሊፍ ጽሁፍ ከአጠና በኋላ እምላኩ አሞን ሀገሩ የፑንት ሰዎች ነው፣ የሐበሻ ሀገር ነው፣ የእግዚአብሔር ሀገር ነው ብሏል። በስዕሉ የሚታዩ የሴቶች አሰባበስ በዛሬ ጊዜ በምሥራቅ ወሎ የሚገኙ የኦሮሞ ሴቶች አሰባበስ የሚመስል ነው። ሕዝብ የሚለው ቃል የግብጽ ታሪክ ምሁራን በስሀተት እስክ ዛሬ ድረስ ግብፃዊ ቃል በግሰብ እንደ አራኞች ወይም እንደጢግሞች ይተረጉሙት ነበር። ይህ አጠራር ግን የሐበሻ ሕዝብን የአክሱም መንግሥት ከመሠረቱት አንዱ ሲሆን የሰድብ አጠራር ዓረብኛ ቋንቋ ድብልቅ የሚለው ምንም ማንኙነት የለውም። በዚህ መሠረት ኢትዮጵያ አቢሲኒያ ተብላ ትጠራለች። በጥንት ጊዜ ዓረቦች ቀይ ባህርን "ባህር አል ሐበሻህ" ብለው ይጠሩት እንደነበረ ከንቲ ሮሲኒ[1] ባአወጣው የጥንት ጂኦግራፊ ካርታ ያስረዳል በዚሁ መሠረት ንጉሥ ኢዛና የአቢሲኒያ ንጉሥ ተብሎ ነበር ይጠራ ነበረ። የግብጽ ባህረተኞች የሠፈሩበት ትክክለኛ ቦታ፣ ከሀገሩ ህዝብ ያደረጉት ማንኙነት ወዘተ...፣ በቤተመቅደሱ የሚገኙ ስዕሎች አተረጓጎም መሠረት በማድረግ ከላይ የጠቀስኳቸው 3 የታሪክ ፀሐፊዎች የሰጡት ሃሣቦች ብቻ በግተኮር ከዚህ በታች የአንዳንድ አስተያየት አቀርባለሁ ። 1/ አቶ ተክለ ፃድቅ መኩሪያ እንደሚለው ሀታሱ ንግሥት ወታደሮችዋን ወደ ፑንት ልካ እንዳስመታች፣ ከፑንት መሰፍን ፓራሁ ጋራ ተዋግተው እንደአሸነፈችና እንደ ግረክች ከዚያ የሚያስፈልጋቸውን እጣን፣ ከርቤ፣ ሽቶ፣ የዝሆን ጥርስ ወዘተ... ከባሪያዎች ሰርፈው ወደ ሀገራቸው እንደተመለሱ /ቴብ/፣ ከተግረኩትም በሃል የሀገሩ መሪ ፓራሁ እንደ ነበረ ቦታውም በኡጋዲን በአውሣ፣ በሶግሌ እንደነበረ በግስት ደምድመዋል። 2/ ኮንቲ ሮሲኒ የግብጽ ወታደሮች የሁለቱ ሀገሮች /ፑንትና ግብጽ/ የጋራ አምላክ የሆነው በአሞን ትእዛዝ ወደ ፑንት ሀገር በሰላም እንደደረሱ ያመለክታል፣ ገፀ በረክት በሰላማዊ መንገድ ላኩ ንጉሥ ስፓራሁ እንደ አቀረቡ፣ ፓራሁም በደስታ እንደተቀበላቸው፣ አቲ የምትባለው ሚስቱም በአህያ ወጥታ እንደ መጣች፣ ግብጾችን ሲቀበሏቸው ፓራሁ የሚኩተሰውን ንግግር እንዳደረገ ይገልፃል። "በዚህ የግብጽ ሰዎች የግታውቱት ቦታ እንዲት መጣችሁ? በሰማይ ነው የመጣችሁት ወይንስ ከእግዚአብሔር ሀገር በመርከብ ነው እናንተ የመጣችሁት?። ከፀሐይ ነው ምክንያቱም ከግብጽ ንጉሥ ትንሩስ ተስይቶ መኖር አይቻልም፣ እኛም በእሱ ትንሩስ ነን የምንኖረው"። ከዚህ በኋላ የወዳጅነት ማንኙነት ይፈጠራል። የሚለዋወጡት እቃዎች ግብር የመክፈልና የግስክፈል ሣይሆን የንግድ ልውውጥ ግድረግ ይመስላል። ምንም እንኳን እንደጣሊያኖች የተሰመደ አነጋገር የፑንት ሰዎች "እንዲገኑ" ብለው ቢጠራቸውም የግብጾች ተልእኮ በሰላማዊ መንገድ የንግድ ልውውጥ እንደተፈፀመ አመልክቶ፣ ነገር ግን ወደ መጨረሻ ግብጾች ከሚንዋቸው ነገሮች የሀገሩ ሰዎች ከነልጆቻቸው በመርከብ ተጭነው ነበረ። ስለዚህ በመጨረሻ ግብጾች ሀገሩን እንደዘረፉና አንዳንድ ሰዎችን ለባርነት ግርከው እንደወሰዱባቸው ያስመሰላል ብለዋል። ከንቲ ሮሲኒ ባህረተኞች ያረፉበት

[1] C, Conti - Rossini = Storia d' Etiopia tavola XV

L'Arabia del sud-ovest nei tempi antichi secondo dati epigrafici

ቀጸ ባሕር በጥንት ጊዜ ስሙ ያበሻ ባሕር እንደነበረ የሚያሳይ ፎቶ ኮፒ ከከንቲ ሮሲኒ Storia d' Etiopia tavola xv የተወሰደ


HAŠID
DAN
BAKIL
Korsa
Yaja
Garian
Sarin
Kasa (Khor Abu Seid)
Kassala
Sabderat
Sabderat arz
Sabderat
Sabderat arz
Sabderat
Sabderat arz

በታም በሚመለከት በቱካር ሰምሀር አካባቢ መሆን እንዳለበት ብሉ ደምድመዋል። [1] ጀንዶሬስ የግብጽ መርከቦች የንግድ መሆናቸውን ከአመለከተ በኋላ ለወረራና ለዘረፋ የሚውል የጦር መሣሪያ እንዳልጫኑ፣ የሚሄዱበት ሀገርም ንግድ በሰላማዊ መንገድ የሚካሄድበት ሠላማዊ ወዳጅ ሀገር መሆኑን፣ ሀገሩንም የእግዚአብሔር ሀገር ተብሎ የሚጠራ ቅዱስ ሀገር መሆኑን የሁለቱ ሀገሮች /ግብጽና ፑንት/ የጋራ እግዚአብሔር በአሞን የሚያምኑ መሆናቸውን ይገልጻል። ባህረተኞች ያረፉበት ቦታም በኤደን ባህረ ሰላጤ አካባቢ መሆን እንዳለበት ገምቷል። ስለዚህ ዘረፋ ሊካሄድ እንደማይችል ይገመግማል፣ ይኸም ትክክለኛ አገላለጥ ይመስላል።

6. የኢትዮጵያውያን በጉግ መከፋፈል

የኤውሮፓ ታሪክ ፀሐፊዎች ኢትዮጵያ የሚል ስም የሰጡን ግሪኮች ናቸው ትርጉሙም በፅሐይ ፊቱ የተቃጠለ ነው ብለን እምነን እንድንቀበል አድርገውናል። እንደዚሁም ካም የሚለው ስም የተሰጠን ከመጽሐፍ ቅዱስ ነው ተብሎ ተወሰዷል። ነገር ግን በኢትዮጵያውያን የነገሥታት ስም ዝርዝር ተብሎ የቀረበው ጽሁፍ እንደሚያመለክተው ከነገደ ዮቅጣን ኢትዮጵስ 1ኛ የሚባል ንጉሥ ከክርስቶስ ልደት በፊት ዘ1771 ኢትዮጵስ 2ኛ ዘ1730 እንደነበረ ያመለክታል። ይህ ማለት ከግሪኮቹ ሆሜርና ሄሮዶቱስ 1000 ዓመት በፊት መሆኑ ነው። ካምና ኩሽ የሚል ስም የተሰጠንም እሰራኤሉት መጽሐፍ ቅዱስ በሚጽፉበት ጊዜ ከግብፃውያን በመውሰድ ነው። በሀገራችን ፀሐፊዎች የቀረበ ጽሁፍ ትክክለኛ ያልሆነ ታሪክ ነው ብለን ልንክደው አንችልም፣ ምክንያቱም ከግሪኮች እና ከመጽሐፍ ቅዱስ ያላነሰ ማስረጃነት አለው። አቶ ተክለ ፃድቅ መኮሪያ በኢትዮጵያ ታሪክ ኑቢያ እክሱም፣ ባጥዊ የሚለው መጽሐፉ በአጠቃላይ በደረሳቸው የታሪክ ግምግምዎች በአንዳንድ ነጥቦች ላይ የመቃወማያ ሃሣብን ለማቅረብ እገደዳለሁ 1ኛ. መሠረተ ሃሣብ ብሉ የያዘው የባሬዪቱ ኢትዮጵያ የአክሱም ነገደ ሴም ዮቅጣን ከደቡብ ዓረብ ለመው ለአሁኑ መንግሥታችን ሥጣኔአችን ፈደላችን ቋንቋችን ዘራችን ልግዳችን መሠረትና አባት የሆነውና ንግሥተ ሣባና ሐበሻ የመጡባት፣ በአንፃሩም፣ የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ የምትባለው ኑቢያ ለዛሬው ሥልጣኔያቸው ፈደላችን ቋንቋችን ልግዳችን መሠረትና አባት ያልሆነው የነገደ ካም ማለቱ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም። ልዩነት ቢኖር እንኳን የዘር ልዩነት አይደለም፣ የቋንቋ ልዩነት ብቻ ነው። ቋንቋም ቢሆን ኢትዮጵያ ከመሰሉ የአማርኛና የትግረኛ ቋንቋ ተናጋሪ ብቻ አይደለችም። ከደቡብ ዓረብ የመጣ የሚለው የማንቀበለው ዘባህላችን የሌለ ኩተረት የማያልፍ ታሪክ ከመሆኑ ነው 2ኛ. ትግሬ ቋንቋ ተናጋሪ ናታታ ባይደርስም ከመፅሀፍ አካባቢ በዘመቻ ከአክሱም ሄደው የሰፈሩበት ማያሆን ከጥንት ጀምሮ ሀገራቸው ነው። ከየመን ሀገር ወደ ኢትዮጵያ ተሻግረው የመጡ 3 ነገድ ተባብረው ነገድ ዮቅጣን ሳባ በትግሬ አበል በአፋር፣ አፈር በአጋዔን ሰፍረዋል። ራማ የሚባለው በሚቶና ኢትዮጵያን ይጥ የነበረ የሀንድ ንጉሥ አፀንር ነገደ ካም ብቻ ሰፍሮባት የነበረች ኢትዮጵያ ነፃ ስለአወጡ ነፃ አውጪዎች እግአዚያን ተባሉ፣ ቋንቋቸውም ግዕዝ ተባለ የሚለው ታሪክ ትክክለኛ ቢሆን ኖሮ 3 የዮቅጣን ልጆች ግዕዝ ቋንቋ ተናጋሪ በሆኑ ነበር። አሁን ቡተግባር የሚታየው ግን ግዕ ብቻ የግዕዝ ተናጋሪ ሲሆን አባልና አፈር ግን በኩሽ የማመደቡ አፋሪኛና

[1] ተክለ ጻድቅ መኮሪያ ibd ገጽ 26

ሶማሊኛ ቋንቋ ተናጋሪ ናቸው። ታሪኩ እውነተኛነት ቢኖረውም በቋንቋ ላይሆን በዘር ነው 3ኛ ግባ ኢትዮጵያዊት መሆንዋ የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም። ሀ/ መጀመሪያ እስዋ በነበረችበት ዘመን የደቡብ ዓረብ /የመን/ ፀታሪክ እትታወቅም ነበረ። ለ/ የኢትዮጵያ ምሁራን በታሪክ ነገሥት የቀድሞ ነገሥታት ስም ተብሎ የወጣ ስም ዝርዝር ከክም ነገድ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ2404 የግባ ስም ተጠቅሶ ይገኛል።[1] እንዲሁም ከነገደ ዮቅጣን ከክርስቶስ ልደት በፊት የግባ ስም በ1985 ግባ 2ኛ በ1871 ሐ/ በ1453 ግቢ መ/ በ1036 ግቢ ተብሎ ተጠቅሶ ይገኛል። ይህ ማለት ከየመናዊት ግባ ሀልውና በፊት በኢትዮጵያ የግባ ስም የተለመደ እንደነበረ ነው የሚያሣየው። የየመን ግባ ስም ለንግሥተ ግባ ክብር ከኢትዮጵያ የተወሰደ መሆን አለበት። በአቶ ተክለፃድቅ መኮሪያ የሁለቱ ሀገሮች የመንና ኢትዮጵያ ንግሥት ነበረች የሚል አስታራቂ ሃሣብም እናትና ልጅ በእኩል ደረጃ ግወዳደር ስለሚሆን ጥንታዊት አንጋፋ ትልቋ ሀገር ኢትዮጵያ ከትንሽዋ የመን ግባ ግወዳደር ተገቢ አይሆንም። 4ኛ/ አቶ ተክለፃድቅ መኮሪያ ኢትዮጵያውያን የክርስትና ሃይማኖት ከመቀበላቸው በፊት የእስራኤል የመሴ ሀግ ይከተሉ ነበር የሚለው ታሪክ፣ እንደዚሁም ሳሰታ አገው ነገደ ይሁዳ መሆናቸውን የሚለው ታሪክ አይቀበለውም። የኢትዮጵያ ነገሥታት በናፓታ የሚገኘው በአሞን ቀግውስት አለቃ ተከታይ ነበሩ እንጂ አገዳንዶቹ የእኛ ሊቃውንት እንደሚሉት በአሪትና በእግዚአብሔር የሚያመልኩ አልነበሩም በማለት አጥላልቶ ጽፈዋል። ሰለእነሱ ነገደ ይሁዳ መሆናቸው ከአለቃ ታዬ የተፃፈው ታሪክም ሲታይ አለቃ ታዬ የእነሱን ዘር ከፈዋት ከእስራኤል ንጉሥ የልጅ ግድረጋቸው ነው ይኸውም ሲሆን የአገው ዘር ኩሽ መሆኑ ቀርቶ ሴግዊ ሊሆኑ ነው ካለ በኋላ አለቃ ታዬ ለአፃፃፋቸው ይላሉ አሉ እንጂ አሳረጋገጡም በማለት ጽሁፉን ደምድመዋል ገጽ 392። ነገር ግን አለቃ ታዬ ሰለእነሱ ሳሰታ ነገደ ይሁዳ መሆናቸውን በግላቸው የፈጠሩት ታሪክ ግያሆን የቆየ በሁሉም የታወቀ ታሪክ ነው። ዋና መሠረታቸው ሳሰታ ሆኖ ነገደ ይሁዳ ነን የሚሉ ህዝቦች በዳሞት በወጐንና በሳሰታ ብቻ አይደለም የሚገኙት። በኢርትራ አንድ አውራጃ ሰሉ /ሠራዬ/ ከሳሰታ የፈለሱ ነገደ ይሁዳ ነን የሚሉ ናቸው፣ እንደዚሁም ሱጉ የመሰሉ በሐማሴን በሠራዬና በአካለ ጉባይ አውራጃዎች የሚገኙ፣ በተጨማሪም ግሐርቲ የተባሉ በሐማሴን አውራጃ የሚሰቃለሉ ነገደ ይሁዳ ነን የሚሉ ናቸው። የዩዲት መነሣት ታሪክ የተከሰተው እንደሚባለው ከክርስትና በፊት የነበረ የእስራኤል የእረት ህግ ትተው አብዛኛው ህዝብ የክርስትና ሀይማኖት ሲቀበል በሳሰታ፣ በአገው በዳሞትና በሰሜን የነበረው ህዝብ ግን የክርስትና ሀይማኖትን መቃወም የተደረገ ሥርነት አስከፊና የሰው እልቂት እንደአስከተሉ ታሪክችን ይመሰክራል። በዩዲት ጊዜ ብቻ ግያሆን በሌሎች የኢትዮጵያ ነገሥታትም እንደ አጼ መላክ ሰገድ በ1580 ዓ.ም. በሰሜን በተለይ በፈላሾች ላይ ዘመቻ በግድረግ ብዙ የሰው እልቂት ተፈጽሟል። ትዳሚ ያዘበራል እይክበርም በሚለው ክርክርም በየዘመናቱ ብዙ ውዝግብ አስነስቷል፣ የሰው እልቂትም አስከትሏል። ይህ ሁሉ የሚያግየው የኢትዮጵያ ህዝብ ቅድመ ክርስትና የአረት ህግ ይከተል እንደነበረ ነው። ተዳግሞ ሚኒልክ ከአሰራኤል ወደ ኢትዮጵያ በተመለሰበት ጊዜ 12 ነገደ እሰራኤል አጅበውት መጥተው ሰንደነበረ ይተረካል። ከነገደ ይሁዳ እላይ የተጠቀሱ ህዝቦች ሲሆኑ ከነገደ ዜኑያም እንወለዳለን የሚሉም አሉ። እነሱም በኢርትራ በሐማሴንና

[1] ተክለፃድቅ መኮሪያ ገጽ 24

በእክለጥዛይ የሚኖሩ ናቸው፡ የእስራኤል ባህል ዘኢትዮጵያ መግባት ዘዚሁ ብቻ የተወሰነ አይደለም፣ እስከ አሁን የሚታየው የጋብቻ መሳሳትና የወንድ ልጅ ግርዝ ክርስትና ከመነሣቱ በፊት፣ በጽናጽልና በከበሮ እየታጀቡ እየተወዛወዙ መንፈሳዊ ፀሎት ማድረግ ወዘተ ከእስራኤል የተወረሱ ናቸው። አቶ ተክለ ፃድቅ መኮሪያ ከክርስትና በፊት በናፓታም ሆነ በእክሰም የነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታት እንዲሁም ህዝብ ህገ አሪት አልተተበለም ብለው በመጽሐፉ በተደጋጋሚ የሚጽፈውና የማጠቅሳቸው ዋና ዋና ምክንያቶች ለቀድሞ አግልክቶቻቸው ዘሐውልቶቻቸው የተቀረው የምሥጋናና የአምልኮት ጽሁፎች በመመልከት ይሆናል። ነገር ግን ይህ በቂ ምክንያት ሊሆን አይችልም። በዚያን ጊዜ የሀይማኖት ቅራኔና ጥለቻ እልነበረም። የታሪታይ ግብጽ አምላክ ፕታህ የላዕላይ ግብጽ ግን አሞን ሲሆኑ ንጉሡ ለሁለቱ በእኩል ደረጃ ያከብር ነበረ። ደግሞም አዲሱ የአሪት እምነታቸው በግል ይዘውት ይሆናል የቀድሞ አግልክቶቻቸው ደግሞ እንደብሔራዊ ባህል ይወሰዱት ይሆናል። ዘሀይማኖት ምክንያት ዘዓለም ቅራኔና ጥላቻን የተፈጠረ ከሰልምና ሃይማኖት መስፋፋት በኋላ ነው። የሮማ መንግሥት ክርስቲያኖችን ያሣድድ የነበረ በሃይማኖት ምክንያት ሣይሆን መግሥትን ለመገልበጥ ዓላማ አላቸው ብሎ ይጠረጥራቸው ስለነበረ ነው። ከዚህ በላይ እንደተገለጸው የግብጾች ሀይማኖት ከአሪት ሕግ ጋር ተግሣሣይነት አለው ተብሏል። የሰልምና እምነትም ከክርስትና እምነት ጋራ ተመሣሣይነት እንዳለው ለግሣመን ተሞክሮ ነበር። በዚህ መሠረት የጥንት ግብጻውያን ሃይማኖት የአሪት ህግን የክርስትና ሃይማኖቶችን የሰልምና ሃይማኖትን እንደፈጠሩ መሠረት የጣሉ ናቸው ለግለት ይቻላል። ይኸውም ከሌላ ሥልጣኔያቸው በቀደምትነት ይልቅም ካበረከቷቸው ሌላ በተጨማሪ ግብጻውያን ዘሀይማኖትም አባቶችና መሥራቾች መሆናቸውን ያስረዳናል። ነዚዩ መሐመድ የእስልምና ሀይማኖት ያሠራጨው ለየሀገሩ መሪዎች ሰለ ዓላማው በግብራራት ይብዳቢ በመፃፍ ነበር። በዚሁ መሠረት ለኢትዮጵያ ንጉሥም ደብዳቤ ጽፎ ነበረ። ደብዳቤውም እንደሚከተለው ነበረ። "እኔ መሐመድ ነቢዩ[1] ዘአንድ እምላክ አምናለሁ። ኢየሱስ የማርያም ልጅ መሆን እመለክራለሁ እሱም የእግዚአብሔር መንፈስና ቃሉ ነው። በማርያም ድንግል እንዲወርድ አድርጉ ተወለደ። የእኔን ሃይማኖት ተከታይ ሁን። እኔ የእግዚአብሔር ሐዋርያ ነኝ። ጃፋር የሚባል የአጉቱ ልጅ ከአንዳንድ መብሊሞች ጋር ወደ አንተ ግዛት ልከዋለሁ። ድጋፍህ እንዳይለየው፤ ለሚያስፈልገው ሁሉ እርዳው። የኢትዮጵያ ንጉሥ የመሐመድ ደብዳቤና መልእክተኞች በታላቅ አክብሮት ነበር የተቀበለው። መሐመድ ይሁዶችንና በጣኦት የሚያመልኩ ይዋጋል፤ በአንድ ግዚአብሔር ብቻ ያመልካል። ኢየሱስና ማርያም ያከብራል፤ ስለዚህ እንደ እኛ እውነተኛ እርቶዶክስ ነው በሚል እምነት ነበረ አቀባበል የተደረገለት። የመሐመድ ደብዳቤዎች በሌሎች ህገሮች ተጨባጭ ውጤት ሲያገኙ በኢትዮጵያ ግን ከወዳጅነት በቀር በጣም አነስተኛ ተከታዮች ነበረ ሊያፈራ የቻለው። መሐመድ ከኢትዮጵያ በኋላ ለግብጽ የክርስቲያን ሀይማኖት መሪ ግኩላስ የላከው ደብዳቤ ግለሰቡ በቢዛንታይን ንጉሠ ነገሥት አማዝ በነበረው የግል ጥላቻ የተነሣ ተቃባይነት አግኝቶ ግብጽ እሰላማዊት ሀገር በመሆንዋ ኢትዮጵያም ቡተዘዋሪ ስለነካት ከክርስትና ዓለም ተከታዮች ግንኙነትዋን እንድታቋርጥ አድርጓታል። የሀይማኖት ጥላቻ ባለመኖሩ ኢትዮጵያ ለመሐመድ ያደረገችው አቀባበል ለውጥ ባያመጣም፤ ግብጽ

[1] Alberto Pollera Lo Stato Etiopico e la sua Chiesa p 275

በሞልተኝነት ለመሐመድ ያደረገችለት ጥሩ አቀባበል በዛች ሀገር ሰር ነቀል ለውጥ ሊያመጣ ችሏል። ግብጽ የክርስትና ሃይማኖትዋን ለውጣ ታሪኳን ቋንቋዋንና ባህልዋን የሚቀይር ሰር ነቀል ለውጥ እንድታመጣ ያደረገው ማኮላስ የተባለው ሰው ሰሙ እንደሚያስረዳው ግብነዊ አይደለም ግሪካዊ ነው። ኢትዮጵያም እንደግብጽ የነብዩ መሐመድ ጥሪ ተቀብላ ብትሆን ኖሮ ኢትዮጵያውያን የግብፃውያን ዓይነት እጣ ይደርሰብን ነበረ፣ ቋንቋችን፣ ባህላችን ረሰተን ዓረባውያንና እስላማውያን እንሆን ነበረ። የአሪት ሕግ ከሞነት ግብፃውያን ሀይማኖት የተቀዳ ሰለሆነ የመሲ የአሪት ህግና የግብጽ አምልኮት ተመሣሣይ አለው ተብሏል። በዚህ መሠረት አቶ ተክለ ፃድቅ መኮሪያ ኢትዮጵያ ከክርስትና በፊት የአሪት ህግ ተቀብላለች ወይም አልተተበለችም የሚለውን ጥርጣሬ በራሱ መጽሐፍ በመጥቀስ መልስ አሰጣለሁ።

"በፈት ዳግማዊ ራምሲስ ወደ ሶሪያና ወደ ፓለስታይን በዘመተ ጊዜ መሥያደርግ ሸሽተውበት እርሱ ብቻውን ተጋጠመ ከሚለው ሥፍራ ላይ አሠላኩን አሞንን እንደምን እንደ ለመነው አሞን በምን አኳኋን መልስ እንደሰጠው አሁን ደግሞ ፒያንኪ ለንሥሩድና ለታፍክት የሚልከው መሥያደርገን ተዋጉ ብሎ ሉልክ የተናገረው ወታደሮቹና ታፍነቅት ለርሱ የሚሰጡት ያንጋገር ሁኔታ ልክ እስራኤሎች እርሷ በርሳቸው ወይም ከእውነተኛው አምላካቸው ጋር ከሚያደርጉት ንግግር ፀሎት ጋር ይመሳሰላል። የግብፅ ፈርዖኖችና የጣኦት ካህናት ለአግልክቶቻቸው የሚያቀርቡት ንግግር ጋር ተመሣሣይነቱ ግልጽ ነው። ይህን የመሰለ የቢያንዚና የታፍነክታን አነጋገር የመሰለ በዳዊት መዝሙር በብዙ ቦታ ይገኛል።

እስራኤሎች 400 ዓመት ያህል በግብጽ ሲኖሩ የግብጽን ሥልጣኔ አጻጻፍና አነጋገር መውረሳቸው የታወቀ ነው። በተለይ የእስራኤሎች የመጀመሪያው መሪ ሕግና ሥርዓት ጽፎ የሰጣቸው መሲ በዳግማዊ ራምሲስ ዜት መንግሥት የፈርዖኑ የለጅ ልጅ እየተባለ የግብጾችን ግናቸውንም ጥበብና ፅውቀት እየተማረ ካደገ በኋላ ሕጉንና ሥርዓቱን እርሱም ሊሉችም ሊቃውንት እነ አሮን ከግብጽ የወረሱትን ፅውቀት ለወገኖቻቸው ለእስራኤሎች ሰጥተው ይህ እውቀት ሲወርድ ሲዋረድ እሰከ ዳዊት ከዚያም እሰከ ልጅ ልጅ ደርሶ ይሠራበት ነበር ማለት ነው።

እንደዚሁም የኢትዮጵያውያን የፒያንኪ ያባቶቹና የተከታዮቹ ሥልጣኔና ልማዳቸው ብቻ ሳይሆን ሃይማኖታቸው ንግግርና አፃፃፋቸው ዘመሉ የግብጾች መሆኑ ጥርጥር የለውም። ነገር ግን እነዚህን የናፓታና የመረዋ ነገሥታት በግብጻውያን የጣኦት አግልክት በነአሞን በነጥታህ ማምለክ ብቻ ሣይሆን ነገሥታቱ ለአግልክቱ ሊታን ካህናት እየሆኑ የሠሩትን በአሪት እንደሚያምኑ እውነተኛውን እግዚአብሔር እንደሚያመልኩ አድርገው ያሣራችን ሊቃውንት ከቀድሞ ጀምሮ የነቱት እሰከ ዛሬ ድረስ የኢትዮጵያ ነገሥታት ከክርስትና በፊት በዘነ አሪት እያመኑ እውነተኛው እግዚአብሔርን ያምኑ ነበር እየተባለ ይነበባል። ይህንንም የናፓታንና የመርዌን የእክሰምን ታሪክ ከማጥናቴ ከአሥር ዓመት በፊት እኔ ራሴ አምን ነበር። ነገር ግን ምናልባት ዛሬ ባንድ ከፍል በሰሜን ወይም በቤንሻንጉል ግዛት እንደሚገኙት ፈላሾች ያንኒዝም የነዘህ አባቶች ከእስራኤል ሀገር መጥተው በእግዚአብሔር እያመኑ ባንዱ ከፍል አንዳንድ ነገድ ሆነው ተቀምጠው ይሆናል እንጂ ህዝቡ ከንጉሡ በዚያን ዘመን በአሪት ህግና በእውነተኛው አምላክ የማያምኑ መሆናቸውን የሐውልቱም የብራናውም ፓፒሩስ ጽሁፍ ያስረዳል። ያንዳንዶቹ

ስም አስተርካሚን አርድ አሚን አስሮ አርከሚን ሲል የአሞን አሚን ቤተ መቅደስ አገልጋይነታቸውንና የዚህ ጣኦት ፍቅረኛ መሆናቸውን ለመግለጽ ነው። እንኳን አነርሱ የመጀመሪያ ካማዊ ንጉሥ የምናደርገው ሰዋታህ የሚባለው በታህታይ ግብጽ ዋነኛ አምላክ በፕታህ የሚያምን መሆኑ ስመ ያስረዳል[1]

ተራ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ ነኝ ሐበሻ ነኝ ይላል፣ ነገር ግን የኩሽ ወይም የካም ዘር ነኝ ብሎ አያምንበትም። ይህን የሚሉት ከኩሽ የናህ የልጅ ልጅ በማለድ የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ምሁራን ናቸው። የውጭ ሀገር ምሁራንም የቃሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ በመውሰድ ነገር ግን ከኩሽ የናህ ልጅ ጋራ ግያዛምዱ ኢትዮጵያውያንን የኩሽ ወይም የካም ዘር ብለው ይመድቡዋቸዋል። የኢትዮጵያውያን የኩሽ ወይም የካም ዘር ተብለው የተመደቡበት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ዘር በካም፣ ሴም፣ ያፌት በመመደባቸው አይደለም። ካም ወይም ኩሽ የሚል አጠራር ለኢትዮጵያውያን ከኤውሮጳውያን ምሁራን የተሰጠ ስያሜ ከሊሉት አፍሪካውያን ጥቁሮች እንደዚሁም ከዓረቦች፣ ኤውሮጳውያን፣ ከብጫ ህዝቦች ለመለየት እና በዘር ተለይተን እንድንመደብ ብቻ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ የሰው ዘር አከፋፈል በሀይማኖት የተመሠረተ ስለሆነ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም። እንዲሁም በኤሮጳውያን የተሰጠን የዘራችን አጠራር ተቀባይነት አይኖረውም፣ ምክንያቱም ካምና ኩሽ በግለት ዘራችን መጥራት የኢትዮጵያ ህዝብ ስሜትና ፍላጉት ከግንዛቤ ስለማይገባ ነው። የኤውሮጳውያን ምሁራን በአንድ በኩል ኩሽ ወይም ካም ለኢትዮጵያውያን ብቻ የተሰጠ ሰያሜ ሲያደርጉ በሴላ በኩልም በአካባቢያችን የሚመሳሰሉን ህዝቦች (ግሩፕ) አንድ አካል አድርገው ይመድቡናል። ኮንቲ ሮሲኒ የካም ዘሮች በአንትሮፖሲጂስቶች ኢትዮጵያውያን ተብለው ይጠራሉ ካለ በኋላ የአመጣጣቸው የተለያዩ አስተሳሰቦች እንዳሉ ይጠቅሣል።

1ኛ/ አንዳንዶቹ የነጭ ዘርና የጥቁር ዘር ድብልቅ ክልሶች ናቸው ይሉዋቸዋል።

2ኛ/ ሌሎች ንፁህ ህዝብ ራሱን የቻለ ዘር ያልተከለለ አፍሪካዊ የሆኑ አድርገው ሲመድቧቸው

3ኛ/ ሌሎችም የነጭ ዘር መደብ የሆኑ የዓረቦችና የጥቁሮች ክልሶች ያደርጋቸዋል።

ኮንቲ ሮሲኒ በፊሎሎጂ በኩል ስለካም ወይም ኩሽ ዘሮች የተደረሰበት የቋንቋ አከፋፈል የካም ቋንቋዎች ሁሉ ካማዊ ወይንም ኩሻዊ የተባሉ የጋራ ጠባያቸው ተለይቶ የሚታወቁ መሆናቸውን ከገለጹ በኋላ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በ3 ይከፈሉ እንደ ነበረ ገልጸ፣ እነሱም

1ኛ/ ኢትዮጵያዊ 2ኛ/ የቀንት ግብጻዊ 3ኛ/ የበርበር ሊቢያዊ ተብለው ይታወቁ እንደነበረ በግለት ይዘረዝራል። ከካም ቋንቋዎች ጉን ለጉን የሚሄዱ የሴም ቋንቋዎችም አሉ። እነሱም 1ኛ/ የአሲሮ ባቢሰናውያን 2ኛ/ ፊኒሚውያን 3ኛ/ ዕብራይስጥ 4ኛ/ ዓረብኛ ናቸው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተካሄዱ ምርምሮች ግን ከላይ የተጠቀሱ ቋንቋዎች ሁሉ ለአራት ይከፈላሉ፣ እነሱም 1ኛ/ ጥንታዊ የግብጽ ቋንቋ 2ኛ ሴማዊ 3ኛ/ በርበር ሊቢያዊ 4ኛ/ ኩሻዊ ተብለው ሲጠሩ፣ በመካከላቸው ትስስርና ግንኙነት ያላቸው ናቸው ይባላል። ይህ የቋንቋ ግንኙነት መሠረቱ የት እንደተፈጠረ ለሚቀርበው ጥያቄ የተለያየ መልስ ተሰጥቶበታል። 1ኛ/ ኩሻዊነቱ አፍሪቃ 2ኛ/ ከዓረብ ሀገር 3ኛ/ ከሌላ አስያዊ ሀገር።

በኢትዮጵያ የኩሽ ቋንቋዎች በበኩላቸው 1ኛ/ ላይኛው ኩሽ፣ በኛ 2ኛ/ ግዕዝላዊ ኩሽ አገው 3ኛ/ ደቡብ ምሥራቅ ኩሽ የታችኛው ኩሽ፣ ማለ፣ አፋር ፣ ሰማል፣ አሮሞ፣ ሲዳማ የተባሉ ይከፈላሉ።

ኮንቲ ሮሲኒ ከተጠቀሰው የካም ዘር አመራርና አከፋፈል ሌላ ሌዶ ቼሞሪያኒ የተባለው ኢጣሊያዊ በአንትሮፖሎጂ ወይንም በፊሎሎጂ የዘር አከፋፈል ግይራቅቅ በደፈና ኩሻውያን ሁሉ በአንድ የጋራ ሰም ኢትዮጵያውያን ብሎ በመጥራት ነው። ሌዶ ቺፕሪያኒ ኢትዮጵያውያን፣ ሶግሊያውያን፣ ሱዳናውያን በአጠቃላይ የምስራቅ አፍሪካ ሕዝቦች ብቻ አይደሰም ኢትዮጵያውያን ብሎ የጠራቸው፣ በመላው አፍሪካ የሚገኙ የኢትዮጵያ መልክ ያላቸው ሕዝቦች ኢትዮጵያውያን ናቸው ወይም የኢትዮጵያ (ጉሩጥ) ናቸው ይላቸዋል። እንደ ምሳሌ ብሎ የሚያተርባቸው በደቡብ አፍሪካ የሚገኙ ዙሉ የተባሉ ጎሳዎች ይገኙባቸዋል። በመጀመሪያ ግን ሌዶ ቺፕሪያኒ ግነው የኢትዮጵያ እና የመላው አፍሪካ ጥቁር ሕዝብ ጠላት አንጂ ወዳጅ ተብሎ የሚጠረጠር ሰው አይደለም። ወረ- አፍሪካውያን በርካታ መጻሕፍቶች የደረሰ አከራረ ዘረኛ ግለሰብ ነው። አፍሪካውያንን ሰግጥናት በመላው አፍሪካ በመዘዋወር ከደረሳቸው መጻሕፍቶች በአሥሩ አንዳንድ ፍሬ ነገር ለመጥቀስ ያህል ኢትዮጵያዊ በአፍሪካ ምድር የተፈጠረ ሰው ነው ወይስ ከአስያ የመጣ ነው ሆሚሉ ጥያቄዎች ቀርቧል ለወደፊትም ሊቀርቡ ይችላሉ። በዚህም ጥያቄ የነጭና ጥቁር ዘር ድብልቅ እንዳልሆነ በአፍሪካ የተፈጠርን ራሳችንን የቻልን ንፁህ ዘር መሆናችንን የዙሉ ኢትዮጵያውያን እምነት መሆኑን እገምታለሁ። መራት ብዙ የሰፅዋት አይነት እንደምታፈራ ሁሉ ብዙ ዓይነት የሰው ዘርም አፍርታለች። ከሰው ዘሮች አንዱ ከፍል እኛ ኢትዮጵያውያን ነን። ኤውሮጳውያን ማስረጃ ሳይኖራቸው የሌላ ዘር ቅጥያ ሊያደርጉንም አይገባቸውም። ኢትዮጵያውያን ለሴምና ለኩሽ እንደሚከፈሉ በሰፊው ይነገራል፣ እንዲሁም ሴም የሚባሉ የኢትዮጵያ ታሪክ ሰሪ ሌሎች በኢትዮጵያ ታሪክ ከፍተኛ ታሪክ ያልተጫወቱ ይሽውም አባባል አሳሳች ነው፣ የቋንቋ ጉዳይ ነው የዘር ጉዳይ አይደለም።

[1] ሌዶ ቺፕሪያኒ ዘረኛ ብቻ ሊባል አይገባም የስውየውን ማንነት በትክክል አይገልፀውም የዘረኞች አለቃ፣ አንፀባራቂ ኮከብ ዘረኛ ቢባል ምናልባት ማንነቱን በመጠኑ ይገልፅ ይሆናል። ቺፕሪያኒ እንደ ጀርመኖች ዘረኝነቱን ያተኮረው በይሁዶች አይደለም፣ የቺፕሪያኒ ዘረኝነት በጥቁሮች ብቻ ያተኮረ ነው። አፍሪካን እየተዘዋወረ ከንዘኝ በኋላ በደረሳቸው መጻሕፍቶች ስለ ጥቁሮች የሐንጎል ዝቅተኛነት ከመግፋም በላይ አፍሪካውያን ዝቅተኞች ሰዎች ናችሁ በሚሉት ጊዜ ቅሬታ ሊያድርባቸው አይገባም፣ አንዲያውም ማንነታቸውን አውቀው የነጮች የበታች መሆናቸውም ቅር ሳይላቸው አምነው ተቀብለው፣ ዝቅተኛ የጉልበት ስራዎች በቅንነት አገልግሎታቸውን መሥጠት አለባቸው በማለት ለጥቁሮች ምክሩን ይሰግላል። ይህን የምርምር ስራ በሚባልበት ከፍተኛ ድጋፍ ለስጡት በደቡብ አፍሪካ የኢጣሊያ አምባሳደር ምስጋናውን ያቀርባል። መጽሐፉም ወደ እትመት ሊቀርብ ደጋፊና አስታዋቂቂ የነበረው ከግርቲኒ በኋላ የኤርትራ ገዢ የነበረው ኮፊዶ ዮሲ የተባለው ሰው ነበረ። ቺፕሪያኒ እንደሚሰው አፍሪካ መጥተው ከግያውቁ ኤውሮጳውያን ብዙ ተቃውሞ እንዳጋጠመው ጠቅሶ፣ ነገር ግን በአፍሪካ ብዙ ጊዜ ከኖሩ ኤውሮጳውያን ውስጥ ከነጋገራቸው ሚሲዮውያን፣

[1] Lido Ciprisni: Considerazioni Sopra Il Passato E L'Avvenire Delle popolazioni Africane

ሳይንቲስቶች፣ አስተዳዳሪዎች፣ ሰፋፊ የእርሻ መሬት ያላቸው ዝቡሬዎች ከእሱ ጎሳብ እንደሚሰግሙ ስለሚያውቅ ፀሰራው እንዲጎብት አድርገዋል።

የሰው አንጎል የውጭም የውስጥም በመሰካት አስተግግኝ የከፍተኛ እና የዝትተኛ ዘር ምልክት ሰላልተገኘ በደም ምርመራ ግሰሪኛ የሚሆን ስለጠፉ የጥቁር ሕዝቦች ዝትተኛ ፍጡር መሆናቸውን የሚረዳ ግሰሪኛ የጣውሉጂ ጉዳይ ነው ወይም "የሚንታል" ጉዳይ ነው በማለት ምርምራ በግድረግ ተጥሏል። አፍሪካውያን በአሁኑ ጊዜ ዘራቸው በወሊድ ማነስ እየመነመነ በመሄድ ላይ ይገኛል።

ለወደፊት አፍሪካን የሚኖሩባት ነሮች ናቸው። ከነሮች ውስጥም እንደ ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ የመሳሰሉት ያረጁ ሕዝቦች አምራች የሰው ኃይል መስጠት የማይችሉ ስለሆኑ አምራች የሰው ኃይል መስጠት የምትችል ኢጣሊያ ብቻ ናት ይላል።

ወደፊት አፍሪካ ኢጣሊያዊት እንደሚትሆን ጥርጥር የለውም። በመላው አፍሪካ ከጥቁር ሰዎች ጉን ቀያይ ሰዎች እንደሚገኙ አመልክቱ፣ ይህ ሁኔታ ብዙ የኤውሮጳ ተመራማሪዎች የጥንት ግብጾች ግዛት በመላው አፍሪካ ተሰፋፍቶ እንደነበረ ብለው ሲተረጉሙት፣ ቺፕሪያኒ ግን በመላው አፍሪካ ተሰራጭተው የሚገኙ ቀያይ ዘሮች የጥንት ግዘፃውያን ሳይሆኑ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን እምነቱ ይገልፃል።

በመላው አፍሪካ የሚገኙ የጥንት የግብፅ ቁሳቁሶችና የሰልጣኔ ምልክቶች ከግብፅ የመጡ ሳይሆኑ ከአፍሪካውያን ወደ ግብፅ የተሰራፉ መሆናቸውን አምነቱ ይገልፃል።

በዚህም መሠረት ሰታላቁ ለግብፅ ሰልጣኔ መሠረት የጣለት አፍሪካውያን መሆናቸውን ይገመግማል። ቺፕሪያኒ ኢትዮጵያውያን በሚመለከት በተሰይ ወገናዊነት የሌለው አስተያየቱ ለመሰጠት ያህል በማለት የዛሬ እና የአለፈው የአፍሪካውያን ታሪክ በማጤን የሰውነታቸውና የእውቀታቸው አያሽቆለቆ ከመሄድ ላይ ዘመሆኑ በአፍሪካ ባደረገው ሰፊ ጥናት መሠረት ኢትዮጵያውያን ስልጣኔን የመቀበል ችሎታ እንደሌላቸው በግያሻግ ሁኔታ መወሰን እንደሚቻል ገልጧል።

የመጽሐፉ አስተዋዋቂ መጽሐፉ በታተመበት ጊዜ የኢርትራ አገረ ገዥ የነበረው ኮሬደ ዞሲ የተባለው የቺፕሪያኒ ሃሳብ መሰረ በመሰረ በመደገፍ ከፍ ያለ አድናቆት ገልጸዋል። የኢትዮጵያ ዘር /የነም ዘር/ በአፍሪካ ከመቼ ጀምሮ እንደሆነ በሚመለከት በሞላው አፍሪካ ለምርምር የተካሄዱ ቁፋሮዎች የአንድ ጥቁር /ኔግሮ/ ወይም ቦቪማን ወይም ድንክ ሰው የሚመስሉ የጭንቅላት አጥንት ቅሪቶች አልተገኙም። በአንፃሩ ኢትዮጵያውያን የሚመስሉ በብዛት ተገኝተዋል። አንዳንድ ምሁራን ጥቁሮች /ኔግሮ/ በአፍሪካ የታዩበት ዘከርስቶስ ልደት በፊት 1500 አካባቢ ሲያደርጉ ይሄ ባይሆንም ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ3200 ዓመት እንደማያልፍ ገምተዋል

አፍሪካ የኢትዮጵያውያን ዋና ሀገራቸው መሆኗን ብዙ ማሰረጃዎች አሉ ካለ በኋላ በዋቢነት በርቶን የተባለ ደራሲ ያጠቅሳል፣ የኢትዮጵያውያን ዓይነት የሰው ልጅ ሰድሚ በአፍሪካ ጥንታዊነት በብዙ ሺህ ዓመት ተብለ የሚለካ አያደለም። በአርኪዎሎጂ ቁፋሮ ሰድሚ የማወሰን ነው።

በአፍሪካ የተካሄደው ማንኛውም ሰልጣኔ በኢትዮጵያውያን ወይም ከኢትዮጵያውያን የተገመዱ ሕዝቦች ሙከት በመሆናቸው የአፍሪካ የጥንት ታሪክ የኢትዮጵያ ተብሎ ሊጠራ ይገባዋል።

ንፁህ ጥቁር /ኔግሮ ዘር/ በጊኒ ኮባሕረ ሰላጤ አካባቢ ካልሆነ በስተቀር በሊላ የአፍሪካ ምድር ቢበዛም ቢያንስም ከኢትዮጵያውያን ያልተገቀሉ አይገኙም።

ከአፍሪካ ምድር ወገብ በታች የሕዝቡ 2/3 የባንቱ ዘር ናቸው። በመላው አፍሪካ ተሰራጭተው የሚገኙ ባንቱ የተባሉ ጎሳዎች የኢትዮጵያውያን ከልሶች ናቸው ተብሏል። በተሰይ የሚጠቀሱ የደቡብ አፍሪካ ዙሉ፣ የሩዋንዳ ብሩንዲ፣ ሳንኩሩ፣ የዛምቢያ፣ ባይሳ፣ የሰኔጋል፣ ቁኩለቺና ሰንኪ ሊሉችም ቶልቢ እና ወሎፍ የተባሉ ይገኙባቸዋል። ሊሉች በዘር የተለያዩ ሲሆኑ በተለይ ከኢትዮጵያውያን የሚገናኙ የናይጀሪያው አውሳ የተባሉ በቋንቋ ነው።

ፀረ- ጥቁር ሕዝብን የኢጣሊያ ዘረኝነት ከፋሽስት የመጣ አይደለም። የኢጣሊያ ፋሽስቶች መሪ ሞሶለኒ ዘረኛ አልነበረም፣ ዘረኞች ግን ተጠቅመውበታል።

ጣሊያኖች በሙሉ ፀረ- ጥቁር ሕዝብ ዘረኞች ናቸው ለማለትም አይቻልም ይሆናል። ቺፕሪያኒ የሚወክለው በተለይ የአንድ የኢጣሊያ ከፍለ አገር የኢትሩስካ ወይንም ቶስካና ነው።

ኤትሩስካውያን ዘራቸው በትክክል ባይታወቅም የነጭ ዘር ወይም አሪያን ካውካዝያን ዘር እንዳልሆኑ ግን ተረጋግጧል። ይሄም ሆኖ በአሁን ጊዜ እንደ ቶስካና ከማርቲኒና ቺፕሪያኒ ጀምሮ ነሮች ነኝ በማለት የሚኮራ ሌላ ነሞ ዘር ያለ አይመስለኝም። ኢትሩስካውያን የሮማ መንግሥት ከመሠረቱ ሦስት ጎሳዎች አንዱና ዋንኛው ናቸው። ወደ ኢጣሊያ የሰፈሩት ከትንሿ እስያ መጥተው ነው። ቶስካና በተለይ ዋና ከተማዋ ፈሬንትሴ ለኢጣሊያ ቋንቋ የፈጠረች ናት። በኢጣሊያ ሩኒዝም ስርገው ገብተው ዘረኛ እንዲሆን ያደረጉ እነሱ ናቸው። በኢርትራ ዘረኝነት እንዲመሠረት፣ ሕዝቡ ትምህርት አልባ ሆኖ እንዲኖር ያደረገ ትልቁ አገረ ገዥ ነኝ እያለ ራሱ ይጠራ የነበረው ፈርዲናንዶ ማሪቲኒ የቶስካና ተወላጅ ነው። ቺፕሪያኒም የዘረኝነት ሞያው ያካሄደ የነበረው ፈሬንስ ከተማ ዋና ጣቢያው በማድረግ ነው።

ይህና የመሳሰሉት ሁኔታዎች እያንጸባረቡን እኛ እርስ በርሳችን እየተፋጀን የዓለም ሕዝብ መሳቅያ ዘመሆን እንገኛለን። በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያውያን አይደለንም እያልን ስማችን እና ዘራችን እስከ መካድ ደርሰናል። በታሪክና በዘር የሚያቀራርበን ዘመፈለግ ይልቅ የሚለያዩን ጥቃቅን ጉዳዮች እንዲንፀባረቁ እያደረግን እንገኛለን። ኩሽ ወይም ካም የሚለው መጠሪያ ትተን እንደዘሁም ዘቋንቋ መለያየታችን መሠረታዊ ልዩነት አለመሆኑም እያመነን ሁላችን ዘረኛው ቺፕሪያኒ እንኳን ያመነበት በእንድ ኢትዮጵያዊ የሚለው መጠሪያ ተሰባስበን ሀገራችንን ብንገነባ እሞቲዎች ያደርግን ነበር፣ የኢጣሊያ ቅኝ ገዥዎች መሣሪያም እንሆንም ነበር።

የቋንቋ ጉዳይ ጊዜ የሚለየው ጉዳይ ነው። ቋንቋዎች እርስ በእርሳቸው ተጠላይረው ተቀባይነት ያገኙና የተስፋፋ ቋንቋ ብሔራዊ ቋንቋ ይሆናል፣ ሊሉች ቋንቋዎች ይጠፋሉ። ኤውሮጳውያንም በዚህ አይነት ነው እንድ ቋንቋ ለመናጠር የቻሉት። በቋንቋቸው እንጠቀማለን የሚሉ ቡድኖች ካሉ እገዛ ሳያደረግላቸው ብሔራዊ ኢትዮጵያዊ ቋንቋ እማርኛ ግን እንዲዳብር መጣር ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚለው ሁሉ ተግባር ነው።

የተለያየ አስተሳሰብ ያላቸው የውጭ ሀገር ሰዎች ሳይቀሩ ኢትዮጵያውያን ብለው ሲጠሩን እኛ ግን በሰማችን መጠቀም እንኳን

አንፈቅድም። ተፈጥሮ አንድ ያደረገን በሰው ሰራሽ ሰግፍረስ እየሞከርን እንገኛለን።

ብሔራዊ ኢትዮጵያዊ ቋንቋ ለመሆን መመዘኛ የሚያሟላ አማርኛ ቋንቋ ነው። አማርኛ ብሔራዊ ቋንቋ ቢሆን የሚጠቀም እንጂ የሚጐዳ ኢትዮጵያዊ አይኖርም። ባለፉት ጥቂት ዓመታት እንደታየው ኢትዮጵያ ሀገራችን አንድነቷ በፅኑ መሠረት የተገነባ ባይሆን ኖሮ ከፍ ያለ አደጋ ሰሕልውናችን የሚያሰጋ ይደርስብን ነበረ። አንድ ሀገር የቋንቋ አንድነት ከሌለው እንድነቱ አስተማማኝ እንዳይሆን ሊያደርገው ሰለሚችል በተቻለ መጠን አንድ ቋንቋ ብቻ መፍጠርና መጠቀም ይኖርብናል።

ፊረንጆች ኢትዮጵያውያንን የጎሳዎች ከምችት ወይንም የጎሳዎች ሙዘየም /ሞዛይክ/ እያሉ ይጠሩናል። ይሄ ግን የራሳቸው ጎሳዎች በመርሳት ነው፤ ለምሳሌ ግሊያኖች ከእኛ የበለጡ ጐሳዎችና ቋንቋዎች ነበሯቸው፤ አሁንም አሏቸው፤ ነገር ግን ቋንቋቸው ቋንቋ ተብለው አይጠሩም ዲያለክት ተብለው እየተጠሩ አሁንም ይጠቀመብታል።

7ኛ. <u>የደቡብ ዓረብ ሳባውያን እና ኢትዮጵያውያን</u>

ኤውሮፓያውያን የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፊዎች ሁሉ በአቀራረብ ቢለያዩም አማርኛ እና ትግርኛ ተናጋሪ የኢትዮጵያ ሕዝብ የዓረብ ክልሰ አድርገው ይመድባቸዋል። ይህ አባባል የሕዝቡ ሰሚትና እምነት ያልተከተለ፣ በታሪክም በቂ ማስረጃ ያልተገኘበት፣ መሠረት የሌለው ሰለሆነ የታወቀው ኢጣሊያዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ደራሲ ኮንቲ ሮሲኒ አቀራረብ በመከተል እቃወመዋለሁ። ከቀይ ባሕር በስተምሰራቅ ዓረቦች ከጥንት ጀምረው ሰፍረው ይገኛሉ።የደቡብ ዓረብ /የመን/ ከሌሎች የተለዩ ናቸው፣ ይህውም [illegible] የብዙዎቹ ምሁራን [illegible] ደንበኛ ዓረቦች አይደሉም። የደቡብ ዓረብ /የመን/ መሬት ከዓረቦች በፊት ቀድሞ የሠፈሩበት የክም ዘሮች መሆናቸውን ተረጋግጧል። ሰብዙ ዘመናት ዓረቦች ተብለው ይጠሩ የነበረ የግእከላዊና ሰሜናዊ የዓረብ ክፍለ ሀገር ብቻ ነበሩ። በቋንቋም ልዩነት አሳቸው በሰሜናዊ ዓረብኛ እንደ ፊረንጆች አርቲክል ለመግለጽ ሊፈልጉ "አል" በቃሉ መጀመርያ ይጨምራሉ፤ አልማሊክ። በደቡብ ዓረብ ግን በቃሉ መጨረሻ "አን" ይጨምራል ማሊካን፣[1] በአማርኛ ንጉሡ የሚለው ከደቡብ ዓረብ ተመሳሳይነት እንዳለው ያሳያል። ደቡብ ዓረቦች አንድ ጎሳ ብቻ አልነበሩም፣ ሚአይና ሰባውያን የታወቁ ሲሆኑ በቅድሚያ የበላይነት የነበራቸው ሚአናውያን ነበሩ፣ በኋላ ዘመን ሳባውያን ን የበላይነት ጨብጠው ነበር። ደቡብ ዓረቦች የንግድ ሰዎች ነበሩ፣ "ንግዳቸውም እጣን፣ ከርቤ፣ ወርቅ፣ ሽቶ፣ ወዘተ... ነበረ።

ከየመንና ከአካባቢያቸው ወደ የሥልጣኔ መእከል ሆነው የነበሩ የመካከለኛ ምሥራቅ ሀገሮች በግመል ማመላለስ ከእነሱም የሚያስፈልጓቸውን ሸቀጦች ወደ ሀገራቸው ማምጣት ነበረ፣ በኋላ ጊዜም በባሕር ንግድ ያደርጉ ነበረ። ኮንቲ ሮሲኒ ከ18ኛው የግብፅ ሥርወ መንግሥት ጀምረው ደቡብ ዓረቦች በባሕር ንግድ ግብፃውያንን ተክተው እንደነበረ ብሎ የፃፈው ትክክል አይመስልም፣ ምክንያቱ ከክርስቶስ ልደት በፊት 1500 ዓመት /18ኛው ዲናስቲ/ ደቡብ የመን የታወቁ አልነበሩም።

[1] Conti - Rossini : Storia d' Etiopia p 91

8ኛ የኢትዮጵያ ፊደል

ደቡብ ዓረቦች ወደ መካከለኛ ምሥራቅ በንግድ ሲመላለሱ ፊደል ከቀድሞ የግሪክ ኮንሶናንታዊ ፊደል ወደ ሀገራቸው አስገብተው ነበር። ስለሚን ዓረቦችም ሲያሰራፉት ቆይተዋል። ኮንቲ ሮሲኒ[1] ኮንሶንታዊ ደብብ ዓረቦች ከግሪክ የመሰጿቸው ፊደሎች አስራ አንደኛው መቶ ክ/በፊት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው ይላል፣ ይህ ግን ሊሆን የማይችል ነው፤ ምክንያቱም ግሪኮች ራሳቸው ከፊኒሳውያን ፊደል የተማሩት በ1000 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው።[2]

ስለዚህ ሳባውያን ከግሪኮች ፊደል የወሰዱት ቢያንስ 2-3 መቶ ዓመት በኋላ መሆን አለበት። ስለፊደል ሠምናስብበት ጊዜ የእኛ ፊደል የሳባውያን ፊደል ነው እየተባለ በአሁን ጊዜ በዙ ኢትዮጵያውያን የላቲን ፊደል ነው የሚለማማን እያሉ በላቲን ፊደል ሲጠቀሙ እናያለን። ነገር ግን ትክክል አገማማያ አያደለም፣ ወደ ኋላ ሲጉተታቸው ካልሆነ በስተቀር የላቲን ፊደል ለቋንቋቸው የሚስማማቸው አያደለም።

የፊደል ፈጣሪዎች እንዳልሆን ተቆጥረን ከባዕድ ፊደል መበደር አሳፋሪ ነው። በኅለም ፊደል /የሂሮግሊፊክ/ ፊደል ፈጣሪዎች ግብፃውያን መሆናቸው የታወቀ ነው። ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ1500 ባለው ጊዜ /ፊኒሳውያን/ ባለኮንሶናንት ብቻ የሆነ ፊደል 20 የግብፃውያን ምልክቶች ሠመሙሰደ የሴማውያን ፊደል በ1000 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ፈጠሩ። ግሪኮች ሰልጣኔ በሂዱበት ሀገር ሁሉ ፊደላቸው ሰላሰፋፋ ሮማውያንም ከግሪኮች መሰደው ባስ 23 ፊደል አቋቋሙ። ሰሂሮግሪፊክ ፊደሎች ሁሉ መሠረት የሆነው ስናስታውስ ወደ ሀገራችን የሚሰዘን ነገር አለ። ኮንቲ ሮሲኒ እንደጎሰፀው የግብፅ ሂሮግሪፍክ ጽሕፈት ምልክት በፈረንሳዊው ቻንፖሊዮን ጥበብ ሊነበብ የተቻለ ሲሆን፣ በመሮዊ የሚገኘው ሞንሆዊ /ያልሰለጠነ/ የሂሮግሪፊክ ፊደል እስከ አሁን ሊነበብ ሰላልተቻለ ብዙ የዘገራችን ታሪክ ታፍኖ ቀርቷል።

ሊነበብ ያልተቻለ ጥንታዊው የሂሮግሊፊክ ፊደል በሞሮዊ ብቻ አይደለም የተገኘው፣ በአክሱም፣ በዳዕሮ[3] ጳውሎስም ከአስመራ በስተደቡብ ተመሳሳይ ጽሁፍ ተገኝቷል። ኮንቲ ሮሲኒ እንደሚለው ከግብፃውያን የተሰራጨ የሰልጣኔ ምልክት ነው ብሎ ይተረጉመዋል። ነገር ግን ያልሰለጠነ ጥንታዊ ጽሑፍ ወይም ስእል ከግብፃውያን ሊመጣ አይችልም፣ ጥንታውያን ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን የፈጠሩት የመጀመርያ ስእል ወይም ፊደል ቀብሰ መወሰድ አለበት። ግብፀውያን የኢትዮጵያውያንን ሂሮግሊፊክ ፊደል አሻሽለው አዲስ የሂሮግሊፊክ ፊደል ፈጥሯል ቢባል ትክክለኛ ታሪክ ይመስላል። ስፊደል ጀማሪዎች እንግዶች ስላልነበርን ነው፣ ከሳባውያን ፊደል መሰደን አሻሽሰን አዲስ ለቋንቋችን የሚስማማ ፊደል የፈጠርነው። ኢትዮጵያዊ ፈጠኖን ታርሐቃ የተባለው ከክርስቶስ ልደት በፊት 788፣ በስራ ላይ ባዋውልም "ዲሞቲክ" የተባለ ፊደል /ፈጥሮ ለግብፃውያን ዘርግቶላቸው ነበረ። ግብፃውያን ግን የተሻሻለ ለመናዊ ፊደል ቢመጣም የቀደሞው ፊደላቸው ሂሮግሊፊክ መጠቀም ቀጥሏል። ኤሮጳውያን የሀገራችን ታሪክ ፀሐፊዎች ኢትዮጵያውያንን ታሪክ አልባ፣ ሰልጣኔ አልባ አድርገው በመቁጠር፣

[1] Conti - Rossini ibd p 94
[2] New Standard Encyclopedia V.A
[3] Conti - Rossini Storia d' Etiopia p 108

በእንግሩም ዓረቦች የስልጣኔ አባቶች በመገመት፣ ደቡብ ዓረቦች ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋ፣ ስልጣኔ፣ ፊደል እስገቡ እያሉ በሐንጎላችን እንዲቀረጽ አድርገውብናል።

በአጠቃላይ በዓለም የፊደል መፈጠር እንደትውልድ ሀረግ ስንገመግመው

1. የመጀመርያ ኢትዮጵያዊ የሄሮግሊፊክ ምልክት ፊደል ሲፈጠር
2. የግብፃውያን የሄሮግሊፊክ ምልክት ፊደል ተጣዩ ሆነ
3. የፈኒሳውያን ደንበኛ ባለ ኮንሶናንት ብቻ ሴማዊ የመጀመርያ ፊደል ተፈለሰፈ
4. ከፈኒሳውያን ተበድረው የኤውሮጳውያን ኮንሶናንት እና ቫውል ያለው የግሪክ ፊደል ተፈለሰፈ
5. የላቲን ፊደል ከግሪክ ተበድሮ ተሻሽሎ የተፈጠረ ነው
6. የራሺያ " " " " " "
7. የሳባውያን" " " " " "
8. የዓረብኛ ፊደል ከሳባውያን ተሻሽሎ የተፈጠረ ነው
9. የዕብራይስጥ " " " "
10. የኢትዮጵያ ፊደል " " " "

ኮንቲ ሮስኒ እንደጻፈው ከመቼ እስከ መቼ ብሉ ባይገልፅም የደቡብ ዓረቦች /የመን/ ለብዙ መቶ ዘመናት ዓረቦች ተብለው አይታወቁም እና አይጠሩም ነበር።[1] ዛሬ ሳባውያን የሉም የመኖች ዓረቦች በሚል ስም ተጠቃልሏል፣ ፊደላቸውም የለም። የላቲን፣ የሩስያ፣ የሳባውያን ፊደሎች የግሪክ ፊደሎች ተብለው እንደማይጠሩ ሁሉ የኢትዮጵያ ፊደልም የተወሰደው እንደ ዓረብኛ ከሳባውያን ይሁን እንጂ በጣም ተሻሽሎ እና ተለውጦ የተሰራ ስለሆነ ኢትዮጵያዊ ተብሎ ይጠራል እንጂ ሳባዊ ተብሎ አይጠራም። ኮንቲ ሮሲኒ የሌሎች መሁራን ሃሳብ በማንፀባረቅ የሳባውያን ፊደል መልክ ግለት በቆንጅና በዓለም ካሉ ፊደሎች ተወዳዳሪ የለውም ብሎ ፅፏል።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ፊደልም ከብዙ መቶ ዓመታት የለውጥ ሂደት በኋላ የሳባውያን ፊደል ወደ ቋሚ የኢትዮጵያ ፊደል ተለውጧል። ኢትዮጵያውያን በጥንታዊ ሳባዊ ፊደል ያደረጉት ለውጥ መጠነኛ ሲሆን ሳባውያን ግን የራሳቸው ፊደል ብዙ ለውጥ አድርገውበታል፣ ቆቀንት የሳባውያን ፊደል አፃፃፍ እንደ የጥንቱ የግሪክ አፃፃፍ ከቀኝ ጀምሮ ወደ ግራ፣ ከዚህም ወደ ቀኝ፣ እንደገና ወደ ግራ እያለ የሚሄድ ነበር። ኢትዮጵያውያን ግን ከሴሚናች ተለይተው ለመጀመሪያ ጊዜ ከግራ ወደ ቀኝ ብቻ መፃፍ እዘውተሩ። በዕብራይስጥ እና በዓረብኛ ግን ከቀኝ ወደ ግራ አቅጣጫ አፃፃፍ በመያዝ ቋሚ ሆኖ ቀረ። ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ከሳባውያን ፊደሎች እንዳንድ በግስቀረት 30 ፊደሎች ብቻ ወሰዱ። እነዚህ መለረታዊ ፊደሎችም 7 ዓይነት የቫውል ድምፆች በመስጠት በ7ት ተባዝተው በድምሩ 202 ፊደሎች በግድረግ ኢትዮጵያውያን ከሴሚናውያን ውስጥ ፅ ብራይስጥና ዓረብኛ ወዘተ... የቫውል ድምጹ በመፍጠር የመጀመሪያዎቹ ሆኑ፣ እኛ የፊደል አባቶች፣ የፊደላት ፈልሳፊዎች ሆነን ዛሬ በሀገራችን የሚሄድ ፊደል የላቲን የመጠቀም አዝማሚያ ይታያል። ይህ አዝማሚያ ግን መታረም ያለበት ነው። የኢትዮጵያ ፊደል የዳግማዊ ምኒልክ ፊደል ነው

[1] Conti-Rossini Stéfad Ethiopia p 91

አይሰማም ብሎ የሚያምኑ እንኳን ቢሆን፣ በላቲን ፊደል መጠቀም ከጥቅሙ ጉዳቱ ያዘነብላል። የኢትዮጵያ ፊደል ተቃዋሚዎች አብዛኛዎቹ እስላሞች እንደመሆናቸው መጠን በዓረብኛ ፊደል ቢጠቀሙ እንኳን መንገድ ያለው ሲሆን ይችላል።

ኤውሮውጳውያን የራሳቸው ፊደል መፍጠር ሲገባቸው በሮማውያን ላይ አክብሮትንና አምልኮት ስለነበራቸው ለቋንቋቸው የማይስማማ በላቲን ፊደል ይጠቀማሉ። የላቲን ፊደል ለእንግሊዘኛ ቋንቋ በተለይ አይስማማም። ለሌሎችም የኤውሮጳ ቋንቋዎችም አይስማማም። ሳባውያን እና የደቡብ ዓረቦች ከሌሎች የመካከለኛ ምስራቅ ሀገሮች ሲታዩ ጥንታዊ ታሪክ ያላቸው የሚባሉ አይደሉም፣ ኃይለኛ የታወቀ መንግሥትም አላቋቋሙም። በጥቃትን ወረላዎች ተከፋፍለው መካሪብ በሚባሉ በአምልኮት መንፈሳዊ አለቆች መሰነት ይተዳደሩ ነበር።

ሳባውያን ለመጀመርያ ጊዜ ስማቸው በታሪክ የተጠቀሰ በአሲሪያ ንጉሥ ሳርጎን[1] ጊዜ ከክርስቶስ ልደት በፊት 710 ዓመት ነው፣ በሐውልት ጽሑፍ የሳባ መካሪብ ገጽ በረከት ስፈርእን አበርከተዋል የሚል ነበረ። ለሁለተኛ ጊዜ የሳባውያን ስም ተጠቅሶ የተገኘው በፐርሲያ ንጉሥ ዳርዮስ ጊዜ ከክርስቶስ ልደት በፊት 510 ዓመት የሳባ ንጉሥ ተብሎ ሁለት ጊዜ ተጠቅሶ ተገኝቷል። ይህ አንስተኛ የሳባ መንግሥት ብቻው ሆነ ከሌሎች የደቡብ ዓረብ ጎሳዎች ጋራ ሆኖም ወደ ኢትዮጵያ ተሻግረው ከሀገሩ ሕዝብ ጋራ በጋብቻ ተደባልቀው ኢትዮጵያን ሲፈጥሩ አይችሉም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከደቡብ ዓረቦች ጋራ ዝምድና እንዳለው አያምንበትም። የአባቶቻችን አፈ ታሪክ ከሳባውያን ሕልውና እና ዕድሜ በላይ እስከ ንጉሥ ሰለሞን ቀዳማዊ ምኒልክ አፈ ታሪክ ከነሱም በላይ ታሪክ እስተላልፈውልናል፣ ከሳባውያን ዓረቦች እንወለዳለን የሚል ታሪክ ግን አልተውልንም፣ የሳባውያን ፊደል በመጠቀማችን መሠረት በማድረግ ብቻ ኤውሮጳውያን የፈጠሩት ልበወለድ ታሪክ ነው። የሳባዊ ፊደል ወደ ኢትዮጵያ የማስተላለፍ ጉዳይ በግዲታ በሳባውያን በኩል መሆን የለበትም። ይሁዶችም ሊሆኑ ይችላሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብ እስከ ዛሬ ድረስ የእስራኤል አምላክ ሲል ነው የምንሰግው፣ የዓረብ አምላክ ሲል አልሰግንም። እስራኤሎት የጥንት ሀገራቸው ዓረብያ እንደነበረ ይነገራል። በደቡብ ዓረብም ከፍተኛ ግዛት ስለነበራቸው የስልጣን ተቀናቃኝ ለመሆን የበቁ አይሁዶች ስለነበሩ ወደ ኢትዮጵያ ሃይማኖታቸውን ባገቡበት ጊዜ የሳባውያን ፊደል አስገብተው ሲሆኑ ይችላሉ። ኮኒቲሮሲኒም ሆነ ሌሎች የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፊዎች ደብቡ ዓረቦች ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ስለመምጣታቸው የሚያቀርቧቸው ማለረጃዎች ኩተረት የማያልፉ ናቸው። ኤውሮጳውያን የህገራችን ታሪክ ጸሀፊዎች ዘራችን ጨዋ ለማድረግ ከእስራኤሎች፣ ከዓረቦች እንወለዳለን እያልን የብዙ መቶ ዓመት ታሪክ በመዝለል ግዛመድ እንደምንሞከር አድርገው ይተቹናል። ነገር ግን ኮንቲ ሮሲኒ የደቡብ ዓረቦች ባህል ብሉ ያቀረበው ሕብረተሰቡ በባላባቶች እና በተራ ዜጎች መካፋፈል ነው፣ ሳባ የሚባል ደሴት ከምዕዋ አጠገብ ይጠቅሳል፣ እሰብ ከሳባ የመጣ ስም ብለው ይተረጉሙታል። ሰሐርቲ፣ ሐውዜን፣ ሳራዋ /ሰራዬ/ ወዘተ... ከደቡብ ዓረብ የተወረሱ ስሞች ያደርጉታል። ይህ ሁሉ ግን ታሪክ እይደለም ተረት ነው።

የኤውሮጳ ታሪክ ፀሐፊዎች የሚሉት እውነተኛ ታሪክ ቢሆን ኖር ኢግውያን ናቸው የሚባሉ ትግሬ፣ ትግሬኛ፣ እግርኛ፣ ጉራጊኛ፣ አደሬ፣

[1] Conti Rossini Storia d' Ethiopia 1928 p 98

ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ሕዝቦች አፋርኛ፣ ሶማልኛ፣ አሮሚኛ፣ ሲዳምኛ፣ ወላይትኛ፣ ካፊኛ፣ ወዘተ... ቋንቋ የሚናገሩ ሕዝቦች በመልክ /በዘር/ ከፍተኛ ልዩነት ይታይ ነበረ። ነገር ግን በኢትዮጵያ ሕዝብ መሀል በቆዳና በተለያም በኩል በመሀላቸው ምንም ልዩነት አይታይም። ልዩነት የሚታየው በቋንቋ ብቻ ነው፣ ይህ ሁኔታ ብቻ ሲላ ማሰረጃ ሳያስፈልግ የደቡብ ጎረቦች ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ፈልሰው መምጣታቸው ውድቅ ያደርገዋል። ሰለዚህ ከደቡብ ጎረቦች ብቻ ሳይሆን ከአሰራኢሉችም ሞምር ብዙ ቃላቶችና ባህሎች ወሰደናል፣ በዘር ግን አልተቀላቀልንም። ደቡብ ጎረቦች ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል የተባለብት ዘመን የመኖች ጎረቦች ተብለው ይጠሩ አልነበረም። ሰሜን ጎረቦች /የዛሬዋ ሳውዲ ጎረብያ/ ብቻ ነበሩ ጎረብ ተብለው የሚጠሩ። ደቡብ ጎረብ መሬት ውሰጥ የመጀመሪያ ኗሪዎች የካም ዘሮች ነበሩ ይባላል። የካም ዘሮች ያልሰፈሩበት ቦታ አልነበረም። አሮጆቱስ የግሪክ ቀደምት ንዋሪች የካም ዘሮች ነበሩ ብሏል። የካምና የሴም ዘሮች ጉን ለጉን የተፈጠሩ እና የሚኖሩ ሕዝቦች ናቸው። የካም ዘሮች ሆነው ከሴም ቋንቋ ተመሳሳይ የሆነ ግእዝ የሚናገሩ ሕዝቦች በሰሜን ኢትዮጵያ ተፈጥረው ሊሆኑ ይችላሉ። በዘህ ዓይነት ተመሳሳይነት ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር የአውሮጳ ታሪክ ፀሐፊዎች ከባሕላችንና ከአባቶቻችን የወረሰነው ታሪክ የደቡብ ጎረቦችም የማያውቁት ታሪክ ዓረብ ገዥ ኢትዬጵያ ተገዥ ዓረብ አሰልጣኝ ኢትዮጵያ ሰልጣኔ በደንብ የመቀበል ችሎታ የሌሰው /ሰልጣኝ/ አድርገው በመቁጠር ከግማሽ በላይ ኢትዮጵያውያን የዓረብ ክልሰ በማሰት ዘራችን ሊያሰተምሩን መብት የላቸውም።

ሳባ የምትባለው የደቡብ ዓረብ አነሰተኛ መራት ወደ አፍሪካ ተሻግራ ኢትዮጵያን የሚሀል መሬት በቀኝ ግዛት ይዛ ብትሆን ኖሮ ዝናዋና ታሪኳ በዓለም አቀፍ በማያሻማ ሁኔታ ይታወቅ ነበር።

ሳባውያን ከአሰተዳደር ይልቅ ዝና ያገኙት በንግድና ከግሪክ ፊደል ወሰደው ለዓርቦች ለኢትዮጵያውያንና ለይሁዶችም በማሰራጨታቸው ነው። ለዓረቦች ፊደል በመሰጠታቸው ገዝቷል እንዳልተባሉ ሁሉ ለኢትዮጵያም ፊደል በመሰጠታቸው ገዝተዋል ሊባሉ አይችሉም። ሮማውያን ገዥዎች ሆነው ከተገዥዎቹ ከግሪኮች ፊደል ወሰደዋል። ኢውሮጳውያን የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊዎች ሳባውያን ወደ ኢትዮጵያ ያመጡት ከፊደል ሲላ ሰልጣኔን በሚመለከት ነው። ሳባውያን ከባቢሉን ባለፎቅ የሕንፃ ግንባታ ተምረው በሀገራቸው አሰገብተው በሥራ ላይ አውለውታል። በሀገራችን ግን እንኳን ፎቅ ቤት የድንጋይ ቤትም ልምድ ምንም ምልክት የለም። በአክሰም የቆሙ ሐውልቶች ዓይነት በሳባ የሉም። በአምልኮትና በቤተመቅደስ አሰተዳደርም በኢትዮጵያ አይታዩም። በቋንቋችን የሚገኙት ብዙ የዕብራይሰጥ ቃላቶች የሀይማኖት ሳይቀር በአንዳንድ ቦታዎች፣ የኢውሮጳውያን የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊዎች ተገቢ ትኩረት አልሰጠብትም። ክርስትና ከመቀበሏ በፊት ኢትዮጵያ የአስራኢሉች የመሊ ሕግ ተቀብላ ነበር የሚል የኢትዮጵያ የቤተክህነት ምሁራን አባባል በቂ ጥናት አልተደረገበትም። ይሽም ሲባል አንዳንድ ምሁራን እንደሚሉት የኢትዮጵያውያን እና የአስራኢሉች አባቶች የጋራ ሀገር ዓረብ ነው ብለው መገመት ተቀባይነት የሌለው መሠረተቢስ ታሪክ ነው።

፱ኛ. ኢትዮጵያ ሱዳንና ግብፅ

አብዛኛዎቹ አውሮጳውያን ታሪክ ፀሐፊዎች በአፍሪካ ከግብፅ ሥአምራዊ ከሰተት በቀር ምንም የራሷ ሰልጣኔ ያልፈጠረ ሕዝብ የጭሰግ ከሳሰ ዓሰም ብለው ይተርካሰ። ግብፆች አፍሪካውያን አይደሱም ሲግውያን ናቸው ይሰዎቸዋል፣ አንዳንዶቹ የነሞ ዝርያ አርያን ናቸው ይሏቸዋል። ከግብፅ ሀገር ክልል በሰተደቡብ በናፓታ ዋና ከተማ የነበረው የኑቢያ መንግሥት እቶ ተክሰዓዲት መኩሪያ የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ ብሱ ሲጠራ ነበት ሮሰኒ የናፓታ /ኑቢያ/ መንግሥት የተቋቋመው በቴብ ግብፃውያን ቤተመቅደስ አለቆች ነው ይሳል። ይህ ግለት የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ የተባሰችው በግብፅ የተቋቋመች ሰልጣኔዋን ከግብፅ ያገኘች ግሰት ነው። ይህ አባባል እውነት ቢሆን ኖሮ ሳባውያን ቋንቋቸውና ዘራቸው ቀይ ባሕር ተሻግረው አሰገቡ እንደተባለ ሁሉ ግብፃውያንም ቋንቋቸውና ጽሑፎቻቸው ወደ ናፓታ አሰገብተዋል በግለት ወደ መጨረሻ ግምገግ መድረስ በተቻለ ነበረ። የግብፅ ታሪክ ፀሐፊዎች ግን ወደዚሁ ግምገግ መድረስ ተስኖቸዋል። ከንቲ ሮሰኒ እንደሚለው ግብፅ ከመካከለኛ ምስራቅ በምታደርጋቸው ሠፒነቶች የተነሳ እየደከመች ሰለሄደች ናፓታ ከግብፅ እየተሰየች ሄደች ከክሰተ-ዘመን ልደት በፊት 573 [1] 533፣ ለአሞን /አግዚአብሔር/ ቤተመቅደስ በሜሮዊ ተሰራ። ከክርሰቶስ ልደት በፊት 440 - 350 መሮዊ የኑቢያ የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ የዛሬዋ ሰሜን ሱዳን ዋና ከተማ ሆነች። የዋና ከተማ መቸጋሸግ የግብፅ ሰልጣኔ ውድቀት አሰከትሏል። ዘናፓታ የግብፅ ሰልጣኔ መልኩን ቀይሮ ደሕይቶ ነበረ። ወደ መሪዌ ዋና ከተማ በተዘዋወረበት ወቅት ግን ሰልጣኔው ወደ ኋላ ቀርነት /ባርባሪያን/ ተሰውጦ በሐውልት ጽሑፎች ቁንቋም ተሰውሟል፣ የህዝቡም ዘር ተቀይሯል። ሕዝቡ ጥቁር በመሆኑ ለኪነ ጥበብ፣ ለሃይማኖት፣ ለአውቀት ማስፋፋት፣ የራሱ ችሎታ አልነበረውም። ይህም ሆኖ ግን ያለፈው ሰልጣኔ በፒራሚዶችና በቤተመቅደስ በመንግሥት መሰተዳድር በዘገሩ ሕዝብ ዘንድ አድናቆት የሚያተርፍ ነበረ። በሐውልቶች የነበሩ ጽሑፎች በመሪዌ ቋንቋ ነበሩ።

ሰለዚህ አብዛኛው የሀገሩ ታሪክ ማወቅ አልቻልንም። በስእሎቹ የሚታየው የሴት ንጉሥት ግን በበኽ ሕዝብ ዘንድ የሴት እክብሮት ባሕል ያሳየናል። የመርዌ ኪነ ጥበብ የሚያንፀባረቅ የሚመስል በአንድ ዋሻ በዳዕሮ ዱውሰሰ [2] አጠገብ ከአሰመራ በስተደቡብ ተገኝቷል። ስእሉ ያልሰለጠነ የግብፃውያን የተለመደ የሶስት ሰው /አንድ ወንድ አንድ ሴት አንድ ልጅ/ የሚያሳይ ሲሆን ምናልባት የእግዚአብሔራቸው ምልክት ሳይሆን አይቀርም ቀብሱ ተገምቷል። የኮንቲ ሮሲኒ አባባል በዘረኝነት መንፈስ የተመረኮዘ ነው። አንድ ሰልጣኔ ካልሰለጠነ ወደ ሰለጠነ ይሻሻላል እንጂ ወደ ኋላ መመለስ መልኩን ቀይሮ ካልሆነ በስተቀር ራሱ ሰልጡን ሕዝብ ወደ ናፓታና መሪዌ የሚያስተላልፈው ሰልጣኔ የመጨረሻ ውጤት መሆን አለበት። የጽሑፉ ቋንቋም መሮዊ ሳይሆን ቤኻ መባል ነበረበት። መሮዊ ዋና ከተማ እንጂ የጎሳ ስም አልነበረችም። በመሮዊ የተገኘው ጽሑፍ የግብፃውያን ቋንቋ ሰላልሆነ በቻምፖሊዮን ዘዴ ጥበብ ሄሮግለፊክ ሊነበብ አልተቻለም። ሰለዚህ የዋፓታና የመሮዊ ታሪክ እስከ አሁን ያልታወቀ ታሪክ ሆኗል። ነገር ግን ያልሰለጠነ አንደ መሆኑ መጠን ከግብፆች የተወረሰ ሰልጣኔ ብሱ ከመተርጎም

[1] Cantl Rossini Storia d'Ethiopia p 106 - 107
[2] Cantl Rossini ibd p 108

ከግብፅ ሰልጣኔ በፊት የነበረ ለግብፅ ሰልጣኔ ቅድመ ሁኔታ የፈጠረ ተብሎ መወሰድ ይገባዋል። በዚህ መሠረት አቶ ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ እንደ ገመገመው ሳይሆን ከግብፅ እና ከቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ የዛሬዋ ሰሜን ሱዳን በሰልጣኔ ግን ይቀድማል ሊሚለው ጥያቄ ያለምንም መወላወል የኢትዮጵያ ሰልጣኔ ነው የሚቀድመው የሚል መልስ መሆን አለበት። የግብፅ መንግሥት ዘሚነስ (Menes) ሊመሠረት ከክርስቶስ ልደት በፊት 5 ሺህ ወይም 4 ሺህ አመት ከዞን የቀድሞዪቱ የኢትዮጵያ ታሪክ 2000 ሁለት ሺህ ዓመት ታሪክ ከግብፅ በፊት መሆን ሰለሚገባው የኢትዮጵያ ታሪክ ዕድሜ በ7 ወይንም ለ8 ሺህ ዓመት መሆን አለበት። ሰሜን ሱዳን የኢትዮጵያ አካል ናት ለማለት የምንችለው ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ታሪክ ብቻ አይደለም። በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ ቢሆንም የሰሜን ሱዳን አብዛኛው ክፍሉች ከኢትዮጵያ ተቆርሰው የተወሰዱ መሆናቸውን በሊላ ምዕራፍ እንመለከተዋለን። ከዚህ በላይ ዮተዘረዘረው ታሪክ መሠረት ህገራችን ኢትዮጵያ ከንግሥተ ሳባ በመጀመር የ 3000 ዓመት ታሪክ አላት የሚል አባባል ትተን 6-7 ሺህ አመት ታሪክ አላት ለማለት እንችላለን።

[1] ሉካ ዴይ ሳበሊ የተባለው ኢጣሊያዊ ታሪክ ጸሐፊ ሳባውያን ወደ ኢትዮጵያ ከገቡበት ጊዘ ኢትዮጵያ በታሪክ መኖር በመቁጠር ኢትዮጵያ 2500 ዓመት ታሪክ አላት ብሎ ጽፏል። የአቶ ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ አቀራረብ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው። ኢትዮጵያዊት ሰሜን ሱዳን የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ ብሎ መለየሙ ትክክል አጠራር ይመስላል። ነገር ግን የኢትዮጵያ ጎሳዎች በሙሉ የኩሽም ሆነ የሴም ከእስያ መጥቷል ማለቱ ባሕላችንና አፈታሪካችን ትተን ኤውሮጳውያን የሚያስተምሩን ታሪክ መከተል ስለሆነ ተቀባይነት አይኖረውም፤ ልበወለድ ታሪክ ነው። የሳባውያን /የመን/ ዘሮች መሆናችን አባቶቻችን አላስተማሩንም አቶ ተክለ ፃዲቅ በመጽሐፉ በገፅ 23 የሁለተኛ ምዕራፍ ማጠቃለያ የቀድሞዪቱና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ልዩነት በማስመልከት እንደሚከተለው ጽፏል የኑቢያ ታሪክ ከግብፅ የተያያዘ የአከሱም ከደቡብ ዓረብ የተዛመደ ለእሁኑ መንግሥታችንም ለሥልጣኔውም ለፊደሉም ለቋንቋውም ለዘሩም ለልማዱም ሳባና ሐበሻቱ የመጡበት ይሽው ደቡብ ዓረብ መሆኑን በሰፊው እናያለን። ለዛሬው ሰልጣኔያችንና ፊደላችን ቋንቋና ልማዳችን አባት ያልሆነውን የኑቢያን ታሪክም በሰፊው ሰንመለከት ከእከሱም ጋራ የልዩነት ወይም የግንኙት ግጤን ... በዛሬ ጊዘ የመንና ሱዳን ዓረብ ሀገር ተብለው ነው የሚታወቁ፤ በድሮ ጊዘ ግን ሱዳን ኢትዮጵያዊት ነበረች የመንም ዓረባዊት ያልሆነች ሳባውያን ሚናውያን ሐድራሞታውያን ወዙተ ጎሳዎች የሚኖሩባት ሀገር ነበረች ምናልባትም ፑንት ከሚባሉ ሕዝቦች ውስጥ ትቃሰል ነበረች። ሰሰፊዪ ጉዳይ እላይ ዝርዝሬዋለሁ። ሰሰ ቋንቋችን ግን ግእዝ በግድ ከዓረብ የተፈጠረ ነው ሰማለት የሚቻል አይመሰለኝም። ሴም ቋንቋዎች ውስጥ ዕብራይስጥ፤ የደቡብ ዓረብና ዓረብያን የሶርያና የፍልስጤም ዓረብኛ ልዩነት እንዳሰው ሁሉ በቀይ ባሕር /የሐበሻ ባሕር/ በስተ ምዕራብ በሀገራችን በዘር ዓረብ ያልሆኑ ንፁህ የኩሽ ዘር የሆኑ ሕዝቦች ዓረብኛ የሚመስል ቋንቋ ሊኖራቸው ይችላል /ግሕዝ/። ቋንቋ ከደቡብ ዓረቦች ተምረናል ለማለት ግን የማንቀበለው ነው። በዘርና ልማድ ጨርሶ ከዓረቦች ጋራ አንመሳሰልም። ሰሁለት ተከፍላ የነበረች ግብፅ ያዋህደው ከንጉስ መኔስ በፊት የነበረው ሰልጣኔ በናፓታ የኢትዮጵያ ሰልጣኔ ነው።

[1] Luca Dei Sabelli Storia di Abissinia V.I p 100

የግብፅ ታሪክና ሰልጣኔ በተለይ ሄሮግልፊክ ጽሁፍ ሊነበብ ከተቻለበት ጊዜ ጀምሮ በሚገባ የሚታወቅ ሲሆን፤ የተድሞዪቱ ኢትዮጵያ ታሪክ ያልለለጠና የሄሮግሊፍክ ጽሑፍ ሰለሆነ የቋንቋንም ልዩነት ሊኖር ሰለሚችል ሊነበብ ሰላልተቻለ የህገራችን ታሪክ ለማወቅ አልታደልንም። እነ ሄሮዶቱሰና ዲዮዶር ግብፅን ያሰለጠኑት እና በሰልጣኔ ቀደምትነት ያላት ኢትዮጵያ ናት ያሉት እውነተኛውን ታሪክ መቀበል ይኖርብናል። የኑቢያ ታሪክ ለዛሬ ሰልጣኔያችንና ቋንቋችን ልማዳችን አባት አይደለም ለማለት አንችልም።

መሮዌ የምትገኘው አትባራ እና አባይ የሚገናኙበት ሲሆን በዚሁ ቦታ የሰፈሩ ሰዎች አሁንም ያሉት ቤኒዓመር የሚባሉ ሊሉችም ቤጃና ትግሬ ቋንቋ ተናጋሪዎች፣ በተለይ ቤኒዓመር ተብለው የሚጠሩ ጎሳዎች ሁለት ቋንቋ የሚናገሩ ናቸው፤ ትግሬና /ግእዝ/ ቤጃ ሁለቱ ኢትዮጵያውያን ጎሳዎች ናቸው። ሁለት ቋንቋ አየተናገሩ አንድ ጎሳ ሆነው የሚታወቁም ከብዙ ዘመናት /በብዙ ሺህ/ ዓመት ጀምሮ መሆኑን ተገምቷል። ምናልባትም ከናፓታ ዘመን ጀምሮ ሊሆን ይችላል። በዚህ መሠረት ሁለት ኢትዮጵያ ለማለት አንችልም። በናፓታና በመሮዌም ግእዝ ተናጋሪ ከዚጃ ተናጋሪ ጋራ ሆኖ ሰልጣኔ እንደፈጠሩ መቀበል ያሰፈልጋል። ትግሬ ተናጋሪ /ግእዝ/ ከደቡብ ዓረብ መጥተው እስከ መሮዌ ቋንቋቸው አሰፋፍቷል ብማለት ኤውሮጳውያን ታሪካችን ብለን እንድንቀበለው የሚያደርጉብን መሳሪ ተረት ነው።

ሰለዚህ ኢትዮጵያ አንድ ነበረች፣ በልዩ ልዩ ምክንያት ሰሉተዳከመች ግን አንድነቷን ለማሰከዘር አልቻለችም። በመሠረቱ ኢትዮጵያውያን በንገድ አንለያይም፣ ብንለያይም በቋንቋ ነው። ቋንቋ ለአንድነታችን መሰናክል መሆን አይገባውም። ነገደ ሴም ወይንም ነገደ ዮቅጣን የምንላቸው ከሴም ቋንቋ ትንሽ ድብልቅ ያለው፣ ሊላ ደግሞ ቋንቋ ድብልቅ የሊለው ሁሉም ነገዶች ከጥንት ጀምሮ ተደባልቀው የኖሩ ናቸው። በአፍሪካ የተፈጠሩ ክእስያ ያልመጡ ጎሳዎች ናቸው። ምናልባትም በናፓታ ቤጃ ብዛትና የፖለቲካ የበላይነት ሊኖራቸው ይችላል በአክሱም ደግሞ ግእዝ ተናጋሪ ብዛት ሊኖራቸው ይችላል።

10. ኢትዮጵያና ንግሥተ ሳባ

ንግሥተ ሳባ ኢትዮጵያዊት አይደለችም ተብሎ ሊነገረን ሁላችን እናውቃላን ምን ያህል የተቃውሞ ሰሜት እንደሚሰማን። ከዚህም በላይ የንግሥተ ሳባ ዘር ነን የሰለሞን ዘር ነን፤ የሳብያውያን ዘር ነን በምንልበት ጊዜ ዝቅተኛ የሆነ ዘራችን ከፍ ለማድረግ ጨዋ ዘር ለመሆን ፈልገን ነው ተብሎ ሊነገረን፤ የኢትዮጵያ ዘር ከግን ዘር ያንሳል በሚል ሰሜት ተቃውሞዎችን በቁጣ ሊገነፍል ይችላል። በበቂ ማስረጃ ያልተደገፈ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ታሪካችን ሐሰተኛ ማድረግ የታሪካችን ትምህርት ማዋረድ ነው። ንጉሥ ሰለሞን ተረት ሳይሆን በታሪክ የታወቀ የእስራኤል ንጉሥ እንደሆነ ሁሉ፤ የንግሥተ ሳባ ታሪክም ተረት አይደለም። የንግሥተ ሳባ ኢትዮጵያዊት መሆንዋ ኢትዮጵያውያን ሙሉ እምነት እንዳላቸው ሰሴቶቻችን ሳባ፣ ግክዳ፣ አዜብ ብሰን ስም መስጠታችን በቂ ማስረጃ መሆን በቻለ ነበረ። ንግሥተ ሳባ ኢትዮጵያዊት እንጂ ዓረባዊት ልትሆን የማትችልበት ምክንያቶች ከብዙ ባጭሩ

1. የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ የዛሬይቱ ስሜን ሱዳን ስሚ ነብያ ነው፣ ዋና ከተማዋ ናፓታ ነበረ። በአሰልታ ንጉሥ ጊዜ /573-553/ ዋና ከተማ ወደ መሮዌ ተዘዋወረች። አቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያ ንግሥተ ሳባ የመሪዊ ንግሥት አይደለችም ለማለት መሮዌ የተቆቀቆረችበት ዘመን ክክርስቶስ ልደት በፊት ወደ አምሰተኛና አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዝቅ በማድረግ፣ ንግሥተ ሳባ ከነበረችበት ዘመን ክክርስቶስ ልደት በፊት 1000 ዓመት ሰለሚራራት በፍፁም ሊታመን አይችልም ካለ በኋላ ክሌቢያ ሐውልቶች እና ጽሑፎች የንግሥተ ሳባ ስም አይገኝም ወደ ፊትም ሊገኝ የሚችል አይመስልም፣ ምክንያቱም የሷ ንግሥትነት ከነገሷ ከፍል ከሆነው ከዓረብና ከኢትዮጵያ ሰሜን /ሳባ ትግራ/ ሊዘል አይችልም ይላል። የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያውያን ቋንቋቸውና ዘራቸው የኳም ነው ፊደላቸውም ሰልጣኔያቸውም ከጉዘፅ የተወረሰ ነው። የንግሥተ ሳባ ዘርና ቋንቋ ከደቡብ ዓረብ ከሳባውያን የመጣ ነው ይላል። በመጨረሻም ንግሥተ ሳባ [1] የሁለቱ ሀገሮች ኢትዮጵያና የደቡብ ዓረብ /የመን/ ንግሥት ልትሆን ስለምትችል የኢትዮጵያ ናት ወይም የዓረብ ንግሥት ናት እያሉ መሻማት ከንቱ ነው በማለት አስታራቂ ሃሳብ በማቅረብ ጽሑፉን ደምድሟል። ይህ አስታራቂ ሳብና አስተያየት ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም። አሳይ እንዳልኩት ኢትዮጵያውያን ለሁለት የከሙና የሴም ዘር መክፈል ስህተት ነው። ኢትዮጵያውያን ሁሉ በቋንቋ ካልሆነ በቀር በዘር በኩል አንድ ናቸው፣ የኳም ኢትዮጵያዊ ዘር ናቸው። በቋንቋም ቢሆን የሴም ተብሎ የሚመደቡ አንስተኛ የሴም ቃላቶች ተደባልቀው ስለሚጠቀሙ እንጂ ቋንቋው በመሠረቱ የኳም ኢትዮጵያዊ ነው። ስለዚህ የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ /ኑቢያ/ እና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ በዘር አንድ ከመሆናቸውም በላይ በቋንቋም አንድ ናቸው። ምክንያቱ በሁሉም በልማድ የኳምና የሴም ተብለው የሚመደቡ ቋንቋዎች በአኩል ደረጃ ተስፋፍተው ይገኛሉ። በኑቢያ የሚኖሩ ኩሽ ተብለው የሚጠሩ ዘሮች፣ ሌሳ አይደሉም ጥንትም ይኖሩ የነበሩ አሁንም ኗሪ የሆኑ ቢጃ ናቸው። ከሱ ጎንም በጥንትም ይኖሩ የነበሩ አሁንም የሚኖሩ ገፅዝ "ትግሬ" ቋንቋ ተናጋሪ አሉ። ስለዚህ ንግሥተ ሳባ የመሮዌ ንግሥት የማትሆንበት ምክንያት የለም። ዘሯም ወይም ቋንቋዋ ሴማዊ ወይም ዓረባዊ ወይም ገእዝ መሆኑን የሚገልፅ ግለጫ አልተገኘም። ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ታሪክ ባለፀጋ ሆና በማስረጃ ማጣት ግን አልታደለችም። ታሪክችን አሁንም ተደብቆ ነው የሚገኘው። በቂ ቁፋሮና ምርምር አልተደረገበትም። በመሮዌ የሚገኘው የሄሮግሊፊክ ጽሑፍ ግን ከግብፃውያን ቋንቋ የተለየ በመሆኑ ጥንቃቄ፣ ያልለለጠን ከግብፃዊው ቅድሚያ ያለው በመሆኑ ሊነበብ አልተቻለም። ስለዚህ ታሪካችን ሳይገለፅ ለዘላለም ይኖራል። እንደሚነገረው ትግሬ ተናጋሪ ሰዎች በአንድ የአክሱም መንግሥት ዘመን የሰፈሩ አይደሉም፣ ከጥንት የተፈጠሩበት አገር ነው። ምናልባትም እንደ ገእዝ ቋንቋ መለየውጥ ሲታይ የገእዝ ቋንቋ የተመሰረተበት ሀገር ኑቢያ ሳትሆን አትቀርም ብዬ አምታለሁ። ያልለለጠንና የግይነበብ የሄሮግሊፊክ ጽሑፍ በኑቢያ ብቻ አልተገኘም። ጀምስ ብሩስ [2] የተባለው እንግሊዛዊ በአክሱም የግይነበብ የሄሮግሊፊክ ጽሑፍ አግኝቷል።አሳይ እንደገለፅኩትም ከኢሥመራ በስተደቡብ በዳዕሮ ጳውሎስ አጠገብ አንድ ዋሻ ውስጥ የተንታውያን ግብያት የሚመስል ስእል ተገኝቷል። ይህ ሁሉ የሚያመለክተው ሥልጣኔ ከኢትዮጵያ ተጀምሮ ወደ ጉዘፅ እንደተሳለፈ ነው።

[1] ግዕዝ ጻድቅ ገጽ 193
[2] Conti Rossini ibd p.82

ከጉዘፅ የመጣ ቢሆን ኖሮ ጽሑፉ ከመጨረሻው የግብፃውያን ጽሑፍ አንድ ዓይነት መሆን ነበረበት።

2. የንግሥተ ሳባ ኢትዮጵያዊነት በሌላ መንገድ ስንመለከተው ግለት በደቡብ ዓረብ ያለው ሁኔታ በኩል፣ በ1ኛ ተራ ቁጥር ካቀረብኩት ያላነስ ኢትዮጵያንቷን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች ለማቅረብ ይቻላል። በመጀመርያ ንግሥተ ሳባ በነበረችበት ዘመን ደቡብ ዓረቦች ንረብ ተብለው አይጠሩም ነበር። የዓረብ ሕዝብ ባህልና ቋንቋ የሌላውን ሕዝብ መሣብና ማዋሀድ ችሎታ ስላለው ሰሜን ሱዳን ኑቢያ የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ ዓረብ ተብላ ከመመደቧ በላይ ቋንቋዋ ተቀይሮ ዓረብኛ ተናጋሪ ሆናለች። ደቡብ ዓረብ የመን በጎሳ የተከፋፈለች መሆንዋን በማየ እንደሚታየው፣ ዛሬ ተያ ባሕር ተብሎ የሚጠራው "የሐበሻ ባሕር" ተብሎ ይጠራ ነበረ። በታላቁ አክሱንድር ቀይ ባሕር የተባለም እኛ ኢትዮጵያውያን ቀያይ ሰዎች የምንኖርበት ስለሆነ ነው ተብለዋል።

የመን ለትናንሽ መንግሥታት የተከፋፈለች እርስ በእርሳቸው የማይስማሙ፣ የሚተዳደሩም በመጀመርያ ጊዜ በአምልኮት መሪዎች ነበረ። እነሱም ሚናውያን፣ ሳባውያን ዘውዳውያን ኪታባውያን ሀድራመታውያን ተብለው የሚታወቁ ነበሩ። እኛን በሚመለከት አብዛኛው ሳባውያን ናቸው።

ከክርስቶስ ልደት በፊት 1000 ዓመት ንግሥተ ሳባ ትኖርበት የነበረ ዘመንና ግሪኮችም ከፈኒሳውያን ፊደል ተበድረው የወሰዱበት በዚሁ ዘመን ነበረ። ደቡብ ዓረቦች ግን በዚህ ጊዜ በዓለም አደባባይ ኢትዮጵያ ጉንት፣ ኩሽ፣ ኢትዮጵያም /አዘሻ/ ተብላ እየተጠሩ በዓለም የታወቀች ነበረች። ሳባ የምትባል ሀገር ለመጀመርያ ጊዜ ስሟ በታሪክ ተጠቅሶ የተገኘው በአሲሪያዊ ንጉሥ ሳርጎን ክክርስቶስ ልደት በፊት 715 ዓመት መሐሪብ ተብለው በሚጠሩ በአምልኮት ቤተክህነት መሪዎች በምትሰተዳደርበት ጊዜ ነበር[1] ።

ሳባ መሪዎቿ ንጉሥ ተብለው በታወቁበት ጊዜ በታሪክ ለሁለተኛ ጊዜ ልትጠቀስ የበቃችው በንጉሥ ዳሪዮስ ዘመን ክክርስቶስ ልደት በፊት በ500 ዓመት ነበር። በዚህ መሠረት የየመን ደቡብ ዓረብ ሳባውያን ከግሪክ ፊደል ተበድረው የራሳቸው ፊደል ፈጥረው ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለዓረቦችም ለግሰተኛለፍ የታወቁ ቢሆንም እነሱ ሳይታወቁ በፊት ትኖር የነበረች ንግሥተ ሳባ የእነሱ ዘርና ንግሥት ግለት ፈፅሞ የማይቻል ነው። ሳባውያን ብቻቸው ወይንም ሁሉም ደቡብ ዓረቦች አንድ ላይ ሆነው ኢትዮጵያን በቀኝ ግዛት ይዘው ቋንቋቸውና ፊደላቸውን አስተላልፈዋል ግለትም ኤውሮጳውያን የታሪክ ጸሐፊዎች የፈጠሩት ታሪካዊ መሠረት የሌለው ተረት ነው። እኛ የዘራችን ሀረግ ከሳባውያን በፊት እስከ ንጉሥ ሰለሞን መቁጠር የምንችል፣ ከሳባውያን ወይንም ከዓረቦች የምንወለድ ብንሆን ኖሮ በእንዓራዊ እጭር የሆነ ጊዜ መቁጠር አይሳንም ነበር። ይህ በመሆኑ በእኛ በኢትዮጵያውያንም ሆነ በዓረቦች የዚሁ ሐቁ ታሪክ የሚያስታውስ ግዕረጃ የለም።

ፊደል መበደር የተለመደ ነው፣ በተያ ባሕር /የሐበሻ ባሕር / አካባቢ የታወቀ ፊደል የሳባዊያን ስለነበረ፣ እኛ ኢትዮጵያውያን ብንዘይርም በእኛ ሀገር ምሁራን ወይንም በዓረቦች ወይም በይሁዶች አማካኝነት ይሁን

[1] C. Conti - Rossini ibd p 98

እይታወቅም። በቅኝ ግዛት ይዞ ማስተዳደርና ስልጣኔና ዘርን ማስተሳሰፍ ረጅም ጊዜ የሚወስድ ስለሆነ ደቡብ ዓረቦች ይሽንን ተግባር ለማካሄድ የሀገራቸውና የሕዝባቸው እነስተኛነት ሲታይ ከአቅማቸው በላይ ከመሆኑም በላይ በታሪክ ያልተመዘገበ፣ ሁለቱ ሕዝቦች ኢትዮጵያና ደቡብ ዓረብ የማያምኑበት ነው።

ስለዚህ ንግሥተ ሳባ ኢትዮጵያዊት ናት እንጂ ዓረባዊት አይደለችም። ኢትዮጵያውያን ምሁራን ከንግሥተ ሳባ ጀምሮ፣ ከዚያ በፊትም የሚያቀርቡት የነገሥታት ስም ዝርዝር እንዳንድ ስህተት ሊኖረው ይችላል፣ ነገር ግን ስለታሪክነቱ ሊካድ የማይቻል ህቅ ነው።

ሳባውያን ኢትዮጵያን አቀኑ፣ በቅኝ ግዛት ያዙ ክግለት ይልቅ ገናና ስም በነበራት ንግሥተ ሳባ ስም ሳቢ የሚባል ህገር በየመን ተሰየመ ማለት ይቀላል። የነገሥታቱ የስም ዝርዝር[1] ስንመለከተው ሳባ ወይም ሳቢ የሚል ስም ከክርስቶስ ልደት በፊት 1875-1985-1971-1453-1036 እንዲሁም ኢትዮጵያ የሚለውን 1856 እና 1730 እናነኛለን። ይህ ሁሉ የሚያሳየው ሳባ የሚለው ስም ቀድሞ በኢትዮጵያ ከደቡብ ዓረብ በፊት የተለመደ እንደነበረ ነው፣ የኢትዮጵያ ስምም ያኸው ነው። ከዚህም ሌላ አክሱማይ የሚለው ስም ከክርስቶስ ልደት በፊት 788 እና 778 የአክሱም መንግሥት ከመመሰረቱ በፊት ተጠቅሶ ይታያል። ይሄም የሚያሳየን አክሱም ቀደም ብላም ታውቃ እንደነበረች ነው። እንደዚሁም የቀድሞዪቱ ኢትድጵያ የነገደ ኩሽ ዘር ብቻ እንዳልነበረች ከዛሬዪቱ ኢትዮጵያም የነገደ ሴም ወይም ዮቅጣን ብቻ እንዳልነበረች ነው።

ሁለቱ ነገዶች ድሮም ተከፋፍለው እንዳልኖሩ አሁንም ተከፋፍለው እንደማይኖሩ ነው። ኢትዮጵያውያን ሁላችን ነገደ ኩሽ ወይም ነገደ ኢትዮጵያዊ መሆናችን ብቻ ነው የምናውቀው። በነገሥታት ስም ዝርዝር አባቶቻችን ሁለት ነገድ ለይተው ያወጡት ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምራ አሁንም በነገደ ኩሽና በነገደ ዮውቅጣን ተከፋፍላ እንደማትታወቅ የሚያስረዳ ነው። አሁንም ስሜን ሱዳን ያሉት ኢትዮጵያውያን ቋንቋቸው ለውጠው ዓረብኛ ቋንቋችን ብለዉ ቢቀበሉም ዓረቦች አይደሉም። በሃይማኖትም ቢሆን ስሜን ሱዳናውያን የእስልምና ሃይማኖት ከመቀበላቸው በፊት አስቀድመው ተቀብለውት የነበረ የክርስትና ሃይማኖት ነበረ፣ ከዚያ በፊትም የሌላ አምልኮት እምነት ነበራቸው። ክርስቲያን ኢትዮጵያውያንም እንደዚሁ ክርስትና ከመቀበላቸው በፊት ሌላ አምልኮት ይከተሉ ነበር። በዘር ግን ሁለቱ ሕዝቦች ለነገድ ኩሽና ለነገደ ዮቅጣን ወይንም በዘመናችን ቋንቋን መሠረት በማድረግ ብሔር ብሔረሰብ አጠራር ተሰጥቷቸው ሊከፋፈሉ የማይችሉ አንድ ዘር አንድ ነገድ ናቸው።

የሰው ልጅ በሚናገረው ቋንቋ ወይም በሚከተለው ሃይማኖት እንደ ዘር ተቆጥሮ ሊከፋፈል አይገባውም። ይህ ክስተት በሀገራችን ብቻ አይደለም የሚታየው በሌላ ህገርም ለምሳሌ እንደ ፓኪስታን፣ ባንግላዴሽ የተከፋፈሉት በሃይማኖት አንጂ በዘር አይደለም። በሀገራችን ያለው ሁኔታ ስንመልከት ኑቢያ የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ ስሜን ለውጣ ሱዳን አንዴት እንደተፈጠረች ብለን በምንጠይቅበት ጊዜ፣ የማአከላዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ድክመት መሆኑን እንገነዘባለን። ከአክሱም መንግሥት ጀምሮ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ድረስ የነበሩት የኢትዮጵያ ነገሥታት ሱዳንን ከኢትዮጵያ ጋር ለማቀላቀል ያልሞከሩበት ጊዜ የለም። ሆኖም ዓቅማቸው ለሳልፈቀላቸው ዓላማቸው ከግቡ

[1] ተክለጻድቅ ገጽ 193

ለማድረስ አልቻሉም። ኢትዮጵያ ለሁለት ተከፍላ የሰሜኑ ክፍል ባዕድ ህገር የሆነበት የኢትዮጵያ ማእከል ከናፓታ መሮዌ ወደ አክሱም የተዘዋወረበት የሽግግር ጊዜ ታሪክ ገልፅ አልሆነልንም። የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያና የዛፊዪቱ ኢትዮጵያ ብሎ ስም መስጠት ይቻል ይሆናል፣ ቢሆንም አንድ የነበረች ኢትዮጵያ ለመረዋና ለአክሱም ተብላ ተከፋፈለች ቢባል የተሻለ ይመስላል።

ምዕራፍ 2
የአክሱም ዘመን፡

1ኛ ዝንኛው በታሪኳ የምንኮራበት የአክሱም መንግሥት የተቋቋመበት ዘመን ለግዜት ምንም ግለረኛ የለንም። የአክሱም መንግሥት በጽሑፍ ተጠቅሶ የተገኘው በአጋማሚ ነው። በአንድ በአነስተኛ ድንጋይ ጽሑፍ በግሪክ ቋንቋ ተጽፎ የተገኘው ከአቧመራና ከክረን ግሀል [1] በሚገኘው ደቀመሐሪ በተባለው መንደር ከዓደ ተከሰዛን በስተሰሜን ነው። ያፃፈው ንጉሥ ሰምብሩተስ ይባላል። ሰሙ እንደ ኤውሮጳውያን የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፊዎች ሴማዊ አይመስልም፣ ካማዊ ነው። ዘመኑ በሁለተኛ ወይም በሦስተኛ ክፍለ መቶ ዘመን ዓ.ም. ነው፤ ጽሑፉም የአክሱሞች ንጉሠ ነገሥት ትልቁ ሰምብሩተስ ከነገሠበት በ24ኛው ዓመት ይኸንን ጽሑፍ አሰራሁ የሚል ነው። በዚሁ መንደር አካባቢ የቀድሞዎቹ አምልኮት ቤተመቅደስ እንደነበረ ተገምቷል። ንጉሡም ሐውልቱን ያሰራው ለመንፈሳዊ ጉብኝት ወደ ቦታው በሄደበት ወቅት መሆኑን ይመስላል። በተቀራረበ ዓመተ ምህረት ዘግሪክ ቋንቋ የተፃፈባቸውን ሌሎች ሐውልቶች ተገኝቷል፤ 1ኛው በአዱሊስ ምፅዋ አጠገብ 2ኛው በእንዳ አባ ፓንተሌዮን ከአክሰም አጠገብ ናቸው፤ የንጉሡ ስም አልተፃፈባቸውም።

ለአክሱም መንግሥት ታሪክ ትልቁ ወሳኝ ግለረኛ ሆኖ የተወሰደው በአዱሊስ[2] ሐውልት የተገኘው ጽሑፍ ነው። የተገኘው እንደ አጋማሚ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ ሐውልቱ በቦታው አይገኝም፤ ጠፍቷል። ጽሑፉ ያገኘው አንድ ቢዛንታናዊ በ525 ዓ.ም. ከሕንድ ጉብኝት መልስ እንደአጋማሚ አዱሊስ ተገኝቶ የነበረ ኮዝማስ ኢንዲኮፕለውስቱ Indicopleuste የተባለው ደራሲ ነው። ኮዝማስ ከአንድ የሲናይ ተወላጅ የሆነው ነጋዴ ጋራ ሆኖ አባስ በተባለው የራሂት /ሲናይ/ ሀገረ ገዥ ጽሑፉ እንዲቀዳው ቡትሰጠው ትሰባዝ መሠረት በአንድ የንጉሥ ዙፋንና በአንድ የአብነበረድ ድንጋይ የተቀረው የ2 ንጉሦች ረጅም ጽሑፎች መሬት ወድቀው ተሰባብረው አግኝተዋቸው ጽፎ እንዳስቀራቸው ገልጿል። አንደኛው ንጉሥ ግብፃዊ ነው፤ የሚተርከውም በአሰያ ሰላደረጋቸው ጦርነቶች እና ስለተቀዳጅው ድሉች ነው። ሁለተኛው ንጉሥ ኢትዮጵያዊ በየብሰና በባሕር ሰላደረጋቸው ጦርነቶች እና ስለተቀዳጃቸው ድሉች የሚያወሩ ናቸው። የሁለቱ ንጉሶች ስም ሐውልቶቹ በመሰበራቸው ሊታወቅ አልተቻሰም። በዚሁ "አዱሉታዊ" ተብሎ የሚጠራ ሐውልት ማስረጃ መሠረት ኢትዮጵያዊ ንጉሥ በዘገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር ሰፊ ዘመቻዎች ማካሄዱን ሰማወቅ ተችሏል። የአክሱም ታሪክ የምናውቀው በፈራረሰ ድንጋዮችና ፅሑፎች በገንዘቦችም ሳይሆር የሚገኙ ንጉሦች ሰገናቸው ብለው ያስቀረውዋቸው ጽሑፎች ብቻ ነው፤ እነዚህም ማስረጃዎች ዘማም ጥቂቶች ናቸው። የአክሱም ታሪክ የምናውቀው ከመጀመርያው በሚቋቋምበት ጊዜ አይደለም። በጠፋው የአዱሊስ ሐውልት የምናገኘው ጽሑፍ የአንድ አዲስ መንግሥት ሳይሆን የአንድ ረጅም ታሪክ ያሳለፈ፣ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዓመታት፣ የተደራጀ፣ የሥርር ጦርና የባሕር

[1] Carlo Conti - Rossini Storia d' Etiopia p 120
[2] Carlo Conti - Rossini ibd p 121

ኃይል ያለው፣ ከታሳቁ የሮማ መንግሥት በጦር ሚዳ የሚፋሰም መንግሥት ነው። ንጉሡ የሚተርከው በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ሰላደረጋቸው ዘመቻዎች ነው።

2. የአክሱም መንግሥት በሀገር ውሰጥ ዘመቻዎች፣

በሀገር ውሰጥ ባደረጋቸው ጦርነቶች ንጉሡ አሸንፏቸው፣ አስገበርኳቸው ከግዳቸው ሕዝቦች የአክሱም መንግሥት መሰራቾች መሆን ይገባቸው የነበረ ዘግአክሳዊ መንግሥት ቅርብ የሚገኙ አግዓዚያን እና ዓጋሚ ናቸው። ሌሎች ስሞችው ለመለየት የሚያስቸግር ሲጀን ሲሆኑ፣ በአዱሊስ አካባቢ የሚገኙ ሻሚኒ የተባሉ ሕዝቦች፣ ሰው በግይሄድባቸው በበረዶ ዙሪያቸሉ ተራራዎች የሚኖሩ ተጠቅሰዋል፣ ሀገሩም ብርዳማ ነው፣ በረዶም የሰው ጉልበት ድረስ ይደርሳል። በዚሁ አካባቢ ፍል ውሃ ያላቸው ሀገሮች አንዲ፣ ላዚኒ፣ ዘአጋባራ፣ የተባሉ ሕዝቦች ማስገበሩን ይተርካል። ቀጥሎም ተንጋይቲ የተባሉ አሰክ ግብጽ ድንበር ድረስ የሚኖሩ ሕዝቦች አሸንፎ መንገድ እንደሰራ ይናገራል። አነነ በመቲነ፣ ሰላያ፣ በተራራዎች የሚኖሩ ከቦ ከግረካቸው በኋላ ሴቶችና ልጆች በባርነት ወስዶ ንብረታቸውን እንደዘረፈ ገልጿል።

3. መጠነ ሰፊ አክሱም ዘመቻ በግብጽ እና በሰሜን ዓረብ፣ የፖልሚራ ጦርነት

ይህ ባሕርን አቋርጦ የተካሄደ ዘመቻ ኮንቲ ሮሲኒ ያልተሰመደ ከኢትዮጵያውያን አቅም በላይ ብሎታል[1]። በየብስ ወደ ግብፅ መንገድ እያሰራ በመርከብ ተሻግሮ ወደ ሰሜን ዓረብ የተደረጉ ዘመቻዎች የተያያዙ ናቸው።

ሰደቡብ ዓረቦች የንግድ እንቅስቃሴ ደህንነት ለመጠበቅ የተደረገ ዘመቻ ተብሎ ትርጉም ተሰጥቶት ነበረ። የአክሱም ጣልቃ እንዲደረግላቸው በጠየቁት መሠረት ነው ተብሏል። ከግብፅ ዘመቻ ጋር የተገናኘ በመሆኑ ግን ፀረ- ሮማ መንግሥት መሆኑን ያሰረዳል። በተዘዋዋሪ መንገድ አክሱም ፖልሚራን በመደገፍ በፀረ- ሮማ መንግሥት በጦርነቱ ተካፍሉ እንደነበረ ያሰረዳል። የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ ወደ መጨረሻ ውድቀት የዳረጓት የሮማ መንግሥት ከክርስቶስ ልደት በፊት በ23 ዓመት ናፖታን ባወደማት ጊዜ ነው።

በመሮዋ ደካማ መሆን በመጠቀም የአክሱም መንግሥት ወዳጅ የሆነው የብሰሚ በጃ መንግሥት ተቋቁሞ ነበረ። አክሱም ከብሰሚ ቤጃዎችና ከደቡብ ዓረቦች ጋራ ወዳጅነት ለመፍጠር ሰብዙ ዘመናት ፀረ ሮማውያን የጣት ማስፋፋት ፖሊስ ትግል ስታካሄድ ቆይታ ነበር። ይህ ትግል በከፍተኛ ደረጃ የተከሰተው በ262 ዓ.ም. ነበር። የሮማ ንጉሠ ነገሥት የነበረው ባልካናዊ አውሬሊያኑስ ነበረ። በዚሁ ጊዜ ፖልሚራ የተባለው በሰሜን ዓረቢያ ተቋቁሞ የነበረ መንግሥት ሶሪያ፣ ኢራቅና፣ ግብፅን፣ ሰሱችንም የመካከለኛው ምስራቅ ሀገሮችን ከሮማውያን እጅ አሰለቅቆ ጦርነት በገጠመ ጊዜ አክሱም ከወዳጆቿ መንግሥታት ከብሰሚ ቤጃና በደቡብ ዓረቦች

[1] Carlo Conti - Rossini ibd p 123

በመታገዝ ለፖለሚራ ድጋፍ ስትሰጥ ቆይታ ነበር። ጦርነቱ በሮማውያን ድል አድራጊነት ስለተፈፀመ በንጉሡ ነገሥቱ [1] አውሬሊየኖስ መሪነት ድል አድራጊዎች ሮማ ሲገቡ ሮማውያን እንደ ልማዳቸው በ274 ዓ.ም. ከጦር ምርኮኞች ውስጥ ከፖልሚራ ንግሥት ዞኖቢያ ጋራ ብለሚ፣ ቤኛ፣ አክሰማውያን እና የደቡብ ዓረቦች ምርኮኞች በሮማ አደባባይ በከፍተኛ ሥነ-ሥርዓት በስልፍ አልፈዋል። ስለ ጦር ምርኮኞች በስልፍ ማለፋቸው የተረከው ፕቢስኮ የተባለው በጊዜው የነበረው ሮማዊ ታሪክ ፀሐፊ ነው።

ትልቁ የዓረቦች ዘመን መነሳትና የዓረቦች ስልጣኔ ማስፋፋት ያልደረሰ ዘመሆኑ የፖልሚራ ለሚን ዓረብ መንግሥት ተደምስሷል። ምናልባት ግን ለዓረቦች መነሳት መንገድ ዘመክፈት አስተዋጽኦ አድርጉ ይሆናል።[2] ፖልሚራ ለትንሽ ጊዜም ቢሆን ለሁለቱ ታላላቅ መንግሥታት ለነበሩ ለሮማና ለፔርሲያ ሞንግሥታት ተቋቁማ ነፃነቷን ጠብቃ ቆማ ነበር። ከክርስቶስ ልደት በፊት 23 ዓመት ናፖታ ከተደመሰሰችበት ጊዜ በኋላ ደካማው የመሮዋ መንግሥት ከሮማውያን ጋር ግንኙነት ነበራ[illegible]ሌላው ክፍል ግን ከሮማውያንና መሮዋ ጦርነት በኋላ ባዶ ቦታ በረሃማ የነበረው ብለሚ ስፍራውበት፣ መንግሥት አቋቋመውበት ነበረ። ሮማዊ ታሪክ ጸሐፊ ፕቢስኮ ቢለሚ ቤኛ የአክሱም አጋርና ወዳጁ ናቸው ብሏቸዋል።

የአክሱም መንግሥት የቤኛ ብለሚ ወዳጅ ስለሆነ በናፖታ ሞት አልፎ ወደ ሰሜን እስከ ግብጽ ሞዛት ዘመቻ ከማድረጉ በላይ መንገድም ስርቷል። ይኸ የሚያሳየን የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያና የአክሱም ግንኙነት እንዳልተቋረጠ ነው።

ራስ የአክሱም መንግሥትም የቤኛ ተወላጆች ስላሉበት ሞዛቱ እስከ ባርካና እስከ አባይ የሚደርስ ነበር። ቤኛዎች ወደ ግብጽ ሞዛት ዘልቀው አየገቡ ዘረፋ ያካሄዱ ስለነበር ከሮማውያን ጋር የፀብ መንስኤ ነበሩ። አክሱም ዘጦርነቱ ጣልቃ እንድትገባም አስከትሏል። ጥንታዊት መሮዋ እየተዳከመች ብትሄድም ከግብጽና ከሮማውያን ግንኙነትና ወዳጅነት ለመፍጠር ሞክራ ነበር። ከሁሉ ይበልጥ ግን ከአክሱም ጋር የበለጠ ግንኙነት ነበራት፣ የባሕር በሯ አዱሊስ ነበር። የአክሱምና የመሮዋ ወዳጅነት የሚገልፅ "ኢትዮጲካ" የተባለው መጸሐፍ በ"ትረካ"[3] አበን የተፃፈው ይገልፃል። የሳባውያን ጽሑፍ በሰረዋ መገኘት የአክሱም ወይንም የየመን ነጋዲዎች ወደ መረዋ ይመላለሱ እንደነበረ ያስረዳል። እንደገና መረዋ በ254 ዓ.ም. በሮማዊ ንጉሠ ነገሥት ትሬቦኒውስ ጋሉስ ዘመን ከሮማ መንግሥት ጋራ ወዳጅነት ለመፍጠር የሞከረችበት ዘመን ነበረ።

ተረር አማኒ የተባለው የመሮዋ ንጉሥ የአክሱምና የብለሚ ወዳጅነት ስላስፈራው ከበባውን ለመበጠስ በማሰብ ከሮማውያን ጋራ መቀራረብ አስቦ እንደነበረ የሚያስረዳ ፊሌ በተባለው የመሮዋ ከተማ "በዲሞቲክ" ከተቀረፀ ጽሑፍ፣ መሮዋ ወደ ሮማ መልእክተኞቿን መላኳን ይገልፃል። ይህ የመሮዋ አቋም ግዛቷ በአክሱም ሠራዊት አንዲወረር ምክንያት ሆኗል። ምናልባት የመሮዋ መንግሥት ተቋርጠ በብለሚ መንግሥት የተጠቃለለው የብለሚ መንግሥትም የአክሱም አንድ ከፍለ ሀገር ከመሆን አልፎ አንድ መንግሥት ሆኖ አያውቅም። የኤውሮጳ ታሪክ ፀሐፊዎች የቤኛ ወረራ በግለት ይጽፉሉ። ነገር ግን ቤኛ በወረራ ሀገር ይዘው ገዝተዋል ለግለት አይቻልም።

(1) C. Conti - Rossini ibd p 124
(2) C. Conti - Rossini ibd p 126
(3) C. Conti - Rossini ibd p 124

ሥልጎንያቱም ዘላን ስለሆኑ በቋሚነት አንድ ቦታ ሰፍረው መንግሥት ለቋቁመው አያውቁም። ሆኖም ግብፅ በሮማውያን እጅ በነበረችበት ጊዜ ተባይድ እየገቡ ይዘርፉ ነበር። በሰሜን ሱዳን ብቅ እያሉ የሚጠፉ ጥቃትን የቤኛ መንግሥታትም ነበሩ። ቤኛ በንርዶፋን፣ ስናር፣ ገዚራ ሰፍሯል። እንድሁም በዛሬይቱ ኤርትራ ከምፅዋ ጀምሮ እስከ ከሰላ በወረራም በስፈራም ዘራትን ቤኛ ነው የሚሉ ስዎች ይገኛሉ። በከበሳ ከመረብ በስተሰሜንና በስተ ደቡብም ይገኛሉ። ሆኖም ቤኛ በሄዱበት ቦታ አንድ ጠባይ አላቸው፣ ይኸውም ቋንቋቸውን ትተው የአካባቢውን ሕዝብ ቋንቋ በመናገር የአካባቢውን ሕዝብ መስለው የመኖር ችሎታ አላቸው። በዚህ መሠረት በግብፅና ሱዳን የዓረብኛ ተናጋሪ ሆነው ዓረብ ሆነዋል። በኤርትራ እና በትግራይ ትግሪኛና ትግሬ ቋንቋ ተናጋሪ ሆነዋል። በኢርትራ ሰሜን ምዕራብ ሰፍረዋል። በሃይማኖትም እንደዚሁ እስላሞችና ክርስቲያኖች ሆነዋል። ኮንቲ ሮሲኒ በመጽሐፉ ምዕራፍ 12 ስለቤኛ የስልጣኔ ቅሪት ምልክቶች ብሎ ጽፏል። ቤኛም ሆነ ግእዝ ተናጋሪ ለእኛ ልዩነት የለውም፣ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የኩሽ ጉሳ ናቸው። የቤኛ ተብሎ የተገኘው የታሪክ ቅሪቶች በደምቢዛን እና በካርንሽም /ሀማሴን/ ፊደል መስል የተባሉ በድንጋይ ስሌዳ የተቀረፁ ጽሑፎች ናቸው። እንደ ፊደል ለማንበብ የማይቻል ቢሆንም ቅድመ "ሄሮግሊፈክ" ጽሑፍ የሚል ግምት ብንሰጣቸው ተገቢ ይመስላል። የቤኛ ቅሪት የተባሉ በየቦታው የተገኙ ሬክታንግል ቅርፅ ያላቸው መቃብር ናቸው። በሱዳን በባርካ፣ በሳሂል፣ ከሰላ አካባቢ በብዛት ይገኛሉ። እነዚህ መቃብሮችም ቅድመ ፒራሚድ ተብለው ግምት ቢሰጣቸው ተገቢ ይመስላል። ይህ ሁሉ ሲታይ ኢትዮጵያ በስልጣኔ ከግብፅ ቀደምትነት አላት ለማለት የሚያስደፍር በቂ ተጨማሪ ማስረጃ ነው። ድሮም ሆነ አሁን በሰሜን ነገደ ኩሽ በደቡብ ነገደ ዮቅጣን የተከፈሉ ሕዝቦች እንዳልነበሩና እንደሌሉ እንነነባባለን። የኢትዮጵያ ማእከል ወደ አክሱም የተዛወረበት ዋናው ምክንያት የግብፅ መንግሥት እና ስልጣኔ መውደቅ ነው።

ኮንቲ ሮሲኒ[1] ቤኛ በ5 ጎሳዎች ይከፈላሉ ብሎ ጽፏል፣ እነሱም

1. አባብደ (Ababde) በደቡብ ግብፅ የሚኖሩ ዓረብኛ ተናጋሪ የሆኑ ከዓረብ የተዳቀሉ
2. ቢሺዓሪ (Bishiari) ሱዳን የሚኖሩ ቋንቋቸው ዓረብኛ
3. ሀደንዶዋ (Hadendoa)
4. ሐለንጋ (Halenga) (ኤርትራ)
5. ቤኒአመር በኢትዮጵያ የሚኖሩ ሲሆኑ ቋንቋቸውም ግማሽ ትግሬ ነው። ግማሾቹ ቤኛ ቋንቋ ተናጋሪ ናቸው።

የቤኛ ሕዝብ ምንም እንኳ ቋንቋቸው ወደ መጥፋት የተቃረበ እነሱተኛ ሕዝብ ቢመስሉም በኢትዮጵያ ታሪክ ከፍ ያለ ቦታ የሚሰጣቸው ናቸው። በጥንታዊት ግብፅ ታሪክና ስልጣኔ በቀዋታም ሆነ በተዛዋዋሪ የተካፈሉ ናቸው። የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ የጀርባ አጥንት ነበሩ። የዛሬዪቱ ሱዳን በሕዝብ በብዛትም በአመራርም የበላይነት ያላቸው ናቸው። በሰሜን ኢትዮጵያ ተሰራጭተው የሚኖሩ ናቸው። በተሰይ ቤኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ በኢትዮጵያ ብቻ ስለሚገኙ የቤኛ ሀገርና ማእከል ኢትዮጵያ ናት ለማለት ያስቻላል። የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ የምትባለው መስኗ ከየት ወዴት እንደሆነ በትክክል ባይታወቅም ዋና ከተማዋ ናፖታ በነበረበት ጊዜ በአሁኑ አስተደደር ሱዳን ውስጥ ሲሆን፣ ዋና ከተማዋ መሮዋ በነበረበት ጊዜ ግን በአሁኑ

(1) C. Conti - Rossini ibd p 271

አስተዳደር በኢትዮጵያ ግዛት (ኤርትራ) ውስጥ ናት። ስለዚህ በአሁኑ አስተዳደርም ቢሆን የቀድሞዪት ኢትዮጵያ በሙሉ በሱዳን ውስጥ አይደለችም። አነስተኛ ክፍል በኢትዮጵያ ውስጥ አለች። የቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ ዋና ከተማ ከናፓታ ወደ መሮዋ መዛወሩን ትርጉም ሊኖረው ይችላል። ድሮም እንደዛሬ የቋንቋ አቀማመጥ ከሆነና የግእዝ ቋንቋ ከደቡብ ዓረብ የመጣልን ነው ብለን ካላመንን መሪዋ አካባቢ የኖረው የግእዝ ቋንቋ ተናጋሪ ሌላ ቋንቋ የኩም ቋንቋ ተናጋሪ በናፓታ አካባቢ በሚኖረው ሕዝብ ኃይሉ የአስተዳደር ስልጣን በመረከቡ ነው ብለን ትርጉም ልንሰጠው እንችላለን። በአጠቃላይ ይሄ የአክሱም መንግሥት ያደረገው ዘመቻ የግዛት ማስፋፋት ሳይሆን የእንድነት ማስከበርና የሁለቱ ሕዝቦች መመሀድ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ከክርስቶስ ልደት በፊት 1581 ዓመት ጀምሮ በተሰያዩ የግብፅ ፈርአኖች አማካኝነት ግብፅ በቀድሞዪቱ ኢትዮጵያ /ኑቢያ/ ወሰን እያለፈች ገዝታለች የሚለው አባባል ትክክል አይሆንም። ምክንያቱም የግብፅ እና የናፓታ መንግሥታት ሁለቱም በጋብቻ የተሳሰሩ ስለነበሩ ሁለቱ መንግሥታት መዋሀድ የተለመደ ነው። ከክርስቶስ ልደት በፊት በ1200 አመት ግብፅ በእስያም በእፍሪካም ሽንፈት በገጠማት ነበረ። በዚሁ ዘመን ሊብያዊ ፈርአን ሆኖ በቴብ መቅደሙ ለመቃወም የቤተ መቅደስ አለቆች ከሊቢያውያን ቀድሞ የነበሩ የሰርወ መንግሥት ወራሾች በመያዝ በናፓታ መንግሥት ለመመስረታቸው ኢትዮጵያ ከግብፅ ተገንጠለች። በተራቸው ዘመን ጠብቀው የናፓታ ነገሥታትም በግብፅ ላይ የበላይነት በመቀዳጀታቸው ናፓታ ከግብፅ ከተገንጠለች 500 ዓመት በኋላ ሁለቱ መንግሥታት አዋሕደው ፈርአን ተብለው 75 አመት ግዝተዋል። ይህ የሆነበት ምክንያት ካስዘታ የፒያንኪ 2ኛ አባት የፈርአን ሴት ልጅ አግብቶ ስለነበረ ልጁ የፒያንኪ የፈርአን ዘውድ ይገባኛል፣ ተወላጅ ነኝ በማለት በኃይል ወሮ ከያዘ በኋላ የተዋሀዱ የግብፅና የኢትዮጵያ ናፓታ ፈርአን ለመሆን በትተዋል።[1]

3. መጠነ ሰፊ የአክሱም በባህር ዘመቻ ወደ ደቡብ

በመርከቦች ወደ ደቡብ የተደረገው ዘመቻ በኢትዮጵያ ታሪክ ተደርጎ የማይታወቅ ነው። ምንም እንኳን ተጨማሪ ሌላ ማስረጃ ባይገኝም ከሁሉ የበለጠ የአክሱም መንግሥት የመጨረሻ ዓላማው ነበረ። የአዱሊስ የሐውልት ጽሑፍ[2] የሚለውን ብቻ በመጥቀስ ረሐውሊና ሶላቱ ለማሊያና ከአዛንያ በታች ያሉ ሕዝቦች እጣን ከሚንገዱ የበርበር ሀገር በሰፈው ሚዳዎች ውሃ የማይገኝባቸው የሚኖሩ ሕዝቦች አስገብሮ የባሕር ወደብ እንዲጠብቁ አዘዛቸው ካለ በኋላ ከባርባሪ ሰዎች ደቡብ አገራቸው ተራራዎች የበዙበት ሲሆን ራሴ በሠር ሚዳ ተሞግቼ ከአሸንፋኪቸው በኋላ ግብር እንዲከፍሉ አዝዠ በነሳ ለቀቅኳቸው ይላል።

ወደ ደቡብ ሀገሮች ዘመቻ የመጨረሻ ዓላማ የሀገሩ ስም ባይታወትም የወርቅ ሀገር ለመድረስ ነበረ ብለዋል። ይህ ስሙ ያልታወቀ ሀገር ግን ኮንቲ ሮሲኒ እንደሚለው ወለጋ ሊሆን እያችልም። ወርቅ በብዛት የሚገኝበት ንግሥተ ሳባም ወደ ንጉሠ ሰለሞን ከመሄዷም በፊት በመርከብ የተሳፈረችበት በመጽሐፍ ቅዱስ አፈር ተብሎ የሚጠራው ወደብ ሶፍላ ወደብ ነው። የወርቅ ሀገርም ዝኛው ትልቁ የሞኖሞታፓ መንግሥት ሀገር ዚምባቡዌ ነው።

[1] C. Conti - Rossini ibd p 271
[2] C. Conti - Rossini ibd p 121

ስለዚህ ይህ የአክሱም ዘመቻ የደረሰበት ሀገር ዚምባቡዌ መሆን እንዳለበት ይታመናል። በቀድሞ ጊዜ የወርቅ ማዕድን በሚመረትበት ጊዜም የኢትዮጵያውያን እጅም እንደነበረበት ብዙ ማስረጃዎች ይገኛሉ።

4. <u>የአክሱም መንግሥት ደቡብ ዓረብን ከግዛቱ ማቀላቀል</u>

የአክሱም መንግሥት ቀይ ባሕርን ተሻግሮ በደቡብ ዓረብ የግዛቱን ማስፋፋት ዘመቻ አካሂዶ ነበር። ነገር ግን ዘመቻ መካሄዱ የሚገልፁ ማስረጃ የለም። በተዘዋዋሪ ግን ዘመቻ መካሄዱ እና ደቡብ ዓረብ በአክሱም መንግሥት ቁጥጥር ስር መዋሏን የሚገልፁ ሁኔታዎች ኮንቲ ሮሲኒ እንደሚከተለው ያብራራዋል። በ281 ዓ.ም. ደቡብ ዓረብ ዝነኛው የነበረው ሻሚር በተባለው ንጉሥ ትገዛ ነበረ። ይህ በጥረቤት ሳህርታን ጦርነት ገጥሞ ያሸነፋቸው ለመሆኑ የሚገልፅ ጽሑፍ በመገኘቱ ሳህርታን ግሰትም የአበሻ ጎሳ በመሆናቸው አድራጎቱ የአክሱም መንግሥት ያሰቆጣል። ከጭፍጨፋ የተረፈ ሕዝብም እርዳታ ስለጠየቁ የአክሱም መንግሥት ቀይ ባሕርን ተሻግሮ የመንን ከግዛቱ ግጠቃለሉ የሚገልፁ ምልክቶች ብሉ ኮንቲ ሮሲኒ በመጻፉ የጠቀሳቸው የአክሱም መንግሥት ከዚህ በፊት ሲጠራበት የነበረው የአክሱም መንግሥት የሚል ሰያሜ በተጨማሪ የሒሚያር፣ የራይዳን፣ የሳባና የባልሄን ንጉሥ ተብሉ በመጠራቱ ከንጉሥ ሻሚር በኋላ የየመን ንጉሦች ተራ ቀያረው በታሪክ ተቋርጠ በመገኘቱ፣ የመን ለብዙ ዓመታት በአክሱም መንግሥት ቁጥጥር ስር እንደነበረች የሚያሰረዳ ነው።[1]

ዘመቻውን ያካሄደው አክሱማዊ ንጉሥ ማን ነበረ? ለሚለው ጥያቄ መልስ ለመሰጠት ቀጥተኛ የሆነ የጽሑፍ ማስረጃ ከየመን ከኢትዮጵያ፣ ከግሪክና፣ ከሮማ ገለልተኛ ሀገሮችም ማስረጃ አልተገኘም። ይህ በመሆኑ ኑሚዝማቲክ (Numismatic)[2] በጊዜው የነበሩ ንጉሦች ያሳተሟቸው ገንዘቦች ዘመጠቀም በአራተኛ መቶ ክፍለ ዘመን ዓ.ም. በአክሱም የነበረ ንጉሥ አፈላስ እንደነበረ ባሳተሟቸው ገንዘቦች ለማወቅ ተችሏል። በዚሁ መሠረት ድል አድራጊው ኢትዮጵያዊ ንጉሥ አፈላስ መሆኑን ለመገመት ተችሏል። አፈላስ በገንዘቦቹ ላይ የተጠቀመበት ፊደል ግሪክኛ ነበር። ከሱ በኋላ የነገሡ ኢንዲቢስና ዋዜብ የተባሉ ኢትዮጵያውያን ንጉሦች ግን በገንዘቦች ላይ የተጠቀመበት ፊደል ኢትዮጵያዊ ነበር። ትልቁና ዝኛው የአክሱም ንጉሥ ኢዛና የሚያሳትማቸው ገንዘቦች በግሪክ በደቡብ ዓረብና በኢትዮጵያ ፊደል ነበሩ።

የኢዛና መጠሪያም 1. የአክሱም 2. የሰጌምያር 3. ሳባ 4. የራይዳን 5. የሳልሄን 6. የሐበሻ 7. ዲያሞ 8. የካሱና 9. የቢጃ ንጉሥ የሚል ነበረ።
2ኛ. 3ኛ. 4ኛ. 5ኛ. መጠሪያዎች የደቡብ ዓረብ መጠሪያዎች ናቸው። ሐበሻ የሚለውም አክሱም ከሚለው አንዳንድ ጊዜ ይጠቀሰላል። እንደዚሁም አክሱም የሚለው ኢትዮጵያ ተብሉ አንዳንድ ጊዜ ይጠራል። እንደ ሀገር ሊላውን ሀገር ጉልበት አግኝቶ ከገዛ ቋንቋውን ባሕሉንና ዘሩን ሊያስተላልፍ ይችላል። የአክሱም መንግሥት ደቡብ ዓረብን መግዛቱ ዘታሪክ የተረጋገጠ ሲሆን ደቡብ ዓረብ ግን ኢትዮጵያን መግዛቷ በታሪክ የተጠቀሰ ነገር የለም። ኤውሮጳውያን

[1] Carlo Conti - Rossini ibd p 126
[2] Carlo Conti Rossini ibd p 128

ግንኛውንም ስልጣኔ ከአስያና ከአውሮጳ ነው ወደ አፍሪካ ሊሄድ የሚችለው የሚል ዘረኛ አስተሳሰብ ስላለቸው ቀደምት አባቶቻችን የሳብያውያን ፊደል በመውሰዳቸው ልዘመለደ ታሪክ በመፍጠር ደቡብ ዓረብ ኢትዮጵያን በቀኝ ገዥነት ይዛ እንደነበረ ስልጣኔዋና ቋንቋዋን ባሕሏንና ፊደሏን እንደሰጠቻት በማስመሰል በባሕላችን የሌለው ታሪክ እንድንቀበለው በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ዛቂ ግን ደቡብ ዓረብ በላሐርታን ይገኙ የነበሩት የሐበሻ ሕዝቦች በትድመ ታሪክ ከኢትዮጵያ ወደ ደቡብ ዓረብ ተሻግረው ወይንም እሳው ተፈጥረው የሰፈሩ መሆናቸውን የሚጠቁም ነው። የእክሱም መንግሥታት ከላይ እንደተገለፀው ሊላ ሀገርን ለመውረር ላይሆን ዘሮቻቸው የሆኑ የሐበሻ ለዎች ከደቡብ ዓረቦች ጥቃትና ሞፍጨፋ ለማዳን በመቻ አካሂደው ለብዙ ዓመታት ከ281 እስከ 360 የመንን በቱጥራቸው አድርጉዋቸው እንደነበረ በታሪክ የተረጋገጠ ነው። በመቻውና ጦርነቱ አስልጣኞቻችን እና አባቶቻችን በተባሉት በሳብያውያን ላይ ነበረ። ኤውሮጳውያን ምሁራንም ቢሆን ነጮች እና አለያውያን ከፍተኛ ዘር አፍሪካውያን ዝቅተኛ ዘር ከሚለው አመለካከት ሊላቀቁ አይችሉም። ስለዚህ ትክክለኛ ታሪክ ለመፃፍ ችግር አለባቸው።

የላባ የራይዳንት የሐድራመት የላማናት ንጉሥ ተብሎ የሚጠራ ሻማር የሐበሻ ጉላ የሆኑ ሊሐርታን ዳዋአት በተባሉ ጦርነት ገጥሞ እንዳሸነፋቸው የሚገልፅ ጽሑፍ በአንድ ድንጋይ የተቀረፀ በየመን ይገኛል። እነዚህ ሕዝቦች ከእክሱም ንጉሥ አርዳታ በጠየቁት መሠረት አፈላስ ወደ የመን ሊዘመት ችሏል። ስሐርቲ የሚባል ሀገር በኢትዮጵያ ክመረብ በስተሰሜንና በስተደቡብ ይገኛል፣ በየመንም ይገኛል። በየመን ላሐርታን የሚባለው አካባቢ የመን ባሕር ዳርቻ የሚገኘው የሚኖሩ ሕዝቦች ዓረቦች እንደራሳቸው ጎላ አይቆጥሯቸውም፣ ሐበሻ አፍሪካዊ የሚኖርበት ሀገር የዓረቦች አምነት መሆኑን ኮንቲ ሮሲኒ ገልጿል።[1] ስለዚህ ለሐርቲ የዓረብ ስም ሳይሆን ኢትዮጵያዊ ስም ነው ዛዋኦት የተባሉም ኢትዮጵያውያን ናቸው።

እላይ እንደተገለጸው በኮዝማስ በአዱሊስ ሐውልት የተገኘው ማስረጃ ያፃፈው ንጉሥ የመጀመርያና ብቸኛ ከእኔ ጎላ ነገሥታት በማለቱ የእክሱም መንግሥት መሥራች ሊሆን እንደሚችል ተገምቶ ነበረ በማለት ኮንቲ ሮሲኒ ጽፏል። ማስረጃም የተጻፈው በ250 ዓ.ም. ስለሚገመት እሁን ካለንበት ዘመን 1995 ዓ.ም. 250 ሲቀነስ 1745 ዓ.ም. ዝቅ ይላል ማለት ነው። ታሪካችን ከንግሥተ ሳባ በመጀመር ኢትዮጵያ 3000 ዓመት ታሪክ አላት እየተባለ ሲነገር የምንሰማው ጉዳይ ነው። ኤውሮጳውያን የዘገራችን ታሪክ ጸሐፊዎች ደግሞ ደቡብ ዓረቦች ወደ ኢትዮጵያ በመጡበት ዘመን የታሪካችን መነሻ በማድረግ ደቡብ ዓረቦችም ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ የመጡት በ250 ዓመት ክክርስቶስ ልደት በፊት ስለነበሩ ኢትዮጵያ የ2500 ዓመት ታሪክ አላት ትባላለች።

5. <u>የኢትዮጵያ ፊደል</u>

የኢትዮጵያ ፊደልም በሚመለከት ጉዳይ እንደገና በማንሳት አባቶቻችን ፊደሉን የፈጠሩት በጣም አሻሽለው ነው። በመጀመርያ ቡስትሮፈዶን (Bustrophedon)[2] የሚባል የነበረው ማለት ክግራ ወደ ቀኝ አፃፃፍ

[1] C. Conti - Rossini ibd p 127
[2] C. Conti - Rossini ibd p 220

ዘማስቀረት አንደ ግሪኮች ከሌግውያን የመጀመርያና ብቸኛ ክግራ ወደ ቀኝ አፃፃፍ፡ ዘመኮተል አሻሽለውታል። በተለይም በኢትዮጵያ ብዙ ለውጥ በማምጣት በ4ኛ መቶ ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ[1] ፊደል ሊፈጠር ችሏል። የደቡብ ዓረብ ነው የተባለ ጽሑፍ በዋዲ ሐማማት (Wadi Hamamat) [2] የተገኘው ጽሑፍ የኢትዮጵያ ፊደል ይሁን ወይንም የተሻሻለ የደቡብ ዓረብ ፊደል ይሁን መለየት የሚያስቸግር ሆኖ ተገኝቷል።

ስለዚህ ራሳቸው ሳባውያን የዓረብኛ ፊደል ከመኮተላቸው በፊት በኢትዮጵያ ፊደል መጠቀም መጀመራቸውን ያሳያል። በሌላ በኩልም አንዳንድ ምሁራን የተሻሻለው ብዙ ቆይቶ ወይስ ክቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው የሚል አሰተያየት ተሰንዝሮ ነበር። ነገር ግን ኮንቲ ሮሲኒ በዓዲ ቀይህ አጠገብ የሚገኘው በአውዳሴ ተራራ፣ አንዲሁም በአዲ ቀይህ እና ደራ መሐከል የሚገኘው ደራ ቡተባለው መንደር የተገኙ ጽሑፎች የሳባውያን ፊደል ለውጥ ሂደት የሚገልፁ በመሆናቸው ምሁራን ያቀረቡት ሐሳብ ውድቅ በማድረግ ለውጡ የተደረገው በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መሆኑ ጽፏል። የመጀመርያው የኢትዮጵያ ፊደል ጽሑፍ የተገኘው በአንድ መቃብር ሐውልት[3] መታራ (Metara) በተባለማው መንደር በአክለጉዛይ ነው።

ከኢዛና በፊት የነበረ ዋዘብ (Wazeb) የተባለው የእክሱም ንጉሥ ያወጣቸው ገንዘቦችም በአዲሱ የኢትዮጵያ ፊደል የተጻፈ ስለሆነ የኢትዮጵያ ፊደል ጥንታዊነት የሚያረጋግጡ በመሆናቸው የምሁራኑ ተቃውሞ ለውጡ የመጣው በ4ኛ መቶ ክፍለ ዘመን የመጀመርያ አጋማሽ አለመሆኑን የሚያቀርቡት ማስረጃ የለም።

2. ሊላ ጥያቄም ተነስቷል ለውጡ ያመጡት ግን ነበሩ? የሚል ነበረ[4] የኢትዮጵያ ፊደል ከሕንድ ፊደል ግንኙነት አለው በማለት የተወረሰው ከሕንድ ፊደል ነው ብለው የተከራከሩ ነበሩ። ይህ አባባል ግን ሊሆን የማይችል ነገር ነው፣ ምክንያቱም ሕንድና ኢትዮጵያ በጣም የተራራቁ ስለሆነ የቅርብ ግንኙነትም ስላልነበራቸው ተቃውሞው ውድቅ ሆኗል።

3. ፊደሉን ያመጡት ሚሲዮናውያን ክርስቲያኖች ናቸው የሚል አስተያየትም ተሰጥቷል። ይኽም አባባል ትክክል አለመሆኑን የምንረዳው ለውጡ ፊደሉ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው የክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያ ከመሠሠጣቱ በፊት በቅድመ ክርስትና በነበረው አምልኮት ጊዜ መሆኑን ሁሪንገሏል።

4. ፊደሉ ወደ ኢትዮጵያ የመጣው በግሪኮች ምሁራን አማካኝነት ነው የሚሉም ነበሩ፣ ይኽም ቢሆን የማይመስል አስተሳሰብ ነው፣ ምክንያቱም ግሪኮች ለኢትዮጵያ ፊደል ለመፍጠር ይጨነቃሉ ብሎ ማሰብ የማይመስል ነው።

5. ፊደሉ ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡት የኢትዮጵያ ምሁራን ሊሆኑ ይችላሉ የሚል አስተያየትም ተሰንራዝሯል። ይኽም በቂ ማስረጃ ባይኖርም ትክክል የሚመስል ነው።

6. በሰሓርታን ደቡብ ዓረብ ባሕር ዳርቻ ለፍረው የነበሩ ኢትዮጵያውያንን ክሳባውያን ይፈጸምባቸው የነበረ ብደልና አልቂት ለማዳን ወደ ደቡብ ዓረብ ዐረ ሳባውያን የአክሱም መንግሥት ዘመቻ መሪ የነበረው

[1] C. Conti - Rossini ibd p 221
[2] C. Conti - Rossini ibd p 221
[3] C. Conti - Rossini ibd p 221
[4] C. Conti - Rossini ibd p 221

የአክሱም ንጉሥ አፈላስ የጀመተበት ዘመን በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሊጋማሽ ስለሆነ የኢትዮጵያ ፊደልም ከሳባውያን የተወሰደው በዚህ ዘመን ፀሐፍት የሳባ ፊደል ወደ ኢትዮጵያ ያገባ አፈላስ የተባለው የኢትዮጵያ ንጉሥ መሆኑን ፊደሉ የተሻሻለውም በኢዛና ንጉሥ ዘመን መንግሥት መሆኑን አጠያያቂ አይሆንም ብዙ እንመታለሁ። ስለዚህ ፊደሉ ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡት ሳባውያን ሳይሆኑ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ አፈላስ መሆኑን ብለን መደምደም እንችላለን።

7. ከአፈላስ በፊት የነበሩት ነገሥታት በሐውልቶች ያሰቀርጿቸው የነበሩ ጽሑፎች አፈላስ ራሱም ተክታዩ ንጉሥ ኢንዲቢስም ይጠቀሙ የነበሩ በግሪክ ቋንቋ ሲሆን ተጥሉ የንገሠ ንጉሥ ዋዜብ ግን በኢትዮጵያ ፊደል ሻወል የሌለው ተጠቅሟል። ከእሱ ተጥሉ የንገሠ ትልቁ የኢትዮጵያ ንጉሥ ኢዛና እንደእስፈላጊነቱ በሳባ፣ በግእዝ፣ በግሪክ ቋንቋና ፊደል ሻወል የሌለው በመዉረሻም በግእዝ ፊደልና ቋንቋ ሻውል ያለው ይጠቀም እንደነበረ ታውቋል። ስለዚህ ከሳባውያን ተመስዶ ተመሳሳይ ፊደል በኢትዮጵያ የተፈጠረው ኢትዮጵያዊ ፊደል እንደሚባለው ሳባውያን ወደ ኢትዮጵያ ይዘውት የመጡ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከአምስተኛ እስከ ሁለተኛ ያለው መቶ ክፍለ ዘመን ሳይሆን ኢትዮጵያ በአፈላስ ንጉሥ መሪነት ዘመቻ እካሂዳ የመንን ከገዛች ያጠቃለለችበት ጊዜ በ4ኛው መቶ ክፍለዘመን ክክርስቶስ ልደት በኋላ ሲሆን፣ ስራ ላይ የዋለውና የተሻሻለውም በንጉሥ ዋዜብ እና በንጉሥ ኢዛና ዘመን መንግሥት መሆኑን ከዚህ በላይ የተዘረዘሩ ሁኔታዎች በተጨማሪ ለመረዳት እንችላለን። ከአፈላ የየመን ዘመቻ በፊት የሳባ ፊደል ወደ ኢትዮጵያ መግባቱ የሚያመለክት በታሪክ የተመዘገበ ነገር የለም። ለወደፊት በአርኪኦሎጂ ቁፋር ሊላ ታሪካዊ ግለጻዎች ሊገኙ ይችላሉ። ባሉት ጥቂት ግለጻዎች መሠረት ግን ከንጉሥ አፈላስ በፊት የአክሱም ነገሥታት በድንጋይና በሐውልቶች ጽሑፎቻቸው ይጠቀመብት የነበሩት ቋንቋ ዓሰም አቀፋዊ እውቅና በነበረው በግሪክ ፊደልና ቋንቋ ብቻ እንደነበረ እንረዳለን። እንደ ኮንቲ ሮሲኒ አገላለጽ ንጉሥ ኢዛና ክግሪክ ቋንቋና ፊደል ውተጨማሪ በሳባና በግሪክ ፊደልና ቋንቋ ያጻፈው ገናው በአካባቢ ሀገሮች እንዲታወቅለት በግዕብ ሲሆን፣ ዘሳባ ፊደል፣ በግእዝ ቋንቋ የሳባ ቋንቋ እንዳንድ ጊዜ የተቀላቀለበት መገኘቱ የሳብያውያን ቋንቋ ዘቤተመንግሥቱ እንዘዛም እንደማይታወቅ የሚያስረዳ ምልክት ነው ብሉታል። ዘተጨማሪም በኢትዮጵያ ይገዛ የነበረው የደቡብ የመን እንዲገባቸው [1] የኢትዮጵያ ነገሥታት በሐውልቶቻቸው በሳባ ፊደልም ይጽፉ ነበር።

አንድ ሀገር ቋንቋው በፊደል ጽፎ ኩተጠቀመ እስቀድሞ በሥልጣኔ የደረጀ መሆን ይጠበቃል። እኛ የሥልጣኔ ቀደምትነት ያሰን እንደመሆናችን መጠን የተሻሻለ ፊደልም በአፈላስ ዘመቻ ዘመን ከየመን ከሰደን እንጂ፣ ደቡብ ዓረቦች ጊዜው በትክክል የማይታወቅ ዘመን ወደ ሀገራችን እምጥተው ሰጡን አስተማሩን ግስት ልባወስድ ታሪክ ነው።

[1] Conti - Rossini ibd p 132

6. የአክሱም መንግሥት ወደ ዓረብ አገር ተሻግረው የተካሄደው ቅዱስ /የመስቀል/ ጦርነት[1]

ዘመቻው የተካሄደው በንጉሥ ካሌብ በ525 ዓም ነበረ። የተካሄደበትም ምክንያት የጥንት አምልኮት ተከታይ የነበሩ ዓረቦች በክርስትና ተከታይ ዓረቦች ያደረሱት በደልና የጅምላ ጭፍጨፋ ስመበቀል ነበር። በዚሁ የአክሱም መንግሥት ጣልቃ ገብነት ዘመቻ መካሄድ ብዙ የማስረጃ ምንጮች አሉ። ነገር ግን በብዙ መንገድ እና አስተያየት ታሪኩን የሚገልጹ ናቸው። የኢትዮጵያ የመስቀል ጦርነት ከኢውሮጳውያን የመስቀል ጦርነቶች የሚለይበት በኢውሮጳውያን በወዶ ዘመቾች የተካሄደ ሲሆን የኢትዮጵያ ግን በንጉሡ የሚመራ ነበረ።

1. ከክዝግስ የአዱሊስ ሐውልት ጽሑፍ ቀድቶ ስታሪክ ያሰቀረ
2. ከቢዛንታይን
3. ከሶርያ
4. ከዓረብ
5. ከኢትዮጵያ ወገን ምንጮች ናቸው።

ጦርነቱ ስ 3 ክፍል መከፈል ይቻላል

1ኛ. በመጀመርያ የአክሱም ወታደራዊ ዘመቻና ጣልቃ ገብነት ዓላማው የዘርበያ ዓረባዊ መንግሥትን ስመረዳት ይሁን እንጂ፣ ከግዙፍ የሮማ መንግሥት ጥቃት፣ ፀረ- ሮማ መንግሥት ነበር።

2ኛ. በሁስተኛው የአክሱም መንግሥት ወታደራዊ ዘመቻና ጣልቃ ገብነት ዓላማው ያበሻ ዘሮች ከጭፍጨፋ ስማዳን ፀረ ሳባዊ መንግሥት ነበር።

3ኛ. የአክሱም ወታደራዊ ዘመቻና ጣልቃ ገብነት ዓላማው ሃይማኖታዊ የክርስትና እምነት ተክታዮችን ከአልቂት ስማዳን ፀረ - ሂሚያር ይሁዳዊ ዓረባዊ መንግሥት ነበረ። የ1ኛና 2ኛ ጦርነቶች የተካሄዱት በኢትዮጵያ ፍላጉት ብቻ ሲሆን 3ኛ ጦርነት ግን ተጠቃሚና አይዞህ ባይ 3ኛ. ወገን ትልቁ የቢዛንታይን መንግሥት እጅ ነበረበት። ይህ መንግሥት ራሱ ምንም ሳይንቀሳቀስና ስጦርነቱ አስተዋፅእ ሳያደርግ የአክሱም መንግሥትን ብቻ በቀጥታ ልመና በመገፋፋት፣ እንዲሁም የግብፅ አሰክንድሪያ ፓትርያርክም የደቡብ ዓረብ ክርስቲያኖችን እንዲረዳ የአክሱም መንግሥትን እንዲያግልዱ በማድረግ፣ በውጭ ኃይሎች ግፊት የተደረገ ጦርነት ነበር። የቢዛንታይን መንግሥት የፐርሲያን መንግሥት ስግሻነፍ ሰላቃተው ኢትዮጵያን መሣሪያ ያደረገበት ብቻዋን በጦርነት እንድትካፈል ያጋለጣት ወቅት ነበር። ሁለቱ ኃያላን መንግሥታት ፍልሚያ በሚያደርጉበት ጊዜ የኢትዮጵያ ጥቅም በግይነካ ጉዳይ ብቻዋን በጦርነት እዘቅት መግባት እይገባትም ነበር። ስስጉዳዩ ዝርዝር ስንገባ ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ድል አግኝታስች፣ ስሃምሳ ዓመታት የመንን ገዝታስች። እንዳንዶቹ 72 ዓመት ያደርጉታል እስከ 597[2] ነገር ግን የዓረብ ሕዝብ ጥላቻ ብቻ ነበር ያተረፈችው። ዘመቻው ግዙፍ ነበር፣ የኢትዮጵያ ወታደሮች ቀይ ባሕርን ሲያቋርጡ በ191 በቢዛንታይን የንግድ መርከቦችና በ170 አጊ

[1] C. Conti - Rossini ibd p 167
[2] C. Conti - Rossini ibd p 199

ካሌብ ባስራቸው መርከቦች ተሳፍረው ነበር። የመን የደረሱትና አጼ ካሌብ ዘመቻ ያካሄደው በሁለት ዙር ነበር።

በመጀመርያ ጦርነት ሳይገጥመው የኢምያር ንጉሥ እጁን ስለሰጠ ወድያውኑ አጼ ካሌብ ራሱ የሾመው በየዓመቱ ግብር የሚከፍል ክርስቲያን ንጉሥ ትቶ ወደ ሀገሩ ሲመለስ፡ ነገር ግን ስለከዳውና የክርስቲያን ጭፍጨፋ ስለቀጠለ እንደገና ከፍተኛ ወታደራዊ ኃይል ይዞ ከዓረቦች ጋራ ጦርነት ገጥሞ ድልን ተቀዳጀ። ኢምያር ንጉሥ ሸሽቶ በፈረስ እየጋለበ ቀይ ባሕር ውስጥ ገብቶ ሞተ። አዲስ የተሾመ ንጉሡም ብዙ አልቆየም አጼ ካሌብ ንጉሥ አድርጎ የሾመው አብርሃ የተባለውም ወዲያውኒ ከዳ። ከኢትዮጵያ ወታደሮች ግማሾቹ ከዓረብ ሀገር ተባረሩ። በመጨረሻ አብርሃ የንጉሥነት ስልጣን ነጥቆ ያዘ። ቆይቶ ከአጼ ካሌብ ወኪል ጋር ቢታረቅም እንደ ነፃ ንጉሥ ሆኖ ሀገሩን ያመራ ነበር። በኢትዮጵያውያን በኩል እስከ ዘመናችን ድረስ አጼ ካሌብ አጽብሀ ተብሎ እየተጣራ አብርሃ ወአጽብሀ እየተባሉ ከእቡነ ፍርሚናጦስ ከሦቱ ብርሃን እኩል ወደ ኢትዮጵያ ክርስትና ያስገቡ ተብለው እንደ ቅዱሳን ይከበራሉ። በዓረቦች ዘንድ ግን ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ጥላቻ ነበረ ያተረፉት። የሕዝብ ዘፈኖች ዐረ- ኢትዮጵያ የጭቆና አገዛዝ ነበሩ። የዘመኑ የዓረብ ጸሐፊዎች "ሴቶች የሚገርዙ፣ የቁላ ብሊታዎች" ወዘተ... እያሉ ኢትዮጵያውያንን እያጥላሉ ይፅፉ ነበር። የኤውሮጳ ታሪክ ጸሐፊዎች የሚተርኩት በኢትዮጵያና በደቡብ ዓረብ ያለው የስጋ ዝመድና የሚያስታውስ ሲሆን፣ ከዓረብ ወገንም ሆነ ከኢትዮጵያ ወገን ግን ይህን ዝምድና የሚያስታውስ ምንም ማስረጃ የለም።

ዓረቦች ብቻቸው ከኢትዮጵያ ቀንበር አገዛዝ መላቀቅ ስላልቻሉ ለቢዛንታይንን መንግሥት ስሞቻቸውን ሊያለሙ የሚያዳምጧቸው ስላጡ ሬታቸው ወደ ፋርስ ንጉሥ አዞሩ። ፋርስ ከቀይ ባሕር ብዙ የሚርቅ ሀገር ዘመሆኗ፣ ቀይ ባሕር ለመድረስም በረሀማ ቦታዎች አቋርጣ ማለፍ ስለሚያስፈልግ፣ በደቡብ ዓረብ አስተዳደር ግልቃ እንድትገባና የዓረቦች ጥያቄ ለመቀበል ተላል አልነበረም። በመጨረሻ ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ ያላት መሆኑን ስላወቀች 800 ወታደሮች ብቻ በመሳክ የመንን ይገዛ የነበረው የአብርሃ ልጅ ማብሩክ የተነሳበት የሕዝብ ዐመፅ በቁጥጥሩ ስር መዋል ስላልቻለ በዐረ ኢትዮጵያ ዐመፀኞች እየተረዳ የፋርስ መንግሥት በቆላሱ ድል ሊቀዳጅ ችሏል። ኢትዮጵያውያን በመሉ ከዓረብ የተወለዱ ክልሎችም ጭምር ተገደሉ። ኃይለኛ እንደ አጼ ካሌብ ንጉሥ በኢትዮጵያ ቢኖር ኖሮ ለኢትዮጵያ ታሪክና ሕልውና ከሃይማኖት ጉዳይ ሌላ የሞት ሽረት ጉዳይ ስለነበረ ሌላ የተጠናከረ ዘመቻ ማድረግ ባሰፈለገ ነበር። ይህ ባለመደረጉ ኢትዮጵያ የቀይ ባሕር ባለቤት መሆኗ አከተመ። ቀይ ባሕርም እንደ ጥንቱ ያበሻ ባሕር ኢትዮጵያዊ የሚል ስያሜ ተሽሮ በዓረቦች አጠራር ለዘለቄታ ቀይ ባሕር ተባለ የሰማሊ ባሕርም ባርባሪያ ባሕር ተብሎ ይጠራ የነበረው ሕንድ ውቅያኖስ ሆነ። የአዛንያ አጠራርም ተሰርዞ ሰማሊ ኪንያ ታንጋኒካ ወዘተ... የሚል ስም ተሰጣቸው፣ ኢትዮጵያ ግዛት ክልል ከባብ ኢል መንደብ በስተ ደቡብ ያለው አጣች። ለጥቂት ጊዜ ኢትዮጵያ ከዓለም ታላላቅ መንግሥታት ቁጥር ገብታ የነበረችበት ነበረ።[1] በእንዲሁም የውድቀቷ መጀመርያ ምዕራፍ ሆነ።

ከሰለጠነ ዓለም ለመገናኘት በየብስ በግብፅ በኩል እንዳትገናኝ ግብፅ እንደቀድሞ ክርስቲያናዊት አፍሪካዊት ሀገር መሆኗ ቀርቶ እስከማዊት

[1] C. Conti - Rossini ibd p 200

ዓረባዊት ሀገር ስለሆነች፣ ከኢትዮጵያ ጋር የነበራት ግንኙነት ውሱን ነበር። የባሕር በርም ምንም እንኳን ነብዩ መሐመድ ኢትዮጵያ እንግዳ ተቀባይ ብሉ ቢወድስም በሀገሩና በእስልምና ሃይማኖት የተቀበሉ ሀገሮች በኩል ሁሉ ለኢትዮጵያ እንግዳ ተቀባይነት ውለታ ያሳዩት በጎ አመለካከት አልነበረም። ወደ ኢየሩሳሌም ለመሳለም ለመሄድ የሚሞክሩ ምእመናን ኢትዮጵያውያን ብዙዎቹ የሞት ዕጣ ነበር የሚጠብቃቸው። በእንዲሁ የኢትዮጵያ የባሕር ጠረፍ የእስልምና ሃይማኖት ሰብክ ተሰፋፍቶባቸው ኢትዮጵያውያን በሃይማኖት ከፋፈሉን። በመጨረሻም በተለይ በመሐመድ ግራኝ ጊዜ ለአርስ በርስ ጦርነት ገፋፍተው ኢትዮጵያን ለባዕ ለሥልጣኔ ኋላ ቀርነት ዳረጓት። የኢትዮጵያ እንግዳ ተቀባይነቷ የተከፈላት ውለታ በጠላትነት ነበረ። የአክሱም መንግሥት ውድቀት በደረሰበት ዘመን በ705 715 ዓ.ም. በስሜናዊ ዐረብያ ከሙት ባሕር 100 ኪሉ ሜትር በስተደቡብ በአንድ በአማያዲ ቤተ መንግሥት ሕንፃ የክሊፎች መዝናኛ ቦታ በትልቁ ዋና ክፍል ግርግዳ ላይ በካሲፋ የተሸነፉ 4 ከዓለም ታላላቅ ነገሥታት ተስለው ይገኛሉ እነሱም[1]

1ኛ. የቢዛንታናዊ ቂሳር ንጉሠ ነገሥት
2ኛ የፋርስ ንጉሥ ኮስሮዮ
3ኛ. የስፓኝ የመጨረሻ ቪዚጎት ንጉሥ ሮድሪጎ
4ኛ. የኢትዮጵያ ንጉሥ ናኻሺ ናቸው።

7. በሰሜን ኢትዮጵያ የታሪክ ቅሪቶችና ቦታዎች

ስለኢትዮጵያ ታሪካዊ ቦታዎች ስናስታውስ ትዝ የሚሉን አብዛኛው "አቤሊስክ" ተብሰው የሚጠሩ በአክሱም ቆመውና ወድቀው የሚገኙ የአክሱም ሐውልቶች ናቸው። አንድ መቶ የሚጠጉ የአክሱም ሐውልቶች "አቤሊስኮች" ብቻ አይደሉም የኢትዮጵያ የጥንት ሥልጣኔ ቅሪቶች። ደቡብ ዓረቦች ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ይዘው የመጡ ፊደላቸው ብቻ አይደለም። ኮንቲ ሮሲኒ በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎች በማለት አንድ ካርታ[2] አውጥተዋል በዚሁ ካርታ መሠረት በዚሁ ታሪካዊ ቦታዎች የሚገኙት ከአክሱም በስተሰሜን ከናቅፋም በስተሰሜን የሱዳን ግዛትም የሚያጠቃልሉ በባሕር ዳርቻዋም ከአዱሊስ እስከ ራሄይታ የሚደርሱ ናቸው። ከፍተኛ ስልጣኔ በዳበረባቸው ቦታዎች የከተማ የቤት ፍርስራሾች፣ ቤተክርስቲያኖች፣ መቃብሮች፣ አቤስኮች፣ ዙፋኖች፣ የውሃ ማጠራቀሚያዎች፣ ስእሎች እና የሸክላ ስእሎች ፈራርሰው ይገኛሉ። እነዚህ ሁሉ ቅሪቶች ከደቡብ ዓረብ ስልጣኔ ተመሳሳይነት ሊኖራቸው ሲገባ ምንም ተመሳሳይነት የላቸውም። የፈራረሱ ቤቶች የሚገኙ በጥንት ቦታዎችና በአሁኑ ጊዜ ትግሬኛ ተናጋሪ አካባቢ የሚሰሩ የቤቶች አሰራር አንድ ዓይነት ነው። አራት ማእዘን ያለው "ሕድሞ" የተባለው የቤት አሰራር ከደቡብ ዓረብ ሆነ ከግብፅ የቤት አሰራር ሰለማይመሳሰል፣ በአክሱም ጊዜም የተለመደ ነው ተብሎ በመገመት አክሱማዊ የቤት አሰራር ተብሏል። ክቡ የቤት አሰራር ግን በመላው እፍረካ ስለሚገኝ እፍረካዊ የቤት አሰራር ተብሏል። ብዙ የመቃብር ዓይነቶች ተገኝቷል። ከቤተክርስቲያንና ቤተመቅደስ አጠገብ ወይንም ከምድር ቤት በልዩ ሞያ የተሰሩ ወይንም መሬት ቆፍረው ብቻ የተቀበሩ ረጃጅም አቤሊስክች በአክሱም ብቻ ሊገኙ አንስተኛ ቁመት ያላቸው በብዙ ታሪካዊ ቦታዎች

[1] Carlo Conti -Rossini Storia d' Ethiopia p 124
[2] C. Conti -Rossini ibd Indice delle tavole XXVI

ይሻሻሉ። ግን እንደሰራቸው ለማወቅ አይቻልም። በደቡብ ዓረብ የአቤሊስክ ስራ እምብዛም የተሰመደ አልነበረም።

ኢትዮጵያውያን ብቻቸውን ሊሰሯቸው አይችሉም፣ ከግብፅ የመጡ ባለሙያዎች እርዳታ የተሰሩ ናቸው ከግሰት በስተቀር የአሰራራቸው ታሪክ ሰግቆት አልተቻለም። ዙፋኖች በብዛት የሚገኙት በአክሱም ነው። በአዱሊስ፣ በዲከዲክ /ናቅፋ/ ተገኝቷል። ሰአሉት፣ የሸክላ ስራ ምስሎች ወዘተ... ከግንም ሐገር በአሰራራቸው የሚቀራረቡ ሆነው አልተገኙም። ደቡብ ዓረቦች ሰንግድ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ በሚመላለሰብት ጊዜ ፊደል ብቻ አይደለም የተማሩት፣ ባሰ ብዙ ፎቅ የቤት አሰራርም ከባቢሉኒያ ተምረው ወደ ሀገራቸው አምጥተው በሰፊው እንዲሰመድ አድርገው ነበር።

የመዳብ ማእድንን ማቅለጥና መዳቡ ላይ መጻፍ ደቡብ ዓረቦች ከክርስቶስ ልደት በፊት ተምረው ልዩ ችሎታ ነበራቸው። ከጋዛ ተምረው ባለብርና ባለወርቅ የአቴንና የሮግውያን ገንዘቦች በ4ኛ መቶ ክፍለዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት ይሰሩ ነበር። የቤተመቅደስ ፓንቴዮን የመሰራት ችሎታ ነበራቸው። የዚሁ ሁሉ እውቀታቸው በኢትዮጵያ የታየ ነገር የለም። በኢትዮጵያ የሚገኙ የጥንት የሰው ስራዎች ጥቂቶች እንኳን የደቡብ ዓረብ ናቸው የሚባሉ የሉም።

ሰለዚህ ደቡብ ዓረቦች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ከሕዝቡ ጋራ ተዳቅለው አዲስ ሕዝብ ሴም ቋንቋ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን ፈጠሩ ማለት የፈጠራ ታሪክ ነው። ሀገራችን ከጣሊያን በስተቀር በማንም ሕዝብ ተገዝታ አታውቅም አያልን፣ እነስተኛ የሕዝብ ብዛት እንደወረዳ የቆዳ ስፋት ያላቸው ሳባውያን ገዙን፣ ፈጠሩን ብለን መናገር የማይመስል ከመሆኑም በላይ አሳፋሪም ነው። ደቡብ ዓረቦች በብዛት ስፈሩባቸው ተብለው የተገመቱ ቦታዎች ከአክሱም ወደ ሰሜን ምሥራቅ ያሉት ጥቅጥቅ ያሉት ታሪካዊ ቦታዎች ናቸው፣ እነዚህ ቦታዎች የሚገኙ ሕዝቦችም ቢሆኑ የዓረብ ድብልቅ ዘር የለባቸውም። የተለዩ ሕዝቦች መስለው አይታዩም። ከፍተኛ ስልጣኔ ዳብሮባቸው የነበረ ንዑሕ ኢትዮጵያውያን ዘሮች መሆናቸው ብቻ የሚታዩ በቆሐይቶ አካባቢ /አክለገዛይ/ ተቁፍሮ የተገኙ አስከሬኖች ጠንራቸው ጥቁ መሳያ እንደ ጥቁሮች /ኔግሮዎች/ ሳይሆን፣ ወይንም ሱዳ እንደ ዓረቦች ባይሆን እንደ አሁኖቹ ኢትዮጵያውያን በመጡ ከረዳዳ የሆነ ወጥር እንደ ነበራቸው ተረጋግጠዋል። (1) የጭንቅላታቸው አጥንትም የኢትዮጵያውያን እንደሆኑ ተረጋግጠዋል፣ ይሽም ደቡብ ዓረቦች በሰሜን ኢትዮጵያ እንዳልሰፈሩ የሚያስረዳ ተጨማሪ ማስረጃ ሊሆን የሚችል ነው። ቆሐይቶ እንደ ደቡብ ዓረብ ተመሣሣይ ውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳዎች ቅሪቶች ያለባት መንደር ናት። በአዱሊስ ይኖሩ የነበሩ ደቡብ ዓረቦች ከቀይ ባሕር ሐሩር ወጣ ብለው ብርዳማ አየር የሚያገኙበት የመዝናኛ ቦታ ነበረች የተባለች መንደር ናት። በዚሁ መንደር የዓረቦች ሬሳ ምልክት ካልተገኘ የትም ቦታ ሊገኝ አይችልም። ቆሐይቶ እንደ መንደር የሚቆጠር እየደለም። ከአክሱም በፊት የአክሱማውያን ዋና ከተማ የነበረ ሊሆን የሚችል ነው። ይህ ባያሆንም ከቆሐይቶ እስክ አክሱም ያሉት ታሪካዊ ቦታዎች ፍርስራሾች እንደ ትዙንዳሰ፣ ከስክለ፣ ሰንዓፈ ወዘተ... የሚያጠቃልል ከፍተኛ ታሪካዊ የሐውልቶች ፍርስራሾች የሚገኙባቸው ራሳቸው የቻሉ እንደ ግሪክ መንግሥታዊ ከተሞች የሚቆጠሩ ሊሆኑ ይችላሉ ለማለት የሚያስኝ ነው፣ ሰምርምር ብዛ ቁፋሮዎች

(1) Carlo Conti - Rossini Storia d' Etiopia p. 237

አልተደረገም። ከዚህ ቀደም የተደረጉ ቁፋሮዎች ያተኮሩት በአክሱም አካባቢ ብቻ ነው። ፕሪኖሉ የቀይ ባሕር ዙሪያ ጉዞ የሚል መጽሐፍ የደረሰው ሰው አክሱማውያንን የሚገዛ ሦስካለስ የተባለ ዘጣም ሰስታም የሆነ ገንዘብ ማጠራቀም ብቻ የሚወድ በለላ በኩል ግን ጉበዝና የግሪክ ቋንቋ በሚገባ የሚያውቅ(1) ንጉሥ ነበረ ብሎ ጽፏል። ሦስካለስ ይኖር የነበረ በ2ኛው መቶ ክፍለ ዘመን 2ኛው አጋማሽ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ስለሆነ ኢትዮጵያውያን የሳባ ቋንቋና ፊደል ከማወቃቸው በፊት የግሪክ ቋንቋ ያወቁ እንደነበረ የሚጠቁም ነው።

የኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪክ ለማወቅ በቂ የአርኪዮሎጂ ቁፋሮ ባይደረግም ከመሬት በላይ የሚታዩ ታሪካችን አሻራዎች በተለይ በሰሜን ኢትዮጵያ ከክሰላ እስከ ሐይቅ (ወሰ) በብዛት ይገኛሉ። ከጎቲ ሮሲኒ ምንም እንኳን እነዚህ የታሪካችን ምልክቶች በውሂ ሀገር ሰዎች የተሰሩ ናቸው የሚል አስተያየት ቢኖረውም፣ እንደዚሁም የኢትዮጵያ የጥንት ስልጣኔ የአናሳ ሴማውያን ሥልጣኔ ነው የሚል አስተያየት ቢኖረውም፣ ሐውልቶቹን ከመረመረ በኋላ ኢትዮጵያ በዓሰም ከሚገኙ ጥንታዊ ስልጣኔዎች ካላቸው ሀገሮች መካከል በእኩል ደረጃ እንደትሰለፍ የሚያስችሏት መሆናቸው ጽፏል(2) ።

በአክሱም ከሚገኙ ቁጥራቸው አንድ መቶ የሚደርሱ አቤሊስኮች አንዱ ብቁመት በመላው ዓለም ከሚገኙ ተመሳሳይ ሐውልቶች እንደኝነት ያሰው ነው። ላሊበላ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በዓይነታቸው በዓለም ተወዳዳሪ የሌላቸው ናቸው ተብለው ተደንቀዋል።

8. የኢትዮጵያ የጨለማ ዘመን

ስለታወቀው የምሰራባውያን ሀገሮች የጨለማ ዘመን (Middle Age) ተብሎ የሚጠራ ታሪካቸው በዚህ መጻሐፍ መግቢያ ላይ አስተያየቴን ሰጥቻለሁ፣ የሀገራችን ታሪክ ጸሐፊዎች የምዕራባውያን ተመሳሳይ የሆነ የታሪክ ክፍል የጨለማ ዘመን አለ ብለው ጽፈዋል። የሀገራችንና የምራባውያን ሀገሮች ታሪክ የተለየ ቢሆንም እንደ አጋማሚ የጨለማ ዘመን ተብሎ የሚጠራ በሁሉቱ ሀገሮች የክርስትና ሃይማኖት ከገባበት ዘመን ጀምሮ ነው። አቶ ተክለጻዲቅ መኩሪያ የጨለማ ዘመን ብሎ የሚጠራው ከናግራን፣ በአጼ ካሌብ ዘመን፣ በ525 ዙሪደረገው ጦርነት አስክ ዩዲት መነሳት 942 ዓ.ም. 317 ዓመት ያለው ጊዜ ነው። የተባለበትን ምክንያት ሲያብራራ የአክሱም ነገሥታት የሰሩትን ሥራ በታሪክ የተመዘገበ ስላማይገኝ ነው። በኢውሮጳውያን የጨለማ ዘመን ትርጉሙ አንድ ሀገር ከነበረው ከፍተኛ ስልጣኔ ወደ ኋላ የተመለሰበት ዘመን ነው።

ሀገራችን በእነ ንጉሥ ኢዛና እና አጼ ካሌብ ከነበረው ባለ መልክም ዝና ታሪኳና ስልጣኔዋ ወደ ኋላ መመለስ የጀመረችበት ጊዜ ከአጼ ካሌብ ጀምሮ መሰሉ አይታየኝም። የሀገራችን ታሪክ ከምዕራባውያን ሀገሮች በማመሳሰል ብንፈልግ እንኳን የጨለማ ዘመን ተብሎ መጠራት የሚገባው ከአጼ ካሌብ ከናግራን ጦርነት ጀምሮ መሆን የለበትም። የታሪክ ማስረጃ ዘመኖቱም ታሪክ አልተሰራም ለማለት አይቻልም። ከንጉሥ ኢዛና በፊት ወደ ሰሜንና ደቡብ ዓረብ የተደረጉ የአክሱም ዘመቻዎች ማስረጃዎች የተገኘ

(1) Carlo Conti - Rossini Storia d' Etiopia p. 119
(2) C. Conti - Rossini ibd p. 239

በአጋጣሚ ከሀገራችን ወጪ ነበር። ለኢትዮጵያ የጨለማ ዘመን እስ ቢባልም መጀመር ያለበት ከእስልምና ሃይማኖት መከሰትና መስፋፋት በኋላ በተለይም ግብፅ በዓረብ አስላሞች ስር ከወደቀችበት ዘመን ከ 642 ዓ.ም. ጀምሮ መሆን ይገባዋል። ከዚሁ ዓ.ም ጀምሮ ግብጽና ኢትዮጵያ የክርስትና የጋራ እምነታቸውና ግንኙነታቸው ባይቋረጥም አደጋ ላይ የወደቀበት ዘመን ኮፕቲክ የአንድ የክርስቶስ ባሕርይ የክርስትና እምነት ተከታዮች ነበሩ። ኢትዮጵያ ግንኙነቷ የተቋረጠው ከግብጽ ጋራ ብቻ አልነበረም። ከአለጠኑ ምዕራባውያን የክርስትና እምነት ተከታይ ሀገሮች ሁሉ ጭምር ነበረ። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ የክርስትና እምነቷን እና ሕልውናዋን ለመጠበቅ ሰብዙ ዘመናት የትጥቅ ትግል የጀመረችበት ዘመን ነበር።

ስለዚህ ይህ ዓመተ ምህረት ለኢትዮጵያ የጨለማ ዘመን የጀመረችበት ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ኮንቲ ሮሲኒ የሀገራችን ታሪክ የጨለማ ዘመን 500 ዓመት ያደርስዋል፣ ከ7ኛ መቶ ከፍለ ዘመን[1] ስለሞናዊ ነገሥታት በስልጣን አስከ ተመለሱባት ጊዜ 1268 ዓ.ም. ድረስ /ሀ/ በዚሁ ጊዜ የሀገራችን ታሪክ የምናገኛቸው ከተለያዩ የውጭ ሀገር ጸሐፊዎች ነው። የጨለማ ዘመን ከመግባቱ በፊት በ525 አንደ ግዕዛዊ ግብፃዊ ዜጋ የሆነው ኮዝማስ ኢትዮጵያን ጎብኝቶ ስፊ ታሪካዊ ዘገባዎች ተንትነዋል። ወደ ሕንድ ሀገር በምሄድበት ጊዜ ባርባሪያ /ሶማልያ/ በጎበኘበት ጊዜ ከሶማልያ ጉን የነበረውን የዘንግ መንግሥት ለመጎብኘት ፈልጎ ነበር። ነገር ግን ባሕር-ተኞች ስላስፈራሩት ፍላጎቱም አልተሳካለትም። ከሕንድ ሀገር ሲመለስ አዱሊስ እና አክሱምን ጎብኝቶ ዘመፌት እስከ አባይ በመሄድ ግብፅ ሀገር ገብቷል። ኮዝማ እንደጻፈው አዱሊስ የንግድ መናኸሪያ፣ ግሪኮችና ሮማውያን ነጋዴዎች የሚያዛውትሩባት ናት በማለት ጽፏል። በንግድም የምትገናኘው ከየመን ብቻ አይደለም፣ ከፕሮሲያ፣ ከሕንድ እና ከስይሎን ጋራም ትገኛለች። አክሱም ከብሉሚዮች ጋራ በወዳጅነት የተመሰረተ ግንኙነት አላት ከባርባሪያን ጋር በመሬትም በባሕርም ትገናኛለች። አዱሊስና አክሱም ሐውልቶችና ቤተክርስቲያኖች አሏቸው። ኮዝማስ አጼ ካሌብ የመንን ለመውረር ዝግጅት በሚያደርግበት ጊዜ ተመልክቷል። ከንቲ ሮሲኒ ከአጼ ካሌብ የየመን ዘመቻ በኋላም ዚሆን ኢትዮጵያ በ6ኛና 7ኛ መቶ ከፍለ ዘመን ስልጣኔዋን እና የክርስትና ሃይማኖትን ወደ ደቡብ አስፋፍታ እንደ ነበረ የሚያመለክት ስሜን ሰማሊያ፣ የስኮትራ ደሊትም ጭምር ክርስቲያን ሆነው እንደነበሩ ብሎ ጽፏል። /ለ/ 6ኛው መቶ ከፍለ ዘመን ኢትዮጵያ ግንኙነቷ ከደቡብ ዓረብ ጋራ ሊሆን 7ኛ መቶ ከፍለ ዘመን ግን በእስልምና ሃይማኖት መመዕረት ምክንያት ግንኙነቷ ከሰሜን ዓረብ ሆኗል። የሀገራችን ታሪክ በዚሁ ዘመን እና በሚቀጥሉት ዘመናት ለማወቅ የምንችለው ከዓረቦች ጸሐፎች ምንጮች በምናገኛቸው ማስረጃዎች ብቻ ነው። በዚሁ ጊዜ የዓረቦች አስተያየት ኢትዮጵያ ሰላም የሰፈነበት ሀገር፣ ስደተኞች ዓረቦችን የምትቀበል ተብላ ትታወቅ ነበር። ታማኝ የነቢዩ መሐመድ ባርያዎች ኢትዮጵያውን ነበሩ። ነቢዩ መሐመድ በዓለም ከነበሩት 6 ታላላቅ ነገሥታት የእስልምና ሃይማኖት እንዲቀበሉ ደብዳቤ ከላከላቸው ነገሥታት አንዱ የኢትዮጵያ ንጉሥ ነበረ። ነቢዩ መሐመድ ከኢትዮጵያ ነገሥታት ጋራ የወዳጅነት ግንኙነት ነበረው። "ካልነካችሁ ከኢትዮጵያውያን ጋራ ነገር አትጫሩ፣ 9/10 የሰው ዘር ድኖረተና ጀግንነት ለጥቂቶች ነው የተሰጠው"

[1] Conti - Rossini ibd p. 323

በማለት ነብዩ መሐመድ ለቅርብ ረዳቶቹ የተናገረው ቃል ስለኢትዮጵያውያን የነበረው አመለካከት የሚያንፀባርቅ ነው።

/ሐ/. በ872 ዓ.ም. አል ላኩቢ (Ahmed Ibn Wadhih Al- La - Kubil[1] የተባለው የዓረብ ታሪክ ጽሐፊ ዓለምአቀፍ ታሪክ በሚለው መጸሐፍ ስለ ኢትዮጵያ ሲጽፍ ከናይል ወንዝ እስከ ቀይ ባሕር ብዙ ነገሥታት እንዳሉ ይዘረዝራል 1ኛ. የናኪስ ዘር የተባሉ ጎሳዎች ከአስዋን እስከ ባርካ የሚደርስ፣ ዋና ከተማው ሐጂያር 2ኛ ባክሊን ይባላል 3ኛ. በአዘን 4ኛ ጀረን 5ኛ. ከታአላ 6ኛ. የናጃሺ መንግሥት ስፊና ኃይለኛ ነው፣ ዋና ከተማው ካባር ነው። በማዛቱ ውስጥ ብዙ ከተሞች አሉት፣ ዓረቦች ለንግድ ይሄዳሉ፣ የባሕር ዳርቻው ዳህላክ ነው። በኢትዮጵያ የሚገኙ ብዙ ነገሥታት በአንድ ንጉሥ ይታዘዛሉ፣ ግብርም ይከፍላሉ፣ ሃይማኖታቸውም ክርስትና ነው፣ የመጨረሻ በስተደቡብ የኢትዮጵያ ንጉሥ ከሲንድ የሚዋሰን የዘንግ ንጉሥ ከደቡብ ለማልያ በስተደቡብ ይገኛል። የዓረብ ሀገሮች ከኢትዮጵያ ጋራ ያላቸው ብዙ ነው፣ ምክንያቱም ኢትዮጵያ ለመስሊሞች የጦርነት ቀጠና አይደለችም ብለዋል።

/መ/. ማሱዲ (Masudi)[2] የተባለው የታወቀው የዓረብ ታሪክ ጸሐፊም እስከ ማዳጋስካር ድረስ ብዙ ጉብኝት አድርጉ ራሱ በቀጥታ ስላየው ነው የሚጽፈው። በመጨረሻ ጊዜ በ916/7 ጉብኝት ስላደረገበት ስለ ኢትዮጵያ በሚያደርገው ዘገባ፣ ኢትዮጵያ የበለጸገች ሀገር ናት ብሎ ጽፏል። ዋና ከተማዋ ጋባር ናት፣ ሌሎች ብዙ ከተሞችም አሉ፣ ግዛቷ እስከ ሐበሻ ባሕር ይዘልቃል። በዚሁ ባሕርም ዘይላ ዳሕላክና ባጼ /ምዕዋ/ የተባሉ ወደቦች አሏት። በኢትዮጵያ የሚኖሩ ዓረቦች በሰላም ግብር እየከፈሉ መኖር ይችላሉ። ኢትዮጵያ በብልጽግና ዘመን እንደነበረች የሚያስረዳ በንጉሡና በየመን መሪ ኢብራሒም ቤን ዚያድ በ901-2 የተደረገው የወዳጅነት ውል መሠረት የንግድ መርከቦች ብዙ ሸቀጦች ይዘው በ3 ቀን ውስጥ በሁለቱ ሀገሮች ለንግድ ያመላልሱ ነበረ እያለ ጽፈዋል።

/ሰ/. አማር የመናዊ የተባለው ሌላ የዓረብ ታሪክ ጸሐፊ በአባቱ በኢብራሂም ተተክቶ በ981-2 ዓ.ም. የየመን መሪ የነበረው አቡ አል (Abu Al) ጂያይስ ኢሳክ Jiais Jshak የተባለው ለ80 ዓመት በስልጣን የቆየው ከኢትዮጵያ ጋራ ግንኙነት እንደነበረው እና ስመታ በማበርከትም ወዳጅነትን ይፈልግ እንደነበረ ጽፏል።

/ረ/. 977/8 ዓ.ም. የጅግራፊ ምሑር የነበረው አቡ አልከሲም Abu - Alkasim ኢብን ሀውካ የተባለው የዓረብ ተወላጅ ስለዘይላ የኢትዮጵያ ክርስቲያን ከፍለ ግዛትና በውስጡም ባሕር ዳርቻ ከየመን ፊት ለፊት የሚኖሩ በንግድ ከየመን ጋራ መልካም ግንኙነት ያላቸው ናቸው ካለ በኋላ የኢትዮጵያ መሬት ለሙስሊሞች የጦርነት ቀጠና አይደለም ብሏል።

/ሠ/. በ951 -2 ሌላ ዓረባዊ የጅግራፊ ምሑር አል አስታክሀሪ Al - Istakhri የተባለው ተመሳሳይ ሀሳብ ገልጧል። በተደጋጋሚ ዘይላ ኢትዮጵያዊነትና ክርስቲያን መሆኗ መጠቀሱ የኢትዮጵያ መንግሥት ወደ ደቡብ መስፋፋቱን

[1] C. Conti - Rossini ibd p. 274
[2] C. Conti - Rossini ibd p. 281

ያመለክታል። የዚሁ መሰፋፋት ከሚታዩ ብዙ ታሪካዊ ማስረጃዎ እንደምሳሌ የሚከተሉት መጥቀስ ይቻላል። ኢትዮጵያ ወደ ደቡብ ማስፋፋት ማተኮሩዋ ከሚያመለክቱ ምሳሌዎች አንዱ በ1154 ዓ.ም. ኤድሪሰ የተባለው የሲሲሊ ንጉሥ የጆግራፊ ምሑር ስለዓለም አቀፍ የጂኦግራፊ በደረሰው መጽሐፍ፣ ስለ ኢትዮጵያ አንስቶ ሲጽፍ የኢትዮጵያ የባሕር ወደቦች ምጽዋ ምንም ሳይጠቅስ ስለ ዘይላ፣ በርበራ፣ መርካ ሌሎችም የደቡብና የሶሜን ሶማሊ ጠቅሶ ጽፏል። ወደ ሰሜንም ታጁራ ዳህላክ እና ሰዋኪም የኢትዮጵያ ወደቦች ናቸው ብሎ ጽፏል። ሌሎች እንደ ኢብን ሰኢድና አልዲማስኪ የተባሉ የዘመኑ የጂኦግራፊ ምሁራን ዓረቦችም ስለ ዘይላ፣ በርበራ፣ ምቃዲሾ፣ መርካ፣ የኢትዮጵያ ወደቦች መሆናቸውን ጽፏል።
/ቀ/. [1] የግብፅ ፓትሪያርኮች ታሪክ በ921-933 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ እዙን ጴጥሮስ ቡትላኩበት ዘመን ስለ ኢትዮጵያ ግዛት ሰፋታ ሲጽፍ ኢትዮጵያ በጣም ሰፈ ዘመሆኗ የተነሳ ንጉሡ ጉብኝት ለማድረግ ሲፈልግ ወገሩን ጉብኝት ለመጨረስ 1 ዓመት ይወሰድበት ነበር ብሏል። በላሲበላ ዘመን ጊዜ 1210 ዓ.ም. የኢትዮጵያ መልክተኞች ካይሮ መጥተው ስለነበረ ስለ ኢትዮጵያ ለማወቅ ፍላጐት ከነበራቸው ብዙ ሰዎች አንዱ አቡ ባሌሕ ሻዲድ ኢብን ባና የተባለው የአርመን ተወላጅ በደረሰው መጽሐፍ የኢትዮጵያ ንጉሥ ከዳዊት ዘር አይወለድም፣ ሙሴ ወደ ኢትዮጵያ ሄዶ በነበረበት ጊዜ ከንጉሡ ሴት ልጅ ጋራ በተደረገው ጋብቻ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘር የሚሆነው ሊወለድ ችሏል ካለ በኋላ፣ ንጉሡ በጣም ኃይለኛ ነው ከሰሩ ያሉት ነገሥታት ግዛት ጉብኝት ለማድረግ አንድ ዓመት ይፈጅበታል ብሎ ጽፏል።

9. ታሪካዊ ቦታዎች በደቡብ ኢትዮጵያ

በሰሜን ብቻ ሳይሆን በሌሎች የሀገራችን ክፍሎችም የጥንት ታሪክን ምልክቶች ፍርስራሾች ይገኛሉ። በአዲስ አበባ ፋንፋኔ ጠበለ አጠገብ የአክሱም ስልጣኔ ማስፋፋት የሚያመለክት የአንድ ቤተክርስቲያን ፍርስራሽ ይገኝ ነበረ። እንደዚሁም ከአዲስ አበባ በስተምዕራብ ጀባልቲ በተባለው ተራራ የአንዲት የአክሱማዊት የክተማ ፍርስራሽ ይገኛል።

ይህ ሁሉ የሚያመለክተው የአክሱም ወደ ደቡብ ማስፋፋት በተያያዘ ሁኔታ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ማእከል እንድትሆን የተመረጠችው በአጼ ምኒልክና በእቴጌ ጣይቱ ዘመን መሆኑ ቀርቶ በአክሱም ዘመን ምንግሥት መሆኑ ነው። አጼ ምኒልክም አዲስ አበባ ዋና ኩተማ እንድትሆን የመረጠበት ምክንያት በኢትዮጵያ ሌሎች የፍል ውሀ ጠበል ቦታዎች ጠፍተው ሳይሆን ቀደምት አባቶቹ የኢትዮጵያ ነገሥታት ፈለግ በመከተልና በግእከልነት ተመርጦ የነበረው ቦታ ዘመቀበል ነው። ከአክሱም አጉላ አሸንጌ የሚወሰደው ጥንታዊ መንገድ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ሥልጣኔም ከአክሱም ወደ አሸንጌና ፈንፈን መሰፋፋቱ ያሳያል። በዚሁ መሠረት ከአሸንጌ ሐይቅ አጠገብ በአጼ ቴዎድሮስ ላይ የዘመተው የእንግሊዝ ጦር ላባል የሆነው አንድ ወታደር የሰባተኛ መቶ ክፍለ ዘመን የአክሱም ገንዘብ አግኝቷል። በዚሁ አካባቢ በአክሱም ጊዜ ሕዝብ ሰፍረውበት የነበሩ ምልክቶች በስተምዕራብ የአሸንጌ ሐይቅ ተገኝቷል። በዝዋይ ሐይቅ ትራቪርሲ፣ ሚሊዮስና ዲካስትሮ የተባሉ ጣሊያኖች በአጼ ምኒሊክ ጊዜ በኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩ የአክሱም መሰል

[1] C. Conti - Rossini Storia d'Etiopia p 289

ሐውልቶች፣ አቤሊስኮችና መስቀሎች በብዙ ቦታዎች አግኝተናል ብሏል። ኪያሪኒ የተባለው ኢጣሊያዊ ሀገር ጐብኚ ከአንኮበር በስተምስራቅ የግሪክ የድንጋይ አሰራር የሚመስል በአንድ ሕንጻ ቤተሰይም በበሩ ደጃፍ አግኝተዋል። በአጉላ በምስራቅ ትግራይ ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚውሉ የቤተ ፍርስራሾች ተገኝተዋል። ሀገራችንን የጐበኘ ቼኪ የተባለው ሴላም ኢጣሊያዊ በሸዋ ከአንኮበር በስተምስራቅ 6.35 ሜትር ርዝመት ያለውና ሴላው ደብረ ብርሀን አጠገብ አቤሊስክ አግኝቷል። ዳባዲ ታዋቂው የፈረንሳይ ሀገር ጐብኚ ከአባይ በስተደቡብ በሲበን ሁለት ሜትር ርዝመት ያለው አቤሊስክ አግኝቶ ነበር፣ ነገር ግን ደጃዝማች ጐሹ ወልዴ ለአሮሞዎች የጣኦት እምልኮት ነው ብሎ ሰባብሮታል።

ሀረሪ /አደሬ/ በሀረር ኩተማ የተወሰነ ቋንቋ አንዲሁም የጉራጌ ቋንቋ በመሀል አገር በሰፊው የተሰራጨ ከትግሪኛና ከአማርኛ ቋንቋዎች ጋራ የሚዛመዱ የሴም ቋንቋ ተብለው ሊመደቡ የተለመደ ነው። በነዚህ ሁለቱ ለአካባቢዎች የአክሱም ስልጣኔ ምልክቶች ተገኝተዋል።[1] በትግራይና የሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኙ የሰልጣኔ ምልክቶች ከጥንት ግብፃውያን ወይንም ደቡብ ዓረብ ጠበብቶች የተሰሩ ናቸው እንደሚባለው ሁሉ፣ በሲላ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር የሚገኙ የሰልጣኔ ቅሪቶች በደፈናው ከአክሱም የመጡ ናቸው ይባላሉ። አልፎ አልፎ በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ አቤሊስቶች የቢተክርስቲያን ህንፃ ፍርስራሾች የአክሱም ሥልጣኔ መስፋፋት ጊዜ የተሰሩ ሲሆኑ ሌሎች እንደ መቃብሮች የመሳሰሉት ግን ከቀደምት ነዋሪ ሕዝብ የተሰሩ ለጥንት ግብፃውያን የሥልጣኔ ምልክት የሆኑት ፒራሚዶች እንዲዳብሩ መሠረት የጣሉ ሊሆኑ ይችላሉ።

በጉራጌ ሙጄር ሶዶ አካባቢ ጢአ፣ ሰምቦ፣ ሰደን ወዙተ የተባሉ ቦታዎች ሁለት ክሰማንያ ሜትር ያላነሰ ቁመት ያላቸው በግዙፍ የድንጋይ ከምችት ከፍታ ያላቸው በጎሹ ቦታዎች የተሰሩ በተለይ በሰደን 150 የሚሆኑ ባለአራት ማእዘን መቃብሮች ተገኝተዋል። በመቃብሮቹ የተካሄደው ምርምር አጥጋቢ ውጤት ያላሰገኘበት ምክንያት ሬሳዎቹን የሚሸፍነው ድንጋይ የአሲድ ጠባይ ስላለው አጥንቶች አመድ ሆነው ሰለተገኙ ነው። አንዳንድ ጊዜም በመቃብሮቹ ላይ ስእል ተገኝቷል። እንደዚሁም የግብፃውያን መሰል ጉራጂና ቢላ ተገኝተዋል። አንዳንድ ጊዜም በመቃብሩ ላይ ሐውልት የሚመሰል ወይንም በአክሱም የኢዛና ጽሑፍ ያሉባቸው ድንጋዮች የሚያስቃሙ ናቸው።

እነዚህ ሁሉ ሰራዎች በአክሱማውያን የተሰሩ መሆናቸውን አያጠራጥርም። በምስራቅ ኢትዮጵያ ከሐረር 50 ኪሎ ሜትር በስተምስራቅ አባ አዘይስ የተባሉ ፈረንሳዊ ካቶሊክ ላዛሪስት ሚስዮናዊ "ደልመን" ብሎ የጠራቸው መቃብሮች አግኝተዋል። ደልመን በብዙ የዓለም ክፍሎች ተገኝተዋል፣ በግብፅ ግን አልተገኘም። በምሥራቅ ኢትዮጵያ በሐረርጌ የተገኙ መቃብሮች በኮንቲ ሮሲኒ አስተያየት ደልመን ሳይሆኑ በሰሜን ኢትዮጵያ ከሚገኙ መቃብሮች ተመሳሳይ ናቸው። በሰሜን ኢትዮጵያ ከሚገኙ መቃብሮች ዋናውና ትልቁ በአክሱም ኩተማ ንፋስ መውጫ በሚባለው ቦታ የሚገኘው መቃብር ነው። የሐረር ጉራጌ ቋንቋዎች የተፈጠሩት ከጥንታዊ ኢትዮጵያዊ ቋንቋ ከግዕዝ በቀጥታ ወይንም ከግዕዝ በፊት የነበረው የኢትዮጵያ ቋንቋ ሲሆን ይችላል፣ ከትግሪኛ ጋራ ብዙ ይዛመዳሉ። መቃብሮቹ የተሰሩበት ዘመን ለማወቅ ጨርሶ አይቻልም። የሐረር እና የጉራጌ አካባቢ

[1] Conti -Rossini ibd p . 282-3

የአክሱም ስልጣኔ ሳይጠፋ ለረጅም ጊዜ መቆየቱ ነው እንጂ በመላው ኢትዮጵያ ከምዕራብ ከፋ እስከ ምስራቅ ከሰሜን እስከ ደቡብ ኦሞ የአክሱም ስልጣኔ ምልክት የሌለበት አካባቢ አይገኝም። በዓረብ ሀገር የፖለቲካና የወታደራዊ ሽንፈት ካጋጠማት በኋላ በአፍሪካ ብቻ ተወስና፣ እንቅፋት ባያጋጥማት ስልጣኔዋና ቋንቋዋን በማስፋፋት ኢትዮጵያ ባለ እንደ ቋንቋ ሀገር ልትሆን ትችል ነበር። ይህ ባይቻልም አሁን የሚታዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በሙሉ እንደ ሀረሪና ጉራጌ የግዕዝ ቋንቋ ድብልቅ መሆናቸው አይተርም ነበር።

ስለዚህ አሁን ትግሪኛ አማርኛ እደሪኛ ጉራጊኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን የሴም ቋንቋ ተናጋሪ ተብለው እንደሚመደቡ ሁሉ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሴም ቋንቋ ተናጋሪ ይባል ነበር። ነገር ግን የአክሱም መንግሥት ወደ ደቡብና ምዕራብ ያደረገው ማስፋፋት ከባድ እንቅፋት ስላጋጠመው ብዙ ሳይቆይ በ10ኛ ክፍለ መቶ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ ግቷረዋ የተገደደበት በዩዲት ጊዜ ነበረ። ኢትዮጵያ ዘዩዲት እርስ በእርስ ጦርነት ዘመን ጀምሮ ከምስራቅ ሰሜን ሶዳን እስከ ደቡባዊ ሶማሊያና ሶኮትራ ደሴት ድረስ የነበረ ሞዛ የደቡብ ክፍላተ አገሮች ሥምር ከቁጥጥሯ ውጭ ሊሆኑ ችለዋል። የአስተዳደር መዋቅርም በጦርነት ስለ ወደመ ይህ የዩዲት ዘመን የጨለማ ዘመን ተብሎ ሊጠራ ይችላል። የዛሞዊ ዘመነ መንግሥትም የግዛት አንድነት ለማስከበር ትኩረት ስላልሰጠ በዚሁ ረገድ ከጨለማ ዘመን ውስጥ ሊጠቃለል ይችላል። ሰሎሞናዊ ንጉሣዊ አገዛዝ ከተመሰረተ በኋላ ግን ኢትዮጵያ ከግዛቷ ተንጥለው የነበሩ የምሥራቅ እና የደቡብ ክፍላተሀገር፣ ከስሚንም፣ ለማስመለስ የጣረችበት ዘመን ስለነበረ የጨለማ ዘመን አብቅቷል ለማለት ይቻል ይሆናል። ጥረቱ ሙሉ በሙሉ የተሳካ ሊሆን ያልቻለበት ምክንያት በምሥራቅ የአፋርና የሶማሌ ግዛት የእስልምና ሃይማኖት በመቀበላቸው እንደገና ለግዛሀድ ቀላል ሆኖ ሰላልተገኘ ነው።

በመሐመድ ግራኝ እና በአሮሞዎች እርስ በእርስ ጦርነት ጊዜ የሥልጣኑዋ ቅርሶች በባሰ ሁኔታ ስስወደመባት አለከፈ የሆነው እንደገና በጨለማ ዘመን ወድቃለች ለማለት ይቻላል። ስለዚህ ይህ ዘመን የኢትዮጵያ የጨለማ ዘመን ተብሎ ሊጠራ ይገባዋል። የቀሩት ዘመናት ግን እላይ የጠቀስኳቸው የታሪክ ማስረጃዎች እንደሚያስረዱ የጨለማ ዘመን ተብለው ሊጠሩ አይገባም።

8. <u>የዮዲት ዘመን</u>

ዮዲት የምትባለው ንግሥት በኢትዮጵያ ታሪክ መክሰቱ በሁሉም የግይካድ ቢሆንም ዝርዝር ታሪኳ እና ማንነቷ በሚመስክት ግን በትክክል አይታወቅም። ዩዲት የነገሠች በ921-933 ዓ.ም. የአክሽንድራያ ጳጳስ ከነበሩት አቡነ ኮዝማ ለኢትዮጵያ ጳጳስ ሆነው የተላኩ በየዋሁ አቡነ ጴጥሮስ ላይ ኢትዮጵያ የፈጸመችው ግፍ እግዚአብሔር የላከባት የቅጣት መቅሰፍት ነው ተብሏል። እንደ ሀገራችን ታሪክ ጸሐፊዎች አቀራረብ ዮዲት አይሁዳዊት ናት የአሪት ሕግ በመደገፍ የክርስትና ሐይማኖት አንቀበልም ያሉት በስሚንና፣ በወገራ፣ ወልቃይት፣ በላስታ የነበሩት ፈላሾች አሰባስባ ወደ ትግራይ ዘመታ ሐውልቶቹንና አብያተክርስቲያናትን አቃጥላ ሕዝበ ክርስቲያንን ፈጅታ በደብረ ዳሞ ተራራ ይኖሩ የነበሩትን ክነገሥታት የሚወለዱትን መሣፍንት አሳርዳ የነገሠች ናት ብሏታል። የእስክንዲሪያ ፓትያራኮች ታሪክ ላይ ዮዲት የባኒ አል ግግያህ ንግሥት ብሎ ይጠሯታል። በኢትዮጵያ ግን በዚሁ ስም

የሚጠራ ክፍለ ሀገር የለም[1] ከአጼ ካሌብ ጀምሮ እስክ ዮዲት ዘመን 300 ዓመት በኢትዮጵያ ታሪክ የጨለማ ዘመን ተብሎ የሚጠራ ብዙ የታሪክ ማስረጃዎች የማይገኙበት ዘመን ስለነበረ ነው። ሆኖም ይህ ዘመን ምናልባት ኢትዮጵያ ስልጣኔዋን ያስፋፋችበት ጊዜ ስለነበረ ወርቃማ የብልጽግና ዘመን ነበር።[2]

በ979 - 1003 ዓ.ም. በእስክዲሪያ መንበረ ፓትሪያርክ የነበሩ አቡነ ፈስተዩስ Fileteus[3] በነበሩበት ጊዜ ኢትዮጵያ ክአቡነ ጴጥሮስ ጀምሮ ሕጋዊ አቡን ስላልነበራት ለይፈ አረድ የተባለ የኢትዮጵያ ንጉሥ ጊዮርጊስ ለተባለው የኑቢያ ንጉሥ የእስክንድሪያ ሊቀ ጳጳስ ለኢትዮጵያ ጳጳስ ይልኩ ዘንድ እንዲያግልደው ደብዳቤ ጽፎ ነበር። የኑቢያ ንጉሥ የግብፁ ፓትሪያርክ ወደ ኢትዮጵያ ጳጳስ እንዲልኩ ባቀረበው ልመና መሠረት አቡነ ዳንኤል ሊላኩ ኢትዮጵያውያን በታላቅ ደስታ ተቀብሉዋቸዋል። የኢትዮጵያ ንጉሥ ለኑቢያ ንጉሥ በግእዝ ቋንቋ የፃፈው ደብዳቤና የወቅቱ የኢትዮጵያውያን የታሪክ ፀሃፊዎች ያቀረቡት ዘገባ የሚጠቁመን ነገር ኢትዮጵያ በዚያን ዘመን በታሪኳ በወሳኝ ምዕራፍ ትገኝ እንደነበረ ነው።

ምንም እንኳን ኢትዮጵያውያን የታሪክ ጸሐፊዎችና የግብፅ ፓትሪያርኮች ታሪክ መዛግብቶች በዓመተ ምህረትና በእንዳንድ ዝርዝር ሁኔታዎች ቢለያዩም በመሠረቱ ታሪኩ በማይለያዩበት ሁኔታ ገልፀውታል። ክርስቲያን የኢትዮጵያ መንግሥት ሊጠፋ ትንሽ ነበር የቀረው። ክርስቲያን ሕዝብም ባሪያ ሆኖ ክመሸጥ ያመለጠ ሸሽቶ ወደ ሌላ ክፍላተ ሀገር ይሰደድ ነበር። ንጉሡም ወደ ሸዋ በመሸሽ የሞት ሽረት ፍልሚያ በማድረግ ወሳኝ ሚና ተጫውቷል።

በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ እስከ ዘመናችን የነሳ ጦርነት የተደረገበት ጉዞ የለም። የሃይማኖት ጦርነቶች ግን ተደርጓል። በዮዲት የተቀሰቀሰው ጦርነትም የኦሪት ሕግ ተከታይ የሆኑ ኢትዮጵያውያንና በክርስትና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑት ኢትዮጵያውያን መሀከል የተደረገው የሃይማኖት ጦርነት ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፊዎች ያቀረቡት ዘገባ ይኸንን ሁኔታ መኖሩን የሚያስተጋባ ነው። በሚቀጥሉት ዘመናትም በእስላሞች ኢትዮጵያውያን እና በክርስቲያኖች መሀከል ጦርነቶች ተካሄዷል።

ሌሎች ታሪክ ጸሐፊዎች ኢትዮጵያውያን ያቀረቡት ታሪክ ጨርሶ ሳይክዱ የግብፅ ፓትሪያርኮች ታሪክ በኒ አል ሐመዱህ ብሎ የጠሯት ንግሥት የእጻጻፍ ስህተት ነው ብለዋል፣ አል ደሙታህ ተብሎ መነበብ እንዳለበት በማመን ዮዲትን ከአባይ በስተደቡብ ይገኝ የነበረው ትልቁ ዳሞት የዛሬው ምዕራብ ሸዋና ወለጋ ንግሥት እድርጓታል። በኢትዮጵያ ታሪክም እስከ 13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ዳሞት የሚባል መንግሥት ተዘግቧል። በመጨረሻ ዮዲት በመሞቷ ጦርነቱ በኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት ድል እድራጊነት ቢደመደምም ጦርነቱ ኢትዮጵያ ደካማ መንግሥት እድራጓት ነበረ ያብቃው። ኢትዮጵያ የደቡብ ክፍለ ሀገሮች ለመቆጣጠር ሳትችል ከመቅረቷ ሌላ እስከ 10ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ዓ.ም. ክርስቲያን የነበሩ እንደ ዘይላ፣ በርበራ፣ የባሕር ጠረፍ ወደቦቿ፣ የእስልምና ሃይማኖት ተሰፋፍተውባቸው ስለነበረ በኢትዮጵያውያን መሐከል

(1) C. Conti - Rossini ibd p. 286
(2) C. Conti - Rossini ibd p. 285
(3) C. Conti - Rossini ibd p. 286

በክርስቲያኖችና በእስላሞች የሃይማኖት መርኃቶች እንዲከሄዱ መንገድ ከፍቷል።

ቀደም ብሎ የእስልምና ሃይማኖት የገባ በዳዕላክ ሲሆን፣ በ14ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ዓ.ም. በሱዋኪን እስልምና ገብቶ ነበር። እንደዚሁም በዚሁ ጊዜ የባርካ፣ ቤጀ ጎሳዎች እና የሳሆ ጎሳዎች፣ ታጁራ ወደብ አካባቢ እስላም ሆነው ነበረ። በአጠቃላይ በባሕር ጠረፍ ወደቦች ብቻ ሳይሆን ወደ መሀል ሀገር በ13 መቶ ክፍለ ዘመን እንደ ሐረር፣ ዝዋይ፣ ሀዲያ ድረስ እስልምና ተስፋፍቶ ነበር።

ዮዲት ወደ ትግራይ ዘመቻ አያርጋ ዘመጣችበት ጊዜ በደብረ ዳሞ ታጉሮ ይኖሩ የነበሩ ሰለሞናዊ ዘር ያላቸው ከፊጀች በኋላ ከእልቲት ያመለጡ ጥቂቶች ወደ ሸዋ መንገ ሸሽተው ሄደው ነበር።

ዮዲት መሞቷ ሲሰማ አምበሳ ውይም በተባለው የተዳሞው ንጉሥ ልጅ ወደ ትግራይ ዘመምጣት ለ20 ዓመት እንደገና በአባቶቹ ዙፋን ተቀምጠ ሲገዛ ቆይቶ ሞተ። ልጁ ግን መንግሥት ለመያዝ ከላስታ የተነሳ ዓመፅ ሊቋቋም ሰላልቻለ እንደ አባቱ እንደገና ከአክሱም ወደ ሸዋ ሸሽቶ ሄደ። መራ ተክለሃይማኖትም የዛጉዌን ላስታ መንግሥት መሠረተ።

ምዕራፍ 3

ኢትዮጵያ ድኅረ ዛጉዌ በሰለሞናውያን ነገሥታት ዘመን

በ1268 ዓ.ም. የመንግሥት መሪነት ስልጣን ከዛጉዌ ነገሥታት ወደ ሰለሞናዊ ዘር ያላቸው ነገሥታት በይኩኖ አምላክ መሪነት በሰላማዊ መንገድ በመሉ ሐይት በሚገኘው ገዳምና በደብረ ሊባኖስ ሸዋ ከሚገኘው ገዳም አባቶች አማካኝነት ሊዘዋወር ችሏል። የአስተዳደር ማእከልም ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሸዋ ተዛወረ። ሸዋ በጀዮግራፊ አተማመጧም የኢትዮጵያ ማእከል በመሆኗ፣ የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት በምሥራቃዊ የሀገሪቷ ክፍል በተቋቋሙት እስላማውያን ትናንሽ መንግሥታት የሀገሪቷን አንድነት የሚያናጉ የሚሰነዝሩባት ጥቃቶችን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር፣ ብሎም ለመግታት እንዲቻል፣ የኢትዮጵያ መስተዳደር በሸዋ ማእከላዊነት መሆኑ አመቺ ሁኔታዎች ፈጥረዋል። በሰለሞናዊ ነገሥታት መሪነት በሸዋ ማእከላዊነት የተቋቋመው የኢትዮጵያ መንግሥት የነበረው ደካማ ጐን እንደ ቀድሞ ጊዜ እንደ አክሱምና ላሊበላ ቋሚ ዋና ከተማ መፍጠር ያለመቻሉ ነው። ይህ ዘመሆኑ የማሕበራዊ ኑሮ ግንባታዎች በማከናወን ለመጪው ትውልድ ታሪክ ማስተላለፍ አልቻለም። ጠንካራ ጐኑ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ዘየወቅቱ የተከናወኑትን የመንግሥት ሥራዎች በጽሑፍ ለወጪው ትውልድ ማስተላለፍ ነው። ሌላ ጠንካራ ጐኑ ወሳኝ ፈተናዎች በማሳለፍ የሀገር አንድነትን ለመጠበቅ አስደናቂ የኢትዮጵያውያን ጀግንነት የታየበትና በታሪክ የተመሰከረበት ዘመን ነበረ። ለ300 ዓመት ገድማ የዘለቀው በሸዋ ማእከላዊነት የኢትዮጵያ መንግሥት፣ በሃይማኖት የተነሱ የእርስ በርስ ጦርነቶችን ተቋቁሞ ኢትዮጵያ በአክሱም መንግሥት ዘመን የነበራት የመሬት ስፋት ከሞላ ጐደል ተረክቢ ሆና ለመጠበቅ ሞክረዋል፣ አንስተኛ የግእዝና የአማረኛ ስነ ጽሑፎችም ዳብረዋል፣ ከምዕራባውያን ጋራ የውጭ መንግሥታትም ግንኙነት ለመፍጠር ሞክረዋል፣ ዘመኑ ምዕራባውያን ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ መኖሩዋን በትክክል ያወቁበት ነበር። የሰለሞናዊ ነገሥታት ስልጣን ሲጨብጡ የኢትዮጵያ አመራር ብሩህ ተስፋ አልጠበቃቸውም። በባሕር ጪረፍ የሚገኙ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገሮች የእስልምና ሃይማኖት የሆኑ ለሚቃወሳቸው የክርስቲያን መንግሥታት የማይታዘዙ መንግሥታት ተቋቁመው ነበረ። ይኸም ሁኔታ ለእርስ በእርስ ጦርነት የሚጋብዝ ነበር። ከይኩኖ አምላክ መንግሥት ጀምሮ እስከ ግራኙ መሐመድ ሞት ድረስ ለ300 ዓመት የኢትዮጵያ ታሪክ በእስላሞችና ክርስቲያኖች የማያቋርጥ ጦርነት የተካሄደበት ጊዜ ነበር። ይህ በሀገራችን የተካሄደው የሃይማኖት ጦርነት በመካከለኛ ምስራቅና በኤውሮጳ የተካሄደው ጦርነት አካልና ነፀብራቅ ነበር። ዓረቦች በእስልምና ሃይማኖት በመመራት በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ ባልታሰበ ሁኔታ ወታደራዊ ወረራ በመፈጸም መካከለኛው ምስራቅ ሀገሮችን በቁጥጥራቸው ለማድረግ ችሏል። ነብዩ መሐመድ ከሞተ በኋላ በሰድስተኛው ዓመት በ689 ዓ.ም. ጉዘፅ በዓረቦች እጅ ወደቀች። ዓረቦች ወደ ሰሜን አፍሪካ ወረራቸውን በመቀጠል በ689 በካርታጅ ከቢድ

ጦርነት አካሂደው ከግራኒት በኋላ በእሳት አቃጠሏት። ከዚህ ጊዜ ጀምሮም ስሟ ከታሪክ ተሰርዟል። በ711ዓ.ም. በበርበር የተገነባ 12,000 የዓረቦች ጦር የጂብራልታር ካናል ተሻግሮ ወደ ስፓኝ ገባ። ሁለት ዓመት ባልሞላ ጊዜ የቪዚጎት መንግሥትን አሸንፎ መላው ሰፔኝን ለመቆጣጠር በቅቶ ነበር። ቀጥሎም ዓረቦች ወደ መሐል ፈረንሳይ ዘልቀው በመግባት መላው ኤውሮጳ እስላማዊት ዓረባዊት ለማድረግ ተቃርበው ነበር። ነገር ግን በቻርል መዶሻ የሚመራው የፈረንሳይ ጦር ፑዋቴ በተባለው ቦታ በ732 ዓ.ም. በተደረገው ጦርነት በዓረቦች ላይ ድል ስለተቀዳጀ የዓረቦች ወረራ ለዘለቄታው ሊገታ ችሏል። ከዚሁ ጦርነት በኋላ የክርስትና ሃይማት ሕልውና እና የኤውሮጳ ሀገሮች ነፃነት ተከብሮ ሊቆይ ችሏል። ከ300 ዓመት በኋላ ሌላ እስላማዊ የቱርክ መንግሥት ተነስቶ በዓረቦች ተተክቶ በዓረቦች ያልተያዘውን የቪዘንታይን መንግሥት በቁጥጥሩ ከገዋሱ በላይ በምስራቅ በኩል በኤውሮፓ ላይ ወረራ በማድረግ ሀንጋሪና አስትሪያ ድረስ ደርሶ ነበረ። የኤውሮጳ ሀገሮችም ተባብረው ያደረጓቸው የመስቀል ጦርነቶች ውጤት አልሰጡም ነበር። በዚሁ ጊዜም ኤውሮፓ በቱርክ እስላማዊ መንግሥት ስር ለመውደቅ ተቃርባ ነበር። ዳሩ ግን ቱርኮች በቪዬና አጠገብ ሽንፈት ሰለደረሰባቸው ኤውሮጳ ከቱርኮች ወረራ ልትድን ችላለች።

የዓረቦችም ሆነ የቱርኮች ግዛታቸውና ሃይማኖታቸውን የማስፋፋት ዓላማ ዋና ትኩረታቸው ወደ ኤውሮፓ ቢሆኑም ወደ ህገራችንም ወኪሎቻቸው መላካቸው አልቀረም። በየጊዜው የነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታትም በክፉ ዓይን የሚያዩዋቸው በሀገራቸው መሬትና የራሳቸው ሕዝብ በእስላማዊ ሐይማኖት የሚያምኑ መንግሥታት ዙርያቸው መቋቋማቸው በማየት በመንግሥታቸው ሕልውና አደጋ ማንጃበቡ መገንዘባቸው አልቀረም ነበር።

ይኩኖ አምላክ ስልጣን በያዘበት ጊዜ የሁኔታው አሳሳቢነት በመመለከት ከቢዛንታይን መንግሥት ጋር ግንኙነት ለማድረግ በመፈለግ ደብዳቤና ሰጠታ ልኮ ነበር። ነገር ግን ራሱ የቢዛንታይን መንግሥት የራሱ ሕልውና እንኳን ለማስከበር በማይችልበት ወቅት ስለነበረ ሙከራው ውጤት ሊያገኝ አልቻለም።

ይህ በመሆኑ በይኩኖ አምላክ የተተካ ንጉሥ ከግብፅ ጋራ መልካም ግንኙነት ለመፍጠር ከከበቡት ኢትዮጵያውያን የእስላም መንግሥታት ግንኙነት አሻሽሉ በሰላም ለመኖር እሰዐ፣ ወሰኑ ለእስላም ነጋዴዎች ክፍት አድርጎ ነበር። ይህ በሰላም የመኖር ሙከራ ግን ጥሩ ውጤት ሊሰጥ አልቻለም።

9. አጼ ዓምደጽዮን(1)

በኢትዮጵያውያን እስላሞችና ክርስቲያኖች አርስ በአርስ አስከፊ ጦርነቶች የተጀመሩበት በይኩኖ አምላክ የልጅ ልጅ በሆነው በንጉሥ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ነበር። ዓምደ ጽዮን የነገሡው ከ1312 - 1342 ዓ.ም. ለሰላሳ ዓመታት ነበረ። ከአጼ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ጀግንነታቸውን ያሰመሰከሩበት ዘመናት ነበሩ።

ኤውሮጳውያን አንዳደረጉት ሁሉ በክርስትና እምነታቸው ፀንተው ለመኖር ያደረጉት ትግል ነበረ። ከዳዲት ጦርነት በኋላ በደቡብና በምስራቅ ኢትዮጵያ ተቋቁመው የነበሩት መንግሥታት ለሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ።

(1) Luca Dei Sabelli ibd VI p 267

1ኛ. በአዉቃላይ ስማቸው ሲዳማ ተብለው የሚጠሩ፣ ወዶም የደቡብ ኩሽ የሚባሉ፣ በጥንት ጊዜ ከስሜን የፈለሱ ናቸው የሚባሉ። የአክሱም መንግሥት አሁን የሚታወቀውን የኢትዮጵያ ደቡብዋ ወሰን ከገዛዋይ ሐይቅ እስከ ሩዶልፍ ሐይቅ ከከፋ እስከ ዘይላ። የባሕር ወደብም እስከ ደቡብ ሶማሊያና አባኒያ ተቆጣጥሮ እንደነበረ ታሪክ ያረጋግጣል። ከሲዳማ መንግሥታት መሐል 1ኛ ጃንጀሮ 2ኛ ቦሻ 3ኛ እናሪያ (ሊመ) 4ኛ አንፈሶ ምዕራብ(ወሊ) 5ኛ ጋፋት ዮቱባሉ የሚወጥሱ ናቸው። ከነገሥታትም ሆነ ከባለባቶች ከስሜን አንወሰዳለን የማይሉ የሉም፣ ይህም የሚያረጋግጠው የአክሱም መንግሥት ተቆጣጥሯው እንደነበረ ነው።

2ኛ. የእስልምና እምነት የሚከተሉ የሱልጣን መንግሥታት ተብለው የሚጠሩ የሚከተሉት ናቸው። 1ኛ. ሐዲያ፣ ጉራጌን የሚያዉቃልል 2ኛ. ፋጢጋር 3ኛ. ይፋት 4ኛ. ዳዋሮ 5ኛ. ባሌ 6ኛ. ሐረር ኩጦማ 7ኛ. ማና 8ኛ. አዳል። ጦርነቱ የተካሂደው በኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥትና በተጠቀሱት 8 አስላማዊ መንግሥታት መሐል ነበር። የስዳማ መንግሥታት የያዙት ገለልተኛ አቋም ነበረ።

ከእስላም መንግሥታት ከሁሉም ጎልቶና የበላይነት የነበረው የይፋት መንግሥት ነበረ። ይህ መንግሥት በክርስቲያኖች ዘንድ የአረመኔዎች መስፍን ተብሎ ይጣራ ነበር። ይፋት ወሳዝማ ተብሰው በሚጠሩ የነገሥታት ዘር ሀረግ ይመራ ነበር። ይህ ስርወ መንግሥት የተመሠረተው በዑመር ወሳዝማ ነው። እስም ከነቢዩ መሐመድ ጎሳ ከሆነው ከኮሬይሰቶች ከሚወለደው ከደህያ የሚወለድ ነበር። አሰም በበኩሉ አል ሐሰን ከተባለው ከነብዩ መሐመድ የልጅ ልጅ የሚወለድ ነው። በአጼ ዓምደ ጽዮን ጊዜ የይፋት ንጉሥ ሐሰ አዲን ይተባለው ነበረ። ጦርነቱ የተቀሰቀሰው የግብፅ መንግሥት በአስክንዲሪያ ፓትሪያርክ ስለሚፈጽመው በደል ለመበቀል አጼ አምደ ጽዮን የአባይ ወንዝ አቅጣጫውን እቀይረዋለሁ ብሎ በመዛቱ፣ እንዲሁም በእስላም ነጋዴዎች የበቀል እርምጃ በመውሰዱ ነው። እነ አዲን አጠፋውን በመመለስ ቤተክርስቲያኖችን በማቃጠል ቁሶችን ሐይማኖታቸው እንዲክዱ በማድረግ በክርስቲያን መንግሥት ውስጥ ግብት ዘልቆ በመግባት የዓምደ ጽዮን ሚስት ባሪያ እንደሚያደርጋትና የቤቱ እህል እንድትፈጭ እንደሚያደርጋት ዛቻ ያሰማ ነበር። ከዚህም ሌላ ወደ ካይሮ ተልኮ የነበረ የኢትዮጵያ መልእክተኛ በመግረከ ሃይማኖቱን አልክደም በማለቱ በእሰቃቂ ሁኔታ ሰለገደለው በሕዝቡና በመንግሥቱ ቁጣ ሰላስከተለ ነበረ። አጼ ዓምደ ጽዮን ጦሩን በመምራት ባደረገው ዘመቻ ይከተለው የነበረው መመሪያ፣ ጠሩ በብዙ አቅጣጫ በማስማራት ድንገተኛ አደጋ በመጣል ለጠላት ፋታ አለመስጠት በጠላት ላይ ሽብርና ፍርሀት መፍጠር ነበር።

ሐሰ አዲን በሊሊት አደጋ በመጣል ቢሞክርም አጼ ዓመደ ጽዮን ጦራውን በማከሸፍ የሐሰ አዲን ወንድም ወደ ነበረበት ጦር ግንባር ጥቃት በመሰንዘር በጉራዴ ራሱ ከገደለው በኋላ ጥቃቱን በመቀጠል በፈረሰኞች እየተረዳ የጠላቶች መደናገጥ በመጠቀም ጠላቶችን በማሳደድ ሐሰ አዲንን ግርኮ ግዛቶቹ ይፋትና ፋጢጋርን በኢትዮጵያ መንግሥት ቁጥጥር ስር ሆኖ አስተዳደሩ ሌሐሰ አዲን ወንድም ሰላብር አዲን በመሰጠት በ1328 ዓ.ም. የመጀመሪያ የአጼ ዓመደ ጽዮን ዘመቻ በድል አድራጊነት ፍጻሜ ሆነ።

የእስላሞች የተባበሩት ነገሥታት ሱልጣኖች ግን ሽንፈታቸው አላመኑም ነበር። በወገራ፣ በሰሜን፣ በደንቢያ፣ በቤጌምድር፣ በጣና ሐይቅ አካባቢዎችና በተከዜ ወንዝ አካባቢ የኖሩ የነበሩ ሕዝቦች በክርስትና እምነት አያምኑም ነበረ። ከአሪት ሕግ ገና አልተላቀቁም ነበር። ላብር አዲን

እንዲተባበሩትና የክርስቲያን መንግሥትን እሱ በምስራት ሲዋጋ በሰሜን እንዲጠብቅ ወኪሉቹን በመላክ ይሰብካቸው ጀምሮ ነበረ። የሐዲያና የዳዋሮ ሱልጣኖቹም ከባብር አዲን ጐን ቆመው ነበረ። አጼ ዓምደ ጽዮን ግን የጣላቶቹ እቅድ በሚገባ ስላወቀ ለየብቸቸው ጥቃት ለመፈጸም ባወጣው አቅድ መሠረት ወታደሮቹ መደ በዲያ ልኮ የሐዲያ ሱልጣን ድንገተኛ ወረራ ስለተፈጸመበት ተማረከ። ሌሎች የአጼ ዐምደ ጽዮን ወታደሮች በተመሳሳይ ጊዜ ከሐዲያ በሚያዋስነው ወረራ በመፈጸም ድል ተቀዳጁ። ሳብር አዲን ወያሚገኝበት ስፈር ደርሰው ነበር። ነገር ግን ሱልጣኑ ሸሽቶ ሊያመልጥ ችሏል። አጼ ዐምደ ጽዮን በዳዋሮ ጣቢያ በግድረግ ወደ ፋጢጋር አመራ። ሳብር አዲን ጠርንት ለመግጠምም ተገዶ ተሸነፈ። ሚስቶቹና ልጆቹ ተማረኩ፣ ከተማው ወደመ። በእጼ ዐምደ ጽዮን ሚስት በዙል ምህረት በመጠየቅ እማላጅ ላከ። ዐምደ ጽዮን ግን ራሱ እፊቱ መቅረብ አለበት ብሉ የሚሉቱ እማላጅነት ሳይቀበለው ቀረ። ሳብር አዲን ድንጋይ በትከሻው ጭኖ ይቅርታ በጠየቀበት ጊዜ የዐምደ ጽዮን ወታደሮች እንዲገደል ቢጠይቁም፣ ንጉሡ ግን እንዲታሠር ብሉ ፍርድ ሰሰሰጠ ታስሮ በእስር ላይ እንዳለ ሞተ።

በሐዲያ፣ ፋጢጋር፣ ይፋት፣ ዳዋሮ ሱልጣኖች ላይ የተደረገው ጠርንት እንዳያበቃ አሁንም የመንግሥቱን ስልጣን ለሳብር አዲም ወንድም ሰጀግል አዲን ስጥቶ መደ ሽዋ በግመለሰበት ጊዜ የአዳልና የግራ ሱልጣኖች በመመሳጠር መደ ኋላ የግመለሰው የአጼ ዐምደ ጽዮን ሠራዊት በደፈጣ ውጊያ በመጠቀም ግጥቃት ጀመሩ፣ ብዙ ወታደሮችም ፈጁ። በዚሁ ጊዜ አጼ ዐምደ ጽዮን በጠላት ውጊያ ስልት በመጠቀም እነሱም ወደሚሰበሰቡበት በፈረሰኞች ደፈጣ በግድረግ ጠበቋቸው። እቅዱ ሙሉ በሙሉ ሰለተሳካ ደፈጣው ሞክረው ተመልሰው በተሰበሰቡበት ቦታ አግኝቷቸው ፈጃቸው። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ይፋትንና አካባቢዋን መልሶ ለመያዝ ግንኛውም ምኞት ውድት ሰለሆነ ጠታደሮች የተግረከውን ንብረት ይዘው ወደ ተጉስት ሰመመለስ ትጉተው ነበር። የንጉሡ አስተሳሰብ ግን ሌላ ነበረ። ጠላቶቹ ወታደሮቻቸውን ይዘ ወደ ተራራማ ደጋ ቦታዎች ተዋጉ እንጂ ቆላ ሀገራቸው ሰለዚህ ተከታትሎ በግጥቃት ቡተገኘው ድል በመጠቀም ጠላት ተመለሰ እንዳያንሰራራ ማድረግ አስፈላጊ ነው የሚል ነበር። በዚህ መሠረት ንጉሡ ዐምደ ጽዮን ከይፋት ወደ ዳዋሮ ጉዞውን ጀመረ። ወታደሮቹ ወደ ቆላ እንሂድም ብለው ተቃወሙት። ነገር ግን ንጉሡ የቁርባን ሕብስት በግውጣት ጠላቶችን ሳልያመስሰ አልመለስም ብሉ በመግል ሰኔ ወር 1330 ዓ.ም. ወደ ቆላ ሀገር አመራ። የአጼ ዐምደ ጽዮን ጦር የሚያቋርጠው የቆላ ሀገር በባሕር ዘኩል ከምጽዋ አስከ ሕንድ ውቅያኖስ የሚያጠቃልል ሲሆን ወደ መሀል ሀገርም እስከ ዝዋይ ሀያት ዉርዉር ሐረር ወዙተ... የሚዘልቅ ነበረ። ወደ ቆላ ሀገር የሚያመራው የኢትዮጵያ ጦር የአዳልና የግራ ሱልጣኖች በቆላ ከሚገኙ ጉሳዎች ከተመለመለ ጦራቸው በደፈጣ ያሰግጀረዋ ያስወጉት ነበረ። ዓለግው ፈት ለፈት ውጊያ በግስወገድ ወራሪውን ጦር በግድክም በሸሽታ በድክም፣ በውሀ እጥረት፣ ጦሩ እንዲያልቅ ነበረ። የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት ወታደሮች በክባድ ችግር መሆናቸውን ስላወቁ አስላሞች ጥቃታቸውን መሰንዘር ጀመሩ። በዚሁ ጊዜ ንጉሡ የመንፈስ ጥንካሬ ስለነበረው ወታደሮቹን በግንቃት እጥቂያቹን ለመቋቋም አሰችሏቸዋል። በሁለቱ ወገን ወሳኝ ፈልጊያ ነበረ። በቁለች ስብከት የተቀሰቀሱ ብዙት ያላቸው ገበሬዎች እንደ መስቀል ጦርነት ጊዜ የንጉሡን ጦር ያጠናክሩ ነበር። በበኩላቸው አስላሞች ቅዱስ ጦርነት ጅሀድ በግወጅ ያላቸው ኃይል

ዘሙሉ አሰልፈው ነበር። የኢትዮጵያ ሠራዊት በግያውቀው በቆላ ሀገር ዘጦርነት ተወዋር መሆኑን ስላወቀ ዘአጼ ዓምደ ጽዮን ቀደም ብሉ በያዘው የእስላም ዘገሮች ዘገረ ጉዥ ሆኖ ተሾሞ የነበረው ጀግል አልዲን ከደቱ የኢትዮጵያ ጦር በሱተጀርባ መደኋላ ሸሽቶ እንዳያመልጥ ውጊያ ለግድረግ ሞክር ነበረ። የአስላም ጦር በመሉ አስተባባሪም በመካ ባላባት ቤተሰብ ተወላጅ፣ ዘሆነው ሼክ ሰሊህ ቡተባለው ሐረር ከተማ ዋና ሠፈሩና ማዛቱ ዘግድረግ ነበረ፣ ተጨማሪ ጎሳዎችም ዘጦርነቱ ገብተው ነበር። ዘዚሁ ዓይነት ዘተሰዘለለው የእስላም ጦር ቁጥሩ እርባ ሺህ /40,000/ ይደርስ ነበረ የባላል። በዚሁ ወሳኝ ፍልሚያ ጊዜ ንጉሡ ታመመ። ሠራዊቱ ሥጋት ሳይ ወድቆ ነበረ። ከርስቲያኖች ከእደጋ ያዳናቸው አስላሞች ዘፈጸሟቸው ስዘተቶች ነበረ። 1ኛ.ሸክ ሳለህና የአዳልና የግራ ሱልጣኖች የፈጸሟቸው ስህተት ጥሩ ውጤት ይሰጧቸው የነበሩ የደፈጣ ውጊያ ትተው በግንባር መግጠም ነበረ። 2ኛ. ስህተት የጀግል አልዲን ጦር እስኪቀላቀል ድረስ አለግጠበቃቸው ነበረ። አጼ ዓምደ ጽዮን ታሞ ስድስት ቀኖች ከአልጋ ሳያነሳ ምግብ ባይቀምስ ቆይቶ ነበረ። ግንባር ቀደም የነበረ ጠሩ ከጠላት ጦር ተጋጭቷል፣ ጠላት ለውጊያ ተዘጋጅቶ እየገሰገሰ መሆኑን ዘሰግ ጊዜ ከአልጋ ተነስቶ መቆም አቅቶት ነበር። ከጐኑ የነበሩ ሁለት ሚስቶቹ ወደ ኋላ ለግፈገፈግ መክሩት፣ ዳሩ ግን ንጉሡ "እንደ ሴት ሆኜ ልመ-ኮ" ብሉ መለሰላቸው። ዘዚሁ ጊዜ እንደኛዋ ንግሥት የዮውርዳኖስ ውዘና የጉልታ መሬት ስጠቸው። እንድ ቄስ ረጨበት ድካሙም በቅጽበት ተወው፣ እሱም ራሱ ለወታደሮቹ ረጨባቸው። ከዚህ በኋላ ለጦርነቱ ትእዛዝ ሰጠ። የክርስቲያን የግንባር ጦር ወደ ኋላ ለግፈገፈግ ተገዶ ነበር። ንጉሡ በጦሩ መሀል ገብቶ በእጁ የቀኝ ክንፍ የነበሩ መሪዎች ገደላቸው። ፈረሰኞችም የመሀል ጦር ግንባር እወደመ፣ ቀሪውን በሱተገራ የነበረውን ዘየመን የመጡ ዘገሩን የግያውቁ ወታደሮች ነበሩ። ትንሽ ጊዜ ዘቆዩ በኋላ እነሱም ግፈገፈግ ጀመሩ። ከዚህ በኋላ የክርስቲያን ጦር ፋታ ሳይሰጥ ዘመሸሽ ላይ የነበሩ እስላሞች ላይ እንዳያመልጡ መንገድ እየዘጋ ይጨፈጭፋቸው ጀመር። ከሬሳዎች መሀከል የሼክ ሳሊህ ነበረ። የግራ ሱልጣን የሚሸሹ ወታደሮችን ሰብስቦ ለመከላከል ሞክሮ የአጼ ዓምደ ጽዮን ወኔ ግን ዕድል አልሰጠውም፣ ወታደሮቹ ተደመሰሱ፣ ሱልጣኑ ተግርኮ ተሰቀለ፣ ሚስቱም ክርሲያኖችን ጠንቋይ ይሏት የነበረ ተይዛ ገላዋን ተቆራርጦ ለጅቦች ተሰጠ። ጦርነቱ የተካሄደው ሐምሌ ወር ወደ መጨረሻ 1330 ዓ.ም. ነበረ። አሁንም የአጼ ዓምደ ጽዮን ወታደሮች አቅማቸው እንደተሟጠጠ ለንጉሡ ቢያመለክቱም ንጉሡ ግን አልተቀበላቸውም፣ እፊቱ መከላከል አቅም የሌላቸው የጠላት ቦታዎች ነበሩ። የዓምደ ጽዮን ወታደሮች እየገሰገሱ ጠላቶቹን መደምሰስ ቀጠሉ፣ ከተሞች ተቃጠሉ፣ ተዘረፉ፣ ተወሰደው ታረዱ። የአዳል ሱልጣንም ወረራውን ለግቆም ሞክር ነበር። ጦርነቱ ለክርስቲያን ፈረሰኞች ምቹ በሆነ ግልፅ ቦታ ተካሂዶ የእስላም ወታደሮች በክርስቲያን ፈረሰኞች ተከበው ግምለሚ እጥተው አለቁ፣ የአዳል ሱልጣን በጦር ሚዳ ሞተ። ወደ መጨረሻ የቀረ የሐረር ሱልጣን ነበረ። የመጨረሻ ፅዕል ለመሞከር በሱልጣኑ ዙሪያ የቀሩት እስላሞች በሙሉ ተሰበሰቡ፣ ከእነሱ ውስጥም 99 ባላባቶችና ሱልጣኖች ነበሩ፣ ሕዝቡም ወንድ ሴት ሳይለይ ተካፋይ ነበረ። አሁንም የወሳኝነት ሚና የተጫወተው ሱልጣኑን ከፈረሱ በጦር ወግቶ በመገደል ዓምደ ጽዮን ነበረ። አሁን ግን የሚጽጽመው ኃይል አልነበረም። ሁሉም የመሸሽ ብቻ ነበረ የተያያዙት። አሁን የቀረ ስራ መስኒዶችን ማፍረስ ከተሞችን ግቃጠል ሰዎቹንም ወንድ ሴት ልጅ እዋቂ ሳይለዩ መገደል

ነበረ። የእጼ ዓምደ ጽዮን ወታደሮች እራት የተባለው በክርስቲያኖች ላይ ጥላቻ የነበረው ቦታ ደረሱ። በዚህ ቦታ ብዙ ክርስቲያኖች ጅሮዋቸውን እናንጫጫቸውን የተቆረጠ እንዲሁም የተሰለቡ ሰለነበሩ ንጉሡ ፊት ቀረቡ። በዚው ጊዜ ክርስቲያኖች ቁጣ ገንፍሎባቸው ሰነበረ ወንጀለኞች የሀገሩ ሰዎች እንዳያመልጡ በማሰብ የመሸሸ በማለመሰል ወደኋላ ሲመለሱ ሕዝቡ ወደ እየቤቱ ተመለሰ። ነገር ግን ክርስቲያኖች ተመልሰው በመጣት በክርስቲያኖች ላይ የተፈጸመው በደል በመሱ በእስላሞች ላይ ሰመድገም ቲም በቀል ፈጽመባቸዋል። ንጉሡ በድል አድራጊነት ወደ ተጉስት ሲመለስ የጀግና አቀባበል ተደርጎለታል።

3. <u>እፄ ይስሀቅ</u>

ያ ሁሉ የእጼ ዐምደ ጽዮን ጀግንነት ውጤት አልባ የሚያደርገው ጠላቶችን እሰከ ባሕር ዳርቻ ምፅዋ፣ አሰብ፣ ታጁራ፣ ዘይላ ራሱ ባሰግባረሩ ነው። ከእጼ ዓምደ ጽዮን ቀጥሎ ከንግሡት ነገሥታት ወደ ባሕር ጠረፍ የደረሰ ከ1414 እሰከ 1429 ዓ.ም. የነገሰ እጼ ይስሀቅ ነበረ። እንደነገሡ የያፋት ንጉሥ ሠኢድ አልዲን ጦርነት ከፈተበት። በመጀመሪያ ግጭት ለክርስቲያኖች የቀኗቸው ነበር። ራሱ የይፋት ንጉሥም ለትንሽ ነበር ከመግረክ ያመለጠው። በ2ኛ ጊዜ ግን ሰይድ አልዲን ኃይሉን አጠናክሮ መጥቶ ወደ ክርስቲያን ምድር በልቆ በመግባት ሰፈ መራት በመያዝ ብዙ ንብረትም ለመማረሩ ችሉ ነበረ። 2ኛ. ዙር የክርስቲያን መንግሥት ሠራዊት ባሩዋ በተባለው የሚመራ ነበረ። ባሩዋ የተከተለው የጦርነት ሰልትም እንደ ቀደምት ኢትዮጵያውያን የተሰያዮ ሱልጣኖችን ሰየብቻቸው መግጠም ነበር። በዚህ መሠረት የመጀመሪያ ጥሪቱ የአዳል ሱልጣን ጦር ከሰዒድ አልዲን ጦር እንዳይገናኝ ማድረግ ነበረ። በአዳል ሱልጣን ሠራዊት ወረራ አድርጎ ሱልጣኑ በጦር ሜዳ ተገደለ፣ ወታደሮቹም ተደመሰሱ። ከዚህ በኋላ የሰኢድ አልዲን ሠራዊትን እያሳደደ መፍጀት ተያያዘው። በመጨረሻም በዘይላ ኩተግ እንዲደበቅ አደረገው። ክርስቲያኖች የኩተግዋን የውሃ መስመር እንዲቋረጥ በማድረግ ከተግውን ከማረኩ በኋላ ሰይድ አልዲን ፈብሯሪ 16 ቀን 1445 ዓ.ም. ተገደለ። የሱ አሰር ልጆች ሸሽተው ወደ ደመጌ ተሻገሩ። መስጊዶችን በማቃጠል በበታቸው ቤተክርስቲያኖች ተሰሩ። ዘይላ ክርስቲያን ሆና ለ20 ዓመት በኢትዮጵያ ቁጥጥር ስር ነበረች። ሆኖም ኢትዮጵያ የባሕር ኃይል ሰላልነበራት የወደብ አሰተዳደርም ልምድ ሰላልነበራት ለዘለቂታው በቁጥጥሯ አድርጋ ለመቆየት አልቻለችም። አሰር የሰይድ አልዲን ልጆችም በየመን መንግሥት እርዳታ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ለጦርነት ሲዘጋጁ ኢትዮጵያ ልትቆጣጠር አልቻለችም። የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት በጦር ሜዳ ባገኘው ድል እንደ ዓምደጽዮን ሲጠቀምበት አልቻለም። በዘይላ በኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት በተያዘበት ጊዜ ጀምሮ የይፋት ነፃ መንግሥት ለዘላዓለም ተሰርዞ በኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት ግዛት ውስጥ ተጠቃለለ። ከዚው ጊዜ ጀምሮ ፀረ ክርስቲያን መንግሥት መሪ ተዋናይ የሚሆነው የአዳል መንግሥት ነው። የወላዝግ ንጉሣዊ ቤተሰብ አንድ ዓመት ከዘይላ መያዝ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ፣ ዋና ከተግቸው ያደረጋት ዳኻር የምትባለው ቦታ ነበረች። እፄ ይስሐቅ፣ኮንቲ ሮሲኒ[1]፣ ጠሪያ ነበረ የሚለው የኢትዮጵያ ንጉሥ፣ በሰሜን ኢትዮጵያም ጦርነት አካሄዷል።

(1) C. Conti - Rossini : Etiopia e genti d' Etiopia p 55

በመጀመሪያ ዘመቻ በዳሕላክ ደሴቶች ሱልጣን ሥር የነበረች ምፅዋ በእፄ ይስሐቅ ወታደሮች ተያዘች፣ ሁለተኛ ዙር ዘመቻ ትልቁ ዳሕላክ ተያዘ፣ በሦስተኛ ዙር ዘመቻ ምፅዋና የዳሕላክ ደሴቶች ከኢትዮጵያ ቁጥጥር ስር ውጭ ሆነው ሰለነበረ እንደገና ተያዙ፣ በጦርነቱም መሪ የነበረ ታዲ ተገደለ።

ሌላ የግዛት ማስፋፋት የተደረገው ከአሪት ሕግ ገና ያልተላቀቁ የነበሩ ወገራና ደምብያ አውራዳ ነበር፣ ቤተዐሹታቸው ወድመው በቦታው ቤተክርስቲያኖች ተሰሩላቸው። ወደ ደቡብ የግዛት ማስፋፋት የተደረገው ዘመቻ ከጊቤ በስተ ደቡብ ምዕራብ የነበሩ የቦሸያ /ጅማ/፣ እናሪያ /ሊሙ/፣ እና ኩዮራ የተባሉ መንግሥታት ነበሩ። ከዚሁም በስተደቡብ የነበረ የኢትዮጵያ መፈት ሰፋት በትክክሰ ባይታወቅም ከስሞጥ ሸለቆ ሐይቆች በስተደቡብ እሰከ ዛንዚባር፣ በምዕራብም እሰከ ናይል ሸለቆ ይዘልቅ ነበረ[1]።

ወደ ደቡብ የግዛት ማስፋፋት የተደረገው ዘመቻ ከግቤ በስተደቡብ ምዕራብ የነበሩ የቦሸያ /ጅማ/ እናሪያ /ሊሙ/ እና ኩዮራ የተባሉ መንግሥታት ነበሩ። ሁሉም ከኢትዮጵያ ጋራ በሸዋ ግዛት የተቀላቀሉ የተድሞ ግዛታቸው የሰይድ አልዲን ልጆች፣ የወላዝግ የነብዮ መሐመድ ዘር የሱልጣኖች ቤተሰቦች የሆኑ ከየመን ተመልሰው መጥተው የአባታቻው ሞት ሰመበቀል ከግብፅ የመጡ ቡቱርክ ውጊያ ሰልት አሰልጣኞች እየተረዱ ዘመናዊ የጠብመንጃና የጦር መሣሪያዎች የነበራቸው፣ የይግም ግራኝ ተመሳሳይ የሆነ መሣሪያ ታጥቀው ሰፈ ዘመቻ ጀምረው ነበር። ነገር ግን ይህ ጠንካራ ይመስል የነበረ ወታደራዊ የግጥጫት ዘመቻ እንደ ተጠበቀው ውጤት አልሰጠም። ንጉሥ ይስሐቅም የጠላቶቹ እንቅስቃሴ ያውቅና ይከታተል ሰነነበረ ሰመልሰ ግጥጫት ተዘጋጅተ ይጠባበቅ ነበር። በመጀመሪያ ጊዜ የዘመቻው ሹም የነበረው የሳይድ አልዲን በኩር ልጅ ሳብር አልዲን ነበረ። የእስላም ወታደሮች በድንገት አደጋ ጥሰው ሸዋ መሀል ገብተው በክርስቲያኖች ላይ ብዙ ሽንፈት አድርሰው ነበር። ንጉሡም ሰመበቀል በእስላም ነጋዲዎች ላይ ጥቃት ከግድረሱም በላይ ያልፈረሱ መስጊዶችን እቃጠላቸው። ጦርነቱ ከ2ቱ ወገኖች አሸናፊ ሳይለይ ለብዙ ዓመታት ቀጠለ፣ በመሀሉ ሁለቱ ወገኖች ሰጊዜያዊ ሰላም ተስማሙ። በዚህ ጊዜ በ1422 ዓ.ም. ሳብር አልዲን ሞተ፣ ወንድሙ ግንቡር መሪነቱን እንደተረከበ ጦርነቱ ቀጠለ። ግንቡር ጦነቱን በግፋፋም በአግራ መሀል ሰመግባት ችሉ ነበር። ነገር ግን ሽንፈት ሰለደረሰበት በ1424 ተግረከ። ጀግል አልዲን ሌላ ወንድማቸው መሪነቱ ተረክቦ ጦርነቱ ቀጠለ። ቤተክርስቲያኖችም ይቃጠሉ ነበረ፣ ክርስቲያኖች የጦር ምርኮኞች በባርነት ይሸጡ ሰሰነበረ የባሪያ ዋጋ በዓረብ ሀገሮች ረክሶ ነበረ። ጦርነቱ አሸናፊ ሳይለይ ሲካሄድ ከቆየ በኋላ በመጨረሻ ክርስቲያኖች መልሶ በማጥቃት ድልን ተቀዳጁ፣ እሰላሞቹንም ከሀገራቸው ሊያሰወጡ ችለዋል። በ1429 ዓ.ም. ጊዜያዊ ሰላም ሰፍኖ በነበረበት ጊዜ አጼ ይስሐቅ ተገደለ። ከሦስት ዓመት በኋላ ታዋቂው ጀግል አልዲን ብቤተሰቦቹ በተፈጠረ ጠብ ሲገደል ሌላ ወንድሙ የመሪነቱን ሥልጣን ተረክቦ ጦርነቱ እንደቀድሞ ጭካኔ በተሞላበት ቀጠለ።

(1) Coulbeaux : Histoire Pollitique et religieuse d' Ethiopia p. 285

4. አፄ ዘርአ ያዕቆብ

በክርስቲያን መንግሥትም ለእጭር ጊዜ ብዙ ነገሥታት ከነገሡ በኋላ ዝነኛው የኢትዮጵያ ንጉሥ ዘርአ ያዕቆብ በ1434 ዓ.ም. ነገሠ። በእሱ ዘመን መንግሥት ሰለሞናዊ ሀረግ ያላቸው ነገሥታት ከፍተኛ ዝናና የእስተዳደር መሻሻል እርምጃ የታየበት ጊዜ ነበር። ተሳላፊ በሽታ በሀገራቱ ገብቶ ስለነበረ ጦርነቱ ሉተወሰን ጊዜ ቆሞ ነበረ። ኢትዮጵያ በአጼ ዓምደጽዮን መሪነት በእስላሞች ላይ የተቀዳጀቻቸው ድሎች ዜና በመካከለኛው ምሥራቅና በምዕራባውያን ተሰምተው ነበር። ዜናዎች ቢሰሙም የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት ፀረ እስላም የሚያካሂደው የሞት ሽረት ትግል ተቆርቋሪ በመሆን፣ የኢትዮጵያ እስላሞች ከዓረብ ሀገሮች እርዳታ እንደሚያገኙ ሁሉ የክርስትና እምነት ያላቸው የኤውሮጳ ሀገሮች በምን ዓይነት መንገድ ለኢትዮጵያ ወታደራዊና ፖለቲካዊ እርዳታ ግድረግ እንደሚችሉ የተደረገ ጥረት አልነበረም። ኢትዮጵያ ከኤውሮጳ መንግሥታት የትኞቹ መንግሥታት እንደሆኑ በቂ ወታደራዊ እርዳታ ሊያደርጉላት የሚችሉ የግዙት ዕድል አልነበራትም። ለምሳሌ ብቸኛ ግለሰብ በወቅቱ ወደ ኢትዮጵያ የደረሰና ስለ ኤውሮጳ ለአፄ ዘርአ ያዕቆብ ያወራ አንቶኒዮ ባርቶሊ የተባለው አንድ ኢጣሊያዊ ነበረ። ኢጣሊያ ደግሞ በዚያን ጊዜ ለራሷ በባእድ መንግሥታት የምትገዛ፣ በተቃቅን መንግሥታት የተከፋፈለች፣ ኢትዮጵያን ለመርዳት የምትመረጥ ሀገር አልነበረችም። ባርቶሊ ለአጼ ዓምደ ጽዮን ይሰጣቸው የነበሩ ዜናዎች ስለ እነዚህ የኢጣሊያ ታናናሽ መንግሥታት ከፍተኛ ስልጣኔና ስለ የሮማ ጳጳስ ትልቅነት ነበረ። ዘርአ ያዕቆብ አስቸኳይ የክርስቲያን መንግሥታት እርዳታ ፈላጊ ቢሆንም ከማን ጋራ ግንኙነት እንደሚያደርግ የሚያስረዳ ሰው ስለሌለው እንደ ቀድሞቹ የኢትዮጵያ መንግሥታት ዓምደ ጽዮንና ይስሐቅ ብቻውን ከእስላሞች ጋራ ጦርነት ገጠመ። ዘርአ ያዕቆብ ዘመጀመሪያ ያካሄደው ጦርነት በሀዲያ አውራጃ በራሱ ግዛት ነበረ። በዘርአ ያዕቆብ የዚሁ አውራጃ ገዥ ሆኖ የተሾመው የአንደኛዋ ሚስቱ ወንድም የሆነው ግሂኑ የተባለው ከአዳል ሱልጣን ጋራ በመመሳጠር ሽፍቶ፣ ነባ መንግሥት አውጆ፣ ሌሎች አውራጃዎችን ወደ እሱ ለመሳብ በምስጢር ግንኙነት አድርጎ ነበር። ዘርአ ያዕቆብ እቅዱ ወደ ተግባር እስከሚፈጽመው ድረስ አልጠበቀውም፣ ከሥልጣኑ አውርዶ ወረረው። ግሂኑ ወደ አዳል ሸሽቶ ለመሄድ ወደ ምሽግ ቦታ ለመግባት ሲሞክር የዘርአ ያዕቆብ ወታደሮች ስለደረሱበት ገደሉት፣ አንገቱን፣ እግሮቹን፣ እጆቹን ተቆራርጠው ወደ ዘርአ ያዕቆብ ተወሰደው በንጉሡ ቤት ደጃፍ ተሰቀሉ። ከሁሉ የላቀ ድል አጼ ዘርአ ያዕቆብ የተቀዳጀው ለአዳል ሱልጣን በጀግል አልዲን ሰልጣን የያዘው የሰይዲ አልዲን ሌላ ልጅ በባድላይ ነበረ። በ1445 ዓ.ም. ባድላይ የዳሞሮን አውራጃ ወሮ ነበረ። ዘርአ ያዕቆብ በእነሰተኛ ወታደሮች ቢገጥመውም የገጠመው በወኔ ሰለነበረ ድሉ የእሱ በመሆኑ በመጀመሪያ መስመር ሆኖ ይዋጋ፣ የነበረ ባድላይ ከአጼ ዘረአ ያዕቆብ ጋራ ተወጋቶ ወደቀና ሞተ። አስከሬኑ ተቆራርጦ ለመላው የመንግሥቱ ግዛት ተከፋፍሏል። የባድላይ ወንድም በመሸሽ ላይ እንዳለ አሳድዶ አዋጅ ወንዝ ለመሻገር በሚሞክርበት ጊዜ ተገደለ። አጼ ዘርአ ያዕቆብ ሁለት ድሉችን በአጭር ጊዜ ቢጎናፀፍም የእስላሞች አደጋነት በመሉ እንዳልተወገደ ስለተረዳና አሳላፊ ስለሆነበት በሁለት መንገድ ዘላቂ መፍትሔ ብሎ የገመታቸው እርምጃዎች ወሰደ። የመጀመሪያ የክርስቲያኖች አንድነትና የእምነታቸው ግጠናከሪያ 2ኛ. ከዓለም ክርስቲያን መንግሥት እርዳታ መጠየቅ ነበረ። አጼ ዘርአ ያዕቆብ በሁሉቱ

መንገዶች ተጠቅመዋል። የክርስትና ሃይማኖት ለግስፋፋት በውድም በግስደድም ሞክሯል። መንፈሳዊ መጽሐፎች ከውጭ ቋንቋ ተተርጉመው እንዲሰሙ አስገድዷል። የግርያም ድንግል በዓላቶችና፣ ያምን ወዘተ ወስኗል። አንዳንድ የውጪ ሀገር ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ በመግባታቸው በርም ካቶሊክ ቤተክርስቲያንና በኢትዮጵያ እርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ያሰው ልዩነት የግዋዋያ እርእስት ሆኖ ነበረ። አጼ ዘርአ ያዕቆብ ከክርስቲያን መንግሥታት እርዳታ ለማግኘት ሰነበረው ምኞት ግን ውጤት አልባና ዓላማውን የሳተ ነበረ ለማለት ይቻላል። አጼ ዘርአ ያዕቆብ የኤውሮጳ መንግሥታትን ማንነት ለይቶ ካለማወቅ የተነሳ በ1450 ዓ.ም. ለናፖሊ ንጉሥ መልእክት ልከዋል። የናፖሊ መንግሥት፣ እንኳን ከኤውሮጳ መንግሥታት ሊወዳጅር ቀርቶ፣ በኢጣሊያ ከነበሩ እነስተኛ መንግሥታትም ከሁሉም ኋላ ቀር የነበሩ መንግሥታት የሆነ ነበረ። ስለዚህ ምንም ዓይነት ጠቃሚ እርዳታ ለኢትዮጵያ መስጠት የሚችል አልነበሙ። የናፖሊ መንግሥት በሰዓሊ ሞያ ስም የላከው ብራንካሌዮ የሚባለው ግለሰብ ቀድሞ ቁስ የነበረ ስለሆነ ጊዜው ያሳለፈው የሃይማኖት ክርክር በመቀስቀስ ብቻ ነበረ። አጼ ዘርአ ያዕቆብ ለዝነኛው የቢዛንታይን ክርስቲያን መንግሥት እርዳታ እንዳይጠይቅ በዚሁ ጊዜ በቱርክ ኦቶማን መንግሥት ተሸንር በ1454 ዓ.ም. ዋና ከተማው ቆስጣንቲኒያ የተማረከበት ወቅት፣ ሕልውናውም ያበቃበት ጊዜ ነበረ። ሌላ አጼ ዘርአ ያዕቆብ በትልቅ ጉጉት እርዳታ እንዲያደርግለት ሊጠባቀቅ የነበረው ክሮማ ጳጳስ ነበረ። ወቅቱ በቱርክ ኦቶማን አማካኝነት የእስልምና ሐይማኖትና መንግሥታት በኤውሮጳም በአፍሪካም ጥንካሬ ያገኙበት ነበረ። በዚሁ የተነሳ የሮማ ጳጳስ የመላው ዓለም ክርስቲያኖች ለማስተባበር በ1440 ዓ.ም. ማሊያን ሀገር በፈሬንሴ ጉባዔ ጠርቶ ነበረ። ኢትዮጵያም የጉበፅ ቤተክርስቲያንም መልእክተኞቻቸው ወደዚህ ጉባዔ ልከው ነበር። የጉበፅ መልእክተኞች የተመሩት እንድሪያ በተባለው የቅዱስ አንቶንዮስ ገዳም አበታ ነበረ። የኢትዮጵያ መልእክተኞች ቀሳውስት የተሳኩት ከአባ ኒቆዲሞስ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት አበታ ወክሎ ነበረ። የሮማ ጳጳስ ዓላማ የዓለም ክርስቲያን በሙሉ የካቶሊክ እምነት ተቀብሎው በእሱ ስር እንዲሆኑ ነበረ። ለክርስቲያኖች ትብብር እንቅፋት የሆነውም ይህ ቅድመ ሁኔታ መሞት ስለነበረ ነው። ኢትዮጵያም ከዚህ ቀደም እርዳታ ከክርስቲያን መንግሥታት ያላገኘችው በዚሁ ቅድመ ሁኔታ ምክንያት ነበር። የጉበጽ መልእክተኛ ለጉባኤው ያደረገው ንግግር የሮማ ጳጳሳት በግወደስ ነበረ። ከተናገረውም ውስጥ የሮማን ጳጳስ በማስመልከት "በዚሁ ዓለም እርሶም እግዚአብሔር ነዎት እርስም የክርስትና እንደራሴ ነዎት፣ እርሰም የዓለም ኗቱፍ ቤተክርስቲያን አለቃ ነዎት ለእርስም የመንግሥተ ሰማያት በር የመክፈት፣ የመዝጋት ቁልፍ ተሰጥቶታል ወዘተ... የሚል ይገኝበታል። የጉበፅ መልእክተኛ ንግግር ከተሰማ ሁለት ቀን በኋላ የኢትዮጵያ መልእክተኞች ፈሪንሴ ገቡ፣ ከሁለቱ መልእክተኞች እንዱ ባደረገው ንግግር የጉበፅ መልእክተኛ ካደረገው ንግግር ተመሳሳይ ቢሆንም ለየት የሚያደርገው ሀገሩ ኢትዮጵያ በሚመለከት ያሰማው የሚያወድሱ ቃላቶች ነበሩ።

ወደ ሮማ ጳጳስ ፊቱን አተኩሮ ሲናገር "ከእርስዎ የተለዩ ሁሉ ወድቀዋል፣ ክሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ከተለዩ ቤተክርስቲያኖች ሁሉ የእኛ ጠንካራና ኃይለኛ ነፃ ሆና ኖራለች፣ ምክንያቱም ሌሎች ቤተክርስቲያኖች ከእርስዎ የተገነጠሉ በክፋት በፍላጎታቸው ነው፣ እኛ ግን ተለይተን የኖርነው በመገደድ፣ ሸርቀት የተነሳ፣ በመንገዱ አደገኛነት ነው፣ ከእርስዎ በፊት የነበሩ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሊቀጳጳሳት ቸልተኝነት ነው፣

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በዚህ ዓለም ከሮማዊት ቤተክርስቲያን ጋራ ከመዋሐድ ሌላ ምኞት የለውም" ወዘተ... የሚል ይገኝበታል።

አጼ ዘርአ ያዕቆብ ሞቱ ወደ ደቡብ አስፋፍቶ ስለነበረ፣ የኢትዮጵያ መልእክተኛ በኩራት አፋን ሞልቶ ሲናገር "የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አንድ መቶ ነገሥታት እንደሚያዝዝ ለጉባኤተኞች ተናግሯል። የፈረንሲ የጉባኤ ቡተሳካ ሁኔታ የተፈጸመ መስሎ ቢታይም መልእክተኞቹ ተመልሰው ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ ካይሮ ሲገቡ የጉባኤው ውሳኔ ሳይፈርም በቀረ ብቸኛ በኢፈሶን ቤተክርስቲያን መልእክተኛ የሚመራ የጉባኤውን ውሳኔ የሚቃወም ንትናቄ ተደርጎባቸው ሁሉም የምሥራች አበያተክርስቲያን የሚያጠቃልል ፀረ ሮማ ቤተክርስቲያን እንቅስቃሴ ተነሱቶ ነበር። ስለዚህ የፈረንሲ ጉባኤ ለሮማ ጳጳስ ክብር ከሰረት ነበር የሆነበት። በእጼ ዓምደ ጽዮን የእጼ ይስሐቅና በእጼ ዘርአ ያዕቆብ ጊዜ በቀይ ባሕር ወደቦች በክርስቲያን ስም ከቱርክ አቶማን ጋራ ትፋለም የነበረችው ከፖርቱጋል መንግሥት ጋራ ኢትዮጵያ ግንኙነት አድርዎ ብትሆን ኖሮ በይግም ግራኝ ጊዜ እርስ በእርስ ጦርነትና የሀገሪቱ አበያተክርስቲያናት የቅርሳቅርሷ የመጻሕፍቶቿና የታሪኳ ውድመት አይደርስባትም ነበር፣ የእሮሞ ታሪክዊ ማስፋፋት ከስተት እያጋጥማትም ነበረ። ከእጼ ዓምደ ጽዮን ጀምሮ ክባሀር ወደቦች በቀር የመሀል ሐገር የአክሱም መንግሥት ዘመን ወደነበራት ስፋት ተመልሶ ነበረ።

በአፈ ታሪክ አባባል ኢትዮጵያ 14 መንግሥታት ነበሯት። ከነዚህም ውስጥም 4 መንግሥታት የወርቅ ዘውድ የሚጭኑ ነበረ እነሱም 1. ትግራይ 2. አማራ /ጎንደር/ 3. ሳሰታ 4. ሸዋ /ጎጃም ናቸው። ሌሎች 4 ነገሥታት የብር ዘውድ የሚጭኑ እንደዚሁም ነገሥታት የነሀስ ዘውድ የሚጭኑ ስማቸው የማይታወቅ ነበረ።

አልቤርቶ [1] ፖሌራ እንደጠቀሰው በ1603 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የነበረው ሚሲዮናዊ አባ ፓየዝ በጻተፈው መሠረት በማድረግ በጥንት ጊዜ ኢትዮጵያ 35 መንግሥታትና 18 ራስ ገዝ አስተዳደሮች ነበሯት።

እንደዚሁም ፖሌራ በ1629 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የነበረ ፖርቱጋላዊ፣ ሚሲዮናዊ ፣ ዳሚዳ የጻፈው መሠረት በማድረግ በጥንት ጊዜ ኢትዮጵያ 36 መንግሥታትና 17 የራስ ገዝ አስተደደር ያላቸው ግዛቶች ነበራት ካሰ በኋላ፣ ባገኘው ሌሎች ዜናዎች ግን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት 60 መንግሥታት ከርስቲያን ያልሆኑ እንደዚሁም ሌሎች ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ገባር መንግሥታት ያዝዝ እንደነበረ ገልጧል።

በተጨማሪም ፖሌራና ኮንቲ ሮሲኒ ገጽ 15 እንደጠቀሱት ከ1624 ዓ.ም. እስከ 1704 ዓ.ም. የኖረው ጀርመናዊ ሉዶልፍ የኢትዮጵያ ቋንቋና ታሪክ አዋቂ በጻፈው መሠረት በማድረግ ዘተለያዩ ጸሐፊዎች የሚነገረው የመንግሥታት ቁጥር የተለያየ ነው ብሎ ካሰጠነቀቀ በኋላ ኢትዮጵያ 30 መንግሥታት ነበሯት በማለት ስማቸውን ይጠቅሳል። የመንግሥታቱ ስም በተመለከተ አብዛኛው አሁን ቢኖርም ያንዳንዶቹ ስም ግን አሁን የለም። ፓየዝ ባወጣው የ35 መንግሥታት ስም ዝርዝር እንደሚከተው ያቀርበዋል 1. ትግራይ ወሰኑ ከዮት ወዴት መሆኑን ባይገልፅም በዛሬዋ ደቡብ ትግራይ ክፍል አበርጋለ፣ ሰሉዋ፣ ወገራት፣ እንዳርታ፣ እንደ አካል ነበረች 2. ደንከል /አፋር/ 3. አንጎት አብዛኛው የዛሬዋ ወሎ 4. ዶባ ከወሎ ትግራይና አፋር መሐል የነበሩ ሕዝቦች 5. አውሳ ደቡብ አፋር 6. አማራ ምናልባት ደቡብ ጎንደር 7. አላቃ 8. ሸዋ ከዮት ወዴት እንደሆነ

[1] Alberto Pollera : Lo Stato Etiopico e la sua Chiesa

አይታወቅም 9. ይፋት 10. ገዳም 11. ጋንች 12 ዳዋሮ/ ምናለባት የዛሬዋ ጨርጨር 13. ፋጢጋር ከይፋት በስተሰሜን የዛሬዋ አርንባ 14. አዩዩ ከዝዋይ ሀይቅ በስተምሥራቅ 15. ባሌ ከዛሬዋ አርሲ እስከ ሶማልያና ሕንድ ውቅያኖስ 16. ሀዲያ 17. አላባ /ቆቃ አካባቢ 18. አክሰሰን 19. ቤቶ ቆቃ አካባቢ 20. ቤቴሪምራ 21. ጉራጌ በጉራጌ ሸም የሚታዘዙ 22. ኮይራ /ከጁባ ወንዝ እስከ ስተፋኒያ ሀይቅ 23. ሀዙማ ከዝዋይ በስተደቡብ 24. ሱፍ ጋሞ የዝዋይ በስተደቡብ በአብያታ ሐይቅ እስከ ቆይራ ባሕር ጋ 25 ባሕር ጋ 26. ከንባታ 27. ቦሻ (ጅማ) 28. ጉመር /ከፋጨጋር በስተደቡብ 29. ጃንጃሮ 30 እናርያ (ሊሙ) 31. ኮንታ 32 ዳሞት 33. ጎጃም 34. ቤጌምድር 35. ደንብያ።

በዚህ ስም ዝርዝር እንደምንመለከተው የዛሬዋ ጎንደር ክፍል ሀገር ለቤጌምድር ደምቢያ አማራ መንግሥታትና በሰሜን ዐለሙቲ ቦራ ፀገሌ ወልቃይት ማዘጋራ ራስ ገዝ አስተዳደሮች ተከፋፍላ ነበረች። ሳሰታ በውስጡ ስም ዝርዝር አይገኝም። ወለጋ የቢሳሞ መንግሥት ተብላ ትጠራ ነበረ። ከዲዲሳ ወንዝ እስከ አባይ ወንዝ ማን ጋፋት ተብሎ ይጠራ ነበረ። ይህ ሰፋ የኢትዮጵያ ግዛት በታሪክ በመልከአ ምድር አቀማመጥ በዘር አንድ የሆኑ ሕዝቦች በአንድ ማእከላዊ መንግሥት ይተዳደሩበት የነበሩ ኢትዮጵያ በእስልምና እምነት ተከታዮች እርስ በእርስ ጦርነት ባትወጠር ዙተሰይም በሌላ አርእስት እንደሚታየው የአሮሞ የማስፋፋት ከስተት ባያጋጥማት በኩልም እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ከዚያም በላም ለመድረስ በእካባቢው የተደራጀ ተቃዋሚ ኃይል ስላልነበረ እንቅፋት አያጋጥማትም ነበረ።

ይህ በማድረጓም በአፍሪካ ስልጣኔ ለማስፋፋት የነበራት ታሪካዊ ተልእኮ መወጣቷ የሚያመለክት ስለሆነ የሚያስመስግናት ነበረ። የኤውሮጳ ታሪክ ጸሐፊዎች ኢትዮጵያን የሚወቅሷት ይህንን ባለማድረጓ ነው። የዛሬዎቹ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ግን የደቡብ ምስራቅና ምዕራብ ኢትዮጵያ ዳግማዊ ምኒልክ በዛሬ አንድ መቶ ዓመት ዘወረራ እንደያዛቸው ስግስመሰል እየሞከሩ ይታያሉ። ከንያ ውስጥ የሚኖሩ የአሮሞ ዝርያዎች የሆኑ ከኢትዮጵያ ተነጥለው ከከንያ ጋራ የተቀላቀሉት ኢትዮጵያ በአሮሞች ምክንያት የጋጠማት የመንግሥቷ ድከመት ነው።

በንግሥት ሳባ ጊዜ ኢትዮጵያ የባሕር ጠረፍ የት ድረስ ይደርስ እንደነበረ በማመልከት [1] ሻለቃ ሩፊሎ ፒሪኒ እንደሚመለከተው ይገልጻዋል "የባሕር ነጋሽ ሥልጣን ከበረኒስ የባሕር ወሰመጥ 24° ዲግሪ በስተሰሜን እስከ የእጣኑ ሀገር ሕንድ ውቅያኖስ ከዚያም እስከ ሶፎላ 20° ዲግሪ ደቡብ ላቲቲዩድ ይደርስ ነበረ። በዚሁ ቦታ የብዙ ሳይንቲስቶች እምነትም ከንእሱ ውስጥም በመጨረሻ ጊዜ የብራቲሽ ሙዝየም ሰራ አስኪያጅ የነበረ ሚቹ ሚስተር ቤንት ባለበት፣ በመጸሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው አፈር የሚባለው ምስጢራዊ ቦታ ንግሥተ ሳባ ወደ ንጉሠ ሰለሞን ወደ ኢየሩሳሌም ሰመሄድ እንድትችል መርከቦች የተሰሩበት መሆኑን ገምቷል"። ስለዚህ ኢትዮጵያውያን ነገሥታት እነ አጼ ይስሐቅ ወደ ደቡብ ያመሩበት የነበረ ሀገር የቅድመ አያቶቻቸው ይዞታ የነበረ መሆኑን በማስታወስ የሆናል።

በነ አጼ ይስሐቅና አጼ ዘርአ ያዕቆብ ዘመን መንግሥት የኢትዮጵያ ስፋት ሉካ ደይ ሳቤሲ [2] እንደሚከተለው ይገልፃል።

[1] Perini Mereh-Melash (Al di qua del Mareb)
[2] Luca Dei Sabellil VII p. 15-17

1. ኢትዮጵያ በሰሜን ወሰኗ እስከ ምፅዋ ይደርሰ ነበር፡፡ ሐማሴን፣ ሰራዬ፣ እክለጉዛይ እውራጃዎች እስከ ቀይ ባሕር ድረስ የባሕር ኃጋሽ መንግሥት አካል ነበሩ፡፡ ዋና ከተማ ድባሩዋ ነበረች፡፡ ሳሄልና ባርካ በቁጥጥሩ ስር ነበሩ፡፡

2. ትግራይ ዋና ከተማ አክሱም ሆኖ በትግራይ መኩንን የሚታዘዝ ነበረ

3. ሰሜን አፋርና ደቡብ አፋር (አዋሳ)

4. ዳሞሮ (ጨርጨር)

5. ባሌ ከዛሬዋ እርሲ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ የሚደርስ በዚህ በኩል የኦሮሞ ከስተት ባያጋጥም ኖሮ የከርስቲያኖች ፖለቲካዊ መስፋፋት መቋቋም የሚችል ተቃዋሚ ኃይል አልነበረም

6. ፋጢጋር ከባሌ በስተምሥራቅ ከመካከለኛ አዋሽ ወንዝ እስከ ዋቢ ወንዝ ምንጭ የሚያጠቃልል

7. አይ ወይንም ወድ ይባል የነበረ ከፍለሀገር ግእከሉ በዝዋይ ሐይቅ አካባቢ ነበረ፡፡ በዚህ አውራጃ በዛሬ አጠራር ሰልጤ የተባሉ ቋንቋቸው ከሐረሪ የሚቀራረብ ጉራጌዎች ይኖራሉ፣ አመጣጣቸውም ከጥንታዊው አክሱም መንግሥት ነው፡፡

8. ከወደ በስተደቡብ ከዝዋይ ሐይቅ እስከ አባያ ሐይቅ ሱፍጋናና ቡዛም የተባሉ ሁለት ትናንሽ መንግሥታት ነበሩ

9. በስተደቡብ ኮይራ ነበረ ለመንግሥት ግብር የሚከፍለው ለወታደሮች የሚያገለግሉ ፈረሶች በማቅረብ ነበረ፡፡ የሚገኘውም ከላይኛው ጁባና ከአባያ ባሕር ሐይማ መሐል ነበረ እስከ አስቴፋኒያ ሀይቅ ከንያን የሚያጠቃልል ነበረ

10. ወላሞና ጋሞ በንጉሥ ይስሐቅ ዘመን ጊዜ የተቀላቀሉ ከአባያ ሐይቅ በስተምዕራብ የሚገኙ ናቸው፡፡ እነዚህ ግዛቶች ሁሉ የታወቀ ተቃዋሚ የተደራጀ ኃይል ስላልነበሩ አሮሞዎች ከኢትዮጵያ ባየነንዋቸው ወሰናቸው እስከ ተፈለገ ሩቅ ሊዘልቅና ሊስፋፋ ይችል ነበር፡፡

11. በስተምዕራቡ በአጼ ይስሐቅ ወደ ግእከላዊ መንግሥት የተቀላቀሉ ትናንሽ መግሥታት ነበሩ ከነሱ ውስጥም እናሪያ /ሊሙ/ በሻ (ጅማ አባጅፋር) ወዘተ... ይገኙባቸዋል

12. በታችኛው እሞ ሰፊ የቾንጆር መንግሥት ነበረ

13. በስተሰሜን ከንባታ ነበረ፡፡ ከእሞ በስተግራ እስከ አቢያታ ሀይቅ

14. ከከንባታ በስተሰሜን ከላይኛው አዋሽ እስከ እሞ በጉራጌ ሹም የሚታዘዙ 1000 በሬዎች ግብር ለመንግሥት የሚከፍል የጉራጌ መንግሥት ነበረ

15. ከጉራጌ አዋሳኝ የሀዲያ ሱልጣን እማዝ ነበር

16. ከሐዲያ እስከ ሸዋ አለማሰ ቱጋር የሚባሉ ትናንሽ መንግሥታት ነበሩ

17. ኪጋንዝ በስተምዕራብ ትልቁ ዳሞት ነበረ

18. በስተምዕራብ በዛሬዋ ወለጋ ቢዛሞ የሚባል መንግሥት ነበረ

19. ከዲዲላ ወንዝ እስከ አባይ ወንዝ ጋፋት ነበረ

20. አባይ ተሻግሮ ጎጃም ይገኛል

21. ከማና ሐይቅ እስከ ተከዜ በጌምድር

22. በዛሬዋ ጎንደር ዙሪያ ደምብያ ነበረ

23. ወደ ሰሜን ዐለምቲ፣ ዐሌ፣ ወልቃይት፣ ሰሜን፣ ማዘጋዝ፣ የተባሉ ከጥንት ጀምሮ አገውና ፈላሻ የሚኖርባቸው ናቸው፡፡

24. ከተከዜ ወንዝ በስተሰሜን ስለዋና አበርጋሌ ይገኛሉ

25. ወገራትና እንደርታ አውራጃዎች ከጥንት ጀምሮ ራሳቸውን የቻሉ ራስ ገዝ አስተዳደር መብት የተሰጣቸው ነበሩ

26. ከንደርታ በስተደቡብ ላስታ

27. ከላስታ በስተምሥራቅ እንጎት የዛሬዋ ወሎ አብዛኛውን የሚያቃልል

ከሞላ ጉደል የኢትዮጵያ አስተዳደር እስፋፊል ካርታ ይሄንን የሚመስል ሲሆን ስፋቱ ከዘሬዪቱ ኢትዮጵያ በጣም የሚበልጥ እንደነበረ ብዙ ማስረጃ ባይኖርም የኢትዮጵያ ግዛት ክንያም ያጠቃልል እንደነበረ የሚጠቁም 200 ዓመት ከአጼ ይስሐቅ ዘመነ መንግሥት በኋላ በአጼ ፋሲሊደስ ዘመነ መንግሥት በኋላ የ'ሞምባሳ Mombassa ንጉሥ በኢትዮጵያ መንግሥት የሚታዘዝ መሆኑን ሱሳ ደይ ሳበሊ[1] ገልፀዋል፡፡ እንደፈረንጆች ቃል አገላለፅ የኦሮሞ ፈኖሚኖን /Oromo phenomenon) በኢትዮጵያ ታሪክ ባያጋጥማቸው ኖሮ ጀግኖች አባቶቻችን በእነ አጼ ይስሐቅና አጼ ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ግዛት እንደ አክሱማውያን እስከ ሶርላ ባይደርስም ክንያንና ደቡብ ሶማሊያ የሚያጠቃልል እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ዘልቆ እንደነበረ፣ ይሽውም ስ200 ዓመት ቀጥሎ እንደነበረ ፈላሻይ የተጠቀሰው የታሪክ ግስረጃ ያመለክታል፡፡ የኦሮሞ ፈኖሚኖን ያልኩበት ምክንያት የኦሮሞ ወደ መሀል ሀገር መስፋፋት የውጭ መረራ አይባልም ወይንም በአንድ ሀገር ውስጥ በሁለት ጎሳዎች ወይም ክፍለ ሀገሮች የተደረገው እርስ በእርስ ጦርነት አይባልም፡፡ ከላይ ከአንደኛ እስከ 27ኛ ተራ ቁጥር የጠቀስኳቸው በኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦችና ክፍላተ ሀገሮች ካርታ የኦሮሞ ስም አልነበረም፡፡ የኦሮሞ ከስተት የመጣው ከተጠቀሰው ዓ.ም. በኋላ ነው፡፡ አሁን የሚታየው የኦሮሞ አሰፋፈር ከምሥራቅ ኢትዮጵያ ሐረርጌ እስከ ምዕራብ ኢሉባቡር ሊሉች ሕዝቦች ሰፍረውበት የነበሩ መሬት መሆኑን እንረዳለን፡፡ ይሽውም የኦሮሞ ከስተት በኢትዮጵያ ልዩ ያደርገዋል፡፡ ዳግማዊ ምኒልክ የሚወክለው የአማርኛ ቋንቋ በደቡብ በምዕራብ ኢትዮጵያ ወረራ በመፈጸም ሌሉች ሕዝቦች በቋንቋቸውና በባሕላቸው እንዳይጠቀሙ አድርገዋል የሚል ወቀሳ በአሁኑ ጊዜ ሲሰነዘር ይሰማል፡፡ ከዳግማዊ ምኒልክ ጀምሮ ለአስተዳደር እንዲያመች የመንግሥት ቋንቋ አማርኛ ሰለነበረ በአገሪቷ አስተዳደር በሚመለከት በተዘረጋው በጣም ዝቅተኛ የአስተዳደር መዋቅር የሌሉች ሕዝቦች ቋንቋዎች ሳይነኩ ከጥንት ጀምሮ እንደነበረ ሁሉ በአማርኛ ቋንቋ መጠቀም ያስተዳደር ቋንቋ ሆኖ ቆየቶ ነበር፡፡

የአማርኛ ቋንቋን ለማሰፋፋት ምክንያት የሆነው ግን በይበልጥ ኪኢጣሊያ ወረራ በኋላ ቢኃይለሥላሴ ጊዜ ትምህርት ቤቶች ስስተስፋፋ ይሆናል፡፡ የሌሉች ሕዝቦች ቋንቋና ባሕል ግጥፋት ብቻ ሳይሆን የሕልውናቸውም ግጥፋት የተፈጸመው በአሮሞች የጋዳ አስተዳደር ዘዴ ነው፡፡ የኦሮሞ ቋንቋ በአጭር ጊዜ በመላው ኢትዮጵያ መስፋፋት ሁኔታ በቂ ማስረጃ ባይኖርም ምናልባት ቀደም ብለው ስፍርበት የነበረውን ሕዝብ በመሉ እየፈጁ ማስለቀት ላይሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን እንድ ሕዝብ የሌላ ሕዝብ ቋንቋና ባሕል በአጭር ጊዜ ውስጥ በስላም ስለግይተበል በከፊል ነዋሪ

[1] Luca Dei Sabelli ibd V 2 p 384

ሕዝቡን እየጨረሱ ቋንቋውንና ባሕሉን የመቀየር ሂደት እንደተካሄደ እያጣራጥርም። በዚሁ መሠረት አሁን የአርሞ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ሕዝቦች የአንድ ጎሳ አባል ሳይሆኑ የብዙ ጎሳዎች ቅልቅል መሆናቸውን ለመረዳት እያስቸግርም። ሰለዚህ ከአግርኛ የበለጠ የአርሞ ቋንቋ የግስፋፋት ዕድል አግኝቷል ለማለት ይቻላል። ብዙዎቹ አሁን በአርምኛ ቋንቋ የሚጠቀሙ ሕዝቦች የድሮ ቋንቋቸው አግርኛ ነበር፣ ወይንም የሲዳማ ቋንቋ ነበረ ሊሉችም በደቡብ ምሥራቅና ምዕራብ የሚገኙ የአርሞኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች አሁን ልናውቃቸው የማንችል የተለያዩ ቋንቋዎች እንደነበሯቸው መገመት እያዳግትም። በሰሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያም እንስተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች የአርሞኛ ቋንቋ ተቀብለው ስለነበረ አሁንም ይጠቀመብታል።

አጼ ምኒልክ 450 ዓመት ከነ አጼ ይስሐቅ ዘመን መንግሥት በኋላ ኢትዮጵያ የቀድሞ ግዛቷ በከፊል እንድታገኝ በማድረጉ የሚደነቅ አይደለም። ወገን ከወገኑ እንዲቀላቀል በማድረጉ ያስመሰግነዋል እንጂ አንዳንድ ወገኖች እንደሚሉት ወራሪ አያሰኝም። ሐቀኛ ኢትዮጵውያን ምኒልክን የሚወቅሱት እንደ አጼ ይስሐቅ በይላን፣ በርበራን፣ ሞቃድሾን ችላ በማለት አለመያዙ ነው። በተለይም ኢርትራ ለኢጣሊያ ገፀ በረከት መስጠቱ በታሪክ ሲያስወቅሰው የሚኖር ስለሆነ ሀገሩን የሸጠ ከዳተኛ ብቸኛ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ በሚል አጠራር ሲያስታውሱት ይኖራሉ።

5. ንግሥት እሌኒ

የኢትዮጵያ መንግሥታት እሰላሞችን ለማጥፋት በኃይል የማይቻል መሆኑን እየተረዱ ስለመጡ የክርስቲያን ግብጾችና ካቶሊኮች ድጋፍ መፈለግ ጀመሩ። ከዓረብ መንግሥታትም ቢቻል ወዳጅነት መፍጠር ካልተቻለም ገለልተኛ አቋም እንዲይዙ ማድረግ ተሞክረዋል። የዓረብ መሪዎችም በሰላማዊ መንገድ አብረው በሰላም ለመኖር እንዲችሉ ተሞክሯል። የዚሁ ፖሰቲካ ቀስቃሽ ንግሥት እሌኒ ነበረች። እዬ ዘርአ ያዕቆብም ቢሆን ከእስላም ጋራ በሰላም ለመኖር በመፈለግ ከሀዲያ አንድ ሚስት አግብቶ ነበር። ንግሥት እሌኒም ራሷ በልጅነቷ እስላም ነበረች። የአጼ ዘርአ ያዕቆብ ልጅ አጼ በእደ ማርያም ሁለት የእስላም ሚስቶች ነበሩት ንግሥት እሌኒና ንግሥት ሮማነ ወርቅ። እነሱም ከአዳል ሱልጣኖች የሚወለዱ ከታወቁት የየመንና የሀድራሞት የመንግሥታት ዘሮች ይዛመዱ የነበሩ ናቸው። በተለይ ንግሥት እሌኒ በዘርአ ያዕቆብ የተተኩ አራት የኢትዮጵያ ነገሥታት በሙስ መንገሥት በውጭ ጉዳይ አመራር ተሰሚነት አግኝታ ነበር። ወደ ዓረብ ሀገር የሚመላለሱ አርሚን፣ ዓረብ፣ ሕንድ፣ ግሪክ፣ ኑጋዲዎች መረጃ እንዲያቀብሏት ታደርግ ነበረ። 500 ሰዎች አባል የነበረው አንድ የኢትዮጵያ መልእክተኛ ቡድን ወደ ግብፅ ሱልጣን ተልኮ ነበረ። በታላቁ ሥነ ሥርዓትና ሰልፍ በካይሮ በታየበት ጊዜ ተቃውሞ ከሕዝቡ ስለተቀሰቀሰበት በባለስልጣኖች እርዳታ ብቻ ከእደጋ ሊያመልጥ ችሏል። ንግሥት እሌኒ ክርስቲያን ብትሆንም ከአዳል ቤተሰቦቿ ግንኙነት አላቋረጠችም ነበር። ጥረቱንም ከንቱ አልሆነም። የአዳል ሱልጣን የነበረው መሐመድ ጦርነት ከማድረግ ይልቅ በሰላም አብሮ መኖር ፈላጊ ሆኖ ነበረ። በጋብቻ በመተሳሰርም በአንድ ሆኖ በሰላም መኖር ደህና ውጤት ያስገኘ መስሎት ነበር። ነገር ግን የሱልጣኖች ስልጣን ስም ብቻ ሆኖ ራሳቸው ስልጣን የጨበጡ እሚር የተባሉ ከክርስቲያን ጋራ በሰላም መኖር የማይዋጥላቸው ሰዎች ተፈጥረው ነበረ። የሰላም ጥረቱም በይበልጥ የከሸፈው በኢውሮጳ በክርስቲያኖችና በዓረቦች እስላሞች መካከል

ይደረግ የነበረው ጦርነት ተፋፍሞ በነበረበት ወቅት በሀገራችንም ስሰተዛመተ ነበር።

ወቅቱ ኤሮውጳ ግዛቷ ወደ ሲላ የዓለም ክፍሎች ማስፋፋት የጀመረችበት ነበረ። ከኤውሮጳውያን የግንባር ቀደም በመሳው የኤውሮጳ ስም የፖርቱጋል ዓላማ የአፍሪካ የባሕር ጠረፍ ዙሪያ ለመቃኘት ነበረ። የሮማ ጳጳስ የፈረንሲ ጉባኤ የጠራ ዓላማውን ግማደገፍ ማንኛውም የአፍሪካ ወደብ በፖርቱጋል የጦር መርከቦች ከተነበኘ የፖርቱጋል እንዲሆን ስለፈቀዱ ፖርቱጋሎች ጥረታቸውን በመቀጠል ምዕራብ አፍሪካን ዞረው ወደ ምሥራቅ አፍሪካ ደረሱ። ከደቡብ ፖርቱጋሎች ቀይ ባሕር ሲደርሱ ቱርኮችም ከስሜን ግዛታቸውን እያስፋፋ ቀይ ባሕር ደርሰው ነበር። በ1517 ዓ.ም. ቱርኮች በድል አድራጊነት ካይሮን ያዙ። በዚሁ ጊዜም ሱዋኪምና ምጽዋን ተቆጣጠሩ። በቀይ ባሕር ፖርቱጋሎችና ቱርኮች በጭካኔ ይፋጁ ነበረ። በኢትዮጵያም በአዳል ሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ጦርነት እንዲቀሰቀስ አስተዋጻ ነበረው።

6. አፄ በእደግርያም

አፄ በእደግርያም የክርስትና ሃይማኖትን ለማስፋፋት በመጀመርያ ጦርነት ያካሂደው በሰሜን፣ በጸለምቲ፣ የነበሩ ፈላሾችና በዶባ ነበረ። በስተመሥራቅ የአዳል ሱልጣን መሀመድ ወደ በእደግርያም መልእክተኛ ልኮ ግብር እየከፈለ የበላይነት እምኖ በሰላም ለመኖር ስስተሰግግ ጊዜያዊ ሰላም ሰፍኖ ነበር። የአዳል ሱልጣን መሐመድ በ1470 ዓ.ም. ሲሞት ልጁ ኢብራሂም ሲተካ ስልጣኑ በኤ፟ሚሮች እጅ ሆኖ ነበር። ሱልጣኑ ለስም ብቻ ተቀምጠ ነበር። በ1474 ዓ.ም. ከአዳል ጋራ በተደረጉ ጦርነቶች ክርስቲያኖች ለመጀመሪያ ጊዜ ሽንፈት ገጠማቸው በአደግርያም ከሞሞቱ በፊት 1478 ዓ.ም. ለግብፁ ሱልጣን በሰላም ለመኖር ውል ለማድረግና ወደ ኢየሩሳሌም ለመሳለም የሚሄዱ ለኢትዮጵያውያን ምእመናን እርዳታ እንዲደረግላቸው ለመጠየቅ መልእክተኛ ልኮ ነበር። መልእክተኞቹ ከግብፅ ቤተክርስቲያን ወደ ፊልስጤም እምርተው ኢየሩሳሌም ሲደርሱ የኢትዮጵያ መነኮሳት ወደ ሮማ እንዲሄዱ ገፋፋቸው። በዚሁ መሠረት መልእክተኞች ወደ ቆስጠንጥኒያ በሚሄድ ፋንታ ወደ ሮም አመሩ። ኖቪምንበር 1481 ዓ.ም. የሮማ ሲቀ ጳጳ፟ሲስቶ4ኛ. በታላቅ ሥነ ሥርዓት ተቀበሏቸው። 1ኛ. አባ ፍራንችስኮ ሳጋራ 2ኛ. አባ ጆቫኒ ዲ ካላብሪያ 3ኛ. አስተርጓሚ ሆኖ ከኢየሩሳሌም አብሮ የመጣ አባ ጆቫኒ ባቲስታ ዲ ኢሞላ የሚባሉ ሚሲዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ ተሳኩ። አባ ሳጋራ ካይሮ ሲደርሱ ሞተ፣ ሁለቱ ግን ኢትዮጵያ ደርሰው ንጉሥ አስክንድር ወደ አለበት ደረሱ። ነገር ግን አባ ጆቫኒ ዲአሞል ወደ ንጉሡ መቅረብ 8 ወር ጠብቆ ሳይሆንለት ሲቀር አባ ጆቫኒ ባቲስታ ዲአምሪ ወደ ኢየሩሳሌም ላከው የሚሲዮናውያንም ተልኮዋቸው ውጤት አልባ ሆኖ ቀረ።

7. አፄ አስክንድር

በበእደ ማርያም ምትክ አስክንድር የአደ ማርያምና የሮማን ወርቅ ልጅ ተተካ። በአደግርያም የሞተው በ1478 ዓ.ም. ነበር። አስክንድርም አንድ ጊዜ ብቻ በአዳል ያልተሳካ ጦርነት አድርጎ በ1495 ዓ.ም. ዐረፈ። በአስክንድር ዘመን መንግሥት በፖርቱጋል ንጉሥ ዮሐንስ ሁለተኛ አልፎንሶ

ዳ ዳይጎ ፒድሮ ዳ ኮቪልሃም የ ባሰው የሐበሻ መንግሥት የት እንደሚገኝ ፈልገው እንዲያገኙ በ1487 ዓ.ም. ትዕዛዝ ሰጧቸው ወደ ግብፅ አመሩ። የሐበሻ ሀገር በአፍሪካ ይኑን በእሰያ የማይታወቅ ሰለነበረ ካይሮ ደርሰው ከሱዋኪም አደን ቢገዙም የሚነግራቸው ሲያጡ እንዱ ወደ አፍሪካ እንዱ ወደ እሰያ ሄደው እንዲፈልጉ ተሰማሙተው አልፎንሶ ዳ ፓይቫ በርበራ ደረሰ፣ እዚያው ተገደሰ። ፒድሮ ዳ ኮቪልሀም ግን ሕንድ ገባ፣ ተመልሶ ወደ አፍሪካ በመምጣት የምሥራቅ አፍሪካ የባሕር ጠረፎች ገብኝቶ ካይሮ ገባ። እዚያው የጓደኛው ሞት ሰማ። ከፖርቱጋል ንጉሥ አዲሰ ትዕዛዝ ሰላልተሰጠው ወደ ጅዳ ሄደ። በመጨረሻ በደላ ገባ፣ ከዚያም ጦርነት የሚደረግበት የአዳል ሀገር በድፍረት አቋርጦ ንጉሥ እሰክንድር ወደሚገኝበት ደረሰ። ንጉሡ ከራሳቅ ከብር ተቀብሎ ወደ ዋና ከተማው ወደ ተጉሰት ወሰደው። ወደ ሀገሩ እንዲመሰስ ግን አልፈቀደሰትም። እሰክንድር እንደሞተ አለመግባባት ተፈጥሮ የእሰክንድር ልጅ የ7 ዓመት ሕፃን ቢነግሥም ሰሰሞተ፣ የእሰክንድር ወንድም ናኦድ ንጉሥ ሆነ። የአዳል ሱልጣን በናኦድ ጊዜ የሰላም ጥረቱ ቢቀጥልም ግፋዲ የተባለው የሐረር ኤሚር ግን በክርስቲያን መንግሥት በየዓመቱ በፋሲካ ዖሙ ጊዜ ጦርነት እየቀሰቀሰ ክርስቲያኖችን እየወሰደ በባርነት እየሸጣቸው ሰለነበረ ከብቶችም ይዘርፍ ሰለነበረ ንጉሥ ናኦድ ጦርነት ገጠማቸው በሐሰት የመሸሽ የጦርነት ሰልት በመጠቀም ክቦ የሐረር ኤሚር ወታደሮቹን ፈጃቸው። የግሕፋድ መሸነፍ የእሰላም ቅዱሰ ጦርነት ጅሀድ መንፈስ አቀዘቀዘው የአዳል ሱልጣንም ከንጉሥ ናኦድ ጋራ ሰላም ሰሰፈጠረ ሰብዙ ዓመታት በምሥራቅ በኩል ሰላም ሰፍኖ ነበር።

8. አፄ ልብነ ድንግል[1]

ንጉሥ ናኦድ ሲሞት በ1508 ዓ.ም. ልብነ ድንግል ብቸኛ ልጁ ሲነግሥ ሀገሪቱ ሰላም አግኝታ ነበር። በፖሰቲካ በኩልም ከፖርቱጋል ጋራ ወዳጅነት በመፍጠር መልካም እርምጃ የታየበት ወቅት ነበር። ልብነድንግል ልጅ ሰለሆነ የመንግሥቱ አመራር በእናቱ በንግሥት እሌኔና በታዋቂው የነበረው ሰው ወሰን ስገድ ይመራ ነበር፣ ተቃውሞም አልነበረውም። በልብነድንግል ዘመነ መንግሥት 60 የውጭ ሀገር ዜጎች በኢትዮጵያ ይኖሩ ነበር። ንግሥት እሌኔ በመንግሥት ሞገዚትነት በነበራት ተደማጭነት የውጭ ሀገር ሰዎችም ምክር በመቀበል ከፖርቱጋል ጋራ ወዳጅነት ሰማጠናከር ትጥር ነበር። የክርስቲያን መንግሥት በእሰላሞች ላይ በየጊዜው እንዳይወረር ያለው አማራጭ የባሕር በሮች ከእሰላም መንግሥታት እንዳይገናኙ ማድረግ ነበር። ይሽንም ማድረግ የምትችለው እንደ ፖርቱጋል ጠንካራ የጦር መርከቦች ያሳት መንግሥት መሆን ይገነዘባል። የፖርቱጋል መልእክተኛ ፒድሮ ዲ ኳቪልሃም ይሽንን ሐሳብ በመደገፍ የባሕር ወደብ ኩተሞች ለፖርቱጋል ከልተሰጡ እርዳታ ለማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል የሚል ሐሳብ አቅርቦ ነበር።

ይህ ሁሉ ሐሳብ ለፖርቱጋል ንጉሥ ለማቅረብ ማቴዎስ የተባለው አንድ አርመናዊ መልእክተኛ ለንግሥት እሌኔ የቅርብ ወዳጅ የሆነው ወደ ፖርቱጋል ለመላክ ተወሰነ። ዘመኑ 1510 ዓ.ም. ነበረ። የልብነ ድንግል ሞገዚትነት ዘመንም 2ኛ ዓመት ነበረ። ማቴዎስ በመጀመሪያ የሄደው ወደ ሕንድ ነበረ። ከዚያም በመርከብ ተሳፍሮ ከ3 ዓመት በኋላ ስ1513 ዓ.ም.

[1] Luca Dei Sabelli ibd V 2 p 43

ሊዝቦን ገባ። ማቴዎስ መካና መዲናን አቃጥሎ ኢየሩሳሌምን ነፃ ለማውጣት የሚል እቅድ ለፖርቱጋል ንጉሥ ሐሳብ አቅርቦ ነበረ። የፖርቱጋል ንጉሥ አማኑኤል በታላቅ ክብር ነበረ የተቀበሰው። የሮማ ጳጳሰም ሊዮን 10ኛ መልእክተኛው ማቴዎሰን ተቀብሰው አነጋግረውታል። 3 ቂሶችም ከፖርቱጋል መልእክተኞቹ ጋራ ተቀላቅሰው ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄዱ አዘዙ። ልብነ ድንግል በ1516 ዓ.ም. ከሞገዚትነት ወጥቶ ሰልጣን እንደያዘ የፖርቱጋል መልእክተኞች አፕሪል 7/1520 ዓ.ም. ምዕዋ ደረሱ። በመጀመሪያ የደረሰ ቢዚን ቂሶች ምዕዋ ድረሰ ሄደው ተሳናኟቸው። ተጥሰውም ባሕር ነጋሽ ዶሪ ከአጼ ናኦድ እናት ሞጋሳ ወንድም ምዕዋ ሄደው ተቀበሏቸው። የክረምት ዝናም በመፍራት መልእክተኞቹ ደብረ ቢዛን ሄደው ተቀመጡ። እዚያው እንዳሉ ማቴዎሰ ታሞ ሞተ። የሚተሳሰፍ በሽታ እንዳይሆን ፈርተው መልእክተኞቹ ወደ ድባሩዋ ሄዱ። አከተህር 1520 ዓ.ም. ፖርቱጋሎቹ ደብረሲባኖስ ሸዋ ደርሰው ከንጉሡ ጋራ ተገናኙ። ፖርቱጋሎቹ ውድ ስጦታ ሰንገሡ አበረከቱ፣ ንጉሡ ግን በሰጠታቸው አልተደሰተም ነበር። ንጉሡ ይጓጓ የነበረው እሰላሞች ከግሪብ ሀገሮች የሚተርብላቸው ዘመን ያፈራቸው የጦር መሣሪያዎች ነበረ። የንጉሡ የተሰላ አተባበል ፖርቱጋሎችን እያሰቀየማቸው ነበር። ንጉሡ ከፖርቱጋሎች የሚፈልገው ሰዋኪም ምዕዋና ዘይላ በፖርቱጋል እንዲያዙ ብቻ ነበረ።

በሌላ በኩልም ፖርቱጋል ኢትዮጵያን ወራ ትይዛለች የሚል ፍራቻ ነበረ። ንግሥት እሌኔ ከኤውሮጳውያን ጋራ መቀራረብ ትጥር የነበረችው ከእሰተዳደሩ ተወግዳ በዕድሜም ገፍታ ሰሰነበረ ጎኟም ተሰሚነት እጥፉ ትኖር ነበር። በዚህ ምክንያት ኢትዮጵያ አፋጣኝ ቅርብ ግንኙነት ከፖርቱጋል ጋራ ሰመፍጠር ከማንኛውም ከእሰላሞች የሚደርሰባት አደጋ የሚያድናት ውል ሰማድረግ ዕድል አመሰጣት። መልእክተኞቹ ቁምነገር ሳይሰሩ በኢትዮጵያ 6 ዓመት ተቀምጠው ኤፕሪል 28/1526 ዓ.ም. ከምዕዋ ወደ ሀገራቸው ተነሱ። ጆቫኒ ቢርሙደስ ሐኪም በኢትዮጵያ እንዲቀር ተደረገ። እሰላሞች ከባድ ወረራ በኢትዮጵያ ላይ የፈፀመብት ጊዜ ተቃርቦ እንደነበረ ማንም ሰው አልተረዳውም ነበረ።

አጼ ልብነድንግል በእሰላሞች ላይ ባገኛቸው መጠነኛ ድሎች ተዝናንቶ ከመጠን በላይ የራሱ ኃይል ሰለገመተ የንግሥት እሌኔ የበሰሰ የውጪ ፖሰቲካ መመሪያ ችላ በማለቱ ኢትዮጵያ ወደ ጥፋት አፋፍ ደረሰች። በኤሚር ግራዝ ጊዜ የሚመሩ አዳሎች በአጼ ልብነድንግል የደረሰባቸው ሽንፈት ለመቀበል በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ሲያደርሰባት በዘይላ በኩል አደጋ ይሰነዘርባት ነበር። ከመካ ከሌሎች አዳሎችም የጅሀድ ጦርነት ቅሰቀሳ ይደረግባቸው ነበረ። የጦር መሣሪያዎችና ተዋጊዎች ለእሰላሞች ይላክላቸው ነበረ፣ አዳሎችም ወጣት ሌትና ወንድ ባሮች በማድረግ ወደ ገበያ ወሰደው በመሸጥ የጦር መሣሪያ ይገዙ ነበር። ሰግሕፋዝ ከብር አንድ የጦር አርማ ልከው ነበር፣ አዳሎች ወደ ፋጢጋር በማምራት ወረራ ፈጸሙ። አጼ ልብነድንግል በአጼ ናኦድ የጦርነት ዘዴ በመጠቀም ከበባ በማዘጋጀት አዳሎች ወደ ፊት እንዳይጠጉ ካደረጋቸው በኋላ ማምለጫ መንገድ በመዝጋት ፈጇቸው። ግሕፋዝ ማምለጫ ሲያጣ ከአንድ ገብረ እንድሪያስ ከተባለው ቂሰ ጋራ በጎራዴ ትግል ገጥሞ ቂሱ የግሕፋዙን አንገት ቆርጦ ለልብነ ድንግል አበረከተ። በዚሁ ጦርነት ብቻ 12,000 አዳሎች ሞተዋል ይባላል። ይህ የመጨረሻው የክርስቲያኖች ድል ነበረ። አጼ ልብነድንግል ዘመቻውን በመቀጠል የአዳል ሀገርን ወረው ወንድ ሌት ሳይለይ በመገደል ባሮችን አደረጋቸው። ከዚህ በኋላ የእሰላም ኃይሎች ዳግም ተመልሰው ለኢትዮጵያ

የሚያሰጋት ጠላት አይሆኑም ተብሎ ተገምቶ ነበረ። ድሉም በመላው ኢትዮጵያ ተከብሯል። እንደተባለውም በሚቀጥሉት ዓመታት ለኢትዮጵያ የብልፅግና የሰላም ዘመናት ነበሩ። አሕመድ ሺል ኢብራሂም ግራኝ በዓረቦችና በቱርኮች እየተረዳ ኢትዮጵያን እስላማዊት ሰግድረግ በነበረው ፍላጎት በዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች ተደራጅቶ በከፈተው ጦርነት ሳይቋረጥ በየጫካውና በየተራራው ለ20 ዓመታት እየተደበቀ ሰሃይማኖቱ በመዋደቅ ኢትዮጵያን ከሞት አፋፍ ያዳኗት እጹ ልብነ ድንግል ነው። በእንግሩ በዘይላ አሚር ማሕፉዝ በፋጢጋር (ናዝሬትና ሞጆ አካባቢ) ያገኘው ከፍተኛ ድል ተዝናንቶ በቸልተኝነት ኢትዮጵያ ለሞት አፋፍ የዳረጋት እጹ ልብነድንግል

ግራኝ የሚመሰምላቸው ወታደሮች አብዛኛዎቹ ከሰማሌ ሲሆኑ የሚመጡለትም ሰዝርፊያ ብቻ ነበረ። ዘርፈው ሃብት ሲያገኙ ወደ ሀገራቸው ሰመመሰስ ነበረ ፍላጎታቸው። ግራኝ ጥሰውት እንዳይመለሱ ብዙ ትግል ሰድረግ ነበረበት። በእጹ ልብነድንግል ሽንፈት ከደረሰባቸው ጀምሮ የአዳል ኢሚሮችና ሱልጣኖች እርስ በእርስ እየተጣሉ ከባድ ውድቀት ደርሰባቸው ነበር። ግራኝ ለልጣን እንዳይዝም ኃይሰኛ ተቃውሞ እጋጥሞት ነበር። ግራኝ በቀላሉ ሊሰሳሰብ የሚችል ጠንካራ የሰው ኃይል አልነበረውም። እጹ ልብነድንግል እንደ አምደጽዮንና ዘርአያዕቆብ ሳይቀደም ቀድሞ በማጥቃት የጦር ስልት በመጠቀም ጠላቶቹን ቢከታተል የሚወዳደረው ኃይል ሊፈጠር አይችልም ነበረ። ይሽንን ባለማድረጉ ግን ግራኝ እስኪጠንክር ድረስ ዝም በማለቱ በ1525 ዓ.ም. ሰመጀመሪያ ጊዜ ከርስቲያኖች በዳሞት፣ (ጨርጨር) ሽንፈት ገጠማቸው። እንደገና በ1527 ዓ.ም. ክርስቲያኖች ስሰተሸነፉ የቤተመንግሥት ልጆች የሚገኙባቸው 400 መቶ ልጆች ሰባርነት ተወሰዱ። ግማሾቹ ለየመን እሚር ሱልጣን በባርነት ገፀበረከት ተሰጡ። ብዛት ያለው መሣሪያ ፈረሶች ድንኳኖች ተማረኩ። ግራኝ በፋጢጋር በኩል ወደ ተጉሰት ድንጉኛ ወረራ እድርጉ ንጉሥን ሰመያዝ አቅዶ ነበር። ወታደሮቹ ስለተቃወሙት እያለቀሰ ተመለሰ። ወታደሮቹን ለማሰልጠን ብዙ እንደሚቀረው ተረዳ። በ1528 ዓ.ም. ግራኝ ወደ ይፋት ዘመቻ እደረገ፣ ብዛት ያላቸው እሰረኞች ተማረኩ፣ ከነሱ ውስጥም የቤተመንግሥት ሰለልት ነበረች። እሷ ግን 1775 ግራም የሚመዝን ወርቅ ሰጥታ ተሰቀቀች፣ በአንጸኪያ የነበረ ቤተክርስቲያን ተቃጠለ፣ በውስጡ የነበሩ ብዛት ያላቸው ወርቅም ግራኝና ተከታዮቹ ተካፈሉት። በ1529 ዓ.ም. ሽንብራ ኩሬ በተባለው ቦታ ግሮች 11 ቀን ሰአንድ ቀን ሙሉ በንጉሥ የሚመራው የክርስቲያን ሠራዊትና በግራኝ የሚመራው የእስላም ሠራዊት መካከል ጦርነት ተካሂዶ በቀኑ መጨረሻ የክርስቲያን ሠራዊት 12,000 ሰው ሞቱበት፣ ንጉሡ ሽሽቶ ወደ ኋላ ተመለሰ። የእስላም ሠራዊትም ብዙ ሰው ሞቶበታል። ከሞቱት ሹማምንቶች መካከል የትግራዩ ሩቤል፣ ወንድሙ ዐቅባ ሚካኤል በግራኝ እጅ የተገደለ፣ የሽሬ ሹም የጸለምቲ ሹምና የዐጋሚ ሹም ይገኙባቸው ነበረ። ኩተግራኩም መካከል የንጉሡ ሚስት ወንድም ተከለመድህን ነበረ። እሱ ግን 50 አውንስ ወይንም 18 ኪሎግራም ወርቅ ከፍሎ ተሰቀቀ። ግራኝ ብዙ ወርቅ ስለነበረ በዘረፈው ወርቅ 7 መድፎችን ከን ተኳጆች ዓረቦች ከዘይላ ገዛ። ፈረሶችና ሌሎች ተዋጊ ዓረቦችም ነበሩት። ግራኝ ለክርስቲያኖች አንዣዳ የሆኑ መሣሪያዎችን በመጠቀም በ1531ዓ.ም. ከክርስቲያኖች ጋራ ይፋት ውስጥ ጦርነት ገጠመ፣ ድልም ተጎናፀፈ። እንደገና ተሰርቶ የነበረ የአንጸኪያ ቤተክርስቲያን ተቃጠለ። እጹ ልብነድንግል ተስፋ ሳይቆርጥ እስላሙ የተባለው የጦሩ አዛዥ ወደ ዳውሮ

እንዲሄድ አዘዘው። በባለታሪክ ተከሰኢየሱስ የአንጎት (ወሎ) አገረ ገዥ የሚመራ ጦርም ለግጠናከሪያ ወደ ዳውሮ ተላከ። ነገር ግን ሁሰት ከክርስቲያን የከዱ ባለስልጣኖች የንጉሡ አቅድ ሰግራኝ ነገሩት፣ በዚሁ መሠረት ሁሰቱ የክርስቲያን ሠራዊት ሳይቀላቀሉ ግራኝ ገጠማቸው። ኢትዮጵያ ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ አልቂት ደረሰባት፣ አብዛኛው ትግሬዎች የሆኑ 130 ሹሞች በጦር ሜዳ ተገደሉባት ከነሱ ውስጥም የሽሬ፣ የጸለምት፣ የሐግሴን፣ የቤጌምድር ሀገረ ገዢዎች ይገኙባቸዋል። ከጦርነቱ በኋላ ግራኝ ለንጉሡ እጁን እንዲሰጥ ላከበት፣ የንጉሡ መልስ ግን በእጁ ይገኙ የነበሩ እስላሞች የጦር እሰረኞች በመግደል ነበረ፣ ጦርነቱም በጭካኔ ቀጠለ። የግራኝ ሠራዊት ሽዋን ወሮ ከዳር እስከዳር ተቆጣጠረ፣ ግለሰቦች ብቻ ሳይሆኑ እውራሽዎችና ክፍለአተ ሀገሮች ሰግራኝ እጃቸውን ሰጡ፣ ሃይማኖታቸውንም ቀየሩ። ብዙ ሐብት ተዘረፈ ከነሱ ውስጥም እስደናቂ የነበረው ሽፋኑ በወርቅ የነበረ በእንድ በደፋት ቤተክርስቲያን የተገኘው መጸሐፍ ቅዱስ ነበረ። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ክብደቱ ሁለት ሰዎች እንድ ላይ ሆነው ለማንሳት የሚያቅታቸው ነበረ። ጦርነቱ ከሽዋ ወደ አማራ ተዛውሮ ቀጠለ ከደብረብርሃን ወደ ሰሜን በሚያመራበት ጊዜ ይማም እግረ መንገዱ እንድ ድንቅ ቤተክርስቲያን እጋጠመው፣ ቤተክርስቲያኑ በወርቅ ያጌጠ ነበረ። የግታ ብርሃን ጨረር ወደ ቤተክርስቲያኑ በሚገባበት ጊዜ ወርቁ እንደ መብራት ያንፀባረቅ ነበር። ቤተክርስቲያኑን ለመገንባት 25 ዓመት ነበር የፈጀው። ከወርቅ ሌላ የቤተክርስቲያኑ ግድግዳ በሌላ ውድ ጌጣጌጥ የተዋበ ነበረ። ይማም እሁንም አወደመው ቤተክርስቲያኖችን እንዲዘርፉና እንዲያቃጥሉ ለየአንዳንዱ የግራኝ ሹማምንት ድርሻቸው ተከፋፍሎ ተሰጣቸው። ለግራኝ መካነ ሥላሴ ቤተክርስቲያን ደረሰው። በቤተክርስቲያኑ የተገኘው የወርቅና የጌጣጌጥ ብዛት ከተጠበቀው በላይ ነበረ። ግራው የውስጥ ግድግዳው ሁሉ በወርቅ የተሰሩ ነበሩ። እንድ ሺህ ወታደር ወርቁን ሰመንቀል ሰብዙ ሰዓቶች ተሰግርተው ነበረ፣ አስተርአየ ማሪያም በተባለው ቤተክርስቲያን በታቦቱና በሌላ መንፈሳዊ ቁሳቁሶች የነበረ ወርቅ 1000 አውንስ ማሰት 35 ኪሎግራም የሚመዝን ነበረ። በበእደማርያም የተሰራ የደብረ ነጎድጓድ ቤተክርስቲያን የእንድ ሰው ቁመት ያለው ቅስት እድናቆት ያተረፈ ተዘርፏል። ዋናው የንጉሡ ንብረት ፍሰጋ ሌላ የግራኝ ጦር ወደ ወሰጋ ተወሰዶ የነበረውን ወርቅና ሌላ ጌጣጌጥ እንዲሁም አልባሳት ከተደበቀበት ተገኝቶ በ500 ግመሎች ተጭኖ ተወሰዷል። የይማም ጦር ወደ እንጎት (ወሎ)፣ ሰግዖራት ሐይቅ የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ደረሰ። ከቤተክርስቲያኑ ወርቅ ለመዝረፍ 150 ሰዎች የመጫን እቅም ያላቸው ሶስት ትልቅ ጀልባዎች ወርቁን ሰመውሰድ ሦስት ዙር ወሰደባቸው። በደብረ እግዚአብሔር በ1342 ዓም ሳሰይፈ ዐረድ የተሰራ ቤተክርስቲያን የተገኘው ወርቅ ክብደቱ አንድ ሚሊዮን አውንስ ነበረ ማለት 35.000 ኪሎግራም ነበረ።

ግራኝ ወደ ደቡብ ክፍለ ሀገር ሀዲያ፣ ከንባታ፣ ወላሞ፣ እሞ፣ ዝዋይ፣ አባያታ፣ ጊቤ፣ እና ሪያ፣ ጋፋት ዘመቻውን በመቀጠል ዛላ በተባለው ቦታ በ1532 ዓ.ም. ባሸነፈ ጊዜ 3000 ክርስቲያኖች በጦር ሜዳ ሞቷል። የባሌ ሕዝብ በሙሉ የአሰልምና ሃይማኖት እንዲቀበል ተገደ የተቃወሙት ሁሉ ተገደሉ። ግራኝ ትግራይን ለመያዝ ያደረገው ጦርነት ከባድ ተቃውሞ ነበረ ያጋጠመው። በጦርነቱ 10,350 ሰዎች ተገድለዋል።

ግራኝ ሽሬ ሲደርስ በአባ ሳሙኤል ቤተክርስቲያን ያገኛቸው 500 ቀሳውስት ተገደሉ። እጹ ልብነድንግል በቤጌምድር ተራራዎች ተደብቆ

ስለነበረ ግራኝ ተከታትሎ በድንገት በእጁ ሊማርካት ያደረገው መከረ ከሸርበት ንጉሥ ሸሽቶ ማምለጥ ችሏል። ግራኝ ወደ ኢርትራ በማምራት ሀገረ ገዢው ተሰፋ ልዑል እሰመግዶ ቲዎድሮስ የሚባል ነበረ የሾመው። ነገር ግን ሕዝቡ በተስፋ ልዑል መሪነት የደፈጣ ውጊያ ሰግድረግ የግራኝ ታማኝ የነበረ ቪዧር አዶሌ የሀገሩ የበላይ አስተዳዳሪ ሆኖ ተሹሞ የነበረ ሳይቀር ገድሎ እንገቱን ቆርጦ ወደ አጼ ልብነ ድንግል ሰመሳክ ክባድ ፍልሚያ አካሄዷል። ግራኝ በበጌምድር ንጉሥን ማሳደድ ትቶ አፍራ የተባለው ባሕር ነጋሽ ሾመ። ሠራዊ ግብር እንዲክፍል ተገደደ የሀገሩ አስተዳደርም በቲዎድሮስ ምትክ ወንድሙ ተሾመ። የሁሉም የበላይ አዛዥ በቪዧር አዶሬ ምትክ ቪጸር አባሰ ሾመ። የትግራይ አብያተ ክርስቲያናት የአክሱም ሳይቀር ተቃጠሉ። ተሳላፊ በሽታም በሀገሩ ገጠቶ ብዙ ሰው ፈጀ ከሞቱትም መካከል የግራኝ ልጅ ከጦር ሜዳ የተወሰደ ነበረ። ግን ሰላም አሰፍኖ ወደ ደምቢያ ሲመለስ ወዲያውኑ በሰራየና በትግራይ የደፈጣ ውጊያ ተጀመረ። ግራኝ ሰሜን እንዲይዝ ፈላሾች መንገድ ከፍተውሰት ነበረ። የመጨረሻ ያልተያዘ ከፍሰ ሀገር ወደ ጎጃም በማምራት ግራኝ ንግሥት እሌኒ ብዙ ንብረታቸው ያፈሰሰብቸው ቤተክርስቲያናት ተቃጠሉ፣ ተዘረፉ በነሱ ውሰጥም መርሀ ሰግራያም የተባሰ ስመ ጥሩ ነበረ። በዚሁ ዓይነት መሳው ኢትዮጵያ በግራኝ ቁጥጥር ውሳ ነበረ። የቀረው ንጉሡን አሳዶ ማያዝ ብቻ ነበር። ሰልብነ ድንግል የተሰፋ ሚሳንሚል የነበረው የፖርቱጋል መልእክተኞች ውጤት ነበረ። ነገር ግን አጼ ልብነድንግል ከዚህ በፊት ያደረገላቸው አቀባበል የቀዘቀዘ ስለነበር እርዳታ የማግኘት ተስፋ እንስተኛ ነበረ። አሰቸኳይ እርዳታ ከክርስቲያን ኤውሮጳ ሰማግኘት የነበረው አማራጭ አጼ ልብነድንግልና ቤተመንግሥቱ በሙሱ የካቶሊክ ሃይማኖት መቀበል ነበረ።

ነገር ግን ይሽም እግራጭ እርምጃ የሕዝቡ ተቃውሞ ሊያስከትል ይችላል ተብሎ ስለተፈራ ሌላ ዘዴ ተቀየሰ። ይሽውም በዕድሜ የገፋ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ የነበሩ አቡን ግርቆስ ሰአንድ ካቶሊካዊ የጵጵሰና ማዕረግ ሰጥተው ስልጣናቸውን እንዲያሰረክቡ ነበር። ይህ ዘዴ ጥሩ መሰሰ ቢታይም ሕጋዊነት አልነበረውም። ምክንያቱም አቡኑም ሰአንድ ካቶሊክ ጵጵስና መሰጠት መብት አልነበረውም፣ ሰጵጵሰና ተሿሚ ግሰሰብም መቀበል አይችልም ስለነበረ ነው። ሰጵጵሰና ማዕረግ የተመረጠ ሰው በርሙዳስ ነበረ። ቤርሙዳስ እንደ ተሾመ ሁኔታውን ሰግስረዳት ወደ ሮም መሄድ ነበረበት። በ1536 ዓም ከአንድ ዓመት ጉዞ በኋላ ከአስላሞች ብዙ እደጋዎች አምልጦ በርሙዳስ ሰርም ሊቃነጳጳሳት ከአጼ ልብነ ድንግል የተላከ መልእክት ይዞ ሮም ገባ። በደብዳቤው ላይ አጼ ልብነ ድንግል የካቶሊክ ሃይማኖት እንደሚከተልና ከርግ የተላከ አቡን በሰተቀር ሌላ አቡን እንደማይቀበል ገልጸ ነበር። በርሙዳስ ወደ ፖርቱጋል ከአጼ ልብነ ድንግል ሰፖርቱጋል ንጉሥ የተላከ መልእክት አቀረበ። ሁሰቱ መንግሥታት የርግና የፖርቱጋል የራሳቸው የውስጥ ችግር ስለነበራቸው የኢትዮጵያ ጉዳይ ችላ ብሰውት ነበር። ሆኖም በርሙዳስ የኢትዮጵያ ከርስቲያን ሕዝብ ሁኔታ በሚገባ በማስረዳቱ የፖርቱጋል ንጉሥ እማኑኤል 5ኛ ከሕንድ 450 የፖርቱጋል ወታደሮች ወደ ኢትዮጵያ እንዲሳኩ አዘዘ። በርሙዳስ ትዕዛዙን ይዞ ወደ ሕንድና ወደ ኢትዮጵያ የመለስ ጉዞ ለመጀመር በሚዘጋጅበት ጊዜ ለ3 ዓመት እስከ 1539 ዓም. ታሞ ሀገሩ ተቀመጠ። የፖርቱጋል ወታደሮች ምዕዋ ሲወርዱ የቻሉት በ1541 ዓም. ነበረ። በኢትዮጵያም ጦርነቱ እየተካሄደ ነበረ። በ1539 ዓም. ግራኝ ለልብነ ድንግል በላከው ደብዳቤ በኢትዮጵያ ሰላም እንዲሰፍን የአጼ ልብነድንግል ልጅ ለማግባት ንጉሡ እንዲፈቅድ ይህ ካልሆነ ግን ኢትዮጵያ

እስላም እንድሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰሰሆነ አጼ ልብነ ድንግል በጦርነቱ ከተፋጠት ሲያመልጠው እንደማይችል እና ቅጣቱ እስከፈ እንደሚሆን አስመነተተው። አጼ ልብነ ድንግል ግን የሰላም ጥሪ ሳይቀበል ሰሰቀረ ጦርነቱ ቀጠለ፣ በመጨረሻም ሳይያዝ ቀርቶ የነበረው የንጉሥታት ዘር ማሳሪያ የተደበቀ ወርቅ ይገኛል ስሰተባሰ የእስላም ተዋጊዎች ሳይነቃባቸው ለመግረክ ሰለቻሉ ከበረቶት በኋላ እቃጠሉት። የተገኘው የወርቅ ብዛት የተነሳ "ወርቅ እንደ ድንጋይ ሆኖ ነበር ልብሶችም እንደ ቅጠል ሆነው ነበረ" በማለት የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፊዎች ዘግበዋል።

አጼ ልብነድንግል በ45 ዓመት ዕድሜው ሲሞት የደረሱ ልጆች ነበሩት። ቪክቶር የተባሰው እልጋወራሽ ልጁ ወደ ዳዋር የሚያዋሰነው ሄዶ የእስላም ሠራዊት ሰሁሰት ከፍሎ የመዋጋት ዓላማ ነበረው ሳይሳካለት ሰሰቀረ ግን በውጊያ ተገደሰ። 2ኛ የአጼ ልብነ ድንግል ልጅ ሚናስ ከአባቱ ጋራ ሆኖ በዋግ አካባቢ ሲዋጋ በእስላሞች ስለተያዘ ባሪያ ሆኖ ለዘፈቀ ፓሻ ተሸጠ። አጼ ልብነ ድንግል በደብረዳሞ አስተማማኝ መደበቂያ በመፈለግ ወደ ደብረ ዳሞ ሄደ። ባሕር ነጋሽ ይሰሐት ከግራኝ ወታደሮች እደጋ እንዳያደርስበት በማሰብ የገዳሙ መውጫና መግቢያ ዘብ በማቆም ይጠብቅ ነበር። ጥቂት ወራት ቆይቶ ሲፕቴምበር 5/1540 ዓም. አጼ ልብነድንግል በዜተሰበቹና በታማኞቹ ተከቦ በሰላም ዐረፈ።

9. አጼ ገላውዲዮስ

አጼ ገላውዲዮስ ከአባቱ ሥልጣን ተረክቦ ጦርነቱን በጠንካራ መንፈስና በተሻለ ዕድል ቀጠለ። የአጼ ገላውዲዮስ እናት ንግሥት ሰብለ ወንጌል በሰሜን የሚኖሩ ሕዝቦችን በግንሳባት ከአዲሱ ንጉሥ ጋራ እንዲቆሙ ያደረገችው ጥረት ስለተሳካላት ሰመጀመሪያ ጊዜ ፈላሾች ለኢትዮጵዊ አዲሱ ንጉሥ ሰገላውዲዮስ ድጋፋቸውን ሰጥተዋል አሰምትም የአነሱ ምሳሌ ተከትለው ድጋፋቸውን ሰጥተዋል። ግራኝ ምርጥ አዛዦች በግሰግራት ሰሜን ሰመያዝ ሊወጋቸው መጥቶ አልተሳካለትም። አጼ ገላውዲዮስ በሰሜን ተራራዎች ሆኖ ከጠላት ጋራ እየተፋለመ በነበረ ጊዜ ንግሥት ሰብለ ወንጌል በደብረዳሞ ገዳም ሆና ታማኞችን እየሰበሰበች የጦር መማሪያ ትሰጥ ነበረ፣ በዚሁ ጊዜ ፖርቱጋሎች ምዕዋ መድረሳቸው ወሬ ሲሰማ ሕዝቡ በደስታ ፈነደቀ። ትግራይ ሁሉ ለንጉሡ ሙሉ ድጋፍ ሰጠ። ፖርቱጋሎች በቤርሙደዝ እየተመሩ ጉራዕ ገቡ። ከዚያም ድባርዋ ድረስ መጥተው ሰብለ ወንጌል ትጠብቃቸው ሰሰነበር ተገናኙ። በታኅሣሥ ወር ፖርቱጋሎች ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ጋራ በመሆን ምግብ እያቀረበችሳቸው ከድባርዋ ተነሱ። አፕሪል 4/1542 ዓም. በፖርቱጋሎችና በግራኝ የሚመራ የእስላም ሠራዊት እናሳ በተባሰው ቦታ በእክለጣዩ ጦርነት ተካሄደ የፖርቱጋሎች መድፎች በእስላሞች ላይ ሽብር ፈጥረው ነበር።

ግራኝ ታፋው ላይ ቆሰለ፣ ፈረሱ ተገደሰ። ግራኝ እስከ ዘዙል ተራራዎች ሸሽቶ በመሄድ ጦሩን ሰማደራጀት ሞከረ። ከጎረብ ሀገር ሁለት ሺህ ዓረቦች፣ቱርከችና አልባናውያን ቅጥር ወታደሮች በዘይላ በኩል እስመጣ። የክርስቲያን ሠራዊት ግራኝን አያሳደደ እስከ እሸንጌ ሐይቅ ድረስ ገሠገሰ። እነሰት በ1542 ዓም. ግራኝ ከባድ ጥቃት እካሄዶ የፖርቱጋሎች ጠር አዛዥ ዶን ክሪስቶፎር ዳ ጋማን እቁሰሉትና በእስቃቂ ሁኔታ ገደሉት። የፖርቱጋል ጦርና ንግሥት ሰብለ ወንጌል እስተድሞ ለክፉ ጊዜ ጦር ሰፈርና ጣብያ አድርገውት የነበረ ወደ ሰሜን ሄዱ። ንጉሡም የእስላም ጦር ጥሶ

ከፖርቱጋሎች ጋራ ተቀላቀለ። ንጉሡ ለፖርቱጋሎች ወረታውን በመመለስ በግስብ ለእየእንዳንዱ ፖርቱጋል ወታደር 1000 አውንስ ወርቅ ስጣቸው (135 ኪሎግራም)። ይህ የሚያሳየው ኢትዮጵያ በእስላሞች ኩተዘረፉ ሃብቷ ሌላ ብዙ የቀራት ወርቅ እንደነበረ ሲሆን ይኸውም ምን ያህል የበለፀገችና ሃብታም ሀገር እንደነበረች የሚያመለክት ነበር።

የክርስቲያን ሠራዊት ከሰሜን ወደ ደቡብ ጎንደር እስላሞችን እያሳደደ ተጓዘ። ግራኝ ከነበረበት ከዘቡል ተራራዎች ዋና ኩተማው ብሉ ወደ መረጣት ወደ ደንቢያ መጣ። ፖርቱጋሎች ዶን አልፎንሶ ከልደራ እዘዛቸው መርጠው ነበረ። አሱም ወዲያው ስስሞተ አንድ ክልስ ዝርያ ያለው አሪዮስ ዲያዝ መረጡ። አጼ ግላውዲዎስ ከፖርቱጋሎች ጋራ በመመካከር ግራኝ ወደ ደንቢያ እንደመጣ እንዲገጥሙት ተወሰነ። ዲያዝ በመጀመሪያ መሥመር ፖርቱጋሎቹን አሰማራ። እስላሞች እያጠቁ ሲመጡ ግራኝ ወታደሮቹ ወደ ኋላ እንዳይመለሱ ፊት ስፊት እየመራቸው ስስነበረ በፖርርቱጋል መድፎች የእሳት እራት ሆነው ቀሩ። አንድ ፖርቱጋላዊ የቀድሞ የፖርቱጋሎች እዛኙ ጆን ኪሪስቶፎር ዳጋማ ጠባቂ የነበረው ፔድሮ ሲዮን የተባለው የጌታውን ገዳይ ለይቶ ስላወቀው በእሱ አነጥሮሮ በመተኩስ ግራኝን አቁስሉ ጣለው። ግራኝ ግን ወታደሮቹ ተስፋ እንዳይቆርጡ በማሰብ በአንድ ዛፌ ስር ለመደበቅ ሞክሮ ነበር። ያቆሰለው ወታደር ግን ግራኝ የሄደበትን ቦታ ተከታትሉ ስላወቀ ለሞት ሲያጣጥር ስላገኘው ላስረጅነት እንድ ጀሮውን ቆርጠ ወስደበት፣ ቦታውን አሁን ድረስ የግራኝ በር ተብሉ ይጠራል። የእስላም ወታደሮች ተሸንፈው ተበታተኑ።

ጦርነቱ በክርስቲያኖች ድል አድራጊነት ቢፈጸምም የሚቀጥለው ዙር በአጼ ግላውዲዎስና በበርሙደስ ያለው ጉዳይ መፍትሄ ማድረግ የሚኖርበት ነበረ። በርሙደስ በውሉ መሠረት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አቡን መሆን አለብኝ ባይ ነበረ። አጼ ግላውዲዎስ ግን በቤተክህነንት ተጽእኖ በርሙደስ ወደ ጎን በመተው እንደ ቀድሞ ከእስክንድሪያ አቡን እንዲላክለት ጠየቀ። በዚሁ ጊዜ በሁለቱ ስዎች መካከል ከፍተኛ ጠብ ተፈጥሮ በርሙደስ የፖርቱጋል ወታደሮች ድጋፋቸውን እንዲስጡት ፈልጎ ነበረ። ግማሾቹ የፖርቱጋል ወታደሮች ወደ ሕንድ ተመልሰው፣ ነበረ በኢትዮጵያ ቀርተው ከነበሩት መሐል ግን አብዛኛውቹ ንጉሡን የሚደግፉ ሆነው ተገኝተዋል። ባተሊይ አዛዣቸው ዲያዝ በግልፅ ከንጉሡ ጋራ ከመቆመም በላይ እንደገና በአርቶዶክስ ክርስትና ተነስቶ ስሙ ማርቆስ ተብሏል። ሌሎችም የአሱን ምሳሌ ተከትሏል። በንጉሡ ሕይወት አደጋ እንዳያጥሉ በማስት በርመደስ ሌሎችም ፖርቱጋሎች ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ እንዲሰደዱ ተደርጓል። በርሙደስ በመጀመሪያ ወደ ደቡብ ጋፋት ተልኮ ቀጥሎም ሌሎች ፖርቱጋሎች ወደ ነበረበት ወደ ዳውሮ ተወሰዶ ከዚያም ወደ ድባርዋና ምዕዋ ሄደ። ከዚያም በኋላ ወደ ህንሩ ተመልሶ አስታዋሽ አጥቶ ቀሪው ዕድሜው አሳ ልፋል። ሌላው ከጦርነቱ በኋላ የተደቀነው ችግር የንጉሡ ነገሥቱ የማት አንድነት ማስከበር ነበር፣ ይሄም የተከናወነው በ1544 ዓ.ም. ነበር። ቪጊር አባስ የአቡን ልጅ የኢማም ወንድም ዳዋሮ፣ የዛሬዋ ናዝሬት መተሀራ አካባቢ እንደዚሁም ባለ ክአርሰ አሰክ ሕንድ ውቅያኖስ የሚያጠቃልል ነፃ መንግሥት እቋቁም መሪ ሆኖ ነበረ። የኢትዮጵያን ሠራዊት ለመቋቋም የሚችል መስሉት ነበር። አጼ ግላውዲዎስ በዋዲ አውራጃ በኩል ወደ ፋጢጋር አልፎ ገሰመው። በአንድ ቀን ጦርነት በአክቶበር 1544 ዓ.ም. አስላሞች ተሸነፈ። በ1545 ዓ.ም. መጀመሪያው ላይ አባስ ተገደለ አጼ ግላውዲዎስ ወደ ዳውሮ ገባ፣ ቤተመንግሥት ሠራ፣ የፈረሱ ቤተክርስቲያኖችም ታነፁ። ባሌም

እንደገና ተያዘ። ሆኖም ባሌ በዚሁ ጊዜ አሮሞ የሚያደርገው መስፋፋት ዋና መነሻ ጣብያ ሆና ስስነበረች ለብዙ ጊዜ ተይዞ አልቆየም። በ1547 ዓ.ም. ሐዲያ እንደ ቀድሞ ወደ ግዛቱ ተቀላቀለች። በ1548 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ ዳሞት ከአባይ በስተደቡብ ዘምቶ ክርስትና ያልተቀበሉ ሕዝቦች ስለነበሩ ወሰኑ እስክ ጊቤና አሞ ወንዞች ደረስ። የሐረር መንግሥት በ1548 እና በ1550 ሁስት ጊዜ ከአጼ ግላውዲዎስ ጋር ጦርነት ገጥማ ሁስት ጊዜ ተሸነፈች። 1552 ግላውዲዎስ ከንባታን እስገብረዋል፣ ጉመር የሚባል አውራጃ በዛሬዋ ደጋማ ክፍል አርሲ አስገብሯል። በዚሁ መሠረት የንጉሠ ነገሥቱ ግዛት ስፋቱ ድሮ ወደ ነበረበት ተመልሶ ነበር። ሐረር እንደገና በ1552 ዓ.ም. ሽፍታ ጦርነት አውጃ ፋጢጋርን ወራ ወደ ሽዋ አምርታ ነበር። አጼ ግላውዲዎስ የደብረ ወርቅ ገዳም እያስራ ይገኝ ስስነበረ፣ 12 ቀን ፈጣን ጉዞ አድርጎ ሐረር ስቅለት /አርብ ቀን/ ጦርነት ገጥሞ ተገደለ። የግራኝ ሚስት አጼ ግላውዲዎስ በመገደሉ የግራኝ መበቀል ሆኖ ስለተሰማት ደስ አላት፣ የግላውዲዎስ ሟንቅላት ተቆርጦ በሐረር ኩተማ መግቢያ ደጃፍ ለሦስት ዓመት ተስቅሉ ነበር።

አጼ ግላውዲዎስ እንደሞተ ሦስት ቀን በኋላ ታማኞቹ አስክሬኑን ወደማሪያም ቤተክርስቲያን ወስደው ቀበሩት። የአጼ ግላውዲዎስ ሟንቅላት በሐረር ኩተማ በር ደጃፍ ተሰቅሉ የነበረው፣ ክርስቲያን ነጋዲዎች ሰርቀው ወስደው በአንድ የይፋት ቤተክርስቲያን በክብር ቀበሩት። አጼ ግላውዲዎስ እንደ ስማእት ሆኖ ይከብር ነበረ።

10. <u>የክርስቲያን መንግሥት አሸናፊነት</u>

ከግራኝ ጦርነት በኋላ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ መንግሥት ምንም እንኳን እንደ ምፅዋ፣ አሰብ ታጁራ፣ ዘይላ የመሳሰሉት የባሕር ጠረፍ ኩተሞች መቆጣጠር ባለመቻሉ ደካማ ጉን እንዳለው መስሉ ቢታይም በባሕር የሚመጡበትን አደጋዎች ጠሳቶችንም ለመቋቋም ችሉ ነበረ። የክርስቲያን መንግሥት የእስራኤል ዝርያ የሆኑ ሰለሞናዊ ነገሥታት እንደነበረ ሁሉ በምስራቅ ኢትዮጵያ የነበሩ የእስላም መንግሥታትም የነቢዩ መሐመድ ዘመድ የሆኑ በዓረቦችና በቱርኮች የሚደገፉ ወላዝማ በሚባሉ ሱልጣኖች የሚመሩ ነበሩ። በመጀመሪያ በክርስቲያን መንግሥት ላይ የተነሳ ይፋት ነበረ። ይፋት ሲዳክም በእዳል ተተካ። አዳል የሚባለው መንግሥት በግራኝ እምባነን አገዛዝ ቁጥጥር ስር ሆኖ የክርስቲያን መንግሥት ያልነበረው የጦር መሣሪያ ታጥቆ መላው ኢትዮጵያን የተቆጣጠረ ቢመስለውም የክርስቲያን መንግሥት ለ20 ዓመታት ወረራውን ለመቋቋም በመቻሉ፣ በመጨረሻ በጥቂት የፖርቱጋል ወታደሮች አርዶታ በአሸናፊነት ሲወጣ ችሏል። ክግራኝ መሸነፍ በኋላ ስግቆጥቆጥ የሞከረው የእስላም መንግሥት በሐረር ኩተማ የተቋቋመው የግራኝ እና የወላዝማ ዝርያ የነበራቸው የግራኝ ሽንፈት ለመቀበል ፍላጉት ያልነበራቸው ሱልጣኖች ነበር። በረከት በተባለው የሐረር መንግሥት ሱልጣን ልጅና አሲ ጋራድ በተባለው የግራኝ ልጅ የሚመሩ የሐረር ወታደሮች ዳውሮን ወረሩ፣ ወረራው ግን የእውራኝው ክርስቲያን ሀገረ ገዥ የነበረው፣ በራሱ ሌላ አርዳታ ሳይጠይቅ ሲያከሽፈው ችሏል፣ መሪዎቹም ተይዘው ታስሩ።

የግራኝ ሚስት ከዓረቦች ጋራ በነበራት ትውውቅ በመጠቀም ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ ውይይት ተደርጎ የእስረኞች ልውውጥ እንዲደረግ ተስማምተው ሚናስ የእዜ ግላውዲዎስ ወንድም በጦር ሚዳ

በግራኝ ተይዞ ወደ የመን ባሪያ ሆኖ ተወሰዶ ስለነበር በሱ ሰውተ በረከት አሊ ጋራድ ወደ ሐረር እንዲመለሱ ተደርጓል። ትንሽ ጊዜ እንደቆዩ የሐረር መንግሥት በ1550 ዓ.ም. ኢትዮጵያን ለመውረር ኑር በሚባለው ሱልጣን መሪነት ሌላ መከራ አድርገዋል። ወረራው ይመራ የነበረው የሞጃሂድ ልጅ ነበረ። ከግራኝ ሞት በኋላ የሞጃሂድ ቤተሰቦች የተድሞ የግራኝ ተዋጊዎች መሰብሰቢያ ሆነው ነበረ። እንዲሁም የግራኝ ሚስት ባቲ ደል ቮምበራ ከሚደገፉ መካከል ዋና ተዋንያን ነበረች። የግራኝ ሚስት በአባቷ በኩል ኢትዮጵያን እየወረሩ ያስቸገሩ ከነበሩ አንዱ የነበረው የግሕፋዝ ልጅ ስትሆን የአሁኑ የኑር የሐረር መንግሥት መሪም በእናቱ የግራኝ እህት ልጅ ስለሆነ፣ ሙሉ እምነት ስለነበራት አትቱን እንዲከተል አዘዘላው ስለነበር ዋና ተልእኮውና ዓላማዋ ሆኖ ነበር። አሁንም እስላሞች አልተናቸውም በታዋቂው የኢትዮጵያ ጦር መሪ ፋኒል የሚመራ የኢትዮጵያ ሠራዊት ኑር ብቻ ሸሽቶ ሲያመልጥ የቀሩት የሐረር ወታደሮች ተደመሰሱ። አጼ ገላውዲዮስ ለፋኒል ሐረርን ወር እንዲይዝ ትዛዝ ሰጠው። ግርች 13 ቀን 1550 ዓ.ም. ሐረር በፋኒል ጦር እጅ ወደቀች ነወሪዎቿም ሸሹ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፋሲል ሞተ፣ አጼ ገላውዲዮስ የተገኘው ድል ሰማከበር 5 ወር ሐረር ተቀመጠ፣ ከርስቲያን ባሪያ ሆኖ ተወሰዶ የነበሩ ተለቀቁ፣ በአንባሩም ብዙ እስላሞች ተገደሉ፣ ባሪያ ሆነውም ተወሰዱ። ሐረር ምንም እንኳን ከባድ ሽንፈት ቢጥግትም ለ3ኛ ጊዜ የኢትዮጵያ ከርስቲያን መንግሥትን ሰማጥቃት ሞከራ ነበር። በኢግር ኑር ምትክ ከርስቲያን የነበረው ዑትማን የተባለው በሐረር ሥልጣን ይዞ ነበር። በዚሁ ዘመን ሁለቱ የሐረር እስላሞችና የኢትዮጵያ ከርስቲያን መንግሥት በእርሞ የጋራ ጠላት ተከሰው በችግር ላይ ወድተው በነበሩ ጊዜ ሐረር ስለ ተዳከመች በሥልጣን ላይ የነበረው የግራኝ ዘመድ ይማም መሐመድ የእርሞች ወረራ ወደ ግያስጋው ወደ አውሳ በ1577 ዓ.ም. ሐረርን ለቆ ለመሄድ የተገደደ። ከዚህ ጊዜ ጀምር የአውሳ ሱልጣን ተመሰረተ፣ የይፋት፣ የአዳል፣ የሐረር መንግሥታት ሀልውናቸው አከተመ።

11. <u>የቱርክ ወረራዎች በኢትዮጵያ</u>

ሌላ የኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላት የነበረው ምፅዋ የሰፈረው የቱርክ ኣዝዝ ነው። ቱርክ ሱዋኪምና ምፅዋን የያዘው በ1517 ዓ.ም. ነበር። የቱርክ መንግሥት በወቅቱ በዓለም ቅድመ ኃያል መንግሥት ለመሆን በቅቶ የነበረ ነው።

ዓረቦች በምዕራብ ኤውሮጳ ገብተው ኤውሮጳን እስላማዊትና ዓረባዊት ለማድረግ እንደሞከሩ ሁሉ የቱርክ መንግሥትም በደቡብ ምስራቅ ኤውሮጳ እስከ መሐል ገብቶ ኤውሮጳን በቁጥጥሩ ለማዋል ተቃርቦ የነበረ መንግሥት ነው። ቱርኮች ከዓረቦች የበለጠ ዓላማቸው ተሳክቶላቸው በእንዳንድ የኤውሮጳ ሀገሮች ሃይማኖት እንዲቀበሉ አድርጓል እንደ ቦስኒያ፣ አልባንያ የመሳሰሉት። ቱርኮች መሃል ኤውሮጳ ገብተው የአንድ ትልቅ ኤውሮጳዊ መንግሥት ዋና ከተማ የሆኑትው በሰልጣኔና በጥበብ የተራቀቀችው ቪዮና ለመያዝ በተቃረበበት ጊዜ ኤውሮጳውያን በሙሉ ተባብረው አሰካለተቋቋሞው ድረስ አስፈሪ ኃይል ነበሩ። በኢትዮጵያ ግን ቱርኮች አራት ጊዜ ወረራ አድርገው ተሸንፈው ወጥቷል። የመጀመሪያ ወረራቸው በመፅዋ በኩል በ1557 ዓ.ም. ነበረ። በዚሁ ጊዜ ቱርኮች ምፅዋን ተቆጣጥረው ወደ ደጋ ዘልቀው በመግባት በድባርዋ ምሽግ በመስራት ባሕር ነጋሽን በሙሉ በቁጥጥራቸው ስር አውለው ነበር። የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ገዛም የሆነው

ያብረ ዳሞት በቱርኮች ተይዞ ተዘረፈ፣ የባሕር ነጋሽ ቆላግ ሰሜናዊና ምዕራባዊ ጎሳዎች ቢኾ የተባሉ በፖሻ አክዝዳመር የሚመሩ እስላሞች ከቱርኮች ጋራ ተባብረው ነበረ። በባሕር ነጋሽ ይስሐቅ በሚመራ የክርስቲያን ሠራዊት ሲያመሰሰሱ መሪያቸው ሸሽቶ ቱርኮች ወዳሰብት ወደ ዱባሩዋ ገብቶ ብዙ ሐብት ከርስቲያኖች የደበቁት አለ በማለት ቱርኮችን ሰሰ አጓጓቸው ፖሻ ሁዝዳመር 800 ፈረሰኞችና በዛት ያላቸው ወታደሮች አስከትሎ ወደ ቦታው ዘመተ። ብዙ ኩተጓዘ በኋላ የተባለው የሐብት ክምችት አገኙ፣ በመሀሉ ግን የቱርክ ፖሻ ትኩሳት ታሞ በታሪዛ ተሸክሞት ተመሰሰ፣ የዘመቱ ሰዎችና እንሰሳት አብዛኛዎቹ ሞቱ፣ ከኢትዮጵያ ጦር በመሐሉ በድባሩዋ ጥቃት ፈፅሞ ዘመከበብ ቱርኮችን ያሰምጣብና ውሀ አሰቀርቷቸው ነበረ። ቱርኮች ያገኙትን ሐብት ሊሊት ከድባሩዋ ሰመመጣት ሲሞክሩ መማሪያ በታጠቁ ገበረዎች ተደመሰሰ፣ ሐብቱንም ማረኩት፣ ድባርዋም ተማረከች። የቱርክ ወታደሮች ከድባርዋ አምልጠው ወደ ምጽዋ ሰመሸሽ ሲሞክሩ በታጠቁ ገበረዎች ተገደሉ፣ የቱርክ ፖሻ ባዶ እጁ ሰለቀረ ሸሽቶ ሱዋኪም ገባ። የቱርክ ወረራ ተመግዶ ይዘታው ዘመፅዋ ተወሰኖ ቀረ፣ ሁሰተኛ የቱርክ ወረራ በአጼ ሚናስ ዘመነ መንግሥት፣ ነበረ በአንደኛ የቱርክ ወረራ በጀግንነት ተዋግቶ የአባረራቸው ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ሥልጣኔ ተሻሙኝ በማለት በንጉሡ ላይ ተቀየመ። አጼ ሚናስ መጀመሪያ ዮሐንስ በተባለው ጦር ላከበት፣ ነገር ግን ይስሐቅ በድንገት አደጋ ጥሎብት አሸነፈው፣ ይስሐቅ ከቱርኮች እርዳታ ለማግኘት ከድባርዋ እስከ ምፅዋ ያሰውን መሬት ሰማቸው። አጼ ሚናስ ፖርቱጋሎች ከይስሀቅ ጋራ ተስማምተው ይሆናል ብሎ ሰለጠረጠራቸው በአንድ ተራራ እንዲቀመጡ አደረጋቸው። አቡነ አርቪየዶና ተከታዮቹ አምልጠው ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ወደ አሰበት ደርሰው ድጋፋቸውን ሰጡት። በዚህ መሠረት ቱርኮች ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ ካቶሊኮችና ሌሎችም የሚናስ ተቃዋሚዎች ግባር ፈጠሩ። ፖርቱጋሎች ከሕንድ የጦር መርከቦች እንደሚያሰመጡ ሰይስሐቅ ተስፋ ለጡት፣ አጼ ሚናስ ግን ጊዜ አልሰጣቸውም አፕሪል 20 1562 ዓ.ም. በተደረገው ጦርነት አሸናፊ ሆነ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ አጼ ሚናስ ከጸባ ጎሳዎች ጋራ ጦርነት ባደረገበት ወቅት በተኩሳት ታሞ ሞተ። ጦሩም ጉዳት ደርሶበት ሰሰነበረ ቱርኮችን እስከ ባሕር ላያባርራቸው ተመሰሰ።

ሦስተኛ የቱርክ ወረራ በኢትዮጵያ በአጼ መላክ ሰገደ ዘመነ መንግሥት ነበረ። ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ እንደገና 1578 ዓ.ም. ከቱርኮች ጋር ተሰማምቶ ለንጉሠ ነገሥቱ አልታዘዝም በማለት የንጉሠ መልእክተኞች ተልከውበት ከቱርኮች ጋራ እንዳይገጥም ቢጠየቅ "ኪፖቻው ጋራ እርቅ አድርጌአለሁ፣ በአንድ ምንጣፍ አንድ ላይ በመተመተ" የሚል መልስ ሰሰሰጠው መላክ ሰገደ ጦሩን ወደ ባሕር ነጋሽ አዘመተ የንጉሠ መምጣት ዜና ሲሰማ ተዋጊዎች ከባሕር ነጋሽ መከዳት ጀመሩ። በሠራዊ ፀረ ባሕር ነጋሽ ዐመፅ ተካሄደ፣ ይስሐቅና ቱርኮች እንጠሮ ተሰበሰቡ፣ በመጀመሪያ ግጥጫ ኖቬምበር 13, 1578 ዓ.ም. ቱርኮች የመላክ ሰገደ ሠራዊት እንዲሸሽ አደረጉ። አሬት ቀን በኋላ ቱርኮች 8 መድፎች በኢትዮጵያ ጦር ላይ ተከሉ፣ በማነጻጸር ብዙ ጉዳት አደረሱ። በዚሁ ጊዜ መላክ ሰገደ የእርሞ ፈረሰኞች አሰግርቶ በቱርኮች ላይ አጠቃ፣ ብዙ ሳይቆይ መድፎቹ ተያዙ፣ የጠላት ይዞታዎችም ተያዙ። ከዚህ በኋላ ይስሐቅ ተሰፋ ሰሰቆረጠ እርቅ ጠየቀ። ንጉሡም ከቱርኮቹ ተዋጊዎቹ ለይቶ አውጥቶ ከቱርሰትያኖች ጋራ ቱርኮችን እንዲወጉ አድርግ የሚል መልስ ሰጠው። ይስሐቅ ከቱርኮች ጋራ እርቅ እንዲደረግ የሚል ሐሳብ አተረበ። የቅርብ ረዳቶች ሳይቀሩ ከዱት።

በተደረገው ሁለተኛ ግዞግዝ ቱርኮችና ይስሐቅ ሽንፈት ገጠማቸው የኢትዮጵያ ጦር የቱርክ ጦር ለፈር ተቆጣጥሮ የቱርኮች እርማና መድፎችን ማረከ። የኢትዮጵያ ሠራዊት እንደልማዱ ከአካባቢ ገበሬዎች ስንቅ ፍለጋ መሔዱ ሲያውቁ ቱርኮችና ይስሐቅ ከምሽጋቸው ወጥተው መድፋቸውን ዘንጉሥ ጦር አያተኩሩ መተኮስ ጀመሩ፣ ንጉሥ ግን ጥቃታቸውን አክሽፎ መልሳቸው። ይስሐቅም ከጥቂት ተከታዮቹ ጋር ሆኖ ወደ ሬት እያመራ በማጥቃት ሞክሮ ነበር። ነገር ግን አንድ ኢትዮጵያዊ ወታደር ለይቶ ሰላወቀው እድሩሀ ትክሻውን አቁስለው። ይስሐቅ ብዙ ደም እየፈሰሰው ወደ መጣበት ተመልሶ ከፈርሰ ጦሩ በመሬት ተጋደመ። ስንት ሩሊጋ ሔደው የነበረ የኢትዮጵያ ወታሮች ሲመለሱ የቱርክ ሠራዊትን ከበው ፈጁት። ይስሐቅ ሞተ የቱርክ ጋሻ የጦሩን እልቂት ፊረሱ ላይ ወጥቶ ያመለክት ነበረ። ጀግናው አንድ የኢትዮጵያ ወታደር ዮናኤል የተባለው ደረቱን ዘመውጋት ሰላቆሰለው ከፈረሱ ወደቀ። ያቆሰለው ወታደርም ወደ ወደቀበት ሄዶ እንቱቱን ቆርጦ ለንጉሥ አበረከተው። ቱርኮች የነበራቸው ሐብትና ብዙ የጦር መሣሪያ ተማረከ የይስሐቅ ረዳቶችም ተማረኩ። ንጉሥ ከጦማረኩት ዋና ዋናዎቹን መርጦ እንዲገደሉ አዘዘ።

4ኛውና የመጨረሻው ኢትዮጵያ ከቱርክ አቶማን ጋራ ያደረጉት ጦር ፍልሚያ በአጼ መላክ ሰገድ ዘመን መንግሥት (1589 ዓ.ም.) ነበረ። ወልደ አዙም የተባለው በአለቃው በትግራይ መሎንን ዳህራቡት ላይ ዐመጸ ተነስቶ ብዙ ባለሥልጣኖችን ገድሎ ቱርኮች ባለፈው ዘመናት ሊቆጣጠሯቸው ሞክረው የነበረ የባሕር ምድር ግዛቶች ለመያዝ በነበራቸው ምኞት ጥቃት ባካሄዱበት ወቅት በመጀሪያ ሲዋጋቸው ከቆየ በኋላ ዘመጨረሻ ግን የቀድሞ የባሕር ነጋሽ ምላሰ ዘመሀመድ ሰቱርክ ጦሣ እጁን ዘጥቶ የባሕር ነጋሽ ሹመት ከቱርኮች ተቀብሎ ከንጉሥ የተላከው ጦር ለመቋቋም ችሎ ነበረ። በአዲሱ ባሕር ነጋሽ ረዳትነት ቱርኮች ድባርዋን ለመያዝ ችለው ነበር።

ዳህራንት ሊያስወጣቸው ሞክሮ ከባድ ሽንፈት ደርሶበታል፣ ቱርኮች መረብን ተሻግረው ትግራይ ገብተው ነበር። ሕዝቡ ግን ተዋግቶ መልሷቸዋል። በሚመለስበት ጊዜ ዐቅባ ሚካኤል የሚባለው መረብ አጠገብ ባደረገባቸው ደፈጣ ስለተከበቡ ከተያዙት 7 ቱርኮች ተሰለቡ፣ ሁለት የበላይ ሹሞች ተገደሉ፣ ንጉሥ ዐቅባ ሚካኤል በፈጸመው ጀግንነት ተደስቶ የባሕር ነጋሽ ሹመት ሰጠው። ዜናው በመላው ኢትዮጵያ እንደምሰሌ ተተረተ። ጋሻው የንጉሥ መምጣት ሳይጠብቅ ወደ ምፅዋ ሄደ፣ ንጉሥ ግን ቱርኮችን ለዘለዓለም ከኢትዮጵያ መሬት መንቅሎ ለማጣት ምፅዋ ድረስ ሄደ። ቱርኮች በምሽጋቸው እና ከባሕር ከመርከባቸው ሆነው ተከላከሉ። ብዙ ቱርኮች ታስሩ ሁሉም እግሮቻቸውና እጆቻቸውን ተቆረጡ። ጋሻው ራሱ ቆሰሉ ነበረ፣ ሰውነቱ ብረት ለብሶ ስለነበረ ግን ከሞት ተረፈ። የኢትዮጵያ ሠራዊት ስንቅ ሰላለቀበት ወደ ደጋ መመለስ ግድ ሆነበት። የኢትዮጵያ ንጉሥ ከበባው እንዳቆመ ወዲያውኑ ቱርኮች የእርቅ ውይይት ጀመሩ። ንጉሡ ከጂውን ወልደ አዙምን ማሳደድ ጀመረ። ዐቅባ ሚካኤለ ተከታትሉ ይዞ ገደለው። ንጉሥ ድባርዋ እንደተመለሰ እጅግ በጣም ብዙ ሰጠታዎች ከጋሻው የተላኩ አገኘ። አጼ መላክ ሰገድ ስጦታዎችን ተቀብለ እርቅና ሰላምም ወረደ። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ግንኙውም የቱርኮች መሰፋፋት ምኞት ለሁሉ ጊዜ አከተመ። ኢትዮጵያ ከባሕር ጠረፎች የሚመጡባት ሁሉ የታላቁ የቱርክ መንግሥት ወረራዎች እንዲሁም በሃይማኖት መነሻ በምሥራቅ ሱልጣኖች የሚፈጽም ጭምር የእርስ በእርስ መርሃቶች ከብዙ ዘመናት ፈተና በኋላ በእሸናፊነት ተወጥታለች።

11. የኦሮሞዎች መስፋፋት ክስተት

ኢትዮጵያ ልታሸንፈው ያልቻለችው ሌላ ጠላት ነበራት፣ ይኸውም የኦሮሞ የመስፋፋት ክስተት ነው። የኦሮሞ ከደቡብ ወደ መሐል ሀገር መስፋፋት ምክንያት ኢትዮጵያ ከባድ ውድቀት ደርሶባታል። የደቡብ ምዕራብና የምሥራቅ ከፍላተ ሀገሮቿ አንድታጣ ተገደደች። በነዚህ ከፍላተ ሀገሮች ይኖሩ የነበሩ ማንነታቸው በውል የማይታወቁ በአጠቃላይ ሲዳማ ወይንም አማራ ብለን የምንጠራቸው ሕዝቦች ከምድረ ገፅ ጠፍቷል፣ ባይጠፉም ቋንቋቸው፣ ባሕላቸው፣ ታሪካቸውና ሰማቸው ጠፍቶ በኦሮሞ ተተክቷል። አሁን ኦሮሞ ሕዝብ ተብለው ሰፍሮባቸው የሚገኙ መሬቶች ኦሮሞ ከመምጣታቸው በፊት ባዶ መሬት አልነበሩም፣ አማራ፣ ጉራጌ፣ ሌሎችም አሁን የደቡብ ሕዝቦች ብለን የምንጠራቸው ወይንም ሌሎች የጠፉት ሰፍረውባቸው ነበረ። ኦሮሞ ከመጡ በኋላ ግን በሙሉ ተገደሉ ለማለትም አይቻልም። ከኦሮሞ ጋራ ተቀላቅለው ዘራቸው ጠፋ ለማለት ይቀላል። ኦሮሞዎች እንደ ይፋት ወይንም እንደ አዳል መንግሥት አልነበራቸውም፣ ወረራ ፈጽመዋል ለማለትም አይቻልም። ኦሮሞዎች ያካሄዱት የመሬት ማስፋፋት ነው፣ ሰፈራ ነው። ኦሮሞዎች መንግሥት ስላልነበራቸው አንድ መሪ አልነበራቸውም፣ በይፋት፣ በአዳልና በቱርኮች ያልተሸፈነ የኢትዮጵያ መንግሥት በኦሮሞች ግን ተሸንፏል፣ ኦሮሞች እንደሌሎች ሕዝቦች ለምላሌ ለግሌ በጦሳ ተከፋፍለው እርስ በእርሳቸው የሚጣሉ አይደሉም። የኢትዮጵያ መንግሥት በሥልጣን ሹክቻ ወይንም በሐይማኖት ምክንያት ከግራኝ ከሐረር እስላማዊ መንግሥት ያደረጋቸው እርስ በእርስ ጦርነቶቹ በመዳከሙ ኦሮሞዎች ተጠቅመውበት ወደ ባለ ውድቀት እንዲደርስ አድርገውታል። ኦሮሞች አዲስ መሬት ለመያዝ እንደ ማዕበል ወደ ፊት ከመገስገስ በቀር የታወቀ ዓላማ አልነበራቸውም። መንግሥት ለማቋቋምም ዓላማ አልነበራቸውም፣ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ ስልጣን ለማጋራት ወይንም የነበረውን መንግሥት ገልብጠው ስልጣን ለመያዝ ዓላማ አልነበራቸውም። በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ጥላቻ እንዳልነበራቸው የሚያስረዳ አንዳንድ ነገሥታት ለውትድርና እየመለመሉ ይጠቀሙባቸው እንደነበሩ ብዙ ጊዜ ያጋጥም እንደነበረ ተዘግቧል።

ኤውሮጳውያን ታሪክ ጸሐፊዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ በጎሳና በቋንቋ ሲከፋፍሉት ኦሮሞችን ደቡባውያን የኩሽ ዘሮች ይመድቧቸዋል። የሀገራችን ታሪክ ጸሐፊዮችም የዚሁ ዓይነት አከፋፈል ነው የሚከተሉት። ይህ አሰራር ቋንቋና ጎሳን ለይቶ ለማወቅ ባለመቻሉ የአንድ ሰው ወይም ሕዝብ ማንነት ቋንቋው ብቸኛ መለኪያ በመውሰድ የሚደረገው የዘር አመዳደብ ዘዴ ነው። በቋንቋው ብቻ የአንድ ሕዝብ ማንነት መመደብ ግን ትክክለኛው ሊሆን አይችልም። በሰሜን ኢትዮጵያ ሴማዊ የተባለው የግእዝ ቋንቋ ከመስፋፋቱ በፊት ከዚያም በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እየፈለሰ ሰለሚሄድ ቋንቋውን ትቶ አዲስ የሰፈረበት ቦታ ቋንቋና ባሕል እንደሚይዝ የታወቀ ነው። ኦሮሞችም ከዚህ ሕግ አይወጡም። ቅድመ ታሪክ ኦሮሞዎች የሰፈሩበት ቦታ በሰሜን በደቡብ ወይንም በመሐል በምሥራቅ ኢትዮጵያ ይሁን አይታወቅም። አቶ ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ በኢትዮጵያ ታሪክ አንደኛ መጸሐፍ ገጽ 30 የሌሎች ጸሐፊዎች ታሪክ በመጥቀስ ከጉቢያ እስከ ኢርትራ ባሕር ተበታትኖ የነበረ ሕዝባችን የሰም ዝርዝር ሲሰጥ በቁጥር 18 ጋሊ የተባለውን ጋላ ብለው ተርጉመታል። መሠረት የሌለው አተረጓጎም

ነው ለግለት አይቻልም። የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ሆኖ ያገለገለ የነበረው ጉብኖው የክርስትና ሐይማኖት ተከታይ ሰው ቡትሮስ ጋሊ ሲሆን ይኸውም ስማቸው ወደ ዓረብኛ ያልቀየሩ የጥንት ጉብኖውያን ሰም ሊሆን ይችላል። ኢጣሊያዊው የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊ ኮንቲ ሮሲኒ ስለጥንታውያን ጉብፅ ጥልቅ ምርምር ያደረጉ የኤውሮጳ ታሪክ ፀሐፊዎች የሰጡት አስተያየት በመጸሐፉ እንደተገለጸው ኢልሚ አርማ (የአርማ ልጆች) ወይንም የኦሮሞ ልጆች ግለት መሆኑን የሚል ትርጉም ተሰጥቷል ይሄም ትርጉም የተሰጠው ቱቲ ሞሲስና ሌሎችም የጉብፅ ፈርአኖች ባሐውልቶቻቸው ስለአስገበሯቸው የኩሽ ዘሮች ሰም ዝርዝር ተቀርፆ በተገኙ ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ ነው።

ኮንቲ ሮሲኒ አስተማማኝ ታሪክነቱ በግሉ ቢከደውም ባለሞያዎች የሰጡት አስተያየት በደፈናው ሐሰት ነው ለግለት አይቻልም። አሮሞዎች ከ1520 ዓ.ም. በፊት ወደ መሐል ኢትዮጵያ ከመንቀሳቀሳቸው በፊት ደቡብ ኢትዮጵያ ቦረና አካባቢና ከኒያ ብቻ ሰፍረው እንደነበሩ የተረጋገጠ ነው። አሮሞች ሰፍረውበት የነበረ ዋናው ግአከል ዋላቡ ከአብያተ ሀይቅ በስተምሥራቅ የሚገኘው ተራራ ነው ተብሏል። በዚህ አንድ አውራጃ የማያሀል መሬት ሰፍረው ተውሰነው ለብዙ ዓመታት ይኖሩ የነበሩ አሮሞዎች በተቂት ዓመታት ውስጥ መላው ኢትዮጵያን ማተለቅለታቸው በየትም የዓለም ክፍሎች ያልታየ ታአምራዊ ክስተት ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት ብዙ ፈተናዎችን አልፎ ቋንቋውን ባሕሉን እና ስልጣኔውን ከሰሜንና ቀይ ባሕር አስክ አንድ ውቅያኖስ ሞንባላ በሚያስፋፉበት ጊዜ፣ አንድ መቶ መንግሥታት ወይንም 35 መንግሥታት ወዘተ... በስሩ አሉት ይባል የነበረው፣ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የአንድ አውራጃ ሕዝብ ብዛት እንኳን ያልነበራቸው አሮሞዎች ከስር መሠረቱ ሊያንኮታኩቱት የቻሉት በጦር መሣሪያ ተጠቅመው አይደለም። ጋዳ ወይም ጉዲፈቻ በተባለው የአስተዳደር ስልታቸው ተጠቅመው ነው። አሮሞዎች ለብዙ ዘመናት ከባንቱ ጎሳዎች በጉርብትና በኖሩበት ጊዜ ጋዳ የተባለው የዕድሜ ክልል መሠረት የሚያደርግ የአስተዳደር ዘዴ ከእነሱ በመውሰድ አስፋፍተውታል። በዚህ ፀባያቸው ከሌሎች የከም ዘሮች ይለያሉ። ሌሎች የከም ዘሮች ሁሉ እርስ በእርሳቸው የሚለያዩ በስጋ ዝምድና ሲሆን አሮሞዎች ግን እንደ ኮከብ ቆጠራ የአንድ ዕድሜ ክልል የሆኑ ሰዎች በአንድ ወገን ይመደባሉ። ጋዳ ብዙ ደረጃ አለው 1. ዳባሌ 2. ፎሌ 3. ቆንዳዳ 4. ዶሪ 5. ሉባ እየተባሉ ይጠራሉ። የጋዳ ደጋፊዎች ዲሞክራሲ አስተዳደር ነው ይሉታል። ነገር ግን እጅግ ጎላ ቀር የሆነ አስተደደር ዘዴ ነው። አሮሞዎች ወደ ሞሐል ሀገር ከመሰራጨታቸው በፊት የሐግኖት መሪዎቻቸውና ጠንቋዮቻቸው እባ ሙዳ ይባሉ ነበር። ሁለት እባ ሙዳዎች ነበሩ። አንዱ በዳሉ ጫካ በነናሌ ወንዝ አጠገብ ሁለተኛው በዋላቡ ተራራ። በጎላ ጊዜ አሮሞዎች ወደ መሐል ሀገር ዘልቀው ገብተው የባሌን መንግሥት በተቆጣጠሩበት ጊዜ የእባ ሙዳ መኖሪያ የአቡል ታሲን ተራራ ጫፍ ታዋቂው ጀሕ ይኖርበትና ያረፈበት ሆነ። የሁለቱ እምነቶች ተዋሕደው የአሮሞዎች ሁሉ ቅዱስ ቦታ ግአከል ለመሆን በቅተዋል። አሮሞዎች ለዘመናት በሰላም በደስታ ይኖርበት ከነበሩ ሰፈራቸው ለቀው ወደ መሐል ኢትዮጵያ እንዲሰራጩ ምክንያት የሆኗቸው ሶማሊዎች ናቸው ተብሏል። በግራኝ ጦርነት ጊዜ አሮሞች አይታወቁም ሰለነበረ ግራኝ ለውትድርና ሊመለምላቸው አላሰበም። ግራኝ ለተዋጊነት የተጠቀመባቸው ሶማሊዎች ብቻ ነበሩ። መጠነ ሰፊ የሆነ የቀንድ ከብቶች፣ ወርቅ የጦር መሣሪያና ባሮች

ከክርስቲያን ኢትዮጵያ ሶማሊዎች በግራኝ ጦርነት ጊዜ ዘርፈው ያመጧቸው ብዛየታቸው አሮሞዎች በሶማሊዎች ከመሬታቸው ሰለተፈናቀሉ ወደ መሐል ኢትዮጵያ እንደ ባሕር ማእከል ተሰራጩ። አሮሞዎች ከመምጣታቸው በፊት ምዕራብ ወለጋ እንፈሉ ተብሎ ይጠራ ነበረ። ወሎም የቀድሞ ሰመ እንጎት ነበረ ወዘተ... ጋፋት፣ ትልቁ ዳሞት፣ ዳሞር፣ ፋጢጋር፣ ግራ፣ አዳል፣ ወዘተ ተብለው ይጠሩ የነበሩ ከፍለተ ሀገሮች ወይንም መንግሥታት ታሪካቸውና ስማቸው ቋንቋቸውና ባሕላቸው ጠፍቷል፣ በአሮሞ ቋንቋና ባሕል ተተክቷል ወይንም ዘራቸው በሙሉ ጠፍቷል።

ይህ ታሪክ የተፈጸመው በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሲሆን አውራዎች እንኳን ዘራቸው አንዳይጠፋ እንክብካቤ ይደረግላቸዋል። በዛሬ አንድ መቶ ዓመት ላግማዊ አጼ ሚኒልክ የቀድሞ አባቶቻችን የነበሏት የኢትዮጵያ ግዛት አንድነት ባስከበረበት ጊዜ አንደገና ወደ ኢትዮጵያ የተቀላቀሉት ከፍለ ሀገሮች ቋንቋቸው እና ባሕላቸው እንኳን ባይቻል የቀድሞ ስማቸው እንዲያገኙ ማድረግ ይገባው ነበር። አጼ ምኒልክ ይሽንን ባለማድረጉ የኦሮሞ ቋንቋና ባሕል እንዳይኳኳ በማድረጉ የዛሬ አንደንድ አሮሞዎች አጼ ምኒልክን በወረራ እንደያዛቸው ሲቆጥሉ ይታያሉ። አጼ ሚኒልክ ያዘመተው የአማራ የኦሮሞ የትግሬ ወዘተ... ያሉበት የኢትዮጵያ ሠራዊትም ነፍጠኛ እየተባለ ስም ማጥፋትና ታሪካዊ ቅዱስ ጎላማውና ተልኮው የተወጣበት እድናቆትና ምስጋና ሲገባው የኢትዮጵያ ጠላቶች የሚያናፍሱትን ወሬ በማስተጋባት ይገኛሉ። ዛሬ አሮሞዎች የሰፈሩባቸው ከፍላተ ሀገሮች ምሥራቅ ደቡብና ምዕራብ ሸዋ፣ ሐረርጌ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ወለጋ፣ ኢሉባቡር እና ጅማ ባዶ መሬት አልነበሩም። ቅድመ አሮሞ የነበሩ ሕዝቦች በግዲታ የአሮሞ ቋንቋ በተዲፈቻ ሀመውሰድ አሮሞ ተባሉ አንጂ በዘር አሮሞ አይደሉም። ስለዚህ አሮሞ ቋንቋ ነው እንጂ ዘር አይደለም። በዘር ከሆነ አሮሞ የአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎሳዎች በውሰጡ ያቀፈ ነው። ስለዚህ አሮሞ ተናጋሪ የሆኑት የሁሉም የኢትዮጵያ ጎሳዎች ስለሆኑ በኢትዮጵያ ጎሳዎች ላይ ጥላቻና ቅራኔ ሊኖራቸው አይገባም። አሮሞ ሳይታሰብ ቋንቋውን በመላ ኢትዮጵያ አማርኛ ያልቻለው በተአምር ሊያስፋፋ ችሏል። ይህ በመሆኑ አሮሞዎች ሊደሰቱ ይገባቸዋል እንጂ በግንባር ቀደም በቋንቋችን እንዳንጠቀም ያለፉት መንግሥታት ጨቆኑኝ ለግለት አይችሉም። በአሮሞ ፋንታ አማርኛ ከዳር እስከዳር ባለመስፋፋቱ ቁጭት ሊኖራቸው የሚገባ አማርኛ ተናጋሪ ብቻ ሳይሆኑ ሀገሩን የሚወድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሊያድርበት ይገባል። በአሮሞ መሬታቸውን ተነጥቀው ባሕላቸውንና ቋንቋቸውን ያጡ ሕዝቦችም በፅድላቸው ሊያዝኑ ይችላሉ። የአሮሞ ሕዝብ ግን ከማንኛውም የኢትዮጵያ ሕዝብ በላይ መብቱ የተጠበቀለት ስለሆነ እሁን ሲነገር እንደምንሰማው መብቱ አልተከበረም ብሎ ቅሬታ ማሰማት ባለፈው ታሪካችን አንፃር ተቀባይነት የለውም። በማንኛውም ጦርነት እንደሚያጋጥም የምኒልክ ሠራዊትም በለላማዊ ሰዎች ላይ ጭፍጨፋ ተሠጽሞ ይሆናል፣ አሮሞዎች ከፈጸሙት ጭፍጨፋ ግን የሚነጻጸር አይደለም። ብዙ የሰው እልቂት የተፈጸመ ወቅት ቢኖርም በምኒልክ ዘመን ጊዜ ከሁሉ የባሰ በአሮሞዎች አካባቢ የተደረጉ ጦርነቶች አልነበረም። ከሁሉ የባሰ ጭፍጨፋ የተፈጸመው አሮሞዎች እንደ ጅግ አባጅፋር የተካፈሉበት በከፋ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ዘመን ጊዜ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ብዙ ቃላቶች ያለአግባብ እንጠቀማለን።

ለአሮሞዎችና በሌሎች ሕዝቦች ያለውና የነበረው ግንኙነቶች ወራሪና ተወራሪ ፕሮና ተገዥ ብለን ለመጠቀም ብንፈልግ ግን የአሮሞ ሕዝብ ወራሪ ነው እንጂ በሀገሩ ላይ አለተወረረም። ለም መሬት ነጥቆ ከሌሎች በመያዙ

ገዥ ነው እንጂ ተገዢ አይደለም። የአማርኛ ቋንቋ እንኳን የመንግሥት ቋንቋ ሆኖ ያላደረገው እሮሞዎች ሌሎች ሕዝቦች ቋንቋቸው ባሕላቸውና ስማቸው እንዲቀየሩ አድርገዋል። አማራ ማለት እንደ እሮሞ ቋንቋ ነው እንጂ የነሳ ስም አይደለም። አማርኛ እንደ እሮምኛ ብዙ ነሳዎች የሚጠቀመብት ቋንቋ ነው። አብዛኛው ዛሬ አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ዘራቸው አገው ነው፣ አገው ባይሆኑም ከትግራይ የመጡ ናቸው።

እሮሞኛ ቋንቋ እየተናገሩ እሮሞ እንዳልሆኑ ከሚያምኑ ሕዝቦች የወርጂ በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። ወርጂ ከትግራይ እንደሚመለዱ ያምናሉ።[1] በንጉሥ ዐምደ ፅዮን ዘመን ከአፋር ኗሪዎች እስላሞች ከሊሎች እስላሞችም ጋራ ሆነው ዐረ ክርስቲያን የኢትዮጵያ መንግሥት ግንባር የፈጠሩ ተብሰው ተጠቅሰዋል።[2] ዘራቸው ከአፋር ወይንም ከሰማሌ አይደሉም፣ ጉራጌዎች ከትግራይ መጣን እንደሚሉ፣ እንደዚሁም በሲዳማ የነበሩ የነገሥታት ዘራቸው ከትግራይ መሆኑን እንደሚያምኑ፣ ቡተመሳሳይ ወርጂ ከትግራይ መምጣታቸው ይናገራሉ። በአዋሽ ከእሮሞች ሚታ በቾ ይዋሰናሉ።

እሮሞች ዘታሪካቸው በሰማሌዎች ከሰሚን ወደ ደቡብ እንዲፈልሱ ተደርገዋል፣ በባንቱ ከደቡብ ወደ ሰሚን እንዲፈልሱ ተገፏል፣ ተጥሎም ከ100 ዓመት ባነስ ጊዜ ከሲዳማ (ደቡብ ሕዝቦች) እና ከአማራ ባደረጉዋቸው ጦርነቶች አሁን የሚኖሩባቸው ሰፋፊ መሬቶች ለማግኘት በቅቷል። በመሬሻም ጠብመንጃ ታጥቀው ሊዋጉዋቸው ከመጡ አዲሶች የአማራ ወራሪዎች ጋራ ፍጬዜ ይዘው እንኂን ለመከላከስ ሳይሞክሩ ነፃነታቸው ተነጥቀዋል በማለት ቸሩሲ ሰሰ እሮሞች መሰፋፋት ከስተት ባጭር ገልጸታል[3]። እሮሞ ድል የተመቱበት የማሩ ኩሪቾ (Sella Maru) በተባለው ቦታ በራስ ጉብና የሚመራው ዘኢትዮጵያ ሠራዊት ነው። ራስ ጉብና ጨቦ በእሮሞች ላይ ጦርነት ገጥሞ ድል ተጐናጽፎ ወደ ጊዜና ምዕራብ ኢትዮጵያ ለመገስገስ መንገድ የከፈተበት ወሳኝ ድል የተጐናጸፈበት ቦታ ነው።

1. ጋዳ አስተዳደር

የእሮሞና የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ ብዙ አይታወቅም። ስለ እሮሞ ተጽፎ የሚገኘው ስለ ጋዳ የዕድሜ አስተዳደር ነው። ቸሩሲ እንዳጸፈው ከባንቱ የተወረሰው የጋዳ አስተደደር መሠረት በድሮ ጊዜ እንድ ጐሣ በሁለት ዘር የተከፈ 10 የጋዳ ደረጃዎች ነበሩት። አባትና ልጅ በተቃራኒ ጋዳ ሲመደቡ፣ የልጅ ልጅ ከአያቱ ጋራ ይመደባል። እንደዚህ እያለ በየ8 ዓመት እየተቀያየረ 1ኛ ደባለ ከ1 እስከ 8 ዓመት ዕድሜ 2ኛ ፎሌ ከ8 እስከ 16 3ኛ. ቆንዳላ ከ17 እስከ 24 4ኛ ቆሬ ከ25 እስከ 28 5ኛ ሉባ ከ29 እስከ 32 6ኛ. ዩባ ከ33 እስከ 40 ተብለው የሚጠሩ ይከፈላሉ። የፖለቲካ ሥልጣን የሚገኘው በግል ችሎታ ሳይሆን በዕድሜ ነው። ልዩ ሥነ ሥርዓት እየተደረገ 8 ዓመት እንደተቈጠረ ከእንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ ይዛወራሉ። ይህ ጥንታዊ የጋዳ አስተዳደር ሳይቀየር የቀጠለው በክርስቲያን እሮሞች ብቻ ነው፣ እስልምና የተቀበሉ ግን ጋዳ አስተዳደር ከእምነታቸው ጋራ አልተጣጣመም። በሸዋ የሚኖሩ የእሮሞ

[1] Cerulli : Etiopia occidentale p. 14
[2] Cerulli : ibd p. 14
[3] Cerulli ibd p. 19

ጐሣዎች ጥንት 10 ጋዳ የነበሩ ለእምስት ስለተጠቃለሉ አባት ልጅና የልጅ ልጅ ወዙተ ባንድ ይመደባሉ 1ኛ ጂደ 2ኛ አቢቹ 3ኛ. ጉምቢቹ 4ኛ. ሚቶ 5ኛ ጉለሌ 6ኛ. እቦራ የሚባሉ በምዕራብና ደቡብ ሸዋ የሚኖሩ የእሮሞ ጐሣዎች በመሃላቸው ጥቃቅን ልዩነቶች ቢኖራቸውም የጋዳ ስምና ደረጃ ተመሣሣይ ነው። የጋዳ ስሞች 1ኛ. ሆራታ 2ኛ. ሚቺሌ 3ኛ. ዴሎ 4ኛ. ሮባሌ 5ኛ. ቢርማጂ ተብለው ይጠራሉ። የጋዳ ደረጃዎች 1ኛ. ደባለ ነኛ. ፎሌ 3ኛ. ቀንዳላ 4ኛ. ዶሪ 5ኛ. ሉባ 6ኛ ዮባ ናቸው። በጂዳ ጐሣዎች ዶሪና ሉባ ለ4 ዓመት ብቻ ስለሚቈዩ የአንድ ደረጃ ንኡስ ክፍል ናቸው። በአቢቹ ጐሣ ዶሪ ቀርቷል፣ 8 ዓመት ሲጨርሱ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጀ በሚተላለፉበት የሚደረገው ሥነ ሥርዓት ቡታ ይባላል። ዩባ ደረጃ ካላቸው አንዱ ተመርጦ አባ ዳባለ እየተባለ ጋዳ የሚጀምሩ ልጆችን ይሁ ለተሰበሰበው ሕዝብ ያቀርባቸዋል። ከሥነ ሥርዓቱ በኋላ ዩባ የሆኑ ሁሉ ይገረሳሉ። ፎሌ ደረጃ ያሉት ሁሉ ጅንጀሮ ቆዳ ፊታቸውን ሽፍነው ፎጀርሳ የተባለው ዱላ ይዘው ይዘዋወራሉ። ከመሃከላቸው ዘፎጀርሳ ዱላ ደብድቦ ከራሣቸው ጐሳ ውስጥ አንድ ፍየል ወይንም አንድ በግ መዝረፍ የቻለ "ሐዩ" ተብሎ አለቃቸው ይሾማል። የተዘረዘፈው በግ ወይንም ፍየል ወዲያውኑ ተሰብስበው ይበሉታል። ዶሪ ወደ ሉባ ደረጃ ሲሸጋገሩ የሚደረገው ቡታ በሬ አርደው ሥነ ሥርዓት እሰቃቸው ሐዩን ይመርጡና፣ ሳሱም ጠጉሩ ተላጭቶ፣ ውተት ፈሰበት፣ በለባ ደባለ እጅ ፊቱ በበሬ ቆዳ ግንባርና ቀንድ ይሸፈናል፣ እንደ በሬም ይጮሃል። ይህ ሽፋን ሐርዙ ይባላል። ጐሣቸውን ለመምራት የፖለቲካ ሥልጣን የሚሰጣቸው ዶሪ ወይንም ሉባ ደረጃ ያላቸው ናቸው። ናቱ ደረጃዎች የጐሣ አባላት ለጋብቻ ዘር ለመቀጠር ይጠቀመብታል። ከ5 ተውልድ በላይ ካልተቈጠረ ጋብቻ አይፈቀድም።

እሮሞች እጹ ምኒልክ ከሞቱ ጋራ ከማዋሐዱ በፊት የ365 ቀናት የጎሰት መቁጠሪያ ነበራቸው። ዓመቱ የሚጀምረው በመስቀል ስለሆነ የጥንት ከኢትዮጵያ አንድነታቸው የሚያሳይ ምልክት ነው። / 1.መዳ መስከረም 2 ሐደሲኛ ነሐሴ ዳዋ ጥቅምት 4 ዋር ጥሪ፣ ጎዳር/ 5 ፋርማ (Furma) የካቲት 6 ሺያን ሰኔ 7 ቦሩ ሺያን ሐምሌ።
በሰማሌም የዓመት መጀመሪያ ቀን እሳት በማንደድ ይከበራል።[1]

እሮሞች በዙቋላ የሚገኘውን የአቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ገዳም አቦ (አቡነ) በማለት ያከብሩታል። አሶ የሚል አጠራር በሁሉም የተለመደ ነው። እንደዚሁም በፊንፊኔ ጠበል ለአቦ ክብር እየተባለ በየዓመቱ በውሃው ውስጥ የፍየል ወተት ማፍሰስ፣ የወፎች ጠጉር ማበርከት ልምድ ነበረ። በተራሮችና በምንሮች እምነት ማዘውተር ከጣእት እምነት የመጣ ነው ቢባልም፣ ከርስቲያንም በጣእት እምነት የተተካ ስለሆነ የቀደምት አባቶቻችን የኢትዮጵያ የጋራ የክርስቲያን እምነት ምልክት መሆን አለበት[2]።

2. እሮሞና ሲዳማ

በእሮሞች ወረራ ዘራቸውና ቋንቋቸው የጠፋ የሲዳማ ሕዝቦች የመጨረሻዎቹ ከእዔ ምኒልክ ዘመን በፊት በጅግ እካባቢ ብዙ እርምኛ ያልሆኑ ቃላቶች ይቀላቀላሉ። ንጉሥ ለማለት በእርምኛ ሞቲ ሲሆን በልግድ ግን ጐይታ ተብሎ ይጠራል፣ ጐይታም ወደ ጎፍታ ተቀይረዋል 2 አልጋ

[1] Cerulli ibd p 58
[2] Cerulli ibd p 59

ወራሽ ከሲዳማ ቋንቋ ተወስዶ ዶናቾ ተብሎ ይጠራል። 3 የንጉሡ ሚስት ከሲዳማ ቋንቋ ተወስዶ ጌን ተብላ ትጠራለች። በጅማ አካባቢ የነበሩ ነገሥታት እንዳንድ ጉማዎች በጅምላ እንደ ባሪያ የመቍጠር ባሕል ነበራቸው። ጅማ አባ ጅፋር ይህ ባሕል ተቀብሎ አጋንና በሥራ ላይ ያዋለው በጃንጀሮ ሕዝብ ላይ ነው። ጅማ አባ ጅፋር እዬ ምኒልክ ምዕራብ ኢትዮጵያን በምይዝበት ጊዜ ከጦሩ ጋራ በመተባበሩ ውለታ ለመክፈል ጃንጀር ከጦቡ ጋራ እንዲያጠቃልለው ተሰጥቶት ነበር። በዚሁ መብት በመጠቀም ጅማ አባ ጅፋር የጃንጀር ሕዝብ የእሱ ባሪያ ሕዝብ መሆኑን እውጆ ግማሹ በከልሉ እየኖረ የሚሸጥ የሚሰወጥ ሲያደርገው ግማሹ በባርነት መልክ ወደ ምዕራብ ጅማ እንዲዛወር ተገዷል። ይህ ሁኔታ እይቶ ሀገሪ ጠርው የነበረው ራስ ተሰማ የጃንጀር ሕዝብ እስተዳደር ከአባ ጅፋር ነጥቆ በእንድ አማራ እንዲስተዳደር ሥር ሰግድረግ ግድ ሆነበት። 5 ጅማ አባ ጅፋር ወሮ ይዞ ከጦቱ የቀለቀላቸው የሲዳማ መንግሥታት የመጨረሻ ቦሻ ነው። ስሙ ቀይሮ ግን ጋኖ ተብሎ ተሰይሞ የጅማ ከፍሰ ሀገር አካል ሆነዋል። ቦሻ ከከፋ ተመግሣይ ጉማ ሲዳማ ናቸው፣ ሁስት ቋንቋ ተናጋሪ ሆነዋል፣ ቋንቋቸውና አርምኖ። በጅማ ኩተገቡ ጀምሮ ሁሉም የእስልምና ሃይማኖት ተቀብሏል የቁድሞ የቦሻ ነገሥታት ወራሾች ከፈል እሰረኛ በመሆን ጅረን ኩተማ (ጅማ ኩተማ) እጠገብ እንዲቀመጡ ተገዷል። ስማቸው አባ ቡቸያን ቡሳሲዬ ይባላሉ። የቦሻ ነገሥታት ዘር ሐረግ ሰከፋ፣ ለምጫና ለእንፊሉ ነገሥታት የሚሆኑ ሰዎች የሰጡ ናቸው።

6 የጅማ ወሰን መግቢያ በሲዳማ እጠራር ከላ ይባላል፣ ነፃ መንግሥታት በነበሩ ጊዜም ገለልተኛ በወሰናቸው የሚገኘው መሬት "ሞገ" የተባሰ ነበረ።

7 ጅማ ሌሎችም ድሮ የእርሞ ነፃ መንግሥታት የነበሩ የሚስተደደሩ ከሲዳማ የተወሰደ በዘውድ እገዛ ስሰሆን የጋዳ አስተደደር አሰራር ጨርሰ ባይቀርም ንጉሡ የማይሾማቸው ባሰሥልጣናት በሕዝብ ብቻ የሚመረጡ ሊኖሩ ስለማይችሉ የጋዳ አሰራር ከአዲሱ ሥርዓት መጣጣም ግድ ሆኖበት ነበር። የጋዳ ደረጃዎች ስሁስት ብቻ ተቀንሱ ራባና ሉባ የሚባሉ። ጋዳ የሚደረጅው በጉማ መሆኑ ቀርቶ በመንደር ነበር።

8 የጅማ እርሞች እስልምና ሃይማኖት የተቀበሉ በቅርብ ጊዜ ነው፣ ባለፈው መቶ ዘመን አጋማሽ ነው፣ ሊቀበሉ የቻሉም ንጉሣቸው በወርጂና በዳሪታ የጉንደር እስላሞች ነጋዲዎች ተሰብከ በመጀመሪያ እስልምና ሲቀበል፣ ዘንቹም በእስላሞች የታረደ ሥጋ እንዲበሉ ስላስገደዲቸው ነው። ማንኛው ሰው ያረደው ሥጋ መብላት የዝትተኛ ዘሮች ምልክት ይቈጠር ስሰነበረ ግዲታ እስላሞች መሆን ነበረባቸው። እስካሁን ድረስ የጅማ እስላሞች መስያ የሆነው እንደ ክርስቲያኖች ጠላና ጠጅ መጠጣታቸውና ሜት አለማዘውተራቸው ነው።

9 ጅማ በእርሞች ከመያዙ በፊት ከከፋ ሕዝብ ተመግሣይ ዘር የሆኑ የሲዳማ ሕዝቦች በንጉሥ እገዛ የሚስተዳደሩ ይኖሩበት ነበር[1]። እርሞች ከቀድሞ ነዋሪዎች ከሲዳማ ተምረው የጋዳ አስተዳደር አሰቀርተው የዘውድ እገዛ ተቀበሉ። እንዳንድ የእርሞ የጉማ መሪ የሀገር መሪ (ንጉሥ) ከእነሱ ጉማ ብቻ እንዲሆን ከመቻላቸውም በላይ፣ ከሕዝብ የሚመረጥም በጋዳ ሳይሆን በውርስ ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ አደረጉ። የዚህም ምሳሌ የታየው በሲየካ ቀለም ሞቲ ተብሎ የሚጠራ ነበር፣ በሕዝብ የሚመረጠው ግን ሊየካ ዋዩ ይባል ነበር (Lieca wayou)

(1) Cerulli ibd p 91

10 ከላ በከፋ ቋንቋ የቤት በር ሲሆን እርሞች ግን፣ የነበሩ መንግሥታት ወሰን ለማመልከት ብቻ ይጠቀሙብት ነበር።

11 በእርሞች ስሴቶች ሥልጣን መስጠት ልምድ አልነበረም፣ ከሲዳማ ተምረው ግን ሌቶች ሥልጣን ተሰሚቸው "ጌን" ጌታ ንግሥት ተባሉ። መስፍን፣ አልጋ ወራሽም ከሲዳማ ተወስዶ ነውቲ፣ ዳኛ "ወደ ደንዞ" "ዶንዲዮ" "ዶናጂዮ" እየተሰወጠ በከፋ በ ሚጫ በአንፊሉ መስፍን ሰማት የሚጠቀመብት ነበር።

12 በሰው ስም ብቻ ሳይሆን ከሲዳማ የተዉረሱ በሀገርና በቦታ ስሞችም እርሞች ሲጠቀሙብት ይታያሉ። የቦሰ ተራራ (ጅማ የሚገኘው) በሸ ከሚባሰው የከፋ ጉማና ቦሺያ ከሚባለው የሲዳማ መንግሥት የተወሰደ ነው። ግና የሚባል ሰፈር በጅማና በከፋ አሉ። በጅማ ሳራዶ ተራራና ሳደሮ ወረዳ ሲኖር በከፋ ሺራይ ወረዳ አስ። ጌሺ ወረዳ በጅማ ሲኖር በከፋ ጌሽ አስ። በደቡባዊ ጅማ ስማጀ ተብሎ የሚጠራ ወረዳ በከፋ ሺየማዶ የሚባል አስ። የሊሙ ዋና ኩተማ ኮሳ ሲሆን በከፋም ኮሺየ የሚጠራ አስ። የሊሙ ሳጋ ኩተማ ሲኖር በከፋ ሺያጋ አስ። የእገዚአትን ግርየም መቅደስ በሊሙ ጉዶ ግርያም ተብሎ የሚጠሩ ተራራ ሲኖር ጉዶ ግስት በከፋ ተራራ ግስት ነው። የጉማ መንግሥት የነበረው ስም በከፋ የአንድ ወንዝ ስም ነው። በጉማ የአጋር መንደር ሲኖር በከፋም አጋር የሚባል መንደር አለ። በጅማ የሚገኘው ያቦ ወንዝ ከከፋ ያቦ ዘባባ የተወሰደ ነው። የጌራ ወና ኩተማ የነበራቸው ቹራ በከፋ ስመ ጥሩ ሺፒናዎ የኖረበት የተወሰደ ቦታ አለ። እንደራቻ የስው ስም በጌራ ዋና ኩተማ አጠገብ የሚገኘው ቦታ የከፋና ሚጫ ዋና ኩተማ ስም ነው። በጅማ የኪየቾኮ ጠበል ሲኖር፣ በከፋም ኪየሺዮ ፍል ውሃ ጠበል ይገኛል። ያንጋቺያ የሚባለው የጌራ ከከፋ ኢንጋጂያ የመጣ ነው። የጠበቀ ጥናት ቢደረግ ብዙ ሌሎች ስሞች ሊገኙ ይችላሉ[1]።

ቸሩሲ ከኢትዮጵያውያን አዋቂዮች አገኘሁ ብሉ እንደዘገበው የዛሬዪቱ ጅማ ከልል ስሜን ምሥራቅ የጃንጀር መሐልና ደቡብ ከፍል የቦሻ እንስተኛ ከፍልም የአናሪያ ነበረ። የዛሬዪቱ ቦሻ ገደላግደል በመሆኑ ከሰሜንና ከምዕራብ የመጡቸው ጠላቶች በመከላከል ሽሽተው የስፈናበት ይመስላል። ተዋቂው በነበረ የአናሪያ መንግሥት ዛሬ በእርሞች ወረራ ከምድረ ገጽ የጠፉ ይናገረው የነበረ ቋንቋ ይበልጥ ተመግሣይነት የነበረው ከከፋ ሣይሆን ከሸሻ ቋንቋ ነበረ። እርሞች ወደ ጅማ የመጡበት አቅጣጫ በሚመስከትም ሁሉም በአፈ ታሪክ የሚያረጋግጡት የጅማ እርሞች ከመጫ እርሞች አንድ ክፍል (አንድ ጉማ) መሆናቸውና ከወለጋ ወለል ከሚባለው ቦታ መመጣታቸውን ይናገራሉ። 6ቱ የጅማ ጉማዎች ከወለል ተነስተው ወደ ምሥራቅ አምርተው ግማሾቹ በደቡብ የነበረው የሲዳማ ሀገር በመያዝ የዛሬዪቱ ጅማ መሠረቱ። እርሞች ወደ ጅማ የገቡ በስተሰሜን ከጃንጀር የነበረው ጠባብ መተላለፊያ መሆኑን ይጠቁማል። አሁንም ከዳደሌና ድኖ የመጫ ጉማዎች ኩታ ገጠም ይኖሩ፣ ከዚህም ወደ ምዕራብ የወለጋ ሊየካ ይገኛሉ። ከ6ቱ የጅማ ጉማዎች ወደ ደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ ወረራ ያልተካፈሉ እስካሁን ከአባይ እስከ ገቤ ወንዝ ሰፍረው የሚገኙ ጅማ ገቦ 2 ጅማ ሆር 3 ጅማ ራፌ 4 ከሞማ ወንዝ የዲደሳ ገባር አካባቢ ጅማ አርጆ ሲሆኑ ሁሉም ከጅማ አባ ጅፋር ዝምድና እንዳላቸው የሚያስታወሱ ናቸው። እርሞች ወደ ጅማ የመጡበት ዓመተ ምህረት በትክክል ባይታወቅም 1567 እና 1568 አዬ መላክ ሰንድ ወደ እናሪያና ቦሻ የመጣበት ጊዜ የንጉሡ ታሪክ

(1) Cerulli ibd p 101 - 2

ፀሐፊ በአነዚህ መንግሥታት እሮሞች መገኘታቸው አልመዘገበም፣ ዳሩ ግን በ1703 ዓ.ም. ትልቁ አፄ ኢያሱ ቀዳማዊ ወደ እናሪያ ሲዘምት ሀገሩ በሚጨ እሮሞች ተከበ ስላገኘው በጦር ኃይል ጦርነት በማካሄድ ብቻ መንዳሩን በመከፈት ወደ እናሪያ የሲዳማ መንግሥት ሲደርስ ችሏል።

ከ1419 እስከ 1429 ዓ.ም. የነገሡው የአፄ ይስሐቅ ታሪክ ፀሐፊ ቦሻ ለኢትዮጵያ መንግሥት ግብር በወርቅ ከሚከፍሉ ግዛቶች እንዱ እንደነበረ፣ የእናሪያ አዋሳኝ እንደነበረ ስለተዘገበ የድሮ ቦሻ የዛሬ ጅማ በእሮሞች ሲያዝ ስሙ ጅማ ካካ ነበረ። ካካ በእሮሞ ቋንቋ ዘረፋ ግለት ስለሆነ ሀገሩ በዘራፊዎች እንደተያዘ ያሳያል። ቀጥሎም የአባ ጅፋር ጉሳ ባዲ ለሚባል ሀገሩ ጅማ ባዲ ተብሎ ይጠራ ነበር። በ1840 በዳባዲ ዘመን (Abbadie) ጅማ በዚሁ ስም ትጠራ ነበር። በመጨረሻም በንጉሣዊ ስም ጅማ አባ ጅፋር ተብላ ተጠራች።

ጅማን ለማስገበር የጉጃሙ ንጉሥ ተክለሃይማኖትና የሸዋው ምኒልክ ለውድድር ቀርበው በ1883 በእምባበ ጀኑዋሪ ጦርነት ገጥመው ጉጃም በመሸነፉ ጅማ ወደ ሀገሩ የሚገቡ ነጋዲዎች ምኒልክን በጦር ኃይል መቋቋም እንደማይችል በሰጡት ምክር መሠረት ተሽቀዳድሞ ከንጉሥ ምኒልክ በመሰማማት ከሲሎች የእሮሞ መንግሥታት ተለይቶ ለንጉሥ ምኒልክ መገበር ጀመረ።' በዚህም ምክንያት የውስጥ አስተዳደር ነፃነት (ራስ ገዝ) አግኝቶ በኢትዮጵያ ወታደሮች ላይያዝ ለመኖር በቅቷል። ሌሎች የእሮሞ መንግሥታት ግን በሰላም መገበር ባለመፍቀዳቸው በጦር ኃይል ብቻ በምኒልክ ጦር ሲያዙ ችሏል። የጅማ ዋና ከተማ በድሮ ጊዜ ጂረን ተብላ ትጠራ ነበር። አሁን ግን ዋና ከተማዋም ከፍለ ሀገሩም ለሙ ጅማ ተብለው ይጠራሉ። የጅማ አካባቢ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ ከተዋሐደ ጀምሮ ዝነኛው የእናሪያ መንግሥት የቀድሞ ስሙ ግማኘት ነበረበት፣ ይህ ባለመደረጉ የኢትዮጵያ መንግሥት ደካማነት ያሳያል። የሲሙ ጉሣ እንደ ጅማ ከተሳ ወሰል ወሊጋ የመጡ ናቸው። በቀድሞ ጊዜ የእናሪያ መንግሥት (በከፋ ቋንቋ ኢኖእሪ ቶቶ) ከጉደብ ወንዝ ዳሪቻ ግራና ቀኝ የሚገኙ መሬቶች ያጠቃልል ነበር። ከእናሪያ ነገሥታት ትልቁ ዝነኛው ቪፒናዎ ነበረ። ዋና ከተማው ቾሪኮ አጠገብ ነበረ። በኋላ ግን በእሮሞች ስለተሸነፈ ወደ ከፋ ክፍል ጉጀብ ተሰዶ ሄዶ ጭሳ በተባለው ቦታ ጋዋተ ራቪዮ የከፋ ክፍለ ሀገር መቀመጫው አድርጎ ይኖር ነበር። በከፋ መንግሥት ዘመን በኢትዮጵያ አሰኩተያዘበት ድረስ የእናሪያ ንጉሥ የክብር መጠሪያ ብቻ ሆኖ ቆይቶ ነበረ። የእናሪያ ነገሥታት ወርቅ፣ በስደት የነበሩ የእናሪያ ነገሥታት ከልጅ ወደ የልጅ ልጅ ያስተላልፍ ነበር። የቪፒናዎ ዋና ከተማ ቾሪኮ የምትገኘው ጌራ ውስጥ ቺያዳ በተባለው ተራራ ስር ዋራ በተባለው ቦታ የአምልኮት ቅዱስ ቦታ የነበረው አጠገብ ነበረች። ስለዚህ የእናሪያ መንግሥት ግዛት በሲሙ ብቻ የተወሰነ አልነበረም፣ በትክክል ባይታወቅም ሰፊ ግዛት ያጠቃልል እንደነበረ ይገመታል። ቪፒናዎ ክርስቲያን ንጉሥ ኢየሩሳሌምን ሰመሳለም የሄደው ከሀገሩ የመጀመሪያ ሰው ነው። ከኢየሩሳሌም ሲመለሱ ታቦት ይዞ መጥቷል። ስለ ቪፒናዎ በአፈታሪክ የሚወራ ብዙ ነው። ቪፒናዎ በእናሪያ ቤተክርስቲያን ሰርቷል፣ ከዚህ በኋላ እንድ ትልቅ ዘመቻ ወደ ከፋ አድርገዋል። ቪፒናዎ በመንገድ ሲጓዝ ሴሎች ሰዎች የሚጠቀሙበት አይሄድም። ከሠራዊቱ ጋራ ሲሄድ በአቋራጭ መንገድ ይጓዝ ነበር። በጉዞው መሰናክል እያጋጥመውም፣ በወንዞች ሲያልፍ ከመቅጽበት ትልቅ ድልድዮች ሠርቶ ያልፋል። በሰው እግር ለማለፍ የሚዳጉቱ ተራራዎች ሲያጋጥሙት በጉራዲው በመስበር ያልፍ ነበር። ዛሬ እንደራቻ አጠገብ በረታ ወንዝ

በጉርጉቶ በቪፒናዎ የተሰራ ቸሩ በተባለው ቦታ ላይ በኩታ ክፍለ ሀገር አንድ ደንጋያማ ተራራ የእናሪያ ንጉሥ በጉራዴ የሰበረው ተመልካች ሁሉ የሚያደንቅቸው ይታያሉ። ቪፒናዎ ወደ ከፋ በምዕራብ በኩል ገብቶ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አነፀ፣ ከኢየሩሳሌም ያመጣው ታቦትም አረገበት። ከዘህም ወደ ጠቋቁሮች ሀገር ወደ ሻሻ ደርሶ ከዚያ ወዲት እንደሄደ ላይታወቅ ጠፋ። ይህ እንደ ተረት የሚነገርለት የእናሪያ ንጉሥ ኮንቲ ሮሲኒ በእፄ መላክ ሰገድ ክርስትና የተነሳ የእናሪያ ንጉሥ ስፐንሒ መሆኑን ትርጉም ሰጥቷታል። በበሐ ቅዱስ ጊዮርጊስ ታቦት መመሥረቱ እውነት መሆኑን የተረጋገጠ ነው። በታቦቱ ያለው ጽሑፍ በጊራ ወረዳ ይኖር የነበረ ካቶሲክ ቄስ ሚሲዮናዊ አባ ለዮን ቀድቶ ስለወሰደው፣ አንድ ኢጣሊያዊ ምሑር ተርጉሞታል[1] ትልቁ ዳሞት ሳይቀር ሁሉም ሌሎች የሲዳማ መንግሥታት በእሮሞች ወረራ ፈራርሰው ሲጠፉ በምዕራብ ከሚገኙ ለዘመናት በንጉሣዊ አገዛዝ የሚስተዳደሩ ብርቱ ትግል አድርጎ ሳይጠፉ መኖር የቻሉየከፋ መንግሥት ብቻ ነው።

የእሮሞ ለዎች አንድ አማራ መግደል ዘራ እንደ መግደል ነው ብለው ሲኮሩ የከፋ ለዎችም በበኩላቸው እንድ እሮሞ መግደል ኩበት እንደመግደል ይቁጠራል እያሉ ይዘፍኑ ነበር። የከፋ መንግሥት ሕልውናን ማስጠበቁ ብቻ ሳይሆን የሲዳማ ነገሥታት ዘር የነበሩ በእሮሞች ሲወረሩ በግዛቱ በክብር የንጉሥ የክብር ማዕረግ ተሰሟቸው እንዲኖሩ ያደርግ ነበር። ለዚሁም የበቁ የዳሞትና የእናሪያ ነግሣታት ይጠቀሳሉ። ይኸንም የሚያደርግበት ምክንያት የራሱ ዘር የሲዳማ ዘር በመሆናቸውና የማይዘገርጉቱ እምነት ስለነበረው የምዕራብ ሲዳማ መንግሥታት ጠባቂ መሆኑም እምነት ስለነበረው ከአፄ ምኒልክ ሠራዊትም ጭምር ራሱን ለመከላከል እንደሚችል የነበረው እምነት፣ በእሮሞች ላይ በነበረው የበላይነት ስሜት ተደፋፍሮ ነው። ይህ በመሆኑ ከፋ በአፄ ምኒልክ ሠራዊት የተሸነፈው ለ17 ዓመት ከተዋጋ በኋላ ነው። ከፋ ከጥንት ጀምሮ በዘውድ አገዛዝ የተመሠረተ መንግሥት መሆኑን በምላሌነት የሚጠቀስ ነው። ንጉሡ የሚገኝ ጉሣ የበላሾ ቤተሰብ ነበረ። የንጉሡ ፈላጭ ቆራጭነት ገደበ የሚወሰኑ ደምቦችም ነበሩ። ① የንጉሡ የክብር ዘበኛ አዛዥ የሚሆነው ካታማ ራቪዮ የሚባለው ከዚዮ ጉሣ ይመረጣል። ② የጊምቦ ክፍለ ሀገር አስተዳደሪ ከኢርጎ ጉሣ ③ የቢታ አስተዳዳሪ ከአማሮ ጉሣ ብቻ መመረጥ ነበረባቸው ወሰኑ። ሹመቱም የሚሰጠው በልምድ ነበረ፣ ጉሣው በሚኖርበት አካባቢ አልነበረም። የከፋ ንጉሥ እንደ መልአክ ይቁጠር ነበር፣ ዜጎቹም ፊቱን ከማየት ይቁጠቡ ነበረ። የመጨረሻም የከፋ ንጉሥ ዘውድ የነበረ አፄ ምኒልክ ለሰዋተዘርላንድ ተወላጅ ኢልግ ስለሰጠው በዙሪያ በሚገኘው በመሐንዲሱ ቤተሰብ ቤት ተቀምጦ ይገኛል። የንጉሡ መቀመጫ (ዋና ከተማ) ቦንጋ (ቦንጌ ዳቦ Bonghe Dabbo) በተባለው ንጉሡ ለሰማይ እግዚአብሔር አምልኮት ያደርግበት በነበረው ተራሪ ፊት ለፊት ነበረ። 10 ኪሎ ሜትር ክቦንጋ የሚርቅ በእንደራቻ የከፋ ንጉሥ ሌላ ሁለተኛ መቀመጫ ነበረው ይህ ቦታ ግን ለውጭ ሰዎች የተከለከለ ነበረ። ንጉሡ የሚሰራው ሥራ ሁሉ ቁጥጥር ይደረግበት ነበር። አታለች የተባለ ሰው ንጉሡ የሚበላውና የሚጠጣው የሚቆጣጠር ነበረ። ንጉሡ ብዙ እንዳይበላም እንዳይጣጣም መከልከል መብት ነበረው። የንጉሡ ሥራዎች የሚከተሉት ነበሩ 1. ሀገረ ገዢዎች መሾም፣ 2. ከውጭ መንግሥታት ጋራ በመልእክተኞች በኩል ግንኙነት ማድረግ፣ 3. የዳኝነት ሥራ፣ የሞት ቅጣት፣

[1] Cerulli ibd p 197

በባርነት የሚሸጥ መብት። በክፋ በተለይ ለባርነት የሚዳረጉ ሰዎች ቁጥር፣ ቡዳ ተብለው የሚከሰሱ ሰዎች ናቸው። ዶቾ (Doccio) በተባሉ ቁሶች በኩል ለፍርድ ወደ ንጉሡ ሲቀርቡ ያለ ምንም ሊለ ማስረጃ ይገባኝ የሌለበት ባርያ ተብለው ይፈረድባቸው ነበር። 4. በመርነት ተሸንፈው ስለተማረኩ ሰዎች ፅ ጣ፣ ንጉሡ ባሪያ እንዲሆኑ ማድረግ ወይም አለማድረግ መብት ነበረው። ባሪያ ናቸው ከተባሉ ንጉሡ በወየቀ ጊዜ ወደ ውጭ የሚሸጡ ናቸው። የዚሁ ዓይነት ዕድል ያጋጠማቸው ናቸ የሚባሉ ከሚሩ ጐሣ የሚመነሠሡ፣ ከክፋ ደቡብ የሚገኝ ናቸው፣ ለንጉሡም የገቢ ምንጭ ናቸው፣ ታቲ ናቸ (tate nao) ይባሉ ነበር (የንጉሡ ናአ)። በአርሞ ነገሥታትም ናአ ሞቲ እየተባሉ በታማኝነታቸው ተፈላጊ ነበሩ። 5. ንጉሡ የዝቅተኛ ዘሮች የበላይ ጠባቂ ነበረ፣ እንደ ብረት ቀጥቃጭ ሸክላ ሠሪ (Manna) እዝማሬ፣ ማንጆ (Manjio tato) ማንጆ ታቶ ለንጉሡ ብቻ ወርቅ የሚሠራ ነው። በጂግ አባ ጅፋርም ወርቅ ሰሪ ለንጉሡ ብቻ ነው ወርቅ የሚሠራ 6. ንጉሡ የውጭ ሀገር ሰዎች ጠባቂ ነው፣ ወደ ክፋ የሚገቡ ነጋዴዎች ብቻ ነበሩ። ዝቡያዎች ለክርስቲያን በቦንጋና በካያ ብቻ ነበሩ። በቋሚነት ኗሪ መሆን ለሚፈልጉ እስላሞች 15 ኪሱ ሚትር ርቀት ከካያ በሚገኘው ቶንኮላ በተባለው ቦታ እንዲሰፍሩ ይደረግ ነበር። ክርስቲያን በካሬኛ አሮ በቦንጋ ልዩ መንደር ተሰጥቷቸው እንዲሰፍሩ ይደረግ ነበር። አማር እንደ ክፋ ጐሣ ሆነው የተዋሐዱ የቢታ ክፍለ ዘገር አስተዳደር መብት ያላቸው በድሮ ዘመን ከሰሜን ኢትዮጵያ መጥተው የሰዋሐዱ ናቸው። ከፋ ለ4 ትከፈል ነበር፣ 1 ቦንጋ 2 እናሪያ 3 ከፋ 4 ሐዲያ[1] የከፋ ጐሣዎች አስተዳዳሪ ሆነው የሚመረጡ የገዢ መደቦችና የማይመረጡ ሰሁለት ይከፈሉ ነበር፣ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው 1 ማንጆ የንጉሡ ዘር 2 ይራንጎ 3 ሂዮ 4 አማር 5 አርጊፓ 6 ሚየጠቺዮ የገዢ መደብ ያልሆኑ ጐሣዎች ሂኒግቾ (Hinnimachio) 2 ሂናካሮ (Hinacaro) 3 ሂኑቺዮ (Hinnucio) 4.እሾ 5 ቱራ ነበሩ። መንግሥቱ በጐሣ ልዩነት በመሬት ክልል የተከፈለ ነበረ፣ አስተዳዳሪዎች ራቺዮ ይባላሉ (ከአማረኛ ራስ የመጣ ቃል) ከፍለ ሀገሮች 10 ነበሩ ካፌ (Cafe) ጊምቢ፣ ቺያተታሉ፣ ኛቢ ቡተ፣ ቢተ፣ ጋዋተ፣ ጊዮቺየ፣ አዲ። ለቤተመንግሥት ብቻ የተወሰኑ 3 ራቺዮ ነበሩ፣ (ፀ) አዲየ የክብር ዘበኛ ፈረሰኛ (ሰ) ጉቺ የንጉሥ ባሪያዎች ሹም (ሐ) ካታሚ የንጉሡ ግቢ ዘብ አዛዥ። ከፋ ከጥንት ጀምሮ ኢትዮጵያ አካል እንደነበረች በከፋ የሚገኙ የክርስትና ሃይማኖት መልክቶች ያስረዳሉ፣ ቤተክርስቲያኖችም ነበሩ።[2] ከፋ ከኢትዮጵያ ተለይታ በኖረችበት ረጅም ዘመናት የጣአት እምነት ብትከተልም የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ዋና ዋና በዓላት ከግከበር ሕዝቡ አልከለከለውም[3]። የከፋ ንጉሣዊ አገዛዝ የግይናጋ ቀጣይነት እንዲኖረው የሚያደርገው የንጉሡ ፈላጭ ቆራጭነት ሥልጣን ገደብ በግድረግ የሚቆጣጠሩ 6 አባላቱ ያሉት በንጉሡ አማካሪዎች የተደገፈ ሰለነበረ ነው፣ እነሱም 1 ጉቺ ራቺዮ የከፈቾ ከርስቲያን ተጠሪ 2 ከተማ ራቺዮ 3 አደል ራቺዮ ከኡኮ ጐሣ 4 አርባሽ ራቺዮ ከአርጋጋ ሐዲ ጐሣ ከኡኮ ጐሣ 5 አርባሽ ራቺያ ከአርግጋ ሐዲ ጐሣ 6 በንዳ ራቺያ ከአርጋጋ ሐዲ ጐሣ 7 አርሶ ራቺያ ከከፋ ግቾዮ ጐሣ። ሹመታቸው በምርጫ ላይሆን በዘር የሚወረስ ነው። የአማካሪዎች የበላይ ሹም ጉቺ ራቺያ ነው። የዚሁ ጐሣ መሥራች በጥንት ከፋ የኢትዮጵያ አካል በነበረችበት ጊዜ የከፋ የጦር አዛዥ

(1) Cerulli ibd p 484
(2) A Cecchi : Da Zeila alle Frontiere di Kaffa VI p. 484
(3) A Cecchi ibd p. 486

በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የኩሉና የጉቺ የንጉሥ እንደራሴ ሆኖ ተሾሞ ሰለነበረ ነው። የጉቺ ራቺያ ሥልጣን ከፍተኛ ነበረ። ንጉሡ ሕግንና የሀገሩ ባሕልን የማያከብር ከሆነ ከሌሎች አባላት ጋራ በመመካከር ንጉሡን ከሥልጣን አውርዶ ተራ ሰው ሊያደርገው ይችላል።[1]

3. ክርስትና በከፋ

ስለ ኢትዮጵያ አርቶዶክስ ሃይማኖት አከባበር ወግና ሥነ ሥርዓት አሰታየታቸውን የሚሰጡ የኢጣሊያ ፀሐፊዎች ከጥንት ቅድመ ክርስትና ከነበረው የጣኦት አምልኮቶች ያልተላቀቀ መሆኑን እያሱ ሲጽፉ ይታያሉ። በከፋ ስለነበረው የክርስትና ሃይማኖት በዚሁ መንፈስ አጋንነው ጽፈዋል። ቸኪ በዶዮክ በሚባለው የጣኦት እምነት በከፋ አብዛኛው ሕዝብ የሚያጠቃልል ነው ካለ በኋላ በከፋ ሰሰይጣን አምላክም ማምለክ እምነት ስለነበራቸው የተለያዩ ኩብቶችን ለመስዋእትነት ያቀርቡላቸው ነበር ብሏል። በጣኦት እማልክቶች ማመን፣ መሰዋትነትን ማቅረብ ከፋዎች የክርስትና እምነት ሥነ ሥርዓትንም ከማከበር አይከለክላቸውም ነበር። ከጣኦት አምልኮት በእስክፈንቱ የሚጠቀስ የጣኦት ቤተመቅደስ ሰዎች (ቁሶች) ቡዳ በተባሉ ሰዎች ሌሊት ወደ ጅብነት የሚለወጡ ናቸው ተብለው ተክሰው ወደ ቁሶች በሚቀርቡበት ጊዜ፣ ቡዳ ናቸው ብለው ከፈረዱባቸው፣ ምስክር ሳያስፈልግ፣ ይግባኝ በሌለበት ወደ ንጉሡ ቀርበው ባሪያ እንዲሆኑ ይፈረድባቸው ነበር። በዚህ ዓይነት ጊራ ይገኝ በነበረው የካቶሊክ ሚሲዮናዊ ቁስ በአባ ጐን ሞት በየዓመቱ ለከፋ ንጉሥ 500 ባርያዎች ያስገኝለት ነበር። ቸኪ አባባል በክርስትና ብቻ የሚያምኑ የከፋ ሰዎች በቀር ሌሎች በስም ብቻ ክርስቲያን ናቸው በተግባር አይደሉም። የክርስትና እምነታቸውን የሚገልጹትም 1ኛ. በሰመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፣ በግሰት 2ኛ ጸም በግከበር 3 በመገረዝ 4 ወደ ቤተክርስቲያን ሄደው እንደ ገና፣ ፋሲካ ፍልሰታ ወዘተ የመሳሰሉ ዋና ዋና የክርስትና በዓላት በግከበር ሲሆን፣ በሌላ ተግባራቸው ግን ከግአት እምላኪዎች የተሻሉ አይደሉም፣ እንደ እስላሞች ብዙ ሚስቶች ያገባሉ በግለት ተችተዋል። በክፋ ቤተክርስቲያኖች በመላው ኢትዮጵያ እንደሚሰሩ ዓይነቶች ናቸው፣ በዛፎች የተከበቡ ናቸው፣ የምውታን መቃብሮችም አሏቸው። ከሁሉ የታወቀ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ነው። በዚሁ ቤተክርስቲያን የጣአት ዶዮክ አምላክ የሚያምኑም ሳይቀሩ ወደ ጦርነት ከመሄዳቸው በፊት፣ ካፈቾ በሙሉ ለመጸሰይና ስለት ሰግድረስ ይሄዳሉ። በታቦቱ ያለው በግእዝ የተጻፈ ይለባቸው ነበር። ክርስትና ከፋ የገባው ምናልባት ከእክሱም ዘመነ መንግሥት መሆኑን መገመት እንችላለን። ቸኪ የ18 የከፋ ነገሥታት ስም ዝርዝር አውጥቷል[2] በ15ኛው ንጉሥ ጋንቺዮ ለ24 ዓመት የነገሠ የግዮ ራቺዮ ጐሣ ዘመን መንግሥትን ለመገልበጥ አሊረዋል ተብለው የተከሰሱ 600 ፈረሰኞችና ወታደሮች ተገድለዋል። በ16ኛው ንጉሥ ጋዊርሰር ዘመን ብዙ ክርስቲያኖች ተገድለዋል። 17ኛው ንጉሥ ነገሥት ካም የጋዊ ዘሮ ልጅ ለ13 ዓመት የነገሠ በ1870 የሞተ፣ የዶአከ አምላክ አከራሪ ተከታይ ነበረ፣ እንደ አባቱ ብዙ ክርስቲያኖች ፈጅቷል። 18ኛ ንጉሥ በ1878 በሕይወት የነበረ የ45 ዓመት ጉልማሳ ስሙ ጋሊቶ ጋሊ ጋዎ (Gallito - Galli - Gao) ነበር። ሚንጂዮ ከግቶ ተረከቦ የቦንጋ

(1) A Cecchi : ibd p 488
(2) A. Cecchi : ibd p 490

ንጉሥ በመባል የንጉሠ ነገሥት ሥልጣን ሲይዝ እናሪያን ከግዙቱ አጠቃለላት። በዚሁ ጊዜ እናሪያ ቡሳሰ በተባሉ በንጉሣዊ ቤተሰብ ትገዛ ነበር። የካቶሊክ ሚሲዮን በጌራ ሲመሠረት 70 (ሰባ) ከእነዚህ ቤተሰብ አባላት የክርስትና እምነት ተከታይ በመሆናቸው ለሃይማኖታቸው ሲሉ ከስፋ ተሰደው በ1878 ወደ ጌራ በመሄድ ከካቶሊክ ሚሲዮናውን ተቀላቅለው ለመኖር መምረጣቸው በቀድሞ እናሪያ የክርስትና ሃይማኖት እንዳልጠፋ ምስክር ነው።[1] ወደ ጌራ የተሰደዱ የእናሪያ ሰዎች አለቃ 80 ዓመት ዕድሜ የነበረው አባ ታባኮ የተባለው ወደ ጌራ እንደመጣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የጌራው አባ ኮሮ የጦር አለቃ ሆኖ ተሾሞ በክፋ ላይ ለመዝመት ፈቃደኛ እንዲሆን የጌራ ንጉሥ ቢጠይቀው በሀገሬ ላይ አልዘምትም ብሎ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል። የጌራ ንግሥትም ጌን እስላም እንዲሆን ብትጠይቀው እስላም ከሚሆን ገላው ተቄራርጦ ለእሞራዎች ቢሰጥ እንደሚመርጥ የሚል መልስ ሰጥታታል። እንደዚሁም አንድ የዙሳሲ ልዕልት ልጅዋ እስላም እንዲሆን ብላ ብትጠይቃት የሰጠችው መልስ ተመሣሣይ ነበረ። ከፋ የዓመት መጀመሪያና መስቀል የሚያከብረው ልክ እንደ ኢትዮጵያ አከባበር ነው። ንጉሡ ነገሥቱ በዓመት መጀመሪያ ቀን ከእሱ በፊት የነበረው መቃብር ወደሚገኝበት ቦታ በመሄድ የከብቶች መሰዋእት ያቀርባል ዜጎቹም አበባ እያበረከቱ ረጅም ዕድሜ ይመኙለታል። በመስቀል ቀን ንጉሡ ነገሥቱ ለሸማምንቶቹ ትልት የምሳ ግብዣ ያደርጋል። ግለሰቦችም መሰከረም 17 በየቤታቸው ያከብሩታል፣ መሰከረም 18 ብዙ የሚነድ ዕንጨት ይከማቻል፣ መሰከረም 19 እውነተኛ የመስቀል በዓል ከንጉሡ ቤት ጀምሮ ትልቅ ሕዝባዊ ሰልፍ ይደረጋል፣ 3 የተለያዩ ቀለማት ያላቸው አርማዎች በመያዝ ጃ ባሮ ማለካሮ እያሉ እየዘፈኑ ይሄዳሉ። ንጉሡ ነገሥቱም ወደ ፭ዓሉ መጨረሻ ጎ ባሮ ማለካሮ እያለ ይዘፍናል።

4. ደቡብ ምዕራብ ከኢትዮጵያ ጋራ ግዋሐድ

የመጨረሻ የጌራ ንጉሡ የነበረው የአባ ራጉ አጎት ለጉብኝት ወደ እሱ ለሄደው ኢጣሊያዊ ቸሩሊ (Cerulli) እንዳጫወተው ጌራ ለእፄ ምኒልክ ጦር የተማረከችው በጀግናው ኢትዮጵያዊው ደጃዝማች በሻህ አቡዬ የሚመራው ጦር አራት ጥይት ብቻ በመተኩስ ነበረ። ንግግሩም በመቀጠል ደጃዝማች በሻህ ደፋርና ጀግና ርሕሩሑም ነበረ፣ በዓድዋ ጦርነት ጊዜ በጦር ሜዳ በጣሊያኖች ተገድለዋል። እላይ እንደተገለጸው የከፋ የጥንት ታሪክና ባህል አድናቆት የሚስብ ነው። ጅማ አባጅፋር ከፋን ለማስገበር ከምኒልክ ጦር ጋራ በመስለፉ የሰው ደም በከንቱ እንዳይፈስ ላደረገው ውለታ የውስጥ አስተዳደር ነፃነት እንደተሰጠው ሁሉ ለከፋም ለጥንታዊ ወጉና ባሕሉ ክብር እንዲሁም ላላየው ጀግንነት ከጅማ የበለጠ የውስጥ አስተዳደር ነፃነት ለማግኘት መመዘኛ ነበረው። አፄ ምኒልክ ግን በጠባብ የዘውድ ጥቅም ብቻ የሚመራ ሰለነበረ ከፋ የጅማ ዕድል አልተሰጠውም። አፄ ምኒልክ እንደ አጋማሚ ዘመቻቸው የሆኑባቸውን አደራ ኢትዮጵያ" ከደኩማ ምዕራብ ጭፍራት ጥንት የነበሩዋት ግዛቶች ለግዋሐድ በተደረገው ትግል፣ የጅማ አባ ጅፋር ትብብር በደስታ ሲቀበል የጉጃሙ ንጉሡ ተከለሃይማኖት ግን በዘመቻው እንዳይከፈል ጦርነት ገጥሞ በግሸንፍ አስቀርቶታል። ከዚህም ሌላ የልጁ ዘውዲቱ ባል የአፄ ዮሐንስ ልጅ አርአያ ሥላሴ በአባቱ ትእዛዝ በዘመቻው

[1] A Cecchi : ibd p. 341

ተካፋይ መሆን ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሸዋ መጣ። አፄ ምኒልክ በመጣበት እንዲመለስ አድርጎታል።

የአፄ ምኒልክ ሠራዊት ወደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ለመዝመት በሚዘጋጅበት ጊዜ የጅማ ንጉሥ አባ ጅፋር የምኒልክ ጦር ለመቋቋም እንደግይችል በመገንዘቡ ለምኒልክ ለመገበር እንደወሰን ሁሉ እንደዚሁም ቃቢያና በተባለው በጉራጌ ሀገር ሱልጣን የነበረው ያግር ባክስ የተባለው አክራሪ ሙስሊም የባሪያ ነጋዴ የነበረው፣ በየጊዜው ለሥራ ምክንያት ወደ ሸዋ በመመላለስ አፄ ምኒልክ የነበረው የጦር ኃይል ስለተረዳ ለምኒልክ በሰላም ለመገበር ተሽቀዳድሞ ወሰነ። በአፄ ምኒልክና በያግር ባክሳ መካከል የተደረሰው ስምምነት ያስከተለው ውጤት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የቻሃ፣ ምሑር፣ ጆቸሪት፣ እነሞር ጉራጌዎችና ከ2 ሺህ እስከ 3ሺህ የሚደርሱ እግረኞች በ1876 የደረሰ እልቂት ነው[1]። ኢግም ተብሎ የሚጠራው የያግር ባክሳ ከንጉሥ ምኒልክ እርዳታ እንዲያደርግላቸው አደራ ተብለው ወደ ጅማ ከፋ ለመዝለቅ ፈልገው ወደ ግዙቱ የመጡ ቸኪና ኪያሪኒ የሚባሉ ጣሊያኖች ወደ ግዙቱ ሲገቡ የሚከተለው ንግግር በግድረግ ተቀበላቸው። "እኖምጡኝ እናንተ እንደ እኔ ትልቅ ሰዎች ናችሁ፣ ንጉሥ ምኒልክ ወደ እኔ አደራ ብሎ ልከዋችኋል፣ ነገር ግን እናንተም ለእኔ ግድረግ አለባችሁ። እኔ እንደ አሮሞች ልብሶች መሰተዋቶች ለዝቅተኛ ሰዎች የሚሰጡ እቃዎች አልጠይቃችሁም። እኔ ብዙ ጠላቶች አሉኝ፣ እናንተ ከእነሱ ለመገላገል እኔን መርዳት አለባችሁ የምጠይቃችሁ ከፈጸማችሁልኝ እኔ ራሴ ወደ ጅማ አባ ጅፋር እሸኛችኋለሁ። ብዙ ነገር አልጠይቃችሁም። የእናንተ አንድ ጠብመንጃ ብቻ በርቀት ሁኜ አንድ የጉራጌ ጦሣ ከርስቲያን የእኔ ጠላቶች ለመደምሰስ ይበቃኝ ነበር በማለት ጥያቄውን ደምድመዋል። ጣሊያኖች ግን አሁን ያሉን ጠብመንጃዎች ለራሳችን ለመከላከያ ብቻ የሚያገለግሉን ናቸው ሸዋ ለሚገኘው አለቃችን መልእክት ልከን ጠይቀን ግን እንዲሰጥህ ግድረግ እንችላለን አሉት። በዘመኑ በቃቢና በኩል በየዓመቱ 400 ባሪያዎች ተገዝተው ወደ ሸዋ ይወሰዳሉ። አብዛኛዎቹ ከቻሃና ከአርባራግ በሲሊት ተሰርቀው የሚመጡ ናቸው፣ የሚገዙም በገንዘብ ሳይሆን በጎሐስ ነጥር ነው፣ አንድ ነጥር 432 ግራም ነው የገበያ ሁኔታ እንደሚከተለው ነበር

1	ወንድ ልጅ ቁመት 1ሜትር	20 ነጥር
2	ሴት ልጅ ቁመት 1 ሜትር	13 - 15 ነጥር
3	ትልቅ ልጅ 12 - 16 ዓመት	26 - 28 ነጥር
4	ሴት ልጅ	25
5	ወንድ ልጅ 20 - 24 ዓመት	20 - 30
6	ሴት ልጅ ቆንጆ	40
7	ሴት ልጅ መለስተኛ	30
8	ሴት ልጅ ዝቅተኛ	25 - 20 - 15
9	ቆንጆ ልጃገረድ	60 - 70
10	አሮጊት	6 - 7
11	ሽማግሌ	8 - 10
12	ሽማግሌ ጠንካራ	20

ኢግም ያግር ባክሳ ጠብመንጃ ከመጠየቅ አላቋረጠም፣ ጣሊያኖችም ተስፋ እየሰጡት ነበር። አንድ ቀን አግስት 25,1878 "0ሽከሮቻችሁ

[1] A Cecchi : ibd VII p 52

ከመሣሪያዎቻቸው ወደ አንድ ክርስቲያን ጉራጌ መንደር ከእኔ ጋራ ሄደው እንዲዘርፉ ፍቀዱልኝ የምናገኘው ገቢ እካፍላቸኋለሁ ብሎ ጣሊያኖችን ጠየቃቸው፤ ይሁን እንጂ ጣሊያኖች የጥያቄው አደጋነት በመገንዘብ፤ ከሁሉ ጋራ ወዳጅ ለመሆን ስለሚፈልጉ ለአንድ ወገን ማዳላት እንደማይሹ ነገሩት።

ጣሊያኖች ለጉዞቸው መሰናክል መሆኑን ስለተረዱ ከጉራጌዎች ጋራ መተራረብ ፈለጉ፤ ጉራጌዎችም ሀገራቸውን እንዲጉበኙላቸው ጋበዙዋቸው። በዚሁ መሠረት ከሁለቱ ጣሊያኖች አንዱ ወደ ጉራጌ ሀገር ሄዶ ጥናት እንዲያደርግ ወሰኑ፤ ዕጣም ለኪያሪኒ ደረሰው። መንገድ መሪዎች ጉራጌዎችን ይዞ ኪያሪኒ ወደ ጉራጌ መራት ገባና ቤተክርስቲያኖችን አስጎበኙት። ወደ መጨረሻም አስጉብኟው ከዝናብ ለመጠለል ወደ ቤቱ አስገባው። በዚሁ ጊዜ ፈረንጅ ብዙ ሰው ተሰብስቦው ብዙ ጥያቄዎችን ያቀርቡለት ነበር። ከቀረቡትም ጥያቄዎች ከሮት ሀገር እንደመጣ፤ ሃይማኖቱ ክርስቲያን እንደሆነ ወይንም እስላም፤ ከሁለቱ ሃይማኖቶች የትኛው እንደሚሻል፤ በቀንደኛ ጠላቶቻቸው በእስላሞች ድል ይቀዳጁ እንደሆነ ወይስ አይቀዳጁም ወዘተ። ኢጣም ያገር ባለሳ ብቻ ሳይሆን የምኒልክ ወታደሮቹም ክርስቲያን መሆናቸው እያወቁ ከኢጣም ተከታዮች ጋራ በመሰማማት ያለ ምንም ርሕራሔ ያላቸውን ንብረት እየዘረፉ ቤተክርስቲያኖቻቸውን ሳይቀሩ ያቃጥሉባቸው እንደነበረ በምሬት ያወሩለት ነበር። ጉራጌዎች ምሑር ሰለ ሃይማኖት ብዙ ነገር ባያውቁም ሁሉም ግን ክርስቲያን ነን በማለት ይነግሩት ነበር[1] ። ኪያሪኒ እግረመንገዱ ከኢሻ ንጉሥ ጋራ ተዋወቀ ንጉሡም ፈረንጁ ያላቸው መሣሪያዎች ካደነቀ በኋላ "እንተ ዓለምን ሙሉ ማቃጠል ችላለህ፤ የእኔ ሀገር እትንካ እንተ ቁስ ነህ እኔም እወድሃለሁ፤ እንተ የእግዚአብሔር ሰው ነህ እዜ ምኒልክና አሰላም ንብረታቸው እየዘረፉ ሊያጠፏቸው እየጣሩ ያሉት እነዚህ ምስኪን ሕዝቦች ደስተኞች ልታርጋቸው ትችላለህ"። የሚል ንግግር እደረገ[2] ከንጉሡ ተሰናብቶ እንደሄደ የጣሊያኑ መምጣት ወሬ ሰለተሰማ በፊት ቁስ ብቻ ይቁጥሩት የነበረ እሁን እንደ ቅዱስ ለው ሁሉን ነገር የሚያውቅ እደረጉት። በሸዋ ሰዎች ልጆቻቸው የተወለዱባቸው በሕይወት እንዳሉ እንዲነግራቸው ይጠይቁት ነበር። ኪያሪኒ ከአካባቢው ተነስቶ እንደሄደ ቸሃ መሬት ደርሶ በኩሪያው ለተሰበሰበ የተለመዱ ጥያቄዎችን ለሚያቀርብ ሕዝብ ዕድሳቸውን እንዲነግራቸው፤ በጠላቶቻቸው በአግራ የተወሰዱባቸው ልጆቻቸው ወንድሞቻቸው የት እንደደረሱ እንዲነግራቸው ይጠይቁት ነበረ። በመቀጠልም ኪያሪኒ ከዳሞ ንጉሥ ተዋወቀ፤ ጥሩ መስተንግዶ ተደረገለት። "የዚህ ሀገር ሕዝብ የቃበናውን ይግም አይደለም የሚፈሩ፤ በእሱ አማካኝነት የምኒልክ ጦር እንዳይወራቸው ነው ሲጋቻቸው[3]። ከእኛ ጋራ ሆነህ እንዝመት እስላሞችን እናጥፋቸው እያሉ ለክብሩ ይዘፍኑ ነበር። ንግሥቲቱም ለብቻው ወሰዳ የቀቢያና ይግም እግራ እመጣባችኋለሁ እያለ እያስፈራራን ነው፤ መብሊን ሊያደርገን እየሞከረ ነው፤ የጉራጌ ሕዝብ እንደ በግ ነው የሚነዳው፤ ሃይማኖቱን ሊከድ ይችላል፤ እግሮች የግይመጡ መሆናቸው ቢያውቅ ግን ሕዝቡ ኢግመጉ መሳቂያ ያደርገው ነበር። እንተ ትልቅ ሰው ነህ፤ ሕዝቡ ከውድቀት እንዲድን እድርገው፤ ቃልህን እንዲያምኑ ያዝካቸው መሣሪያዎችን አሳያቸው" ብላ ንግግሩዋን ከጨረሰች በኋላ ኪያሪኒ መልስ ለመሰጠት

(1) A Cecchi ibd VII p 77
(2) A Cecchi : ibd p 80
(3) A Cecchi : ibd p 87

ተቸገረ[1] ንግሥቲቱ ላቀረበቻቸው እንዛብጋቢ ጥያቄዎች ኪያሪኒ "የእናንተ ሁኔታ ይገባኛል የተቻለኝን ለማድረግ እሞክራለሁ። አግሮች ይመጣሉ እያለ የማር ባክሳ የማስፈራሪያ ጉራ ስለሚነዛባችሁ ጉዳይ አትቸገሩ፤ ንጉሥ ምኒልክ ባሁኑ ወቅት ለእዜ ዮሐንስ ግብር ለመክፈልና የበላይነት ለመቀበል ተሰማምቷል፤ እዚህ መምጣት አይችልም ከርስቲያኖችን ከእስላሞች ጥቃት መጠበቅ አለበት እንጂ ከርስቲያኖችን አይፈጅም። እኔና ጓደኞዩ የእስላሞች ሀገር አቋርጠን ስለምናልፍ ችግር እንዳይፈጥሩብን አሁን ያልኳችሁ ነገር ለማንም አትናገሩ።" በማለት የማደፋፈሪያ ቃላቶች ሰጣት። ንግሥቲቱም መልስ ለቅሰጠው "በእስላሞች ሀገር ለማለፍ ግዲታ የለባችሁም፤ ወደ እኛ ከመጣችሁ በእቋራጭ መንገድ ምንም ሳትከፍሉ በቾንጀር ሀገር በኩል ወይንም በጅማ በኩል ወደ ከምባታ ወላሞ እናደርሳችኋለን፤ የጅማ ንጉሥ ሚስት የቻሀ ተወላጅ የእባጋስ ልጅ ናት" አለችው። ኪያሪኒ በንግሥቲቱ ንግግር በጣም ተደሰቶ አመሰገናት። ጉራጌዎች ከሰሜን ኢትዮጵያ እንደሚወለዱ ለኪያሪኒ ሲያስረዱ እንደሚከተለው ገልጸውለታል "ከእርሲ፤ ከሬዩ፤ ቱሉማ፤ መጫ፤ ጋላ ተከበው በችግር ላይ በነበሩ ጊዜ ከሀገራቸው እንዲያባሩሯቸውና እንዲፈጁዋቸው ይፈልጉ ስለነበረ ጉራጌዎች ወደ ጉጋደር ለንጉሡ ነገሥቱ መልእክተኞቻቸው ልከው ከእሮሞች እልቂት እንዲድኑ እርዳታ እንዲደረግላቸው በጠየቁት መሠረት እነሱ እጥናፍ ሰገድ የሚሉት ንጉሥ የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊዎች ግን ሱሲኒዮስ የሚሉት ንጉሥ የትግራዩ ሹም የነበረው እዝማች ሰብሐት ለእርዳታ ላከላቸው፤ እሱም የተላከበትን ዓላማ እንደተዋጣ፤ ወታደሮቹ ቅጥራቸው በመቀነሱ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ለመመለስ ስላልቻሉ በዝዋይ ሐይቅ የምትገኘው ትልቋ ደሴትና እካባቢው ለፍረወጋ ጉራጌዎች ንጉሥ ብሎ ራሱን ሰየመ። የእዝማች ሰብሐት ትውልድ ሐረግ ብዙ ዓመት ነገሠ፤ በመጨረሻ ግን በንጉሥ ሣህለሥላሴ የምኒልክ እያት ተደመሰሰ። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ጉራጌዎች እውነተኛ ንጉሥ የላቸውም፤ ጉልበት ያለው ሁሉ ደካሞችን እያስቸገረ ንጉሥ ይባል ነበር መሬታቸውንም ይነቀቁዋቸው ጀመር። በዚሁ የተነሳ የጉራጌ ቋንቋ ከግእዝ ተመሣሣይነት አለው[2] ።

ከጉራጌዎች የክርስትና ሥነ ሥርዓት በጥብቅ የሚከተሉ ምሁር ናቸው። ኢንደጋን፤ የንር፤ መገር፤ እስላሞች ያረዱትን ሲጋም ይበላሉ። ጉራጌዎች ባለሥልጣን አያውቁም፤ ሲለ ንጉሥ ሲያውሩ እንደ ተራ ሰው ነው የሚያከብሩት፤ ሃብት ያለው ብቻ ንጉሥ የሚባለው። ንጉሥ የሚባሉ ሃብትና ጀግንነት ያላየ ሰው ነው። ከእነሱም ትልቁ ብቻ ዳሞ ወይንም ጉይታ ይባላል።

ጣሊያኖች ወደ ከፋ ለመድረስ የቻሀ ንጉሥ ግጋናሰ ባቀረበላቸው ሃሳብ መሠረት በጅማ ወይንም በሊሙ ከግለፍ፤ በጉሬጌ፤ ቾንጅር፤ ከምባታ፤ ወላሞ እንዳዝ ኪያሪኒ እምናበት ተሰማምቶ ነበር። ሆኖም አብሮዋቸው የሚጓዙ ከብት ሚኖች መንገዱን ስለማያውቁ በዚሁ መንገድ ለመሄድ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ። በመጨረሻ ከቃቢና ሞጂየር ወደ ሊሙ ጉዞዋቸውን ቀጠሉ።

እዜ ምኒልክ ተድሞ የኢትዮጵያ እንድ አካል የነበሩ፤ አሮሞች ባካሄዱት ጦርነቶች ምክንያት ከኢትዮጵያ ተለይተው ይኖሩ የነበሩ ግዛቶች መልሶ ለግዋሐድ የፈጸመው ተግባር በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ለዘለዓለም

(1) A Cecchi : ibd VII p 88
(2) A Cecchi : ibd VII p 89

የግይረሳ ውሰታ የሚያስገኝለት ቢሆንም አላይ እንደተገለጸው አክራሪ ሙስሊሞች እንደ ኢማም የግር ባከሳ ባሰኟል አድርጎ በጉራጌ ክርስቲያኖች ከፍተኛ ጥቃት እንዲያደርስ መፍቀዱ ከባድ የአስተዳደር ስህተት በመፈጸሙ በታሪክ ያስወቅሰዋል።

5. <u>የእናሪያ የመሬት ስፋት</u>

ተጓዦች ማሊያኖች ቸኪና ኪያሪኒ ተፈቅዶላቸው ወደ ሊሙ ገቡ። በቀድሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ዘመን የእናሪያ የመሬት ስፋት ከአባየና አዋሽ መንዞች ከፋም በውስጡ የሚያጠቃልል የግቢና የጉጀብ ሜዳዎች ያቀፈ ነበረ። ይህ ግዛት በንጉሥ እንደራሴ ይገዛ ነበር። ከ1545 ጀምሮ በእርሞ ሚጫ ወራሪዎች ግዛቱ ሲፈራረስ ገዢዎች ግግሾቹ ወደ ጉጃም ሲሸሹ ግግሾቹ በከፋ ሰሜናዊ ክፍል ሰፍረው ያጡት የሰፈ ሀገራቸው ስም የሰፈሩበት አንድ የከፋ ክፍለ ሀገር እናሪያ ብለው ሰይመው በቀድሞ ገባሮቻቸው ከንበሩ የወረታ ጉማዎች በመተባበር ሰእርሞ ማስፋፋት ከፍተኛ መከላከያ በማድረጋቸው ለከፋ በነፃነት መቄየቱ ከፍተኛ አስተዋጽእ አድርገዋል። የቀድሞ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከመፈራረሱ በፊትና እናሪያ በመጫ እርሞች ከመወረሩዋ በፊት የሀገሩ ነዋሪዎች አፈ ታሪክ እንዳቄየው ሁለት የፖርቱጋል ወታደሮች ሲጋሮ (Sigaro) እና ሰፔራ (Sapera) የተባሉ፣ ከከሪስቶፎር ዳ ጋማ ጋራ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ በአፄ ግላውዲዎስ ከሰሜን ኢትዮጵያ ተባርረው እናሪያ መኖሪያቸው አድርገዋት ነበር፣ በሰነ ምግራቸውም በሕዝቡ ዘንድ ትልቅ አክብሮት አግኝተው ነበር። በዚህም የተነሳ የነበራቸው አክብሮት እየጨመረ በመሄዱ በእናሪያ የአስተዳደር የበላይነት አግኝተው ነበር። ሲጋሮ በሰሜን እናሪያ መኖሪያው አደረገ፣ ሳፔራ ወደ ደቡብ ሳፓ (Sappa) ተብላ የተጠራቸው መንደር ሰፈረ። ከሳፓ ቤተሰብ አንዱ የአባ ባኒቦ እባት አባ ጎሮሊ በከህደት የሲጋሮ ግዛት ወደ ግዛቱ አጠቃልሉ አንድ የሊሙ መንግሥት አቋቋመ። አንደ አቡነ ግሣያ ምሰክርነት አባ ጎሮሊ የነጭ ዘር ይመስል ነበረ[1]። ሊሙ ከ80 ዓመት ወዲህ የአስልምና ሃይማኖት ተከታይ ቢሆንም መሰጊዶች በብዛት አይታዩም። ማሊያኖች /ቸኪና ኪያሪኒ/ በነበሩበት ዘመን (1878) በሊሙ ተላላፊ በሽታ ተሰፋፍቶ ነበር። በሊሙ የሕዝቡ ግማሽ በበሽታ አልቋል[2]፣ በጉግ 2/3 በበሽታ አልቀዋል። ማሊያኖችም እየታመሙ ይድኑ ነበረ። ከሁለቱ አንዱ ኪያሪኒ ታሞ ሲሞት በጌራ ንግሥት ተመርዞ ነው የሞተ ተብሎ ተወራ።

6. <u>ጉግ</u>

ጉግ በተንት ጊዜ የሲዳማ አማራ የሚባሉ ይኖሩባት ነበር። በእርሞ ነዋሪዎች ጊዜ ነዋሪዎቹ በሙሉ ተገድሰው አልቀዋል። ክርስቲያን ሕዝብ ይኖሩበት እንደነበረ በግያሻማ ሁኔታ ግሰረኝ የተገኘው የአንድ ቤተክርስቲያን ፍርስራሽ በዲደሳ ወንዝ ዳሩ (Daru) ከተባለው ተራራ አጠገብ ጉልጉታ ተብሎ በሚጠራ ቦታ በመገኘቱ ነው[3]። ሜላ የጌራ ዋና ከተማ የሁሉ ዓይነት የባሪያ ክምችት የሚታዩባት ናት።

(1) A Cecchi : ibd VII p 156
(2) A Cecchi : ibd p 199
(3) A Cecchi : ibd p 239

1. ወረታ ጉማዎች ከሁሉ፣ ወሊሶ፣ ኮንታ መንግሥታት የመጡ
2. ካፊኞ 3 ጃንጀሮ 4 ጉራጌ 5 ከምባታ 6 ሻንቅላ 7 ጋላ የተሰያዩ ጉማዎች ሶዶ፣ በቶር፣ አጋሉ[1] ። የጌራ ሕዝብ የእርሞ፣ ሲዳማ፣ አማራ ድብልቅ ነው። ሌላ ዋምባሪ የተባሉ ዝቅተኛ ዘር የሚገመቱም አሉ። የቤተመንግሥት ዘር የእርሞ ዘር ከወላሞ ምሥራቅ ደቡብ የመጡ ናቸው[2]። በጌራ ቤተመንግሥት ከ3000 ያላነሱ ባሪያዎች ይኖራሉ። እነሱም 12 የንጉሡ ሚስቶች ቢጋብቻቸው ጊዜ ሰጥሉሽ ተሰጧቸው ይዞዋቸው የመጡ ናቸው። ባሮች ወደ ውጭ ይሸጣሉ በሀገር ውስጥም በእቃ ይቀየራሉ፣ 6-7 ባሪያዎች በአንድ የጦር ፈረስ ይለወጣሉ ወዘተ። ይህ ሀኔታ የአፄ ምንልክ ጣልቃ ገብ ጦር እነዚህ ጥቃትን መንግሥታትን መውረሩ ሕጋዊ ያደርገዋል።

7. <u>ጃንጀሮ</u>

ጃንጀሮ ደብተሮችና የካፊኞ ሽግግሌዎች እንደሚተርኩ የዚሁ አካባቢ የመጀመሪያ ነዋሪዎች ናቸው። በተጨማሪም አፈታሪክ እንደሚናገረው ጃንጀሮና ሲዳማ በሐይቆች ይኖሩ የነበሩ የአንድ እናት ልጆች ናቸው። ጃንጀሮ የግቢ ዳውሮ አጠገብ አዞዎች ያመልኩ ነበር። ንጉሣቸው ኩርማ በሬዎች ለአዞዎች አንዲበሏቸው በመሰዋእትነት ያቀርብ ነበር። ንጉሥ ሲታመም ጤና እንዲያገኝ ሰዎች ወደ ግቢ አዞዎች ለመሰዋእትነት ይወረውሩ ነበር። ይህ የጣእት እምነታቸው ግን አንዳንድ የኢትዮጵያ የክርስትና ሥነ ሥርዓት እንደ አስተርእዮ ግርያምና መሰቀል ከግክበር አያግዳቸውም[3] ይህ የሚያመለክተው ኢትዮጵያ ከግራኝና ከእርሞ በፊት በግዛቷ በሙሉ የክርስትና ሃይማኖት ያልደረሰበት ቦታ አልነበረም።

8. <u>ቦሻ</u>

በቦሻ ከእርሞች ጋራ የሚኖር ሕዝብም ከትግራይ መምጣታቸውን ለማስታወስ "ቲግር ቦሻ" ተብሰው ይጠራሉ፣ በሀገራቸው የቤተክርስቲያን ቅሪቶች ይታያሉ፣ ብዙ ዘመን ከአዋሽ በስተደቡብ ይኖሩ እንደነበረ ያወራሉ፣ በዚሁ ጊዜም ሀገሩ በኢትዮጵያ መንግሥት ስር ሆኖ እናሪያ ተብሎ ይጠራ ነበር። በእርሞች ተገፍተው ከሀገራቸው ተፈናቅለው፣ በመጀመሪያ አሁን ቦቶር ባሉብት ይኖሩ ነበር፣ በመጨረሻ አሁን ባሉብት ሰፈሩ። ቋንቋቸው ከካፊኞ ተመሳሳይ ነው።

9. <u>ዋሬታ</u>

በአጠቃላይ ስማቸው ዋሬታ ወይንም ዳውሮ ተብለው የሚጠሩ ሕዝቦች 1 ኩሉ 2 ኮንታ 3 ኩዊሽ 4 ማሮ 5 ጉልዳ ከእሞ ወንዝ በስተምሥራቅ የሚገኙ ናቸው። በኢትዮጵያውያን ታሪክ አዋቂዮች ደብተሮች አባባል በኢትዮጵያ ታሪክ ዝንኞች ናቸው። ምክንያቱም በ1300 ዓ.ም. በአጼ ዓምደ ፅዮን ዘመን መንግሥት ከኢትዮጵያ ግዛት ጋራ የተቀላቀሉ ናቸው።

(1) A Cecchi : ibd p 258
(2) A Cecchi : ibd VII p 266
(3) A Cecchi : ibd p 355

ሕዝቡ ራሱም የቀድሞ የኢትዮጵያ አገዛዝ በሚገባ ያስታውሳል፡ ከአጼ ንግሥ ፅዮን ወታደሮች ጋራ ዘራቸው በጋብቻ የተደባለቁ መሆናቸውና ዘሀገራቸው ከብዙ ዘመን ጀምሮ እንዲኖሩ ያወራሉ፡፡ የኢትዮጵያ አገዛዝ ምልክቶች ብዙ የትግሪኛ ቃላቶች በቋንቋቸው መገኘታቸውና የክርስትና ባሕሉት በእነሱተኛ ደረጃ ቢሆኑም መገኘታቸው ለዋንታዊ ኢትዮጵያዊነታቸው ሀቂ ማስረጃዎች ናቸው፡፡ እንደ ጋሮ ቦሻ ሕዝብ የዋራታ ሕዝብም ኪስታን ወይንም ቤተ ኪስታን የሚሏቸው የቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ቅዱስ ሚካኤል ፣ ቅዱስ ገብርኤል ፣ የእባ ገብረመንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያኖች አሏቸው፡፡ በቤተክርስቲያኖቻቸውም በራዎች እርደው እግዚአ መሐረነ ክርስቶስ እያሉ ይጸልያሉ፡፡ በመልካቸው ወረታዎች ቁመታቸው አጠር ያለ ቢሆንም ከጥቁር ዘር ይልቅ ወደ ዓረብ ዘር ይሰባቸዋል፡ ከጉረቤቶቻቸው ከጥቁሮች የተቀላቀሉ ጥቁር ያሉም አሏቸው፡፡ ከዋራታዎች መሐል የኩሉ መንግሥት በከፋ መንግሥት ስር ተጠቃልሉ ነበር፡፡ ወላሞ ክርስቲያን ነበሩ፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን እስልምና እየተቀበሉ ናቸው፡፡ የክርስትና እምነት የሚያኩሩ እንደ ላሊበላ ቤተክርስቲያኖች በመሬት ተቁፍረው የተሰሩ ቤተክርስቲያናት አሏቸው፡፡ ከግሉና ወላሞ በሰተደቡብ ዶኮ የሚባሉ ጥቁር ሕዝብ የሚኖርበት ሀገር ነው፡፡ ከንታ ወይንም ቀቦ የሚባል ሕዝብ ሶማሌዎች እማራ ይሉዋቸዋል ምክንያቱም ከእማራ ነጋዴዎች ጋራ የመጡ ናቸው ይባላል፡፡ ጉረቤታቸው የሆኑ እንድ ዓይነት ቋንቋ የሚናገሩ ሕዝቦች ከፉ ናቸው፣ ሰው ይበላሉ ይሏቸዋል፡፡ የእሞ ወንዝ ከዋረታዎች የተሰጠው ስም ነው፡፡

የኦሮሞ ታሪክ የተለያዩ አስተያየቶች

ስለ ኦሮሞ ታሪክና አሰፋፈር ከተለያዩ የውጭ ሀገር ፀሐፊዎች የተለያዩ ተቃራኒ አስተያየቶች ሊሰነዘሩ የቻሉት እብዛኛው ጊዜ በእጠቃላይ የኢትዮጵያ ታሪክ ማቀነባበር ባለመቻላቸው ነው፡፡ ቸኪ[1] የጠቀሳቸው ፀሐፊዎች ጋሊኒየ (Galinier) ኦሮሞች በአፍሪካ ምሥራቃዊ ደቡባዊ 5ኛ 10ኛ ዲግሪ ደቡብ ሳቲቲዮድ በዛንዚባር ይኖሩ የነበሩ ያደርጋቸዋል 2) Pellogrino Matteucci ፕለግሪኖ ማቴውቺ በአፍሪካ ካገኘናቸው ሕዝቦች ያስገረመን ኦሮሞች ነጭና ከርስቲያን በመሆናቸው ነው ካለ በኋላ ለምን ነጭ (ቀይ) ሆኑ ለምን ከርስቲያን ሆኑ ብሎ ይጠይቃል፡፡

3) Pritard ፕሪካርድ) አስከ ዛሬ ስለ ጋላ ያለን መረጃዎች በጣም ጥቂቶች ናቸው፣ ስለ ታሪካቸው የምናውቀው ነገር ባይኖርም፣ ከሥልጣኔ ሩቅ መሆናቸው ደምበኛ ኋላ ቀር መሆናቸውና የከብት ጭራ ተከትለው የሚኖሩ፣ ዘላኖች አረኞች ከኢትዮጵያ በሰተደቡብ የሚኖሩ መሆናቸው ብቻ እናውቃለን ብለዋል፡፡

4)Cap. Owen (ኻምበል አወን) በኢኳቶሪያል አፍሪካ ጨካኝ ሕዝብ እስከ ጆባ ወንዝ የሚደርስ ጋላ ሕዝብ አለ፡፡ በባሕር ወደቦች ሶማሌዎች ይኖራሉ፣ ከጋላ ሕዝብ በጣም ይለያሉ፣ ጠባያቸው ለስላሳ ነው፣ ጥሩ ነው፣ እሰላሞች ናቸው፣ በባሕር ወደቦች ንግድ ያካሄዳሉ፡፡ ሶልት (Salt) እና ሌሎች ፀሐፊዎች ስለ ጋላ ቋንቋ ባደረጉት ጥናት ጋሉች፣ ሶማሌዎች፣ እንዲሁም አፋሮች አንድ ትውልድ ሀረግ እንዳላቸው ያሳያል ብሏል፡፡

---

(1) A. Cecchi : ibd VII p 496

5 ፊደሪኮ ሔልወርድ (Federico Hell ward) ኦሮሞች የሰፈሩበት መሬት እስከ ትልቁ የአፍሪካ ተራራ ኪሊማንጃሮ ይደርሳል፣ እንደ ሶማሌዎች ከጥቁር አሳሪካ ሕዝብ ጋራ አይመሳሰሉም ብሏል፡፡

6 ግራፕት(Grapt) ጋላ ወደ ሰው ሀገር ሄዶ የሚሰፍር ግለት ነው ብሏል፡፡

7 ብሬነር (Brenner) በባሕር ዳርቻ ያሉ ሕዝቦች ጋላ ግለት ሃይማኖት የሌለው ሰው ያደርጓቸዋል፡፡

8 ጋሎች ራሳቸው ኦሮሞ ተብለው ይጠራሉ ትርጉመም ኃይለኛ ጀግና ግለት ነው

9 ብሩስ (Bruce) ጋላ በመጠኑ ቀያይ ናቸው፣ ጠጉራቸው ጥቁር ረዘም ያለ ነው፣ በቆላ የሚኖሩ ግን በጣም ጥቁር ናቸው ይላል፡፡

10 ውድ (wood) ጋላ በቆዳቸው ቀለም ከሐበሾች ይጠቁራሉ፣ ከዚሁ በመነሳት Johnstone (ጆንስቶን) የተባለ ፀሐፊ የጋላ ቃል ትርጉሙ ከካላ የመጣ ጥቁር ማለት ነው ብሏል፡፡

11. ለፊርቫር (Lefevre) ስለ ጋላ ብሏል ስለ ዘራቸው ያለው ነገር የለም፡፡

12. ሃርትማን (Hartman) ጋላ ዋና ሀገራቸው ከዚሊማንጀሮ ተራራ ስር ነው፣ ንፁሕ ጥቁር ናቸው፣ በብዙ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራት ሰፍረዋል፣ ከበቆ፣ አገውና ሐበሾች ጋራ ተዋሕደዋል ብሏል፡፡

13 ቸኪ የራሴ ሃሳብ ብሎ የሚያጠቃልለው ጋላ ከዓረብ ሀገር ወደ አፍሪካ መጥተው የቀድሞ ነዋሪዎችን አባርረው ከማንም ዘር ሳይቀላቀሉ የሚኖሩ ናቸው፡፡

2. የኦሮሞ አፈ ታሪክ

14. ቸኪ የኦሮሞች አፈ ታሪክ፣ ብዙ የሀገር ሽማግሌዎች የተለያዩ ጉዛዎችን ጠይቄ ያገኘሁት ነው ብሎ እንደሚከተለው ያቀርበዋል፡፡ ኦሮሞች ሁሉ በአንድ ድምጽ "እኛ የአንድ ሽማግሌ አባት ልጆች ነን፣ አሱም ኢሳው ይባላል የከነአግ ጉሣ፡፡ ሐዳር የምትባለው ሚስቱ አገባና ኢሊፋሰ ወለደች፣ ኢሊፋሰም ኦመር ወለደ፡፡ ለቀድሞ እናታችን /አያታችን/ ሐደር ክብር እናት ለማለት ሐዳር እንላለን፡፡ ወደዚሁ ሀገር ከመምጣታቸው በፊት አባቶቻችን ገላድ የሚባል ሀገር ይኖሩ ነበር የኦሮሞ ልጅ መሬት ስለጠበበው ከጉሣው ተለይቶ ባሕር ተሻግሮ በርበራ ገባ፣ ከበርበራም ወደ ሐረር መጣ፣ ቀጥሎም ከአርሲ አጠገብ በወላሞ ሀገር ሰፈረ፡፡ ከኦሮሞች መሐከል አንድ ትልቅ አለቃ መሐን በመሆኑ ልጅ መውለድ ሰላልቻለ አንድ አማራ ሴት ዘሀገሩዋ ወንጀል ሰርታ፣ ወንድ ልጇዋን ይዛ ከኦሮሞች ጋራ ትኖር ስለነበረ ልጅዋን በሞጋሳ ወይንም ጉዲፈቻ ደምብ መሠረት አሳደገው፡፡ ይህ ልጅ ለመጣንባት ሀገር ማስታወሻ ስመ ገላድ ተባለ፡፡ ከዚሁ ስም በመውለድ እግሮች ኦሮሞችን ሁሉ ጋላ ብለው ይጠሩዋቸዋል፡፡ ኦሮሞች ገላድ በሞጋሳ ያደገ ስለሆነ ጋላ ተብለው እንዲጠሩ አይወዱም፣ በኦሮሞ መጠራት ይመርጣሉ፡፡ አሳዳጊ አባቱ ሲሞት ገላድ ከጉሣው ተባረረና በግራኝ ጊዜ ከአብቦ /ወላሞ/ ሀገር ወደ ሸዋ ጠረፍ ሰፈረ፡፡ ገላድ 3 ሚስቶች ነበሩት፣ ከእነሱም 4 ልጆች ወልዷል በኩር ልጁ ከአንድ ባሪያ የተወለደ ነበረ፣ ስሙም መጫ ተባለ፣ ሕገ ወጥ ግለት ነው፡፡ 2ኛ ልጁ አርሲ 3ኛ ተሉማ 4ኛ ኢቱ ተባሉ፡፡ ከበኩር ልጁ ከመጫ በቀር ሌሎች ከንፁህ ኦሮሞ ሌቶች የተወለዱ ናቸው፡፡ ገላድ ሲሞት ልጆቹ በመሬት አከፋፈል ምክንያት ተጣሉ፡፡ መጫ ከአዋሽ በሰተደቡብ እናሪያ በሚባለው የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር ሰፈረ፡፡ በዘመኑም ኢትዮጵያ በግራኝና በቱርኮች በተከፈቱባት ጦርነቶች ተዳክማ

የአክሱም ንጉሥ አረጋስ የዘመተበት ዘመን በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ስለሆነ የኢትዮጵያ ፈደልም ከሳባውያን የተወሰደው በዚህ ዘመን ቢመሆኑ የሳባ ፊደል ወደ ኢትዮጵያ ያጣ አረጋስ የተባለው የኢትዮጵያ ንጉሥ መሆኑን ፈደሉ የተሻሻለውም በኢዛና ንጉሥ ዘመን መንግሥት መሆኑን አጠያያቂ አይሆንም ብዬ እምታለሁ። ስለዚህ ፈደሉ ወደ ኢትዮጵያ ያስገቡት ሳባውያን ሳይሆኑ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ አረጋስ መሆኑን ማስገንዘብ እንችላለን።

7. ከአረጋስ በፊት የነበሩት ነገሥታት በሐውለቶች ያስቀርጿቸው የነበሩ ጽሑፎች አረጋስ ራሱም ተከታዩ ንጉሥ ኢንዲቢስም ይጠቀሙ የነበሩ በግሪክ ቋንቋ ሲሆን ተጥሉ የነገሠ ንጉሥ ዋዜብ ግን በኢትዮጵያ ፊደል ሻወል የሌለው ተጠቅሷል። ከእሱ ቀጥሎ የነገሠ ትልቁ የኢትዮጵያ ንጉሥ ኢዛና እንደአስረዳኒኑ በሳባ፣ በግእዝ፣ በግሪክ ቋንቋና ፊደል ሻወል የሌለው በመጨረሻም በግእዝ ፊደልና ቋንቋ ሻውል ያለው ይጠቀም እንደነበረ ታውቋል። ስለዚህ ከሳባውያን ተወስዶ ተመሳሳይ ፊደል በኢትዮጵያ የተፈጠረው ኢትዮጵያዊ ፊደል እንደሚባለው ሳባውያን ወደ ኢትዮጵያ ይዘውት የመጡ ክርስቶስ ልደት በፊት ከአምስተኛ እስከ ሁስተኛ ያለው መቶ ክፍለ ዘመን ሳይሆን ኢትዮጵያ በአፈላስ ንጉሥ መሪነት ዘመቻ አካሂዳ የመንን ከግዛቷ ያጠቃለለችበት ጊዜ በ4ኛው መቶ ክፍለዘመን ክርስቶስ ልደት በኋላ ሲሆን፣ ሰራ ላይ የዋለውና የተሻሻለውም በንጉሥ ዋዜብ እና በንጉሥ ኢዛና ዘመነ መንግሥት መሆኑን ከዚህ በላይ የተዘረዘሩ ሁኔታዎች በተጨማሪ ለመረዳት እንችላለን። ከአፈላ የየመን ዘመቻ በፊት የሳባ ፊደል ወደ ኢትዮጵያ መግባቱ የሚያመለክት በታሪክ የተመዘገበ ነገር የለም። ለመደረት በአርኪኦሎጂ ቁፋር ሲላ ታሪካዊ ማስረጃዎች ሊገኙ ይችላሉ። ባሉት ጥቂት ማስረጃዎች መሠረት ግን ከንጉሥ አፈላስ በፊት የአክሱም ነገሥታት በድንጋይና በሐውልቶች ጽሑፎቻቸው ያጠመዘቡት የነበሩት ቋንቋ ጎልጭ አቀፋዊ አውቅና በነበረው በግሪክ ፊደልና ቋንቋ ብቻ እንደነበረ እንረዳለን። እንደ ኮንቲ ሮሲኒ አገላለጽ ንጉሥ ኢዛና ከግሪክ ቋንቋና ፊደል በተጨማሪ በሳባና በግሪክ ፊደልና ቋንቋ ያጻፈው ገና በአነባበቢ ዘገባች እንዲታወቅለት በግሰብ ሲሆን፣ በሳባ ፊደል፣ በግእዝ ቋንቋ የሳባ ቋንቋ እንዳንድ ጊዜ የተቀላቀለበት መገኘቱ የሳብያውያን ቋንቋ በዚኒ መንግሥቱ እንብዛም እንደማይታወቅ የሚያስረዳ ምልክት ነው ብለዋል። ከተጨማሪም በኢትዮጵያ ይዝ የነበረው የደቡብ የመን እንዲገባቸው [1] የኢትዮጵያ ነገሥታት በሐውልቶቻቸው በሳባ ፊደልም ይጽፉ ነበር።

እንድ ሀገር ቋንቋው በፊደል ጽሮ ከተጠቀመ እስተድሞ በሥልጣኔ የደረጀ መሆን ይጠበቃል። እኛ የሥልጣኔ ቀደምትነት ያለን እንደመሆናችን መጠን የተሻሻለ ፊደልም በአፈላስ ዘመቻ ዘመን ከየመን መስድን እንጂ፣ ደቡብ ዓረቦች ጊዜው በትክክል የማያታወቅ ዘመን ወደ ሀገራችን አምጥተው ሰጡን እስተግሩን ግለት ልዘወስድ ታሪክ ነው።

[1] Conti - Rossini ibd p 132

6. የአክሱም መንግሥት ወደ ዓረብ አገር ተሻግረው የተካሄደው ቅዱስ /የመስቀል/ ጦርነት[1]

ዘመቻው የተካሄደው በንጉሥ ካሌብ በ525 ዓ.ም ነበረ። የተካሄደበትም ምክንያት የጥንት አምልኮት ተከታይ የነበሩ ዓረቦች በክርስትና ተከታይ ዓረቦች ያደረሱት በደልና የጅምላ ጭፍጨፋ ስመበቀል ነበር። በዚሁ የአክሱም መንግሥት ጣልቃ ገብነት ዘመቻ መካሄድ ብዙ የማስረጃ ምንጮች አሉ። ነገር ግን በብዙ መንገድ እና አስተያየት ታሪኩን የሚገልጹ ሃሞው። የኢትዮጵያ የመስቀል ጦርነት ከኢውሮጳውያን የመስቀል ጦርነቶች የሚለይበት በኢውሮጳውያን በወዶ ዘመቾች የተካሄደ ሲሆን የኢትዮጵያ ግን በንጉሡ የሚመራ ነበረ።

1. ከክዝግስ የአዱሊስ ሐውልት ጽሑፍ ቀድቶ ስታሪክ ያስቀረ
2. ከቢዛንታይን
3. ከአርያ
4. ከዓረብ
5. ከኢትዮጵያ ወገን ምንጮች ናቸው።

ጦርነቱ ለ 3 ክፍል መክፈል ይቻላል

1ኛ. በመጀመርያ የአክሱም ወታደራዊ ዘመቾና ጣልቃ ገብነት ዓላማው የዘርቢያ ዓረባዊ መንግሥትን ስመረዳት ይሁን እንጂ፣ ከግዙፍ የሮማ መንግሥት ጥቃት፣ ፀረ- ሮማ መንግሥት ነበር።

2ኛ. በሁስተኛው የአክሱም መንግሥት ወታደራዊ ዘመቾና ጣልቃ ገብነት ዓላማው ያበሻ ዘሮች ከጭፍጨፋ ስማዳን ፀረ ሳባዊ መንግሥት ነበር።

3ኛ. የአክሱም ወታደራዊ ዘመቾና ጣልቃ ገብነት ዓላማው ሃይማኖታዊ የክርስትና እምነት ተከታዮችን ከእልቂት ስማዳን ፀረ - ሂሚያር ይሁዳዊ ዓረባዊ መንግሥት ነበረ። የ1ኛና 2ኛ ጦርነቶች የተካሄዱት በኢትዮጵያ ፍላጐት ብቻ ሲሆን 3ኛ ጦርነት ግን ተጠቃሚና እይዞህ ባይ 3ኛ. ወገን ትልቁ የቢዛንታይን መንግሥት እጅ ነበረበት። ይህ መንግሥት ራሱ ምንም ሳይንቀሳቀስና ለጦርነቱ አስተዋፅኦ ሳያደርግ የአክሱም መንግሥትን ብቻ በቀጥታ ልመና በመገፋፋት፣ እንዲሁም የግብፅ እስክንድሪያ ፓትርያርክም የደቡብ ዓረብ ክርስቲያኖችን እንዲረዳ የአክሱም መንግሥትን እንዲያግልዱ በግድረግ፣ በውጭ ኃይሎች ግፊት የተደረገ ጦርነት ነበር። የቢዛንታይን መንግሥት የፐርሲያን መንግሥት ስግሽነፍ ስላቃተው ኢትዮጵያን መጣሪያ ያደረገበት ብቻዋን በጦርነት እንድትካፈል ያጋስጣት ወቅት ነበር። ሁስቱ ኃያላን መንግሥታት ፍልሚያ በሚያደርጉበት ጊዜ የኢትዮጵያ ጥቅም በማይነካ ጉዳይ ብቻዋን በጦርነት እዘትት መግባት እይገባትም ነበር። ስለጉዳዩ ዝርዝር ስንገባ ኢትዮጵያ ጊዜያዊ ድል አግኝታለች፣ ለሃምሳ ዓመታት የመንን ገዝታለች። እንዳንዶቹ 72 ዓመት ያደርጉታል እስከ 597[2] ነገር ግን የዓረብ ሕዝብ ጥላቻ ብቻ ነበር ያተረፈችው። ዘመቻው ግዙፍ ነበር፣ የኢትዮጵያ ወታደሮች ቀይ ባሕርን ሲያቋርጡ በ191 በቢዛንታይን የንግድ መርከቦችና በ170 አዜ

[1] Conti - Rossini ibd p 167
[2] Conti - Rossini ibd p 199

ካሌብ ባሰራቸው መርከቦች ተሳፍረው ነበር። የመን የደረሱትና አጼ ካሌብ ዘመቻ ያካሄደው በሁለት ዙር ነበር።

በመጀመርያ ጦርነት ላይገጥመው የኢምያር ንጉሥ እጅን ሰለሰጠ ወድያውኑ አጼ ካሌብ ራሱ የሾመው በየዓመቱ ግብር የሚከፍል ክርስቲያን ንጉሥ ትቶ ወደ ሀገሩ ሲመለስ። ነገር ግን ስለክዳውና የክርስቲያን ጭፍጨፋ ስለቀጠለ እንደገና ከፍተኛ መታደራዊ ኃይል ይዞ ከዓረቦች ጋራ ጦርነት ገጥሞ ድልን ተቀዳጀ። እምያር ንጉሥ ሸሽቶ በፈረስ እየጋለበ ቀይ ባሕር ውስጥ ገብቶ ሞተ። አዲስ የተሾመ ንጉሡም ብዙ አልቆየም አጼ ካሌብ ንጉሥ አድርጎ የሾመው አብርሃ የተባለውም ወዲያውኒ ከዳ። ከኢትዮጵያ መታደሮች ግማሾቹ ከዓረብ ሀገር ተባረሩ። በመጨረሻ አብርሃ የንጉሥነት ስልጣን ነጥቆ ያዘ። ቆይቶ ከአጼ ካሌብ ወኪል ጋር ቢታረቅም እንደ ነፃ ንጉሥ ሆኖ ሀገሩን ይመራ ነበር። በኢትዮጵውያን በኩል እስከ ዘመናችን ድረስ አጼ ካሌብ እጽብህ ተብሎ እየተጣራ አብርሃ ወአጽብህ እየተባሉ ከአቡነ ፍርሚናጦስ ከሣቱ ብርሃን አኩል ወደ ኢትዮጵያ ክርስትና ያስገቡ ተብለው እንደ ቅዱሳን ይከበራሉ። በዓረቦች ዘንድ ግን ኢትዮጵውያን ከፍተኛ ጥላቻ ነበረ ያተረፉት። የሕዝብ ዘፈኖች ዐረ- ኢትዮጵያ የጭቆና አዝዝ ነበሩ። የዘመኑ የዓረብ ጸሐፊዎች "ሲቶች የሚገርዙ፣ የቁላ ብሊታዎች" ወዘተ... እያሉ ኢትዮጵያውያንን ኢያጥላሉ ይፅፉ ነበር። የኤውሮጳ ታሪክ ጸሐፊዎች የሚተርኩት በኢትዮጵያና በደቡብ ዓረብ ያለው የሰጋ ዝመድና የሚያስታውስ ሲሆን፣ ከዓረብ ወገንም ሆነ ከኢትዮጵያ ወገን ግን ይህን ዝምድና የሚያስታውስ ምንም ማስረጃ የለም።

ዓረቦች ብቻቸው ከኢትዮጵያ ቀንበር አገዛዝ መላቀቅ ስላልቻሉ ለዚዛንታያን መንግሥት ስሞቻቸውን ሊያስሙ የሚያዳምጧቸው ስላጡ ፈታቸው ወደ ፋርስ ንጉሥ አዞሩ። ፋርስ ከቀይ ባሕር ብዙ የሚርቅ ሀገር በመሆኗ፣ ቀይ ባሕር ለመድረስም በረዘማ ቦታዎች አቋርጣ ማለፍ ስለሚያስፈልግ፣ በደቡብ ዓረብ አስተዳደር ጣልቃ እንድትገባና የዓረቦች ጥያቄ ለመቀበል ተላል አልነበረም። በመጨረሻ ከፍተኛ የሕዝብ ድጋፍ ያላት መሆኑን ስላወቀች 800 ወታደሮች ብቻ በመላክ የመንን ይገዛ የነበረው የአብርሃ ልጅ ማብሩክ የተነሳበት የሕዝብ ዐመፅ በቁጥጥሩ ስር መዋል ስላልቻለ በፀረ ኢትዮጵ ዐመፀኞች እየተረዳ የፋርስ መንግሥት በቆሳሉ ድል ሊቀዳጅ ችሏል። ኢትዮጵውያን በመሉ ከዓረብ የተወለዱ ከልሶችም ጭምር ተገደሉ። ንጉሠ ነገሥት አንደ አጼ ካሌብ ንጉሥ በኢትዮጵያ ቢኖር ኖሮ ለኢትዮጵያ ታሪክና ሕልውና ከሃይማኖት ጉዳይ ሌላ የሞት ሽረት ጉዳይ ስለነበረ ሌላ የተጠናከረ ዘመቻ ማድረግ ባስፈለገ ነበር። ይህ ባለመደረጉ ኢትዮጵያ የቀይ ባሕር ባለቤት መሆኗ አከተመ። ቀይ ባሕርም እንደ ጥንቱ ያበሻ ባሕር ኢትዮጵያዊ የሚል ስያሜ ተሸር በግሪኮች አጠራር ለዘለቄታ ቀይ ባሕር ተባለ የሶማሊ ባሕርም ባርባሪያ ባሕር ተብሎ ይጠራ የነበረው ሕንድ ውቅያኖስ ሆነ። የአዛንያ አጠራርም ተሰርዞ ሶማሊ ኪንያ ታንጋኒካ ወዘተ... የሚል ስም ተሰጣቸው፣ ኢትዮጵያ ግዛት ክልል ከባብ ኤል መንደብ በስተ ደቡብ ያለው አጣች። ለጥቂት ጊዜ ኢትዮጵያ ከዓለም ታላላቅ መንግሥታት ቁጥር ገብታ የነበረችበት ነበረ።[1] በአንፃሩም የውድቀቷ መጀመርያ ምዕራፍ ሆነ።

ከሰለጠነ ዓለም ለመገናኘት በየብስ በግብፅ በኩል እንዳትገናኝ ግብፅ እንደቀድሞ ክርስቲያናዊት አፍሪካዊት ሀገር መሆኗ ቀርቶ አስከግዊት

[1] C. Conti - Rossini ibd p 200

ዓረባዊት ሀገር ስለሆነች፣ ከኢትዮጵያ ጋር የነበራት ግንኙነት ውሱን ነበር። የባሕር በርም ምንም እንኳን ነብዩ መሐመድ ኢትዮጵያ እንግዳ ተቀባይ ብሉ ቢወድስም በሀገሩና በእስልምና ሃይማኖት የተቀበሉ ሀገሮች በኩል ሁሉ ለኢትዮጵያ እንግዳ ተቀባይነት ውለታ ያሳዩት ሀገ አመለካከት አልነበረም። ወደ ኢየሩሳሌም ስመሳለም ለመሄድ የሚሞክሩ ምእመናን ኢትዮጵያውያን ብዙዎቹ የሞት ፅጣ ነበር የሚጠብቃቸው። በአንፃሩ የኢትዮጵያ የባሕር ጠረፍ የእስልምና ሃይማኖት ስብካ ተስፋፍቶባቸው ኢትዮጵያውያን በሃይማኖት ክፋፈሉን። በመጨረሻም በተለይ በመሐመድ ግራኝ ጊዜ ለእርስ በርስ ጦርነት ገፋፍተው ኢትዮጵያን ለባሰ ለሥልጣኔ ኋላ ቀርነት ዳረጓት። የኢትዮጵያ እንግዳ ተቀባይነቷ የተከፈላት ውለታ በጠላትነት ነበረ። የእክሱም መንግሥት ውድቀት በደረሰበት ዘመን በ705 715 ዓ.ም. በሰሜናዊ ዐረብያ ከሙት ባሕር 100 ኪሎ ሜትር በስተደቡብ በአንድ በአማያዲ ቤተ መንግሥት ሕንፃ የካሊፎች መዝናኛ በታ በትልቁ ዋና ከፍል ግርግዳ ላይ በካሊፋ የተሸነፉ 4 ከዓለም ታላላቅ ነገሥታት ተስለው ይገኛሉ. እነሱም[1]

1ኛ. የቢዛንታናዊ ቁሳር ንጉሠ ነገሥት
2ኛ የፋርስ ንጉሥ ኮስሮ
3ኛ. የስፓኝ የመጨረሻ ቪዚጎት ንጉሥ ሮድሪጎ
4ኛ. የኢትዮጵያ ንጉሥ ናጃሺ ናቸው።

7. በሰሜን ኢትዮጵያ የታሪክ ቅሪቶችና በታዎች

ስለኢትዮጵያ ታሪካዊ በታዎች ስናስታውስ ትዝ የሚሉን አብዛኛው "አቤሊስክ" ተብለው የሚጠሩ በአክሱም ቆመውና ወድቀው የሚገኙ የአክሱም ሐውልቶች ናቸው። አንድ መቶ የሚጠጉ የአክሱም ሐውልቶች ብቻ አይደሉም የኢትዮጵያ የጥንት ሥልጣኔ ቅሪቶች። ደቡብ ዓረቦች ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ይዘው የመጡ ፊደላቸው ብቻ አይደለም። ከጉቲ ሮሲኒ በሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኙ ታሪካዊ በታዎች በግለት አንድ ካርታ[2] አውጥተዋል በዚሁ ካርታ መሠረት በዚሁ ታሪካዊ በታዎች የሚገኙት ከአክሱም በስተሰሜን ከናቅፋም በስተሰሜን የሱዳን ግዛትም የሚያጠቃልሉ በባሕር ዳርቻዋም ከአዱሊስ እስከ ራሄይታ የሚደርሱ ናቸው። ከፍተኛ ስልጣኔ በዳበረባቸው በታዎች የከተማ የቤት ፍርስራሾች፣ ቤተክርስቲያኖች፣ መቃብሮች፣ አቤስኮች፣ ዙፋኖች፣ የውሃ ማጠራቀሚያዎች፣ ስእሎች እና የሸክላ ስእሎች ፈራርሰው ይገኛሉ። እነዚህ ሁሉ ቅሪቶች ከደቡብ ዓረብ ስልጣኔ ተመሳሳይነት ሊኖራቸው ሲገባ ምንም ተመሳሳይነት የላቸውም። የፈራረሱ ቤቶች የሚገኙ በጥንት በታዎችና በእሁኑ ጊዜ ትግሪኛ ተናጋሪ አካባቢ የሚሰሩ የቤቶች አሰራር አንድ ዓይነት ነው። አራት ማእዘን ያለው "ሕድሞ" የተባለው የቤት አሰራር ከደቡብ ዓረብ ሆነ ከግብፅ የቤት አሰራር ስለማይመሳሰል፣ በአክሱም ጊዜም የተለመደ ነው ተብሎ በመገመት አክሱማዊ የቤት አሰራር ተብሏል። ክቡ የቤት አሰራር ግን በመላው አፍሪካ ስለሚገኝ አፍሪካዊ የቤት አሰራር ተብሏል። ብዙ የመቃብር ዓይነቶች ተገኝቷል። ከቤተክርስቲያንና ቤተመቅደስ አጠገብ ወይንም ከምድር ቤት በልዩ ሞያ የተሰሩ ወይንም መሬት ቆፍረው ብቻ የተቀበሩ ሬሳጅም እቤሊስክች በአክሱም ብቻ ሲገኙ እነሰተኛ ቁመት ያላቸው በብዙ ታሪካዊ በታዎች

[1] Carlo Conti -Rossini Storia d' Ethiopia p 124
[2] C. Conti -Rossini ibd Indice delle tavole XXVI

ይኖሯቸው፤ ግን እንደሰራቸው ለማወቅ አይቻልም። በደቡብ ዓረብ የኦቤሊስክ ስራ እምብዛም የተለመደ አልነበረም።

ኢትዮጵያውያን ብቻቸውን ሊሰሯቸው አይችሉም፣ ከግብፅ የመጡ ባለሙያዎች እርዳታ የተሰሩ ናቸው ከማለት በስተቀር የአሰራራቸው ታሪክ ለማወቅ አልተቻለም። ዙፋኖች በብዛት የሚገኙት በአክሱም ነው። በአዱሊስ፣ በዲክዲክ /ናቅፋ/ ተገኝቷል። ስእሎች፣ የሸክላ ስራ ምስሎች ወዘተ... ከማንም ሐገር በአሰራራቸው የሚቀራረቡ ሆነው አልተገኙም። ደቡብ ዓረቦች ለንግድ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ በሚመላለስባቸው ጊዜ ፈደል ብቻ አይደለም የተማሩት፣ ባለ ብዙ ፎቅ የቤት አሰራርም ከባቢሎኒያ ተምረው ወደ ሀገራቸው አምጥተው በሰፊው እንዲለመድ አድርገው ነበር።

የመዳብ ግእድንን ማቅለጥና መዳቡ ላይ መጻፍ ደቡብ ዓረቦች ከክርስቶስ ልደት በፊት ተምረው ልዩ ችሎታ ነበራቸው። ከጋዛ ተምረው ባለብርና ባለወርቅ የአቴንና የሮማውያን ገንዘቦች በ4ኛ መቶ ከፍለዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት ይሰሩ ነበር። የቤተመቅደስ ጋንቴዮን የመሰራት ችሎታ ነበራቸው። የዚሁ ሁሉ እውቀታቸው በኢትዮጵያ የታየ ነገር የለም። በኢትዮጵያ የሚገኙ የጥንት የሰው ስራዎች ጥቂቶች እንኳን የደቡብ ዓረብ ናቸው የሚባሉ የሉም።

ስለዚህ ደቡብ ዓረቦች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ከሕዝቡ ጋራ ተዳቅለው አዲስ ሕዝብ ሲም ቋንቋ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን ፈጠሩ ማለት የፈጠራ ታሪክ ነው። ሀገራችን ከማሊያን በስተቀር በማንም ሕዝብ ተገዝታ አታውቅም አያልን፣ አንስተኛ የሕዝብ ብዛት እንደወረዳ የቆዳ ስፋት ያላቸው ሳባውያን ገዙን፣ ፈጠሩን ብለን መናገር የማይመስል ከመሆኑም በላይ አሳፋሪም ነው። ደቡብ ዓረቦች በብዛት ስፈሩባቸው ተብለው የተገመቱ ቦታዎች ከአክሱም ወደ ሰሜን ምሥራቅ ያሉት ጥቅጥቅ ያሉት ታሪካዊ ቦታዎች በደቡብዋ አከለጉዛይ የሚገኙ ቦታዎች ናቸው፣ እነዚህ ቦታዎች የሚገኙ ሕዝቦችም ቢሆኑ የዓረብ ድብልቅ ዘር የለባቸውም፣ የተለዩ ሕዝቦች መሰለው አይታዩም። ከፍተኛ ስልጣኔ ዳብሮባቸው የነበረ ንፁሕ ኢትዮጵያውያን ዘሮች መሆናቸው ብቻ የሚታዩ በቆሐይቶ አካባቢ /አከለጉዛይ/ ተቁፍሮ የተገኙ አስከሬኖች ጠጉራቸው ጥጥ መሳይ እንደ ጥቁሮች /ኔግሮዎች/ ላይሆን፣ ወይንም ለጫ እንደ ዓረቦች ባይሆን እንደ አሁኖቹ ኢትዮጵያውያን በመጠኑ ከርዳዳ የሆነ ፀጉር እንደ ነበራቸው ተረጋግጠዋል። [1] የሞንቅላታቸው አጥንትም የኢትዮጵያውያን እንደሆኑ ተረጋግጠዋል፣ ይኸም ደቡብ ዓረቦች በሰሜን ኢትዮጵያ እንዳልሰፈሩ የሚያስረዳ ተጨማሪ ማስረጃ ሊሆን የሚችል ነው። ቆሐይቶ እንደ ደቡብ ዓረብ ተመሣሣይ ውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳዎች ቅሪቶች ያለባት መንደር ናት። በአዱሊስ ይኖሩ የነበሩ ደቡብ ዓረቦች ከቀይ ባሕር ሐሩር ወጣ ብለው ብርዳማ አየር የሚያገኙበት የመዝናኛ ቦታ ነበረች የተባለች መንደር ናት። በዚሁ መንደር የዓረቦች ሬሳ ምልክት ካልተገኘ የትም ቦታ ሊገኝ አይችልም። ቆሐይቶ እንደ መንደር የሚቆጠር አይደለም። ከእነሱም በፊት የአክሱማውያን ዋና ከተማ የነበረ ሊሆን የሚችል ነው። ይህ ባይሆንም ከቆሐይቶ እስከ አክሱም ያሉት ታሪካዊ ቦታዎች ፍርስራሾች እንደ ትኩንዲሰ፣ ከክሰለ፣ ለንዓፈ ወዘተ... የሚያጠቃልል ከፍተኛ ታሪካዊ የሐውልቶች ፍርስራሾች የሚገኙባቸው ራሳቸው የቻሉ እንደ ግሪክ መንግሥታዊ ከተሞች የሚቆጠሩ ሊሆኑ ይችላሉ ለማለት የሚያሰኝ ነው፣ ለምርምር ዘቲ ቲፋኖዎች

(1) Carlo Conti - Rossini Storia d' Etiopia p. 237

አልተደረገም። ከዚህ ቀደም የተደረጉ ቁፋሮዎች ያተኮሩት በአክሱም አካባቢ ብቻ ነው። ፕሪኘሉ የቀይ ባሕር ዙሪያ ጉብ የሚል መጽሐፍ የደረሰው ሰው አክሱማውያንን የሚገዛ ዘስካስለ የተባለ በማም ስለታም የሆነ ገንዘብ ማጠራቀም ብቻ የሚወድ በሊላ በኩል ግን ጉበዝና የግሪክ ቋንቋ በሚገባ የሚያውቅ[1] ንጉሥ ነበረ ብሎ ጽፏል። ዘስካለስ ይኖር የነበረ በ2ኛው መቶ ከፍለ ዘመን 2ኛው አጋማሽ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ለለሆነ ኢትዮጵያውያን የሳባ ቋንቋና ፊደል ከማወቃቸው በፊት የግሪክ ቋንቋ ያወቁ እንደነበረ የሚጠቁም ነው።

የኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪክ ለማወቅ በቂ የአርኪዮሎጂ ቁፋሮ ባያደረግም ከመሬት በላይ የሚታዩ ታሪካዊ አሻራዎች በጥሰድ በሰሜን ኢትዮጵያ ከሰላ እስከ ሐይቅ (ወሰ) በብዛት ይገኛሉ። ኮንቲ ሮሲኒ ምንም እንኳን እነዚህ የታሪካችን ምልክቶች በውጭ ሀገር ሰዎች የተሰሩ ናቸው የሚል አስተያየት ቢኖረውም፣ እንደዚሁም የኢትዮጵያ የጥንት ስልጣኔ የአናሳ ሴማውያን ሥልጣኔ ነው የሚል አስተያየት ቢኖረውም፣ ሐውልቶቹን ከመሬመረ በኋላ ኢትዮጵያ በዓለም ከሚገኙ ጥንታዊ ሰልጣኔዎች ካላቸው ሀገሮች መካከል በእኩል ደረጃ እንድትሰለፍ የሚያስችሏት መሆናቸው ጽፏል[2] ።

በአክሱም ከሚገኙ ቁጥራቸው አንድ መቶ የሚደርሱ ኦቤሊስኮች አንዱ በቁመት በመላው ዓለም ከሚገኙ ተመሳሳይ ሐውልቶች እንደኝነት ያለው ነው። ላሊበላ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በዓይነታቸው በዓለም ተወዳዳሪ የሌላቸው ናቸው ተብለው ተደንቀዋል።

8. የኢትዮጵያ የጨለማ ዘመን

ስለታወቀው የምዕራባውያን ሀገሮች የጨለማ ዘመን (Middle Age) ተብሎ የሚጠራ ታሪካቸው በዚህ መጻሐፍ መግቢያ ላይ አስተያየቴን ሰጥቻለሁ / ፤የሀገራችን ታሪክ ጸሐፊዎች የምዕራባውያን ተመሳሳይ የሆነ የታሪካችን የጨለማ ዘመን አለ ብለው ጽፈዋል። የሀገራችንና የምራአባውያን ሀገሮች ታሪክ የተለየ ቢሆንም እንደ አጋማሚ የጨለማ ዘመን ተብሎ የሚጠራ ዘሁለቱ ሀገሮች የክርስትና ሃይማኖት ከገባበት ዘመን ጀምሮ ነው። አቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያ የጨለማ ዘመን ብሎ የሚጠራው ከናግራን፣ በአጼ ካሌብ ዘመን፣ በ525 ዙሪደረገው ጦርነት እስከ ዩዲት መነሳት 942 ዓ.ም. 317 ዓመት ያለው ጊዜ ነው። የተባለበትን ምክንያት ሲያብራራ የአክሱም ነገሥታት የሰሩትን ሥራ በታሪክ የተመዘገበ ስላግኘን ነው። በአዉሮጳውያን የጨለማ ዘመን ትርጉሙ አንድ ሀገር ከነበረው ከፍተኛ ስልጣኔ ወደ ኋላ የተመለሰበት ዘመን ነው።

ሀገራችን በእነ ንጉሥ ኢዛና እና አጼ ካሌብ ከነበረው ባለ መልካም ዝና ታሪኳና ሰልጣኔዋ ወደ ኋላ መመለስ የጀመረችበት ጊዜ ከአጼ ካሌብ ጀምሮ መሰሉ አይታየኝም። የሀገራችን ታሪክ ከምዕራባውያን ሀገሮች በማመሳሰል ብንፈልግ እንኳን የጨለማ ዘመን ተብሎ መጠራት የሚገባው ከአጼ ካሌብ ከናግራን ጦርነት ጀምሮ መሆን የሰበትም። የታሪክ ማስረጃ ዘመኖቹም ታሪክ አልተሰራም ለማለት አይቻልም። ከንጉሥ ኢዛና በፊት ወደ ሰሜንና ደቡብ ዓረብ የተደረጉ የአክሱም ዘመቻዎች ማስረጃዎች የተገኘ

(1) Carlo Conti - Rossini Storia d' Etiopia p. 119
(2) C. Conti - Rossini ibd p. 239

በአጋጣሚ ከሀገራችን ወጪ ነበር። ለኢትዮጵያ የጨለማ ዘመን አለ ቢባልም መጀመር ያለበት ከእስልምና ሃይማኖት መከሰትና መስፋፋት በኋላ በተለይም ግብፅ በዓረብ እስላሞች ስር ከወደቀችበት ዘመን ከ 642 ዓ.ም. ጀምሮ መሆን ይገባዋል። ከዚሁ ዓ.ም ጀምሮ ግብጽና ኢትዮጵያ የክርስትና የጋራ እምነታቸውና ግንኙነታቸው ባይቋረጥም አደጋ ላይ የወደቀበት ዘመን ኮፐቲክ የአንድ የክርስቶስ ባሕርይ የክርስትና እምነት ተከታዮች ነበሩ። ኢትዮጵያ ግንኙነቷ የተቋረጠው ከግብጽ ጋራ ብቻ አልነበረም። ከሰለጠኑ ምዕራባውያን የክርስትና እምነት ተከታይ ሀገሮች ሁሉ ጭምር ነበረ። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ የክርስትና እምነቷን እና ሕልውናዋን ለመጠበቅ ለብዙ ዘመናት የትጥቅ ትግል የጀመረችበት ዘመን ነበር።

ስለዚህ ይህ ዓመተ ምህረት ለኢትዮጵያ የጨለማ ዘመን የጀመረችበት ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ኮንቲ ሮሲኒ የሀገራችን ታሪክ የጨለማ ዘመን 500 ዓመት ያደርሰዋል፤ ከ7ኛ መቶ ከፍለ ዘመን[1] ስለሞናዊ ነገሥታት በስልጣን እስከ ተመለሱባት ጊዜ 1268 ዓ.ም. ድረስ /ሀ/ በዚሁ ጊዜ የሀገራችን ታሪክ የምናገኛቸው ከተለያዩ የውጭ ሀገር ጸሐፊዎች ነው። የጨለማ ዘመን ከመግባቱ በፊት በ525 አንደ ግፈኛዊ ግብፃዊ ዜጋ የሆነው ኮዝማስ ኢትዮጵያን ጎብኝቶ ለፊ ታሪካዊ ዘገባዎች ተንትነዋል። ወደ ሕንድ ሀገር በምሄድበት ጊዜ ባርባርያ /ሶማልያ/ በጎበኘበት ጊዜ ከሶማልያ ጦን የነበረውን የዘንግ መንግሥት ለመጎብኘት ፈልጎ ነበር። ነገር ግን ባሕር-ተኞች ስላስፈራሩት ፍላጎቱም አልተሳካለትም። ከሕንድ ሀገር ሲመለስ አዱሊስ እና አክሱምን ጎብኝቶ በመሬት እስክ አባይ በመሄድ ግብፅ ሀገር ገብቷል። ኮዝማ እንደጻፈው አዱሊስ የንግድ መናኸሪያ፣ ግሪኮችና ሮማውያን ነጋዴዎች የሚያዛውትሩባት ናት በማለት ጽፏል። በንግድም የምትገናኘው ከየመን ብቻ እይደለም፣ ከፐርሲያ፣ ከሕንድ እና ከስይሎን ጋራም ትገኛለች። አክሱም ከብለሚዮች ጋራ በወዳጅነት የተመሰረተ ግንኙነት አላት ከባርባሪያን ጋር በመሬትም በባሕርም ትገናኛለች። አዱሊስና አክሱም ሐውልቶችና ቤተክርስቲያኖች አሏቸው። ኮዝማስ አጼ ካሌብ የመንን ለመውረር ዝግጅት በሚያደርግበት ጊዜ ተመልክቷል። ከንቲ ሮሲኒ ከአጼ ካሌብ የየመን ዘመቻ በኋላም ቢሆን ኢትዮጵያ በ6ኛና 7ኛ መቶ ከፍለ ዘመን ስልጣኔዋን እና የክርስትና ሃይማኖትን ወደ ደቡብ አስፋፍታ እንደ ነበረ የሚያመለክት ሰሜን ሱማሊያ፣ የሶኮትራ ደሴትም ጭምር ክርስቲያን ሆነው እንደነበሩ ብሎ ጽፏል። /ሰ/ 6ኛው መቶ ከፍለ ዘመን ኢትዮጵያ ግንኙነቷ ከደቡብ ዓረብ ጋራ ሲሆን 7ኛ መቶ ከፍለ ዘመን ግን በእስልምና ሃይማኖት መመዕረት ምክንያት ግንኙነቷ ከሰሜን ዓረብ ሆኗል። የሀገራችን ታሪክ በዚሁ ዘመን እና ከሚቀጥሉት ዘመናት ለማወቅ የምንችለው ከዓረቦች ጸሐፊዎች ምንጮች በምናገኛቸው ማስረጃዎች ብቻ ነው። በዚሁ ጊዜ የዓረቦች አስተያየት ኢትዮጵያ ሰላም የሰፈነበት ሀገር፣ ስደተኞች ዓረቦችን የምትቀበል ተብላ ትታወቅ ነበር። ታማኝ የነቢዩ መሐመድ ባርያዎች ኢትዮጵያውን ነበሩ። ነቢዩ መሐመድ በዓለም ከነበሩት 6 ታላላቅ ነገሥታት የእስልምና ሃይማኖት እንዲቀበሉ ደብዳቤ ከላከላቸው ነገሥታት አንዱ የኢትዮጵያ ንጉሥ ነበረ። ነቢዩ መሐመድ ከኢትዮጵያ ነገሥታት ጋራ የወደጅነት ግንኙነት ነበረው። "ካልነኒችሁ ከኢትዮጵያውያን ጋራ ነገር አትጫሩ፣ 9/10 የሰው ዘር ድናረትና ጀግንነት ሰጥቷሮች ነው የተሰጠው"

[1] Conti - Rossini ibd p. 323

በማለት ነብዩ መሐመድ ለቅርብ ረዳቶቹ የተናገረው ቃል ስለኢትዮጵያውያን የነበረው አመለካከት የሚያንፀባርቅ ነው።

/ሐ/. በ872 ዓ.ም. አል ላኩቢ (Ahmed Ibn Wadhih Al- La - Kubil[1]) የተባለው የዓረብ ታሪክ ጽሐፊ ዓለምአቀፍ ታሪክ በሚለው መጸሐፍ ስለ ኢትዮጵያ ሲጽፍ ከናይል ወንዝ እስከ ቀይ ባሕር ብዙ ነገሥታት እንዳሉ ይዘረዝራል 1ኛ. የናኪስ ዘር የተባሉ ጎሳዎች ከአስዋን እስከ ባርካ የሚደርስ፣ ዋና ከተማው ሐጂያር 2ኛ ባክሲን ይባላል 3ኛ. በእዘን 4ኛ ጀሪን 5ኛ. ከታአብ 6ኛ. የናጃሺ መንግሥት ለፊና ታይሰኛ ነው፣ ዋና ከተማው ካባር ነው። በግዛቱ ውስጥ ብዙ ከተሞች አሉት፣ ዓረቦች ለንግድ ይሄዳሉ፣ የባሕር ዳርቻው ዳህላክ ነው። በኢትዮጵያ የሚገኙ ብዙ ነገሥታት በአንድ ንጉሥ ይታዘዛሉ፣ ግብርም ይከፍላሉ፣ ሃይማኖታቸውም ክርስትና ነው፣ የመጨረሻ በስተደቡብ የኢትዮጵያ ንጉሥ ከሲንድ የሚዋሰን የዘንግ ንጉሥ ከደዘብ ሶማልያ በስተደቡብ ይገኛል። የዓረብ ሀገሮች ከኢትዮጵያ ጋራ ያላቸው ንግድ ብዙ ነው፣ ምክንያቱም ኢትዮጵያ ለሙስሊሞች የጦርነት ቀጠና አያደለችም ብለዋል።

/መ/. ማሱዲ (Masudi)[2] የተባለው የታወቀው የዓረብ ታሪክ ጸሐፊም እስክ ማዳጋስካር ድረስ ብዙ ጉብኝት አድርጉ ራሱ በተጥታ ስላየው ነው የሚጽፈው። በመጨረሻ ጊዜ በ916/7 ጉብኝት ስላደረገበት ስለ ኢትዮጵያ በሚያደርገው ዘገባ፣ ኢትዮጵያ የበለጸገች ሀገር ናት ብሎ ጽፏል። ዋና ከተማዋ ጋባር ናት፣ ሌሎች ብዙ ከተሞችም አሉ፣ ግዛቷ እስክ ሐዘሻ ባሕር ይዘልቃል። በዚሁ ባሕርም ዘይላ ዳሕላክና ባጹ /ምፅዋ/ የተባሉ ወደቦች አሏት። በኢትዮጵያ የሚኖሩ ዓረቦች በስላም ግብር እየከፈሉ መኖር ይችላሉ። ኢትዮጵያ በብልጽግና ዘመን እንደነበረች የሚያስረዳ በንጉሡና በየመን መሪ ኢብራሒም ቤን ዚያድ በ901-2 የተደረገው የወዳጅነት ውል መሠረት የንግድ መርከቦች ብዙ ሸቀጦች ይዘው በ3 ቀን ውስጥ በሁለቱ ሀገሮች ለንግድ ያመላልሱ ነበረ እያለ ጽፈዋል።

/ስ/. እማር የመናዊ የተባለው ሌላ የዓረብ ታሪክ ጸሐፊ በእባቱ በኢብራሂም ተተክቶ በ981-2 ዓ.ም. የየመን መሪ የነበረው አቡ አል (Abu Al) ጂያይስ ኢሳክ Jiais Jshak የተባለው ለ80 ዓመት ዘስልጣን የቆየው ከኢትዮጵያ ጋራ ግንኙነት እንደነበረው እና ስጦታ በማበርከትም ወዳጅነትን ይፈልግ እንደነበረ ጽፏል።

/ረ/. 977/8 ዓ.ም. የጆግራፊ ምሑር የነበረው አቡ አልከሲም Abu - Alkasim ኢብን ሀውካ የተባለው የዓረብ ተወላጅ ስለዘይላ የኢትዮጵያ ክርስቲያን ከፍለ ግዛትና በሁሉም ባሕር ዳርቻ ከየመን ፊት ለፊት የሚኖሩ ዘንግድ ከየመን ጋራ መልካም ግንኙነት ያላቸው ናቸው ካለ በኋላ የኢትዮጵያ መሬት ለሙስሊሞች የጦርነት ቀጠና አይደለም ብሏል።

/ሠ/. በ951 -2 ሌላ ዓረባዊ የጆግራፊ ምሑር አል አስታክሀሪ Al - Istakhri የተባለው ተመሳሳይ ሀሳብ ገልጧል። በተደጋጋሚ ዘይላ ኢትዮጵያዊነትና ክርስቲያን መሆኗ መጠቀሱ የኢትዮጵያ መንግሥት ወደ ደቡብ መስፋፋቱን

[1] C. Conti - Rossini ibd p. 274
[2] C. Conti - Rossini ibd p. 281

ያመለክታል። የዚሁ መስፋፋት ከሚታዩ ብዙ ታሪካዊ ማስረጃዎ እንደምሳሌ የሚከተሉት መጥቀስ ይቻላል። ኢትዮጵያ ወደ ደቡብ ማስፋፋት ማተኮሩዋ ከሚያመለክቱ ምሳሌዎች አንዱ በ1154 ዓ.ም. ኤድሪስ የተባለው የሲሲሊ ንጉሥ የጀዮግራፊ ምሑር ስለዓለም እቀፍ የጂዮግራፊ በደረሰው መጽሐፍ፣ ስለ ኢትዮጵያ እንስቶ ሲጽፍ የኢትዮጵያ የባሕር ወደቦች ምጽዋ ምንም ሳያጠቅስ ስለ ዘይላ፣ በርበራ፣ መርካ ሌሎችም የደቡብና የሰሜን ሶማሊ ጠቅሶ ጽፏል። ወደ ሰሜንም ታጁራ ዳዘላክ እና ሰዋኪም የኢትዮጵያ ወደቦች ናቸው ብሎ ጽፏል። ሌሎች እንደ ኢብን ሰኢድና አልዲማሽኪ የተባሉ የዘመኑ የጂዮግራፊ ምሁራን ዓረቦችም ስለ ዘይላ፣ በርበራ፣ ምቃዲሾ፣ መርካ፣ የኢትዮጵያ ወደቦች መሆናቸውን ጽፏል።

/ተ/. [1] የግብፅ ፓትሪያርኮች ታሪክ በ921-933 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ አቡነ ጴጥሮስ ቡትላኩበት ዘመን ስለ ኢትዮጵያ ግዛት ሰፋ ሲጽፍ ኢትዮጵያ በጣም ሰፊ በመሆኗ የተነሳ ንጉሡ ጉብኝት ለማድረግ ሲፈልግ ሀገሩን ጉብኝት ስመጨረሰ 1 ዓመት ይወስድበት ነበር ብሏል። በላሊበላ ዘመን ጊዜ 1210 ዓ.ም. የኢትዮጵያ መልክተኞች ካይሮ መጥተው ስለነበረ ስለ ኢትዮጵያ ለማወቅ ፍላጐት ከነበራቸው ብዙ ሰዎች አንዱ አቡ ባሊሕ ሻዲድ አብን ባና የተባለው የአርመን ተወላጅ በደረሰው መጽሐፍ የኢትዮጵያ ንጉሥ ከዳዋት ዘር እያወሰድም፣ ሙሴ ወደ ኢትዮጵያ ሄዶ በነበረበት ጊዜ ከንጉሡ ሴት ልጅ ጋራ በተደረገው ጋብቻ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘር የሚሆነው ሊወለድ ችሏል ካለ በኋላ፣ ንጉሡ በጣም ኃይለኛ ነው ከስሩ ያሉት ነገሥታት ግዛት ጉብኝት ለማድረግ አንድ ዓመት ይፈጅበታል ብሎ ጽፏል።

9. ታሪካዊ ቦታዎች በደቡብ ኢትዮጵያ

ዘሰሜን ብቻ ሳይሆን በሌሎች የሀገራችን ክፍሎችም የጥንት ታሪካችን ምልክቶች ፍርስራሾች ይገኛሉ። በአዲስ አበባ ፋንፋኔ ጠበለ አጠገብ የእክሱም ስልጣኔ ማስፋፋት የሚያመለክት የአንድ ቤተክርስቲያን ፍርስራሽ ይገኝ ነበረ። እንደዚሁም ከአዲስ አበባ በስተምዕራብ ጀባልቲ በተባለው ተራራ የእንዲት የእክሱማዊት የኩጣ ፍርስራሽ ይገኛል።

ይህ ሁሉ የሚያመለክተው የእክሱም ወደ ደቡብ ማስፋፋት በተያያዘ ሁኔታ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ማእከል እንድትሆን የተመረጠችው በእጼ ምኒልክና በእቴጌ ጣይቱ ዘመን መሆኑ ቀርቶ በእክሱም ዘመነ ምንግሥት መሆኑ ነው። እጼ ምኒልክም አዲስ አበባ ዋና ኩጣ እንድትሆን የመረጠበት ምክንያት በኢትዮጵያ ሌሎች የፍል ውሀ ጠበል ቦታዎች ጠፍተው ሳይሆን ቀደምት አባቶቹ የኢትዮጵያ ነገሥታት ፈለግ በመከተልና በግእክልነት ተመርጦ የነበረው ቦታ ዘመቀበል ነው። ከእክሱም እጥላ እሸጌ የሚወሰደው ጥንታዊ መንገድ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ሥልጣኔም ከእክሱም ወደ እሸጌና ፌንፌነ መስፋፋቱ ያሳያል። በዚሁ መሠረት ከእሸጌ ሐይቅ እጠገብ በእጼ ቴዎድሮስ ላይ የዘመተው የእንግሊዝ ጦር አባል የሆነው አንድ ወታደር የሰባተኛ መቶ ከፍለ ዘመን የእክሱም ገንዘብ እግኝቷል። በዚሁ አካባቢ በእክሱም ጊዜ ሕዝብ ሰፍረውበት የነበሩ ምልክቶች በስተምዕራብ የእሸጌ ሐይቅ ተግኝቷል። በዝዋይ ሐይቅ ትራቪርሲ፣ ሚሊዮስና ዲካስትሮ የተባሉ ጣሊያኖች በእጼ ምኒሊክ ጊዜ በኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩ የእክሱም መሰል

[1] C. Conti - Rossini Storia d'Etiopia p 289

ሐውልቶች፣ አቤሊስኮችና መስቀሎች በብዙ ቦታዎች አግኝተናል ብሏል። ኪያሪኒ የተባለው ኢጣሊያዊ ሀገር ጐብኚ ከእንኮበር በስተምስራቅ የግሪክ የድንጋይ አሰራር የሚመስል በእንድ ሕንጻ በተለይም በበሩ ደጃፍ አግኝተዋል። በአጉላ በምስራቅ ትግራይ ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚውሉ የቤት ፍርሰራሾች ተገኝተዋል። ሀገራችንን የጐበኘ ቼኪ የተባለው ሌላም ኢጣሊያዊ በሸዋ ከእንኮበር በስተምስራቅ 6.35 ሜትር ርዝመት ያለውና ሌላው ደብረ ብርሀን አጠገብ አቤሊስክ አግኝቷል። ዳባዲ ታዋቂው የፈረንሳይ ሀገር ጐብኚ ከአባይ በስተደቡብ በሊበን ሁለት ሜትር ርዝመት ያለው አቤሊስክ አግኝቶ ነበር፣ ነገር ግን ደጃዝማች ጐሹ ወልዲ ለአሮሞዎች የጣኦት አምልኮት ነው ብሎ ለባብሮታል።

ሀረሪ /አደሬ/ በሀረር ኩጣ የተወሰነ ቋንቋ እንዲሁም የጉራጌ ቋንቋ በመሀል አገር በሰፊው የተሰራጨ ከትግሪኛና ከአማርኛ ቋንቋዎች ጋራ የሚዛመዱ የሴም ቋንቋ ተብለው ሲመደቡ የተለመደ ነው። በነዚህ ሁለቱ ለአካባቢዎች የአክሱም ስልጣኔ ምልክቶች ተገኝተዋል።[1] በትግራይና የሰሜን ኢትዮጵያ የሚገኙ የስልጣኔ ምልክቶች ከጥንት ግብፃውያን ወይንም ደቡብ ዓረብ ጠበብቶች የተሰሩ ናቸው እንደሚባለው ሁሉ፣ በሌላ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር የሚገኙ የስልጣኔ ቅሪቶች በደፈናው ከአክሱም የመጡ ናቸው ይባላሉ። አልፎ አልፎ በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ አቤሊስቶች የቢተክርስቲያን ህንፃ ፍርሰራሾች የአክሱም ሥልጣኔ መስፋፋት ጊዜ የተሰሩ ሲሆኑ ሌሎች እንደ መቃብሮች የመሳሰሉት ግን ከቀደምት ነዋሪ ሕዝብ የተሰሩ ለጥንት ግብፃውያን የሥልጣኔ ምልክት የሆኑት ፒራሚዶች እንዲዳብሩ መሠረት የጣሉ ሊሆኑ ይችላሉ።

በጉራጌ ሙሄር ሶዶ አካባቢ ጪአ፣ ሰምቦ፣ ሰደን ወዘተ የተባሉ ቦታዎች ሁለት ከሰማንያ ሜትር ያላነሰ ቁመት ያላቸው በግዙፍ የድንጋይ ክምችት ከፍታ ያላቸው በጎሹ ቦታዎች የተሰሩ በተለይ በሰደን 150 የሚሆኑ ባለአራት ማእዘን መቃብሮች ተገኝተዋል። በመቃብሮቹ የተካሄደው ምርምር አጥጋቢ ውጤት ያላስገኘበት ምክንያት ሬሳዎቹን የሚሸፍነው ድንጋይ የአሲድ ጠባይ ስላለው አጥንቶች አመድ ሆነው ስለተገኙ ነው። አንዳንድ ጊዜም በመቃብሮቹ ላይ ስእል ተገኝቷል። እንደዚሁም የግብፃውያን መሰል ቢላ ተገኝተዋል። አንዳንድ ጊዜም በመቃብሩ ላይ ሐውልት የሚመስል ወይንም በአክሱም የኢዛና ጽሑፍ ያሉባቸው ድንጋዮች የሚያስታውሱ ናቸው።

እነዚህ ሁሉ ሰራዎች በአክሱማውያን የተሰሩ መሆናቸውን አያጠራጥርም። በምስራቅ ኢትዮጵያ ከሐረር 50 ኪሎ ሜትር በስተምስራቅ አባ አዘይስ የተባሉ ፈረንሳዊ ካቶሊክ ላዛሪስት ሚሲዮናዊ "ደልመን" ብሎ የጠራቸው መቃብሮች አግኝተዋል። ደልመን በብዙ የዓለም ክፍሎች ተገኝተዋል፣ በግብፅ ግን አልተገኘም። በምሥራቅ ኢትዮጵያ በሐረርጌ የተገኙ መቃብሮች በክንቲ ሮሲኒ አስተያየት ደልመን ሳይሆኑ በሰሜን ኢትዮጵያ ከሚገኙ መቃብሮች ተመሳሳይ ናቸው። በሰሜን ኢትዮጵያ ከሚገኙ መቃብሮች ዋናውና ትልቁ በእክሱም ኩጣ ንፋስ መውጫ በሚባለው ቦታ የሚገኘው መቃብር ነው። የሐረር ጉራጌ ቋንቋዎች የተፈጠሩት ከጥንታዊ ኢትዮጵያዊ ቋንቋ ከግዕዝ በቀጥታ ወይንም ከግዕዝ በፊት የነበረው የኢትዮጵያ ቋንቋ ሊሆን ይችላል፣ ከትግሪኛ ጋራ ብዙ ይዛመዳሉ። መቃብሮቹ የተሰሩበት ዘመን ለማወቅ ጨርሶ አይቻልም።

[1] Conti -Rossini ibd p . 282-3

የአክሱም ስልጣኔ ሳይጠፋ ሰረጅም ጊዜ መቆየቱ ነው እንጂ በመላው ኢትዮጵያ ከምዕራብ ክፋ እስከ ምስራቅ ከሰሜን እስከ ደቡብ እሞ የአክሱም ስልጣኔ ምልክት የሌለበት አካባቢ አይገኝም። በዓረብ ሀገር የፖለቲካና የወታደራዊ ሽንፈት ካጋጠማት በኋላ በአፍሪካ ብቻ ተወስና፣ እንቅፋት ባያጋጥማት ስልጣኔዋና ቋንቋዋን በማስፋፋት ኢትዮጵያ ባለ አንድ ቋንቋ ሀገር ልትሆን ትችል ነበር። ይህ ባይቻልም አሁን የሚታዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በሙሉ እንደ ሀረሪና ጉራጌ የግዕዝ ቋንቋ ድብልቅ መሆናቸው አይቀርም ነበር።

ስለዚህ አሁን ትግሪኛ አማርኛ አደሪኛ ጉራጊኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን የሴም ቋንቋ ተናጋሪ ተብለው እንደሚመደቡ ሁሉ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሴም ቋንቋ ተናጋሪ ይባል ነበር። ነገር ግን የአክሱም መንግሥት ወደ ደቡብና ምዕራብ ያደረገው ማስፋፋት ከባድ እንቅፋት ሰላጋጠመው ብዙ ሳይቆይ በ10ኛ ክፍለ መቶ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ ግቋረጥ የተገደደበት በዳዲት ጊዜ ነበረ። ኢትዮጵያ በዳዲት እርስ በእርስ ጦርነት ዘመን ጀምሮ ከምሰራቅ ሰሜን ሱዳን እስከ ደቡባዊ ሶማሊያና ሶኮትራ ደሴት ድረስ የነበረ ግዛቷ የደቡብ ክፍላተ አገሮች ጭምር ከቁጥጥሯ ውጭ ሊሆኑ ችለዋል። የእስተዳደር መዋቅርም በጦርነት ስለ ወደመ ይህ የዳዲት ዘመን የጨለማ ዘመን ተብሎ ሊጠራ ይችላል። የዛሚዊ ዘመነ መንግሥትም የግዛት አንድነት ለማስከበር ትኩረት ስላልሰጠ በዚሁ ረገድ ከጨለማ ዘመን ውስጥ ሊጠቃለል ይችላል። ሰሎሞናዊ ንጉሣዊ አገዛዝ ከተመሰረተ በኋላ ግን ኢትዮጵያ ከግዛቷ ተነጥሰው የነበሩ የምሥሰራቅ እና የደቡብ ክፍላተሀገር፣ ከሰሜንም፣ ለማስመለስ የጣረችበት ዘመን ስለነበረ የጨለማ ዘመን አብቅቷል ለማለት ይቻል ይሆናል። ጥረቱ ሙሉ በሙሉ የተሳካ ሊሆን ያልቻለበት ምክንያት በምሥራቅ የአፋርና የሶማሌ ግዛቷ የእስልምና ሃይማኖት በመቀበላቸው እንደነና ለግዋሀድ ቀላል ሆኖ ስላልተገኘ ነው።

በመሐመድ ግራኝ እና በኦሮሞዎች እርስ በእርስ ጦርነት ጊዜ የሥልጣኔዋ ቅርሶች በባሰ ሁኔታ ስለወደመባት አስከፊ የሆነው እንደነና በጨለማ ዘመን ወድቃለች ለማለት ይቻላል። ስለዚህ ይህ ዘመን የኢትዮጵያ የጨለማ ዘመን ተብሎ ሊጠራ ይገባዋል። የቀሩት ዘመናት ግን እላይ የጠቀስኳቸው የታሪክ ግሰረጃዎች እንደሚያሰረዱ የጨለማ ዘመን ተብለው ሊጠሩ አይገባም።

8. <u>የዮዲት ዘመን</u>

ዮዲት የምትባለው ንግሥት በኢትዮጵያ ታሪክ መዝሰቱ ብሁሉም የግይካድ ቢሆንም ዝርዝር ታሪኳ እና ግንኙቷ በሚመለከት ግን በትክክል አይታወቅም። ዩዲት የነገሠች በ921-933 ዓ.ም. የእስክንድራያ ጳጳስ ከነበሩት አቡነ ኮዝማ ስኢትዮጵያ ጳጳስ ሆነው የተሳኩ በየዋሁ አቡነ ጴጥሮስ ላይ ኢትዮጵያ የፈጸመችው ግፍ እግዚአብሔር የላከባት የቅጣት መቅሰፍት ነው ተብሏል። እንደ ሀገራችን ታሪክ ጸሐፊዎች አቀራረብ ዮዲት አይሁዳዊት ናት የእሪት ሕግ በመደገፍ የክርስትና ሐይማኖት አንቀበልም ያሉት በሰሜንና፣ በወገራ፣ ወልቃይት፣ በላስታ የነበሩት ፈላሾች አሰባስባ ወደ ትግራይ ዘመቻ ሐውልቶቹንና አብያተክርስቲያናትን አቃጥላ ሕዝበ ክርስቲያንን ፈጅታ በደብረ ዳሞ ተራራ ይኖሩ የነበሩትን ከነገሥታት የሚወለዱትን መሣፍንት አሳርዳ የነገሠች ናት ብሏታል። የእስክንዲሪያ ፓትያራኮች ታሪክ ላይ ዮዲት የባኒ አል ግግያህ ንግሥት ብሎ ይጠራታል። በኢትዮጵያ ግን በዚሁ ሰም

የሚጠራ ክፍለ ሀገር የለም[1] ከአጼ ካሌብ ጀምሮ እስከ ዮዲት ዘመን 300 ዓመት በኢትዮጵያ ታሪክ የጨለማ ዘመን ተብሎ የሚጠራ ብዙ የታሪክ ግሰረጃዎች የማይገኙበት ዘመን ስለነበረ ነው። ሆኖም ይህ ዘመን ምናልባት ኢትዮጵያ ስልጣኔዋን ያስፋፋችበት ጊዜ ሰለነበረ ወርቃማ የብልጽግና ዘመን ነበር።[2]

በ979 - 1003 ዓ.ም. በእስክዲሪያ መንበረ ፓትሪያርክ የነበሩ አቡነ ፊስተዩስ Fileteus[3] በነበሩበት ጊዜ ኢትዮጵያ ከአቡነ ጴጥሮስ ጀምሮ ሕጋዊ አቡን ስላልነበራት ሰይፈ አረድ የተባሰ የኢትዮጵያ ንጥሥ ጊዮርጊስ ሰተባለው የኑቢያ ንጥሥ የእስክንድሪያ ሊቀ ጳጳስ ሰኢትዮጵያ ጳጳስ ይልኩ ዘንድ እንዲያግልደው ደብዳቤ ጽፎ ነበር። የኑቢያ ንጥሥ የግብፁ ፓትሪያርክ ወደ ኢትዮጵያ ጳጳስ እንዲልኩ ባቀረበው ልመና መሠረት አቡነ ዳንኤል ሲሳኩ ኢትዮጵያውያን በታሳቅ ደስታ ተቀብሉዋቸዋል። የኢትዮጵያ ንጥሥ ሰኑቢያ ንጥሥ በግእዝ ቋንቋ የግፈው ደብዳቤና የወቅቱ የኢትዮጵያውያን የታሪክ ፀሃፊዎች ያቀረቡት ዘገባ የሚጠቁመን ነገር ኢትዮጵያ በዚያን ዘመን በታሪኳ በወሳኝ ምዕራፍ ትገኝ እንደነበረ ነው።

ምንም እንኳን ኢትዮጵያውያን የታሪክ ጸሐፊዎችና የግብፅ ፓትሪያርኮች ታሪክ መዛግብቶች በዓመተ ምህረትና በአንዳንድ ዝርዝር ሁኔታዎች ቢሰያዩም በመሠረቱ ታሪኩ በግይለያዩበት ሁኔታ ገልፀውታል። ክርስቲያን የኢትዮጵያ መንግሥት ሊጠፋ ትንሽ ነበር የቀረው። ክርስቲያን ሕዝብም ባሪያ ሆኖ ክመሸዋ ያመሰጠ ሸሽቶ ወደ ሌላ ክፍላተ ሀገር ይሰደድ ነበር። ንጉሡም ወደ ሸዋ በመሸሽ የሞት ሽረት ፍልሚያ በማድረግ ወሳኝ ሚና ተጫውቷል።

በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ እስከ ዘመናችን የነሳ ጦርነት የተደረገበት ጉዜ የለም። የሃይማኖት ጦርነቶች ግን ተደርጓል። በዮዲት የተቀሰቀሰው ጦርነትም የእሪት ሕግ ተከታይ የሆኑ ኢትዮጵያውያንና በክርስትና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑት ኢትዮጵያውያን መሀከል የተደረገው የሃይማኖት ጦርነት ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፊዎች ያቀረቡት ዘገባ ይኸንን ሁኔታ መኖሩን የሚያስተጋባ ነው። በሚቀጥሉት ዘመናትም በእስላሞች ኢትዮጵያውያን እና በክርስቲያኖች መሀከል ጦርነቶች ተካሄዷል።

ሌሉች ታሪክ ጸሐፊዎች ኢትዮጵያውያን ያቀረቡት ታሪክ ጨርሶ ሳይከዱ የግብፅ ፓትሪያርኮች ታሪክ በኒ አል ሐመ·ያህ ብሎ የጠሯት ንግሥት የአጻጻፍ ስህተት ነው ብለዋል፣ አል ደመ·ታህ ተብሎ መነበብ እንዳለበት በማመን ዮዲትን ክአባይ በስተደቡብ ይነኝ የነበረው ትልቁ ዳሞት የዛሬው ምዕራብ ሸዋና ወለጋ ንግሥት አድርጓታል። በኢትዮጵያ ታሪክም እስክ 13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ዳሞት የሚባል መንግሥት ተዘግቧል። በመጨረሻ ዮዲት በመሞቷ ጦርነቱ በኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት ድል እድራጊነት ቢደመደምም ጦርነቱ ኢትዮጵያ ደካማ መንግሥት እድራጓት ነበረ ያብቃው። ኢትዮጵያ የደቡብ ክፍለ ሀገሮች ሰመቆጣጠር ሳትችል ክመቅረቷ ሌላ እስክ 10ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ዓ.ም. ክርስቲያን የነበሩ እንደ ዘይላ፣ በርበራ፣ የባሕር ጠረፍ ወደቦቿ፣ የእስልምና ሃይማኖት ተስፋፍተውባቸው ሰለነበረ በኢትዮጵያውያን መሐከል

---

[1] C. Conti - Rossini ibd p. 286
[2] C. Conti - Rossini ibd p. 285
[3] C. Conti - Rossini ibd p. 286

በክርስቲያኖችና በእስላሞች የሃይማኖት መርኆቱ እንዲካሄዱ መንገድ ከፍቷል።

ቀደም ብሎ የእስልምና ሃይማኖት የጣዖት በዓለላክ ሲሆን፣ በ14ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ዓ.ም. በሱዋኪን አስልምና ገብቶ ነበር። እንደዚሁም በዚሁ ጊዜ የባርካ፣ ቢጀ ጎሳዎች እና የሳሆ ጎሳዎች፣ ታጁራ መደብ አካባቢ እስላም ሆነው ነበረ። በአጠቃላይ በባሕር ጠረፍ መደቦች ብቻ ሳይሆን ወደ መሀል ሀገር በ13 መቶ ክፍለ ዘመን እንደ ሐረር፣ ዝዋይ፣ ሀዲያ ድረስ እስልምና ተስፋፍቶ ነበር።

ዮዲት ወደ ትግራይ ዘመቻ አደርጋ በመጣችበት ጊዜ በደብረ ዳሞ ታጉሮ ይኖሩ የነበሩ ሰለሞናዊ ዘር ያላቸው ከፈጅች በኋላ ከአልቲት ያመለጡ ጥቂቶች ወደ ሸዋ መንገዝ ሸሽተው ሄደው ነበር።

ዮዲት መሞቷ ሲሰማ እምበሳ ውድም በተባለው የተደሞው ንጉሥ ልጅ ወደ ትግራይ ዘመምጣት ለ20 ዓመት እንደገና በእባቶቹ ዙፋን ተቀምጠ ሲገዛ ቆይቶ ሞተ። ልጁ ግን መንግሥት ለመያዝ ከላስታ የተነሳ ዓመፅ ሲቋቋም ስላልቻለ እንደ አባቱ እንደገና ከአክሱም ወደ ሸዋ ሸሽቶ ሄደ። መራ ተክለሃይማኖትም የነገዋን ላስታ መንግሥት መሠረተ።

ምዕራፍ 3

ኢትዮጵያ ድኅረ ዛጉዌ በሰለሞናውያን ነገሥታት ዘመን

በ1268 ዓም. የመንግሥት መሪነት ስልጣን ከዛጉዌ ነገሥታት ወደ ሰለሞናዊ ዘር ያላቸው ነገሥታት በይኩኖ አምላክ መሪነት በሰላማዊ መንገድ በመሉ ሕዝቡ በሚገኘው ፍፁምና በደብረ ሊባኖስ ሸዋ ከሚገኘው ገዳም አባቶች አማካኝነት ሊዘዋወር ችሏል። የእሰተዳደር ማእከልም ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሸዋ ተዛወረ። ሸዋ በጀዮግራፊ አቀማመጧም የኢትዮጵያ ማእከል በመሆና፣ የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት በምሥራቃዊ የሀገራቷ ክፍል በተቋቋመት እስላማውያን ትናንሽ መንግሥታት የሀገራቷን እንድነት የሚያናጉ የሚሰንዘሩባት ጥቃቶችን ለመከላከል፣ ለመቋጣጠር፣ ብሎም ለመግታት እንዲቻል፣ የኢትዮጵያ መስተዳደር በሸዋ ማእከላዊነት መሆኑ አመቺ ሁኔታዎች ፈጥረዋል። በሰለሞናዊ ነገሥታት መሪነት በሸዋ ማእከላዊነት የተቋቋመው የኢትዮጵያ መንግሥት የነበረው ደካማ ጉን እንደ ቀድሞ ጊዜ እንደ አክሰምና ላስበላ ቋሚ ዋና ኩተማ መፍጠር ያለመቻሉ ነው። ይህ በመሆኑ የማእከራዊ ኑሮ ግንባታዎች በማከናወን ለመጪው ትውልድ ታሪክ ማስተላለፍ አልቻሉም። ጠንካራ ጉኑ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በየወቅቱ የተከናወኑትን የመንግሥት ሥራዎች በጽሑፍ ለወጪው ትውለድ ማስተላለፍ ነው። ሌላ ጠንካራ ጉኑ ወሳኝ ፈተናዎች በማሳለፍ የሀገር እንድነትን ለመጠበቅ አስደናቂ የኢትዮጵያውያን ጀግንነት የታየበትና በታሪክ የተመሰከረበት ዘመን ነበረ። ለ300 ዓመት ጎድግ የዘለቀው በሸዋ ማእከላዊነት የኢትዮጵያ መንግሥት፣ በሃይማኖት የተነሱ የእርስ በርስ ጦርነቶችን ተቋቁሞ ኢትዮጵያ በእክሱም መንግሥት ዘመን የነበራት የመሬት ስፋት ከሞላ ጉደል ተረካቢ ሆና ለመጠበቅ ሞክረዋል፣ አነስተኛ የማእገና የአግረኛ ስን ጽሑፎችም ዳብረዋል፣ ከምዕራባውያን ጋራ የውጭ መንግሥታትም ግንኙነት ለመፍጠር ሞክረዋል፣ ዘመኑ ምዕራባውያን ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ መኖሩዋን በትክክል ያወቁበት ነበር። የሰለሞናዊ ነገሥታት ስልጣን ሲጨብጡ የኢትዮጵያ አመራር ብሩህ ተስፋ እልጠበቃቸውም። በባሕር ጫፍ የሚገኙ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገሮች የእስልምና ሃይማኖት የሆኑ ለማዕከላዊ የክርስቲያን መንግሥታት የግይታዘዙ መንግሥታት ተቋቁመው ነበረ። ይኸም ሁኔታ ለእርስ በእርስ ጦርነት የሚጋብዝ ነበር። ክይኩኖ አምላክ መንግሥት ጀምሮ እስከ ግራኙ መሐመድ ሞት ድረስ ለ300 ዓመት የኢትዮጵያ ታሪክ በእስላሞችና ክርስቲያናች የማያቋርጥ ጦርነት የተካሄደበት ጊዜ ነበር። ይህ በሀገራችን የተካሄደው የሃይማኖት ጦርነት በመካከለኛ ምስራቅና በኤውሮጳ የተካሄደው ጦርነት አካልና ነፀብራቅ ነበር። ዓረቦች በእስልምና ሃይማኖት በመመራት በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ ባልታሰበ ሁኔታ ወታደራዊ ወረራ በመፈጸም መካከለኛው ምስራቅ ሀገሮችን በቁጥጥራቸው ለማድረግ ችሏል። ነብዩ መሐመድ ከሞተ በኋላ በስድስተኛው ዓመት በ689 ዓም. ግብፅ በዓረቦች እጅ ወደቀች። ዓረቦች ወደ ሰሜን አፍሪካ ወረራቸውን በመቀጠል በ689 በካርታጅ ከሊድ

ጦርነት አካሂደው ከግሪኳት በኋላ በአሳት አቃጠሏት። ከዚህ ጊዜ ጀምሮም ስሟ ከታሪክ ተሰርዟል። በ711ዓም. በበርበር የተገነባ 12,000 የዓረቦች ጦር የጂብራልታር ካናል ተሻግሮ ወደ ስፓኝ ገባ። ሁለት ዓመት ባልሞላ ጊዜ የቪዚጎት መንግሥትን አሸንፎ መላው ስፔኝን ለመቆጣጠር በቅቶ ነበር። ቀጥሎም ዓረቦች ወደ መሐል ፈረንሳይ ዘልቀው በመግባት መላው ኤውሮጳ እስላማዊት ዓረባዊት ለማድረግ ተቃርበው ነበር። ነገር ግን በቻርል መዶሻ የሚመራው የፈረንሳይ ጦር ፕዋቴ በተባለው ቦታ በ732 ዓ.ም. በተደረገው ጦርነት በዓረቦች ላይ ድል ስለተቀዳጀ የዓረቦች ወረራ ለዘለቄታው ሊገታ ችሏል። ከዚሁ ጦርነት በኋላ የክርስትና ሃይማት ሕልውና አና የኤውሮጳ ሀገሮች ነፃነት ተከብሮ ሊቆይ ችሏል። ከ300 ዓመት በኋላ ሌላ እስላማዊ የቱርክ መንግሥት ተነስቶ በዓረቦች ተተክቶ በዓረቦች ያልተያዘውን የዚዘንታይን መንግሥት በቁጥጥሩ ከግዋሉ በላይ በምስራቅ በኩል በኤውሮፓ ላይ ወረራ በማድረግ ሀንጋሪና አስትሪያ ድረስ ደርሶ ነበረ። የኤውሮጳ ሀገሮችም ተባብረው ያደረጓቸው የመስቀል ጦርነቶች ውጤት አልሰጡም ነበር። በዚሁ ጊዜም ኤውሮፓ በቱርክ እስላማዊ መንግሥት ስር ለመውደቅ ተቃርባ ነበር። ዳሩ ግን ቱርኮች በቪዬና አጠገብ ሽንፈት ስለደረሰባቸው ኤውሮጳ ከቱርኮች ወረራ ልትድን ችላለች።

የዓረቦችም ሆነ የቱርኮች ግዛታቸውና ሃይማኖታቸውን የማስፋፋት ዓላማ ዋና ትኩረታቸው ወደ ኤውሮፓ ቢሆኑም ወደ ሀገራችንም ወኪሎቻቸው መላካቸው አልቀረም። በየጊዜው የነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታትም በክፋ ዓይን የሚያዩዋቸው በሀገራቸው መሬትና የራሳቸው ሕዝብ በእስላማዊ ሐይማኖት የሚያምኑ መንግሥታት ዙርያቸው መቋቋማቸው በማየት በመንግሥታቸው ሕልውና አደጋ ማንጃበቡ መገንዘባቸው አልቀረም ነበር።

ይኩኖ አምላክ ስልጣን በያዘበት ጊዜ የሁኔታው አሳሳቢነት በመመለከት ከቢዛንታይን መንግሥት ጋር ግንኙነት ለማድረግ በመፈለግ ደብዳቤና ስጦታ ልኮ ነበር። ነገር ግን ራሱ የቢዛንታይን መንግሥት የራሱ ሕልውና እንኳን ለማስከበር በማይችልበት ወቅት ስለነበረ መኳራው ውጤት ሊያገኝ አልቻለም።

ይህ በመሆኑ በይኩኖ አምላክ የተተካ ንጉሥ ከግብፅ ጋራ መልካም ግንኙነት ለመፍጠር ከከበቡት ኢትዮጵያውያን የእስላም መንግሥታት ግንኙነት አሻሽሉ በስላም ለመኖር አሰቡ፣ ወስኑ ለእስላም ነጋዲዎች ክፍት አድርጎ ነበር። ይህ በሰላም የመኖር ሙከራ ግን ጥሩ ውጤት ሊሰጥ አልቻለም።

9. <u>አጼ ዓምደጽዮን</u>[1]

በኢትዮጵያውያን አስላሞችና ክርስቲያኖች አርሰ በአርሰ አስከፊ ጦርነቶች የተጀመሩበት በይኩኖ አምላክ የልጅ ልጅ በሆነው በንጉሥ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ነበር። ዓምደ ጽዮን የነገሡው ከ1312 - 1342 ዓ.ም. ለሰላሳ ዓመታት ነበረ። ከአጼ ዓምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ጀግንነታቸውን ያስመስከሩበት ዘመናት ነበሩ።

ኤውሮጳውያን አንዳደረጉት ሁሉ በክርስትና እምነታቸው ፀንተው ለመኖር ያደረጉት ትግል ነበረ። ከዲት ጦርነት በኋላ በደቡብና በምስራቅ ኢትዮጵያ ተቋቁመው የነበሩት መንግሥታት ለሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ።

[1] Luca Dei Sabelli ibd VI p 267

1ኛ. በአጠቃላይ ስማቸው ሲዳማ ተብለው የሚጠሩ፣ ወይም የደቡብ ኩሽ የሚባሉ፣ በጥንት ጊዜ ከስሜን የፈለሱ ናቸው የሚባሉ። የአክሱም መንግሥት አሁን የሚታወቀውን የኢትዮጵያ ደቡብዊ ወሰን ከገሞያ ሐያት እስከ ሩዶልፍ ሐይቅ ከከፋ እስከ ዘይላ። የባሕር ወደብም እስከ ደቡብ ስማሊያና አዛኒያ ተቆጣጥሮ እንደነበረ ታሪክ ያረጋግጣል። ከሲዳማ መንግሥታት መሐል 1ኛ ጃንጀሮ 2ኛ ቦሻ 3ኛ እናሪያ (ለ.መ.) 4ኛ አንፈሉ ምዕራብ(ወለ.ጋ) 5ኛ ጋፋት የተባሉ የሚጠቀሱ ናቸው። ከነገሥታትም ሆነ ከባለፀጉች ከስሜን እንመለሳለን የማይሉ የለም፣ ይህም የሚያረጋግጠው የአክሱም መንግሥት ተቆጣጥሯው እንደነበረ ነው።

2ኛ. የእስልምና እምነት የሚከተሉ የሰልጣን መንግሥታት ተብለው የሚጠሩ የሚከተሉት ናቸው። 1ኛ. ሐዲያ፣ ጉራጌን የሚያጠቃልል 2ኛ. ፋጢጋር 3ኛ. ይፋት 4ኛ. ዳዋሮ 5ኛ. ባሌ 6ኛ. ሐረር ከተማ 7ኛ. ግና 8ኛ. እዳል። ጦርነቱ የተካሄደው በኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥትና በተጠቀሱት 8 እስላማዊ መንግሥታት መሐል ነበር። የሲዳማ መንግሥታት የያዙት ገለልተኛ አቋም ነበረ።

ከእስላም መንግሥታት ከሁሉም ኃይለኛና የበላያንት የነበረው የይፋት መንግሥት ነበረ። ይህ መንግሥት በክርስቲያኖች ዘንድ የአረመኔዎች መስፍን ተብሎ ይጣራ ነበር። ይፋት ወላገማ ተብለው በሚጠሩ የነገሥታት ዘር ሀረግ ይመራ ነበር። ይህ ስርወ መንግሥት የተመሠረተው በዑመር ወላገማ ነው። እሱም ከነቢዩ መሐመድ ጎሳ ከሆነው ከኮሬይሰቶች ከሚወለደው ከያህያ የሚወለድ ነበር። አሱም በዘኩሉ አል ሐሰን ከተባለው ከነብዩ መሐመድ የልጅ ልጅ የሚወለድ ነው። በአጼ ዓምደ ጽዮን ጊዜ የይፋት ንጉሥ ሐስ አዲን የተባለው ነበረ። ጦርነቱ የተቀሰቀሰው የግብፅ መንግሥት በአስክንዲሪያ ፓትሪያርክ ስለሚፈጽመው በደል ለመበቀል አጼ አምደ ጽዮን የአባይ ወንዝ አቅጣጫውን እቀይረዋለሁ ብሎ በመዛቱ፣ አንዲሁም በአስላም ነጋዲዎች የበቀል እርምጃ በመውሰዱ ነው። አክ አዲን አጠፋውን በመመለስ ቤተክርስቲያኖችን በማቃጠል ቁሶችን ሐይማኖታቸው እንዲክዱ በማድረግ በክርስቲያን መንግሥት ውስጥ ግዛት በልቶ በመግባት የዓምደ ጽዮን ሚስት ባሪያ እንደሚያደርጋትና የቤቱ እህል እንድትፈጭ እንደሚያደርጋት ዛቻ ያሰማ ነበር። ከዚህም ሌላ ወደ ካይሮ ተልኮ የነበረ የኢትዮጵያ መልእክተኛ በመግረክ ሃይማኖቱን አልክድም በማለቱ በአሰቃቂ ሁኔታ ስለገደለው በሕዝቡና በመንግሥቱ ቁጣ ስላስነሳ ነበረ። አጼ ዓምደ ጽዮን ጦሩን በመምራት ባደረገው ዘመቻ ይኩተለው የነበረው መመሪያ፣ ጠሩ በብዙ አቅጣጫ በማሰግራት ድንገተኛ አደጋ በመጣል ለጠላት ፋታ አለመስጠት በጠላት ላይ ሽብርና ፍርሀት መፍጠር ነበር።

ሐስ አዲን በሊሊት አደጋ በመጣል ቢሞክርም አጼ ዓመደ ጽዮን መኳራውን በማከሸፍ የሐስ አዲን ወንድም ወደ ነበረበት ጦር ግንባር ጥቃት በመሰንዘር በጉራዴ ራሱ ከገደለው በኋላ ጥቃቱን በመቀጠል በፈረሰኞች እየተረዳ የጠላቶች መደናገጥ በመጠቀም ጠላቶችን በማሳደድ ሐስ አዲንን ግርኮ ገዛቱቹ ይፋትና ፋጢጋርን በኢትዮጵያ መንግሥት ቁጥጥር ስር ሆኖ አስተዳደሩ ለሐስ አዲን ወንድም ለሳብር አዲን በመስጠት በ1328 ዓ.ም. የመጀመሪያ የአጼ ዓመደ ጽዮን ዘመቻ በድል እድራጊነት ፍጻሜ ሆነ።

የእስላሞች የተባበሩት ነገሥታት ሱልጣኖች ግን ሽንፈታቸው አላመኑም ነበር። በወገራ፣ በሰሜን፣ በደንቢያ፣ በቤጌምድር፣ በማና ሐይቅ አካባቢዎችና በተከዜ ወንዝ አካባቢ የኖሩ የነበሩ ሕዝቦች በክርስትና እምነት አያምኑም ነበረ። ከአሪት ሕግ ጥና አልተላቀቁም ነበር። ሳብር አዲን

እንዲተባበሩትና የክርስቲያን መንግሥትን እሱ በምስራቅ ሲዋጋ በሰሜን እንዲወጉት ወሊሶቹን በመላክ ይሰብካቸው ጀምሮ ነበረ። የሐዲያና የዳዋር የጣላቶቹ እትዮ በሚገባ ሰላመቀ ለየብቸቸው ጥቃት ለመፈጸም ባወጣው እቅድ መሠረት ጠታደሮቹ ወደ ሀዲያ ልኡ የሐዲያ ሱልጣን ድንገተኛ ወረራ ሰሰተፈጸመበት ተማረከ። ሌሉች የአጼ ዐምደ ጽዮን ወታደሮች በተመሳሳይ ጊዜ ከሐዲያ በሚያዋስነው ወረራ በመፈጸም ድል ተቀዳጁ። ሳብር አዲን ወደሚገኝበት ሰፈር ያርሰው ነበር። ነገር ግን ሱልጣኑ ሸሽቶ ሊያመልጥ ችሏል። እጼ ዐምደ ጽዮን በዳዋሮ ጣዚያ በማድረግ ወደ ፋጢጋር አመራ። ሳብር አዲን ጠርነት ለመግጠም ተገዶ ተሸነፈ። ሚስቶቹና ልጆቹ ተማረኩ፣ ከተማው ወደመ። በአጼ ዐምደ ጽዮን ሚስት በዙል ምህረት በመጠየቅ አማላጅ ላከ። ዐምደ ጽዮን ግን ራሱ አፈቱ መቅረብ አለበት ብሎ የሚሉቱ አማላጅነት ሳያቀበለው ተረ። ሳብር አዲን ድንጋያ በትክሻው ሞኖ ይቅርታ በጠየቀበት ጊዜ የዐምደ ጽዮን ወታደሮች እንዲገደል ቢጠይቁም፣ ንጉሡ ግን እንዲታሠር ብሎ ፍርድ ሰለሰጠ ታስሮ በእሰር ላይ እንዳለ ሞተ።

በሐዲያ፣ ፋጢጋር፣ ይፋት፣ ዳዋሮ ሱልጣኖች ላይ የተደረገው ጠርነት እንዳያበቃ አሁንም የመንግሥቱን ሰልጣን ሰሳብር አዲም ወንድም ለጀግል አዲን ስጥቶ ወደ ሽዋ በሚመለስበት ጊዜ የአዳልና የግራ ሱልጣኖች በመመሳጠር ወደ ኋላ የሚመለሰው የአጼ ዐምደ ጽዮን ሠራዊት በደረጣ ውጊያ በመጠቃም ማጥቃት ጀመሩ፣ ብዙ ወታደሮችም ፈጁ። በዚሁ ጊዜ አጼ ዐምደ ጽዮን በከላት ውጊያ ሰልት በመጠቀም እነሱም ወደሚሰበሰቡበት በፈረሰኞች ደፈጣ በማድረግ ጠበቋቸው። እቅዱ ሙሉ በሙሉ ሰሰተሳካ ደፈጣው ሞክረው ተመልሰው በተሰበሰቡበት ቦታ እግኙቷቸው ፈጃቸው። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ይፋትንና እካባቢዋን መልሶ ለመያዝ ማንሻውም ምኞት ውድት ሰለሆነ ወታደሮች የተግረከውን ንብረት ይዘው ወደ ተጉለት ለመመለስ ንጉሡ አስተሳሰብ ግን ሌላ ነበረ። ጠላቶቹ ወታደሮቻቸውን ይዞ ወደ ተራራማ ደጋ ቦታዎች ተዋጉ እንጂ ቆላ ሀገራቸው ግን በጠርነት ስላልተነካ እንደገና ጦርነት ሊያስነሱ ይችላሉ የሚል ነበር። ስለዘህ ተከታትሎ በማጥቃት ዙተገኘው ድል በመጠቀም ጠላት ተመለሰ እንዳያንሰራራ ማድረግ አስፈላጊ ነው የሚል ነበር። በዚህ መሠረት ንጉሥ ዐምደ ጽዮን ከያፋት ወደ ዳዋር ጉዞውን ጀመረ። ወታደሮቹ ወደ ቆላ እንሂድም ብለው ተቃወሙት። ነገር ግን ንጉሡ የቁርባን ሕብስት በግውጣት ሰሳቶቹን ሳልደመስስ አልመለስም ብሎ በመግል ስኔ ወር 1330 ዓ.ም. ወደ ቆላ ሀገር አመራ። የአጼ ዐምደ ጽዮን ጦር የሚያቋርጠው የቆላ ሀገር በባሕር ዙሁል ከምጽዋ አሰከ ሕንድ ውቅያኖስ የሚያጠቃልል ሲሆን ወደ መሀል ሀገርም አሰከ ዝዋይ ሀይቅ ጨርጨር ሐረር ወዙተ... የሚዘልቅ ነበረ። ወደ ቆላ ሀገር የገያመራው የኢትዮጵያ ጦር የአዳልና ግራ ሱልጣኖች በቆላ ከሚገኙ ጉሳዎች ከተመለመለ ጦራቸው በደፈጣ ያሰግቋረጥ ያስወጉት ነበረ። ዓለግው ፈት ሰፈት ውጊያ በግሰወገድ ወራረውን ጦር በግድክ በዐሸታ ሰድክም፣ በውሀ እጥረት፣ ጦሩ እንዲያልቅ ነበረ። የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት ወታደሮች በክላድ ችገር መሆናቸውን ሰላወቁ እስላሞች ጥቃታቸውን መሰንዘር ጀመሩ። በዚሁ ጊዜ ንጉሡ የመንፈስ ጥንካሬ ስለነበረው ወታደሮቹን በግንቃቃት እጥቂዎቹን ለመቋቋም አሰችሏቸዋል። በሁለቱ ወገን ወሳኝ ፈልጊያ ነበረ። በቁሶች ስብክት የተቀሰቀሱ ብዛት ያላቸው ገበሬዎች እንደ መስቀል ጦርነት ጊዜ የንጉሡን ጦር ያጠናክሩ ነበር። በባኩላቸው አስላሞች ቅዱስ ጦርነት ጅሀድ በግወጅ ያላቸው ኃይል

ዘመኑ አሰልፈው ነበር። የኢትዮጵያ ሠራዊት በግያውቀው በቆላ ሀገር ዘጦርነት ተወዋሮ መሆኑን ስላወቀ በአጼ ዓምደ ጽዮን ተደም ብሎ በያዘው የአሰላም ሀገሮች ሀገረ ገዥ ሆኖ ተሾሞ የነበረው ጀግል አልዲን ከደቶ የኢትዮጵያ ጦር በስተጀርባ ወደኋላ ሽሽቶ እንዳያመልጥ ውጊያ ለግደረግ ሞክሮ ነበረ። የአሰላም ጦር ዘመኑ አስተባባሪም ዘመካ ባላባት ዜተስብ ተወላጅ፣ ዘሆነው ሼክ ሰሊዘ ዙተባለው ሐረር ኩተግ ዋና ሠፈሩና ሞዙቱ ግድረግ ነበረ፣ ተጨግረ ጎሳዎችም ዘጦርነቱ ገብተው ነበር። በዚሁ ዓይነት ዙተሰበሰበው የአሰላም ጦር ቁጥሩ እርባ ሺህ /40,000/ ይደርስ ነበረ የባላል። በዚሁ ወሳኝ ፍልግያ ጊዜ ንጉሡ ታመመ። ሠራዊቱ ሥጋት ላይ ወደቆ ነበረ። ከርስቲያኖች ከአደጋ ያዳናቸው አስላሞች ዘፈጸሟቸው ስዙተቶች ነበረ። ፲ኛ.ሽህ ሳልዘና የአዳልና የግራ ሱልጣኖች የፈጸሟቸው ስዙተት ጥሩ ውጤት ይሰጧቸው የነበሩ የደፈጣ ውጊያ ትተው በግንባር መግጠም ነበረ። 2ኛ. ስዙተት የጀግል አልዲን ጦር አስዘቀላቀል ድረስ አስግጠዘቃቸው ነበረ። አጼ ዓምደ ጽዮን ታሞ ስድስት ቀኖች ከአልጋ ሳይነሳ ምግብ ባያቀምስ ቆይቶ ነበረ። ግንባር ቀደም የነበረ ጦሩ ከጠላት ጦር ተጋጭቷል፣ ጠላት ለውጊያ ተዘጋጅቶ እየገስገሰ መሆኑን በሰግ ጊዜ ከአልጋ ተነስቶ መቀም እቅቶት ነበር። ከጉኑ የነበሩ ሁለት ሚስቶቹ ወደ ኋላ ለግፈግፈግ መከሩት፣ ዳሩ ግን ንጉሡ "እንደ ሴት ሆኜ ልመት"? ብሎ መለሰላቸው። ዘዚሁ ጊዜ እንደኛዋ ንግሥት የዮውርዳኖስ ውሀና የጉልጉዕ መሬት ሰጠችው። አንድ ቁስ ረጨበት ድካሙም በቅጽበት ተወው፣ እሱም ራሱ ለወታደሮቹ ረጨባቸው። ከዘህ በኋላ ለጦርነቱ ትእዛዝ ሰጠ። የክርስቲያን የግንባር ጦር ወደ ኋላ ለግፈግፈግ ተገዶ ነበር። ንጉሡ በጦሩ መሀል ገብቶ በእጁ የቀኝ ክንፍ የነበሩ መሪዎች ገደላቸው። ፈረሰኞችም የመሀል ጦር ግንባር እወደመ፣ ቀሪውን ዘስትግራ የነበረውን ከየመን የመጡ ሀገሩን የግያውቁ ወታደሮች ነበሩ። ትንሽ ጊዜ ከቆዩ በኋላ እነሱም ግፈግፈግ ጀመሩ። ከዘህ በኋላ የክርስቲያን ጦር ፋታ ሳይሰጥ በመሸሽ ላይ የነበሩ እስላሞች ላይ እንዳያመልጡ መንገድ እየዘጋ ይጨፈጭፋቸው ጀመር። ከሬሳዎች መህክል የሼክ ሳሊህ ነበረ። የግራ ሱልጣን የሚሸሹ ወታደሮችን ሰብስቦ ለመከላከል ሞክሮ የአጼ ዓምደ ጽዮን ወኔ ግን ዕድል አልሰጠውም፣ ወታደሮቹ ተደመሰሱ፣ ሱልጣኑ ተግርኮ ተሰቀለ፣ ሚስቱም ክርሊያኮኖች ጠንቋይ ያሏት የነበረ ተይዛ ገላዋን ተቆራርጦ ለጅቦች ተሰጠ። ጦርነቱ የተካሄደው ሐምሊ ወር ወደ መጨረሻ 1330 ዓ.ም. ነበረ። አሁንም የአጼ ዓምደ ጽዮን ወታደሮች አቅማቸው እንደተሟጠጠ ለንጉሡ ቢያመለክቱም ንጉሡ ግን አልተቀበላቸውም፣ አፈቱ መክላል እትም የሊላቸው የጠላት ቦታዎች ነበሩ። የዓምደ ጽዮን ወታደሮች እየገሰጉ ጠላቶቹን መደምሰስ ተጠሱ፣ ኩተሞች ተቃጠሉ፣ ተዘረፉ፣ ተወሰደው ታረዱ። የአዳል ሱልጣንም ወረራውን ለግቆም ሞክሮ ነበር። ጦርነቱ ለክርስቲያን ፈረሰኞች ምቹ በሆነ ግልፅ ቦታ ተካሄደ የአሰላም ወታደሮች በክርስቲያን ፈረሰኞች ተከበው ግምሰሜ እጥተው አለቁ! የአዳል ሱልጣን በጦር ሜዳ ሞተ። ወደ መጨረሻ የቀረ የሐረር ሱሰጣን ነበረ። የመጨረሻ ዕድል ለመሞከር በሱልጣኑ ዙሪያ የቀሩት እስላሞች በሙሉ ተሰበሰቡ፣ ከእነሱ ውስጥም 99 ባላባቶችና ሱልጣኖች ነበሩ፣ ሕዝቡም ወንድ ሴት ሳይለይ ተከፋይ ነበረ። እሁንም የወሳኙነት ሚና የተጫወተው ሱልጣኑን ከፈረሱ በጦር ወግቶ በመገደል ዓምደ ጽዮን ነበረ። እሁን ግን የሚቋቋመው ኃይል አልነበረም። ሁሉም የመሸሽ ብቻ ነበረ የተያያዙት። እሁን የተረ ስራ መስጊዶችን ማፍረስ ከተሞችን ግቃጠል ሰዎቹንም ወንድ ሴት ልጅ እዋቂ ሳይለዩ መገደል

ነበረ። የእጼ ዓምደ ጽዮን ወታደሮች እራት የተባለው በክርስቲያኖች ላይ ጥላቻ የነበረው ቦታ ደረሱ። በዚህ ቦታ ብዙ ክርስቲያኖች ጀሮዋቸውን እናንዲቆርጡ የተቆረጠ እንዲሁም የተሰለቡ ሰለነበሩ ንጉሡ ፊት ቀረቡ። በዚሁ ጊዜ ክርስቲያኖች ቁጣ ገንፍሎባቸው ሰነበረ ወንጀለኞች የሀገሩ ሰዎች እንዳያመልጡ በማሰብ የመሸሸ በማሰመሰል ወደኋላ ሲመለሱ ሕዝቡ ወደ እየቤቱ ተመለሰ። ነገር ግን ክርስቲያኖች ተመልሰው በመምጣት በክርስቲያኖች ላይ የተፈጸመው በደል በመሱ በእሰላሞች ላይ ለመድገም ቸም በቀል ፈጽመባቸዋል። ንጉሡ በድል አድራጊነት ወደ ተጉለት ሲመለስ የጀግና አቀባበል ተደርጎለታል።

3. አፄ ይስሀቅ

ያ ሁሉ የእጼ ዐምደ ጽዮን ጀግንነት ውጤት አልባ የሚያደርገው ጠላቶችን እሰከ ባሕር ዳርቻ ምፅዋ፣ አሰብ፣ ታጁራ፣ ዘይላ ራሱ ባለማባረሩ ነው። ከእጼ ዓምደ ጽዮን ቀጥሎ ከነገሡት ነገሥታት ወደ ባሕር ጠረፍ የደረሰ ከ1414 እሰከ 1429 ዓ.ም. የነገሰ አጼ ይስሀቅ ነበረ። እንደነገሡ የይፋት ንጉሥ ሠኢድ አልዲን ጦርነት ከፈተበት። በመጀመሪያ ግጭት ለክርስቲያኖች የቀኛቸው ነበር። ራሱ የይፋት ንጉሥም ለትንሽ ነበር ከመማረክ ያመለጠው። በ2ኛ ጊዜ ግን ሰይድ አልዲን ኃይሉን አጠናክሮ መጥቶ ወደ ክርስቲያን ምድር ዘልቆ በመግባት ሰፈ መሬት በመያዝ ብዙ ንብረትም ለመዝረፍ ችሉ ነበረ። 2ኛ. ዙር የክርስቲያን መንግሥት ሠራዊት ባሩዋ በተባለው የሚመራ ነበረ። ባሩዋ የተከተለው የጦርነት ስልትም እንደ ቀደምት ኢትዮጵያውያን የተለያዮ ሱልጣኖችን ለየብቻቸው መግጠም ነበር። በዚህ መሠረት የመጀመሪያ ጥረቱ የአዳል ሱልጣን ጦር ከሰዒድ አልዲን ጦር እንዳይገናኝ ማድረግ ነበረ። በአዳል ሱልጣን ሠራዊት ወረራ አድርጎ ሱልጣኑ በጦር ሜዳ ተገደለ፣ ወታደሮቹም ተደመሰሱ። ከዚህ በኋላ የሰኢድ አልዲን ሠራዊትን እያሳደደ መፍጀት ተያያዘው። በመጨረሻም በዘይላ ከተማ እንዲደበቅ አደረገው። ክርስቲያኖች የከተማዋን የውሃ መሰመር እንዲቋረጥ በማድረግ ከተማውን ከማረኩ በኋላ ሰይድ አልዲን ፈብሯሪ 16 ቀን 1445 ዓ.ም. ተገደለ። የሱ አሰር ልጆች ሸሽተው ወደ ደመን ተሻገሩ። መስጊዶችን በማቃጠል በቦታቸው ቤተክርስቲያኖች ተሰሩ። ዘይላ ክርስቲያን ሆና ለ20 ዓመት በኢትዮጵያ ቁጥጥር ሰር ነበረች። ሆኖም ኢትዮጵያ የባሕር ኃይል ሰላልነበራት የወደብ አስተዳደርም ልምድ ሰላልነበራት ለዘለቄታው በቁጥጥሯ አድርጋ ለመቆየት አልቻለችም። አሰር የሰይድ አልደን ልጆችም በየመን መንግሥት እርዳታ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ለጦርነት ሲዘጋጁ ኢትዮጵያ ልትቆጣጠር አልቻለችም። የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት በጦር ሜዳ ባገኘው ድል አንደ ዓምደጽዮን ሲጠቀምበት አልቻለም። ዘይላ በኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት በተያዘበት ጊዜ ጀምሮ የይፋት ነፃ መንግሥት ለዘላዓለም ተሰርዞ በኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት ግዛት ውስጥ ተጠቃለለ። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ፀረ ክርስቲያን መንግሥት መሪ ተዋናይ የሚሆነው የአዳል መንግሥት ነው። የወላዝማ ንጉሣዊ ቤተሰብ አንድ ዓመት ከዘይላ መያዝ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሲመለሱ፣ ዋና ኩታግቸው ያደረጋት ዳካር የምትባለው ቦታ ነበረች። አፄ ይስሐቅ፣ኮንቲ ሮሲኒ[1]፣ መረኛ ነበረ የሚለው የኢትዮጵያ ንጉሥ፣ በሰሜን ኢትዮጵያም ጦርነት አካሄዷል።

[1] C. Conti - Rossini : Etiopia e genti d' Etiopia p 55

በመጀመሪያ ዘመቻ በዳሕላክ ደሴቶች ሱልጣን ሥር የነበረች ምፅዋ በእጼ ይስሐቅ ወታደሮች ተያዘች፣ ሁለተኛ ዙር ዘመቻ ትልቁ ዳሕላክ ተያዘ። በሦስተኛ ዙር ዘመቻ ምፅዋና የዳሕላክ ደሴቶች ከኢትዮጵያ ቁጥጥር ሰር ውጭ ሆነው ሰለነበረ እንደገና ተያዙ፣ በጦርነቱም መሪ የነበረ ቃዲ ተገደለ።

ሌላ የግዛት ማስፋፋት የተደረገው ከአሪት ሕግ ገና ያልተላቀቁ የነበሩ ወገራና ደምብያ አውራጃ ነበር፣ ቤተዐሌታቸው ወድመው በበታው ቤተክርስቲያኖች ተሰሩላቸው። ወደ ደቡብ የግዛት ማስፋፋት የተደረገው ዘመቻ ከጊቤ በስተ ደቡብ ምዕራብ የነበሩ የቦሽያ /ጅማ/፣ እናሪያ /ሊሙ/፣ እና ኩዮራ የተባሉ መንግሥታት ነበሩ። ከዚሁም በስተደቡብ የነበረ የኢትዮጵያ መሬት ሰፋት በትክክለ ባይታወቅም ከስምጥ ሸለቆ ሐይቆች በስተደቡብ እሰክ ዛንዚባር፣ በምዕራብም እሰክ ናይል ሸለቆ ይዘልቅ ነበረ[1]።

ወደ ደቡብ የግዛት ማስፋፋት የተደረገው ዘመቻ ከጊቤ በስተደቡብ ምዕራብ የነበሩ የቦሽያ /ጅማ/ እናሪያ /ሊሙ/ እና ኩዮራ የተባሉ መንግሥታት ነበሩ። ሁሉም ከኢትዮጵያ ጋራ በሸዋ ግዛት የተቀላቀሉ የቀድሞ ግዛታቸው የሰይድ አልዲን ልጆች፣ የወላዝማ የነብሮ መሐመድ ዘር የሱልጣኖች ቤተሰቦች የሆኑ ከየመን ተመልሰው መጥተው የአባታቸው ሞት ለመበቀል ከጉበፅ የመጡ ቡቱርክ ውጊያ ሰልት እሰልጣኞች እየተረዱ ዘመናዊ የጠብመንጃና የጦር መሣሪያዎች የነበራቸው፣ የይግዛ ግራኝ ተመሳሳይ የሆነ መሣሪያ ታጥቀው ሰፊ ዘመቻ ጀምረው ነበር። ነገር ግን ይህ ጠንካራ ይመስል የነበረ ወታደራዊ የግጥታት ዘመቻ እንደ ተጠበቀው ውጤት አልሰጠም። ንጉሥ ይስሐቅም የጠላቶቹ እንቅስቃሴ ያውቅና ይከታተል ሰለነበረ ለመልሶ ግጥታት ተዘጋጅቶ ይጠብቅ ነበር። በመጀመሪያ ጊዜ የዘመቻው ሹም የነበረው የሳይድ አልዲን በኩር ልጅ ሳብር አልዲን ነበረ። የእስላም ወታደሮች በድንገት እደጋ ጥለው ሸዋ መሀል ገብተው በክርስቲያኖች ላይ ብዙ ሽንፈት አድርሰው ነበር። ንጉሡም ለመበቀል በእሰላም ነጋዲዎች ላይ ጥቃት ከግድረሰም በላይ ያልፈረሱ መስጊዶችን እቃጠላቸው። ጦርነቱ ከ2ቱ ወገኖች እሸናፊ ሳይለይ ለብዙ ዓመታት ቀጠለ። በመሀሉ ሁለቱ ወገኖች ለጊዜያዊ ሰላም ተሰማሙ። በዚሁ ጊዜ በ1422 ዓ.ም. ሳብር አልዲን ሞተ፣ ወንድሙ ግንሱር መሪነቱን እንደተረከበ ጦርነቱ ቀጠለ። ግንሱር ጦነቱን በማፋፋም በእግሬ መሀል ለመግባት ችሉ ነበር። ነገር ግን ሽንፈት ሰለደረሰበት በ1424 ተግረከ። ጀግል አልዲን ሌላ ወንድማቸው መሪነቱ ተረክቦ ጦርነቱ ቀጠለ። ቤተክርስቲያኖችም ይቃጠሉ ነበረ፣ ክርስቲያኖች የጦር ምርኮኞች በባርነት ይሸጡ ሰለነበረ የባሪያ ዋጋ በዓረብ ሀገሮች ረከሰ ነበረ። ጦርነቱ እሸናፊ ሳይለይ ሲካሄድ ከቆየ በኋላ በመጨረሻ ክርስቲያኖች መልሶ በማጥቃት ድልን ተቀዳጁ፣ እስላሞቹንም ከሀገራቸው ሊያስወጡ ችለዋል። በ1429 ዓ.ም. ጊዜያዊ ሰላም ሰፍኖ በነበረበት ጊዜ አጼ ይስሐቅ ተገደለ። ከሦስት ዓመት በኋላ ታዋቂው ጀግል አልዲን በቤተሰቦቹ በተፈጠረ ጠብ ሲገደል ሌላ ወንድሙ የመሪነቱን ሥልጣን ተረክቦ ጦርነቱ እንደቀድሞ ጭካኔ በተሞላበት ቀጠለ።

[1] Coulbeaux : Histoire Pollitique et religieuse d' Ethiopia p. 285

4. አፄ ዘርአ ያዕቆብ

በክርስቲያን መንግሥትም ለአጭር ጊዜ ብዙ ነገሥታት ከነገሡ በኋላ ዝነኛው የኢትዮጵያ ንጉሥ ዘርአ ያዕቆብ በ1434 ዓ.ም. ነገሠ። በእሱ ዘመን መንግሥት ሰላሞናዊ ሀረግ ያላቸው ነገሥታት ከፍተኛ ዝናና የአስተዳደር መሻሻል እርምጃ የታየበት ጊዜ ነበር። ተሳላፊ በሽታ በሀገሪቱ ገብቶ ሰለነበረ ጠርነቱ ለተወሰነ ጊዜ ቆሞ ነበረ። ኢትዮጵያ በአጼ ዓምደጽዮን መሪነት በእስላሞች ላይ የተቀዳጀቻቸው ድሉች ዜና በመካከለኛው ምሥራቅና በምዕራብያን ተሰምተው ነበር። ዜናዎች ቢሰሙም የኢትዮጵያ ክርስቲያን መንግሥት ፀረ እስላም የሚያካሄደው የሞት ሽረት ትግል ተቆርቋሪ በመሆን፣ የኢትዮጵያ እስላሞች ከዓረብ ሀገሮች እርዳታ እንደሚያገኙ ሁሉ የክርስትና እምነት ያላቸው የአውሮጳ ሀገሮች በምን ዓይነት መንገድ ለኢትዮጵያ ወታደራዊና ፖሊቲካዊ እርዳታ ማድረግ እንደሚችሉ የተደረገ ጥረት አልነበረም። ኢትዮጵያ ከኤውሮጳ መንግሥታት የትኞቹ መንግሥታት እንደሆኑ በቂ ወታደራዊ እርዳታ ሊያደርጉላት የሚችሉ የማወቅ ዕድል አልነበራትም። ለምሳሌ ብቸኛ ግለሰብ በወቅቱ ወደ ኢትዮጵያ የደረሰና ሰለ ኤውሮጳ ለአፄ ዘርአ ያዕቆብ ያወራ አንቶኒዮ ባርቶሊ የተባለው አንድ ኢጣሊያዊ ነበረ። ኢጣሊያ ደግሞ በዚያን ጊዜ ለራሷ በባእድ መንግሥታት የምትገዛ፣ በጥቃቅን መንግሥታት የተከፋፈለች፣ ኢትዮጵያን ለመርዳት የምትመረጥ ሀገር አልነበረችም። ባርቶሊ ለአጼ ዓምደ ጽዮን ይሰጣቸው የነበሩ ዜናዎች ሰለ እነዚህ የኢጣሊያ ታናናሽ መንግሥታት ከፍተኛ ሰልጣኔና ሰለ የሮማ ጳጳስ ትልቅነት ነበረ። ዘርአ ያዕቆብ አስቸኳይ የክርስቲያን መንግሥታት እርዳታ ፈላጊ ቢሆንም ከግን ጋራ ግንኙነት እንደሚያደርግ የሚያሰረዳ ሰው ሰለሌለው እንደ ቀድሞቹ የኢትዮጵያ መንግሥታት ዓምደ ጽዮንና ይስሐቅ ብቻውን ከእስላሞች ጋራ ጦርነት ገጠመ። ዘርአ ያዕቆብ በመጀመሪያ ያካሄደው ጦርነት በሀዲያ አውራጃ በራሱ ግዛት ነበረ። በዘርአ ያዕቆብ የዚሁ አውራጃ ገዥ ሆኖ የተሾመው የአንደኛዋ ሚስቱ ወንድም የሆነው ግሂነ፣ የተባለው ከአዳል ሱልጣን ጋራ በመመሳጠር ሽፍቶ፣ ነፃ መንግሥት አወጀ፣ ሌሎች አውራጃዎችን ወደ እሱ ለመሳብ በምስጢር ግንኙነት አደርጎ ነበር። ዘርአ ያዕቆብ እቅዱ ወደ ተግባር እስከሚፈጽመው ድረስ አልጠበቀውም፣ ከሥልጣኑ አውርዶ ወረረው። ግሂኮ ወደ አዳል ሸሽቶ ሰመሄድ ወደ ምሽግ ቦታ ሰመግባት ሲሞክር የዘርአ ያዕቆብ ወታደሮች ሰሰደረሰብት ገደሉት፣ አንገቱን፣ እግሮቹን፣ እጆቹን ተቆራርጠው ወደ ዘርአ ያዕቆብ ተወሰደው በንጉሡ ቤት ደጃፍ ተሰቀሱ። ከሁሉ የላቀ ድል እጼ ዘርአ ያዕቆብ የተቀዳጀው ለአዳል ሱልጣን በጀግል አልዲን ሰልጣን የያዘው የሰይዲ አልዲን ሲላ ልጅ በባድላይ ነበረ። በ1445 ዓ.ም. ባድላይ የዳዋሮን አውራጃ ወር ነበረ። ዘርአ ያዕቆብ በአነስተኛ ወታደሮች ቢገጥመውም የገጠመው በወኔ ሰሰነበረ ድሉ የእሱ በመሆኑ በመጀመሪያ መስመር ሆኖ ይዋጋ የነበረ ባድላይ ከእጼ ዘረአ ያዕቆብ ጋራ ተወግቶ ወደቀና ሞተ። አስክሬኑ ተቆራርጦ ሰመላው የመንግሥቱ ግዛት ተከፋፍሏል። የባድላይ ወንድም በመሸሽ ላይ እንዳለ አሳድዶ አዋሽ ወንዝ ሰመሻገር በሚከርበት ጊዜ ተገደለ። እጼ ዘርአ ያዕቆብ ሁለት ድሉችን በአጭር ጊዜ ቢናገፍም የእስላሞች አደጋነት በሙሉ እንዳልተወገደ ሰለተረዳና አሳሳቢ ሰለሆነበት በሁለት መንገድ ዘላቂ መፍትሔ ብሎ የገመታቸው እርምጃዎች ወሰደ። የመጀመሪያ የክርስቲያኖች እንድነትና የእምነታቸው ግጠናከሪያ 2ኛ. ከዓለም ክርስቲያን መንግሥት እርዳታ መጠየቅ ነበረ። እጼ ዘርአ ያዕቆብ በሁለቱ

መንገዶች ተጠቅመዋል። የክርስትና ሃይማኖት ለማስፋፋት በውድም በግስገደድም ሞክሯል። መገረሳዊ መጽሐፎች ከውጭ ቋንቋ ተተርጉመው እንዲሰጡ አሰገድዷል። የግርያም ድንግል በዓላቶችና፣ ያምን ወዙተ ወሰኗል። አንዳንድ የውጪ ሀገር ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ በመግቢያቸው በርም ኩቶሊክ ቤተክርስቲያንና በኢትዮጵያ እርቶዳክስ ቤተክርስቲያን ያለው ልዩነት የግዋዋያ እርእሰት ሆኖ ነበረ። አጼ ዘርአ ያዕቆብ ከክርስቲያን መንግሥታት እርዳታ ለማግኘት ለነበረው ምኞት ግን ውጤት አልባና ዓላማውን የሳተ ነበረ ለማለት ይቻላል። አጼ ዘርአ ያዕቆብ የኤውሮጳ መንግሥታትን ማንነት ለይቶ ካለማወቅ የተነሳ በ1450 ዓ.ም. ለናፖሊ ንጉሥ መልእክት ልከዋል። የናፖሊ መንግሥት፣ እንኳን ከኤውሮጳ መንግሥታት ሊወዳደር ቀርቶ፣ በኢጣሊያ ከነበሩ እነስተኛ መንግሥታትም ከሁሉም ኋላ ቀር የነበሩ መንግሥታት የሆነ ነበረ። ሰለዚህ ምንም ዓይነት ጠቃሚ እርዳታ ለኢትዮጵያ መስጠት የሚችል አልነበረ። የናፖሊ መንግሥት በሰዓሊ ሞያ ከም የላከው ብራንካሊዮ የሚባለው ግለሰብ ቀድሞ ቄስ የነበረ ሰለሆነ ጊዜው ያሳሰፈው የሃይማኖት ክርክር በመቀስቀስ ብቻ ነበረ። እጼ ዘርአ ያዕቆብ ስዝነኛው የቢዛንታይን ክርስቲያን መንግሥት እርዳታ እንዳይጠይቅ በዚሁ ጊዜ በቱርክ ኦቶማን መንግሥት ተሸንፎ በ1454 ዓ.ም. ዋና ከተማው ቆስጣንቲኖፕል የተማረከበት ወቅት፣ ሕልውናውም ያበቃበት ጊዜ ነበረ። ሲላ እጼ ዘርአ ያዕቆብ በትልቅ ጉጉት እርዳታ እንዲያደርግለት ሊጠባቀቅ የነበረው ከሮማ ጳጳስ ነበረ። ወቅቱ በቱርክ ኦቶማን አማካኝነት የእስልምና ሐይማኖትና መንግሥታት በኤውሮጳም በእፍሪካም ጥንካሬ ያገኙበት ነበረ። በዚሁ የተነሳ የሮማ ጳጳስ የመላው ዓለም ክርስቲያኖች ለማስተባበር በ1440 ዓ.ም. ማሊያን ሀገር በፈረንሲ ጉባዔ ጠርቶ ነበረ። ኢትዮጵያም የጉበኔ ቤተክርስቲያንም መልእክተኞቻቸው ወደዚህ ጉባዔ ልከው ነበር። የጉበኔ መልእክተኞች የተመሩት እንድሪያ በተባለው የቅዱስ አንቶንዮስ ገዳም አለቃ ነበረ። የኢትዮጵያ መልእክተኞች ቀሳውስት የተላኩት ከአባ ኔቆዲሞስ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት አለቃ ወክሱ ነበረ። የሮማ ጳጳስ ዓላማ የዓለም ክርስቲያን በሙሉ የካቶሊክ እምነት ተቀብሎው በእሱ ስር እንዲሆኑ ነበረ። ለክርስቲያኖች ትብብር እንቅፋት የሆነውም ይህ ቅድመ ሁኔታ መግባት ሰሰነበረ ነው። ኢትዮጵያም ከዚህ ቀደም እርዳታ ከክርስቲያን መንግሥታት ያላገኘችው በዚሁ ቅድመ ሁኔታ ምክንያት ነበር። የጉበጽ መልእክተኛ ለጉባኤው ያደረገው ንግግር የሮማ ጳጳሳት በግወደሰ ነበረ። ኩተናገረውም ውሰጥ የሮማን ጳጳስ በግስመልከት "በዚሁ ዓለም እርሶም እግዚአብሔር ነዎት እርሰም የክርስትና እንደራሲ ነዎት፣ እርሰም የዓለም ኢቀፍ ቤተክርስቲያን አለቃ ነዎት ለእርሰም የመንግሥተ ሰማያት በር የመክፈት፣ የመዝጋት ቁልፍ ተሰጥቶታል ወዘተ... የሚል ይገኝበታል። የጉበኔ መልእክተኛ ንግግር ኩተሰማ ሁለት ቀን በኋላ የኢትዮጵያ መልእክተኞች ፈረንሲ ገቡ፣ ከሁለቱ መልእክተኞች አንዱ ባደረገው ንግግር የጉበኔ መልእክተኛ ካደረገው ንግግር ተመሳሳይ ቢሆንም ለየት የሚያደርገው ሀገሩ ኢትዮጵያ በሚመለከት ያሰማው የሚያወድሱ ቃላቶች ነበሩ።

ወደ ሮማ ጳጳስ ፈቱን አተኩሮ ሲናገር "ከእርሰም የተለዩ ሁሉ ወድቀዋል፣ ከርማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ኩተለዩ ቤተክርስቲያኖች ሁሉ የእኛ ጠንካራና ኃይለኛ ነፃ ሆና ናራለች፣ ምክንያቱም ሌሎች ቤተክርስቲያኖች ከእርሰም የተነጠሉ በክፋት በፍላጎታቸው ነው፣ እኛ ግን ተለይተን የኖርነው በመገደድ፣ ለፍተት የተነሳ፣ በመንጌ አደገኛነት ነው፣ ከእርሰም በፊት የነበሩ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሊቀጳጳሳት ቸልተኝነት ነው፣

የኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት በዚህ ዓለም ከሮማዊት ቤተክርስቲያን ጋራ ከመዋሐድ ሌላ ምርጫ የለውም" ወዘተ... የሚል ይገኝበታል።

አጼ ዘርአ ያዕቆብ ንግሱ ወደ ደቡብ አስፋፍቶ ሰፊነበረ፣ የኢትዮጵያ መልእክተኛ በኩራት አፉን ሞልቶ ሲናገር "የኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት አንድ መቶ ነገሥታት እንደሚያዝዝ ለጉባኤተኞች ተናግሯል። የፈረንሲ የጉባኤ በተሳካ ሁኔታ የተፈጸመ መስሎ ቢታይም መልእክተኞቹ ተመልሰው ወደ ኢያሩሳሌምና ወደ ካይሮ ሲገቡ የጉባኤው ውሳኔ ሳይፈርም በቀረ ብቸኛ በኢፈሶን ቤተክርስቲያን መልእክተኛ የሚመራ የጉባዔውን ውሳኔ የሚቃወም ንትናቴ ተደርጎባቸው ሁሉም የምሥራቅ አበያተክርስቲያን የሚያጠቃልል ፀረ ሮማ ቤተክርስቲያን እንቅስቃሴ ተነስቶ ነበር። ስለዚህ የፈረንሲ ጉባዔ ለሮማ ጳጳስ ክብሯ ከሰረት ነበር የሆነበት። በአጼ ዓምደ ጽዮን የአጼ ይስሐቅና በአጼ ዘርአ ያዕቆብ ጊዜ በቀይ ባሕር ወደቦች በክርስቲያን ስም ኩቋርስ አቶማን ጋራ ትፋለም የነበረችው ከፖርቱጋል መንግሥት ጋራ ኢትዮጵያ ግንኙነት እድርዋ ብትሆን ኖሮ በይማም ግራኝ ጊዜ እርስ በእርስ ጦርነትና የሀገሪቱ አበያተክርስቲያናት የቅርሳቅርሷ የመጻሕፍቶቿና የታሪኳ ውድመት አይደርስባትም ነበር፣ የአሮሞ ታሪካዊ ማሰፋፋት ከስተት አያጋጥማትም ነበረ። ከአጼ ዓምደ ጽዮን ጀምሮ ክባሀር ወደቦች በቀር የመሀለ ሐገር የአክሱም መንግሥት ዘመን ወደነበራት ሰፋት ተመልሶ ነበረ።

በአፈ ታሪክ አባባል ኢትዮጵያ 14 መንግሥታት ነበሯት። ከነዚህም ውስጥም 4 መንግሥታት የወርቅ ዘውድ የሚጭኑ ነበረ እነሱም 1. ትግራይ 2. አማራ /ጎንደር/ 3. ላስታ 4. ሸዋ /ጎጃም ናቸው። ሌሎች 4 ነገሥታት የብር ዘውድ የሚጭኑ እንደዚሁም ነገሥታት የነሀስ ዘውድ የሚጭኑ ስማቸው የማይታወቅ ነበረ።

አልቤርቶ [1]ፖሌራ እንደጠቀሰው በ1603 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የነበረው ሚሲዮናዊ አባ ፓየዝ በጻተፈው መሠረት በማድረግ በጥንት ጊዜ ኢትዮጵያ 35 መንግሥታትና 18 ራስ ገዝ አስተዳደሮች ነበሯት።

እንደዚሁም ፖሌራ በ1629 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የነበረ ፖርቱጋላዊ፣ ሚሲዮናዊ ፣ ዳሚዳ የጻፈው መሠረት በማድረግ በጥንት ጊዜ ኢትዮጵያ 36 መንግሥታትና 17 የራስ ገዝ አስተደደር ያላቸው ግዛቶች ነበራት ካለ በኋላ! ባገኘው ሌሎች ዜናዎች ግን የኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት 60 መንግሥታት ከርስቲያን ያልሆኑ እንደዚሁም ሌሎች ቁጥራቸው ዘውል የማይታወቅ ገባር መንግሥታት ያዝዝ እንደነበረ ገልጧል።

በተጨማሪም ፖሌራና ኮንቲ ሮሲኒ ገጽ 15 እንደጠቀሱት ከ1624 ዓ.ም. እስከ 1704 ዓ.ም. የኖረው ጀርመናዊ ሱዶልፍ የኢትዮጵያ ቋንቋና ታሪክ አዋቂ በጻፈው መሠረት በማድረግ በተሰያዩ ጸሐፊዎች የሚነገረው የመንግሥታት ቁጥር የተለያየ ነው ብሎ ካሰጠቀቀ በኋላ ኢትዮጵያ 30 መንግሥታት ነበሯት በማለት ስማቸውን ይጠቅሳል። የመንግሥታቱ ስም በተመለከተ አብዛኛው አሁን ቢኖርም ያንዳንዶቹ ስም ግን አሁን የለም። ፓየዝ ባወጣው የ35 መንግሥታት ስም ዝርዝር እንደሚከተው ያቀርበዋል 1. ትግራይ ወሰኑ ከየት ወዲት መሆኑን ባያገልፅም በዛሬዋ ደቡብ ትግራይ ከፍል አበርጋለ፣ ሰሎዋ፣ ወገራት፣ እንዳርታ፣ እንደ አካል ነበረች 2. ደንከል /አፋር/ 3. አንትት አብዛኛው የነሬዋ ወሎ 4. ዶባ ዘወሰ ትግራይና አፋር መሐል የነበሩ ሕዝቦች 5. አውሳ ደቡብ አፋር 6. አግራ ምናልባት ደቡብ ጎንደር 7. አላታ 8. ሸዋ ከየት ወዴት እንደሆነ

(1) Alberto Pollera : Lo Stato Etiopico e la sua Chiesa

አይታወቅም 9. ይፋት 10. ጎዳም 11. ጋንች 12 ዳዋሮ/ ምናለባት የዛሬዋ ጨርጨር 13. ፋጢጋር ከይፋት በስተሰሜን የዛሬዋ አርነባ 14. እዩዩ ከዝዋይ ሀይቅ በስተምሥራቅ 15. ባሌ ከዛሬዋ አርሲ እስከ ሶማልያና ሕንድ ውቅያኖስ 16. ሀዲያ 17. አላባ /ቆቃ አካባቢ 18. አከሰለን 19. ቤቶ ቆቃ አካባቢ 20. ቤቴሪምራ 21. ጉራጌ በጉራጌ ሸም የሚታዘዙ 22. ኮይራ /ከጁባ ወንዝ እስከ ስተፋኒያ ሀይቅ 23. በዙማ ከዝዋይ በስተደቡብ 24. ሱፍ ጋሞ የዝዋይ በስተደቡብ በአጠያቃ ሐይቅ እስከ ቆይራ ባሕር ጋ 25 ባሕር ጋ 26. ከንባታ 27. ቦሸ (ጅማ) 28. ጉመር /ከፋጢጋር በስተደቡብ 29. ጃንጃሮ 30 እናርያ (ሲሙ) 31. ኩንታ 32 ዳሞት 33. ጎጃም 34. ቤጌምድር 35. ደንብያ።

በዚህ ስም ዝርዝር እንደምንመለከተው የዛሬዋ ጎንደር ክፍለ ሀገር ለቤጌምድር ደምቢያ አማራ መንግሥታትና በስሜን ፀለምቲ ቦራ ፀገለ ወልቃይት ማዘጋራ ራስ ገዝ አስተዳደሮች ተከፋፍላ ነበረች። ላስታ በሁለም ስም ዝርዝር አይጎኝም። ወለጋ የቢላሞ መንግሥት ተብላ ትጠራ ነበረ። ከዲዲሳ ወንዝ እስከ አባይ ወንዝ ግን ጋፋት ተብሎ ይጠራ ነበረ። ይህ ሰፋ የኢትዮጵያ ግዛት በታሪክ በመልክአ ምድር አተማመጥ በዘር አንድ የሆኑ ሕዝቦች በአንድ ማእከላዊ መንግሥት ይተዳደሩባት የነበሩ ኢትዮጵያ በእሰልምና እምነት ተከታዮች እርስ በእርስ ጦርነት ባትወጠር በሌላ አርእሰት እንደሚታየው የአሮሞ የማሰፋፋት ከስተት ባያጋጥማት በዜንያ በኩልም እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ከዚያም በላም ለመድረስ በአካባቢው የተደራጀ ተቃዋሚ ኃይል ሰላልነበረ እንቅፋት አያጋጥማትም ነበረ።

ይህ በማድረጉም በአፍሪካ ስልጣኔ ለማሰፋፋት የነበራት ታሪካዊ ተልእኮ መወጣቷ የሚያመሰክት ስለሆነ የሚያስመሰግናት ነበረ። የአውሮጳ ታሪክ አሐፊዎች ኢትዮጵያን የሚወቅሷት ይህንን ባለማድረጓ ነው። የዛሬዎቹ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ግን የደቡብ ምስራቅና ምዕራብ ኢትዮጵያ ዳግማዊ ምኒልክ በዛሬ አንድ መቶ ዓመት በወረራ እንደያዛቸው ለማስመሰል እየሞከሩ ይታያሉ። ከንያ ውስጥ የሚኖሩ የአሮሞ ዝርያዎች የሆኑ ከኢትዮጵያ ተንጥለው ከከንያ ጋራ የተቀላቀሉት ኢትዮጵያ በአሮሞች ምክንያት የጋጠማት የመንግሥቷ ድከመት ነው።

በንግሥት ሳባ ጊዜ ኢትዮጵያ የባሕር ጠረፍ የት ድረስ ይደርስ እንደነበረ በማመልከት [1] ሻለቃ ሩፊሎ ፒሪኒ እንደሚመለከተው ይገልጸዋል "የባሕር ነጋሽ ሥልጣን ከበረኒሰ የባሕር ወሰመጥ 24° ዲግሪ በስተሰሜን እስከ የእማኑ ሀገር ሕንድ ውቅያኖስ ከዚያም እስከ ሶፎላ 20° ዲግሪ ደቡብ ላቲቲዩድ ይደርስ ነበረ። በዚሁ ቦታ የብዙ ሳይንቲስቶች እምነትም ከንአሱ ውስጥም በመጨረሻ ጊዜ የብራቲሽ ሙዝየም ሰራ አስኪያጅ የነበረ ሚቼ ሚስተር ቤንት ባለበት፣ በመጸሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው አፌር የሚባለው ምስጢራዊ ቦታ ንግሥተ ሳባ ወደ ንጉሥ ሰለሞን ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ እንድትችል መርከቦች የተሰሩበት መሆኑን ገምቷል"። ስለዚህ ኢትዮጵያውያን ነገሥታት እነ አጼ ይስሐቅ ወደ ደቡብ ያመሩበት የነበረ ሀገር የቅድመ አያቶቻቸው ይዞታ የነበረ መሆኑን በማስታወስ የሆናል።

በነ አጼ ይስሐቅና አጼ ዘርአ ያዕቆብ ዘመን መንግሥት የኢትዮጵያ ሰፋት ሱካ ደይ ሳቤሲ[2] እንደሚከተለው ይገልፃል።

(1) Perini Mereh-Melash (Al di qua del Mareb)

(2) Luca Dei Sabellil VII p. 15-17

1. ኢትዮጵያ በሰሜን ወሰኗ እስከ ምፅዋ ይደርስ ነበር። ሐማሴን፣ ሰራዬ፣ አክሰጉላይ አውራጃዎች እስከ ቀይ ባሕር ድረስ የባሕር ኃጋሽ መንግሥት አካል ነበሩ። ዋና ከተማ ድባሩዋ ነበረች። ሳሄልና ባርካ በቁጥጥሩ ስር ነበሩ።

2. ትግራይ ዋና ከተማ አክሱም ሆና በትግራይ መኩንን የሚታዘዝ ነበረ

3. ሰሜን አፋርና ደቡብ አፋር (አዋሳ)

4. ዳዋሮ (ዉርዉር)

5. ባሌ ከዛሬዋ አርሲ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ የሚደርስ በዚህ በኩል የአርሞ ክስተት ባያጋጥም ኖሮ የክርስቲያኖች ፖለቲካዊ መሰፋፋት መቋቋም የሚችል ተቃዋሚ ኃይል አልነበረም

6. ፋጢጋር ከባሌ በስተምሥራቅ ከመካከለኛ አዋሽ ወንዝ እስከ ዋቢ ወንዝ ምንጭ የሚያጠቃልል

7. አይ ወይንም ወድ ይባል የነበረ ከፍለሀገር ግእከሉ በዝዋይ ሐይቅ አካባቢ ነበረ። በዚህ አውራጃ በዛሬ አጠራር ስልጤ የተባሉ ቋንቋቸው ከሐረሪ የሚቀራረብ ጉራጌዎች ይኖራሉ፣ አመጣጣቸውም ከጥንታዊው አክሱም መንግሥት ነው።

8. ከወደ በስተደቡብ ከዝዋይ ሐይቅ እስከ አባያ ሐይቅ ሱፍጋኖና በዛሞ የተባሉ ሁለት ትናንሽ መንግሥታት ነበሩ

9. በስተደቡብ ኮይራ ነበረ ለመንግሥት ግብር የሚከፍለው ለወታደሮች የሚያገለግሉ ፈረሶች በማቅረብ ነበረ። የሚገኘውም ከላይኛው ጁባና ከአባያ ባሕር ሐይግ መሐል ነበረ እስከ አስቴፋኒያ ሀይቅ ከንያን የሚያጠቃልል ነበረ

10. ወላሞና ጋሞ በንጉሥ ይስሐቅ ዘመን ጊዜ የተቀላቀሉ ከአባያ ሐይቅ በስተምዕራብ የሚገኙ ናቸው። እነዚህ ግዛቶች ሁሉ የታወቀ ተቃዋሚ የተደራጀ ኃይል ስላልነበሩ አሮሞዎች ከኢትዮጵያ ባየገነጥሏቸው ወሰናቸው እስከ ተፈለገ ሩቅ ሊዘልቅና ሊሰፋፋ ይችል ነበር።

11. በስተምዕራቡ በአጼ ይስሐቅ ወደ ግእከላዊ መንግሥት የተቀላቀሉ ትናንሽ መንሥታት ነበሩ ከነሱ ውስጥም እናሪያ /ሊሙ/ ቦሻ (ጅማ አባጅፋር) ወዘተ... ይገኙባቸዋል

12. ሰታችኛው አሞ ሰፈ የጃንጃሮ መንግሥት ነበረ

13. በስተሰሜን ከንባታ ነበረ። ከአሞ በስተግራ እስከ አቢያታ ሀይቅ

14. ከከንባታ በስተሰሜን ከላይኛው አዋሽ እስከ አሞ በጉራጌ ሹም የሚታዘዙ 1000 በሬዎች ግብር ለመንግሥት የሚከፍል የጉራጌ መንግሥት ነበረ

15. ከጉራጌ እዋሳኝ የሀዲያ ሱልጣን አገዛዝ ነበር

16. ከሐዲያ እስከ ሸዋ አሰግስ ቁጋር የሚባሉ ትናንሽ መንግሥታት ነበሩ

17. ኪጋንዝ በስተምዕራብ ትልቁ ዳሞት ነበረ

18. በስተምዕራብ በዛሬዋ ወለጋ ቢዛሞ የሚባል መንግሥት ነበረ

19. ከዲዲሳ ወንዝ እስከ አባይ ወንዝ ጋፋት ነበረ

20. አባይ ተሻግሮ ጎጃም ይገኛል

21. ከጣና ሐይቅ እስከ ተከዜ በጌምድር

22. በዛሬዋ ጎንደር ዙሪያ ደምብያ ነበረ

23. ወደ ሰሜን ፀሰምቲ፣ ዊሊ፣ ወልቃይት፣ ሰሜን፣ ግዘጋዘ፣ የተባሉ ከጥንት ጀምሮ አገውና ፈላሻ የሚኖርባቸው ናቸው።

24. ኩተከዜ ወንዝ በስተሰሜን ስሰዋና አበርጋሌ ይገኛሉ

25. ወገራትና እንደርታ አውራጃዎች ከጥንት ጀምሮ ራሳቸውን የቻሉ ራስ ገዝ አስተዳደር መብት የተሰጣቸው ነበሩ

26. ከንደርታ በስተደቡብ ላስታ

27. ከላስታ በስተምሥራቅ እንጎት የዛሬዋ ወሎ አብዛኛውን የሚያቃልል

ከሞላ ጎደል የኢትዮጵያ አስተዳደር አከፋፈል ካርታ ይሄንን የሚመስል ሲሆን ስፋቱ ከዛሬዪቱ ኢትዮጵያ በጣም የሚበልጥ እንደነበረ ብዙ ግስረጃ ባይኖርም የኢትዮጵያ ግዛት ከንያም ያጠቃልል እንደነበረ የሚጠቁም 200 ዓመት ከአጼ ይስሐቅ ዘመነ መንግሥት በኋላ በአጼ ፋሲሊደስ ዘመነ መንግሥት በኋላ የ'ሞምባሳ Mombassa ንጉሥ በኢትዮጵያ መንግሥት የሚታዘዝ መሆኑን ለካ ደይ ሳበሊ[1] ገልፀዋል። እንደፈረንጆች ቃል አነጋገር የአሮሞ ፊኖሚኖን /Oromo phenomenon) በኢትዮጵያ ታሪክ ባያጋጥማቸው ኖሮ ጀኖች አባቶቻችን በእነ አጼ ይስሐቅና አጼ ዘርአ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ግዛት እንደ አክሱማውያን እስከ ሶርላ ባይደርስም ከንያንና ደቡብ ሶማሊያ የሚያጠቃልል እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ዘልቆ እንደነበረ፣ ይሽውም ለ200 ዓመት ቀጥሎ እንደነበረ ፈክላይ የተጠቀሰው የታሪክ ግስረጃ ያመስክታል። የአሮሞ ፊኖሚናን ያልኩበት ምክንያት የአሮሞ ወደ መሀል ሀገር መስፋፋት የውጭ መረራ አይባልም ወይንም በእንድ ሀገር ውስጥ በሁለት ነሳዎች ወይም ከፍለ ሀገሮች የተደረገው እርስ በእርስ ጦርነት አይባልም። ከላይ ከእንደኛ እስከ 27ኛ ተራ ቁጥር የጠቀስኳቸው በኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦችና ከፍላተ ሀገሮች ካርታ የአሮሞ ስም አልነበረም። የአሮሞ ክስተት የመጣው ኩተጠቀሰው ዓ.ም. በኋላ ነው። አሁን የሚታየው የአሮሞ አሰፋፈር ከምሥራቅ ኢትዮጵያ ሐረርጌ እስከ ምዕራብ ኢሉባቡር ሌሎች ሕዝቦች ስፍረውበት የነበሩ መሬት መሆኑን እንረዳለን። ይሽውም የአሮሞ ክስተት በኢትዮጵያ ልዩ ያደርገዋል። ዳግማዊ ምኒለክ የሚወክለው የአማርኛ ቋንቋ በደቡብ በምዕራብ ኢትዮጵያ ወረራ በመፈጸም ሌሎች ሕዝቦች በቋንቋቸውና በባሕላቸው እንዳይጠቀሙ አድርገዋል የሚል ወቀሳ በአሁኑ ጊዜ ሲሰነዘር ይሰማል። ከዳግማዊ ምኒለክ ጀምሮ ለአስተዳደር እንዲያመች የመንግሥት ቋንቋ አማርኛ ስለነበረ በአገሪቷ አስተዳደር በሚመለከት በተዘረጋው በጣም ዝቅተኛ የአስተዳደር መዋቅር የሌሎች ሕዝቦች ቋንቋዎች ሳይነኩ ከጥንት ጀምሮ እንደነበረ ሁሉ በአማርኛ ቋንቋ መጠቀም ያስተዳደር ቋንቋ ሆኖ ቆየቶ ነበር።

የአማርኛ ቋንቋን ስማስፋፋት ምክንያት የሆነው ግን በደበልቱ ከኢጣሊያ ወረራ በኋላ በኃይለሥላሴ ጊዜ ትምህርት ቤቶች ስስተስፋፋ ይሆናል። የሌሎች ሕዝቦች ቋንቋና ባሕል ግጥፋት ብቻ ሳይሆን የሕልውናቸውም ግጥፋት የተፈጸመው በአርሞች የጋዳ አስተዳደር ዘዲ ነው። የአሮሞ ቋንቋ በአጭር ጊዜ በመላው ኢትዮጵያ መስፋፋት ሁኔታ በቂ ግስረጃ ባይኖርም ምናልባት ቀደም ብለው ስፍርበት የነበረውን ሕዝብ በሙሉ እየለጁ ግስሰቱት ላይሆን ይችላል። ነገር ግን አንድ ሕዝብ የሌላ ሕዝብ ቋንቋና ባሕል በአጭር ጊዜ ውስጥ በስላም ስለግይቀበል በከፊል ነዋሪ

(1) Luca Dei Sabelli ibd V 2 p 384

ሕዝቡን እየጨረሱ ቋንቋውንና ባሕሉን የመቀየር ሂደት እንደተካሄደ አያጣራጥርም። በዚሁ መሠረት አሁን የእርሞ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ሕዝቦች የአንድ ጎሳ አባል ሳይሆኑ የብዙ ጎሳዎች ቅልቅል መሆናቸውን ለመረዳት አያስቸግርም። ሰለዚህ ከአማርኛ የበለጠ የእርሞ ቋንቋ የግስፋፋት ዕድል አግኝቷል ለግለት ይቻላል። ብዙዎቹ አሁን በእርምኛ ቋንቋ የሚጠቀሙ ሕዝቦች የድሮ ቋንቋቸው አማርኛ ነበር፣ ወይንም የሲዳማ ቋንቋ ነበረ ሌሎችም በደቡብ ምሥራቅና ምዕራብ የሚገኙ የእርሞኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች አሁን ልናውቃቸው የማንችል የተሰያዩ ቋንቋዎች እንደነበሯቸው መገመት አያዳግትም። በሰሜን ምሥራቅ ኢትዮጵያም እነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች የእርሞኛ ቋንቋ ተቀብለው ሰሰነበረ አሁንም ይጠቀሙበታል።

እጼ ምኒልክ 450 ዓመት ከነ እጼ ይሰሐቅ ዘመነ መንግሥት በኋላ ኢትዮጵያ የቀድሞ ሞዟ በከፊል እንድታገኝ በማድረጉ የሚያነጋግር አይደለም። ወገን ከወገኑ እንዲቀላቀል በማድረጉ የሚደነቅ ነገር አንዳንድ ወገኖች እንደሚሉት ወራሪ አያሰኝም። ሐቀኛ ኢትዮጵውያን ምኒልክን የሚወቅሱት እንደ እጼ ይሰሐቅ ዘይላን፣ በርበራን፣ ሞቃድሾን ችላ በማለት አለመያዙ ነው። በተሰይም ኤርትራ ለኢጣሊያ ገፀ ባረከት መሰጠቱ በታሪክ ሲያሰወቅሰው የሚኖር ሰሰሆነ ሀገሩን የሸጠ ከዳተኛ ብቸኛ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ በሚል አጠራር ሲያሰታውሱት ይኖራሉ።

5. <u>ንግሥት እሌኒ</u>

የኢትዮጵያ መንግሥታት እሰላሞችን ለማጥፋት በኃይል የማይቻል መሆኑን እየተረዱ ሰለመጡ የክርስቲያን ግብጻችና ኩዶሲኮች ድጋፍ መፈለግ ጀመሩ። ከዓረብ መንግሥታትም ቢቻል ወዳጅነት መፍጠር ካልተቻለም ገለልተኛ እጭም እንዲይዙ ማድረግ ተሞክረዋል። የዓረብ መሪዎችም በሰላማዊ መንገድ እብረው በሰላም ለመኖር እንዲችሱ ተሞክረዋል። ፖሊቲካ ቀሰቃሽ ንግሥት እሌኒ ነበረች። እጼ ዘርአ ያዕቆብም ቢሆን ከእሰላም ጋራ በሰላም ለመኖር በመፈለግ ከሀዲያ አንድ ሚሰት አግብቶ ነበር። ንግሥት እሌኒም ራሷ በልጅነቷ እሰላም ነበረች። የእጼ ዘርአ ያዕቆብ ልጅ እጼ በእደ ማርያም ሁሰት የእሰላም ሚሰቶች ነበሩት ንግሥት እሌኒና ንግሥት ሮማነ ወርቅ። እነሱም ከአዳል ሱልጣኖች የሚወሰዱ ከታወቁት የየመንና የሀድራሞት የመንግሥታት ዘሮች ይዛመዱ የነበሩ ናቸው። በተሰይ ንግሥት እሌኒ በዘርአ ያዕቆብ የተተኩ አራት የኢትዮጵያ ነገሥታት ዘመነ መንግሥት በውጭ ጉዳይ እመራር ተሰሚነት አግኝታ ነበር። ወደ ዓረብ ሀገር የሚመላለሱ እርሜን፣ ዓረብ፣ ሕንድ፣ ግሪክ፣ ነጋዲዎች መረጃ እንዲያቀብሏት ታደርግ ነበረ። 500 ሰዎች አባል የነበረው አንድ የኢትዮጵያ መልእክተኛ ቡድን ወደ ግብፅ ሱልጣን ተልኮ ነበረ። በታላቅ ሥነ ሥርዓትና ሰልፍ በካይሮ በታየበት ጊዜ ተቃውሞ ከሕዝቡ ሰሰተቀሰቀሰበት በባሰሰልጣኖች እርዳታ ብቻ ከአደጋ ሲያመልጥ ችሏል። ንግሥት እሌኒ ክርስቲያን ብትሆንም ከአዳል ቤተሰቦቿ ግንኙነት አሳቋረጠችም ነበር። ጥረቱንም ከንቱ አልሆነም። የአዳል ሱልጣን የነበረው መሐመድ ጦርነት ከማድረግ ይልቅ በሰላም አብሮ መኖር ፈላጊ ሆኖ ነበረ። በጋብቻ በመተሳሰርም በአንድ ሆኖ በሰላም መኖር ደህና ውጤት ያስገኛ መሰሎት ነበር፣ ነገር ግን የሱልጣኖች ስልጣን ስም ብቻ ሆኖ ራሳቸው ስልጣን የጨበጡ እግር የተባሱ ከክርስቲያን ጋራ በሰላም መኖር የማይዋጥላቸው ሰዎች ተፈጥረው ነበረ። የሰላም ጥረቱም በይበልጥ የከሸፈው በኢውሮጳ በክርስቲያኖችና በዓረቦች እሰላሞች መካከል ይደረግ የነበረው ጦርነት ተፋፍሞ በነበረበት ወቅት ዘሀገራችንም ስስተዛመተ ነበር።

ወቅቱ ኢሮውጳ ሞዟ ወደ ሌላ የዓለም ክፍሎች ግስፋፋት የጀመረችበት ነበረ። ከኤውሮጳውያን የግንባር ቀደም በመሳው የኤውሮጳ ስም የፖርቱጋል ዓላግ የአፍሪካ የባሕር ጠረፍ ዙሪያ ለመቃኘት ነበረ። የርግ ጳጳስ የፊሬንኒ ጉብኤ የጠራ ዓላማውን ግለመደገፍ ግንኛውም የአፍሪካ ወደብ በፖርቱጋል የጦር መርከቦች ከተነበን የፖርቱጋል እንዲሆን ስለፈቀዱ ፖርቱጋሎች ጥረታቸውን በመቀጠል ምዕራብ አፍሪካን ዞረው ወደ ምሥራቅ አፍሪካ ደረሱ። ከደቡብ ፖርቱጋሎች ቀይ ባሕር ሲደርሱ ቱርኮችም ከሰሜን ሞዟቸውን እያሰፋፋ ቀይ ባሕር ደርሰው ነበር። በ1517 ዓ.ም. ቱርኮች በድል አድራጊነት ካይሮን ያዙ። በዚሁ ጊዜም ሱዋኪምና ምጽዋን ተቆጣጠሩ። በቀይ ባሕር ፖርቱጋሎችና ቱርኮች በጭካኔ ይፋጁ ነበረ። በኢትዮጵያም በአዳል መስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ጦርነት እንዲቀሰቀስ አስተዋጻ ነበረው።

6. <u>አፄ በእደማርያም</u>

አፄ በእደማርያም የክርስትና ሃይማኖትን ለማሰፋፋት በመጀመርያ ጦርነት ያካሂደው በሰሜን፣ በጸሰምቱ፣ የነበሩ ፈላጮችና በዶባ ነበረ። በስተምሥራቅ የአዳል ሱልጣን መሀመድ ወደ በእደማርያም መልእክተኛ ልኮ ግብር እየከፈለ የበላይነት እምኖ በሰላም ሰመኖር ስለተስማማ ጊዜያዊ ሰላም ሰፍኖ ነበር። የአዳል ሱልጣን መሐመድ በ1470 ዓ.ም. ሲሞት ልጁ ኢብራሂም ሲተካ ሰልጣኑ በኢ.ሚሮች እጭ ሆኖ ነበር። ሱልጣኑ ሰሰም ብቻ ተቀምጦ ነበር። በ1474 ዓ.ም. ከአዳል ጋራ በተደረጉ ጦርነቶች ክርስቲያኖች ለመጀመሪያ ጊዜ ሽንፈት ገጠማቸው በእደማርያም ከሞሞቱ በፊት 1478 ዓ.ም. ለግብፁ ሱልጣን በሰላም ለመኖር ውል ስማድረግና ወደ ኢየሩሳሌም ለመሳለም የሚሄዱ ለኢትዮጵያውያን ምእመናን እርዳታ እንዲደረግሳቸው ለመጠየቅ መልእክተኛ ልኮ ነበር። መልእክተኞቹ ከግብፅ ቤተክርስቲያን ወደ ፈልሰጤም አምርተው ኢየሩሳሌም ሲደርሱ የኢትዮጵያ መነኮሳት ወደ ሮማ እንዲሄዱ ገፋፋቸው። በዚሁ መሠረት መልእክተኞች ወደ ቆስጠንጥኒያ በመሄድ ፋንታ ወደ ሮም አመሩ። ኖቪምንበር 1481 ዓ.ም. የሮማ ሊቀ ጳጳስ ሲክስቶስ4ኛ. በታላቅ ሥነ ሥርዓት ተቀበሏቸው። 1ኛ. አባ ፍራንችስኮ ሳጋራ 2ኛ. አባ ጆቫኒ ዲ ካላብሪያ 3ኛ. አስተርጓሚ ሆኖ ከኢየሩሳሌም አብሮ የመጣ አባ ጆቫኒ ባቲስታ ዲ ሊሞላ የሚባሉ ሚሲዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ ተላኩ። አባ ሳጋራ ካይሮ ሲደርሱ ሞተ፣ ሁለቱ ግን ኢትዮጵያ ደርሰው ንጉሥ እስክንድር ወደ አለበት ደረሱ። ነገር ግን አባ ጆቫኒ ዲአሞል ወደ ንጉሡ መቅረብ 8 ወር ጠብቆ ላይሆንለት ሲቀር አባ ጆቫኒ ባቲስታ ዲአምሪ ወደ ኢየሩሳሌም ላከው የሚሲዮናውያንም ተልኮዋቸው ውጤት አልባ ሆኖ ቀረ።

7. <u>አፄ እስክንድር</u>

በበእደ ማርያም ምትክ እስክንድር የእደ ማርያምና የሮማን ወርቅ ልጅ ተተካ። በእደማርያም የሞተው በ1478 ዓ.ም. ነበር። እስክንድርም እንድ ጊዜ ብቻ በአዳል ያልተሳካ ጦርነት አድርጎ በ1495 ዓ.ም. ዐረፉ። በእስክንድር ዘመነ መንግሥት በፖርቱጋል ንጉሥ ዮሐንስ ሁለተኛ አልፎንሶ

ዳ ጳጵሳ ፔድሮ ዳ ኮቪልሃም የ ባሰው የሐበሻ መንግሥት የት እንደሚገኝ ፈልገው እንዲያገኙ በ1487 ዓ.ም. ትዕዛዝ ስጧቸው ወደ ግብፅ አመሩ። የሐበሻ ሀገር በአፍሪካ ይዩን በእስያ የማይታወቅ ስለነበረ ካይሮ ደርሰው ከሱዋኪም እደን ቢገቡም የሚንገራቸው ሲያጡ አንዱ ወደ አፍሪካ አንዱ ወደ እስያ ሄደው እንዲፈልጉ ተስማሙተው አልፎንሶ ዳ ፓይቫ በርበራ ደረሰ፣ እዚያው ተገደሰ። ፔድሮ ዳ ኮቪልሀም ግን ሕንድ ገባ፣ ተመልሰ ወደ አፍሪካ በመምጣት የሥራት አፍሪካ የባሕር ጠረፎች ገብኝቶ ካይሮ ገባ። እዚያው የጓደኛው ሞት ሰማ። ከፖርቱጋል ንጉሥ አዲስ ትዕዛዝ ስላልተሰጠው ወደ ጅዳ ሄደ። በመጨረሻ ዘይላ ገባ፣ ከዚያም ጦርነት የሚደረግባት የአዳል ሀገር በድፍረት አቋርጦ ንጉሥ እስክንድር እንደሞተ አሰመግባባት ተፈጥሮ የእስክንድር ልጅ የ7 ዓመት ሕፃን ቢነግሡም ስለሞተ፣ የእስክንድር ወንድም ናአድ ንጉሥ ሆነ። የአዳል ሱልጣን በናአድ ጊዜ የሰላም ጥረቱ ቢቀጥልም ግሩዲ የተባለው የሐረር ኤሚር ግን በክርስቲያን መንግሥት በየዓመቱ በፋሲካ ያም ጊዜ ጦርነት እየቀሰቀሰ አሰመግባባት ተፈጥሮ የእስክንድር ልጅ የ7 ዓመት ሕፃን ቢነግሡም ስለሞተ፣ የእስክንድር ወንድም ናአድ ንጉሥ ሆነ። የአዳል ሱልጣን በናአድ ጊዜ የሰላም ጥረቱ ቢቀጥልም ግሩዲ የተባለው የሐረር ኤሚር ግን በክርስቲያን መንግሥት በየዓመቱ በፋሲካ ያም ጊዜ ጦርነት እየቀሰቀሰ ክርስቲያኖችን እየወሰደ በባርነት እየሸጣቸው ስለነበረ ክብቶችም ይዘርፍ ስለነበረ ንጉሥ ናአድ ጦርነት ገጠማቸው በሐሰት የመሸሽ የጦርነት ስልት በመጠቀም ከቦ የሐረር ኤሚር ወታደሮቹን ፈጃቸው። የማሕፉድ መሸነፍ የአስላም ቅዱስ ጦርነት ጅሀድ መንፈስ አቀዘቀዘው የአዳል ሱልጣንም ከንጉሥ ናአድ ጋራ ሰላም ስለፈጠረ ሰብዙ ዓመታት በምሥራቅ በኩል ሰላም ሰፍኖ ነበር።

8. አጼ ልብነ ድንግል[1]

ንጉሥ ናአድ ሲሞት በ1508 ዓ.ም. ልብነ ድንግል ብቸኛ ልጁ ሲነግሥ ሀገሪቱ ሰላም አግኝታ ነበር። በፖለቲካ በኩልም ከፖርቱጋል ጋራ ወዳጅነት በመፍጠር መልካም እርምጃ የታየበት ወቅት ነበር። ልብነድንግል ልጅ ስለሆነ የመንግሥቱ አመራር በእናቱ በንግሥት እሌኒና በታዋቂው የነበረው ስው ወስን ስገድ ይመራ ነበር፣ ተቃውሞም አልነበረውም። በልብነድንግል ዘመን መንግሥት 60 የውጭ ሀገር ዜጎች በኢትዮጵያ ይኖሩ ነበር። ንግሥት እሌኒ በመንግሥት ሞገዚትነት በነበራት ተደማጭነት የውጭ ሀገር ስዎችም ምክር በመቀበል ከፖርቱጋል ጋራ ወዳጅነት ሰማጠናከር ትጥር ነበር። የክርስቲያን መንግሥት በእስላሞች ላይ በየጊዜው እንዳይወረር ያለው አግራሞ የባሕር በሮች ከእስላም መንግሥታት እንዳይገናኙ ማድረግ ነበር። ይሽንኑም ማድረግ የምትችለው እንደ ፖርቱጋል ጠንካራ የጦር መርከቦች ያላት መንግሥት መሆን ይገነዘባል። የፖርቱጋል መልእክተኛ ፔድሮ ዳ ኮቪልሃም ይሽንን ሐሳብ በመደገፍ የባሕር ወደብ ኩተሞች ለፖርቱጋል ከልተሰጡ እርዳታ ሰማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል የሚል ሐሳብ አቅርቦ ነበር።

ይህ ሁሉ ሐሳብ ለፖርቱጋል ንጉሥ ለማቅረብ ማቴዎስ የተባለው እንድ እርመናዊ መልእክተኛ ለንግሥት እሌኒ የቅርብ ወዳጅ የሆነው ወደ ፖርቱጋል ሰመላክ ተወሰነ። ዘመኑ 1510 ዓ.ም. ነበረ። የልብነ ድንግል ሞገዚትነት ዘመንም 2ኛ ዓመት ነበረ። ማቴዎስ በመጀመሪያ የጂው ወደ ሕንድ ነበረ። ከዚያም በመርከብ ተሳፍሮ ከ3 ዓመት በኋላ ማ1513 ዓ.ም.

[1] Luca Dei Sabelli ibd V 2 p 43

ሊዝቦን ገባ። ማቴዎስ ወክና መዲናን አቃተሎ ኢየሩሳሌምን ነፃ ሰማውጣት የማል እቅድ ሰፖርቱጋል ንጉሥ ሐሳብ አቅርቦ ነበረ። የፖርቱጋል ንጉሥ አማኑኤል በታላቅ ክብር ነበረ የተቀበለው። የርግ ጳጳስም ሊዮን 10ኛ መልእክተኛው ማቴዎስን ተቀብለው አነጋገረውታል። 3 ቂሶችም ከፖርቱጋል መልእክተኞች ጋራ ተቀላቅለው ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄዱ አዘዙ። ልብነ ድንግል በ1516 ዓ.ም. ከሞገዚትነት ወቀቱ ስልጣን እንደያዘ የፖርቱጋል መልእክተኞች አፕሪል 7/1520 ዓ.ም. ምዕዋ ደረሱ። ዘመጀመሪያ የደብረ ቢዜን ቄሶች ምዕዋ ድረስ ሄደው ተሳናኟቸው። ተጥሎም ባሕር ኑጋሽ ደረ ከአጼ ናአድ እናት ሞጋሳ ወንድም ምዕዋ ሄደው ተቀበሏቸው። የክረምት ዝናም በመፍራት መልእክተኞቹ ደብረ ቢዜን ሄደው ተቀመጡ። እዚያው እንዳሉ ማቴዎስ ታሞ ሞተ። የሚተሳሰሩ በሽታ እንዳያሆን ፈርተው መልእክተኞቹ ወደ ድባሩዋ ሄዱ። አክቶበር 1520 ዓ.ም. ፖርቱጋሎቹ ደብረሲባኖስ ሰዋ ደርሰው ከንጉሡ ጋራ ተገናኙ። ፖርቱጋሎቹ ሙድ ስጠታ ሰንጉሡ አበረከቱ፣ ንጉሡ ግን በስጦታቸው አልተደሰተም ነበር። ንጉሡ ይጓጓ የነበረው አስላሞች ከዓረብ ሀገሮች የሚተርብላቸው ዘመን ያፈራቸው የጦር መሣሪያዎች ነበረ። የንጉሡ የቀበቶ አተባበል ፖርቱጋሎችን እያስተየግቸው ነበር። ንጉሡ ከፖርቱጋሎች የሚፈልገው ሱዋኪም ምዕዋና ዘይላ ዘፖርቱጋል እንዲያዙ ብቻ ነበረ።

በሌላ በኩልም ፖርቱጋል ኢትዮጵያን ወራ ትደግሰች የሚል ፍራቻ ነበረ። ንግሥት እሌኒ ከኤውሮጳውያን ጋራ መተራረብ ትጥር የነበረችው ከአስተዳደሩ ተወግዳ በዕድሜም ገፍታ ስለነበረ ጎጃም ተሰሚነት አጥታ ትኖር ነበር። በዚህ ምክንያት ኢትዮጵያ አፋጣኝ ቅርብ ግንኙነት ከፖርቱጋል ጋራ ለመፍጠር ከማንኛውም ከእስላሞች የሚደርስባት አደጋ የሚያድናት ውል ሰማድረግ ፅድል አመሰማት። መልእክተኞቹ ቂምነገር ሳይሰሩ በኢትዮጵያ 6 ዓመት ተቀምጠው ኤፕሪል 28/1526 ዓ.ም. ከምዕዋ ወደ ሀገራቸው ተነስ። ጆቫኒ ቤርመደስ ሐኪም በኢትዮጵያ እንዲቀር ተደረገ። እስላሞች ከባድ ወረራ በኢትዮጵያ ላይ የፈፀመብት ጊዜ ተቃርቦ እንደነበረ ማንም ሰው አልተረዳውም ነበረ።

አጼ ልብነድንግል በእስላሞች ላይ ባገኛቸው መጠነኛ ድሉች ተዝናንቶ ከመጠን በላይ የራሱ ኃይል ሰሰገመተ የንግሥት እሌኒ የበሰሰ የውጪ ፖለቲካ መመሪያ ችላ በማለቱ ኢትዮጵያ ወደ ጥፋት አፋፍ ደረሰች። በኢሚር ግራዝ ጊዜ የሚመሩ አዳሎች በአጼ ልብነድንግል የደረሰባቸው ሽንፈት ለመቀበል በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ሊያደርሰባት በዘይላ በኩል አደጋ ይሰነዘርባት ነበር። ከመካ ከሊሎች አዳሎችም የጅሀድ ጦርነት ቅስቀሳ ይደረግባቸው ነበረ። የጦር መሣሪያዎችና ተዋጊዎች ለእስላሞች ይላክላቸው ነበረ፣ አዳሎችም ወጣት ሴትና ወንድ ባሮች በግድረግ ወደ ገበያ ወሰደው በመሸጥ የጦር መሣሪያ ይገዙ ነበር። ሰግሕፋዝ ክብር አንድ የጦር አርማ ልከው ነበር፣ አዳሎች ወደ ፋጢጋር በግሥራት ወረራ ፈጸሙ። አጼ ልብነድንግል በአጼ ናአድ የጦርነት ዘዴ በመጠቀም ከበባ በግዘጋጅት አዳሎች ወደ ፊት እንዳይጠጉ ካደረጋቸው በኋላ ግምለጫ መንገድ በመዝጋት ፈጃቸው። ግሕፋዝ ግምለጫ ሲያጣ ከእንድ ገብረ እንድሪያስ ከተባለው ቄስ ጋራ በንራዲ ትግል ገጥሞ ቄሱ የግሕፋዙን እንገት ቆርጦ ለልብነ ድንግል አበረከተ። በዚሁ ጦርነት ብቻ 12,000 አዳሎች ሞተዋል ይባላል። ይህ የመጨረሻው የክርስቲያኖች ድል ነበረ። አጼ ልብነድንግል ዘመቻውን በመቀጠል የአዳል ሀገርን ወረው ወንድ ሌት ሳይለይ በመገደል ባሮችን አደረጋቸው። ከዚህ በኋላ የእስላም ኃይሎች ዳግም ተመልሰው ለኢትዮጵያ

የሚያሰጋት ጠላት አይሆኑም ተብሎ ተገምቶ ነበረ። ድሉም በመላው ኢትዮጵያ ተከብሯል። እንደተባለውም በሚተዋሉት ዓመታት ለኢትዮጵያ የብልፅግና የሰላም ዘመናት ነበሩ። አሕመድ ሺል ኢብራሂም ግራኝ በዓረቦችና በቱርኮች እየተረዳ ኢትዮጵያን አስላግዊት ለማድረግ በነበረው ፍላጎት በዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች ተደራጅቶ በክፈተው ጦርነት ሳይቋረጥ በየሚካውና በየተራራው ለ20 ዓመታት እየተደበቀ ለሃይማኖቱ በመዋደቅ ኢትዮጵያን ከሞት እፋፍ ያዳኗት እጹ ልብነ ድንግል ነው። በእንፃሩ በዘይላ አሚር ግሕፋዝ በፋጢጋር (ናዝሬትና ሞጆ አካባቢ) ያገኘው ከፍተኛ ድል ተዝናንቶ በቸልተኝነት ኢትዮጵያ ለሞት አፋፍ የዳረጋት እጹ ልብነድንግል ነው።

ግራኝ የሚመሰምላቸው ወታደሮች አብዛኛዎቹ ከሶማሌ ሲሆኑ የሚመጡለትም ሰዝርፊያ ብቻ ነበረ። ዘርፈው ሃብት ሲያገኙ ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ነበረ ፍላጎታቸው። ግራኝ ጥለውት እንዳይመለሱ ብዙ ትግል ማድረግ ነበረበት። በእጹ ልብነድንግል ሽንፈት ከደረሰባቸው ጀምሮ የእዳል ኢሚሮችና ሱልጣኖች እርስ በእርስ እየተጣሉ ከባድ ውድቀት ደርሶባቸው ነበር። ግራኝ ስልጣን እንዳይዝም ኃይሰኛ ተቃውሞ እጋጥሞት ነበር። ግራኝ በቀላሉ ሊሰሰብ የሚችል ጠንካራ የሰው ኃይል አልነበረውም። እጹ ልብነድንግል እንደ አምደጽዮንና ዘርአያዕቆብ ሳይቀደም ቀድሞ በማጥቃት የጦር ስልት በመጠቀም ጠላቶቹን ቢከታተል የሚወዳደረው ኃይል ሊፈጠር አይችልም ነበረ። ይሽንን ባሰማድረጉ ግን ግራኝ እሰኪጠነክር ድረስ ዝም በማለቱ በ1525 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስቲያኖች በዳዋሮ፣ (ጨርጨር) ሽንፈት ገጠማቸው። እንደገና በ1527 ዓ.ም. ክርስቲያኖች ስለተሸነፉ የቤተመንግሥት ልጆች የሚገኙባቸው 400 መቶ ልጆች ለባርነት ተወሰዱ። ግማሾቹ ለየመን እሚር ሱልጣን በባርነት ገፀበረከት ተሰጡ። ብዛት ያለው መሣሪያ ፈረሶች ድንኳኖች ተማረኩ። ግራኝ በፋጢጋር በኩል ወደ ተጉለት ድንገተኛ ወረራ እድርጉ ንጉሥን ለመያዝ አቅዶ ነበር። ወታደሮቹ ስለተቃወሙት እያለቀሰ ተመለሰ። ወታደሮቹን ለማለልጠን ብዙ እንደሚቀረው ተረዳ። በ1528 ዓ.ም. ግራኝ ወደ ይፋት ዘመቻ እደረገ፣ ብዛት ያላቸው እሰረኞች ተማረኩ፣ ከነሱ ውስጥም የቤተመንግሥት ለሰልት ነበረች። እሷ ግን 1775 ግራም የሚመዝን ወርቅ ሰጥታ ተለቀቀች፣ በእንጸኪያ የነበረ ቤተክርስቲያን ተቃጠለ፣ በውስጡ የነበሩ ብዛት ያላቸው ወርቅም ግራኝና ተከታዮቹ ተካፈሉት። በ1529 ዓ.ም. ሽንብራ ኩሬ በተባለው ቦታ ግሮች 11 ቀን ለእንድ ቀን ሙሉ በንጉሥ የሚመራው የክርስቲያን ሠራዊትና በግራኝ የሚመራው የእስላም ሠራዊት መካከል ጦርነት ተካሄደ በቀኑ መጨረሻ የክርስቲያን ሠራዊት 12,000 ሰው ሞቱበት፣ ንጉሡ ሸሽቶ ወደ ኋላ ተመለሰ። የእስላም ሠራዊትም ብዙ ሰው ሞቶበታል። ከሞቱት ሹማምንቶች መካከል የትግሬዉ ሩቤል፣ ወንድሙ ዑቅባ ሚካኤል በግራኝ እጅ የተገደለ፣ የሽሬ ሹም የጸለምቲ ሹምና የወጋሚ ሹም ይገኙባቸው ነበረ። ከተማረኩም መካከል የንጉሡ ሚስት ወንድም ተከለመድህን ነበረ። እሱ ግን 50 እውንስ ወይንም 18 ኪሎግራም ወርቅ ከፍሎ ተለቀቀ። ግራኝ ብዙ ወርቅ ስለነበረ በዘረፈው ወርቅ 7 መድፎችን ከነ ተኳሾች ዓረቦች ከበይላ ገዛ። ፈረሶችና ሴሎች ተዋጊ ዓረቦችም ነበሩት። ግራኝ ለክርስቲያኖች እንግዳ የሆኑ መሣሪያዎችን በመጠቀም በ1531ዓ.ም. ከክርስቲያኖች ጋራ ይፋት ውስጥ ጦርነት ገጠመ፣ ድልም ተጎናፀፈ። እንደገና ተሰርቆ የነበረ የእንጸኪያ ቤተክርስቲያን ተቃጠለ። እጹ ልብነድንግል ተስፋ ሳይቆርጥ እስላሙ የተባለው የጦሩ አዛዥ ወደ ዳውሮ

እንዲሄድ አዘዘው። በባለታሪክ ተከለኢየሱስ የእንጎት (ወሎ) አገረ ገዥ የሚመራ ጦርም ለማጠናከሪያ ወደ ዳውሮ ተላከ። ነገር ግን ሁለት ከክርስቲያን የከዱ ባለስልጣኖች የንጉሡ እቅድ ለግራኝ ነገሩት፣ በዚሁ መሠረት ሁለቱ የክርስቲያን ሠራዊት ሳይቀላቀሉ ግራኝ ገጠማቸው። ኢትዮጵያ ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ እልቂት ደረሰባት፣ አብዛኛው ተገሬዎች የሆኑ 130 ሹሞች በጦር ሜዳ ተገደሉባት ከነሱ ውስጥም የሽሬ፣ የጸለምት፣ የሐግሴን፣ የቤጌምድር ሀገረ ገዢዎች ይገኙባቸዋል። ከጦርነቱ በኋላ ግራኝ ለንጉሡ እጁን እንዲሰጥ ላከበት፣ የንጉሡ መልስ ግን በእጁ ይገኙ የነበሩ እስላሞች የጦር አስረኞች በመግደል ነበረ፣ ጦርነቱም በጭካኔ ቀጠለ። የግራኝ ሠራዊት ሽዋን ወሮ ከዳር እስከዳር ተቆጣጠረ፣ ግለሰቦች ብቻ ሳይሆኑ አውራጃዎችና ከፍለአተ ሀገሮች ለግራኝ እጃቸውን ሰጡ፣ ሃይማኖታቸውንም ቀየሩ። ብዙ ሐብት ተዘረፈ ከነሱ ውስጥም አስደናቂ የነበረው ሽፋኑ በወርቅ የነበረ በእንድ በይፋት ቤተክርስቲያን የተገኘው መጻሐፍ ቅዱስ ነበረ። ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ከብደቱ ሁለት ሰዎች እንድ ላይ ሆነው ለማንሳት የሚያቅታቸው ነበረ። ጦርነቱ ከሸዋ ወደ አማራ ተዛውሮ ቀጠለ ከደብረብርሃን ወደ ስሜን በሚያመራበት ጊዜ ይማም እማረ መንገዱ እንድ ድንቅ ቤተክርስቲያን አጋጠመው፣ ቤተክርስቲያኑ በወርቅ ያጌጠ ነበረ። የማታ ብርሃን ጨረር ወደ ቤተክርስቲያኑ በሚገባበት ጊዜ ወርቁ እንደ መብራት ያንፀባረቅ ነበር። ቤተክርስቲያኑን ለመገንባት 25 ዓመት ነበር የፈጀው። ከወርቅ ሌላ የቤተክርስቲያኑ ግድግዳ በሌላ ውድ ጌጣጌጥ የተዋበ ነበረ። ይማም እሁንም እወደመው ቤተክርስቲያኖችን እንዲዘርፉና እንዲያቃጥሉ ለየእንዳንዱ የግራኝ ሹማምንት ድርሻቸው ተከፋፍሎ ተሰጣቸው። ለግራኝ መካነ ሥላሴ ቤተክርስቲያን ደረሰው። በቤተክርስቲያኑ የተገኘው የወርቅና የጌጣጌጥ ብዛት ከተጠበቀው በላይ ነበረ። ጣራው የውስጥ ግድግዳው ሁሉ በወርቅ የተሰሩ ነበሩ። እንድ ሺህ ወታደር ወርቁን ለመንቀል ለብዙ ሰዓቶች ተሰማርተው ነበረ፣ አሰተርእዮ ማሪያም በተባለው ቤተክርስቲያን በታቦቱና በሌላ መንፈሳዊ ቁሳቁሶች የነበረ ወርቅ 1000 እውንስ ማለት 35 ኪሎግራም የሚመዝን ነበረ። በዐእደማርያም የተሰራ የደብረ ነጎድጓድ ቤተክርስቲያን የእንድ ሰው ቁመት ያለው ቅስት እድናቆት ያተረፈ ተዘርፏል። ዋናው የንጉሡ ንብረት ፍሰጋ ሌላ የግራኝ ጦር ወደ ወለጋ ተወስዶ የነበረውን ወርቅና ሌላ ጌጣጌጥ እንዲሁም እልባሳት ከተደበቀበት ተገኝቶ በ500 ግመሎች ተጭኖ ተወስዷል። የይማም ጦር ወደ እንጎት (ወሎ)፣ ለማምራት ሐይቅ የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ደረሰ። ከቤተክርስቲያኑ ወርቅ ለመዝረፍ 150 ሰዎች የመጫን አቅም ያላቸው ሶስት ትልቅ ጀልባዎች ወርቁን ለመውሰድ ሦስት ዙር ወስደባቸው። በደብረ እግዚአብሔር በ1342 ዓ.ም ባሰይፈ ዐረድ የተሰራ ቤተክርስቲያን የተገኘው ወርቅ ከብደቱ እንድ ሚሊዮን እውንስ ነበረ ማለት 35.000 ኪሎግራም ነበረ።

ግራኝ ወደ ደቡብ ከፍለ ሀገር ሀዲያ፣ ከንባታ፣ ወላሞ፣ እሞ፣ ዝዋይ፣ አባያታ፣ ጊቤ፣ እናሪያ፣ ጋፋት ዘመቻውን በመቀጠል ዛሳ በተባለው ቦታ በ1532 ዓ.ም. ባሸነፈ ጊዜ 3000 ክርስቲያኖች በጦር ሜዳ ሞቷል። የባሌ ሕዝብ በሙሉ የእስልምና ሃይማኖት እንዲቀበል ተገዶ የተቃወሙት ሁሉ ተገደሉ። ግራኝ ትግራይን ለመያዝ ያደረገው ጦርነት ከባድ ተቃውሞ ነበረ ያጋጠመው። በጦርነቱ 10,350 ሰዎች ተገድለዋል።

ግራኝ ሽሬ ሲደርስ በአባ ሳሙኤል ቤተክርስቲያን ያገኛቸው 500 ቀሳውስት ተገደሉ። እጹ ልብነድንግል በቤጌምድር ተራራዎች ተደብቆ

ስለነበረ ግራኝ ተከታትሉ በድንገት በእጁ ለማስገባት ያደረገው መከራ ከሽፎበት ንጉሡ ሸሽቶ ግምሰጥ ችሏል። ግራኝ ወደ ኢርትራ በማምራት ሀገረ ገርው ተሰፋ ልዑል አስመግዶ ቴዎድሮስ የሚባል ነበረ የሾመው። ነገር ግን ሕዝቡ በተሰፋ ልዑል መሪነት የደፈጣ ውጊያ ለማድረግ የግራኝ ታማኝ የነበረ ቪዜር አዶሊ የሀገሩ የበላይ አስተዳዳሪ ሆኖ ተሹሞ የነበረ ሳይቀር ገድሎ አንገቱን ቆርጦ ወደ አጼ ልብነ ድንግል ለመላክ ክባድ ፍልሚያ አካሄዷል። ግራኝ በበጌምድር ንጉሥን ማሳደድ ትቶ አፍራ የተባለው ባሕር ንጋሽ ሾመ። ሠራዊ ገብር እንዲከፍል ተገደደ የሀገሩ አስተዳደርም ቤቴዎድሮስ ምትክ ወንድሙ ተሾመ። የሁለም የበላይ አባዝ በቫሪር አደራ ምትክ ቪጺር አባስ ሾመ። የትግራይ አብያተ ክርስቲያናት የአክሱም ሳይቀር ተቃጠሉ። ተሳላፊ በሽታም በሀገሩ ንብቶ ብዙ ሰው ፈጀ ከሞቱትም መከከል የግራኝ ልጅ ከጦር ሜዳ የተወሰደ ነበረ። ግን ሰላም አስፍኖ ወደ ያመቢያ ሲመለስ ወዲያውኑ በሸራየና በትግራይ የደፈጣ ውጊያ ተጀመረ። ግራኝ ሰሜን እንዲይዝ ፈላሾች መንገድ ከፍተውለት ነበረ። የመጨረሻ ያልተያዘ ከፍለ ሀገር ወደ ጎጃም በማምራት ግራኝ ንግሥት እሌኒ ብዙ ንብረታቸው ያፈሰሱባቸው ቤተክርስቲያናት ተቃጠሉ፣ ተዘረፉ በነሱ ውስጥም መርዙ ለግራያም የተባለ ስመ ጥሩ ነበረ። በዚሁ ዓይነት መላው ኢትዮጵያ በግራኝ ቁጥጥር ውላ ነበረ። የቀረው ንጉሡን አሳዶ ማያዝ ብቻ ነበር። ለልብነ ድንግል የተሰፋ ጭላንጭል የነበረው የፖርቱጋል መልእክተኞች ውጤት ነበረ። ነገር ግን አጼ ልብነድንግል ከዚህ በፊት ያደረገላቸው አቀባበል የቀዘቀዘ ሰለነበር እርዳታ የማግኘት ተስፋ አነስተኛ ነበረ። አስቸኳይ እርዳታ ከክርስቲያን ኤውሮጳ ለማግኘት የነበረው አማራጭ አጼ ልብነድንግልና ቤተመንግሥቱ በሙሉ የካቶሊክ ሃይማኖት መቀበል ነበረ።

ነገር ግን ይኸም አማራጭ እርምጃ የሕዝቡ ተቃውሞ ሊያስከትል ይችላል ተብሎ ስለተፈራ ሌላ ዘዴ ተቀየሰ። ይኸውም በዕድሜ የገፋ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ የነበሩ አቡነ ግርቆስ ለአንድ ካቶሊካዊ የጵጵስና ማዕረግ ሰጥተው ሰልጣናቸውን እንዲያስረክቡ ነበር። ይህ ዘዴ ጥሩ መስሎ ቢታይም ሕጋዊነት አልነበረውም። ምክንያቱም አቡኑም ለአንድ ካቶሊክ ጵጵስና መሰጠት መብት አልነበረውም፣ ለጵጵስና ተሿሚ ግለሰብም መቀበል አይችልም ሰለነበረ ነው። ለጵጵስና ማዕረግ የተመረጠ ሰው በርሙደስ ነበረ። በርሙደስ እንደ ተሾመ ሁኔታውን ለግስረዳት ወደ ሮም መሄድ ነበረበት። በ1536 ዓ.ም ከአንድ ዓመት ጉዞ በኋላ ከእስላሞች ብዙ አደጋዎች አምልጦ በርሙደስ ሰሮም ሊቃነጳጳሳት ከአጼ ልብነ ድንግል የተላከ መልእክት ይዞ ሮም ገባ። በደብዳቤው ላይ አጼ ልብነ ድንግል የካቶሊክ ሃይማኖት እንደሚከተልና ከሮማ የተላከ አቡን በስተቀር ሌላ አቡን እንደማይቀበል ገልጾ ነበር። በርሙደስ ወደ ፖርቱጋል ከአጼ ልብነ ድንግል ለፖርቱጋል ንጉሥ የተላከ መልእክት አቀረበ። ሁለቱ መንግሥታት የሮማና የፖርቱጋል የራሳቸው የውስጥ ችግር ስለነበራቸው የኢትዮጵያ ጉዳይ ችላ ብለውት ነበር። ሆኖም በርሙደስ የኢትዮጵያ ክርስቲያን ሕዝብ ሁኔታ በሚገባ በማሰረዳቱ የፖርቱጋል ንጉሥ አማኑኤል 5ኛ ከአንድ 450 የፖርቱጋል ወታደሮች ወደ ኢትዮጵያ እንዲላኩ አዘዘ። በርሙደስ ትዕዛዙን ይዞ ወደ ሕንድና ወደ ኢትዮጵያ የመልስ ጉዞ ለመጀመር በሚዘጋጅበት ጊዜ ለ3 ዓመት እስከ 1539 ዓ.ም. ታዞ ሀገሩ ተቀመጠ። የፖርቱጋል ወታደሮች ምፅዋ ሲወርዱ የቻሉት በ1541 ዓ.ም. ነበረ። በኢትዮጵያም ጦርነቱ እየተካሄደ ነበረ። በ1539 ዓ.ም. ግራኝ ለልብነ ድንግል በላከው ደብዳቤ በኢትዮጵያ ሰላም እንዲሰፍን የአጼ ልብነድንግል ልጅ ለማግባት ንጉሥ እንዲፈቅድ ይህ ካልሆነ ግን ኢትዮጵያ

እስላም አንድሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰለሆነ አጼ ልብነ ድንግል በጦርነቱ ከገፋበት ሊያመልጠው እንደማይችል እና ቅጣቱ አስከፊ እንደሚሆን አስጠነቀቀው። አጼ ልብነ ድንግል ግን የሰላም ጥሪ ሳይቀበል ሰለቀረ ጦርነቱ ቀጠለ፣ በመጨረሻም ሳይያዝ ቀርቶ የነበረው የነገሥታት ዘር ማጥፊያ የተደበቀ ወርቅ ይገኛል ስለተባለ የእስላም ተዋጊዎች ሳይነቃባቸው ለመግረሽ ሰለቻሉ ከዘረፉት በኋላ አቃጠሉት። የተገኘው የወርቅ ብዛት የተነሳ "ወርቅ እንደ ድንጋይ ሆኖ ነበር ልብሶችም እንደ ቅጠል ሆነው ነበረ" በማለት የኢትዮጵያ ታሪክ ጸሐፊዎች ዘግበዋል።

አጼ ልብነድንግል በ45 ዓመት ዕድሜው ሲሞት የደረሱ ልጆች ነበሩት። ቪክቶር የተባለው አልጋወራሽ ልጅ ወደ ዳዋሮ የሚያዋስነው ሄዶ የእስላም ሠራዊት ለሁለት ከፍሎ የመዋጋት ዓላማ ነበረው ሳይሳካለት ሰለቀረ ግን በውጊያ ተገደለ። 2ኛ የአጼ ልብነ ድንግል ልጅ ሚናስ ከአባቱ ጋራ ሆኖ በዋግ አካባቢ ሲዋጋ በእስላሞች ሰለተያዘ ባሪያ ሆኖ ለዘረጋ ፖሻ ተሸጠ። አጼ ልብነ ድንግል በደብረዳሞ አስተማማኝ መደበቂያ በመፈለግ ወደ ደብረ ዳሞ ሄደ። ባሕር ነጋሽ ይሰሐቅ ከግራኝ ወታደሮች እደጋ እንዳይደርስበት በማሰብ የገዳሙ መውጫና መግቢያ ዙብ በማቆም ይጠብቅ ነበር። ጥቂት ወራት ቆይቶ ሴፕቴምበር 5/1540 ዓ.ም. አጼ ልብነድንግል በቤተሰቦቹና በታማኞቹ ተከቦ በሰላም ዐረፈ።

9. አጼ ገላውዲዮስ

አጼ ገላውዲዮስ ከአባቱ ሥልጣን ተረክቦ ጦርነቱን በጠንካራ መንፈስና ዘዴ ተሻለ ዕድል ቀጠለ። የአጼ ገላውዲዮስ እናት ንግሥት ሰብለ ወንጌል በሰሜን የሚኖሩ ሕዝቦችን በማነሳሳት ከአዲሱ ንጉሥ ጋራ አንዲቆሙ ያደረገችው ጥረት ሰለተሳካላት ለመጀመሪያ ጊዜ ፈላሾች ለኢትዮጵዊ አዲሱ ንጉሥ ለገላውዲዮስ ድጋፋቸውን ሰጥተዋል ጸለምትም የእነሱ ምሳሌ ተከትለው ድጋፋቸውን ሰጥተዋል። ግራኝ ምርኮ አዛዦች በማሰማራት ሰሜን ለመያዝ ሊወጋቸው መጥቶ አልተሳካለትም። አጼ ገላውዲዮስ በሰሜን ተራራዎች ሆኖ ከጠላት ጋራ እየተፋለመ በነበረ ጊዜ ንግሥት ሰብለ ወንጌል በደብረዳሞ ገዳም ሆና ታማሞችን እየሰበሰበች የጦር መሣሪያ ትሰጥ ነበረ፣ በዚሁ ጊዜ ፖርቱጋሎች ምፅዋ መድረሳቸው ወሬ ሲሰማ ሕዝቡ በደስታ ፈነደቀ። ትግራይ ሁሉ ለንጉሡ ሙሉ ድጋፍ ሰጠ። ፖርቱጋሎች በበርሙዳዝ እየተመሩ ጉራዕ ገቡ። ከዚያም ድባርዋ ድረስ መጥተው ሰብለ ወንጌል ትጠብቃቸው ሰለነበር ተገናኙ። በታኅሣሥ ወር ፖርቱጋሎች ከንግሥት ሰብለ ወንጌል ጋራ በመሆን ምጣብ እያቀረበችላቸው ከድባርዋ ተነሱ። እጥረል 4/1542 ዓ.ም. በፖርቱጋሎችና በግራኝ የሚመራ የእስላም ሠራዊት እናሳ በተባለው ቦታ ለእክለጉዛይ ጦርነት ተካሄደ የፖርቱጋሎች መድፎች በእስላሞች ላይ ሽብር ፈጥረው ነበር።

ግራኝ ታፋው ላይ ቆሰለ፣ ፈረሱ ተገደለ። ግራኝ እስከ ዘቡል ተራራዎች ሸሽቶ በመሄድ ጦሩን ለማደራጀት ሞከረ። ከዓረብ ሀገር ሁለት ሺህ ዓረቦች፣ቱርኮችና አልባኖውያን ቅጥር ወታደሮች በዘይላ በኩል እስመጣ። የክርስቲያን ሠራዊት ግራኝን እያሳደደ እስከ አሻንጉ ሐይቅ ድረስ ገሠገሰ። እጎአ በ1542 ዓ.ም. ግራኝ ከባድ ጥቃት አካሄዶ የፖርቱጋሎች ጠር አዛዥ ዶን ክሪስቶፎር ዳ ጋማን አቁሰሉትና በእስታቂ ሁኔታ ገደሉት። የፖርቱጋል ጦርና ንግሥት ሰብለ ወንጌል እስቶድሞ ለክፉ ጊዜ ጦር ሰፈርና ጣብያ አድርገውት የነበረ ወደ ሰሜን ሄዱ። ንጉሡም የእስላም ጦር ጥሶ

ከፖርቱጋሎች ጋራ ተቀላቀለ። ንጉሡ ለፖርቱጋሎች ወረታውን በመመስከ በግሰብ ለእየአንዳንዱ ፖርቱጋል ወታደር 1000 አውንስ ወርቅ ሰጣቸው (135 ኪሎግራም)። ይህ የሚያሳየው ኢትዮጵያ በእስላሞት ከተዘረፉ ሃብቷ ሌላ ብዙ የቀራት ወርቅ እንደነበረ ሲሆን ይኸውም ምን ያህል የበለፀገችና ሃብታም ሀገር እንደነበረች የሚያመለክት ነበር።

የክርስቲያን ሠራዊት ከሰሜን ወደ ደቡብ ጎንደር እስላሞችን እያሳደደ ተጓዘ። ግራኝ ከነበረበት ከዘቡል ተራራዎች ዋና ከተማው ብሉ ወደ መረጣት ወደ ደንቢያ መጣ። ፖርቱጋሎች ዶን አልፎንሶ ከልደራ አዘዣቸው መርጠው ነበረ። እሱም ወዲያው ስለሞተ አንድ ክልሳ ዝርያ ያለው አሪዮስ ዲያዝ መረጡ። አጼ ግላውዲዎስ ከፖርቱጋሎች ጋራ በመመካከር ግራኝ ወደ ደንቢያ እንደመጣ እንዲገጥሙት ተወሰነ። ዲያዝ በመጀመሪያ መሥመር ፖርቱጋሎቹን አሰማራ። እስላሞች እያጠቁ ሲመጡ ግራኝ ወታደሮቹ ወደ ኋላ እንዳይመለሱ ፊት ለፊት እየመራቸው ስለነበረ በፖርቱጋል መድፎች የእሳት እራት ሆነው ቀሩ። አንድ ፖርቱጋላዊ የቀድሞ የፖርቱጋሎች አዛዥ ጆን ኪሪስቶፎር ዳጋማ ጠባቂ የነበረው ፔድሮ ሲዮን የተባለው የጌታውን ገዳይ ለይቶ ስላወቀው በእሱ አነጣጥሮ በመተኮስ ግራኝን አቁስሎ ጣለው። ግራኝ ግን ወታደሮቹ ተስፋ እንዳይቆርጡ በማሰብ በአንድ ዛፌ ስር ስመደበት ሞክሮ ነበር። ያቆሰለው ወታደር ግን ግራኝ የሄደበትን ቦታ ተከታትሎ ስላወቀ ስሞት ሲያጣጥር ስላገኘው ላስረጅነት እንድ ጆሮውን ቆርጦ ወስደበት፣ ቦታውን አሁን ድረስ የግራኝ በር ተብሎ ይጠራል። የእስላም ወታደሮች ተሸንፈው ተበታተኑ።

ጦርነቱ በክርስቲያኖች ድል አድራጊነት ቢፈጸምም የሚቀጥለው ዙር በአጼ ግላውዲዎስና በበርሙደስ ያለው ጉዳይ መፍትሄ ማድረግ የሚኖርበት ነበረ። በርሙደስ በውሉ መሠረት የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አቡን መሆን አስብኝ ባይ ነበረ። አጼ ግላውዲዎስ ግን በቤተክህንነት ተጽእኖ በርሙደስ ወደ ጎን በመተው እንደ ቀድሞ ከእስክንድሪያ አቡን እንዲላክለት ጠየቀ። በዚሁ ጊዜ በሁለቱ ሰዎች መካከል ከፍተኛ ጠብ ተፈጥሮ በርሙደስ የፖርቱጋል ወታደሮች ድጋፋቸውን እንዲሰጡት ፈልጎ ነበረ። ግማሾቹ የፖርቱጋል ወታደሮች ወደ ሕንድ ተመልሰው፣ ነበረ በኢትዮጵያ ቀርተው ከነበሩት መሐል ግን አብዛኞዎቹ ንጉሡን የሚደግፉ ሆነው ተገኝተዋል። በተለይ አዛዣቸው ዲያዝ በግልፅ ከንጉሡ ጋራ ከመቆመም በላይ እንደገና በአርቶዶክስ ክርስትና ተነስቶ ስሙ ማርቆስ ተብሏል። ሌሎችም የእሱን ምሳሌ ተከትሏል። በንጉሡ ሕይወት አደጋ እንዳይጥሉ በማለት በርመደስ ሌሎችም ፖርቱጋሎች ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ እንዲሰደዱ ተደርጓል። በርሙደስ በመጀመሪያ ወደ ደቡብ ጋፋት ተልኮ ቀጥሎም ሌሎች ፖርቱጋሎች ወደ ነበረበት ወደ ዳውሮ ተወሰዶ ከዚያም ወደ ድባርዋና ምፅዋ ሄደ። ከዚያም በኋላ ወደ ህገሩ ተመልሶ አስታዋሽ አጥቶ ቀሪው ዕድሜው አሳ ልሩል። ሌላው ከጦርነቱ በኋላ የተደቀነው ችግር የንጉሡ ነገሥቱ የማዛት እንድነት ማስከበር ነበር፣ ይሄም የተከናወነው በ1544 ዓም. ነበር። ቪዜር አባስ የአቡን ልጅ የኢማም ወንድም ዳዋሮ፣ የዛሬዋ ናዝሬት መተሀራ አካባቢ እንደዚውም ባለ ከአርሲ እስከ ሕንድ ውቅያኖስ የሚያጠቃልል ነፃ መንግሥት አቋቁሞ መሪ ሆኖ ነበረ። የኢትዮጵያን ሠራዊት ሰመቋቋም የሚችል መስሎት ነበር። አጼ ግላውዲዎስ በዋዲ አውራሻ በኩል ወደ ፋጢጋር አልፎ ገሰገው። በአንድ ቀን ጦርነት በአክቶበር 1544 ዓም. አስላሞች ተሸነፈ። በ1545 ዓም. መጀመሪያው ላይ አባስ ተገደለ አጼ ግላውዲዎስ ወደ ዳውሮ ገባ፣ ቤተመንግሥት ሠራ፣ የፈረሱ ቤተክርስቲያኖችም ታነፁ። ባሌም

እንደገና ተያዘ፣ ሆኖም ባሌ በዚሁ ጊዜ አሮሞ የሚያደርገው መስፋፋት ዋና መነሻ ጣብያ ሆና ስለነበረች ለብዙ ጊዜ ተይዞ አልቆየም። በ1547 ዓም. ሐዲያ እንደ ቀድሞ ወደ ግዛቱ ተቀላቀለች። በ1548 ዓም. የኢትዮጵያ ሠራዊት ወደ ዳሞት ከአባይ በስተደቡብ ዘምቶ ከርስትና ያልተቀበሉ ሕዝቦች ስለነበሩ ወስኑ እስከ ጊቤና እሞ ወንዞች ደረሰ። የሐረር መንግሥት በ1548 እና በ1550 ውስት ጊዜ ከአጼ ግላውዲዎስ ጋር ጦርነት ገጥማ ሁለት ጊዜ ተሸነፈች። 1552 ግላውዲዎስ ከንባታን አስገብረዋል፣ ጉመር የሚባል አውራጃ በዛሬዋ ደጋማ ክፍል አርሲ አስገብሯል። በዚሁ መሠረት የንጉሡ ነገሥቱ ግዛት ስፋቱ ድሮ ወደ ነበረበት ተመልሶ ነበር። ሐረር እንደገና በ1552 ዓም. ሽፍታ ጦርነት አውጃ ፋጢጋርን ወራ ወደ ሽዋ አምርታ ነበር። አጼ ግላውዲዎስ የደብረ ወርቅ ገዳም እያሰራ ይገኝ ስለነበረ፣ 12 ቀን ፈጣን ጉዞ እድርጎ ሐረር ስቅስት /አርብ ቀን/ ጦርነት ገጥሞ ተገደለ። የግራኝ ሚስት አጼ ግላውዲዎስ በመገደሉ የግራኝ መበቀል ሆኖ ስለተሰማት ደስ አላት፣ የግላውዲዎስ ጭንቅላት ተቆርጦ በሐረር ከተማ መግቢያ ደጃፍ ሰሦስት ዓመት ተሰቅሎ ነበር።

አጼ ግላውዲዎስ እንደሞተ ሦስት ቀን በኋላ ታማኞቹ አስከሬኑን ወደማሪያም ቤተክርስቲያን ወስደው ቀበሩት። የአጼ ግላውዲዎስ ጭንቅላት በሐረር ከተማ በር ደጃፍ ተሰቅሎ የነበረው፣ ክርስቲያን ነጋዲዎች ስርቀው ወስደው በአንድ የይፋት ቤተክርስቲያን በክብር ቀበሩት። አጼ ግላውዲዎስ እንደ ሰማእት ሆኖ ይከብር ነበረ።

10. <u>የክርስቲያን መንግሥት አሸናፊነት</u>

ከግራኝ ጦርነት በኋላ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ መንግሥት ምንም እንኳን እንደ ምዕዋ፣ አሰብ ታጁራ፣ ዘይላ የመሳሰሉት የባሕር ጠረፍ ከተሞች መቆጣጠር ባለመቻሉ ደካማ ጐን እንዳለው መስሉ ቢታይም በባሕር የሚመጡበትን አደጋዎች ጠላቶችንም ለመቋቋም ችሉ ነበረ። የክርስቲያን መንግሥት የእስራኤል ዝርያ የሆኑ ሰለሞናዊ ነገሥታት እንደነበረ ሁሉ በምስራቅ ኢትዮጵያ የነበሩ የእስላም መንግሥታትም የነቢዩ መሐመድ ዘመድ የሆኑ በዓረቦችና በቱርኮች የሚደገፉ ወላዝማ በሚባሉ ሱልጣኖች የሚመሩ ነበሩ። በመጀመሪያ በክርስቲያን መንግሥት ላይ የተነሳ ይፋት ነበረ። ይፋት ሲዳከም በአዳል ተተካ። አዳል የሚባለው መንግሥት በግራኝ እምባነን አዛዣዝ ቁጥጥር ስር ሆኖ የክርስቲያን መንግሥት ያልነበረው የጦር መሣሪያ ታጥቆ መላው ኢትዮጵያን የተቆጣጠረ ቢመስለውም የክርስቲያን መንግሥት ለ20 ዓመታት ወረራውን ለመቋቋም በመቻሉ፣ በመጨረሻ በጥቂት የፖርቱጋል ወታደሮች አርደታ በአሸናፊነት ሊወጣ ችሏል። ከግራኝ መሸነፍ በኋላ ስግቆጥቆጥ የሞከረው የእስላም መንግሥት በሐረር ከተማ የተቋቋመው የግራኝ እና የወላዝማ ዝርያ የነበራቸው የግራኝ ሽንፈት ለመቀበል ፍላጐት ያልነበራቸው ሱልጣኖች ነበር። በረከት በተባለው የሐረር መንግሥት ሱልጣን ልጅና አሊ ጋራድ በተባለው የግራኝ ልጅ የሚመሩ የሐረር ወታደሮች ዳውሮን ወረሩ፣ ወረራው ግን የእውራጃው ክርስቲያን ህገረ ገሸር የነበረው፣ በራሱ ሌላ አርዳታ ሳይጠይቅ ሊያከሽፈው ችሏል፣ መሪዎቹም ተይዘው ታሰሩ።

የግራኝ ሚስት ከጎረቦች ጋራ በነበራት ትውውቅ በመጠቀም ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ ውይይት ተደርጎ የእስረኞች ልውውጥ እንዲደረግ ተስማምተው ሚናስ የእኔ ግላውዲዎስ ወንድም በጦር ሚዳ

በግራኝ ተይዞ ወደ የመን ባሪያ ሆኖ ተወሰደ ሰሰነበር በሱ ለውጥ ባረከት አሊ ጋራድ ወደ ሐረር እንዲመለሱ ተደርጓል። ትንሽ ጊዜ እንደቆዩ የሐረር መንግሥት በ1550 ዓ.ም. ኢትዮጵያን ለመውረር ኑር በሚባሰው ሱልጣን መሪነት ሌላ መኸራ አድርገዋል። ወረራው ይመራ የነበረው የሞጃሂድ ልጅ ነበረ። ከግራኝ ሞት ብኋላ የሞጃሂድ ቤተሰቦች የቀድሞ የግራኝ ተዋጊዎች መስበሰቢያ ሆነው ነበረ። እንዲሁም የግራኝ ሚስት ባቲ ደል ዋምባራ ከሚደገፉ መካከል ዋና ተዋንያን ነበረች። የግራኝ ሚስት በእባቷ በኩል ኢትዮጵያን እየወረሩ ያስቸገሩ ከነበሩ እንዱ የነበረው የግሕፋዝ ልጅ ስትሆን የአሁኑ የኑር የሐረር መንግሥት መሪም በእናቱ የግራኝ እህት ልጅ ስለሆነ፣ ሙሉ እምነት ሰሰነበራት አትቱን እንዱነቀል አስምላው ሰሰነበር ዋና ተልእኮዋና ዓላማዋ ሆኖ ነበር። አሁንም እስላሞች አልተናቸውም በታዋቂው የኢትዮጵያ ጦር መሪ ፋኒል የሚመራ የኢትዮጵያ ሠራዊት ኑር ብቻ ሽሽቶ ሲያመልጥ የቀሩት የሐረር ወታደሮች ተደመሰሱ። አጼ ገላውዲዎስ ሰፋኒል ሐረርን ወር እንዲይዝ ትዛዝ ሰጠው። ግርች 13 ቀን 1550 ዓ.ም. ሐረር በፋኒል ጦር እጅ ወደቀች ነወሪዎቿም ሸሹ። ከተቂት ጊዜ በኋላ ፋሲል ሞተ፣ አጼ ገላውዲዎስ የተገኘው ድል ሰግከበር 5 ወር ሐረር ተቀመጠ፣ ከርስቲያን ባሪያ ሆኖ ተወሰዶ የነበሩ ተሰቀቱ፣ በእንባሩም ብዙ እስላሞች ተገደሱ፣ ባሪያ ሆነውም ተወሰዱ። ሐረር ምንም እንኳን ከባድ ሽንፈት ቢገጥማትም ለ3ኛ ጊዜ የኢትዮጵያ ከርስቲያን መንግሥትን ለማጥቃት ሞከራ ነበር። በኤሚር ኑር ምትክ ከርስቲያን የነበረው ዑትማን የተባለው በሐረር ሥልጣን ይዞ ነበር። በዚሁ ዘመን ሁለቱ የሐረር እስላሞችና የኢትዮጵያ ከርስቲያን መንግሥት በእርሞ የጋራ ጠላት ተከለው በችግር ላይ ወድቀው በነበሩ ጊዜ ሐረር ሰሰ ተዳከመች በሥልጣን ላይ የነበረው የግራኝ ዘመድ ይማም መሐመድ የእርሞች ወረራ ወደ ግያሰጋው ወደ አውሳ በ1577 ዓ.ም. ሐረርን ሰቶ ሰመሄድ የተገደደ። ከዘህ ጊዜ ጀምር የአውሳ ሱልጣን ተመሰረተ፣ የይፋት፣ የአዳል፣ የሐረር መንግሥት ህልውናቸው አከተመ።

11. <u>የቱርክ ወረራዎች በኢትዮጵያ</u>

ሌላ የኢትዮጵያ ቀንደኛ ጠላት የነበረው ምፅዋ የሰፈረው የቱርክ አገዛዝ ነው። ቱርክ ሱዋኪምና ምፅዋን የያዘው በ1517 ዓ.ም. ነበር። የቱርክ መንግሥት በወቅቱ በዓለም ትድመ ኃያል መንግሥት ለመሆን በቅቶ የነበረ ነው።

ዓረቦች በምዕራብ ኢውሮጳ ንብተው ኢውሮጳን አስላግዊትና ዓረባዊት ለማድረግ እንደሞከሩ ሁሉ የቱርክ መንግሥትም በደቡብ ምስራት ኢውሮጳ እስከ መሐል ንብቶ ኢውሮጳን በቁጥጥሩ ለማዋል ተቃርቦ የነበረ መንግሥት ነው። ቱርኮች ከዓረቦች የበለጠ ዓላማቸው ተሳክቶላቸው በአንዳንድ የኢውሮጳ ሀገሮች ሃይማኖት እንዲቀበሉ አድርጓል እንደ ቡስኒያ፣ አልባንያ የመሳሰሉት። ቱርኮች መሃል ኢውሮጳ ንብተው የአንድ ትልት ኢውሮጳዊ መንግሥት ዋና ኩተማ የሆነችው በስልጣኔና በጥበብ የተራቀቀችው ቪዮና ለመያዝ በተቃረበበት ጊዜ ኢውሮጳውያን በሙሉ ተባብረው አስካለቀጵዋቸው ድረስ አስፈሪ ኃይል ነበሩ። በኢትዮጵያ ግን ቱርኮች አራት ጊዜ ወረራ አድርገው ተሸንፈው ወጥቷል። የመጀመሪያ ወረራቸው በመፅዋ በኩል በ1557 ዓ.ም. ነበረ። በዚሁ ጊዜ ቱርኮች ምፅዋን ተቆጣጥረው ወደ ደጋ ዘልቀው በመግባት በድባርዋ ምሽግ በመስራት ባሕር ነጋሽን በሙሉ በቁጥጥራቸው ስር አውለው ነበር። የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ገዛም የሆነው

ደብረ ዳሞት በቱርኮች ተይዞ ተዘረፈ፣ የባሕር ነጋሽ ቆላማ ሰሚናዊና ምዕራባዊ ጎሳዎች ቤኝ የተባሉ በፓሻ አከዝዳመር የሚመሩ እስላሞች ከቱርኮች ጋራ ተባብረው ነበረ። በባሕር ነጋሽ ይሰሐቅ በሚመራ የከርስቲያን ሠራዊት ሲደመሰሱ መሪያቸው ሽሽቶ ቱርኮች ወዳሰብት ወደ ዱባሩዋ ገብቶ ብዙ ሐብት ከርስቲያኖች የደበቁት አሰ በግሰት ቱርኮችን ሰለ አጓጓቸው ፓሻ ዑገዳመር 800 ፈረሰኞችና በዛት ያላቸው ወታደሮች አሰከትሉ ወደ ቦታው ዘመቱ። ብዙ ኩተጓዘ በኋላ የተባሰው የሐብት ከምችት አገኙ፣ በመሀሉ ግን የቱርክ ፓሻ ትኩሳት ታሞ በቃሬዛ ተሸክሞት ተመለሰ፣ የዘመቱ ሰዎችና አንሰሳት አብዛኛዎቹ ሞቱ፣ ከኢትዮጵያ ጦር በመሐሉ በድባሩዋ ጥቃት ፈፅሞ በመከበብ ቱርኮችን ያሰምጉብና ውሀ አስቀርቷቸው ነበረ። ቱርኮች ያገኙትን ሐብት ሌሊት ከድባሩዋ ሰመውጣት ሲሞክሩ መሣሪያ በታጠቁ ገበሬዎች ተደመሰሱ፣ ሐብቱንም ማረኩት፣ ድባርዋም ተማረከች። የቱርክ ወታደሮች ከድባርዋ አምልጠው ወደ ምጽዋ ለመሸሽ ሲሞክሩ በታጠቁ ገበሬዎች ተገደሱ፣ የቱርክ ፓሻ ባዶ እጁ ሰሰቀረ ሸሽቶ ሱዋኪም ገባ። የቱርክ ወረራ ተመግዶ ይዞታው በመፅዋ ተወሰኖ ቀረ፣ ሁለተኛ የቱርክ ወረራ በአጼ ሚናስ ዘመን መንግሥት፣ ነበረ በእንደኛ የቱርክ ወረራ በጀግንነት ተዋግቶ የአባረራቸው ባሕር ነጋሽ ይሰሐቅ ሥልጣኔ ተሻመኝ በግሰት በንጉሥ ላይ ተቀየመ። አጼ ሚናስ መጀመሪያ ዮሐንስ በተባለው ጦር ላከበት፣ ነገር ግን ይሰሐቅ በድንገት አደጋ ጥሰብት አሸነፈው፣ ይሰሐቅ ከቱርኮች እርዳታ ለማግኘት ከድባርዋ እስከ ምፅዋ ያሰውን መሬት ሰጣቸው። አጼ ሚናስ ፖርቱጋሎች ከይስሀቅ ጋራ ተሰግምተው ይሆናል ብሰው ሰለጠረጠራቸው በአንድ ተራራ እንዲቀመጡ አደረጋቸው። እቡነ አርሼያዶና ተከታዮቹ አምልጠው ባሕር ነጋሽ ይሰሐቅ ወደ አሰበት ደርሰው ድጋፋቸውን ሰጡት። በዚህ መሠረት ቱርኮች ባሕር ነጋሽ ይሰሓት ካቶሊኮችና ሌሎችም የሚናስ ተቃዋሚዎች ግንባር ፈጠሩ። ፖርቱጋሎች ከሕንድ የጦር መርከቦች እንደሚያስመጡ ሰይሰሐት ተሰፋ ሰጡት፣ አጼ ሚናስ ግን ጊዜ አልሰጣቸውም አፕሪል 20 1562 ዓ.ም. በተደረገው ጦርነት አሸናፊ ሆነ። ከተቂት ጊዜ በኋላ አጼ ሚናስ ከዶባ ጎሳዎች ጋራ ጦርነት ባደረገበት ወቅት በትኩሳት ታሞ ሞተ። ጦሩም ጉዳት ደርሶበት ሰሰነበረ ቱርኮችን እስከ ባሕር ሳያባርራቸው ተመለሰ።

ሦስተኛ የቱርክ ወረራ በኢትዮጵያ በአጼ መላክ ሰገደ ዘመነ መንግሥት ነበረ። ባሕር ነጋሽ ይሰሐቅ እንደነና 1578 ዓ.ም. ከቱርኮች ጋር ተሰግምቶ ለንጉሥ ነገሥቱ አልታዘዝም በግሰት የንጉሡ መልእክተኞች ተልከውበት ከቱርኮች ጋራ እንዳይነጥም ቢጠየቅ "ከፓሻው ጋራ እርቅ አድርጌአለሁ፣ በአንድ ምንጣፍ አንድ ላይ በመተመተ" የሚል መልስ ሰሰሰጠው መላክ ሰገደ ጦሩን ወደ ባሕር ነጋሽ አዘመተ የንጉሡ መምጣት ዜና ሲሰማ ተዋጊዎች ከባሕር ነጋሽ መከዳት ጀመሩ። በሠራዊ ፀረ ባሕር ነጋሽ ዐመፅ ተካሂደ፣ ይሰሐቅና ቱርኮች እንጪጮ ተሰበሰቡ፣ በመጀመሪያ ግተሚያ ኖቬምበር 13, 1578 ዓ.ም. ቱርኮች የመላክ ሰገድ ሠራዊት እንዲሸሽ አደረጉ። አራት ቀን በኋላ ቱርክች 8 መድፎች በኢትዮጵያ ጦር ላይ ተከሱ፣ በማነፃጸር ብዙ ጉዳት አደረሱ። በዚሁ ጊዜ መላክ ሰገደ የእርሞ ፈረሰኞች አሰማርቶ ቱርኮች ላይ አጠቃ፣ ብዙ ሳይቆይ መድፎቹ ተያዙ፣ የጠላት ይዞታዎችም ተያዙ። ከዘህ በኋላ ይሰሐቅ ተሰፋ ሰለቆረጠ እርቅ ጠየቀ። ንጉሡም ኩርኮቹ ተዋጊዎቹ ለይቶ አውጥቶ ከክርስትያኖች ጋራ ቱርኮችን እንዲወጉ አድርግ የሚል መልስ ሰጠው። ይሰሐቅ ከቱርኮች ጋራ እርቅ እንዲደረግ የሚል ሐሳብ አቀረበ።

በተደረገው ሁለተኛ ግጭሚያ ቱርኮችና ይሲሐት ሽንፈት ገጠማቸው የኢትዮጵያ ጦር የቱርክ ጦር ሰፈር ተቆጣጥሮ የቱርኮች አርማና መደርጀትን ማረከ። የኢትዮጵያ ሠራዊት እንደልማዱ ከአካባቢ ገበሬዎች ስንት ፍለጋ መሐዱ ሲያውቁ ቱርኮችና ይሲሐት ከሠሽጋቸው ወጥተው መደፋቸውን ዘንጉሥ ጦር እያተኮሩ መተኮስ ጀመሩ፤ ንጉሥ ግን ጥቃታቸውን አክሽፎ መለሳቸው። ይሲሐትም ከጥቂት ተከታዮቹ ጋር ሆኖ ወደ ሬት እያመራ በግጥቅት ሞክሮ ነበር። ነገር ግን አንድ ኢትዮጵያዊ ወታደር ለይቶ ስላወቀው አድፍጦ ትዘሻውን አቆሰለው። ይሲሐት ብዙ ደም እየፈሰሰው ወደ መጣበት ተመልሶ ከፈርሱ ወርዶ በመሬት ተጋደመ። ስንት ፍለጋ ሔደው የነበረ የኢትዮጵያ ወታደሮች ሲመለሱ የቱርክ ሠራዊትን ከዘው ፈጁት። ይሲሐት ጥቂ የቱርክ ፖሻ የጦሩን እልቂት ፈርሱ ላይ ወጥቶ ያመለክት ነበረ። ጀግናው አንድ የኢትዮጵያ ወታደር ዮናኤል የተባለው ደረቱን ዘመውጋት ሰላቆሰለው ከፈረሱ ወደቀ። ያቆሰለው ወታደርም ወደ ወደቀበት ሄዶ አንገቱን ቆርጦ ለንጉሥ አበረከተው። ቱርኮች የነበራቸው ሐብትና ብዙ የጦር መሣሪያ ተማረከ የይሲሐት ረዳቶችም ተማረኩ። ንጉሥ ኩራማረኩት ዋና ዋናዎቹን መርጦ እንዲገደሉ አዘዘ።

4ኛውና የመጨረሻው ኢትዮጵያ ከቱርክ አቶማን ጋራ ያደረገችው ጦር ፍልሚያ በአጼ መላከ ሰንደ ዘመነ መንግሥት በ1589 ዓ.ም. ነበረ። ወልደ አዙም የተባለው በአለቃው በትግራይ መኮንን ዳህራበት ላይ ዐመጸ ተነስቶ ብዙ ባለሥልጣኖችን ገደሉ ቱርኮች ባለፈው ዘመናት ሲቆጣጠሯቸው ሞክረው የነበረ የባሕር ምድር ግዛቶች ለመያዝ በነበራቸው ምኞት ጥቃት ባካሄዱበት ወቅት በመጀሪያ ሲዋጋቸው ከቆየ በኋላ በመጨረሻ ግን የቀድሞ የባሕር ንጋሽ ምሳሌ በመከተል ለቱርክ ፖሻ አጁን በጥቶ የባሕር ንጋሽ ሹመት ከቱርኮች ተቀብሎ ከንጉሡ የተላከው ጦር ለመቋቋም ችሎ ነበረ። በአዲሱ ባሕር ንጋሽ ረዳትነት ቱርኮች ድባርዋን ለመያዝ ችለው ነበር።

ዳህራበት ሊያስወጣቸው ሞክሮ ከባድ ሽንፈት ደርሶበታል፤ ቱርኮች መረብን ተሻግረው ትግራይ ገብተው ነበር። ሕዝቡ ግን ተዋግቶ መልሷቸዋል። በሚመለሰበት ጊዜ ዑቅባ ሚካኤል የሚባለው መረብ አጠገብ ባደረገባቸው ደፈጣ ስለተከበበ ከተያዙት 7 ቱርኮች ተሰለቡ፤ ሁለት የበላይ ሹሞች ተገደሉ፤ ንጉሡ ዑቅባ ሚካኤል በፈጸመው ጀግንነት ተደሰቱ የባሕር ንጋሽ ሹመት ሰጠው። ዜናው በመላው ኢትዮጵያ እንደምሳሌ ተተረተ። ፖሻው የንጉሡ መምጣት ሳይጠብቅ ወደ ምፅዋ ሄደ፤ ንጉሡ ግን ቱርኮችን ለዘለዓለም ከኢትዮጵያ መሬት መንቅሎ ለማውጣት ምፅዋ ድረስ ሄደ። ቱርኮች በምሽጋቸው እና ከባሕር ከመርከባቸው ሆነው ተከላከሉ። ብዙ ቱርኮች ታስሩ ሁሉም አግሮቻቸውና እጆቻቸውን ተቆረጡ። ፖሻው ራሱ ቆስሎ ነበረ፤ ሰውነቱ ብረት ለብሶ ሰለነበረ ግን ከሞት ተረፈ። የኢትዮጵያ ሠራዊት ስንቅ ስላለቀበት ወደ ደጋ መመለስ ግድ ሆነበት። የኢትዮጵያ ንጉሥ ከበባው አንዳቆመ ወዲያውኑ ቱርኮች የአርቅ ውይይት ጀመሩ። ንጉሡ ከጂውን ወልደ አዙምን ማሳደድ ጀመረ። ዑቅባ ሚካኤል ተከታትሎ ይዞ ገደለው። ንጉሡ ድባርዋ እንደተመለሰ እጅግ በማም ብዙ ሰጠታዎች ኪሻው የተላኩ አገኘ። አጼ መላከ ሰንደ ለጠታዎችን ተቀበለ እርቅና ሰላምም ወረደ። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ግንኙውም የቱርኮች መስፋፋት ምኞት ለሁሉ ጊዜ አከተመ። ኢትዮጵያ ከባሕር ጠረፎች የሚመጡባት ሁሉ የታላቁ የቱርክ መንግሥት ወረራዎች እንዲሁም በሃይማኖት መነሻ በምሥራቅ ሱልጣኖች የሚሬኝም ጭምር የእርስ በእርስ ጦርነቶች ከብዙ ዘመናት ፈተና በኋላ በአሸናፊነት ተወጥታለች።

11. የኦሮሞዎች መስፋፋት ክስተት

ኢትዮጵያ ልታሸንፈው ያልቻለችው ሌላ ጠላት ነበራት፤ ይኸውም የኦሮሞ የመስፋፋት ክስተት ነው። የኦሮሞ ከደቡብ ወደ መሐል ሀገር መስፋፋት ምክንያት ኢትዮጵያ ከባድ ውድቀት ደርሶባታል። የደቡብ ምዕራብና የምሥራቅ ክፍላተ ሀገሮቿ እንድታጣ ተገደደች። በነዚህ ክፍላተ ሀገሮች ይኖሩ የነበሩ ማንነታቸው በውል የማይታወቁ በአጠቃላይ ሲዳማ ወይንም አማራ ብለን የምንጠራቸው ሕዝቦች ከምድረ ገፅ ጠፍቷል፤ ባይጠፉም ቋንቋቸው፤ ባሕላቸው፤ ታሪካቸውና ስማቸው ጠፍቶ በኦሮሞ ተተክቷል። አሁን ኦሮሞ ሕዝብ ተብለው ስፍሮባቸው የሚገኙ መሬቶች ኦሮሞ ከመምጣታቸው በፊት ባዶ መሬት አልነበሩም፤ አማራ፤ ጉራጌ፤ ሌሎችም አሁን የደቡብ ሕዝቦች ብለን የምንጠራቸው ወይንም ሌሎች የጠፉት ስፍራውባቸው ነበረ።። ኦሮሞ ከመጡ በኋላ ግን በሙሉ ተገደሉ ለማለትም አይቻልም። ከኦሮሞ ጋራ ተቀላቅለው ዘራቸው ጠፋ ለማለት ይቀላል። ኦሮሞዎች እንደ ይፋት ወይንም እንደ አዳል መንግሥት አልነበራቸውም፤ ወረራ ፈጽመዋል ለማለትም አይቻልም። ኦሮሞዎች ያካሄዱት የመሬት ማስፋፋት ነው፤ ሰፈራ ነው። ኦሮሞዎች መንግሥት ስላልነበራቸው እንድ መሪ አልነበራቸውም። በይፋት፤ በአዳልና በቱርኮች ያልተሸፈነ የኢትዮጵያ መንግሥት በኦሮሞች ግን ተሸንፏል። ኦሮሞች እንደሌሎች ሕዝቦች ለምሳሌ ሶማሌ በጉሳ ተከፋፍለው እርስ በእርሳቸው የሚጣሉ አይደሉም። የኢትዮጵያ መንግሥት በሥልጣን ሹክቻ ወይንም በሐይማኖት ምክንያት ከግራኝ ከሐረር አስላማዊ መንግሥት ያደረጋቸው እርስ በእርስ ጦርነቶቹ ዘመዳከሙ ኦሮሞዎች ተጠቅመውበት ወደ ባሰ ውድቀት እንዲደርስ አድርገውታል። ኦሮሞች አዲስ መሬት ለመያዝ እንደ ማዕበል ወደ ፊት ከመገስገስ በቀር የታወቀ ዓላማ አልነበራቸውም። መንግሥት ለማቋቋምም ዓላማ አልነበራቸውም፤ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ ስልጣን ለማጋራት ወይንም የነበረውን መንግሥት ገልብጠው ስልጣን ለመያዝ ዓላማ አልነበራቸውም። በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ጥላቻ አንዳልነበራቸው የሚያስረዳ አንዳንድ ነገሥታት ለውትድርና እየመለመሉ ይጠቀመባቸው እንደነበሩ ብዙ ጊዜ ያጋጥም እንደነበረ ተዘግቧል።

ኤውሮጳውያን ታሪክ ጸሐፊዎች የኢትዮጵያ ሕዝብ በጎሳና በቋንቋ ሊከፋፍሉት ኦሮሞችን ደቡባውያን የኩሽ ዘሮች ይመድቧቸዋል። የሀገራችን ታሪክ ጸሐፊዎችም የዚሁ ዓይነት አከፋፈል ነው የሚከተሉት። ይህ አስራር ቋንቋና ጎሳን ለይቶ ለማወቅ ባለመቻሉ የአንድ ሰው ወይም ሕዝብ ማንነት ቋንቋው ብቸኛ መለክያ በመውሰድ የሚደረገው የዘር አመዳደብ ዘዴ ነው። በቋንቋው ብቻ የአንድ ሕዝብ ማንነት መመደብ ግን ትክክለኛው ሊሆን አይችልም። በሰሜን ኢትዮጵያ ሴማዊ የተባለው የግእዝ ቋንቋ ከመስፋፋቱ በፊት ከዚያም በኋላ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እየፈለሰ ስለሚሄድ ቋንቋውን ትቶ አዲስ የሰፈረበት ቦታ ቋንቋና ባሕል እንደሚይዝ የታወቀ ነው። ኦሮሞችም ከዚህ ሕግ አይወጡም። ቅድመ ታሪክ ኦሮሞዎች የሰፈሩበት ቦታ በሰሜን በደቡብ ወይንም በመሐል በሞሯቸ ኢትዮጵያ ይሁን አይታወቅም። አቶ ተክለ ፃዲቅ መኩሪያ በኢትዮጵያ ታሪክ እንደኛ መጸሐፍ ገጽ 30 የሌሎች ጸሐፊዎች ታሪክ በመጥቀስ ከኩፊያ እስከ ኢርትራ ባሕር ተበታትኖ የነበረ ሕዝባችን የሰም ዝርዝር ሲሰጥ በቁጥር 18 ጋሊ የተባለውን ጋላ ብለው ተርጉሞታል። መሠረት የሌለው አተረጓጎም

ነው ለግለት እይቻልም። የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ ሆኖ ያገለገል የነበረው ጉብዩዊው የክርስትና ሐይማኖት ተከታይ ስሙ ቡትሮስ ጋሊ ሲሆን ይኸውም ሰግቸው ወደ ዓረብኛ ያልቀየሩ የጥንት ጉብዩውያን ስም ሲሆን ይችላል። ኢጣሊያዊው የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊ ኮንቲ ሮሲኒ ስለጥንታውያን ጉብፅ ጥልቅ ምርምር ያደረጉ የኤውሮጳ ታሪክ ፀሐፊዎች የሰጡት እስተያየት በመጸሐፉ እንደተገለጸው ኢልሚ አርግ (የአርግ ልጆች) ወይንም የአሮሞ ልጆች ግለት መሆኑን የሚል ትርጉም ተሰጥቷል ይሂም ትርጉም የተሰጠው ቱት ሞሲስና ሌሎችም የጉብፅ ፈርኦኖች ቤሐውልቶቻቸው ስለእስገበሯቸው የኩሽ ዘሮች ስም ዝርዝር ተቀርፆ በተገኙ ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ ነው።

ኮንቲ ሮሲኒ እስተግግኝ ታሪክነቱ በግሉ ቢክደውም ባለሞያዎች የሰጡት እስተያየት በደፈናው ሐሰት ነው ለግለት አይቻልም። አሮሞዎች ከ1520 ዓ.ም. በፊት ወደ መሐል ኢትዮጵያ ከመንቀሳቀሳቸው በፊት ደቡብ ኢትዮጵያ ቦረና አካባቢና ከኒያ ብቻ ሰፍረው እንደነበሩ የተረጋገጠ ነው። አሮሞች ሰፍረውበት የነበረ ዋናው ማእከል ዋላቡ ከአብያተ ሀይቅ በስተምሥራቅ የሚገኘው ተራራ ነው ተብሏል። በዚህ እንድ አውራጃ የማያሀል መሬት ሰፍረው ተውሰነው ለብዙ ዓመታት ይኖሩ የነበሩ አሮሞዎች በጥቂት ዓመታት ውስጥ መላው ኢትዮጵያን ማጥለቅለቃቸው በየትም የዓለም ከፍሎች ያልታየ ታአምራዊ ክስተት ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት ብዙ ፈተናዎችን አልፎ ቋንቋውን ባሕሉን እና ስልጣኔውን ከሰሜንና ቀይ ባሕር እስክ ሕንድ ውቅያኖስ ምንባሳ በሚያስፋፋበት ጊዜ፣ አንድ መቶ መንግሥታት ወይንም 35 መንግሥታት ወዘተ... በስሩ ለሉት ይባል የነበረው፣ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የአንድ አውራጃ ሕዝብ ብዛት እንኪን ያልነበራቸው አሮሞዎች ከስር መሠረቱ ሊያንኮታኩቱት የቻሉት በጦር መግሪያ ተጠቅመው እይደለም። ጋዳ ወይም ጉዲፈቻ ቡተባለው የአስተዳደር ስልታቸው ተጠቅመው ነው። አሮሞዎች ለብዙ ዘመናት ከጣንቱ ጎሳዎች በጉርብትና በኖሩበት ጊዜ ጋዳ ቦተባለው የዕድሜ ክልል መሠረት የሚያደርግ የአስተዳደር ዘዴ ከእነሱ በመውሰድ አስፋፍተውታል። በዚህ ፀባያቸው ከሌሎች የካም ዘሮች ይለያሉ። ሌሎች የካም ዘሮች ሁሉ አርስ በእርሳቸው የሚለያዩ በሰጋ ዝምድና ሲሆን አሮሞዎች ግን እንደ ኮኩብ ቆጠራ የአንድ ዕድሜ ክልል የሆኑ ሰዎች በአንድ ወገን ይመደባሉ። ጋዳ ብዙ ደረጃ አለው 1. ዳባሌ 2. ፎሌ 3. ቆንዳዳ 4. ዶሪ 5. ሉባ እየተባሉ ይጠራሉ። የጋዳ ደጋፊዎች ዲሞክራሲ አስተዳደር ነው ይሉታል። ነገር ግን አጅግ ኋላ ቀር የሆነ አስተደደር ዘዴ ነው። አሮሞዎች ወደ ሞሐል ሀገር ከመሰራጨታቸው በፊት የሐግኖት መሪዎቻቸውና ጠንቋዮቻቸው አባ ሙዳ ይባሉ ነበር። ሁሰት አባ ሙዳዎች ነበሩ። አንዱ በዳሉ ጫካ በገናሌ ወንዝ አጠገብ ሁለተኛው በዋላቡ ተራራ። በኋላ ጊዜ አሮሞዎች ወደ መሐል ሀገር ዘልቀው ገብተው የባሌን መንግሥት በተቆጣጠሩበት ጊዜ የአባ ሙዳ መናሪያ የአቡል ታሲን ተራራ ጫፍ ታዋቂው ቪክ ይኖርበትና ያረፈበት ሆነ። የሁሰቱ እምነቶች ተዋሕደው የአሮሞዎች ሁሉ ቅዱስ ቦታ ማእከል ለመሆን በቅተዋል። አሮሞዎች ለዘመናት በሰላም በደስታ ይኖርበት ከነበሩ ሰፈራቸው ለቀው ወደ መሐል ኢትዮጵያ እንዲሰራጩ ምክንያት የሆኗቸው ሶማሌዎች ናቸው ተብሏል። ዐግራኝ ጦርነት ጊዜ አሮሞች አይታወቁም ስለነበረ ግራኝ ለውትድርና ሊመለምላቸው እሳሰቡም። ግራኝ ለተዋጊነት የተጠቀመባቸው ሶማሌዎች ብቻ ነበሩ። መጠነ ሰፊ የሆነ የቀንድ ከብቶች፣ ወርቅ የጦር መግሪያና ባሮች

ከክርስቲያን ኢትዮጵያ ሶማሌዎች በግራኝ ጦርነት ጊዜ ዘርፈው ያመጧቸው በግየታቸው አሮሞዎች በሶማሌዎች ከመሬታቸው ስለተፈናቀሉ ወደ መሐል ኢትዮጵያ እንደ ባሕር ማእከል ተሰራጩ። አሮሞዎች ከመምጣታቸው በፊት ምዕራብ ወለጋ አንፈሉ ተብሎ ይጠራ ነበረ። ወሎም የቀድሞ ስሙ አንጎት ነበረ ወዘተ... ጋፋት፣ ትልቁ ዳሞት፣ ዳሞር፣ ፋጢጋር፣ ግራ፣ አዳል፣ ወዘተ ተብለው ይጠሩ የነበሩ ክፍለተ ሀገሮች ወይንም መንግሥታት ታሪካቸውና ሰግቸው ቋንቋቸውና ባሕላቸው ጠፍቷል፣ በአሮሞ ቋንቋና ባሕል ተተክቷል ወይንም ዘራቸው በሙሉ ጠፍቷል።

ይህ ታሪክ የተፈጸመው በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሲሆን አውሬዎች እንኪን ዘራቸው እንዳይጠፋ እንክብካቤ ይደረግላቸዋል። በዛሬ እንድ መቶ ዓመት ዳግማዊ አጼ ሚኒልክ የቀድሞ አባቶቻችን የገነቧት የኢትዮጵያ ግዛት እንድነት ባስከበረበት ጊዜ እንደገና ወደ ኢትዮጵያ የተቀላቀሉት ከፍለ ሀገሮች ቋንቋቸው እና ባሕላቸው እንኪን ባይቻል የቀድሞ ሰግቸው እንዲያገኙ ግድረግ ይገባው ነበር። አጼ ምኒልክ ይሽንን ባለግድረጉ የአሮሞ ቋንቋና ባሕል እንዳይኖ በግድረጉ የዛሬ እንደንድ አሮሞዎች አጼ ምኒልክን በወረራ እንደያዟቸው ሲቆጥሱ ይታያሉ። አጼ ሚኒልክ ያዘመተው የአግራ የአሮሞ የትግሬ ወዘተ... ያሉበት የኢትዮጵያ ሠራዊትም ነፍጠኛ እየተባለ ስም ግተፋትና ታሪካዊ ቅዱስ ዓላግውና ተልኮው የተወግበት እድናቆትና ምስጋና ሊገባው የኢትዮጵያ ጠላቶች የሚያናፍሱትን ወሬ በግስተጋባት ይገኛሉ። ዛሬ አሮሞዎች የሰፈሩባቸው ከፍላተ ሀገሮች ምሥራቅ ደቡብና ምዕራብ ሸዋ፣ ሐረርጌ፣ አርሲ፣ ባሌ፣ ወለጋ፣ ኢሉባብር እና ጅግ ባዶ መሬት አልነበሩም። ቅድመ አሮሞ የነበሩ ሕዝቦች በግዲታ የአሮሞ ቋንቋ በጉዲፈቻ በመውሰድ አሮሞ ተባሉ አንጂ በዘር አሮሞ አይደሉም። ስለዚህ አሮሞ ቋንቋ ነው እንጂ ዘር አይደለም። በዘር ከሆነ አሮሞ የአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጎሳዎች በውስጡ ያቀፈ ነው። ስለዚህ አሮሞ ተናጋሪ የሆኑት የሁሉም የኢትዮጵያ ጎሳዎች ስለሆኑ በኢትዮጵያ ጎሳዎች ላይ ጥላቻና ቅራኔ ሊኖራቸው አይገባም። አሮሞ ሳይታሰብ ቋንቋውን በመላ ኢትዮጵያ አማርኛ ያልቻለው በተአምር ሊያስፋፋ ችሏል። ይህ በመሆኑ አሮሞዎች ሊደሰቱ ይገባቸዋል አንጂ በግንባር ቀደም በቋንቋችን እንዳንጠቀም ያሰፋት መንግሥታት ጨቆኑኝ ለግለት አይችሉም። በአሮሞ ፋንታ አማርኛ ከዳር እስከዳር ባለመስፋፋቱ ቁጭት ሊኖራቸው የሚገባ አማርኛ ተናጋሪ ብቻ ሳይሆኑ ሀገሩን የሚወድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሊያድርበት ይገባል። በአሮሞ መሬታቸውን ተነጥቀው ባሕላቸውንና ቋንቋቸውን ያጡ ሕዝቦችም በዕድላቸው ሊያዝኑ ይችላሉ። የአሮሞ ሕዝብ ግን ከግንኛውም የኢትዮጵያ ሕዝብ በላይ መብቱ የተጠበቀለት ስለሆነ አሁን ሲነገር እንደምንሰማው መብቴ አልተከበረም ብሎ ቅሬታ ማሰማት ባለፈው ታሪካችን እንፃር ተቀባይነት የለውም። በግንኛውም ጦርነት እንደሚያጋጥም የሚኒልክ ሠራዊትም በሰላማዊ ሰዎች ላይ ጭፍጨፋ ተፈጽሞ ይሆናል፣ አሮሞዎች ከፈጸሙት ጭፍጨፋ ግን የሚነጻጸር አይደለም። ብዙ የሰው አልቂት የተፈጸመ ወቅት ቢኖርም በሚኒልክ ዘመን ጊዜ ከሁሉ የባሰ በአሮሞዎች አካባቢ የተደረጉ ጦርነቶች አልነበረም። ከሁሉ የባሰ ጭፍጨፋ የተፈጸመው አሮሞዎች እንደ ጅግ አባጅፋር የተካፈሉበት በከፋ ንፋሙ ነገሥት መንግሥት ዘመን ጊዜ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ብዙ ቃላቶች ያለአግባብ እንጠቀማለን።

ስለሮሞዎችና በሌሎች ሕዝቦች ያለውና የነበረው ግንኙነቶች ወራሪና ተወራሪ ግርና ተገዥ ብለን ለመጠቀም ብንፈልግ ግን የአሮሞ ሕዝብ ወራሪ ነው እንጂ በሀገሩ ላይ አለተወረረም። ለም መሬት ነጥቆ ከሌሎች በመያዙ

ገዥ ነው አንጂ ተገዢ አይደለም። የአማርኛ ቋንቋ አንኳን የመንግሥት ቋንቋ ሆኖ ያላደረገው ኦሮሞዎች ሌሎች ሕዝቦች ቋንቋቸው ባሕላቸውና ስማቸው አንዲቀየሩ አድርገዋል። አማራ ማለት እንደ ኦሮሞ ቋንቋ ነው አንጂ የጎሳ ስም አይደለም። አማርኛ አንደ ኦሮምኛ ብዙ ጎሳዎች የሚጠቀሙበት ቋንቋ ነው። አብዛኛው ዛሬ አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ዘራቸው አገው ነው፣ አገው ባይሆኑም ክትግራይ የመጡ ናቸው።

ኦሮሞኛ ቋንቋ እየተናገሩ ኦሮሞ አንዳልሆኑ ከሚያምኑ ሕዝቦች የወርጂ በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። ወርጂ ከትግራይ አንደሚወሰዱ ያምናሉ።[1] በንጉሥ ዐምደ ፅዮን ዘመን ከአፋር ኗሪዎች እስላሞች ከሌሎች እስላሞችም ጋራ ሆነው ፀረ ክርስቲያን የኢትዮጵያ መንግሥት ግንባር የፈጠሩ ተብለው ተጠቅሰዋል።[2] ዘራቸው ከአፋር ወይንም ከሶማሌ አይደሉም፣ ጉራጌዎች ከትግራይ መጣን እንደሚሉ፣ እንደዚሁም በሲዳማ የነበሩ የነገሥታት ዘራቸው ከትግራይ መሆኑን እንደሚያምኑ፣ በተመሣሣይ ወርጂ ከትግራይ መምጣታቸው ይናገራሉ፡ በአዋሽ ከኦሮሞች ሚታ በቾ ይዋሰናሉ።

ኦሮሞች በታሪካቸው በሶማሌዎች ከሰሜን ወደ ደቡብ እንዲፈልሱ ተደርገዋል፣ በባንቱ ከደቡብ ወደ ሰሜን እንዲፈልሱ ተገዷል፣ ቁጥሩም ከ100 ዓመት ባነሰ ጊዜ ከሲዳማ (ደቡብ ሕዝቦች) እና ከአማራ ባደረጉዋቸው ጦርነቶች አሁን የሚኖሩባቸው ለፋፊ መሬቶች ስማግኘት በቅቷል። በመረሻም ጠብመንጃ ታጥቀው ሊዋጉዋቸው ከመጡ አዲሶች የአማራ ወራሪዎች ጋራ ፍጬቤ ይዘው እንኳን ስመከላከል ሳይሞክሩ ነፍጎታቸው ተነጥቀዋል በማሰት ቾሩሲ ሰለ ኦሮሞች መስፋፋት ከሰተት ባሏዊ ገልጸታል[3]። ኦሮሞ ድል የተመቱበት የማሩ ኮሪጅ (Sella Maru) በተባለው ቦታ በራስ ጉበና የሚመራው በኢትዮጵያ ሠራዊት ነው። ራስ ጉበና ጨቦ በኦሮሞች ላይ ጦርነት ገጥሞ ድል ተጉናጽፎ ወደ ጊቤና ምዕራብ ኢትዮጵያ ስመገስገስ መንገድ የከፈተበት ወሳኝ ድል የተጉናጸፈበት ቦታ ነው።

1. ጋዳ አስተዳደር

የኦሮሞና የደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክ ብዙ አይታወቅም። ስለ ኦሮሞ ተጽፎ የሚገኘው ስለ ጋዳ የዕድሜ አስተዳደር ነው። ቾሩሲ እንዳጸፈው ከባንቱ የተወረሰው የጋዳ አስተደደር መሠረት በድሮ ጊዜ አንድ ጉማ በሁለት ዘር የተከፈ 10 የጋዳ ደረጃዎች ነበሩት። አባትና ልጅ በተቃራኒ ጋዳ ሲመደቡ፣ የልጅ ልጅ ከአያቱ ጋራ ይመደባል። እንደዚህ እያለ በየ8 ዓመት አየተቀያየረ 1ኛ ደባለ ከ1 አስከ 8 ዓመት ዕድሜ 2ኛ ፎሌ ከ8 አስከ 16 3ኛ. ቆንዳላ ከ17 አስከ 24 4ኛ ቆራ ከ25 አስከ 28 5ኛ ሉባ ከ29 አስከ 32 6ኛ. ዩባ ከ33 አስከ 40 ተብለው የሚጠሩ ይከፈላሉ። የፖለቲካ ሥልጣን የሚገኘው በግል ችሎታ ሳይሆን በዕድሜ ነው። ልዩ ሥነ ሥርዓት አየተደረገ 8 ዓመት እንደተቈጠረ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ ይዛወራሉ። ይህ ጥንታዊ የጋዳ አስተዳደር ሳይቀየር የቀጠለው በክርስቲያን ኦሮሞች ብቻ ነው፣ አሰልምና የተቀበሉ ግን ጋዳ አስተዳደር ከአምነታቸው ጋራ አልተጣጣመም። በሸዋ የሚኖሩ የኦሮሞ

(1) Cerulli : Etiopia occidentale p. 14
(2) Cerulli : ibd p. 14
(3) Cerulli ibd p. 19

ጉሣዎች ጥንት 10 ጋዳ የነበሩ ለአምስት ሰለተጠቃለሉ አባት ልጅና የልጅ ልጅ ወዘተ ባንድ ይመደባሉ 1ኛ ጂደ 2ኛ አቢቾ 3ኛ. ጉመቢቾ 4ኛ. ሚታ 5ኛ ጉለሌ 6ኛ. አቦራ የሚባሉ በምዕራብና ደቡብ ሸዋ የሚኖሩ የኦሮሞ ጉሣዎች በመሃላቸው ጥቃቅን ልዩነቶች ቢኖራቸውም የጋዳ ስምና ደረጃ ተመሣሣይ ነው። የጋዳ ሰሞች 1ኛ. ሆራታ 2ኛ. ሚቾሌ 3ኛ. ዴሉ 4ኛ. ሮባሌ 5ኛ. ቢርማጂ ተብለው ይጠራሉ። የጋዳ ደረጃዎች 1ኛ. ደባለ 2ኛ. ፎሌ 3ኛ. ቶንዳላ 4ኛ. ዶሪ 5ኛ. ሉባ 6ኛ ዩባ ናቸው። በጂዳ ጉሣዎች ዶሪና ሉባ ለ4 ዓመት ብቻ ስለሚቈዩ የአንድ ደረጃ ንኡስ ክፍል ናቸው። በአቢቾ ጉሣ ዶሪ ቀርቷል፣ 8 ዓመት ሲጨርሱ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ በሚተላለፉበት የሚደረገው ሥነ ሥርዓት ቡታ ይባላል። ዩባ ደረጃ ካላቸው አንዱ ተመርጦ አባ ዳባለ እየተባለ ጋዳ የሚጀምሩ ልጆችን ይህ ለተሰበሰበው ሕዝብ ያቀርባቸዋል። ከሥነ ሥርዓቱ በኋላ ዩባ የሆኑ ሁሉ ይገረዛሉ። ፎሌ ደረጃ ያሉት ሁሉ ጅንጀሮ ቆዳ ፌታቸውን ሽፍነው ፎሮርሳ የተባለው ዱላ ይዘው ይዘዋወራሉ። ከመሃከላቸው በፎሮርሳ ዱላ ደብድቦ ከረጫቸው ጉሳ ውስጥ አንድ ፍየል ወይንም አንድ በግ መዝረፍ የቻለ "ሐዩ" ተብሎ አስቃቾው ይሾማል። የተዘረፈው በግ ወይንም ፍየል ወዲያውኑ ተሰብስበው ይበሉታል። ዶሪ ወደ ሉባ ደረጃ ሲሸጋገሩ የሚደረገው ቡታ በራ አርደው ሥነ ሥርዓት አለቃቾው ሐዩን ይመርጡና፣ አሱም ጠጉሩ ተላጭቶ፣ ወተት ፈሰበት፣ በሉባ ደባለ እጅ ፈቱ በበራ ቆዳ ማንባርና ቀንድ ይሸፈናል፣ እንደ በራም ያርሃል። ይህ ሽፋን ሒርቡ ይባላል። ጉሣቾውን ለመምራት የፖለቲካ ሥልጣን የሚሰጣቾው ዶሪ ወይንም ሉባ ደረጃ ያላቾው ናቾው። 5ቱ ደረጃዎች የጉሣ አባላት ለጋብቻ ዘር ለመቀጠር ይጠቀመባታል። ከ5 ትውልድ በላይ ካልተቈጠረ ጋብቻ አይፈቀድም።

ኦሮሞች አዲ ምኒልክ ከሞቱ ጋራ ከግዋሐዱ በፊት የ365 ቀናት የዓመት መቀጠሪያ ነበራቾው። ዓመቱ የሚጀምረው በመስቀል ስለሆነ የጥንት ከኢትዮጵያ አንድነታቾው የሚያሳይ ምልክት ነው። 1.ሙዳ መስከረም 2 ሐደለቾ ነሐስ ዳዋ ጥቅምት 4 ጥር ጥሪ፣ ጎዳር 5 ፋርማ (Furma) የካቲት 6 ቪያነ ሰኔ 7 ቦሩ ቪያነ ሐምሌ።
በሶማሌም የዓመት መጀመሪያ ቀን አሳት በማንደድ ይከበራል።[1]

ኦሮሞች በዙቋላ የሚገኘውን የአቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ገዳም አቦ (አቡነ) በማለት ያከብሩታል። አሶ የሚል አጠራር በሁሉም የተለመደ ነው። እንደዚሁም በፌንፌኔ ጠበል ለአቦ ከብር አየተባለ በየዓመቱ በውሃው ውስጥ የፍየል ወተት ማፍሰስ፣ የወፎች ጠጉር ማበርከት ልምድ ነበረ። በተራሮችና በምንጮች አምነት ማዘውተር ከጣአት አምነት የመጣ ነው ቢባልም፣ ከርስቲያንም በጣአት አምነት የተተካ ስለሆነ የቀደምት አባቶቻችን የኢትዮጵያ የጋራ የክርስቲያን አምነት ምልክት መሆን አለበት[2]።

2. ኦሮሞና ሲዳማ

በኦሮሞች ወረራ ዘራቸውና ቋንቋቸው የጠፉ የሲዳማ ሕዝቦች የመጨረሻዎቹ ከአፄ ምኒልክ ዘመን በፊት በጅማ አካባቢ ብዙ ኦሮምኛ ያልሆኑ ቃላቶች ይቀላቀላሉ። ንጉሥ ለማለት በኦሮምኛ ሞቲ ሲሆን በልማድ ግን ጉይታ ተብሎ ይጠራል፣ ጉይታም ወደ ንፍታ ተቀይረዋል 2 አልጋ

(1) Cerulli ibd p 58
(2) Cerulli ibd p 59

ወራሽ ከሲዳማ ቋንቋ ተወስዶ ዶናቾ ተብሉ ይጠራል። 3 የንጉሡ ሚስት ከሲዳማ ቋንቋ ተወስዶ ጌን ተብላ ትጠራለች። በጅማ አካባቢ የነበሩ ነገሥታት አንዳንድ ጉግሶች በጅምላ እንደ ባሪያ የመቱጠር ባሕል ነበራቸው። ጅማ አባ ጅፋር ይህ ባሕል ተቀብሉ አጋንና በሥራ ላይ ያዋለው በጃንጀሮ ሕዝብ ላይ ነው። ጅማ አባ ጅፋር አዬ ምኒልክ ምዕራብ ኢትዮጵያን በምይዝበት ጊዜ ከጦሩ ጋራ በመተባበሩ ውለታ ለመክፈል ጃንጀሮ ከጦቱ ጋራ እንዲያጠቃልለው ተሰጥቶት ነበር። በዚሁ መብት ለመጠቀም ጅማ አባ ጅፋር የጃንጀሮ ሕዝብ የእሱ ባሪያ ሕዝብ መሆኑን አውጆ ግማሹ በክልሉ እየኖረ የሚሸጥ የሚሰወጥ ሲያደርገው ግማሹ በባርነት መልክ ወደ ምዕራብ ጅማ እንዲዛወር ተገዷል። ይህ ሁኔታ እይቶ ሀገሪ ፕሮው የነበረው ራስ ተሰማ የጃንጀሮ ሕዝብ አስተዳደር ከአባ ጅፋር ነጥቆ በአንድ እማራ እንዲስተዳደር ሥር ሰማድረግ ግድ ሆነበት። 5 ጅማ አባ ጅፋር ወሮ ይዘ ከማዝ የቀሰቀላቸው የሲዳማ መንግሥታት የመጪረሻ ቦሻ ነው። ስሙ ቀይሮ ግን ጋና ተብሉ ተሰይሞ የጅማ ከፍሰ ሀገር አካል ሆነዋል። ቦሻ ከከፋ ተመሣሣይ ጉግ ሲዳማ ናቸው፤ ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ሆነዋል፤ ቋንቋቸውና እርምዳ። በጅማ ከተገዙ ጀምሮ ሁሉም የእስልምና ሃይማኖት ተቀብሏል የቁድሞ የቦሻ ነገሥታት ወራሾች ከፈል እሰረኛ በመሆን ጅረን ኩተማ (ጅማ ከተማ) አጠገብ እንዲቀመጡ ተገዷል። ሰማቸው አባ ቡሽያን ብሳሲዩ ይባላሉ። የቦሻ ነገሥታት ዘር ሐረግ ለከፋ፣ ለሚና ለአንፈሉ ነገሥታት የሚሆኑ ሰዎች የሰጡ ናቸው።

6 የጅማ ወሰን መዝሊያ በሲዳማ አጠራር ከሳ ይባላል፤ ነፃ መንግሥታት በነበሩ ጊዜም ገለልተኛ በወሰናቸው የሚገኘው መሬት "ሞጎ" የተባለ ነበረ።

7 ጅማ ሲሉችም ድሮ የእርሞ ነፃ መንግሥታት የነበሩ የሚስተዳደሩ ከሲዳማ የተወሰደ በዘውድ አዝዝ ስለሆነ የጋዳ አስተዳደር አሰራር ጨርሶ ባይቀርም ንጉሡ የግይሾማቸው ባለሥልጣናት በሕዝብ ብቻ የሚመረጡ ሲኖሩ ሰለማይችሉ የጋዳ አሰራር ከአዲሱ ሥርዓት መጣጣም ግድ ሆኖበት ነበር። የጋዳ ደረጃዎች ሰሁለት ብቻ ተቀንሱ ራባና ሉባ የሚባሉ። ጋዳ የሚደረጁም በጉግ መሆኑ ቀርቶ በመንደር ነበር።

8 የጅማ እርሞች እስልምና ሃይማኖት የተቀበሉ በቅርብ ጊዜ ነው፤ ባለፈው መቶ ዘመን አጋማሽ ነው፤ ሊቀበሉ የቻሉም ንጉሦቸው በወርጂና በዳሪታ የጉንደር እስላሞች ነጋዲዎች ተሰብኮ በመጀመሪያ እስልምና ሲቀበል፤ ዜጎቹም በእስላሞች የታረደ ሥጋ እንዲበሉ ሰላስገደጃቸው ነው። ግንኛው ስው ያረደው ሥጋ መብላት የዝትተኛ ዘሮች ምልክት ይቁጠር ስለነበረ ግዲታ እስላሞች መሆን ነበረባቸው። እስካሁን ድረስ የጅማ እስላሞች መሰያ የሆነው እንደ ክርስቲያኖች ጠላና ጠጅ መጠጣታቸውና ሚት አለማዘውተራቸው ነው።

9 ጅማ በእርሞች ከመያዙ በፊት ከከፋ ሕዝብ ተመሣሣይ ዘር የሆኑ የሲዳማ ሕዝቦች በንጉሡ አዝዝ የሚስተዳደሩ ይኖሩበት ነበር[1]። እርሞች ከተድሞ ነዋሪዮች ከሲዳማ ተምረው የጋዳ አስተዳደር አሰቀርተው የዘውድ አዝዝ ተቀበሉ። አንዳንድ የእርሞ የጉግ መሪ የሀገር መሪ (ንጉሥ) ከአነሱ ጉግ ብቻ እንዲሆን ከመቻላቸውም በላይ፣ ከሕዝብ የሚመረጥም ቢጋዳ ሳይሆን በውርስ ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ አደረጉ። የዘህም ምሳሌ የታየው በሊያካ ቀለም ሞቲ ተብሉ የሚጠራ ነበር፣ በሕዝብ የሚመረጠው ግን ሊያካ ዋዩ ይባል ነበር (Lieca wayou)

(1) Cerulli ibd p 91

10 ከላ በከፋ ቋንቋ የቤት በር ሲሆን እርሞች ግን፣ የነበሩ መንግሥታት ወሰን ሰማመልከት ብቻ ይጠቀመብት ነበር።

11 በእርሞች ለሲቶች ሥልጣን መስጠት ልምድ አልነበረም፤ ከሲዳማ ተምረው ግን ሴቶች ሥልጣን ተሰጧቸው "ጊን" ጊታ ንግሥት ተባሉ። መስፍን፣ አልጋ ወራሽም ከሲዳማ ተወስዶ ነውቲ፣ ዳኛ "ወደ ደንዞ" "ዶንዲዮ" "ዶናጂዮ" እየተለወጠ በከፋ በ ሚጫ በአንፌሉ መሰፍን ለማት የሚጠቀመብት ነበር።

12 በሰው ስም ብቻ ሳይሆን ከሲዳማ የተወረሱ በሀገርና በቦታ ስሞችም እርሞች ሲጠቀመብት ይታያሉ። የቦሰ ተራራ (ጅማ የሚገኘው) በሾ ከሚባለው የከፋ ጉግና ቦሺያ ከሚባለው የሲዳማ መንግሥት የተወሰደ ነው። ግና የሚባል ሰፈር በጅማና በከፋ አሉ። በጅማ ሳራዶ ተራራና ሳደሮ ወረዳ ሲኖር በከፋ ሺራይ ወረዳ አሰ። ጌሼ ወረዳ በጅማ ሲኖር በከፋ ጌሽ አሰ። በደቡባዊ ጅማ ሰግጸ ተብሉ የሚጠራ ወረዳ በከፋ ሺየማዶ የሚባል አሰ። የሲሙ ዋና ኩተማ ኮሰ ሲሆን በከፋም ኮሺየ የሚጠራ አሰ። የሊሙ ሳፓ ኩተማ ሲኖር በከፋ ሺያፓ አሰ። የእግዚአትን ግርየም መቅደስ በሊሙ ጉዶ ግርያም ተብሉ የሚጠሩ ተራራ ሲኖር ጉዶ ግሰት በከፋ ተራራ ግሰት ነው። የጉግ መንግሥት የነበረው ስም በከፋ የአንድ ወንዝ ስም ነው። በጉግ የአጋር መንደር ሲኖር በከፋም አጋር የሚባል መንደር አሰ። በጅማ የሚገኘው ያቦ ወንዝ ከከፋ ያቦ ዘባባ የተወሰደ ነው። የጌራ ወና ኩተማ የነበራቸው ቹራ በከፋ ሰመ ጥሩ ሺፒናዎ የናረበት የተወሰደ ቦታ አሰ። እንደራቻ የሰው ስም በጌራ ዋና ኩተማ አጠገብ የሚገኘው ቦታ የከፋና ሚጫ ዋና ኩተማ ስም ነው። በጅማ የኪየቺዮ ጠበል ሲኖር፣ በከፋም ኪየሺዮ ፍል ውሃ ጠበል ይገኛል። ያንጋቺያ የሚባሰው የጌራ ከከፋ ኢንጋጂያ የመጣ ነው። የጠበቀ ጥናት ቢደረግ ብዙ ሌሉች ሰዎች ሲገኙ ይችላሉ[1]።

ቸሩሲ ከኢትዮጵያውያን አዋቂዮች አገኘሁ ብሉ እንደዘገበው የዛሬዪቱ ጅማ ከልል ሰሚን ምሥራቅ የጃንጀሮ መሐልና ደቡብ ከፍል የቦሻ አነስተኛ ከፍልም የአናሪያ ነበረ። የዛሬዪቱ ቦሻ ገደላገደል በመሆኑ ከሰሚንና ከምዕራብ የመጡባቸው ጠላቶች በመከላከል ሸሽተው የስፈሩበት ይመስላል። ተዋቂው በነበረ የአናሪያ መንግሥት ዛሬ በእርሞች ወረራ ከምድረ ገጽ የጠፋ ይናገረው የነበረ ቋንቋ ይበልጥ ተመሣሣይነት የነበረው ከከፋ ሣይሆን ከቦሻ ቋንቋ ነበረ። እርሞች ወደ ጅማ የመጡበት አቅጣጫ በሚመለከትም ሁሉም በአፈ ታሪክ የሚያረጋግጡት የጅማ እርሞች ከመጪ እርሞች አንድ ክፍል (አንድ ጉግ) መሆናቸውና ከመለጋ ወለል ከሚባለው ቦታ መመጣታቸውን ይናገራሉ። 6ቱ የጅማ ጉግሶች ከመለል ተነስተው ወደ ምሥራቅ አምርተው ግግሾቹ በደቡብ የነበረው የሲዳማ ሀገር በመያዝ የዛሬዪቱ ጅማ መሠረቱ። እርሞች ወደ ጅማ የገቡ በስተሰሜን ከጃንጀሮ የነበረው ጠባብ መተላለፊያ መሆኑን ይጠቁማል። አሁንም ከዳደሌና ድኖ የመጪ ጉግሶች ኩታ ገጠም ይኖሱ፤ ከዚህም ወደ ምዕራብ የወሰጋ ሲያካ ይገኛሉ። ከ6ቱ የጅማ ጉግሶች ወደ ደቡብ ምሥራቅ አትጣጪ ወረራ ያልተካፈሉ እስካሁን ከአባይ እስከ ገዜ ወንዝ ሰፍረው የሚገኙ ጅማ ነቦ 2 ጅማ ሆር 3 ጅማ ራሬ 4 ከግማ ወንዝ የዲደሳ ገባር አካባቢ ጅማ አርጆ ሲሆኑ ሁሉም ከጅማ አባ ጅፋር ዝምድና እንዳላቸው የሚያስታወሱ ናቸው። እርሞች ወደ ጅማ የመጠበት ዓመተ ምህረት በትክክል ባይታወቅም 1567 እና 1568 አዬ መላክ ሰገድ ወደ እናሪያና ቦሻ የመጣበት ጊዜ የንጉሡ ታሪክ

(1) Cerulli ibd p 101 - 2

ፀሐፊ በእነዚህ መንግሥታት ኦሮሞች መገኘታቸው አልመዘገበም፣ ዳሩ ግን በ1703 ዓ.ም. ትልቁ አፄ ኢያሱ ቀዳማዊ ወደ እናሪያ ሲዘምት ሀገሩ በሚጨ ኦሮሞች ተከበ ሰላገኘው በጦር ኃይል ጦርነት በማካሄድ ብቻ መንገዱን በመክፈት ወደ እናሪያ የሲዳማ መንግሥት ሲደርስ ችሏል።

ከ1419 እስከ 1429 ዓ.ም. የነገሠው የአፄ ይስሐቅ ታሪክ ፀሐፊ ቦሻ ለኢትዮጵያ መንግሥት ግብር በወርቅ ከሚከፍሉ ግዛቶች አንዱ እንደነበረ፣ የእናሪያ አዋሳኝ እንደነበረ ስለተዘገበ የድሮ ቦሻ የዛሬ ጅማ በኦሮሞች ሲያዝ ለሙ ጅማ ካካ ነበረ። ካካ በኦሮሞ ቋንቋ በረሩ ማሰት ስለሆነ ሀገሩ በዘራፊዎች እንደተያዘ ያሳያል። ቀጥሎም የአባ ጅፋር ጉሳ ባዲ ስለሚባል ሀገሩ ጅማ ባዲ ተብሎ ይጠራ ነበር። በ1840 በዳባዲ ዘመን (Abbadie) ጅማ በዚሁ ስም ትጠራ ነበር። በመጨረሻም በንጉሣዊ ሰም ጅማ አባ ጅፋር ተብሳ ተጠራች።

ጅማን ለማስገበር የጉጃሙ ንጉሥ ተክለሃይማኖትና የሸዋው ምኒልክ ለውድድር ቀርበው በ1883 በእምባበ ጀኑዋሪ ጦርነት ገጥመው ጉጃም በመሸነፉ ጅማ ወደ ሀገሩ የሚገቡ ነጋዴዎች ምኒልክን በጦር ኃይል መቋቋም አንደማይችል በሰጡት ምክር መሠረት ተሽቀዳድሞ ከንጉሥ ምኒልክ በመስማማት ከሌሎች የኦሮሞ መንግሥታት ተለይቶ ለንጉሥ ምኒልክ መገበር ጀመረ።' በዚህም ምክንያት የውስጥ አስተዳደር ነፃነት (ራስ ገዝ) አግኝቶ በኢትዮጵያ ወታደሮች ሳይያዝ ለመኖር በቅቷል። ሌሎች የኦሮሞ መንግሥታት ግን በሰላም መገበር ባለመፍቀዳቸው በጦር ኃይል ብቻ በምኒልክ ጦር ሊያዙ ችሏል። የጅማ ዋና ኩተማ በድሮ ጊዜ ጂረን ተብሳ ትጠራ ነበር። አሁን ግን ዋና ኩተማዎም ክፍለ ሀገሩም ስሙ ጅማ ተብለው ይጠራሉ። የጅማ አካባቢ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋራ ኩተዋሐደ ጀምሮ ዝኛው የእናሪያ መንግሥት የቀድሞ ስሙ ማግኘት ነበረበት፣ ይህ ባለመደረጉ የኢትዮጵያ መንግሥት ደካማነት ያሳያል። የሲሙ ጉማ እንደ ጅማ ኩቲሳ ወለል ወለጋ የመጡ ናቸው። በቀድሞ ጊዜ የእናሪያ መንግሥት (በክፋ ቋንቋ ኢኖአሪ ቶቶ) ከጉጀብ ወንዝ ዳሪቻ ግራና ቀኝ የሚገኙ መሬቶች ያጠቃልል ነበር። ከእናሪያ ነገሥታት ትልቁ ዝኛው ቪፒናዎ ነበረ። ዋና ኩተማው ቸሪኮ አጠገብ ነበረ። በኋላ ግን በኦሮሞች ስለተሸነፈ ወደ ክፋ ክፍል ጉጀብ ተሰዶ ሄዶ ጨሳ በተባለው ቦታ ጋዋተ ራቪዮ የክፋ ክፍለ ሀገር መቀመጫው አድርጎ ይኖር ነበር። በክፋ መንግሥት ዘመን በኢትዮጵያ አስከተያዘበት ድረስ የእናሪያ ንጉሥ የክብር መጠሪያ ብቻ ሆኖ ቆይቶ ነበረ። የእናሪያ ነገሥታት ወርቅ፣ በስደት የነበሩ የእናሪያ ነገሥታት ከልጅ ወደ የልጅ ልጅ ያስተላልፍ ነበር። የቪፒናዎ ዋና ኩተማ ቸሪኮ የምትገኘው ጌራ ውስጥ ቂያዳ በተባለው ተራራ ሰር ዋራ በተባለው ቦታ የአምልኮት ቅዱስ ቦታ የነበረው አጠገብ ነበረች። ስለዚህ የእናሪያ መንግሥት ግዛት በሲሙ ብቻ የተወሰነ አልነበረም፣ በትክክል ባይታወቅም ሰፊ ግዛት ያጠቃልል እንደነበረ ይገመታል። ቪፒናዎ ክርስቲያን ንጉሥ ኢየሩሳሌምን ለመሳለም የሄደው ከሀገሩ የመጀመሪያ ሰው ነው። ከኢየሩሳሌም ሲመለስ ታቦት ይዞ መጥቷል። ስለ ቪፒናዎ በአፈታሪክ የሚወራ ብዙ ነው። ቪፒናዎ በእናሪያ ቤተክርስቲያን ሰርቷል፣ ከዚህ በኋላ አንድ ትልቅ ዘመቻ ወደ ክፋ አድርገዋል። ቪፒናዎ በመንገድ ሲጓዝ ሌሎች ሰዎች የሚጠቀመብት አይሄድም። ከሠራዊቱ ጋራ ሲሄድ በአቋራጭ መንገድ ይጓዝ ነበር። በጉዞው መሰናክል አያጋጥመውም፣ በወንዞች ሲያልፍ ከመቅጽበት ትልቅ ድልድዮች ሠርቶ ያልፋል። በሰው እግር ለማለፍ የሚዳግቱ ተራራዎች ሲያጋጥሙት በጉራዴው በመስበር ያልፍ ነበር። ዛሬ እንደራቻ አጠገብ በረታ ወንዝ

በጉርጉቶ በቪፒናዎ የተሰራ ቸሩ በተባለው ቦታ ላይ በኩታ ክፍለ ሀገር አንድ ድንጋያማ ተራራ የእናሪያ ንጉሥ በጉራዴ የሰበረው ተመልካች ሁሉ የሚያደንቃቸው ይታያል። ቪፒናዎ ወደ ከፋ በምዕራብ በኩል ገብቶ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አነፀ፣ ከኢየሩሳሌም ያመጣው ታቦትም አረገበት። ከዚህም ወደ ጠቋቁሮች ሀገር ወደ ሻሻ ደርሶ ከዚያ ወዴት እንደሄደ ሳይታወቅ ጠፋ። ይህ እንደ ተረት የሚነገርለት የእናሪያ ንጉሥ ኮንቲ ሮሲኒ በአፄ መላክ ሰገድ ክርስትና የተነሳ የእናሪያ ንጉሥ ሰፐንሓ መሆኑን ትርጉም ሰጥቷታል። በዘሐ ቅዱስ ጊዮርጊስ ታቦት መመሥረቱ እውነት መሆኑን የተረጋገጠ ነው። በታቦቱ ያለው ጽሑፍ በጌራ ወረዳ ይኖር የነበረ ካቶሲክ ቄስ ማሲዮናዊ አባ ለዮን ቀድቶ ሰለወሰደው፣ አንድ ኢጣሊያዊ ምሑር ተርጉሞታል[1] ትልቁ ዳሞት ሳይቀር ሁሉም ሌሎች የሲዳማ መንግሥታት በኦሮሞች ወረራ ፈራርሰው ሲጠፉ በምዕራብ ከሚገኙ ለዘመናት በንጉሣዊ አገዛዝ የሚሰተዳደሩ ብርቱ ትግል አድርጎ ሳይጠፋ መኖር የቻለ የክፋ መንግሥት ብቻ ነው።

የኦሮሞ ሰዎች አንድ አማራ መግደል በራ እንደ መግደል ነው ብለው ሲኩሩ የክፋ ሰዎችም በበኩላቸው አንድ ኦሮሞ መግደል ከብት እንደመግደል ይቁጠራል እያሉ ይዘፍኑ ነበር። የክፋ መንግሥት ሕልውናን ማስጠበቁ ብቻ ሳይሆን የሲዳማ ነገሥታት ዘር የነበሩ በኦሮሞች ሲወረሩ በማቱ በክብር የንጉሥ የክብር ማዕረግ ተሰጧቸው እንዲኖሩ ያደርግ ነበር። ለዚሁም የበቁ የዳሞትና የእናሪያ ነገሣታት ይጠቀሳሉ። ይኸንም የሚያደርግበት ምክንያት የራሱ ዘር የሲዳማ ዘር በመሆናቸውና የማይዘገርጉቱ እምነት ስለነበረው የምዕራብ ሲዳማ መንግሥታት ጠባቂ መሆኑም እምነት ስለነበረው ከአፄ ምኒልክ ሠራዊትም ጭምር ራሱን ሰመከላከል እንደሚችል የነበረው እምነት፣ በኦሮሞች ላይ በነበረው የበላይነት ስሜት ተደፋፍሮ ነው። ይህ በመሆኑ ከፋ በአፄ ምኒልክ ሠራዊት የተሸነፈው ለ17 ዓመት ኩተዋጋ በኋላ ነው። ከፋ ከጥንት ጀምሮ በዘውድ እገዛገ የተመሠረተ መንግሥት መሆኑን በምሳሌነት የሚጠቀስ ነው። ንጉሡ የሚንጀ ጉማ የበላሽ ቤተሰብ ነበረ። የንጉሡ ፈላጭ ቆራጭነት ገደበ የሚወስኑ ደምቦችም ነበሩ። ① የንጉሡ የክብር ዘበኛ አዛዥ የሚሆነው ካታማ ራቪዮ የሚባለው ከዚዮ ጉማ ይመረጣል። ② የጊምቦ ክፍለ ሀገር አስተዳደሪ ከኢርጎ ጉማ ③ የቢታ አስተዳዳሪ ከአማሮ ጉማ ብቻ መመረጥ ነበረባቸው ወዘተ። ሹመቱም የሚሰጠው በልምድ ነበረ፣ ጉማው በሚኖርበት አካባቢ አልነበረም። የክፋ ንጉሥ እንደ መልአክ ይቁጠር ነበር፣ ዜጎቹም ፊቱን ከማየት ይቁጠቡ ነበረ። የመጨረሻም የክፋ ንጉሥ ዘውድ የነበረ አፄ ምኒልክ ለስዊትዘርላንድ ተወላጅ ኢልግ ሰለሰጠው በዙሪያ በሚገኘው በመሐንዲሱ ቤተሰብ ቤት ተቀምጦ ይገኛል። የንጉሡ መቀመጫ (ዋና ኩተማ) ቦንጋ (ቦንጌ ዳቦ Bonghe Dabbo) በተባለው ንጉሡ ለስግይ እግዚአብሔር አምልኮት ያደርግበት በነበረው ተራራ ፊት ለፊት ነበረ። 10 ኪሎ ሜትር ክቦንጋ የሚርቅ በእንደራቻ የክፋ ንጉሥ ሲሳ ሁለተኛ መቀመጫ ነበረው ይህ ቦታ ግን ለውጭ ሰዎች የተከለከለ ነበረ። ንጉሡ የሚሰራው ሥራ ሁሉ ቁጥጥር ይደረግበት ነበር። አታለች የተባለ ሰው ንጉሡ የሚበላውና የሚጠጣው የሚቆጣጠር ነበረ። ንጉሡ ብዙ እንዳይበላም እንዳይጣጣም መከልከል መብት ነበረው። የንጉሡ ሥራዎች የሚከተሉት ነበሩ 1. ሀገረ ገዢዮች መሾም፣ 2. ከውጭ መንግሥታት ጋራ በመልእክተኞች በኩል ግንኙነት ማድረግ፣ 3. የዳኝነት ሥራ፣ የሞት ቅጣት፣

[1] Cerulli ibd p 197

በባርነት የሚሸጥ መብት። በክፉ በተለይ ለባርነት የሚዳረጉ ሰዎች ቁምር፣ ቡዳ ተብለው የሚከሰሱ ሰዎች ናቸው። ዶቾ (Doccio) በተባሉ ቁሶች በኩል ለፍርድ ወደ ንጉሡ ሲቀርቡ ያለ ምንም ሌላ ማስረጃ ይግባኝ የሌለበት ባርያ ተብለው ይፈረድባቸው ነበር። 4. በጦርነት ተሸንፈው ስለተማረኩ ሰዎች ፅ ጣ፣ ንጉሡ ባሪያ እንዲሆኑ ማድረግ ወይንም አለማድረግ መብት ነበረው። ባሪያ ናቸው ከተባሉ ንጉሡ በመየቀ ጊዜ ወደ ውጭ የሚሸጡ ናቸው። የዚሁ ዓይነት ዕድል ያጋጠማቸው ናቸው የሚባሉ ከጊሪ ጉማ የሚመጣሡ፣ ከክፉ ደቡብ የሚገኝ ናቸው፣ ለንጉሡም የገቢ ምንጭ ናቸው፣ ታቲ ናዎ (tate nao) ይባሉ ነበር (የንጉሡ ናአ)። በእርሞ ነገሥታትም ናአ ሞቲ አየተባሉ በታማኝነታቸው ተፈላጊ ነበሩ። 5. ንጉሡ የዝቅተኛ ዘሮች የበላይ ጠባቂ ነበረ፣ እንደ ብረት ቀጥቃጭ ሸክላ ሠሪ (Manna) አዝማሪ፣ ማንጆ (Manjio tato) ማንጆ ታቶ ለንጉሡ ብቻ ወርቅ የሚሠራ ነው። በጂግ አባ ጅፋርም ወርቅ ሰሪ ለንጉሡ ብቻ ነው ወርቅ የሚሠራ 6. ንጉሡ የውጭ ሀገር ሰዎች ጠባቂ ነው፣ ወደ ክፉ የሚገቡ ነጋዴዎች ብቻ ነበሩ። ገበያዎች ለክርስቲያን በበንጋና በካያ ብቻ ነበሩ። በቋሚነት ኗሪ መሆን ለሚፈልጉ አስላሞች 15 ኪሎ ሜትር ርቀት ከካያ በሚገኘው ቶንኮላ በተባለው ቦታ እንዲሰፍሩ ይደረግ ነበር። ክርስቲያን በካሬኛ አሮ በበንጋ ልዩ መንደር ተሰጥቷቸው እንዲሰፍሩ ይደረግ ነበር። አማሮ እንደ ክፉ ጉማ ሆነው የተዋሐዱ የቢታ ክፍለ ሀገር አስተዳደር መብት ያላቸው በድሮ ዘመን ከሰሜን ኢትዮጵያ መጥተው የተዋሐዱ ናቸው። ክፉ ለ4 ትከፈል ነበር፣ 1 በንጋ 2 እናሪያ 3 ክፉ 4 ሐዲያ[1] የክፉ ጉማዎች አስተዳዳሪ ሆነው የሚመረጡ የጣር መደቦችና የማይመረጡ ለሁለት ይከፈሉ ነበር፣ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው 1 ሚንጆ የንጉሡ ዘር 2 ይረንጎ 3 ሂዮ 4 አማሮ 5 አርጎፓ 6 ሚየጠቺዮ የጣዢ መደብ ያልሆኑ ጉማዎች ሂኒማች (Himnimachio) 2 ሂናካሮ (Hinacaro) 3 ሂኒቺዮ (Hinnucio) 4.አዎ 5 ቱራ ነበሩ። መንግሥቱ በጉማ ልዩነት በመሬት ከልል የተከፈለ ነበረ፣ አስተዳዳሪዎች ራቺዮ ይባላሉ (ከአማርኛ ራስ የመጣ ቃል) ከፍለ ሀገሮች 10 ነበሩ ካፌ (Cafe) ጊምቢ፣ ቺያተታሉ፣ ኛቢ ቡተ፣ ቢተ፣ ጋዋተ፣ ጊዮቺየ፣ አዲ። ለቤተመንግሥት ብቻ የተወሰኑ 3 ራቺዮ ነበሩ፣ (ሀ) አዲየ የከብር ዘበኛ ፈረሰኛ (ለ) ቱቺ የንጉሥ ባሪያዎች ሹም (ሐ) ካታሚ የንጉሡ ግዚ ዘብ አዛዥ። ክፉ ከጥንት ጀምሮ ኢትዮጵያ አካል እንደነበረች በክፉ የሚገኙ የክርስትና ሃይማኖት መልክቶች ያስረዳሉ፣ ቤተክርስቲያኖችም ነበሩ።[2] ክፉ ከኢትዮጵያ ተለይታ በኖረችበት ረጅም ዘመናት የጣኦት እምነት ብትከተልም የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ዋና ዋና በዓላት ከማክበር ሕዝቡ አልከለከለውም[3]። የክፉ ንጉሣዊ አገዛዝ የማይናጋ ቀጣይነት እንዲኖረው የሚያደርገው የንጉሡ ፈላጭ ቆራጭነት ሥልጣን ገደብ በማድረግ የሚቆጣጠሩ 6 አባላቱ ያሉት በንጉሡ አማካሪዎች የተደገፈ ስለነበረ ነው፣ እነሱም 1 ጉቺ ራቺዮ የካፊኛ ክርስቲያን ተጠሪ 2 ኩተማ ራቺዮ 3 አደል ራቺዮ ከኡኮ ጉማ 4 አርባቺ ራቺዮ ከአርጋፓ ሐዲ ጉማ ከኡኮ ጉማ 5 አርባቺ ራቺያ ከአርጋፓ ሐዲ ጉማ 6 በንዳ ራቺያ ከአርጋፓ ሐዲ ጉማ 7 አርሶ ራቺያ ከክፉ ማቹዮ ጉማ። ሹመታቸው በምርጫ ሳይሆን በዘር የሚወረስ ነው። የአማካሪዎች የበላይ ሹም ጉቺ ራቺያ ነው። የዚሁ ጉማ መሥራች በጥንት ክፉ የኢትዮጵያ አካል በነበረችበት ጊዜ የክፉ የጦር አዛዥ

(1) Cerulli ibd p 484
(2) A Cecchi : Da Zeila alle Frontiere di Kaffa VI p. 484
(3) A Cecchi ibd p. 486

በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የኩሉና የጉሺ የንጉሥ እንደራሴ ሆኖ ተሾሞ ስለነበረ ነው። የጉሺ ራቺያ ሥልጣን ከፍተኛ ነበረ፣ ንጉሡ ሕግንና የሀገሩ ባሕልን የማያከብር ከሆነ ከሊሎች አባላት ጋራ በመመካከር ንጉሡን ከሥልጣን አውርዶ ተራ ሰው ሊያደርገው ይችላል።[1]

3. ክርስትና በክፉ

ስለ ኢትዮጵያ አርቶዶክስ ሃይማኖት አከባበር ወግና ሥነ ሥርዓት አስታየታቸውን የሚሰጡ የኢጣሊያ ፀሐፊዎች ከጥንት ቅድመ ክርስትና ከነበረው የጣኦት አምልኮቶች ያልተላቀቀ መሆኑን እያሉ ሲጽፉ ይታያሉ። በክፉ ስለነበረው የክርስትና ሃይማኖት በዚሁ መንፈስ አጋንነው ጽፈዋል። ቸኪ በዶዮክ በሚባለው የጣኦት እምነት በክፉ አብዛኛው ሕዝብ የሚያጠቃልል ነው ካለ በኋላ በክፉ ለሰይጣን አምላክም ማምለክ እምነት ስለነበራቸው የተለያዩ ክብቶችን ለመስዋእትነት ያቀርቡላቸው ነበር ብሏል። በጣኦት እማልክቶች ማመን፣ መስዋትነትን ማቅረብ ክፋዎች የክርስትና አምነት ሥነ ሥርዓትንም ከማክበር አይከለክላቸውም ነበር። ከጣኦት አምልኮት በእለክፈኑቱ የሚጠቀስ የጣኦት ቤተመቅደስ ሰዎች (ቄሶች) ቡዳ በተባሉ ሰዎች ሊሊት ወደ ጅብነት የሚለወጡ ናቸው ተብለው ተከሰው ወደ ቄሶች በሚቀርቡበት ጊዜ፣ ቡዳ ናቸው ብለው ከፈረዱባቸው፣ ምስክር ሳያስፈልግ፣ ይግባኝ ባሉለበት ወደ ንጉሡ ቀርበው ባሪያ እንዲሆኑ ይፈረድባቸው ነበር። በዚህ ዓይነት ጌራ ይገኝ በነበረው የካቶሊክ ሚሲዮናዊ ቄስ በአባ ጅን ማት በየዓመቱ ለክፉ ንጉሥ 500 ባርያዎች ያስገኙለት ነበር። ቆቹኪ አባባል በክርስትና ብቻ የሚያምኑ የክፉ ሰዎች በቀር ሌሎች በስም ብቻ ክርስቲያን ናቸው በተግባር አይደሉም። የክርስትና እምነታቸውን የሚገልጹትም 1ኛ. በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፣ በማለት 2ኛ ጸም በማክበር 3 በመገረዝ 4 ወደ ቤተክርስቲያን ሄደው እንደ ገና፣ ሩሲካ ፍልሰታ ወዘተ የመሳሰሉ ዋና ዋና የክርስትና በዓላት በማክበር ሲሆን፣ በሊላ ተግባራቸው ግን ከጣኦት እምላኪዎች የተሻሉ አይደሉም፣ አንደ አስላሞች ብዙ ሚስቶች ያገባሉ በማለት ተችተዋል። በክፉ ቤተክርስቲያኖች በመላው ኢትዮጵያ እንደሚለሩ ዓይነቶች ናቸው፣ በዛፎች የተከበቡ ናቸው፣ የምዕመን መቃብሮችም አሏቸው። ከሁሉ የታወቀ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ነው። በዚሁ ቤተክርስቲያን የጣኦት ዶዮክ አምላክ የሚያምኑም ሳይቀሩ ወደ ጦርነት ከመሄዳቸው በፊት፣ ካፈኞ በሙሉ ለመጸለይና ስለት ለማድረስ ይሄዳሉ። በታቦቱ ያለው በግእዝ የተጻፈ ይሰባቸው ነበር። ክርስትና ክፉ የገባው ምናልባት ከአክሱም ዘመን መንግሥት መሆኑን መገመት አንችላለን። ቸኪ የ18 የክፉ ነገሥታት ሰም ዝርዝር አውጥቷል[2] በ15ኛው ንጉሥ ጋንቺዮ ለ24 ዓመት የነገሠ የማዮ ራቺዮ ጉማ ዘመን መንግሥትን ለመገልበጥ አሲረዋል ተብለው የተከሰሱ 600 ፈረሰኞችና ወታደሮች ተገድለዋል። በ16ኛው ንጉሥ ጋዊርሰር ዘመን ብዙ ክርስቲያኖች ተገድለዋል። 17ኛው ንጉሥ ነገሥት ካም የጋዊ ሃሮ ልጅ ለ13 ዓመት የነገሠ በ1870 የሞተ፣ የዶአከ አምላክ አከራሪ ተከታይ ነበረ፣ እንደ አባቱ ብዙ ክርስቲያኖች ፈጅቷል። 18ኛ ንጉሥ በ1878 በአዶወት የነበረ የ45 ዓመት ጉልማሳ ለሙ ጋሊቶ ጋሊ ጋዎ (Gallito - Galli - Gao) ነበር። ሚንጂዮ ከማቶ ተረክቦ የበንጋ

(1) A Cecchi : ibd p 488
(2) A. Cecchi : ibd p 490

ንጉሥ በመባል የንጉሠ ነገሥት ሥልጣን ሲይዝ እናሪያን ከግዛቱ አጠቃለላት። በዚሁ ጊዜ እናሪያ ቡሳሰ በተባሉ በንጉሣዊ ቤተሰብ ትገዛ ነበር። የካቶሊክ ሚሲዮን በጌራ ሲመሠረት 70 (ሰባ) ከእነዚህ በተሰብ አባላት የክርስትና እምነት ተከታይ በመሆናቸው ለሃይማኖታቸው ሲሉ ከከፋ ተሰደው በ1878 ወደ ጌራ በመሄድ ከካቶሊክ ሚሲዮናውን ተቀላቅለው ለመኖር መምረጣቸው በቀድሞ እናሪያ የክርስትና ሃይማኖት እንዳልጠፋ ምስክር ነው።[1] ወደ ጌራ የተሰደዱ የእናሪያ ሰዎች አለቃ 80 ዓመት ዕድሜ የነበረው አባ ታባኮ የተባለው ወደ ጌራ እንደመጣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ የጌራው አባ ኮሮ የጦር አለቃ ሆኖ ተሾሞ በከፋ ላይ ለመዝመት ፈቃደኛ እንዲሆን የጌራ ንጉሥ ቢጠይቀው በሀገሬ ላይ አልዘምትም ብሎ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል። የጌራ ንግሥትም ጌን እስላም እንዲሆን ብትጠይቀው እስላም ከሚሆን ገላው ተቈራርጦ ለአሞራዎች ቢሰጥ እንደሚመርጥ የሚል መልስ ሰጥቷታል። እንደዚሁም አንድ የቡሳሲ ልዕልት ልጅዋ እስላም እንዲሆን ብላ ብትጠይቃት የሰጠችው መልስ ተመሣሣይ ነበረ። ከፋ የዓመት መጀመሪያና መስቀል የሚያከብረው ልክ እንደ ኢትዮጵያ አከባበር ነው። ንጉሠ ነገሥቱ በዓመት መጀመሪያ ቀን ከአሉ በፊት የነበረው መቃብር ወደሚገኝበት ቦታ በመሄድ የከብቶች መስዋእት ያቀርባል ዜጎቹም እበባ እያበረከቱ ረጅም ዕድሜ ይመኙለታል። በመስቀል ቀን ንጉሠ ነገሥቱ ለሸማኖቶቹ ትልቅ የምሳ ግብዣ ያደርጋል። ግለሰቦችም መስክረም 17 በየቤታቸው ያከብሩታል፣ መስከረም 18 ብዙ የሚጎድ ዕንጨት ይከማቻል፣ መስከረም 19 እውነተኛ የመስቀል በዓል ከንጉሡ ቤት ጀምሮ ትልቅ ሕዝባዊ ሰልፍ ይደረጋል፣ 3 የተለያዩ ቀለማት ያላቸው እርግቦች በመያዝ ኃ ባሮ ማስካሮ እያሉ እየዘፈኑ ይሄዳሉ። ንጉሠ ነገሥቱም ወደ ፭ባዓሉ መጨረሻ ጎ ባሮ ማስካሮ እያለ ይዘፍናል።

4. ደቡብ ምዕራብ ከኢትዮጵያ ጋራ ግዋሐድ

የመጨረሻ የጌራ ንጉሠ የነበረው የአባ ራጉ አጎት ለጉብኝት ወደ እሱ ለሄደው ኢጣሊያዊ ቸሩሲ (Cerulli) እንዳጫወተው ጌራ ለአፄ ምኒልክ ጦር የተግረከችው በጀግናው ኢትዮጵያዊው ደጃዝማች በሻህ አቡዱ የሚመራው ጦር አራት ጥይት ብቻ በመተኩስ ነበረ። ንግግሩም በመቀጠል ደጃዝማች በሻህ ደፋርና ጀግና ርሕሩሑም ነበረ፣ በዓድዋ ጦርነት ጊዜ በጦር ሜዳ በጣሊያኖች ተገድሰዋል። እላይ እንደተገለጸው የከፋ የጥንት ታሪክና ባህል አድናቆት የሚስብ ነው። ጅማ አባጅፋር ከፋን ለማስገበር ከምኒልክ ጦር ጋራ በመስለፉ የሰው ደም በከንቱ እንዳይፈስ ላደረገው ውለታ የውስጥ አስተዳደር ነፃነት እንደተሰጠው ሁሉ ለከፋም ለጥንታዊ ወጉና ባሕሉ ክብር እንዲሁም ላሳየው ጀግንነት ከጅማ የበለጠ የውስጥ አስተዳደር ነፃነት ለማግኘት መመዘኛ ነበረው። አፄ ምኒልክ ግን በጠባብ የዘውድ ጥቅም ብቻ የሚመራ ስለነበረ ከፋ የጅማ ዕድል አልተሰጠውም። አፄ ምኒልክ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ፊውዳሎች የሚኖሩበት አደሬ ኢትዮጵያ ከደኩማ ዕዳቸውና ጭሰኞች ጥንት የነበሩዋት ግዛቶች ለማዋሐድ በተደረገው ትግል፣ የጅማ አባ ጅፋር ትብብር በደስታ ሊቀበል የጉጃሙ ንጉሠ ተክለሃይማኖት ግን በዘመቻው እንዳይካፈል ጦርነት ገጥሞ በማሸነፍ አሰቀርቶታል። ከዚህም ሌላ የልጁ ዘውዲቱ ባል የአፄ ዮሐንስ ልጅ አርአያ ሥላሴ በአባቱ ትእዛዝ በዘመቻው

(1) A Cecchi : ibd p. 341

ተካፋይ ለመሆን ከሠራዊቱ ጋር ወደ ሸዋ መጥቶ አፄ ምኒልክ በመጣበት እንዲመለስ አድርጎታል።

የአፄ ምኒልክ ሠራዊት ወደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ለመዝመት በሚዘጋጅበት ጊዜ የጅማ ንጉሥ አባ ጅፋር የምኒልክ ጦር ለመቋቋም እንደማይችል በመገንዘቡ ለምኒልክ ለመገበር እንደወሰነ ሁሉ እንደዚሁም ቃቢየና በተባለው በጉራጌ ሀገር ሱልጣን የነበረው የማር ባክሰ የተባለው አክራሪ ሙስሊም የባሪያ ነጋዴ የነበረው፣ በየጊዜው ለሥራ ምክንያት ወደ ሸዋ በመመላለስ አፄ ምኒልክ የነበረው የጦር ኃይል ስለተረዳ ለምኒልክ በሰላም ለመገበር ተሽቀዳድሞ ወሰነ። በአፄ ምኒልክና በያማር ባክሳ መካከል የተደረሰው ስምምነት ያስከተለው ውጤት በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ የቾሃ፣ ምሑር፣ ጆቾሪት፣ እንሞር ጉራጌዎችና ከ2 ሺህ እስከ 3ሺህ የሚደርሱ አማራዎች በ1876 የደረሰ አልቂት ነው[1]። ኢግም ተብሎ የሚጠራው የማር ባክሳ ከንጉሥ ምኒልክ እርዳታ እንዲያደርግላቸው አደራ ተብለው ወደ ጅማ ከፋ ለመዝሰቅ ፈልገው ወደ ግዛቱ የመጡ ቸኪና ኪያሪኒ የሚባሉ ጣሊያኖች ወደ ግዛቱ ሲገቡ የሚከተለው ንግግር በማድረግ ተቀበላቸው። "አዳምጡኝ እናንተ እንደ እኔ ትልቅ ሰዎች ናችሁ፣ ንጉሥ ምኒልክ ወደ እኔ አደራ ብሎ ልከዋችኋል፣ ነገር ግን እናንተም ለእኔ ማድረግ አለባችሁ። እኔ እንደ ኦሮሞች ልብሶች መስተዋቶች ለዝቅተኛ ሰዎች የሚሰጡ እቃዎች አልጠይቃችሁም፣ እኔ ብዙ ጠላቶች አሉኝ፣ እናንተ ከእኔ ለመገላገል እኔን መርዳት አለባችሁ የምጠይቃችሁ ከፈጸማችሁልኝ እኔ ራሴ ወደ ጅማ አባ ጅፋር እሸኛችኋለሁ። ብዙ ነገር አልጠይቃችሁም። የእናንተ አንድ ጠብመንጃ ብቻ በርቀት ሁኜ አንድ የጉራጌ ጉማ ክርስቲያን የእኔ ጠላቶች ለመደምሰስ ይበቃኝ ነበር በማለት ጥያቄውን ደምድመዋል። ጣሊያኖች ግን አሁን ያሉን ጠብመንጃዎች ለራሳችን ለመከላከያ ብቻ የሚያገለግሉን ናቸው ሸዋ ለሚገኘው አለቃችን መልእክት ልከን ጠይቀን ግን እንዲሰጥህ ማድረግ እንችላለን አሉት። በዘመኑ በቃቤና በኩል በየዓመቱ 400 ባሪያዎች ተገዝተው ወደ ሸዋ ይወሰዳሉ። አብዛኛዎቹ ከቾሃና ከኡርባራግ በሴሊት ተሰርቀው የሚመጡ ናቸው፣ የሚገዙም በገንዘብ ሳይሆን በጎሐሰ ነጥር ነው፣ አንድ ነጥር 432 ግራም ነው የገበያ ሁኔታ እንደሚከተለው ነበር

1	ወንድ ልጅ ቁመት 1ሜትር	20 ነጥር
2	ሴት ልጅ ቁመት 1 ሜትር	13 - 15 ነጥር
3	ትልቅ ልጅ 12 - 16 ዓመት	26 - 28 ነጥር
4	ሴት ልጅ	25
5	ወንድ ልጅ 20 - 24 ዓመት	20 - 30
6	ሴት ልጅ ቆንጆ	40
7	ሴት ልጅ መለስተኛ	30
8	ሴት ልጅ ዝቅተኛ	25 - 20 - 15
9	ቆንጆ ልጃገረድ	60 - 70
10	አሮጊት	6 - 7
11	ሽማግሌ	8 - 10
12	ሽማግሌ ጠንካራ	20

ይህም የማር ባክሳ ጠብመንጃ ከመጠየቅ አላቋረጠም፣ ጣሊያኖችም ተስፋ እየሰጡት ነበር። አንድ ቀን እነስት 25,1878 "ዐሽከሮቻችሁ

(1) A Cecchi : ibd VII p 52

ከሰመሪያዎቻቸው ወደ እንድ ከርስቲያን ጉራጌ መንደር ከእኔ ጋራ ሄደው እንዲዘርቱ ፍቀዱልኝ የምናገኘው ገቢ እካፍላቸኋለሁ ብሎ ጣሊያኖችን ጠየቃቸው፤ ይሁን እንጂ ጣሊያኖች የጥያቄው አደጋነት በመገንዘብ፤ ከሁሉ ጋራ ወዳጅ ለመሆን ሰለሚፈልጉ ለእንድ ወገን ግዳጣት እንደማይሹ ነገሩት።

ጣሊያኖች ለጉዞዋቸው መሰናክል መሆኑን ሰለተረዱ ከጉራጌዎች ጋራ መቀራረብ ፈለጉ፤ ጉራጌዎችም ሀገራቸውን እንዲጐበኙላቸው ጋበዙዋቸው። በዚሁ መሠረት ከሁለቱ ጣሊያኖች አንዱ ወደ ጉራጌ ሀገር ሄዶ ጥናት እንዲያደርግ ወሰኑ፤ ዕጣም ለኪያሪኒ ደረሰው። መንገድ መሪዎች ጉራጌዎችን ይዞ ኪያሪኒ ወደ ጉራጌ መሬት ገባና ቤተክርስቲያኖችን አስጐበኙት። ወደ መጪረሻም አስጐብኚው ከዘናግ ለመጠለል ወደ ቤቱ አሰገባው። በዚሁ ጊዜ ፈረንጅ ብዙ ሰው ተሰብስበው ብዙ ጥያቄዎችን ያቀርቡለት ነበር። ከተረበትም ጥያቄዎች ከየት ሀገር እንደመጣ፤ ሃይማኖቱ ክርስቲያን እንደሆነ ወይንም አሰላም፤ ከሁለቱ ሃይማኖቶች የትኛው እንደሚሻል፤ ዘቀንደኛ ጠላቶቻቸው በእስላሞች ድል ይቀዳጁ እንደሆነ ወይስ አይቀዳጁም ወዘተ። ኢጣም ያግር ባክሳ ብቻ ሳይሆን የምኒልክ ወታደሮቹም ክርስቲያን መሆናቸው እያወቁ ከኢጣም ተከታዮች ጋራ በመሰማማት ያለ ምንም ርሕራሔ ያላቸውን ንብረት እየዘረፉ ቤተክርስቲያኖቻቸውን ሳይቀሩ ያቃተሰባቸው እንደነበረ በምሪት ያወሩለት ነበር። ጉራጌዎች ምሑር ሰለ ሃይማኖት ብዙ ነገር ባያውቁም ሁሉም ግን ክርስቲያን ነን በማለት ይነግሩት ነበር[1] ። ኪያሪኒ እግረመንገዱ ከኢሻ ንጉሥ ጋራ ተዋወቀ ንጉሡም ፈረንጅ ያላቸው መሣሪያዎች ካደነቀ በኋላ "እንተ ዓለምን ሙሉ ማቃጠል ችላለህ፤ የእኔ ሀገር እትንካ እንተ ቂሰ ነህ እኔም እወድሃለሁ፤ እንተ የእግዚአብሔር ሰው ነህ እዜ ምኒልክና እሰላም ንብረታቸው እየዘረፉ ሊያጠፏቸው እየጣሩ ያሉት እነዚህ ምስኪን ሕዝቦች ደስተኞች ልታርጋቸው ትችላለህ"። የሚል ንግግር አደረተ[2] ከንጉሡ ተሰናብቶ እንደሄደ የጣሊያኑ መምጣት ወሬ ስለተሰማ በፊት ቂሰ ብቻ ይቂጥሩት የነበረ እሁን እንደ ቅዱስ ሰው ሁሉን ነገር የሚያውቅ እደረጉት። በሽዋ ሰዎች ልጆቻቸው የተወለዱባቸው በሕይወት እንዳሉ እንዲነግራቸው ይጠይቁት ነበር። ኪያሪኒ ከአካባቢው ተነስቶ እንደሄደ ቸሃ መሬት ደርሶ በዙሪያው ለተሰበሰበ የተለመዱ ጥያቄዎችን ለሚያቀርብ ሕዝብ ዕድላቸውን እንዲነግራቸው፤ በጠላቶቻቸው በእግራ የተወሰዱባቸው ልጆቻቸው ወንድሞቸቸው የት እንደደረሱ እንዲነግራቸው ይጠይቁት ነበረ። በመቀጠልም ኪያሪኒ ከዳሞ ንጉሥ ተዋወቀ፤ ጥሩ መስተንግዶ ተደረገለት። "የዚህ ሀገር ሕዝብ የቃበናውን ይግም አይደለም የሚፈሩ፤ በእሱ እግሳኝነት የምኒልክ ጦር እንዳይወራቸው ነው ሲጋቃቸው[3]። ከእኛ ጋራ ሆነህ እንዝመት እስላሞችን እናጥፋቸው እያሉ ለክብሩ ይዘፍኑ ነበር። ንግሥቲቱም ለብቻው ወሰዳ የቀቢየና ይግም እግራ እመጣባችኋለሁ እያለ እያሰፈራራን ነው፤ መሐሊን ሊያደርገን እየሞከረ ነው፤ የጉራጌ ሕዝብ እንደ በግ ነው የሚነዳው፤ ሃይማኖቱን ሊከድ ይችላል፤ እግሮች የማይመጡ መሆናቸው ቢያውቅ ግን ሕዝቡ ኢግሙን መሳቂያ ያደርገው ነበር። እንተ ትልቅ ሰው ነህ፤ ሕዝቡ ከውድቀት እንዲድን እድርገው፤ ቃልህን እንዲያምኑ ያዝካቸው መሣሪያዎችን አሳያቸው" ብላ ንግግሩን ከጨረሰች በኋላ ኪያሪኒ መልስ ለመስጠት

(1) A Cecchi ibd VII p 77
(2) A Cecchi : ibd p 80
(3) A Cecchi : ibd p 87

ተቸገረ[1] ንግሥቲቱ ሳቀረበቸው እንብጋቢ ጥያቄዎች ኪያሪኒ "የእናንተ ሁኔታ ይገባኛል የተቻለኝን ለማድረግ እሞክራለሁ። እግሮች ይመጣሉ እያለ ያግር ባክሳ የማሰፈራሪያ ጉራ ሰለሚነዛባችሁ ጉዳይ አትቸገሩ፤ ንጉሥ ምኒልክ ባሁኑ ወቅት ለእዜ ዮሐንስ ግብር ለመክፈልና የበላይነት ለመቀበል ተስማምቷል፤ እዚህ መምጣት አይችልም ከርስቲያኖችን ከእስላሞች ጥቃት መጠበቅ እለበት እንጂ ከርስቲያኖችን እይፈጅም። እኔና ጓደኞዬ የእስላሞች ሀገር አቋርጠን ሰለምናልፍ ችግር እንዳይፈጥሩብን እሁን ያልኳችሁ ነገር ለማንም አትናገሩ።" በማለት የግደፋፊያ ቃላቶች ሰጣት። ንግሥቲቱም መልስ ሰቅሰጠው "በእስላሞች ሀገር ለማለፍ ግዲታ የለባችሁም፤ ወደ እኛ ከመጣችሁ በእቋራጭ መንገድ ምንም ሳትከፍሉ በጃንጀሮ ሀገር በኩል ወይንም በጅማ በኩል ወደ ከማታ ወላሞ እናደርሳችኋለን፤ የጅማ ንጉሥ ሚስት የቻሀ ተወላጅ የእባጋስ ልጅ ናት" አለችው። ኪያሪኒ በንግሥቲቱ ንግግር በጣም ተደሰቶ እመሰገናት። ጉራጌዎች ከሰሜን ኢትዮጵያ እንደሚወለዱ ለኪያሪኒ ሲያሰረዱ እንደሚከተለው ገልጸውለታል "ከእርሲ፤ ከሪዩ፤ ቱሉ፤ መጫ፤ ጋላ ተከበው በችግር ላይ በነበሩ ጊዜ ከህገራቸው እንዲያባሩሯቸውና እንዲፈጁዋቸው ይፈልጉ ሰለነበረ ጉራጌዎች ወደ ጉንደር ለንጉሥ ነገሡቴ መልእክተኞቻቸው ልከው ከአሮሞች እልቂት እንዲድኑ እርዳታ እንዲደረግላቸው በጠየቁት መሠረት እነሱ እጥናፍ ሰባድ የሚሉት ንጉሥ የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊዎች ግን ሱሲኒዮስ የሚሉት ንጉሥ የትግራዩ ሹም የነበረው እዝግች ሰብሐት ለእርዳታ ላክላቸው፤ እሱም የተላከበትን ዓላማ እንደተዋጣ፤ ወታደሮቹ ቱጥራቸው በመቀነሱ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ለመመለስ ሰላልቻሉ በዝዋይ ሐይቅ የምትገኘው ትልቋ ደሴትና አካባቢው ሰፍረው ጉራጌዎች ንጉሥ ብሉ ራሱን ሰየመ። የአዝግች ስብሐት ትውልድ ሐረግ ብዙ ዓመት ነገሠ፤ በመጪረሻ ግን በንጉሥ ማሕሰላሴ የምኒልክ አያት ተደመሰሰ። ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ጉራጌዎች እውነተኛ ንጉሥ የላቸውም፤ ጉልበት ያለው ሁሉ ደካሞችን እያስቸገረ ንጉሥ ይባል ነበር መሬታቸውንም ይነጥቁዋቸው ጀመር። በዚሁ የተነሳ የጉራጌ ቋንቋ ከግእዝ ተመሣሣይነት አለው[2] ።

ከጉራጌዎች የክርስትና ሥነ ሥርዓት በጥብቅ የሚከተሉ ምሁር ናቸው። ኢንደጋን፤ የነር፤ መገር፤ እስላሞች ያረዱትን ሲጋም ይበላሉ። ጉራጌዎች ባለሥልጣን እያውቁም፤ ሰለ ንጉሥ ሲያወሩ እንደ ተራ ሰው ነው የሚያከብሩት፤ ሃብት ያለው ብቻ ንጉሥ የሚባለው። ንጉሥ የሚባሉ ሃብትና ጀግንነት ያላየ ሰው ነው። ከእነሱም ትልቁ ብቻ ዳሞ ወይንም ጉይታ ይባላል።

ጣሊያኖች ወደ ከፋ ለመድረስ የቻሀ ንጉሥ ግጋናስ ባቀረበላቸው ሃሳብ መሠረት በጅግ ወይንም በሊሙ ከግለፍ፤ በጉሬ፤ ጃንጅሮ፤ ከምባታ፤ ወላሞ እንጓዝ ኪያሪኒ እምኖበት ተስማምቶ ነበር፤ ሆኖም እብሮዋቸው የሚጓዙ ከብት ጫኞች መንገዱን ሰለግደቁ በዚሁ መንገድ ለመሄድ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀሩ። በመጪረሻ ከቃቢና ሞጂየር ወደ ሊሙ ጉዞዋቸውን ቀጠሉ።

እዜ ምኒልክ ቀድሞ የኢትዮጵያ እንድ አካል የነበሩ፤ አሮሞች ባካሄዱት ጦርነቶች ምክንያት ከኢትዮጵያ ተለይተው ይኖሩ የነበሩ ግዛቶች መልሶ ለማዋሐድ የፈጸመው ተግባር በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ለዘለዓለም

(1) A Cecchi : ibd VII p 88
(2) A Cecchi : ibd VII p 89

የማይረሳ ውለታ የሚያስገኝለት ቢሆንም አላይ እንደተገለጸው አክራሪ ሙስሊሞች እንደ ኢማም የግር ባክሳ ባለሟል አድርጎ በጉራጌ ክርስቲያኖች ከፍተኛ ጥቃት እንዲያደርስ መፍቀዱ ከባድ የአስተዳደር ስህተት በመፈጸሙ በታሪክ ያስወቅሰዋል።

5. <u>የእናሪያ የመሬት ስፋት</u>

ተጓዦች ማሊያኖች ቸኪና ኪያሪኒ ተፈቅዶላቸው ወደ ሊሙ ገቡ። በቀድሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ዘመን የእናሪያ የመሬት ስፋት ከአባየና አዋሽ ወንዞች ክፋም በውስጡ የሚያጠቃልል የሸዜና የጉጀብ ሜዳዎች ያቀፈ ነበረ። ይህ ግዛት በንጉሥ እንደራሴ ይገዛ ነበር። ከ1545 ጀምሮ በኦሮሞ ሜጫ ወራሪዎች ግዛቱ ሲፈራረስ ገዢዎች ግማሾቹ ወደ ጉጃም ሲሸሹ ግማሾቹ በክፋ ሰሜናዊ ክፍል ሰፍረው ያጡት የሰፊ ሀገራቸው ስም የሰፈሩበት አንድ የክፋ ክፍለ ሀገር እናሪያ ብለው ሰይመው በቀድሞ ገባሮቻቸው ከነበሩ የወረታ ጉማዎች በመተባበር ለኦሮሞ ግስፋፋት ከፍተኛ መከላከያ በማድረጋቸው ለከፋ በጎነት መቆየቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። የቀድሞ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ከመፈራረሱ በፊትና እናሪያ በመሜ ኦሮሞች ከመወረሩዋ በፊት የሀገሩ ነዋሪዎች አፈ ታሪክ እንዳቆየው ሁለት የፖርቱጋል ወታደሮች ሲጋሮ (Sigaro) እና ሰፔራ (Sapera) የተባሉ፣ ከክሪስቶፎር ዳ ጋማ ጋራ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ በአፄ ግላውዲዎስ ከሰሜን ኢትዮጵያ ተባርረው እናሪያ መኖሪያቸው አድርገዋት ነበር፣ በሰነ ምግባራቸውም በሕዝቡ ዘንድ ትልቅ አክብሮት አግኝተው ነበር። በዚህም የተነሳ የነበራቸው አክብሮት እየጨመረ በመሄዱ በእናሪያ የአስተዳደር የበላይነት አግኝተው ነበር። ሲጋሮ በሰሜን እናሪያ መኖሪያው እደረገ፣ ሳፔራ ወደ ደቡብ ሳፓ (Sappa) ተብላ የተጠራቸው መንደር ሰፈረ። ከሳፓ ቤተሰብ አንዱ የአባ ባኒቦ አባት አባ ጎሎሲ በክህደት የሲጋሮ ግዛት ወደ ግዛቱ አጠቃለሉ አንድ የሊሙ መንግሥት አቋቋመ። እንደ አቡነ ግማያ ምስክርነት አባ ጎሎሲ የነጭ ዘር ይመስል ነበረ[1]። ሊሙ ከ80 ዓመት ወዲህ የእስልምና ሃያግኖት ተከታይ ቢሆንም መስጊዶች በብዛት አይታዩም። ማሊያኖች /ቸኪና ኪያሪኒ/ በነበሩበት ዘመን (1878) በሊሙ ተሳላፊ በሽታ ተስፋፍቶ ነበር። በሊሙ የሕዝቡ ግማሽ በበሽታ አልቋል[2]፣ በጉግ 2/3 በበሽታ አልቀዋል። ማሊያኖችም እየታመሙ ይድኑ ነበረ። ከሁለቱ አንዱ ኪያሪኒ ታሞ ሲሞት በጌራ ንግሥት ተመርዞ ነው የሞተ ተብሎ ተወራ።

6. <u>ጉማ</u>

ጉማ በጥንት ጊዜ የሲዳማ አማራ የሚባሉ ይኖሩባት ነበር። በኦሮሞ ነዋሪዎች ጊዜ ነዋሪዎቹ በሙሉ ተገድለው አልቀዋል። ክርስቲያን ሕዝብ ይኖሩበት እንደነበረ በግያሻማ ሁኔታ ግስረጃ የተገኘው የአንድ ቤተክርስቲያን ፍርስራሽ በዲደሳ ወንዝ ዳሩ (Daru) ከተባለው ተራራ አጠገብ ጉልጉታ ተብሎ በሚጠራ ቦታ በመገኘቱ ነው[3]። ሜላ የጌራ ዋና ከተማ የሁሉ ዓይነት የባሪያ ክምችት የሚታዩበት ናት።

(1) A Cecchi : ibd VII p 156
(2) A Cecchi : ibd p 199
(3) A Cecchi : ibd p 239

1. ወረታ ጉማዎች ከኩሉ፣ ወሊሶ፣ ኮንታ መንግሥታት የመጡ
2. ካፊኞ 3 ጃንጀሮ 4 ጉራጌ 5 ከምባታ 6 ሻንቅላ 7 ጋላ የተለያዩ ጉማዎች ሶዶ፣ በቶሮ፣ አጋሉ[1] ። የጌራ ሕዝብ የኦሮሞ፣ ሲዳማ፣ አማራ ድብልቅ ነው። ሌላ ቅምባሪ የተባሉ ዝቅተኛ ዘር የሚገመቱም አሉ። የቤተመንግሥት ዘር የኦሮሞ ዘር ከወላሞ ምሥራቅ ደቡብ የመጡ ናቸው[2]። በጌራ ቤተመንግሥት ከ3000 ያላነሱ ባሪያዎች ይኖሩሉ። አነሱም 12 የንጉሡ ሚስቶች በጋብቻቸው ጊዜ ለጥሰሽ ተሰጧቸው ይዞዋቸው የመጡ ናቸው። ባሮች ወደ ውጭ ይሸጣሉ በሀገር ውስጥም በእቃ ይቀየራሉ፣ 6-7 ባሪያዎች በአንድ የጦር ፈረስ ይለወጣሉ ወጽተ። ይህ ሀኔታ የአፄ ምንልክ ማልቃ ገብ ጦር እነዚህ ጥቃትን መንግሥታትን መውረሩ ሕጋዊ ያደርገዋል።

7. <u>ጃንጀሮ</u>

ጃንጀሮ ደብተሮችና የካፊኞ ሽማግሌዎች አንደሚተርኩ የዚሁ አካባቢ የመጀመሪያ ነዋሪዎች ናቸው። በተጨማሪም አፈታሪክ እንደሚናገረው ጃንጀሮና ሲዳማ በሐይቆች ይኖሩ የነበሩ የአንድ እናት ልጆች ናቸው። ጃንጀሮ የሸዜ ዳውር አጠገብ አዞዎች ያመልኩ ነበር። ንጉሣቸው ኩርማ በሬዎች ለአዞዎች አንዲበሏቸው በመስዋእትነት ያቀርብ ነበር። ንጉሥ ሲታመም ጤና እንዲያገኝ ሰዎች ወደ ሸዜ አዞዎች ለመስዋእትነት ይወረውሩ ነበር። ይህ የማእት እምነታቸው ግን አንዳንድ የኢትዮጵያ የክርስትና ሥነ ሥርዓት እንደ እስተርእዮ ማርያምና መስቀል ከግክበር እያገዳቸውም[3] ይህ የሚያመለክተው ኢትዮጵያ ከግራኝና ከኦሮሞ በፊት በግዛቷ በሙሉ የክርስትና ሃይማኖት ያልደረሰበት ቦታ አልነበረም።

8. <u>ቦሻ</u>

በቦሻ ከኦሮሞች ጋራ የሚኖር ሕዝብም ከትግራይ መምጣታቸውን ለማሊታወስ "ቲግሮ ቦሻ" ተብለው ይጠራሉ፣ በሀገራቸው የቤተክርስቲያን ቅሪቶች ይታያሉ፣ ብዙ ዘመን ከአዋሽ በስተደቡብ ይኖሩ እንደነበረ ያወራሉ፣ በዚሁ ጊዜም ሀገሩ በኢትዮጵያ መንግሥት ስር ሆኖ እናሪያ ተብሎ ይጠራ ነበር። በኦሮሞች ተገፍተው ከሀገራቸው ተፈናቅለው፣ በመጀመሪያ አሁን ቦቶር ባሉበት ይኖሩ ነበር፣ በመጨረሻ አሁን ባሉበት ሰፈሩ። ቋንቋቸው ከካፊኞ ተመሳሳይ ነው።

9. <u>ዋሬታ</u>

በአጠቃላይ ስማቸው ዋሬታ ወይንም ዳውር ተብለው የሚጠሩ ሕዝቦች 1 ኩሉ 2 ኮንታ 3 ኩዋሽ 4 ማሮ 5 ጉልዳ ከአሞ ወንዝ በስተምሥራቅ የሚገኙ ናቸው። በኢትዮጵያውያን ታሪክ እዋቂዎች ደብተሮች አባባል በኢትዮጵያ ታሪክ ዝነኞች ናቸው። ምክንያቱም በ1300 ዓ.ም. በአጼ ዓምደ ፅዮን ዘመን መንግሥት ከኢትዮጵያ ግዛት ጋራ የተቀላቀሉ ናቸው።

(1) A Cecchi : ibd p 258
(2) A Cecchi : ibd VII p 266
(3) A Cecchi : ibd p 355